አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት— በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች

በ

ዓለሙ ካሣዬ

የካቲት 30/2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት— በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለፎክሎር ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ዓለሙ ካሣዬ



የካቲት 30/2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት— በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች

በ

ዓለሙ ካሣዬ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ፡- ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ --------------------------------

የውስጥ ፈታኝ፡- ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ---------------

የውጭ ፈታኝ፡- ዶ/ር ታረቀኝ አዴቦ ------------------------

# ምሥጋና

በቀዳማይ ደረጃ ይሄን ጥናት በዚህ መልኩ ይቀርብ ዘንድ ስጥለው እንዳነሳው፣ ሳላላው እንዳጠብቀው፣ ስስተው እንዳልመው፣ ስገድፈው እንድይዘው ላተጉኝ መካሬ ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምሥጋና አቀርባለሁ፡፡

በካልዓይ ደረጃ ጥልመ ጥናቱን ዶ/ር ገብሬ ይንቲሶ፣ የደረጃ ማበልፀጊያውን ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ እና አቶ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በማንበብ እና በመፈተን እጅግ ጠቃሚ የማቃኛ ሐሳቦችን በቸርነት ስለሰጡኝ በእጅጉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

በሣልሣይ ደረጃ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ስፖንሰር ስላደረገኝ እና በቁጥቁጥም ቢሆን ደግሞ የጥናቱንም ወጪ የተቻለውን ያህል ስለሸፈነልኝ ምሥጋና ማቅረብ እወዳለሁ፡፡

በራብዓይ ደረጃ የሕይወቴን መንገድ በመቀየስ ብርቱ ውለታ የጣሉብኝን ወንድሞቼን ስለማይረሳ ውለታቸው መጥቀስ እወዳለሁ፡፡ የመጀመሪያው ተጠቃሽ ምክሩ ሁሉ መሬት ጠብ ያላለው መለኛው ወዳጄና ወንድሜ አቶ ሺፈራው ጉርሙ ነው፡፡ ሁለተኛው ተጠቃሽ በማህበራዊ ሳይሆን በተፈጥሯዊ ቅንነት ወጀብ በተነሳብኝ ወቅት መጠጊያ እና ከለላ የሰጠኝ እና በዚህ የትምህርት መስክ ማዕድም እካፈል ዘንድ ያመለከተኝ ወንድሜ አቶ ወንድወሰን አዳነ ነው፡፡ ሁለቱንም እጅግ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ሌሎቹንም አጋሮቼን በዚሁ ሥር አስከትላለሁ፡፡

"የሰው ሰውነቱ የሚለካው በክፉ ቀን ነው" እንዲሉ በአስቸጋሪ ወቅት ከመስመሩ ዝንፍ ሳይል "ነገር ሁሉ ለበጎ ነው" እያለ በሐቅ አቅጣጫ በመቆም ጊዜ እና ባለ ጊዜ አይቶ ያልተለወጠብኝን የሥራ ባልደረባዬን እና ፅኑ ወንድሜን አቶ አማኑኤል አብዲሳንም ስለማይዘነጋ እና የቁርጥ ቀን ሰውነቱ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የረጅም ጊዜ ወዳጄ እና ወንድሜ አቶ ማቲዎስ ታደሰም የጀመርኩትን እጨርስ ዘንድ ያደረገውን ውትወታ እና እገዛ ማስታወስ እና ማመስገን እወዳለሁ፡፡

ምሥጋናዬን የማሳርገው በየጊዜው "ምርምሩ የት ደረሰ?" እያሉ ብርቱ ማበረታቻ የሰጡኝን የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ባልደረቦች አቶ ደረጀ ገብሬን፣ ዶ/ር ጌታሁን አማረን፣ ዶ/ር ሙሉሰው አሥራቴን ውለታ በማስታወስ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እና እዚህም ሥማቸውን ያላነሳኋቸው የትምህርት ክፍሉ ባልደረቦች እና ሌሎችም ቅን ወንድሞቼ እና እህቶቼ ውለታ ሁሉ በወርቅ ቀለም ሊፃፍ የሚገባው መሆኑን አምናለሁ፡፡ ውለታቸውም ሁሉ በሕይወት እስካለሁ ሕያው መሆኑን መግለፅ እወዳለሁ፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


ምሥጋና---i
ማውጫ---iii
አጠቃሎ---VI
ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ካርታዎች---ix

1. መግቢያ---1
 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት---1
 1.2. የጥናቱ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች---4
 1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች---5
 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ---6
 1.5. የጥናቱ ገደብ---7
 1.6. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች---8
 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት---11

2. የግጭት እና የግጭት አፈታት ንድፈ ሐሳብ ቅኝት---14
 2.1. የግጭት ምንነት---14
 2.2. የግጭት ዓይነት---22
 2.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች---24
 2.4. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭት እና ግጭት አፈታት ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ---26
 2.5. የመሰል ጥናቶች ክለሳ---28

3. የጥናቱ ዓይነት እና ዘዴ---38
 3.1. የጥናቱ ዓይነት---38
 3.2. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች---39

4. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ዳራዊ ገለፃ---48

4.1. የቀወት ወረዳ ሕዝብ፣ መልክዓ ምድር እና ማህበራዊ ግንኙነት----------------49
4.2. የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ሕዝብ፣ መልክዓ ምድር እና
ማህበራዊ ግንኙነት---------------------------------------------------------53

5. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ጥንተ አመጣጥ እና
ማንነት ተኮር አፈ ታሪክ---------------------------------------------------------64
5.1. የቀወት ወረዳ አማሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፈ ታሪክ--------65
5.2. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ አመጣጥ እና
ማንነት ተኮር አፈ-ታሪክ--------------------------------------------------74

6. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ጥንተ አመጣጥ፣ ማንነት እና
ግንኙነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ------------------------------------------------78
6.1. የቀወት ወረዳ አማሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር
ጽሑፍ ታሪክ---------------------------------------------------------------78
6.2. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ አመጣጥ እና
ማንነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ----------------------------------------------81
6.3. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግንኙነት ተኮር
ጽሑፍ ታሪክ---------------------------------------------------------------83

7. ከቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች የተሰበሰቡ ሥነቃሎች
እና መልዕክቶቻቸው-------------------------------------------------------------109

8. የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ግጭቶች እና የግጭቶች አፈታት--------129
8.1. የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የግጭት መንሥዔዎች-----------------------------------130
8.2. የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የርስበርስ ግጭቶች አፈታት----------------------------141
8.3. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭቶች መንሥዔዎች---------------------154
8.4. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች የርስበርስ ግጭቶች አፈታት---------------158
8.5. የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች
ግጭቶች መንሥዔዎች------------------------------------------------------------168
8.6. የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግጭቶች አፈታት-------209

9. የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች
ግጭት እና እርቅ አፈፃፀም ትንተና እና ትርጎማ-------------------------------------224

10. የጥናቱ ማጠቃለያ-------------------------------------------------------------------246

የተጠቀሱ ምንጮች---------------------------------------------------------------------252

አባሪ አንድ፡-ሥነቃል፡- ከቀወት ወረዳ የተሰባሰቡ ግጭት ተኮር ሥነቃሎች------------263
አባሪ ሁለት፡- ሥነቃል፡- ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተሰባሰቡ
ግጭት ተኮር ሥነቃሎች----------------------------------------------275
አባሪ ሦስት፡- የመረጃ ምንጮች መዘርዝር----------------------------------------------290

# አጠቃሎ

ይህ “የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙ·ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች” ጥናት የተካሄደው ከአማራ በቀወት፤ ከአፋር ደግሞ በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች ላይ ነው፡፡ ጥናቱም የተደረገው በዓይነታዊ /qualitative/ የጥናት አደራረግ ዘዴ ሲሆን ያተኮረውም በሁለቱ ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች መካል በሚስተዋሉ ነባራዊ እና ተረካዊ ተቀባባይ እና ተደጋጋፊ የግጭት መንሥዔዎች ላይ ነው፡፡

ጥናቱንም ለማካሄድ የተነሳሳሁት ተረክ ወይም ሥነቃል ግጭትን በመትከል፣ በማህዘብ እና በመዘከር ረገድ ያለውን አበርክቶ ለማየት ሲሆን የጥናቱም ዓቢይ ዓላማ የቀወት (አማራ ክልል) እና ሰሙ·ሮቢ ገለአሎ (አፋር ክልል) ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶች ምክንያቶች እንዲሁም የግጭት አፈታት ሂደት ጥንካሬ እና ድክመታቸውን በተለይ ከተረክ፣ ከወግ ልማድ አንፃር ለመመርመር ነበር፡፡

በጥናቱም ሂደት ውስጣዊ እና ውጫዊ የግጭት መንሥዔዎች ሆነው የተገኙት እና የተነሱት ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት አመንጪ ሰበበ-ምክንያቶች ናቸው፡፡ ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-ምክንያቶቹም ከሩቅ ዘመን ወደ ቅርብ በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የባህር በር ቁጥጥር እና የወጪ እና የገቢ ንግድ እና ግንኙነት ማሳለጥ ፍላጎት፣ ለም መሬት የመያዝ ፍላጎት እና ሽኩቻ፣ ድንበር፣ ሣር፣ ውኃ፣ ደን፣ የዱር አራዊት አደን ፣ ሰለባ፣ ግድያ ወዘተ ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡

በኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-ምክንያትነት ደግሞ በሁለቱ ሕዝቦች መሪዎች መካከል የተደረጉ ግጭት ተኮር አፈ-ታሪኮች፣ የኃይማኖት ልዩነቶች (የአማራነት እስላምነት ማለትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖት ተከታይነት፣ የወንድነት መለዮ እና መግለጫ ሁነቶች በተረክነት ማለትም በሥነቃል ልዩ ልዩ ዘውጎች (አፈ ታሪኮች፣ በሽላሎ፣ ፉከራ፣ በሥራ፣ በሰርግ፣ በለቅሶ ግጥሞች እንዲሁም በምሳሌ እና በተረት ወዘተ) ውስጥ ተዘርተው መገኘታቸው እና ተደጋግመውም መለፈፋቸው በተለይም ደግሞ ገዳይነትን በመሻት፣ በማግኘት ማሞካሸታቸው እና ማንቆለጳጰሳቸው፣ ጀግና በሚታጣበትም ወቅት “የጀግና ረሃብ ገባን፣

ጎናችን ሳሳ፣ አገር ያና ወይም ባዶ ሆነ፣ ጥቃት ገባን" እያሉ መቆጫጨታቸው ሆነው ተገኝተዋል።

ከጥናቱ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በግጭት አፈታት ረገድ የሁለቱም ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች የውስጣዊ ግጭት አፈታት ሥልታቸው ቋሚ እና ፀዳቂ ሲሆን እንደ እርቅ ማፅኛም የሚያገለግሉ ትክል ልማዳዊ እና ኃይማኖታዊ የመኃላ ሥርዓቶች አሏቸው።

በውጫዊ ግጭት ረገድ ግን ሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች ተናጠላዊ መጠቃቃትን እና መገዳደልን እንደ ወግ ልማድ የሚቆጥሩ መሆናቸው ታይቷል። በአንፃሩ የተካረሩ ቡድናዊ ግጭቶች ሲከሰቱ ግን አማሮች በባላባቶች ወይም በታዋቂ የአካባቢ ሰዎች እና በቀበሌ ገበሬ ማህበራት አባባይነት ወንድ አረጋውያንን በሽምግልና አመቻቺነት ወደ አፋሮች በመላክ፤ አፋሮች ደግሞ በጎሳ መሪዎች አማካኝነት ሴት አረጋውያንን በሽምግልና ጠያቂነት እና ቀጠሮ አስያዥነት በመላክ የሽምግልና ጥያቄ ያቀርባሉ። የሽምግልናው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ሲሰምርም ልማዳዊ መኃላዎችን በመፈፀም ከደመደሙ በኋላ አፋሮች ላም፣ አማሮች በሬ አቅርበው እና ተለዋውጠው አርደው በአንድ ዳስ ሥር በየፊናቸው በየትየለሌ መስመር ተቀምጠው በልተው ይለያያሉ[1]። በልማዳዊነት ከሚፈፀሙት መኃላዎችም መካከል የአማሮች ከብት መጨበጥ፣ ጠመንጃ መራመድ፤ የአፋሮች የከብት እበት መጨበጥ እና ጠመንጃ መራመድ ይገኙባቸዋል። ከእነዚህም የመኃላ ሥርዓቶች መካከል ሁለቱ በቀጥታ የሚጋሩት ጠመንጃ መራመድ ብቻ ነው።

በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ግጭት ተቀስቅሶ ግጭቱ በሁለቱ ወገኖች የአካባቢ ታዋቂ ሰዎች ጣልቃ ገብነት ካልተፈታ እና ግጭቱ ያስከተለው ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሣራ የበዛ እና የሚዛመት ከሆነ የመንግሥት መዋቅሮች ጣልቃ ገብተው የሚያስታግሱ መሆናቸውን እና ከላይ የተጠቀሱትንም ማሳረጊያዎች እንደሚያስፈፅሙ መረዳት ተችሏል።

ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭቶቻቸውን በተለያዩ ደረጃ ለማርገብ እና ሰላምን ለማስፈን ጥረት ቢያደርጉም ግን ግጭቱ ተመልሶ የሚያገረሽ መሆኑ ደግሞ በጥናቱ

[1] እዚህ ላይ በእርቁ ፍፃሜ ላይ የሚታረዱት እና በየፊናው የሚበሉትም እንስሳት በአማሮቹም ሆነ በአፋሮቹ ሕይወት ውስጥ ከበሬታ ያላቸው መሆናቸውን ያጤኗል።

ሂደት ታይቷል፡፡ ለግጭቱም ማገርሸት የሚጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት መሆናቸው ተወስቷል፡፡

በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ሽምግልና እና እርቅ ወቅት የመጀመሪያዎቹ ጠብ ጫሪዎች ተለይተው አለመሸማገላቸው እና እርቅ አለመፈፀማቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ሽምግልናውም ሆነ እርቁ የሚፈፀመው በቀጥታ ባልተጋጩ ወገኖች አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህም ሽምግልናም ሆነ እርቁ ያልተጣሉ ሰዎች የሚዋቀሱበት እና የሚታረቁበት ነው፡፡


በሁለተኛ ደረጃ ለግጭቱ በየጊዜው ማገርሸት ምክንያት ሆኖ የሚታየው ሁለቱም ሕዝቦች ግጭቱን በተረክነት ቀርፀው እና ሰንደው መያዛቸው፣ በ "ወንድነት" ምግባርነት መግለጫነትም ይዘው ማስቀጠላቸው መሆኑ በጥናቱ ሂደት ታይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ዑደታዊ ሆኗል፡፡

የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ዑደትም ማቆሚያው አጭር፣ ቀላል እና ቅርብም እንዳልሆነ የባህል ሥሪትነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ግጭቶችን በማሳያነት ለማመልከት ተሞክሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ከግጭት አዙሪቱ መውጫው ጠባብ መንገድ የሕይወት ሥርዓት ለውጥ ማለትም የምጣኔ ሀብት፣ የማህበራዊ እና የፖለቲካዊ ግኙኙነት ለውጥ መፍጠር መቻል፣ ሰዎችም በሰውነታቸው እንጂ በትውልድ ዘራቸው እና በእምነታቸው እየተቧደኑ በጥርጣሬ እና በሽኩቻ እንዳይኖሩ፣ በስሜታዊነትም ጎራ ውስጥ እየገቡ እንዳይጋጩ ለማድረግ የሚያስችል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መደላድል መፍጠር፣ ለዚህም አብቂ የሚሆነው እውቀት ከነቢባዊነት ዘልቆ በሳይንሳዊነቱ ቅቡል እና ገቢር ሲሆን ብቻ እንደሚሆን ተገምቷል፡፡


# ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ካርታዎች

ካርታዎቹ ጥናቱ የተካሄደባቸውን ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች በኢትዮጵያ ፣ በአማራ እና አፋር ክልሎች ካርታዎች ውስጥ እንዲሁም እያንዳንዳቸውን ወረዳዎች የሚያመለክቱ ናቸው፡፡


## ሀ/ የአማራ ክልል እና የቀወት ወረዳ




## ለ/ የአፋር ክልል እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ




## ሐ/ ጥናቱ የተካሄደባቸው የአማራ እና የአፋር ክልሎች



## መ/ ቀወት ወረዳ



## ሠ/ ሰሙ-ሮቢ ገለአሎ ወረዳ




**ጠቋሚ፡-** ከዚህ በላይ የቀረቡት ካርታዎች የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ያዘጋጀውን ካርታ መነሻ በማድረግ ጥናቱ የተካሄደባቸውን የአማራ እና የአፋር ክልሎች በጥቅሉ፣ ቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎችን ደግሞ በነቂስ ያመለክቱ ዘንድ ተሻሽለው የቀረቡ ናቸው፡፡የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ያዘጋጀውን ካርታ በመጠቀም ተሻሽሎ የቀረበ (DRMFSS Information Management 2004 E.C)

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ለማካሄድ የተነሳሳሁት ስለ ሁለቱ ሕዝቦች አኗኗር በየጊዜው ስሰማው ከኖርኩት የግጭት ተረክ በመነሳት ሁኔታውን በፎክሎር /በባህል/ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ እና የምርምር አቅጣጫ ለመመርመር ነው፡፡

ይህ ተረካዊ እውቂያ እና ተመክሮም እንደምን እንደሰረፀብኝ፣ የጥናት ስሜቴንና ፍላጎቴንም እንደምን እንደኮረኮረው እንደሚከተለው ለማስፈር እሞክራለሁ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን ጥናት ለማድረግ መነቃቃት የፈጠረብኝ በግንቦት ወር 2002 ዓ.ም. የወረዳ ፎክሎር ጥናት ቅኝት ለማድረግ በቀወት ወረዳ በተዘዋወርኩበት ወቅት ከድንበርተኞቻቸው ሰሙሮቢ ገለአሎዎች ጋር ግጭት እንዳላቸው መስማቴ ነው፡፡ በሁለቱ ተጎራባች ወረዳዎች ማለትም በቀወት (አማራ ክልል) እና ሰሙሮቢ ገለአሎ (አፋር ክልል) ነዋሪዎች መካከል በየጊዜው ግጭት ይከሰታል፣ እርቅም ይካሄዳል ሲባል በመስማቴ፣ የግጭት መንሥዔውን እና እርቁን መልክ ለማወቅ መሻቴ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያቴ ስለ ድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች ከልጅነቴ ጀምሮ ስሰማው የኖርኩት ጆሮ-ጠገብ የሆነ የግጭት እና እርቅ ወሬ ስለነበረ የግጭት እና እርቅ ልማዱ መቀጠሉን እና መኖሩን ለመረዳት በመቻሌ የግጭትና እርቅ ሂደቱ ቋሚነትም ስለኮነኮነኝ ነው፡፡ ይኸውም እንዲህ እንደሚከተለው የተገለፀው ነው፡፡

በየሳምንቱ ቅዳሜ ሸዋ ሮቢት ከተማ ዳርቻ ላይ ዙጢ[1] የሚባል ገበያ ይቆም ነበር፡፡ ገበያው የብሔሮች እና ብሔረሰቦች ማለትም አማራ፣ አፋር፣ ጅሌ፣ አርጎባ መገናኛ ነው፡፡ በእነዚህ የተለያዩ ሕዝቦች መገናኛ ገበያ ላይ ብዙውን ጊዜ በአምባጓሮ

[1] ዙጢ ገበያ ይቆም የነበረው ከሸዋ ሮቢት ወደ ደሴ መውጫ አውራ መንገድ በስተቀኝ ከከተማው ዳርቻ ላይ ነበር፡፡ ዛሬ ገበያው ቀድሞ ከነበረበት የከተማው ዳርቻ ክፍል ተነስቶ ወደ መሃል ከተማው ተዛውሯል፡፡ ገበያው ወደ ከተማው መሃል እንዲዛወር የተደረገውም በየጊዜው በአማራ፣ በአፋር እና በጅሌ ኦሮሞ መካከል ይከሰት የነበረውን መገዳደል፣ ግጭት እንዲሁም የገበያ ሽብር ለማስቀረት ታስቦ ነው፡፡ ይህንንም የገበያ ላይ ግድያ፣ ግጭት እና ሽብር ለማስቆም የተቻለው ፖሊሶችን በከተማው መግቢያ በሮች መመደብ እና ታጣቂ ገበያተኞች ከነትጥቃቸው ወደ ከተማ እንዳይገቡ በማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ፖሊሶቹ ታጣቂ ገበያተኞችን ወደ ገበያ ሲገቡ ትጥቃቸውን አስወርደው መዝግበው ይረከባሉ፡፡ ታጣቂዎቹ ከገበያ ተመልሰው ሲወጡ ደግሞ መሣሪያዎቻቸውን መልሰው ያስረክባሉ፡፡

ፈጣሪነት እና መገዳደል ሳቢያም ስማቸው ጎልቶ ይሰሙ የነበሩት አማሮች፣ አፋሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች ነበሩ። ስለዚህም በቀድሞው ዙጢ ገበያ ላይ ግርግርና ሽብር አይጠፋም ነበር። ግርግርና ሽብሩም ተኩስ እና የሕይወት መጥፋትን ያስከትል ነበር። ይህም ሁሉ ሁኔታ ደግሞ ከቆላ እስከ ደጋ በገበያተኞች ሁሉ አማካኝነት ይነዛ ነበር። የዚህ ክስተት አኳኋን እስከ ዛሬም ድረስ እጅጉን ሲመስጠኝና ሲከነክነኝ ነበር። እናም ዛሬ ጊዜው ፈቅዶ ይህንን ተረካዊ ትውስታ ዛሬ ላይ ነገሩን በአካዳሚያዊ ዓይን እና አግባብ በፅሞና እንዳጠናው ምክንያት ሆኖኛል።

ሦስተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ ዘመኑ ቀጠን ባለበት ማለትም ድርቅ በበረታበት፣ እንስሳት የሚግጡት ሣር፣ የሚጠጡት ውኃ በጠፋበት፣ ረሃብ በጠናበት ወቅት ሁሉ (ቀወቶች ይህንን ብዙውን ጊዜ ክፉ ቀን፣ አንዳንድ ጊዜም ቀጭን ቀን ይሉታል) የግጭት ወሬ ይደምቅ ስለነበር፤ በተቃራኒውም ደግሞ አዝመራውም ሲለው ገፋ አድርጎ በሰጠበትና አውድማው ሁሉ ተጨንቆ "እህል ዱር አደረ" እንዲሁም "የራሳ አውድማ ተጨንቋል" በሚባልበትም ወቅት ሁሉ የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ወሬ ጠንከር ብሎ ይሰማ ስለነበር የከፋ ችግር እና ጥጋብ እንደምን ከግጭት ጋር እንደሚያያዙ የማወቅ ፍላጎት እና ጉጉት ነው። ምክንያቱም የችግር እና የጥጋብ ዘመናት በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የግጭት መባባሻዎች መሆናቸውም እጅጉን ይከነክነኝ ነበርና። እንደማስታውሰው በቀወት እና በአጎራባቾቹም ወረዳዎች ነዋሪዎች ዘንድ አንዳንድ ጊዜ "አፋሩ ዘንድሮ በጣም ተቸግሯል"፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ "አፋሩ ዘንድሮ በጣም ጠግቧል፣ ወደ ላይ ለመውጣት አቆብቁቧል፣ ለወረራ አነጥንጧል፣ በነጌሶ በኩል ይህን ያህል ሰው ሞቷል፣ በራሳ በኩል ተፋጠዋል፣ ዘንድሮ እንጃ በጣም የሚያስፈራ ነው" ወዘተ የሚል አስፈሪና አንሸቅሻቂ ዓይነት ወሬ በየጠላ ቤቱ፣ ሰንበቴው፣ ዕድሩ፣ ማርገጃው ላይ ሁሉ ይደመጥ ነበር። ድንገት ሊመጣ ስለሚችለውም ነገር ሁሉ መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ ምክክር ይደረግ ነበር። እናም ይህ ዓይነቱ ተረክ ከላይ እንዳነሳሁት ዛሬ የከፋ ችግር እና የጥጋብ ዘመን ከግጭቱ ጋር ያላቸው ትስስር ወይም ተዛምዶ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ጭሮብኝ፣ እመረምረውም ዘንድ ሳይገፋፋኝ የቀረ አይመስለኝም።

አራተኛው ምክንያት ደግሞ እዚያው ቀወት ወረዳ ለቅኝት ጥናት መስክ በቆየሁበት እና መረጃዎችን ባሰባሰብኩበት ወቅት በቀወቶችም፣ በሰሙሮቢ ገለአሎዎችም ዘንድ ስለ ግጭት የሚያወሱ ሥነቃሎች መኖራቸውን ማድመጤ፣ ግጭቱን ከተረክ ጋር አስተሳስሬ እና ቀረብ ብዬም እመረምረው ዘንድ ጭላንጭል ብርሃን ስለፈነጠቀልኝ

ነው፡፡ በተለይም  ከወረዳዎቹ ተወላጅ ተማሪዎች ከሰበሰብኳቸው ሥነቃሎች መካከል የተወሰኑት ግጭትን በተለያዬ መልኩ የሚያስተጋባ መልዕክት እንዳላቸውም ማየቴ በሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ዙሪያ አንድ ጥርጣሬ እንዳሳድር አድርጎኛል፡፡ ግጭቱ የማያባራ ወይም ዑደታዊ የሆነው ለምንድነው? የሚል፡፡

ግጭቱ የማያባራ ወይም ዑደታዊ የሆነው በሁለቱ ሕዝቦች ተረኮች ውስጥ ስላለ፣ ስለተተከለ እና አሕዝቦትም ስላገኘ ውስጣዊ የባህል ሥሪትም ስለሆነ ሳይሆን አይቀርም የሚል፡፡ እናም የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት እና እርቅ ዑደታዊነት ምናልባትም ባመዛኙ ተረክ ወለድ ወይም ከተረክ የሚመነጭ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት እንዳሳድር እና ሁኔታውንም በቅርበት እመረምር ዘንድ የኮረኮረኝ ይመስለኛል፡፡

አምስተኛው እና ምናልባትም ዋነኛው የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ደግሞ ግጭቶች ከተጨባጭ /tangible/ ምክንያቶች በተጨማሪ በኢ-ተጨባጭ /intangible/ ምክንያቶች የሚከሰቱ መሆናቸውን የተመለከቱ ጥናቶች አለመኖራቸውን መታዘቤ ነው፡፡ በተለይም በኢ-ተጨባጭ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶች በተጨባጭ ምክንያቶች ከሚከሰቱ ግጭቶች ይልቅ ለመቆጣጠር እና ለመግታት የሚያስቸግሩ፣ መልካቸውን እየለዋወጡም የሚቀጥሉ እና የማያባሩ ወይም ማቆሚያ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት ስላለኝ፡፡ ይኸውም የሆነበትን ምክንያት ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ ኋላ ላይ ደግሞ በመሰል ጥናቶች ክለሳዬ ውስጥ ዘርዘር አድርጌ አወሳለሁ፡፡

ለዚህ ጥናት መደረግ  አንዱ ሰበበ-ምክንያት ከዚህ ቀደም በግጭት እና በግጭት አያያዝ፣ አረጋገብ፣ አገታት ወይም አስተጋገስ እና አፈታት ዙሪያ በኢትዮጵያ የተደረጉት ጥናቶች ግጭቶችን ከተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ብቻ አያይዘው የመረመሩ መሆናቸው እና ኢ-ተጨባጭ የሆነው ሥነቃል ግጭትን በመትከል፣ በመቀስቀስ፣ በማናር እና በማሕዘብ ረገድ ያለውን ሚና ነገሬ ብለው አለመመርመራቸው ነው፡፡ ከዚሁ ጋር የተያያዘው የቀደምት ግጭት ተኮር ጥናቶቹ ውሱንነት የማንነት ተመሳሳይነትም ሆነ ልዩነት ባላቸው ሕዝቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች በዘላቂነት መፈታት አለመፈታታቸውን ወይም የእርቅ ሥርዓቶቻቸውን ዘላቂነት፣ ፅንዑነት ወይም ልልነት አለማመልከታቸው ነው፡፡

ሌላው ቀደምት ጥናቶቹ የሚያነሱት እና የሚያመለክቱት ዓቢይ ጉዳይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶች በባህላዊ ሽምግልና ተቋማት የሚፈቱበት ሥርዓት መኖሩን፣ ተቋማቱም ቅቡልነት ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት

ከተጨባጭ የግጭት ምክንያቶች በተጨማሪ ኢ-ተጨባጭ የግጭት ምክንያቶችን ሊያመለክት ይችላል፡፡ በዚህ ረገድም እስካሁን የነበረውን የምርምር እና የዕውቀት ክፍተት ሊሞላ ይችላል የሚለው ሌላኛው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች

የዚህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" ጥናት ዓቢይ ዓላማ የቀወት ወረዳ አማሮችን እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮችን ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶች ምክንያቶች እንዲሁም የግጭት አፈታት ሂደት ጥንካሬ እና ድክመታቸውን ሁኔታ መመርመር ነው፡፡ ይህንንም ዓቢይ ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ንዑሳን ወይም ዝርዝር ዓላማዎችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲሁም በተጎራባችነታቸው የሚጋጩባቸውን ዓበይት ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ ይህንንም ማድረግ ያስፈለገው የድንበርተኞቹን ሕዝቦች ግጭት እና እርቅ አኳኋን ማወቅ የሚቻለው በመጀመሪያ ደረጃ የሁለቱን ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭቶች መነሻዎች እና የግጭቶች አፈታት ሥልቶቻቸውንም በመረዳት ስለሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም ከውስጣዊ ግጭቶቻቸው እና አፈታቶቻቸው በመነሳት፣ የሁለቱን ሕዝቦች ግጭቶች ምክንያች እና አፈታት ሂደት ማነፃፀር ስለሚገባ፣ በእነዚህም ላይ ተመስርቶ ድግሞ የሁለቱን ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶች እና አፈታት እንዲሁም አረጋገብ እና ወቅታዊ እርጋቶች አኳኋን ማለትም የእርቅ ልልነት እና ፅንዑነት በንፅፅር ማየት ስለሚቻል ነው፡፡

ሥነቃል በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ግጭትን በማመንጨት፣ በመቅረፅ፣ በመትከል፣ በማሰራጨትና በማህዘብ እንዲሁም በማርገብ ረገድ ምን ድርሻ ወይም ሚና እንዳለው ይመረመራል፡፡ በዚህም ሂደት ውስጣዊና /እርስበርስ/፣ ውጫዊ ማለትም በሁለቱ ጎረቤታሞች መካከል ግጭት የሚተከልባቸውን፣ የሚኸዝብባቸውን፣ የሚዛመትባቸውን እና የሚገንባቸውን ሥነ ቃሎች፣ እንዲሁም ሀገረሰባዊ እውቀቶችና ልማዶች ሥርዓት-ሂደቶች ይዘትና ትርጓሜ እየተነፃፀረ ይመላከታል፡፡

ግጭቶቹ ከተከሰቱ በኋላ የሚፈቱባቸውን ባህላዊ የሽምግልና ልማዶች ማለትም ግጭት አረጋግብ፣ አስተጋገስ፣ አገታት ወይም አፈታት ሂደቶች እንዲሁም በሂደቶቹም የሚደረጉትን የእርቅ ሥርዓተ-ክንዋኔዎች፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ክንዋኔዎች እና እሴቶች ይመዘዛል፣ ይገለፃል፣ ይተረጎማልም።

ከዚህ በማስከተል ደግሞ ለመሆኑ ከእነዚህ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች የሚፈልቁት፣ ዓላማዎቹንም ለማሳካት የሚያስችሉት እና የሚበጁት የምርምር ጥያቄዎች[2] ምን ምን ናቸው? የሚለውን በዝርዝር ወደ ማየት እንዝለቅ።

## 1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች[3]

ይህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል።

1) ድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ውስጣዊ ግጭቶች ውስጥ የሚገቡባቸው ተጨባጭ የግጭት ምክንያቶች ምንድናቸው ?
2) ድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ውጫዊ ግጭቶች ውስጥ የሚገቡባቸው ኢ-ተጨባጭ የግጭት መንሥኤዎች ምንድናቸው ?
3) ድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸው መንገዶች ጥንካሬዎች እና ውሱንነቶች ወይም ድክመቶችስ ምን ይመስላሉ?
4) የሁለቱ ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭት መፍቻ ሥርዓት ሥርዓተ አፈፃፀሞች፣ ሂደቶች፣ የእርቅ ማፅኛ ወይም ማሳረጊያ ሥርዓተ መኃላዎች /rituals/ እና ትዕምርቶች ከሁለቱ ሕዝቦች ውጫዊ ግጭት መፍቻዎች ሥርዓተ አፈፃፀሞች ሂደቶች እና የእርቅ ማፅኛ ወይም ማሳረጊያ ሥርዓተ መኃላዎች /rituals/ እና ትዕምርቶች ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላል?

---

[2] የምርምር ጥያቄዎቹ የያዟቸው ሐሳቦች በምርምር ዓላማዎቹ ከተነሱት መሰረታዊ ሐሳቦች የተለዩ አይደሉም። ይሁን እንጂ የምርምር ጥያቄዎቹ ተለይተው እንዲሰፍሩ ያደረግሁት የጥናቱን ሂደት ፍንትው አድርጎ ለማሳየት ያህል ነው።

5) የእርቅ መደምደሚያ ወይም ማሳረጊያ ሥርዓተ መኃላዎች /rituals/ እና ትዕምርቶቹ ትርጓሜ እንዲሁም ፅንዑነታቸው እና ልልነታቸው ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው፡፡

እዚህ ላይ ለመሆኑ ከዚህ በላይ በቀረቡት ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች ውስጥ የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ውስጣዊ የግጭት መንሥኤዎች እና የግጭት መፍቻ ሥርዓቶችን ከሁለቱ ድንበርኛ ሕዝቦች ግጭት እና ግጭት አፈታት ሁኔታ ጋር አካቶ ማቅረብ ያስፈለገው ለምንድነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የዚህም ምክንያቱ ምንም እንኳን የጥናቱ ዓቢይ ጉዳይ የቀወት አማሮችን እና የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችን ግጭት እና ግጭት አፈታት የሚመለከት ቢሆንም የሁለቱን ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭት እና ግጭት አፈታት እንዲሁም ሥነቃል አካቶ መመርመር ያስፈለገው ዋናውን የግጭት ጉዳይ በአፅንኦት ለማየት የሚያስችል አበርክቶ ስላለው ነው፡፡

ከዚህ በማስከተል ከዚህ በላይ ለቀረቡት ዓቢይ እና ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች ከሚሰጠው ምላሽ ምን ጥቅም ሊገኝ ይችላል? የሚለውንም እንመልከት፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ድንበርተኞቹ የቀወት አማሮች እና ሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችን ውስጣዊ እና ውጫዊ ነባር እና ህያው የግጭት መንሥኤዎች እና የግጭት አፈታት ሥልት ለመረዳት ያስችላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሁለቱ ተጎራባች ሕዝቦች ግጭታቸውን በዘላቂነት መፍታት ያልቻሉበትን እና በግጭት እና በእርቅ ዑደት ውስጥ የሚኖሩበትን ምክንያት ያመላክታል፡፡ በዚህም ሂደት የሁለቱን ሕዝቦች የሽምግልና አፈፃፀም ሂደታቸውን እና እርጋታቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለይቶ ያመለክታል፡፡ በዚህም ስለ ሁለቱ ሕዝቦች የግጭትና እርቅ ሁኔታ ያለንን የእውቀት አድማስ ያሰፋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃም የሁለቱን ሕዝቦች ኢ-ተጨባጭ የግጭት መንሥኤዎች፣ መስተጋቢያዎች ወይም የግጭት ሰበቦች ማለትም ተረኮች ወይም ሥነቃሎች፣

ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ ወጎች እና ልማዶች እንዲሁም አፍቅሮተ-ቁሶች በግጭት አተካከል፣ አህዝቦትና ተስተላልፎ ላይ ያሏቸውን አስተዋፅኦዎች ያመለክታል፡፡

በአራተኛ ደረጃም ሁለቱ ተጎራባች ሕዝቦች ሕይወታቸውን በማያቋርጥ ግጭት እና እርቅ ሁኔታ ውስጥ የሚመሩበትን ምክንያት መመርመሩ መሰነዱና መግለፁም እስከ አሁን ድረስ በውል ተለይቶ ያልታወቀውን የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት ታሪካዊነት ምክንያት ለማወቅ ይረዳል፡፡

በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ለሚያሳስባቸውና ግጭቱንም በሰከነ መንገድ ለመፍታት ለሚሹ እና በአካባቢው ግጭት አፈታት ላይ የፖሊሲ ሐሳብ ለሚያመነጩ ወገኖችም የማህበረሰቦቹን ግጭት ተኮር ባህርይ እና ስለ ግጭትም ያላቸውን ዓለማዊ አመለካከት በአፅንኦት እንዲያጤኑ እና በግጭት አመንጪ ባህል ለውጥ ላይ እንዲሰሩ፣ ትምህርትን እንዲያስፋፉ ጥቁምታ ይሰጣቸዋል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የጥናቱን አድማስ እና ወሰን ማለትም ጥናቱ የሚያካልለውን እና የማያካልለውን ወይም የሚነካውን /የሚያካትተውን/ እና የማይነካውን /የማያካትተውን/ ነጥብ ለመቀንበብ እና ለማመልከት ይሞከራል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት ዐቢይ ርዕሰ-ጉዳዩ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" ነው፡፡ ስለዚህም ሁሉንም የአማራና የአፋር ክልል ተጎራባቾች ወይም ድንበርተኞች ግጭትና የግጭት አፈታት ሥርዓት አይመረምርም፡፡ ትኩረቱ በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን ቀወት ወረዳ እና በአፋር ክልል ዞን አምስት ውስጥ በሚገኘው ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭት እና ግጭት አፈታት ሁኔታ ላይ ነው፡፡ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች በኩታ ገጠም መሬት ላይ የሚገኙ እንደመሆናቸው ምርምሩም በዚሁ ገፀ-ምድር ነዋሪዎች ዙሪያ የተወሰነና የተገደበ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጥናቱ ግኝት በተራዛሚ ለአማራ ክልል አማሮች ብቻ ሳይሆን ተጠኚዎቹ ሕዝቦች "አማራ" እና "እስላም" ብለው በተለምዶ ለሚያውቋቸው ሕዝቦች ሁሉ የሚሰራ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ /ፎክሎራዊ/ ጉዳዮች በዓለም ዙሪያ የግጭት ሙሻዙር እየሆኑ

ሰላምና መረጋጋትን እያወኩ እና ነውጥ እያስከተሉ መሄዳቸውን በትንተናው ክፍል ተመልክቶ እናገኛለንና ነው፡፡

በጥናቱም ሂደት የሚዳሰሱት መልክዓ ምድራዊ ገፅታ፣ ሥርዓተ አኗኗር ማለትም ሥራ፣ አመጋገብ፣ አፍቅሮተ-ቁስ፣ አሰፋፈር፣ ሁለቱ ሕዝቦች የሚጋሯቸው ተፈጥሯዊ ሀብቶች (መሬት፣ ውኃ፣ ግጦሽ፣ ደን ወዘተ)፣ ቃል ታሪክና ጽሑፍ ታሪክ፣ አንዳቸው ለሌላኛቸው ያላቸው ማህበራዊ አተያይ ይሆናሉ፡፡ ከእነዚህ ገለፃዎች በተጨማሪም የሁለቱ ሕዝቦች ሥነቃሎች ስለምን እንደሚያወሱ ወይም ስለምን እንደሚባሉ ለማስተዋል እና ሥነ ቃሎቹ ግጭትን እንደምን እንደሚስሉት ለመመርመርና በዚህም ሂደት ሁለቱ ሕዝቦች ስለግጭት ያላቸውን አተያይ ለማጤን ተሞክሯል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ሥነቃል ለግጭት መከሰት፣ መተከልና መዝለቅ የሚኖረውን አበርክቶ በማሳየት የተሟላ ምልከታና ሥዕል ለመስጠት ያህል ሲባል ነው፡፡

ጥናቱ ምንም እንኳን የሁለቱን ሕዝቦች ታሪካዊ ግንኙነት በወፍ በረር ዓይነት ሁኔታ በማስቃኘት እና የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት ታሪካዊነት እና ተረካዊነት[4] ለማሳየት የሚሞክር ቢሆንም ሁለቱ ሕዝቦች በዘመናት ጉርብትናቸው ውስጥ ግጭት ውስጥ የገቡባቸውን ምክንያቶች፣ ያጋጠሙ ሰብአዊና ቁሳዊ ኪሣራዎች፣ ግጭቶቹም ሲበርዱባቸው የቆዩትን መላዎች በዝርዝር አይዳስስም፡፡

## 1.6. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በዚህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳዎች" ጥናት ሂደት ውስጥ ሦስት መሰረታዊ ችግሮች አጋጥመዋል፡፡

የመጀመሪያው የገንዘብ እጥረት ነበር፡፡ የዩኒቨርሲቲው ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ ማካሄጃ የመደበው ገንዘብ በቀወት እና ሰሙሮቢ ቆላማ ወረዳዎች ለመንቀሳቀስ ቀርቶ ደብረ ብርሃንም በወጉ አድርሶ የሚመልስ አልነበረም፡፡ ስለዚህም ከቁልፍ መረጃ ተባባሪዎች ጋር በነበረኝ ቆይታ ወቅት ሁሉ ወግ እና ጨዋታ

[4] እዚህ ላይ ታሪካዊነት እና ተረካዊነት የተያዙ ነገሮችነታቸውን፣ ፎክሎሩም ታሪክና ተረክ ጭምር መሆኑን ያጤኗል፡፡

የማስከፈቻ፣ ጊዜ የማራዘሚያ እና  የማቆያ ወይም የማስቀመጫ ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ ያጥረኝ ነበር። ስለዚህም እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለመወጣት የሞከርኩት ችግሩን በችግር በመወጣት ነበር ማለት ይቻላል። አስቤዛዬን በማሳሳት።

ሁለተኛው መሰረታዊ ችግር በሁለቱ ወረዳዎች ሕዝቦች ዘንድ ስመ-ጥር የሆኑትን የአገር ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪዎች፣ ባላባቶች፣ የጎበዝ አለቆች ለማነጋገር ስሞክር በቀላሉ ይሁንታቸውን ማጣቴ፣ ፈቃደኞች ሆነው ካነጋገርኳቸውም መካከል ሁሉንም በመቅረፀ ድምፅ እና ምስል ለመሰነድ አለመቻሌ ነበር። ይኸውም ሊሆን የቻለው ዓላማዬ በትክክል ለምርምር መሆኑን በመጠራጠራቸው እና በመሥጋታቸው እንደሆነ የነገሩኝ አሉ። ምሳሌዎች ልስጥ።

አንድ ታዋቂነታቸው ተነግሮኝ እና እውነትነቱንም አረጋግጬ፣ በመንገድ መሪ ታግዤ እና ረጅሙን መንገድ ተጉዘን፣ እራሴን አስተዋውቄ፣ ዓላማዬን ገልጬ ስለ ድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች አኗኗር ሁኔታ እና ግንኙነት ሁኔታ ቃለመጠይቅ አደርግላቸው ዘንድ በጎ ፈቃደኝነታቸውን የጠየቅኋቸው የአገር ሽማግሌ እኔንም፣ መንገድ መሪዬንም፣ አካባቢያቸውንም ቃኘት ካደረጉ በኋላ  "አንተ ሰውዬ ዛሬ እኮ የአማራ እና የአፋር ግጭት የለም። የምን ግጭት ነው የምታሚርተው። ዛሬ ብሔር ብሔረሰብ እና ሕዝቦች ፍቅር በፍቅር ሆነው ሳለ አንተ ምንድነው የምትናፍቀው? እኔ በዚህ ላይ ምን ልጨምርበት ነው?" አሉኝ። እኔም "አይ እንዲያው ስለ አማራ እና አፋር አኗኗር እንዲያጫውቱኝ ብዬ ነበር" አልኳቸው። እርሳቸውም "ታዲያ እሱንማ እዚያው አዲስ አበባ ሆነህ በራዲዮና በቴሌቪዥን ትሰማው የለም ወይ? እዚህ ድረስ ምን አንገላታህ?" አሉኝ። እኔም "እንዲያው ድንገት የተለየ ነገር ካለ ብዬ ነበር አልኳቸው"። እርሳቸውም እንደገና ወደ መንገድ መሪዬ መለስ ብለው "አንተ በቃ እኔን ዘመድ ማፍሪያ አድርገህ፣ የእንግዳ አጫዋች ልታድርገኝ ነው ሐሳብህ? ለምን ሰው ታመጣብኛለህ? ደክሞኛል፣ ታክቶኛል ልረፍበት ብዬህም አልነበር ወይ?" አሉት። እርሱም "አይ ይሄ የኛው ሰው ነው። ለወረዳውም ደብዳቤ ይዞ ነው የመጣው፣ ይታወቃል፣ አጠራጣሪ አይደለም። በዚህ በኩል ሥጋት አይግባዎ" ወዘተ እያለ ሊያለሳልሳቸው ሞከረ። አንዳንድ ነገሮች ሰነዘሩ። "አያችሁ ወይ! አላውቅም አንድ ነው። አውቃለሁ ብዙ ነው ሲባል አልሰማችሁም? ደግሞም በኋላ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ይሻላል እንዲሉ በስተርጅና ችግር እንዳላመጣ እፈራለሁና ነው" ካሉ በኋላ እንዲህ ቀጠሉ። "ለማናቸውም አንተ አጥኚ ነኝ የምትለው ወንድሜ! ለሰው አትናገር፣

አትፃፍም እንጂ አማራ እና አፋር ግጭት ልማዳቸው ነው፡፡ ዓመል፣ ልማድ ይለቃል? ይሄው ነው እዚህ አካባቢ ግጭት ልማድ ነው በቃ ! በል እውነቱን ነግሬሃለሁና ይሄን እንደ ሐሳብ ስንቅ ያዝ ሂድና ሌሎቹን ጠይቃቸው፡፡ " ብለው አሰናበቱኝ፡፡

አንድ እውቅ የጎሳ መሪ ደግሞ እቀያቸው እንደደረስኩ "ምን ፈልገህ እዚህ ድረስ መጣህ?" አሉኝ፡፡ እኔም "ስለ አማራ እና አፋር የጉርብትና አኗኗር ሁኔታ እንዲያጫውቱኝ ነበር የመጣሁት" አልኳቸው፡፡ እርሳቸውም ትንሽ አሰብ ካደረጉ በኋላ "ይህንን እኔ አልነግርህም፡፡ ዛሬ ስለዚህ ሁኔታ የሚናገሩት እና የሚያውቁት ልጆቹ ናቸው፡፡ እነሱን ጠይቃቸው፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡ ይልቅስ ደክሟችሁ ይሆናል እና ኑ እቤት ግቡ! የበቆሎ ቂጣ እና ወተት ልጋብዛችሁ" አሉን እኔን እና መንገድ መሪዬን፡፡

እኔ እና መንገድ መሪዬም በዓይን ተያይተን እና ምናልባትም በግብዣው ላይ ቢለሳለሱ በሚልም ተግባብተን እየተከተልናቸው ሳለም ዞር ብለው "እያችሁ ወንድሞቼ! እንደምታውቁት ወሬ እና ጭስ መውጫ አያጣም፡፡ እስከ አሁን ለኔ ያነሳችሁልኝን ነገር እሴት እና እልጅ ፊት እንዳታነሱብኝ፣"[5] ሲሉ አስጠነቀቁን፡፡ እነዚህን ሁለት አብነቶች የጠቀስኳቸው አረጋውያኑ መረጃ ቢኖራቸውም መረጃውን እንዳይሰጡ "ቆፈን" የያዛቸው መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ዓይነቶች መረጃ የመንፈግ ተግዳሮቶች የተወጣኋቸውም መረጃውን ከጥናቱ ውጪ ለብዙኃን መገናኛ ፍጆታ ወይም ለሌላ ተግባር እንደማላውል በአማላጅ ዘመድ አዝማድ በኩል በማስረዳት እና ቃል በመግባት ነው፡፡

ሦስተኛው ችግር በሄድኩበት ሥፍራ ሁሉ በመንግሥት መዋቅር ሥር ያሉ ሰዎች "ማን ነህ? ምንድነህ? ወዴት ነህ? ይህን ማጥናት ለምን አስፈለገህ?" እያሉ፤ ነዋሪዎች ደግሞ የነፍሳቸውን "ደሞ ብላችሁ ብላችሁ የመጣያችንን፣ የመስማሚያችንን ነገር ሁሉ መጎርጎር ገባችሁ?" በሚል አታካች ጥያቄ እየወጠሩኝ ለጥያቄውም መልስ ለመስጠት እረጃጅም ሰዓታት ማባከኔ ነው፡፡ ይሁን እና የጊዜ ብክነቱ ከእኔ ፍላጎት አንፃር እንጂ ለነዋሪዎቹ ጊዜ መውሰድ ቅቡል እሴት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም በቀወቶች ዘንድ ግራ የሚያጋባ እና በፍጥነት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስቸግር ጉዳይ ሲያጋጥማቸው "ከቁርበቴ /ከአልጋዬ/፣ ከመደቤ ጋር ልምከርበት፣ ነገሩን ልተኛበት"

[5] በአካባቢው ልማድ ከባድ ወይም ጥብቅ ሚስጢር ሴቶች እና ልጆች በተሰበሰቡበት አይነሳም፡፡ ከተነሳም ነገሩን ለነፋስ እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡ ተናጋሪውንም ሰው እከሌ "ነገሩን የት እንደሚጥል አያውቅም" ያስብለዋል፡፡

ወዘተ እንዲሁም ሰሙሮቢ ገለአሎዎች "ትዕግሥትና ፅናት የስኬት ትክክለኛ መንገዶች ናቸው" /Umam Kolbaheni Ekhabana Tayshi/ የሚሉ ምሳሌዎች እንዳሏቸው አውቃለሁና፡፡

በተለይ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በመንግሥት መዋቅር የተካተቱ ሰዎች "በጥናት ሰበብ ስንት ነገር እንደሚሰራ እናውቃለን! የሕዝቦች አንድነትና ሰላም በሰፈነበት ዘመን እንዲህ ዓይነት ነገር አጠናለሁ ማለት ጤነኛ ተልዕኮ አይደለም፡፡ ስለዚህ ቀጥ ብለህ በሰላም ወደመጣህበት ተመለስ ጌታው" እያሉ እጅግ ያስቸገሩኝም ነበሩ፡፡ በተለይ እንዲህ ዓይነቶቹን አጠቃላይ የጥናቱን ሂደት አዋኪ ችግሮች ያለፍኳቸው የዞን መስተዳድር ሥሙ-ጥር ባለሥልጣኖችን ሥም በመጥራት፣ እውቂያ እና ግንኙነት በመጠቀም እና የሥሮቹ ማለትም ዝቅተኞቹ ባለሥልጣኖች ፍረጃቸውን እና ጥርጣሬያቸውን እንዲያነሱልኝ፣ ጫናቸውን እንዲያቀሉልኝ እና እንዳይጫኑኝ በማድረግ ነበር፡፡

በአጠቃላይም የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደት ብዙ ተግዳሮቶች ያጋጠሙበት፣ የተፈታተኑበት እና በተለያየዬ መንገድም የታለፉበት ነበር፡፡

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት አሥር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የምዕራፎቹም አደረጃጀት እና ይዘት በሚከተለው አኳኋን የተሰናዳ ነው፡፡

ምዕራፍ አንድ ማለትም ይህ የመግቢያው ክፍል የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ገደብ፣ በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች እንዲሁም ይህን የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉትን አካቷል፡፡

ምዕራፍ ሁለት የግጭት ምንነት፣ ዓይነት እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች የተቃኙበት እንዲሁም ስለ ሁለቱ ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች ግጭት እና ግጭት አያያዝ ሁኔታም ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ለማገግ እና ለማቅረብ የተሞከረበት ነው፡፡

ምዕራፍ ሦስት የጥናቱን ዓይነት እና የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ዘዴዎች ይዘረዝራል፡፡

ምዕራፍ አራት ጥናቱ የተካሄደባቸው የአማራ እና አፋር ክልሎች ድንበርተኛ ወረዳዎች ማለትም ከአማራ የቀወት ወረዳ እና ከአፋር የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ዳራ ማለትም ሕዝብ፣ መልክዓ ምድር፣ የሕዝብ መተዳደሪያ፣ መሰረተ ልማት ማለትም ትምህርት፣ ጤና፣ ኃይማኖት፣ እምነት፣ ጋብቻ፣ የሥራ ባህል፣ አሰፋፈር፣ ቤት አሰራር፣ ኢኮኖሚ ገለፃ የቀረበበት ነው፡፡

ምዕራፍ አምስት የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ሕዝቦችን ጥንተ አመጣጥ፣ ማንነት እና ግንኙነት ተኮር አፈ-ታሪክ ይዳስሳል፡፡ ይኸውም የኋሊት ቅኝት የተደረገበት ዋና ምክንያት በተለይም የሁለቱ ሕዝቦች የግንኙነት አኳኋን አፈ-ታሪክ ለሁለቱ ሕዝቦች ነባራዊ ግጭት አበርክቶ ያለው መሆን አለመሆኑን ለመረዳት እንዲያስችል ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስት የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ሕዝቦችን ጥንተ አመጣጥ፣ ማንነት እና ግንኙነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ ይቃኛል፡፡ ይህንም ቅኝት ማድረግ ያስፈለገው የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት በሥነቃል ጭምር የሚገለፅ ሆኖ በመገኘቱ የሥነቃሉን ተዓማኒነት በታሪክ ሰነድ ምርመራም ማረጋገጥ ግቡዕ ስለሆነ ነው፡፡

ምዕራፍ ሰባት ከቀወትና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች የተሰበሰቡ እና ከአፈ-ታሪክ ውጪ የሆኑ ሥነቃሎች ይዘት የቀረበበትና መልዕክታቸው የተመረመረበት ግጭት ተኮር መልዕክታቸውም ተመዞ የወጣበት እና የተመላከተበት ነው፡፡

ምዕራፍ ስምንት የድንበርተኞቹን ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ የግጭት መንሥኤዎች እና የግጭት አፈታት በሁለት ዓበይት ንዑሳን ርዕሶች ከፍሎ ያመለክታል፡፡ ክፍፍሉም እንደሚከተለው ነው፡፡

የመጀመሪያው ዓቢይ ርዕስ የጥናቱ ተተኳሪዎች የሆኑት የቀወትና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች እርስበርስ ማለትም ውስጣዊ ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸውን ምክንያቶች እንዲሁም እነዚህኑ ውስጣዊ ግጭቶቻቸውን የሚያረግቡባቸውን ወይም የሚገቱባቸውን እና የሚፈቱባቸውን መንገዶች ያመለክታል፡፡

የምዕራፉ ሁለተኛ ዓቢይ ርዕስ ደግሞ የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ተጎራባች ሕዝቦች ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸውን መንሥኤዎች እና የሽምግልና ሂደት፣ የእርቅ አፈፃፀም ሂደት ከጥንካሬ እና ድክመቱ ጭምር ይዘራዘራል፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎችን ግጭት መንሥኤዎች እና ግጭት አፈታት ትንተና እና ትርጎማ ይዟል።

ምዕራፍ አሥር የጥናቱ ማጠቃለያ ነው። የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች ወረዳዎች ግጭትና ግጭት አፈታት ጥናት የተጠቃለለበት።

# 2. የግጭት እና የግጭት አፈታት ንድፈ ሐሳብ ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ለጥናቱ ማዕቀፍ መስጫነት ይረዱ ዘንድ የግጭት ምንነት፣ የግጭት ዓይነቶች እና አፈታት ዘዴዎች ንድፈ ሐሳቦች ይማተራሉ፡፡ እነዚህንም ማካተት እና ማየት ያስፈለገው በአሁኑ ወቅት ስለ ግጭት ምንነት፣ ዓይነት እና አፈታት ዘዴ ያሉትን ዓበይት ንድፈ ሐሳቦች ለመቃኘት እና ይሄም ጥናት የታገገበትን ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ለማመልከት ይረዳ ዘንድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ምዕራፉ ከመጠናቀቁ በፊት ለቀወት እና ለሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግጭት፣ የግጭት ዓይነት እና ግጭት አፈታት ሁኔታ የሚስማማ ተግባራዊ ብያኔ /functional definition/ ይሰጣል፡፡

በምዕራፉ መጨረሻ ደግሞ መሰል ጥናቶች ይከለሳሉ፡፡ በክለሳዎቹም እስከ ዛሬ መሰረታዊ የግጭት መንሥዔዎች እና የግጭት መፍቻዎች ተብለው የተለዩ ተቋማት ይማተራሉ፡፡ የዚህም ጥናት መለዮ ነጥቦች ይጠቆማሉ፡፡

## 2.1. የግጭት ምንነት

ግጭት ምንድነው? ስንል የምናገኘው ምላሽ የተለያዩ ነው፡፡ ለምሳሌ Encyclopedia Britanica (1973:370) ግጭት የማህበራዊ ለውጥ ዋነኛ ማነቃቂያ እና መከሰቻ ስለመሆኑ በማርክሳውያንን አስተምህሮት ላይ ተመሥርቶ ያብራራል፡፡ በተመሳሰይ ሁኔታ እነ Eshleman, Cashion, Basirico (1993፡46-48) ግጭት የማህበረሰብ ሕይወት ቋሚ ገፅታ ነው፡፡ ኅብረተሰብንም በውል መረዳት እና መተንተን የሚቻለው ከግጭት እና ከሥልጣን አንፃር ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ቀደምት የኅብረተሰብ ግጭትን ከማህበራዊ መዋቅር ጋር አስተሳስሮ በመረመረው ካርል ማርክስ አስተሳሰብ ላይ ተመርኩዘው እንዳወሱት የኅብረተሰብ መዋቅር የሚወሰነው በምጣኔ ሀብት ድርጅት በተለይም በሀብት ባለቤትነት ነው፡፡ ሌሎቹ እንደ ኃይማኖታዊ ቀኖና ባህላዊ እሴቶች፣ ግለሰባዊ እምነቶች፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ መደባዊ ክፍፍል ያሉት ሁሉ በመሰረቱ የምጣኔ ሀብት ድርጅቱ ነፀብራቆች ናቸው፡፡ የታሪክም ተረክ የሚያስረዳው ይህንኑ የመደቦች ግጭት ነው ይላሉ፡፡

Coser (1956:8) ደግሞ ግጭት ለእሴት ወይም ለደረጃ፣ ለሥልጣን፣ ለጥሪት ሲባል በቡድኖች ወይም በግለሰቦች መካከል የሚደረግ ትግል መሆኑን፣ ግቡም ተፎካካሪ ኃይሎችን ለማዳከም፣ ለመጉዳት፣ እንዲያም ሲል ለማጥፋት እንደሆነ ይገልፃሉ። Augsberger ም (1992፡18) "ግጭት በየባህሉ የተለያዩ መልክ ቢኖረውም ሁለንታዊ ነው። ስለዚህም በሰው ልጆች ዘንድ ሁሉ የተለመደ፤ ነገር ግን እንደየባህሉ እና እንደየግለሰቡም ደግሞ በተለያዩ ሁኔታ የሚገለፅ ክስተት ነው" ይላሉ።

ስለዚህም ግጭትን በማጥናት ሂደት ውስጥ ግጭትን ከባህላዊ ማንነት እና ማኅበረሰባዊ መዋቅር እና አገልግሎቱ አንፃር መመርመሩ ተገቢነት ይኖረዋል። የግጭትን ማህበረሰባዊነት ማለትም ማህበራዊነት የምናነሳውም ከተግባቦታዊነቱ እና ማህበራዊ ባህርይነቱ እና እሴትነቱ አንፃር ነው። ምክንያቱም ግጭት የሚመነጨው አንዳች ዓይነት ማህበራዊ ተራክቦና ተግባቦት ባለበት ነውና። እንደሚታወቀው አንዳችም ዓይነት ግንኙነት በሌለበት ግጭት አይቀሰቀስም፣ አይከሰትምም። ስለዚህም ግጭት የግንኙነትም፣ የመቀራረብም ውጤት ነው ማለት ይቻላል።

ይሁንና የግጭት ጥናት ሊቃውንቱ ግጭትን የሚበይኑት ከሰብኣዊ ባህርይነት እስከ ማኅበረሰባዊ ክስተትነት በማሳደግ ነው። ስለዚህም የግጭት ተመራማሪዎቹ የግጭትን ምንነት እና አመነጫጨት የሚያዩት ከሰብኣዊነት ወይም ደመ-ነፍሳዊነት እስከ ማኅበረሰባዊነት ለጥጠው[6] ነው ማለት ይቻላል።

Bartos እና Wehr (2002፡1)፣ Lulofs እና Cahn (2000: 9-11)፣ Anderson (1999፡10)፣ Fisher (1982፡567)፣ Galtung (1973:19-22) እና Boulding (1962፡5) እንደሚያወሱት የግጭት ሥረ መሰረቱ የሰው ልጅ ሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሮ እና ባህርይ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ ግጭትን በሁለንተናዊ ሕይወቱ ሁሉ ተለማምዶታል። የኑሮ /ሕይወት/ ትግል አድርጎም ወስዶታል። ለዘመናትም የቀረሰው ክስተት በመሆኑ እንደ ባህርይም ይዞታል።

ግጭትን ከመዋቅራዊነት እና ተግባራዊነት አንፃር በሚመለከቱት ምሁራን ትንታኔ መሰረትም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ውስጣዊ የሰውነት ግንባታ የሚያካሂዱ እንደመሆናቸው፤ የሰውም ልጅ በሕይወት የሚኖረው በዚሁ ተፈጥሯዊ

[6] ለጥጠው የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው አስፍተው እና እንደሚያቅፍ አድርገው በመመልከት እና በመመርመር ነው የሚለውን ለመግለፅ ነው።

ሥርዓት ስለሆነ የሰውነት ግንባታ ያካሂዳል፡፡ በግንባታውም ሥነ ፍጥረታዊ እና ውስጠ-አካላዊ ግጭት በቀይና ነጭ የደም ሲሎቹ አማካኝነት ይካሄድበታል፡፡ ስለዚህም ህልውነቱ የተመሰረተው በግጭት ላይ ነው፡፡ በሰው ልጅ ላይ የሚካሄደው ሥነ ፍጥረታዊ እና ውስጠ-አካላዊ ግጭት ሲያቆምም ሕይወቱ ያልፋል፡፡ በአጭሩም የሰው ልጅ እንዲህ ዓይነቱን ሥነ-ፍጥረታዊ ሥሪትና ባህርይ ማምለጥ አይቻለውም፡፡ ከግጭትም ነፃ አይደለም፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅ ተጋጪነት ውስጣዊ ሥነ ፍጥረታዊ ሥሪት ተደርጎ ይወሰደል፡፡ ምክንያቱም ግጭት የስሜት መወጠር፣ የውስጥ መረበሽ፣ መነሳሳት፣ መጋጋል ወይም የስሜት ሚዛንን ማጣት፣ የአዕምሮ መጨነቅ እና በጡንቻም መወጣጠር የሚገለፅ ክስተት በመሆኑም እንደ ርዕደ ምድር ወይም ፍንዳታ፣ ነጎድጓድ የሚፈነዳ፣ የተጋጋለ ስሜትንም ተከትሎ የሚመጣ ድብድብ፣ ትግል፣ ብጥብጥ፣ ተቃርኖ፣ ትርምስ መሆኑንም እንዲሁ አጠንክረው የሚገልፁ አሉ (Rummel፣ // http: /www. hawaii edu/powerskills 10/9/2012)፡፡

በእነ Avruch (2004:24-27) እና Avruch (1996፡241)፣ Burton (1990)፣ Fisher (1982፡562) እና Galtung (1973: 9-15) አስተሳሰብ መሰረት ደግሞ ግጭት የሚመነጨው በሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት እና ይሄንንም ለማሟላት በሚደረግ ደመ-ነፍሳዊ ጥረት ማለትም በተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ፣ በማህበራዊ እና ተቋማዊ መዋቅር ሳቢያ፣ በአይቀሬ የመደብ ትግል እና ሥልጣን ፉክክር ምክንያት ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን የግጭት መሰረቱ ሥነ ሕይወታዊ እና ሰብኣዊ ተፈጥሮ መሆኑን፣ የግጭትም ታህታይ ምንጩ ደመ-ነፍስ መሆኑን ቢያስምሩበትም ግን ሰዎች ግጭት ውስጥ የሚገቡት በተፈጥሯዊ ባህርያቸው ብቻ እንዳልሆነም ያብራራሉ፡፡ ስለዚህም ሰዎች ወደ ግጭት የሚገቡት የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ጥሪቶችን፣ ሥልጣንን፣ ተቋማትን፣ በባለቤትነት ለመያዝ፣ ለመጨበጥ እና ለመቆጣጠር በጥቅሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደረጃቸውንም ከፍ ለማድረግ ሲሉ በሚያደርጉት መፎካከር እና የማይታረቅ ዓላማ፣ ፍላጎት እና ምኞት ሳቢያ መሆኑንም ያትታሉ፡፡ ስለዚህም ግጭት በተፈጥሮው ሥነ-ፍጥረታዊነትም ማኅበራዊነትም ይገለፅበታል ይላሉ፡፡

የግጭት ምሁራኑ እንደሚያወሱትም ሰዎች የተመኟቸውን ዓላማዎች እና ፍላጎቶች ለማግኘት እና በባለቤትነትም ለመያዝ በሚጣጣሩበት ወቅት ካሰቡበት እንዳይደርሱ የሚያውኩ እና የሚያሰናክሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሟቸውም ሥጋት እና ፍርሃት ይገባቸዋል፡፡ ሥጋትና ፍርሃታቸው እያየለ ሲሄድም፣ ግባቸው

የሚጨናገፍባቸው እና የሚሰናከልባቸውም መስሎ ይሰማቸዋል፡፡ በዚህም መልኩ ሰዎች ያለሙት፣ ያቀዱትና የጣሩበት ጉዳይ የማይሳካ መስሎ ሲሰማቸውና ሲታያቸው አለያም የግብ መንገዱ ዝግ ሲሆንባቸው ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ዓላማውን እና ፍላጎቱን ለማሳካት እና ለመኖር በሚያደርገው ጥረት እና መፍጨርጨር ውስጥ ነባራዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ምቹ ሆነው አይገኙለትም፣ አይጠብቁትምም፡፡ ነባራዊው ዓለም ለሰው ልጅ ሕይወት ምቹና አልጋ በአልጋ ሆኖ ስለማይገኝም የሰው ልጅ ሥነ ፍጥረታዊ ባህርይ የሆነው ግጭት በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ይቀረፃል፣ ይሰርፃል፣ በስሜትም ይገለፃል፣ ይፈነዳል[7]፡፡ በዚህ ሂደትም ግጭት እውንነት ያገኛል፡፡

Pearce እና Little (1997፡29-39) ደግሞ ግጭት የሰው ልጅ ባህርይ መሆኑን ለማስተማመንና ለማስረገጥ የሚሞክሩት ከክርስቲያን ዓለም የሰው ልጅ አመጣጥ ሚት እና ኃይማኖታዊ ተረክ ጋር ጭምር አስተሳስረው ነው፡፡ እነርሱ እንደሚሉት "አዳምና ሔዋንም ከገነት የተባረሩት የተከለከሉትን ዕፀ ፍሬ በልተው፤ በዚያም ሳቢያ ከፈጣሪያቸው ጋር ግጭት ውስጥ ገብተው ነው"፡፡

ግጭትን ከሥነ ሕይወታዊነት ማለትም ከሰብአዊነት ወይም ደመ-ነፍሳዊነት ባህርይነት እስከ ማኅበረሰባዊነት አስተሳስረው የሚያዩና የሚተነትኑ የግጭት ልሂቃን እንደመኖራቸው ሁሉ ይህንን አስተሳሰብ አጠንክረው የሚሄሱ እና ማኅበረሰባዊነቱን የሚያገዝፉም ደግሞ አሉ፡፡ በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱትም መካከል Schellenberg (1996)፣ Imobigine (2003)፣ Levinson and Ember (1996:241)፣ Augsberger (1992)፣ Coser (1968:233)፣ እና Deusdendit (2003) ይገኛሉ፡፡

በእነ Schellenberg (1996፡241)፣ Imobigine (2003፡8)፣ Levinson and Ember (1996፡240-242)፣ Augsberger (1992፡16)፣ Coser (1968፡8)፣ Deusdendit (2003፡1) አስተሳሰብ፣ እምነት እና አስተንትኖ መሰረት የሰው ልጅ ግጭትን እና ፀበኝነትን በመወለድ ወይም በደመ-ነፍስ አላገኛቸውም፡፡ ይልቁንም የሰው ልጅ የተጋጪነት እና ፀበኝነት ባህርይን የሚቀስመው፣ የሚያዳብረው እና ግጭትም ውስጥ የሚገባው ከሚኖርበት ኅበረተሰብ ወይም ማህረሰብ ወይም ከአካባቢው እና ከማህበሩ ሥርዓተ

---

[7] ግጭት ሥነፍጥረታዊ ቢሆንም ሁሉም ዓይነት ግጭት ዘወትር ግልፅ ጥላቻ ወይም አመፅ እና ጦርነት ያስከትላል ማለት ግን አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ግጭት ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም፡፡ አፍራሽ ብቻ ሳይሆን ገንቢ እና ለዕለት ከዕለት ማህበራዊ ሕይወት ለውጥ መንሥዔ የሚሆን ግጭትም አለ፡፡ ለምሳሌ በአስተያየት፣ በዝንባሌ በሐሳብ ወይም አመለካከት (ንፅረተ ዓለም) መለያየት የሚገለፅ ግጭት አውዳሚነት የለውም፡፡ በአንፃሩ ግን አመለካከትን እና ፍላጎትን በኃይል ለማስፈን መጣር እና የሐሳብ ተቀናቃኞችን ማስወገድ አውዳሚ ወይም አፍራሽ ግጭት ነው፡፡

ሕይወት ነው፡፡ ስለዚህም ግጭት ኅብረተሰብ የተገነባበትን ባህላዊ ሁኔታ በጥልቀት የሚያሳይ ክስተት እና የሰውም ልጅ ኃይል መታያ ግልፅ ምልክትነቱን ያሰምሩበታል፡፡

በአጭሩም ይህ አስተምህሮት የሚያጠነጥነው ሰዎች በባህርይ የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ወይም አካባቢ ውጤቶች መሆናቸውን አስረግጦ መግለፅ ላይ ነው፡፡ ይህም አስተሳሰብ የሰው ልጅ የሚኖርበት ማህበረሰብ ባህል /ሥልጣኔ/፣ ወግ እና ልማድ ውጤት ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው የሚሆነው፡፡ ይህም አስተሳሰብ ደግሞ ባህል /ሥልጣኔ/፣ ወግ እና ልማድ ዋነኛው የግጭት መመንጫ እና መከሰቻ ነው ከሚለው የ Huntington (1993) አስተንትኖ ጋር የተገጣጠመ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም በእነዚህ የኒሎኖቹ ወገኖች አተያይ መሰረት ግጭት ደመ-ነፍሳዊና ሥነ-ፍጥረታዊ ባህርይ ተደርጎ መቆጠር ወይም መታየት የለበትም፡፡ ይልቁንም በእነዚህ ወገኖች አተያይ ግጭት የሚመነጨው በደመ ነፍሳዊ ወይም ሥነ ፍጥረታዊ፣ በባህል፣ ወግ ልማድ፣ በውጫዊ አነቃቂ ሁኔታዎች ማለትም መሰረታዊ ፍላጎቶች ምክንያት ማለትም ለመኖር በሚያስፈልጉ ነገሮችና ጥሪቶች ተሻምቶ መንሥዔነት ጥምረት በጥቅሉም በማህበራዊነት ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ልሂቃን አስተሳሰብ ሰብስበን ለማጠቃለል ስንሞክርም ግጭቶች የሚመነጩት ምግብ፣ ልብስ፣መጠለያን ለማሟላት በሚደረግ እንቅስቃሴ፣ ውስን በሆነ የተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ ምክንያት በእሴቶች ወይም በደረጃ ይገባኛል፣ በሥልጣን ማለትም በገገርነት ፍላጎት እና አልገዛም ባይነት፣ ባልተመጣጠነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ሳቢያ ባጭሩም ያለሙትንና ያቀዱትን ዓላማ ማሳካት ባልተቻለበት እና ተስፋ በተቆረጠበት ሁኔታ እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች ምክንያት ሁሉ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በተለይ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያገለግሉት ጥሪቶች በተፈጥሮም ውሱን ስለሆኑ፣ ሰዎችን ለሽሚያ፣ ለመራኮትና ለግጭት ይዳርጓቸዋል፡፡ በሂደቱም ተሸናፊዎቹ ግጭቶቹን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ መልኮች ይሰጧቸዋል (Kuper (1996:124) ፣ Fisher (1982:567)፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶችም እጅግ የሚከሩት በተለይ የግጭቱ ተዋንያን ስለ ግጭት ያላቸው ባህል፣ ዝንባሌ፣ ባህርይ እና ግብር ተመጣጥኖ ወይም አቻዊነት ሲኖረው ነው Galtung (1973፡2)፡፡ ይህም አቻዊነት የሚገለፀው ተጋጪዎቹ ወገኖች የሚኖሩበት ማህበረሰብ ግጭትን በሚረዳበት እና በሚያይበት መንገድ፣ በሚያሳየው ዝንሌ እና በሚተነፍሰው ሥነቃላዊ ወይም ኪነ ጥበባዊ የተግባቦት

አስተያየት፣ በቀረፀው አመለካከት ወይም ንፀረተ-ዓለም እና በሚያሳየው እና በሚፈፅመው ግብር ነው።

Zinn & Eitzen (1991) ደግሞ ኅብረተሰብ በሥርዓት /Order/ እና በግጭት /conflict/ የተሳሰረ እና የተያያዘ ነው ይላሉ።

በሥርዓት ሞዴል /Order/ መሰረት ኅብረተሰብ ተያያዥነትና አንድነት ያላቸው የተለያዩ ክፍሎች ስብስብ እንደመሆኑ በመግባባት፣ በሰላምና በከፍተኛ ህብረት ተሳስሮ ማህበራዊ ግቡንና ባህላዊ እሴቶቹን ጠብቆ፣ አንድነቱን ወይም ቡድናዊነቱን አጠንክሮ ነው የሚኖረው የሚል ስሌት ወይም አስተንትኖ አለ። በዚህ እሳቤ መሰረትም የተለያዩት የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ተጋጋገሮችና ተደጋጋፊዎች ናቸው። በዚህም አተያይ መሰረት ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎችም የጋራ ፍላጎቶችን ለማርካት የሚያስችሉ ምክንያታዊ የመደጋገፊያ ሥልቶች ሆነው ይወሰዳሉ። ይህም ፅንሰ ሀሳብ ኅብረተሰብ ተግባራዊ እና መዋቅራዊ አደረጃጀት እና ትስስር እንዳለው ያመላክታል። ስለዚህም ሁሉም የኅብረተሰብ አድራጎት ሁሉ ተደጋጋፊና የማይነጣጠል ወይም የአዎንታዊ እና አሉታዊ ገፅታዎች ቁርኝት ተደርጎ ይታሰባል፣ ይቆጠራል።

በሌላ በኩል ግጭትም /conflict/ እንደ ሥርዓት /Order/ ሁሉ ሌላኛው አንፃር የኅብረተሰብና የማህበራዊ ሕይወት አብሮ በቀል ወይም ሥሪትና ገፅታ ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህም አዎንታዊ እና ውጤታማም ተደርጎ ይታሰባል። ምክንያቱም ግጭት አንድን ኅብረተሰብ ከአንድ ባህላዊ ሥርዓተ ሕይወት ወደ ሌላ ባህላዊ ሥርዓተ ሕይወት ያሸጋግረዋል ተብሎ ይታመናል። በዚህ አስተሳሰብ ብርቱ አራማጅነታቸው ከሚታወቁት ልሂቃን መካከል Seymour (1986) ይጠቀሳሉ። Seymour (1986:51) ግጭት ቀዳማይ የማህበራዊ ለውጥ ማነቃቂያነቱን በማጉላት፣ ማህበራዊ ተቃርኖዎችንም ለመፍቻነት ቁልፍም ሚና እንደሚጫወት ያትታሉ።

ኅብረተሰብ የሥርዓት እና የግጭት ጣምራ ነው የሚለው አስተሳሰብም በሌላ መልኩ የሚያመላክተን ሥርዓትም የኃይል ውጤትነቱን ይመስላል። ሥርዓት እና ግጭትም ንፅፅራዊነት ያለው ነው እንደ ማለትም ይሆናል። የሥርዓት መኖር የሚታወቀው ግጭት ሲኖር ነው፤ የግጭትም ህልውነት የሚታወቀው እንደዚሁ ሥርዓት ሲኖር ነው እንደማለት።

በአጠቃላይ Zinn & Eitzen (1991) አፅንዖት ሰጥተው የሚያወሱት ኅብረተሰብ የሥርዓትም የግጭትም ድምር ውጤት ስለሆነ ግጭትና ሥርዓትን ነጣጥሎ ከማየት

ይልቅ ውሁድና የማይለያዩ የሰው ልጅ ወይም ኅብረተሰብ ቅቡል ባህርያት አድርጎ መውሰድ እንደሚገባ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ከዚህ በላይ በቀረቡት የግጭት ምንነት እና መንሥዔ ንድፈ ሐሳቦች ውስጥ ግጭት ሰብአዊ እና ማህበረሰባዊ ባህርይን፣ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ማንነትን እንደምን እንደሚተክል እና እነዚህም ማንነቶች የሚኖራቸው ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ፋይዳ እኔ እንደማስበው በስፋት ከባህል ሥሪትነት አኳያ በስፋት እና በጥልቀት አልታየም ወይም አልተመረመረም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በዚህ ረገድ ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት ይሞክራል፡፡ ክፍተቶቹንም በፎክሎር ንድፈ ሐሳብ ለመሙላት ግቡዕ የሚሆነው የፎክሎር ዘውጎች ግጭትን በማመንጨት፣ መትከል እና በማህዘብ ረገድ ያላቸውን አስተዋፅኦ በመመርመር ነው፡፡ በተለይም የተረክ ወይም የሥነ ቃል ሀብት በግጭት አመንጪጨት፣ አተካከል እና አሕዝቦት ላይ ያለው አበርክቶ የትየለሌ ነው፡፡

እዚህ ላይ "ለመሆኑ ተረክ ምንድነው?" የሚለውን ወደ ዋናው ጉዳይ ለመግባት ይቻል ዘንድ በአጭሩ ላስተዋውቅ፡፡

ተረክ "narrative" የዘርፉ ልሂቃን Scholes (1981:205-206) እና ሌሎችም እንደሚያወሱት ተረክ ማለትም አፈ-ታሪኮች፣ ወጎች፣ ተረቶች፣ ሽላሎዎች፣ ፉከራዎች፣ ሙሾዎች፣ የፍቅር፣ የሰርግ፣ የሥራ ዘፈኖች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ እንጉርጉሮዎች፣ ምርቃቶች እና እንቆቅልሾች ወዘተ የነገሮች፣ የሁነቶች እና የግብሮች አኳኋን በምሰላና በዘይቤ የሚቀርብበት ውክል ትዕምርታዊ እና በሴማ የሚቀርብ ወይም ቅደም ተከተላዊ ታሪክ ነው፡፡

ተረክ ትረካውም የሚመነጨው ከሕይወት ልምድ እና ተሞክሮ ነው፡፡ የሕይወት ልምድ እና ተሞክሮም መቀንበቢያ ነው (Lisa and Elinore 1997: www. jestor. org.7/7/2012)፡፡ ስለዚህም ተረኮች በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች እንዲሁም ገፀባህርያት ማለትም በሰው፣ በእንስሳት፣ በአማዕልክት፣ በመናፍስት፣ በሰይጣን፣ በጭራቅ ወዘተ ገፀ-ባህርያት ቢገለፁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያነሱት የሰውን ልጅ ተፈጥሮ፣ አድራጎት፣ እምነት እና ባህርይ በጠቅላላውም ንፅረተ-ዓለሙን /world view/ ነው፡፡

ስለዚህም ተረኮች በሰብአዊና ማኅበራዊ ማንነት መግለጫዎች፣ ማመልከቻዎች፣ መቀንበቢያዎች፣ በጥቅሉም ትርጉም መስጫዎችና መበየኛዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ተቋማዊና ብሔራዊ ትርጉሞችም ማመንጫዎች ሆነው ያገለግላሉ። የፅናት፣ የመቋቋም፣ የጥንተ አመጣጥ፣ የግጭት ድልና ሽንፈት፣ ሰቆቃና ፍስሐ ወዘተ መሰነጃ፣ ማስተላለፊያና ማህዘቢያ እንዲሁም ማጣጣያ መሣሪያዎችም ናቸው። በአጭሩም ነገሮችን፣ ክስተቶችን የመሰነድ እና ለአስተምህሮት አገልግሎት የማዋል ጥቅም አላቸው (Lisa and Elinore 1997. http: /www.readingonline. jestor. org.7/6/2009) ።

እዚህ ተረክ የተባለውም አንድን ሁነት፣ አፋዊ ታሪክ፣ የግለ ሕይወታዊ ትውስታን፣ የሕይወት ውጣ ውረድን፣ ታሪካዊ ክንውንን፣ በዘመን ሂደት የታዩና ያጋጠሙ ሁነቶችን፣ ታሪኮችን ማውጋትን፣ መንገርን፣ መተረክን ለመግለፅ ነው። እነዚህም የሚተረኩት በባህል ውስጥ የሚያስተላልፋት እሴት፣ አገልግሎት እና ግብ ስላለ ማለትም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እሴቶችን ለማንፀባረቅና ባህላዊ እሴቶችን ለመፍጠር ነው። ተረኮች የማህበረሰቦችን፣ ኅበረተሰቦችን ወይም ሕዝቦችን ሥርዓተ አኗኗር፣ ማንነት፣ ትስስር፣ አንድነትና ልዩነት መፍጠሪያዎችም ናቸው። ስለዚህም በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ ያጋጠሙ ስኬቶችን ወይም ድቀቶችን በልዩ ልዩ የተረክ ዘርፎችና ቅርፆች ይሰንዳሉ፣ ይተክላሉ፣ ያህዝባሉም።

ቀደም ሲል የተጠቀሱት Huntington (1993) የዛሬው ዓለም ሕዝቦች ግጭቶች በመመንጨት ላይ ያሉት በማኅበረሰቦች ባህል /ሥልጣኔ/፣ ወግ እና ልማድ እሴቶች ልዩነት ምክንያት ነው ሲሉ ያሰመሩበትን አስተሳሰብ በነገረ ማትክሪያችን ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍነት መመዘኛነት፣ መመልከቻነት እና ማንጠሪያነት ወስደን የግጭትን ነገረ ተፈጥሮ ወይም ሥሪት በአፈ-ታሪኮች፣ ተረቶች፣ ሽለላዎች፣ ፉከራዎች፣ ሙሾዎች፣ የፍቅር፣ የሰርግ፣ የሥራ፣ የልመና ግጥሞች፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሾች፣ እንጉርጉሮዎች ምርቃቶች፣ እርግማኖች፣ መኃላዎች ወይም የሥነቃል ሀብትን ለመመርመር መሞከራችንም በጥቅሉ ባህል ግጭትን በሕዝቦች መካከል ለመቀስቀስ፣ ለመትክል እና ለማስቀጠል ያለውን አበርክቶ ለማየት አስቻይነቱን ያመለክተናል፣ ያሳየናልም ።

በእርግጥም ዛሬ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሕዝቦች ግጭቶች በምጣኔ ሀብት እና ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ልዩነት ላይ የተመሰረቱ አይደሉም። ይልቁንም በማንነት ማለትም ጉልቆ ትውልድ ወይም ዘር፣ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ እምነት፣ ሥነ ምግባር፣ ሕግ፣ ወግ ልማድ ዙሪያ የሚያተኩሩ ናቸው። ስለዚህም ባህል

ግጭትን በመትከል፣ በማራመድ እና በማህዘብ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ያለው ግዙፍ አበርክቶ አለ፡፡ ይህንንም አንደምታ በዚህ ጥናት ለመመርመር እና ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 2.2. የግጭት ዓይነት

የግጭት ምንነቱ እና መንሥኤዎቹ የተለያዩ እንደሆኑ ሁሉ ዓይነቱ እና ደረጃውም እንዲሁ የተለያዩ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎም ግጭቶች እንደምን በዓይነቶች እንደሚከፋፈሉ እንመለከታለን፡፡

ግጭቶችን በዓይነት በመከፋፈል ከሚታወቁት የግጭት ምሁራን መካከል Lulofs እና Cahn (2000፡58-65) የንግግር አለመጣጣም፣ የአመክንዮ ልዩነት፣ ፀብ /ጥል/፣ ሽሚያ፣ አለመግባባት፣ ሞራል፣ አካላዊ ግጭት፣ ተጨባጭ ግጭት፣ ኢ-ተጨባጭ ግጭትና ኢ-ተጨባጭ፣ እውናዊ እና ተጨባጭ፣ ኢ-እውናዊ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት ዓይነቶች እንዳሉ ያወሳሉ፡፡

ግጭቶች በእነማን መካከል ይፈጠራሉ? የሚለውንም እየለዩ የሚያወሱ እና የሚያመለክቱ አሉ (Zartman, 2000:7)፣ (Deutsch, 1971: 42-54)፣ (Galtung, 1973:43-47፣125-154)፡፡ እነዚህ ወገኖች የግጭቶችን ዓይነት የሚዘረዝሩት የግጭቱን ቅለትና ክብደት ወይም ውስብስብነት ደረጃ፣ ግጭቱ ሊቆይ የሚችልበትን የጊዜ እርዝማኔ፣ድንገተኝነት እና የታሰበበትነቱን፣ ጊዜያዊነት እና ዘላቂነቱን፣ ግጭቱ ያስከተለውን ሰብአዊ እና ቁሳዊ ሀብት ኪሣራ፣ ቀውስ፣ በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ወገኖች ማንነት ማለትም ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ጎሳዎች፣ ማህበረሰቦች፣ ብሔረሰቦች፣ ብሔሮች፣ ነገዶች፣ ድርጅቶች ሥርዓቶች፣ አገሮች /መንግሥታት/ እንዲሁም ደግሞ ግጭቱ የተቀሰቀሰበትን የሚያዳርሰውን ከባቢያዊ ሁኔታም በማየት ውስጣዊ፣ ክልላዊ፣ ብሔራዊ፣ ዓለማቀፋዊ እንዲሁም አቅጣጫ በመከተል ሰሜንና ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ፣ የማዕከል እና የጠረፍ፣ የኢኮኖሚ ደረጃን በማየት የካፒታሊስት እና የሶሻሊስት፣ የማህበራዊ አደረጃጀትን እና ሁኔታንም በተመለከተ የቋንቋ፣ የኃይማኖት፣ የልዕለ ኃያላን እና የሌሎች፣ የኃይለኞች እና የደካሞች፣ የግዛት፣ የድርጅቶችና ማህበራት፣ የመደቦች እንዲሁም ግጭቱ የተቀሰቀሰበትን ወዘተ ታሳቢ እያደረጉ ነው፡፡

በመሰረቱ ግን እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የግጭት ሽፋኖች እንጂ መሰረታዊ ሰበበ መንሥኤዎች ናቸው ለማለት ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ልዩነቶች ብቻቸውን ግጭትን የሚያመነጨበት ሁኔታ የለም፡፡ ግጭት ሁሉ የሚመነጨው ወይም የሚወለደው ከአንዳች የምጣኔ ሀብት ወይም የጥቅም ሽሚያ ነው፡፡ ከጥቅም ውጪ ያለው የግጭት ሰበብ የግጭቱን አድማስ ለማስፋት፣ አደገኛ እና ዘላቂም ለማድረግ ተጋጪዎቹ ወገኖች ዋናውን የግጭት ምክንያት በእነዚህ ሽፋናዊ ሁኔታዎች ለተከታዮቻቸው አስርፀው ግጭቱ የመረረ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚጠቀሙበት ሥልት ነው የሚመስለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ግጭቶችን ተጨባጭና ኢ-ተጨባጭ፣ ጣምራ ማለትም ግልፅና ሥውር እያሉ የሚከፋፍሉም አሉ (Ronald በ Zartman & Rasmusse (2005:240) ውስጥ፣ Augsberger (1992: 247-248) ፡፡ በእነዚህ ምሁራን አገላለፅ መሰረት ተጨባጭ የሚሰኙት በግል ሀብት/ በንብረት፣ በሥራ ዓይነትና ደረጃ፣ በተፈጥሮ ሀብት (የመሬት፣ የውኃ፣ የግጦሽ፣ የማዕድን) ወዘተ ምክንያት የሚቀሰቀሱት ሲሆኑ በአንፃሩ ኢ-ተጨባጭ የሚባሉት ደግሞ ምንም ዓይነት የሚታይ፣ የሚዳሰስ ክስተት በሌለበት በአስተሳሰብ ልዩነት ምክንያት ብቻ የሚቀሰቀሱት ናቸው፡፡

እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት ደግሞ ግጭቱ በየትኛውም ዓይነት ምክንያት ቢቀሰቀስ ከተጨባጭ ምክንያቶቹ በላይ ኢ-ተጨባጭ ምክንያቶቹ ግጭትን በማባባስና በማስፋፋት በተጋጪዎቹ ወገኖች መካከልም መተማመን እንዳይፈጠር የማድረግ እና የላቀ ተፅዕኖ የማሳደር ኃይል አላቸው፡፡ እነዚህም የግጭት ማባባሻዎች የሚሆኑት ኢ-ተጨባጭ ምክንያቶች ነገሮችን በውል ያለመረዳት ወይም ያለመገንዘብ፣ በተጋጪው ወገን ላይ አሉታዊ ዝንባሌ መያዝ ወይም ማሳደር፣ የዋህነት ወይም አላዋቂነት የተመላበት ቁርጠኝነትና ሞገደኝነት እንዲሁም የአመለካከትና የተግባቦት ህፀፆች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ከምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች በበለጠ በአመለካከት ሳቢያ የሚከሰቱ ግጭቶች ማባሪያ የሌላቸው የግጭት ሙሻዙሮች ይሆናሉ፡፡

Lulofs እና Cahn (2000:57-73) ደግሞ አራት ዓይነት ግጭቶች መኖራቸውን ያትታሉ፡፡

የመጀመሪያው ቀዳማዊ ግጭት እውነተኛና ተጨባጭ የሚሰኝ ሲሆን ይኸውም በሀብት ወይም ንብረት፣ ድንበር ወዘተ ይገባኛል ባይነት ሳቢያ የሚከሰት ነው፡፡

ሁለተኛው የግጭት ዓይነት ደግሞ እንደ ላይኛው በቂና ተጨባጭ የሀብትና የይገባኛል ባይነት ጥያቄ በሌለበት የሚፈጠር ነው፡፡

ሦስተኛው ዓይነት ግጭት ደግሞ ግጭቱ ስለመኖሩም ሁለቱ ኃይሎች በዕውን በማይገነዘቡበት ሁኔታ አንዱ ወገን ብቻውን ግጭት አለ ብሎ የሚብከነከንበት ነው፡፡

አራተኛው ደግሞ በሐሳብ ባለመግባባት ብቻ የሚገለፅ ዓይነት ግጭት ነው፡፡ ይሁንና እነዚህን ከዚህ በላይ በሦስቱ የግጭት ተመራማሪዎች የቀረቡትን ሐሳቦች አጠቃሎ ቁሳዊና አዕምሮታዊ ብሎም መመደብም የሚቻል ይመስላል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት አንቀፆች ግጭት የተለያዩ ዓይነቶች እንዳሉት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ የግጭት መፍቻ ተብለው የሚሰነዘሩትን መላዎች ለመቃኘት እንሞክር፡፡

## 2.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በቀዳሚዎቹ ርዕሶች ውስጥ  ለማየት እንደተሞከረውም ግጭቶችን በዓይነትና በደረጃ እየከፋፈሉ መግለፅ የተለመደ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ስለዚህም የግጭት ምንነት፣ መንሥዔዎች እና ዓይነቶች የተለያዩ እንደመሆናቸው ሁሉ የአፈታት ሥልቶቹም የተለያዩ መሆናቸውንም እንዲሁ ያጤኗል፡፡

በዓለም ላይ እስከዛሬ በተለያዩ ደረጃ በአንዳች የጥቅም ፍላጎት እና ተሻምቶ ምክንያት የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን ለመፍታትና ሰላምን ለማስፈን ባመዛኙ ጥቅም ላይ ሲውሉ የቆዩት የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

Avruch (2004፡26-27)፣ Lulofs እና Cahn (2000፡ 57-73)፣ Symour (1986:51)፣ እንዲሁም Zartman (1977፡619-638) ግጭትን በመፍታት ሂደት አራት ያህል መንገዶች ማለትም ድርድር /negotiation/ ማለትም በውይይት ተደራድሮ ስምምነት ላይ መድረስ መቻል፣ ክርክር /bargaining/ ማለትም በመከራከር ስምምነት ላይ መድረስ፣ ዳኝነት /adjudication/ ግጭቱን ዳኝነት ማየት ለሚችል የሕግ አካል አቅርቦ በውሳኔው መገዛት መቻልን እንዲሁም የሦስተኛ ወገን ማግባባትን /third party-mediation mediation/ ማለትም በሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት እና ሽምግልና ስምምነት ላይ መድረስ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁነኛ የግጭት መፍቻ ሥልቶች መሆናቸውን ያወሳሉ፡፡

Avruch (2004፡25-26) ፣ Symour 1986) እና Coser (1968፡24-25) ደግሞ ግጭትን ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የግጭት መፍቻ ሥልቶች መፍታት ባልተቻለበት ወቅት ተቀናቃኙን በኃይል ማስወገድም አንዱ የግጭት መፍቻ አማራጭ መሆኑን ያክላሉ፡፡

Galtung (1973፡19) በበኩላቸው ግጭትን ለመፍታት በመጀመሪያ ግጭትን መግታት እና ማቆም ማለትም የሰላም ማስከበር፣ ቀጥሎም ሰላም መፍጠር እና ማስፈን እንዲሁም የሰላም ግንባታ ሥልቶችን መከተል የሚሉ ሦስት ሥልቶችን መከተል እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ በላይ በተለያዩ የግጭት ልሂቃን የቀረቡት ዓበይት ሐሳቦች እንደሚከተለው ለጨመቁ ይችላሉ፡፡

የመጀመሪያውና በሰፊውም ተቀባይነት ያለው ተደርጎ የሚታየው የግጭት መፍቻ ሥልት ድርድር ነው የሚመስለው፡፡ ምክንያቱም ድርድር ተጋጪዎች የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ሳያስፈልጋቸው ባለመግባባቶቻቸው ምክንያቶች ላይ እርስበርሳቸው ተነጋግረው ሁለታቸውንም የማይቆረቁር፣ ምቹ መፍትሔዎች መሻት የሚችሉበት አመርቂ የግጭት አፈታት ሥልት ተደርጎ ይቆጠራልና ነው፡፡

ሁለተኛው የግጭት መፍቻ ሥልት ደግሞ በመረጡት ሦስተኛ ወገን ፊት ቀርቦ በመሸማገል ግጭትን መፍታት መቻል ነው፡፡ ይኸኛው የግጭት መፍቻ ሥልት ቀደም ሲል የግጭት ንድፈ-ሐሳብ በተነሳበት ርዕስ ሥር ፀበኝነት እና ግጭት የማህበራዊ እና ከባቢያዊ ሁኔታዎች ውጤቶች ናቸው የሚሉት ልሂቃን እንዳመላከቱት ሁሉ መፍትሔውም እዚያው ይገኛል የሚል አንድምታ ያለው ይመስላል፡፡ ይህም የአስተሳሰብ አቅጣጫ ባህላዊ አውዱ ግጭትን የማመንጨት አስተዋፅኦ እንዳለው ሁሉ የመከላከልም አበርክቶ እንደሚኖረው የሚጠቁም ነው የሚሆነው፡፡

ሦስተኛው ዓይነት የግጭት መፍቻ ሥልት ደግሞ ግጭትን ለሚዳኝ ሦስተኛ ወገን አቅርቦ በዳኝነቱ ውሳኔ መሰረት ዕልባት ማግኘትን የሚመለከት ነው፡፡

አራተኛው ዓይነት የግጭት መፍቻ አንዱ ወገን ያለውን ኃይል ተጠቅሞ እና በተቀናቃኙ ላይ ድል ተቀዳጅቶ ለግጭቱ እልባት መስጠት የሚችልበት ነው፡፡ ይህም እንግዲህ ጉልበት ወይም ኃይል አንዱ አማራጭ የግጭት መፍቻ መሆኑን ነው የሚያመለክተው፡፡

በዚህ ምዕራፍ እስካሁን የግጭትን ምንነት፣ ዓይነት እና የመፍቻ ሥልት ንድፈ-ሐሳቦች ለማየት ተሞክሯል፡፡

ምዕራፉ ከመጠናቀቁ በፊት ደግሞ ለቀወት እና ሰሙ-ሮቢ.ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኞች ግጭትና እርቅ ሁኔታ የሚስማማ ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ጠቁሞ ማለፍ ይገባል፡፡ ይህንንም ማዕቀፍ መቀንበብ ያስፈለገው የድንበርተኞቹን ግጭትና እርቅ ሁኔታ መመልከቻ መነፅር ስለሚያሻ ነው፡፡

## 2.4. የቀወት እና ሰሙ-ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭት እና ግጭት አፈታት ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ

ከዚህ ቀደም ሲል በቀረቡት ክፍሎች ለማመልከት እንደተሞከረው ግጭትን ከሥነ ሕይወታዊነት እና ሰብአዊነት እስከ ማኅበረሰባዊነት የሚለጥጡ እንዲሁም ማኅበረሰባዊነቱ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ወገኖች እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ የግጭት ሥነ ሕይወታዊ፣ ሰብአዊ እና ማህበራዊ አስተንትኖዎቹ እና የአስተሳሰብ አቅጣጫዎቹም የቀረቡት የዚህን ጥናት ማትኮሪያዎች የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮችን ግጭት ምንነት ለመቀንበብ የሚረዱ የተዛማጅ ጽሑፍ ዳራዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህም ከቀረቡት ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፎች ውስጥ በተጠኚዎቹ ሕዝቦች ግጭት ሂደት ውስጥ ህልውነት ወይም እውንነት እና "ዕድቅነት" ያለውን በመውሰድ በንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍነት እና ማንጠሪያነት የተመረጠውን እንመልከት፡፡

ከንድፈ ሐሳቦቹም ውስጥ ለቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ግጭት እና ግጭት አፈታት ጥናት በዓቢይ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍነት የተመረጠው የእነ Avruch (2004) እና (1996)፣ Levinson and Ember (1996)፣ Augsberger (1992)፣Fisher (1982)፣ Galtung (1973)፣ Coser (1968) እና (1956)፣ Deusdendit (2003)፣ Imobigine (2003) አስተሳሰብ ማለትም ግጭት ኅብረተሰብ የተገነባበትን ባህላዊ እሴት አመልካች ነው የሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህም የተደረገበት ዋናው ምክንያት በጥናቱ ሂደት በአንፃራዊ ሁኔታ በቀላሉ መረጃ ለመሰብሰብ የተቻለው የሁለቱን ማኅበረሰቦች ግጭት ሁኔታ ከአጠቃላይ ባህሎቻቸው እና እሴቶቻቸው አንፃር በመመልከት በመሆኑ ነው፡፡

የሌሎቹ ማለትም የእነ Bartos እና Wehr (2002)፣ Anderson (1999)፣ Schellenberg (1996)፣ Lorenz (1974)፣ Galtung 1973) እና Boulding (1962) አስተሳሰብ ግጭት መሰረቱ

ሥነ ሕይወታዊ እና ሰብኣዊ ተፈጥሮ ከመሆኑ የሚጀምር ነው፡፡ ስለዚህም ይህ የግጭት ንድፈ ሐሳብ ያልተመረጠው ግጭትን ከሥነ ሕይወታዊነት እስከ ማኅበረሰባዊነት[8] አስፍተው የሚመለከቱ በመሆናቸው የእነርሱ መንገድ ለመረጃ አሰባሰብ ሂደት አስቸጋሪ እና ጊዜ-ፈጅ ስለሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም በግጭት እና ግጭት ዓይነት እንዲሁም አፈታት የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ሥር እንደቀረበው ግጭት ከሰብኣዊ ባህርይነት እስከ ማኅበረሰባዊ እና ባህላዊ ማንነት ሥሪት የሚዘልቅ ክስተት ነው፡፡

ስለዚህም ለቀወት እና ለሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት እና ግጭት አፈታት ሁኔታ ስምሙ ይሆናል በሚል የተመረጠው ንድፈ ሐሳብ የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች የግጭት መንሥዔዎች እና አፈታት ሥርዓት ከአጠቃላይ ባህላቸው እና ኑሯቸው አኳያ ለመመርመር እንደሚያስችል በመገመት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህም ሂደት አጠቃላይ ባህላቸው ግጭትን እንደምን እንደሚስለው እና እንደሚያስተጋባው ለማየት፤ በዚሁም ሁነት ግጭት በሁለቱ ሕዝቦች ዓለማዊ አተያይ ውስጥ ግለሰባዊ ማህበራዊ እና ባህላዊ ማንነትን እንደምን እንደሚቀርፅ እና እንደሚገልፅ በመመርመርም

---

[8] የግጭት ጥናት ንድፈ ሐሳባውያን እና ተመራማሪ ምሁራን ግጭትን ከመዋቅራዊነት /structuralism/፣ ተግባራዊነት /functionalism/፣ መዋቅራዊ ተግባራዊነት /functionalism-/structuralism/፣ ድህረ ዘመናዊነት /post-modernism/፣ የግጭት ንድፈ ሐሳብ /conflict theory/ አንፃር በዘውግ እየከፈሉ እና እያገጉ ወይም እየቀነበቡ የማጥናት ልማድ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የግጭት ጥናት ንድፈ ሐሳብ አመንጪዎቹን ንድፈ ሐሳባዊያን እና ግጭት ያጠኑትን ተመራማሪ ምሁራን እና ሊቃውንት በሙሉ በዓቢይ ንድፈ ሐሳቦች ውስጥ እየከተቱ መዋቅራዊያን፣ ተግባራዊያን፣ ድህረ ዘመናዊያን፣ ሥነ ልቦናዊያን ወዘተ እያሉ ማቧደን አልተፈለገም፡፡ ይኸውም የተደረገው ጥናቱን ከመጀመሪያው በተወሰነ ንድፈ ሐሳብ አጥር ዘግቶ በውስን አቅጣጫ ብቻ ላለማየት፣ በመረጃው የተገኘውን ሁሉም እንደየአግባቡ ለመፈተት ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ መረጃ ውስጥ መዋቅራዊነትም /structuralism/፣ ተግባራዊነትም /functionalism/፣ መዋቅራዊ ተግባራዊነትም /functionalism-/ structuralism/፣ ድህረ ዘመናዊነትም /post-modernism/፣ ማኅበራዊ ሥነ ልቦና /social psychology/ አስተንትኖም ሁሉ ተዛንቀው በየቦታው ይከሰታሉና ነው፡፡ ለምሳሌ ግጭትን ከሥነ ፍጥረት ጋር ማስተሳሰር ግጭትን ከቅርፀ እና ክፍለ አካላት መዋቅር ጋር ማያያዝ ነው፡፡ አሁንም የሰው ልጅ ሕይወት በትክለ ሰውነት እና ክፍላተ አካላት ወይም መዋቅር የቆመ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አዕምሮ ለማሰብ፣ ዓይን ለማየት፣ አፍንጫ ለማሽተት፣ አፍ ለመመገቢያና መናገሪያነት፣ ጥርስ ለማኘክ፣ ምላስ ለማበራየት፣ ጉሮሮ ለመዋጥ እና ለመጠጣት፣ አንገት ተዛዙሮ ለማየት ወዘተ እያሉ ሁሉንም ክፍላተ አካላት ከመዋቅራቸው እና ተግባራቸው አንፃር መግለፅ ይቻላል፡፡ አሁንም ሕይወት በቀይ እና በነጭ የደም ሴሎች ትግል ውስጥ መቀጠሉን ስንመለከት ደግሞ ግጭትን ከመዋቅር እና ከተግባር ጋር አያይዘን መመልከታችን ነው፡፡ መገኛቸው ሰውነት፣ ተግባራቸው ሕይወትን መስጠት እና ማቆየት ነውና፡፡ እንደገናም ደግሞ ሰው የማኅበረሰብ ወይም የአካባቢ ውጤት ነው ስንልም አሁንም ግጭትን ከማህበራዊ ሥነ ልቦና ጋር አስተሳስረን ማውሳታችን ነው፡፡ ግጭትን ከተቋማት ጋር አስተሳስረን ስንመለከትም ሂደቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት አደራረግ እና የንድፈ ሐሳብ ክለሳ ውስጥ የተሻለ መንገድ መስሎ የታየኝ የግጭት ጥናት ምሁራንን ከየዓቢይ ማትኮሪያቸው የንድፈ ሓሳብ ትምህርት እና መብቀያ ትምህርት ቤቶቻቸው /school of thought/ እና ዝንባሌያቸው ጋር እያስተሳሰሩ ከማዋገን ይልቅ መሳጭ አስተሳሰቦቻቸውን ከሁሉም ወስዶ የራስን ጥናት መረጃ እና ግኝት መፈለግ እና በተነሱትም የአስተሳሰብ አመክንዮቶች ላይ ተመሥርቶ ትንታኔ ማከል ነው፡፡

ሁለቱ ሕዝቦች ግጭትን በአዎንታ ወይም አሉታ የሚመለከቱነታቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ለቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ግጭት ጥናት የተመረጠው ዓቢይ ንድፈ ሐሳበዊ ማዕቀፍ ግጭትን ከማኅበረሰባዊነት አንፃር መመልከት እና ማንጠር ቢሆንም በዚህ ሥር በንዑስነት የሚታየው ደግሞ ግጭትን ከፎክሎራዊ ፋይዳው አንፃር መመርመር ነው፡፡ ስለዚህም ግጭትን በመትከል፣ በማህዘብ ረገድ የፎክሎር ዘውጎች ያላቸው ሚና ይመረመራል፡፡

ከግጭት ዓይነት አንፃር ሲታይም አሁንም ለዚህ ጥናት የሚቀርበው ተግባራዊ ብያኔ ግጭት ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ ወገኖች ወይም ተዋናዮች ወይም ቡድኖች፣ ጎሳዎች፣ ብሔረሰቦች የሚገቡበት ውስጣዊ እና ውጫዊ፣ ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ ወይም ግልፅ እና ሥውር ምክንያቶች የሚያስከትሉት የሕይወትና የንብረት ውድመት ወይም ድቀት የሚያደርስ ክስተት ነው የሚለው ይሆናል፡፡

ከግጭት አፈታት አንፃር ሲታይም የሁለቱ ወረዳ ሕዝቦች ግጭት የሚፈታው በኃይል ማለትም ጠላትን በኃይል በማስወገድ፣ በሽምግልና እና በሦስተኛ ወገን ማለትም በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነው፡፡

## 2.5. የመሰል ጥናቶች ክለሳ

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች በልዩ ልዩ ምክንያት የተከሰቱ እና የሚከሰቱ ግጭቶችን እና ግጭቶቹንም ለመፍታት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ ባህላዊ የግጭት አረጋገብ ወይም አስተጋገስ እና አፈታት ሥርዓቶችን የመረመሩ ጥናቶች መኖራቸውን የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት በተወሳበት ክፍል መጨረሻ ላይ መጠቆሚ ይታወሳል፡፡ ይሁንና በዚህ የክለሳ ክፍል ቀደምት ጥናቶቹን እየጠቀሱ ማብራሪያ መስጠት እና የዚህን ጥናት መካሄድ አመክንዮታዊ ልዩነት ማመልከቱ የተገባ ይሆናል፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ ከሥነ ጽሑፍና ፎክሎር፣ ከማህበራዊ ሥነሰብ /social anthropology/፣ ከሕግ፣ ከመድበለ-ባህል እና ከታሪክ ወዘተ የትምህርትና ምርምር ዲሲፕሊን ማትኮሪያ ፅንሰ ሐሳበዊ ማዕቀፍ አንፃር ተቀንብበው ወይም ታግገው

የተደረጉት ጥናቶች በነገረ ማትኮሪያ ጉዳያቸው ማለትም ይዘታቸው ሲታዩ በተጨባጭ ወይም ነባራዊ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች እና የእርቅ አፈፃፀም ሂደቶች ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው።

ቀደምት ግጭት ተኮር ጥናቶቹ ከነገረ ማትኮሪያቸው በተጨማሪ ከተካሄዱበት መልክዓ ምድር ወይም ክልል እና ካካተቱትም ሕዝብ አንፃር ሲታዩም ብዙዎቹ የተደረጉት በአንድ ክልል ሕዝብ ማለትም መልክዓ ምድር፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ልማድ፣ ሥነ ልቡና፣ ንፅረተ ዓለም ወዘተ በሚጋሩ እንዲሁም ጥቂቶቹ ደግሞ በተለያዩ (የተጠቀሱትን ነገሮች በማይጋሩ) ሕዝቦች መካከል በሚስተዋሉ ግጭት መንሥዔዎች፣ የግጭት ሂደት እና የግጭት አፈታት ሥርዓት ምርመራና ገለፃ ላይ ነው።

በአንድ ሕዝብ ውስጥ በተከሰቱና በሚከሰቱ ግጭቶች፣ በግጭት አመነጫጨት እና በግጭቶቹ አፈታት ሥርዓት ገለፃ ዙሪያ ከሚያተኩሩት እና በተለያዬ ስፋትና ጥልቀት ደረጃም ቢሆን ግጭትን ከነገረ ፎክሎር አንፃር ማለትም ከሥነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እና ክዋኔ አንፃር በማተኮር ከተደረጉት ጥናቶች መካከልም የጌታቸው (2002)፣ የዮሴፍ (2002)፣ የብርሃን (2002)፣ የሰለሞን (2002)፣ የስለሺ (2002)፣ የደበበ (2001)፣ የመንግሥቱ (1999)፣ የሞላ (1999)፣ የጌታቸው (1999)፣ የአብርሃም (1999)፣ የአበበ (1999)፣ የዓለሙ (1999)፣ የተመስገን (1998)፣ የነፃነት (1998)፣ የአየለ (1998)፣ የየወንድወሰን (1998)፣ የይልማ (1998)፣ የዮሴፍ (1998)፣ የሰለሞን (1998)፣ የሙሉጌታ (1997)፣ የ Menbere (2010)፣ የ Akmel (2010) ጥናቶች ይጠቀሳሉ። እዚህ ላይ ከላይ በየአጥኚዎቹ ስሞች ከተገለፁት ጥናቶች መካከል አንዳንዶቹ እና ሌሎችም ደግሞ ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ (2004) እና (2005) ባደቷቸው ሁለት ቅፆች ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህም መካከል (ሙሉጌታ፣ የወንድወሰን፣ ስለሺ፣ ተመስገን፣ ይልማ፣ ብርሃን፣ ዓለሙ፣ አበበ፣ ደበበ፣ Wubshet፣ Merhatssidk፣ Dejene፣ Tolosa፣ Israel፣ Kahsay (2007)፣ Assefa፣ Koang፣ ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ (2004) እንዲሁም ገብሬ፣ ጌዴዎን እና ፈቃደ፣ ወዲሻ፣ ሥዩም፣ መስፍን፣ Fekadu ወዘተ) ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ (2005) ውስጥ ይገኛሉ።

ገብሬ፣ ፋቃደና አሰፋ (2004፣2005) አሰባስበው እና አርትኦት ፈፅመው በተከታታይ ባሳተሟቸው ጥንድ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትንም ግጭት ተኮር ጥናቶች ስንመለከት በመጀመሪያው መፅሐፍ ውስጥ ከቀረቡት አሥራ ስምንት ያል ጥናቶች አሥራ አምስቱ፣ እና በሁለተኛውም ፅትም ውስጥ ከቀረቡት ሰባት ግጭት

ተኮር ጥናቶች መካከል በድምሩ ሃያ አምስቱ ጥናቶች በሙሉ በውስጣዊ ግጭት እና አፈታት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው።

ቀሪዎቹ በእነ ገብሬ፣ ፊቃደና አሰፋ (2004፣2005) የተካተቱት ጥቂት ጥናቶች ደግሞ በአጠቃላይ ግጭቶች እና ግጭቶች አፈታት ላይ ሳይሆን በተወሰኑ የፆታና የቤተሰብ ተኮር ግጭቶች ላይ ያተኩሩ ናቸው። ሁለቱ ደግሞ በሁለት ብሔረሰቦች አጠቃላይ ግጭት እና ባህላዊ ግጭት አፈታት ጥቅል ገፅታን የዳሰሱ ናቸው። አንዱ ጥናት ደግሞ ጥንቆላም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

Alula እና Getachew (2008) አርትኦት ፊፅመው ባሳተሙት ግጭት ተኮር ጥናት መድብልም ውስጥ Getachew እና Shimelis (2008)፣ Melaku እና Woubishet (2008)፣ Bayisa and Lemessa (2008)፣ Dereje (2008)፣ Biruk and Jira (2008)፣ Areba and Berhanu (2008)፣ Mohammed and Zewdie (2008)፣ Ayele and Mekonnen (2008)፣ Shimels and Tadesse (2008)፣ Sebsib (2008)፣ Mintiwab and Bellese (2008) ወዘተ ያደረጓቸው ጥናቶች እንዲሁም በእነዚህ ጥንድ ግጭት ተኮር መድብሎች ውስጥ ያልተካተቱ መሰል ጥናቶች (Asnake (2010)፣ Kelemework (2000)፣ Medhane (2006)፣ Tirsit (2003) ፣ Yohannes (1998)፣ Dejene (2007) አሉ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በሙሉ ያተኮሩት በተለያዩ አካባቢዎች በሚስተዋሉ እና በተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ፣ በንብረት ይገባኛል ባይነት ምክንያት በሚነሱ ግጭቶች፣ በግጭቶች የሽምግልና አደራረግ ሥርዓቶች፣ ለሽምግልና በሚሰየሙት ሽማግሌዎች ማህበራዊ ደረጃ እና የሽምግልና አኳኋን፣ የእርቅ እና የእርቅ ማፅኛ መኃላ ሥርዓት አፈፃፀም ገለፃ እና ዝርዘራ ላይ ነው።

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው በተናጠል በቀረቡትም ሆነ በእነ ገብሬ፣ ፊቃደ እና አሰፋ (2004፣2005) እንዲሁም Alula እና Getachew (2008) መድብሎች ውስጥ የቀረቡት ጥናቶች በተለያዩ ክልሎች እና ማህበረሰቦች አካባቢዎች የሚስተዋሉ ግጭቶችን ምክንያቶች፣ ግጭቶቹን መፍቻ ተቋማት አደረጃጀት፣ አሰራር፣ ዳኝነት አሰጣጥ፣ ሥርዓተ- እርቅ አፈፃፀም እና የተቋማቱንም ፋይዳ የተመለከቱ ናቸው። ስለዚህም ብዙዎቹ ግጭት ተኮር ጥናቶች ያተኮሩት በአንድ ወጥ ሕዝብ መካከል በሚከሰቱ ውስጣዊ ግጭቶች እና አፈታት ሥርዓቶች ላይ ነው። በአንድ ሕዝብ ውስጣዊ ግጭት ላይ የምላቸውም ጥናቶቹ ቀደም ሲል እንደጠቆምኩት አንድ መልክዓ ምድር፣

ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ልማድ፣ ሥነ ልቡና፣ ንዕረተ ዓለም ወዘተ በሚጋሩ ሕዝቦች መካከል የሚስተዋሉ የግጭት መከሰቻ መንገዶችን፣ የግጭት ሂደት እና የግጭት አፈታት ሥርዓት ምርመራ እና ገለፃ ላይ ስለሚያተኩሩ ነው። ስለዚህ እነዚህ የተጠቀሱቱ በሙሉ በውስጣዊ ግጭቶች መንሥዔዎች እና አፈታት ሥርዓቶች ላይ ያተኩሩ ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ከዚህ በላይ ቀደም ብሎ እንደተገለፀውም በድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭትና የግጭት መፍቻ ሥርዓት ወይም በተለያዩ ክልሎች እና ማህበረሰቦች አካባቢ በሚስተዋሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሰራር፣ ዳኝነት አሰጣጥ፣ ሥርዓተ-እርቅ አፈፃፀም እና የተቋማቱም ተኣማኒነት ላይ አፅንኦት ከሰጡት መካከልም ደግሞ Assefa (20009)፣ Asnake (2010)፣ Betelhem (2010)፣ Assefa (2005)፣ Atikilt (2003)፣ Berihun (1996)፣ Ayalew (1995) ይገኙባቸዋል። እነዚህም ግጭት ተኮር ጥናቶች ያተኮሩት በድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል በሚከሰቱ የግጭት መንሥዔዎች እና ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ገለፃ ላይ ነው። ስለዚህም የእነዚህኞቹም ትኩረት በተለያዩ ሕዝቦች ማለትም የተለያዩ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ልማድ እና ንዕረተ ዓለም ያላቸው ድንበርተኛ ሕዝቦች በተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት፣ ተቀራምቶ ወይም ተሻምቶ፣ በሀብት ተቆጣጣሪነት ፉክክር፣ በንግድ፣ በገንዘብ እና እምነት ማጉደል ሳቢያ ወዘተ ምክንያትሲጋጩ፣ ግጭቶቻቸውን በሚፈቱባቸው የሽምግልና ሥርዓቶች ገለፃ ላይ ነው። ስለዚህም ኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-መንሥዔዎችን ነገሬ ብለው አልመረመሩም።

ይሁንና ከእነዚሁ ከላይ ከተጠቀሱት ግጭት ተኮር ጥናቶች መካከል በተለይ የእኔ ጥናት ድንበርተኛ ወረዳዎች ከሆኑት ውስጥ የአንዱን ወረዳ ማለትም የሰሙ ሮቢ ገለአሉ ወረዳ የሚገኝበትን የአፋር ክልልን የሚመለከቱ ሆነው ያገኘኋቸው እና በክልሉ ውስጥ በመካሄዳቸው የሚጎዳኙኝ የ Kelemework (2011፣ 2000)፣ Menbere (2010)፣ Akmel (2010)፣ Getachew and Shimelis (2008)፣ Kahsay (2007)፣ Medhane (2006)፣ እና Tirisit (2003) ጥናቶች ናቸው። የእነዚህም ጥናቶች አትኩሮት በዚሁ አንቀፅ ውስጥ ከተገለፀው ሐሳብ ውስጥ የሚጠቃለል ነው። ምክንያቱም ጥናቶቹ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብት ምክንያት የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን እና መፍቻ የሽምግልና እና የሽምግልና ዳኝነት አደራረግ ሂደቶችን የሚዘረዝሩ ናቸው። በመሆኑም እነዚህም ጥናቶች እንደላይኞቹ ሁሉ በግጭት መከሰቻ እና ማብረጃ ላዕላይ ሁኔታ ላይ ያተኩሩ ናቸው ለማለት ይቻላል። አንዳንዶቹን ዘርዘር አድርገን እንያቸው።

ለምሳሌም ያህል Kelemework (2011፣2000) የአፋር ሰሜናዊ ክፍል ነዋሪዎችን የእርስበርስ እና ከአጎራባቾቻቸው ትግራዮች ጋር ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸውን ምክንያቶች እና የእርቅ ሂደት እና አፈፃፀም፤ Asnake (2010) የድንበርተኛ አፋሮች እና ከረዩዎችን የግጭት መንሥዔ እና የግጭት አፈታት፤ Akmel (2010) ደግሞ የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮችን ግጭት እና ግጭት አፈታት ሥልት፤ Medhane (2006) የአፋርና ኢሳ ግጭት መንሥዔ እና አፈታት ሂደት የተመለከቱ ጥናቶች አድርገዋል፡፡

Getachew and Shimelis (2008) ም እንዲሁ በአፋር ክልል በዳሉል አካባቢ በሚፈፀም የደም እርቅ ሽምግልና አፈፃፀም ተቋም ማሮ /Maro/ ሥርዓት መርምረዋል፡፡ ጥናቱ የተመለከተውም የተቋሙን መዋቅር፣ የሽምግልና ሂደቱን፣ ግጭት አፈታቱን፣ ጥንካሬና ድክመቱን፣ እንዲሁም የክልሉ መንግሥት ለተቋሙ የሰጠውን እውቅና እና እያደረገም ያለውን ድጋፍ ነው፡፡ ይህ ጥናት በዳሉል አካባቢ ስላሉ አፋሮች ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት የሚያወሳ በመሆኑ ውስጣዊ ግጭትና አፈታቱ ዙሪያ የተቀነበበ ከመሆኑም በላይ ሥነቃል ለግጭት አመነጫጨት ያለውን አስተዋፅዖ አያነሳም፡፡ የእርቅ ሥርዓተ ሂደት ትዕምርቶችንም አይዘረዝርም፣ ለመተርጎምም አይሞክርምም፡፡

ካህሳይ (2004) ደግሞ የኢትዮጵያ አፋሮች በጠቅላላው መተዳደሪያ ባህላዊ ሕግ "ማድዓ" መሰረታዊ ይዘት፣ አሰራር፣ የዳኞች አሰያየም፣ የዳኝነት አመራርና ሂደት እንዲሁም ባህላዊ ሕጉ ከመደበኛው የወንጀልና ሥነ ሥርዓት ሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ከዚሁም ጋር ሲነፃፀር የሚታይበትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የዳሰሰ ጥናት አድርገዋል፡፡

ካህሣይ በሁሉም አፋሮች ዘንድ የሚሰራውን "ማድዓ" የተሰኘውን ባህላዊ የዳኝነት ሕግ በማንሳታቸው እና ይህም ጉዳይ በእኔም ጥናት ወረዳ ውስጥ የአፋሮችን የእርስበርስ ግጭት ለመፍታት የሚያገለግል በመሆኑ የምንጋራው ነጥብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የእኔ ጥናት ትኩረት በውስጣዊው ብቻ ሳይሆን በውጫዊውም ላይ የሚያጠነጥን በመሆኑ እንደገናም ደግሞ በግጭት እና እርቅ ሂደት ዝርዝራዎችን፣ በልዩ ልዩ የቅጣት አጣጣሎችም ግኝት ገለፃዎቻችንም ላይ እንለያያለን፡፡ ስለዚህም ጉልህ የአስተሳሰብ መደራረብ የለንም ለማለት ይቻላል፡፡

በአጭሩም በአፋር ክልል ውስጥ የተካሄዱትም ግጭት ተኮር ጥናቶች ልክ በሌሎቹም አካባቢዎች እንደተደረጉት ጥናቶች ሁሉ የሕዝቡ ግጭት ተኮር አመለካከት ሊገኝና ለመረመር የሚችልበትን፣ በርሱም ላይ በመመሥረት ዝንባሌያቸው ሊታይ

የሚችልበትን የሥነ ቃል ሀብት ፈፅሞ አልመረመሩም። ለአብነትም አፋሮች እራሳቸውን የጦርነት አባት አድርገው ይልቁንም "አላህ ለጦርነት የፈጠረን ሕዝቦች ነን" ብለው የሚያስቡ እና እራሳቸውን ልዩ ኃይሎች አድርገው የሚቆጥሩ መሆናቸውን እና ይሄም ዓይነቱ አመለካከት በግጭት አያያዝ ላይ የሚኖረውን አንድምታ አላዩም፣ ስለ ነገረ ኩነቱም አንስተው ለመመርመር አልሞከሩም።

እነዚህ ግጭት ተኮር ጥናቶቻቸውን በአፋሮች ውስጣዊ እንዲሁም በአፋሮች እና በድንበርተኞቻቸው መካከል (አማራና አፋርን፣ አፋርና ጅሌ ኦሮሞን አይጨምርም) በሚከሰቱ ግጭቶች እና አፈታቶች ላይ ያደረጉት እና የተጠቀሱትም ተመራማሪዎች ጥናቶች ያተኮሩት በግጭት መንሥኤዎቹ እና በግጭት መፍቻ ተቋማቱ አገልግሎት ማለትም ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓቶቹ ለየማህበረሰቦቹ በቅርበት "ፍትህ" የሚሰጡ እና በዚህም የተበላሸውንም የማህበረሰቦቹን ግንኙነት መልሰው የሚወግሹና የሚጠግኑ መሆናቸውን መግለፅ ላይ ነው። ስለዚህም ጥናቶቹ ያተኮሩት በየአካባቢዎቹ የሚስተዋሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አገልግሎትና ጠቀሜታ ላይ ነው።

ስለዚህም ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉት በአንድ አግባብ ብቻ ነው። ይኸውም ሁሉም የእኔም ጥናት ተካታች ወረዳ በሚገኝበት በአፋር ክልል ግጭትና የግጭት አፈታትን ጭብጣቸው እና ጉዳያቸው አድርገው በመነሳታቸው ብቻ ይሆናል።

በአፋር ክልል ከተደረጉት እና ከተጠቀሱት ግጭት ተኮር ጥናቶች ሁሉ ደግሞ በመልክዓ ምድር ረገድ የእኔ ጥናት ማትኮሪያዎች ከሆኑት ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች መካከል በአንዱ ማለትም በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ውስጣዊ ግጭት እና አፈታት ላይ ጥናት ያደረጉት (Akmel፣ 2010) ብቻ ናቸው። Akmel (2010) ከሌሎቹ የበለጠ ከእኔ ጥናት ጋር የተወሰነ ቅርበት ያላቸውም እንደምን እንደሆነ አመለክታለሁ።

Akmel (2010) በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ግጭት እና ግጭት አፈታት ዙሪያ ከእኔ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ያደረጉት ጥናት ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ከእኔ ጥናት ጋር የተወሰነ ቅርበት እና ተጋርቶ ያለውም በመጀመሪያ ደረጃ የጥናቴ አንድ ጠገግ በሆነው ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ላይ በተመሳሳይ ጊዜ በ2002 ዓ.ም መረጃ በመሰብሰባችን እና የእርሳቸው ጥናት ቀድሞ የተጠናቀቀ ስለሆነ፤ በሁለተኛም ደረጃ በማትኮሪያ ጉዳይ እና በአተያይ ጥልቀት ብንለያይም በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ገፀ-ምድር፣ በወረዳው ነዋሪዎች

ኢትኖግራፊያዊ እና ማህበራዊ አደረጃጀት ገለፃ እንዲሁም በተጨባጭ የግጭት መንሥዔዎች እና ግጭት አፈታት ዙሪያ በምናነሳቸው ነጥቦች ተጋርቶ ስላለን ነው፡፡

Akmel (2010) እና እኔ በእነዚህ አንፃራዊ ቋሚነት ባላቸው ገፀ-ምድራዊ እና ማህበራዊ አፅቆች ገለፃዎች ተጋርቶ ቢኖረንም እኔ እነዚህ ነባራዊ ሁነቶች ከጥቅል የአካባቢ ማስተዋወቂያ ገለፃነት በላይ ለግጭት መጫር፣ መቀጠል እና የሕይወት ቋሚ ክስተት መሆን ያላቸውን አስተዋፅዖ ሁሉ ከጉዳዩ ጋር አስተሳስሬ ለመመርመር ሞክሪያለሁ፡፡ Akmel (2010) ከዚህ አንፃር አላዩዋቸውም፡፡ ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ እኔ እና Akmel (2010) የምናነሳቸውን ነጥቦች የምናይበት የአጠናን፣ የአስተነጋገድ፣ የአተረጓጎም ሥልታችን እንዲሁም የመመልከቻ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፋችን ለየቅል ነው፡፡ ምክንያቱም የእኔ ዋነኛ ትኩረት ድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች በግጭት እና እርቅ ዑደት ውስጥ የሚኖሩበትን ምክንያት ከተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት መንሥዔዎች፣ ከተረክ፣ ከአፍቅሮተ-ንዋይ ወይም ቂስ፣ ከእርቅ ሥርዓት አስተራረግ እና ፅንዓት ሁኔታዎች ጋር አስተሳስሮ ማጤን ነው፡፡ Akmel (2010) ይህን አያነሱም፡፡ ለግጭትና እርቁ ዑደታዊነት ምክንያት አድርጌ ከተፈጥሮ ሀብት ተጋርቶ እና ሽሚያ በተጨማሪ የማየው እና የምመረምረውም ሥነቃልን ነው፡፡ ሥነቃል ለግጭት መተከል፣ አሕዝቦትና ዑደት ያለውን ሚና እንዲሁም የእርቅ አፈፃፀም ሂደት እና እርጋት ሥርዓተ ከበራቸውን /ritual/ ፅኑነት ወይም ልልነት መመልከት፡፡ ከዚሁም ጋር ሁለቱ ሕዝቦች ግጭትን በአዎንታ ወይም በአሉታ መመልከታቸውን በሥነቃሎቻቸው ውስጥ ማስተዋል፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ለ Akmel ነገረ ማትኮሪያዎች ወይም ፍሬ ጉዳዮች አይደሉም፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የልዩነት አመክንዮቶች በተጨማሪም የ Akmel (2010) ጥናት ግጭትን በመፍታት የሽምግልና እና እርቅ ሂደት ላይ የሽምግልና ሥፍራ፣ በሽምግልና ሂደት ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶችና ትዕምርቶች ያላቸውን መልዕክት እና እሳቤ ስላልተካተተበት እና ፎክሎራዊ አስተንትኖም ስለሌለው በሰፊው እንለያያለን፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ግጭት ተኮር ጥናቶችም ምርመራቸውን ያደረጉት በዓይን በሚታዩት፣ በእጅ በሚዳሰሱት የግጭት መንስዔዎች እና ግጭቶቹን ለማብረድ በሚወሰዱት የሽምግልና ሥርዓቶች፣ ሂደቶች፣ የእርቅ አፈፃፀም እና እርጋቶች ብቻ ላይ ነው፡፡ እንዲያውም አብዛኞቹ ግጭት ተኮር ጥናቶች የግጭት መንሥዔ አድርገው

የሚያነሱት ቁሳዊ ሀብትን ነው፡፡ የግጭት መፍቻም የሚሉት ሽምግልና እና እርቅን ነው፡፡ እንዲህም በመሆናቸው አትኩሮታቸው በግጭቱም ሆነ በእርቁ አንድ ጠገግ ላይ ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ተጋጪዎቹ የሚኖሩበት ዓለም እና ማህበረሰብ ስለ ግጭት እና እርቅ በልማዱ (ባህሉ) ያካበተውን፣ ያዳበረውን እና የያዘውን አስተሳሰብ፣ ግጭትንም በአዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልኩ የሚመለከት መሆን አለመሆኑን ነገሬ ብለው አላዩም፡፡

እስከዛሬ ድረስ በአንድ ሕዝብ ውስጥም ሆነ በድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ባጋጠሙ እና በሚያጋጥሙ ግጭቶች እና የግጭቶች አፈታት ላይ የተደረጉት ጥናቶች ቁልፍ ጉዳይ ሲጨመቁ የግጭት መንሥኤዎች ብለው ደጋግመው የሚያነሷቸው ምክንያቶች የተፈጥሮ ሀብቶች ተሻምቶዎች እና መቀራመቶች ማለትም ሣር፣ እንስሳት አደን፣ ማዕድን ሽሚያ እንዲሁም የሰው ሰራሽ ሀብት አጠቃቀም ማለትም በንብረት፣ በንግድ ልውውጥ፣ ሳቢያ የሚከሰት የገንዘብ መካካድ እና እምነት ማጉደል፣ በነገር እና በሐሳብ አለመግባባት፣ ማገጣ ወዘተ ናቸው፡፡ ስለዚህም ዋነኛ የግጭት መንሥኤ አድርገው የሚያነሱት ገፀ-ምድራዊ እና ሰው ሰራሽ ሀብት ሲሆን ሁነኛ የግጭቶች ማስታገሻ የሚሉትም የሽምግልና ሥርዓትን እና እርቅን ነው፡፡

በአጠቃላይ በአንድ ወጥ ሕዝብም ሆነ በድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል የሚስተዋሉ ልዩ ልዩ ግጭቶችን እና አፈታቶችን የመረመሩት ጥናቶች በሙሉ በተለይ የሽምግልና ሥርዓትን ሕያውነት፣ ባህላዊነት፣ ግጭት መቆጣጠሪያነትና መፍቻነት ማህበራዊ ተቋምነት፣ ዴሞክራሲያዊነት፣ አቀረብነት፣ ፍትህ ሰጪነት፣ የተጋጪዎችንም ግንኙነት መልሶ ጠጋኝነት፣ አራቂነት፣ ወጪ፣ ጉልበት እና ጊዜ ቆጣቢነት አጉሊዎች ናቸው፡፡

ስለዚህም ሁሉም ጥናቶች ማለትም በአንድ ወጥ ሕዝብ ውስጥም ሆነ በድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭቶች እና የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ላይ የተደረጉት ጥናቶች በሙሉ የባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማቱን አሰራር ሂደት በአዎንታዊነት የሚያዩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በማስከተል የእኔ ጥናት ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች የሚለይበትን ነጥብ ለማመልከት እሞክራለሁ፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ጥናቶቹ በተለያዩ የትምህርት መስኮች እና ተቋሞች በተለያ አካባቢዎች የተደረጉ ቢሆኑም ሁሉም ከእኔ ጋር የሚመሳሰሉባቸው ሁለት አግባቦች አሉ፡፡ አንደኛው ሁሉም ግጭትና የግጭት አፈታትን ጉዳያቸው አድርገው

በመነሳታቸው እና በጭብጣቸውም ሽምግልና የግጭት መፍቻ ተቋምነት መሆኑን በማውሳታቸው ነው።

ይሁን እንጂ በአጠቃላይ እስካሁን የተዘረዘሩት ጥናቶች በሙሉ አንድም የሁለት ሕዝቦችን ውስጣዊና ውጫዊ ግጭት እና እርቅ አጣምረው አያነሱም። ሁለትም ከእኔ የአማራና አፋር ግጭትና ግጭት አፈታት ጥናት ጋር በጥናት ዘዴ ማለትም በጥናት ማንጠሪያና መመልከቻ ሥልት፣ በአስተነጋገድ፣ በግጭት በቋሚነት መገታት እና መቆም ወይም ማገርሸት እና መቀጠል ዙሪያ፤ በእርቅ አፈፃፀም ክዋኔ ፍፁም ዘላቂነት ወይም ልልነት እና ፍርስነት ላይ ያነሱት እና ያሉት ሐቲት የለም።

ጥናቶቹ ምንም እንኳን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በተለያዬ ደረጃ እና ጥልቀት የሚያነሱ ቢሆኑም ሥነቃል ለግጭት መተከል፣ አሕዝቦትና ተስተላልፎ የሚጫወተውን እና የሚተክለውን ንፅረተ ዓለም፤ ንፅረተ-ዓለሙም የሚፈጥረውን ፍላጎት፣ ዝንባሌና የሕይወት ግብ በአፅንኦት አላነሱም። ስለዚህም ጥናቶቹ መሰረታዊ ጉዳያቸው እና ማዕቀፋቸው ግጭትና የግጭት አፈታት ይሁን እንጂ ምርምራቸው ግጭት የባህል ሥሪት ሆኖ ከሚገኝበት ሥነቃል ወይም ተረክ ጋር ያለውን ዝምድና ወይም ቁርኝት አስተሳስሮ የመረመረ አይደለም። ግጭትን ከግጭት ተኮር ሥነቃሎች አንፃር ባለመመርመራቸውም የግጭትን ታህታይ ሥሪት እና ሙሻዙርም ለማጤን አልተቻላቸውም። ስለዚህም የእስካሁኖቹ ግጭት-ተኮር ጥናቶች ከእኔ ማትኩሪያ የትየለሌ የራቁ ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም እኔ በተለይም ግጭትን በመትከል፣ በማህዘብና በማዛመት ረገድ ሥነቃል ያለውን ሚና ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ጥሪት ጋር አዛንቄ አነሳለሁ። እስከዛሬ የተደረጉት ግጭት ተኮር ጥናቶች ይህንን ጉዳይ በዓቢይነት አላነሱምና።

ስለዚህም በእኔ አተያይ ምንም እንኳን ሁሉም አጥኚዎች ዒላማችን ብለው የተነሱበትን ጉዳይ መተው፣ ግባቸውን ቢያሳኩም አንድ ዓቢይ ነገር ተዘንግቷል ብዬ እገምታለሁ። ሥነ ቃል በግጭትና ሰላም ውስጥ ያለውን አበርክቶ አለማስተዋል። ስለዚህም አጥኚዎቹ ሁሉ ሥነቃልን ባለማንሳታቸውም ግጭትን ግዝፈት ከሌለው እና ፊት ለፊት ከማይታየው በአንፃሩ ግን ግጭትን በመትከል እና በማህዘብ ረገድ አበርክቶው የትየለሌ ከሆነው ሥነቃል ነጥለውታል። ግጭትን ከሥነቃል ጋር አስተሳስረው ባለመመልከታቸውም ግጭትን ከሥረ መሰረቱ ከመመልከቻው እና ከመመርመሪያው ወይም ከማዕከላዊ ማትከሪያው ነጥብ ርቀው የመረመሩ ናቸው

ለማለት ይቻላል፡፡ ከተዘረዘሩት የልዩነት አመክንዮቶች በተጨማሪም ቀደምት ጥናቶቹ ግጭትን በመፍታት የሽምግልና እና እርቅ ሂደት ላይ የሽምግልና ሥፍራ፣ በሽምግልና ሂደት ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶችና ትዕምርቶች ያላቸውን መልዕክት እና እሳቤ አይተረጉሙም፡፡ ፎክሎራዊ አስተንትኖም የላቸውም፡፡ ስለዚህም በእነዚህ ሁሉ እንለያያለን፡፡

ከተከለሱት ጥናቶች መካከል የአፋሮችን ባህላዊ የግጭት አፈታት /መፍቻ/ ሥርዓት የመረመሩትም ቢሆኑ ሕዝቡ ግጭትን እንደምን እንደሚመለከተው እና ለግጭት ያለው አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ገፅታ ያለው ስለመሆን አለመሆኑ አልገለፁም፡፡

ስለዚህም እኔ ይህን የቀወት አማሮች እና ሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ግጭት መንሥዔ፣ ሂደት እና አፈታት ሁኔታ የምመረምረው ከተፈጥሮ ሀብትም ከሥነቃል ሀብትም አንፃር ነው፡፡ ይሄ ጥናት እስከዛሬ ከተደረጉት ግጭት ተኮር ጥናቶች የሚለየውም በዚሁ ይሆናል፡፡

እስካሁን የተካሄዱት ሁሉም ግጭት ተኮር ጥናቶች የግጭቶችን ልማዳዊነት ወይም ባህል-በቀልነት ማለትም በሥነ ቃል ወይም ተረክ ውስጥ የተሰናኘነት፣ በርዕዮተ ዓለምነት መቀረፅ፣ መተከል እና በቋሚነት መያዝ ጋር አያይዘው ግጭቶቹም በዘላቂነት መገታት ወይም አለመገታታቸውን እና ዑደታዊነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን አልመረመሩም፣ አላመለከቱምም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረውም እስከዛሬ የተካሄዱት ጥናቶች ግጭትን ከሥነ ሕወታዊነት እና ከፎክ ቡድኖች ርዕዮተ /ንፅረተ/ ዓለም አንፃር አላዩትም፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት እስከ ዛሬ በተደረጉት ግጭት ተኮር ጥናቶች ውስጥ ይታይ የነበረውን የእውቀት ክፍተት የሚያሟላ ይሆናል፡፡

# 3. የጥናቱ ዓይነት እና ዘዴ

በዚህ ርዕስ ሥር የጥናቱን ዓይነት እና የጥናቱ መረጃ የተጠናቀረባቸውን ወይም የተሰበሰበባቸውን ዘዴዎች በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

## 3.1. የጥናቱ ዓይነት

ይህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" ጥናት በዓይነታዊ /qualitative/ የጥናት አደራረግ ዘዴ የተካሄደ ነው፡፡ ዓይነታዊ የጥናት ዘዴ የተመረጠው የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት መንሥዔ እና እርቅ ሁናቴ ከሁለቱ ሕዝቦች መካከል የተውጣጡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች ከሚሰጡት ሐሳብ፣ አስተያየት እና እምነት ላይ በመመሥረት የድንበርተኞቹን ሕዝቦች ግጭት እና እርቅ ልማድ ለመግለፅ፣ ለመተንተን እና ለመተርጎምም ስለሚያስችል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱም የአጠናን ዘዴ መረጃዎችን ከተለያዩ አቅጣጫ ማለትም ከተጠኚዎቹ ማህበረሰቦች ሁለንተናዊ አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ዝንባሌ አኳያ ለመግለፅ እንዲሁም ለመተርጎም ምቹ ነው (Creswel, 2009፡8)፡፡[9]

የምቹነቱም አመክንዮ ሰዎች ስለሚኖሩበት ዓለም እና ባህል የራሳቸውን ፍቺና ትርጉም የሚሰጡ በመሆኑ ነው፡፡ እኔም ይህን አስተሳሰብ በግቡዕነት የወሰድኩት ከመረጃ ተባባሪዎቼ የሰበሰብኩትን ግጭት ተኮር ነገር ሁሉ በማብላላት በኋላ ላይ መተንተን እና መተርጎም እንዲቻለኝ ነው፡፡

ዓይነታዊ /qualitative/ የአጠናን ሂደት የባህል ልዩነቶች ያሏቸውን ሕዝቦች በውስን ሁኔታ ማለትም በመልክዓ-ምድር፣ በሕዝብ ብዛት፣ በርዕሰ-ጉዳይ፣ በማትኩሪያ አላባውያን፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ /ወቅታዊና ታሪካዊ/ ቀንብቦ ውስጣዊና ውጫዊ ባህላዊ ተመሳስሎና ልዩነታቸውን እንዲሁም ድብቅ እሴቶቻቸውን በሥልታዊ ንፅፅር በማጥናት የተወሰኑ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንደሚያስችል፣ የጥናት አደራረጉም ሥልት ግቡዕነት እንዳለውም የሚመከር ነው (Ember እና Ember, 2009:1-6) ፡፡

[9] በዚህ ጥናት ውስጥ የሰፈረው የዘመን አቆጣጠር ምንጮች የተፃፉበትን ቋንቋ ይከተላል፡፡ በዚህም መሰረት ብዙውን ጊዜ ምንጮቹ በአማርኛ ሲሆኑ የኢትዮጵያን አቆጣጠር፣ ምንጮቹ በላቲን የተፃፉ ሲሆኑ ደግሞ የአውሮፓውያኑን ዘመን አቆጣጠር የተከተሉ ይሆናሉ፡፡ የምንጮቹ ሥም በቅርብ ባልሰፈረ ጊዜ ደግሞ እ.ኤ.አ. (እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር) በሚል ይጠቆማል፡፡

ይህ ዓይነታዊ ጥናትም የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት መንሥኤዎች እና ግጭት አገታት ለመግለፅ እና ለመተርጎም ይበጃል፡፡ ይህንንም ማድረግ በፎክሎር ጥናት አደራረግ ሂደት ውስጥ ልሙድ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ የፎክሎር ተመራማሪዎች የሚያተኩሩት በሦስት ዓበይት ነገሮች ማለትም የሚጠኑት ሕዝቦች በራሳቸው ባመነጯቸው እና በሂደት ባዳበሯቸው፣ ትዕምርታዊ አድርገው በሚቆጥሯቸው እና በልማድነት በያዟቸው እና ባዘለቋቸው እውቀቶች፣ ልማዶች እና ክዋኔዎች ላይ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት ተጠኚዎቹ ሕዝቦች ስለሚኖሩበት ዓለም እና ባህል የሚሰጡትን ፍቺ እና ትርጉም እንደምን እንደሚሰጡ ለመረዳት የሚያስችል ይሆናል፡፡

በዚህም ጥናት የሚተኮርባቸው ነገሮች በእነዚሁ ዝርዝሮች ውስጥ የሚካተቱ ነገር ግን ለአካዳሚያዊ ገለፃ እና ትንተና እና ትርጓሜ ያመች ዘንድ ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ ብዬ የምጠራቸው ባህላዊ የግጭት ሰበበ-ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነዚህም እንደ ኑሮ መግፊያ፣ የሕይወት ጣዕም መስጫ፣ እንደ ታሪካዊ ክስተተት መጠቆሚያ፣ እንደ ባህል መገለጫ ወይም መታያ፣ እንደ ሥነ ልቡናዊ ባህርይ መክሰቻ ሆነው የተያዙ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የዘለቁ ባህላዊ /ፎክሎራዊ/ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 3.2. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ /interview/፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት /focused group discussion/፣ ፅሞናዊ ምልከታ /passive observation/፣ መጠይቅ /questionnaire/ እና የቤተ መዛግብት ጥናት ናቸው፡፡ እነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለፎክሎር እና ለሥነሰብ /Anthropology/ የትምህርት መስኮች ጥናቶች ብጁ እና ምቹ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸው ናቸው (Kottak, 1991:23) ፡፡

ከዚህም በማስከተል የተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንዴት እና እንደምን ጥቅም ላይ እንደዋሉ አመላክታለሁ፡፡

ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት /focused group discussion/ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ የዋሉት በኢ-መደበኛ /informal/ አቀራረብ ሲሆን የተደረጉትም በይሆነኝ ወይም ይበጀኝ /purposeful sampling method/ ዒላማ ከተመረጡ ተተኳሪ ግለሰቦች ጋር ነው፡፡ እነዚህንም ከዚህ በኋላ በጥቅሉ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች እያልኩ እጠራቸዋለሁ፡፡

ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች በተጨማሪም የአካባቢው ነዋሪዎች እያልኩ የምጠቅሳቸው የመረጃ ምንጮች አሉ፡፡ እነዚህም በየአጋጣሚው ያገኘኋቸው የድንበርተኞቹ ወረዳዎች ቀበሌዎች ነዋሪዎች ሲሆኑ በዕድሜ ሽማግሌዎች እና ወጣቶች፣ በፆታም ወንዶች እና ሴቶች፣ በሙያም አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ነጋዴዎች እና የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው፡፡ እነዚህንም ሁሉ የመረጃ ተባባሪዎቼንም ያነጋገርኳቸውም በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡

ቁልፍ የመረጃ ምንጮቹንም ሆነ ሌሎቹን ያነጋገርኳቸውም ሦስት ጊዜ ማለትም ከ 01/09/2002 እስከ 30/09/2002፣ ከ 07/01/2003 እስከ 30/01/2003፣ ከ 15/01/2004 እስከ 30/01/2004 ወደ ወረዳዎቹ ምልልስ በማድረግ ነው፡፡ በእነዚህም ጊዜያት የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ የግጭት መነሻዎች እና አፈታት ሁኔታ መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ቁልፍ የመረጃ ምንጮቹም የተመለመሉት የድንበርተኞቹን ቀወት ወረዳ (ሰፊ በረት[10]፣ ደብርና ጀጎል፣ ዓባይ አጥር እና ኩሬ በረት) እና የሰሙ ሮቢ ገለአሎ (አዲሲሂጌ፣ ሐሪሐሙ፣ ሆቲመሮ እና አስጋፊን) ቀበሌዎች ነዋሪዎችን የግጭት እና እርቅ ሁኔታ ጠንቅቀው የሚያውቁ የአገር ሽማግሌዎች በመሆናቸው፣ በስሙ-ጥር ባላባትነታቸው፣ በጎበዝ አለቃነታቸው፣ በጎሳ መሪነታቸው፣ በመልካም ዝናቸው እንዲሁም በሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑ እና የተመሰከረላቸው በመሆናቸው ነው፡፡

በቁልፍ የመረጃ ተባባሪነት በቃለ መጠይቅ /Interview/ ከሁለቱም ወረዳዎች በዕድሜ፣ በልምድ እና ማህራዊ ደረጃ የተቀራረቡ እና የተውጣጡ ሰባት ሰባት በድምሩ አሥራ አራት ሰዎች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በውስጣዊ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭት መንሥዔዎች እና አፈታቶች ላይ ቃለ መጠይቅ የሰጡት ሰባት፤ ሰባት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎችም እንደገና ስድስት አባላት እንዲካተቱበት እና

10 "ሰፊ በረት" የሚለው የቀበሌ ሥም ሰፊ የታጠረ የከብት በረት ከሚለው ጋር የተያያዘ ይመስላል፡፡ ይህም ደግሞ ምናልባትም ቀደምት የአማራ ሰፋሪዎች ሥፍራውን ከእርሻ ሥራ በፊት ለከብት ማሰማሪያነት እና ማሳደሪያነት ሳይጠቀሙበት እንዳልቀሩ ፍንጭ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

እንዲሳተፉበት በተደረገ በውጫዊ ማለትም የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች የግጭት መንሥዔዎች እና አፈታቶች የተተኳሪ ቡድኖች ውይይት /Focused Group Discussion/ እንዲካሄሉ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት በውጫዊ የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሉ ወረዳ ነዋሪዎች ዋነኛ የግጭት መንሥዔዎች እና አፈታቶች ዙሪያ ሦስት ከቀወት፤ ሦስት ከሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳ የተውጣጡ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት ተሳትፈዋል፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱም በብሔር እና በሥፍራ ብቻ ሳይሆን በዕድሜም እርከን ጭምር ተቀራራቢዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው ተቀራራቢ የሕይወት ልምድ እና ተሞክሮ ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ነው፡፡ የተተኳሪ ቡድኖቹ ውይይቶችም የተደረጉት በሁለቱ ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶች እና አፈታቶች ዙሪያ የተረጋገጠ እና የተጣራ ሐሳብ ለማግኘት እንዲቻል ታስቦ እና ታቅዶ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀውም የቡድን ውይይቱን የተጠቀምኩበት ሦስት ዓበይት ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ሦስቱ ዓበይት ጉዳዮችም የአማሮች የእርስበርስ ግጭት መንሥዔዎች እና የግጭት አፈታት ሁኔታ፣ የአፋሮች እርስበርስ ግጭት መንሥዔዎች እና የግጭት አፈታት ሁኔታ እንዲሁም የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች የግጭት መንሥዔዎች እና አፈታት ሁኔታ ናቸው፡፡

ከተመሰረቱት ሦስት ዓይነት የተተኳሪ ቡድኖች ጋር በተደረገው ውይይትም እንደታሰበውም ተደጋጋሚነት ያላቸው ጭብጦች ተገኝተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በቃለ መጠይቅ እና በሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰባሰቡት እና የተገኙት መረጃዎች ተኣማኒነት ለማጎልበት በጅቷል፡፡ ምክንያቱም የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኝነት ማረጋገጥ እና ማገነዛዘብ ተችሏል፡፡

ለቃለ መጠይቅ እና ለተተኳሪ ቡድን ውይይት በቁልፍ የመረጃ ተባባሪነት የተመለመሉትም ሰዎች የተለያዩ ዓይነት ስሜት የነበራቸው ነበሩ፡፡ መረጃ ለመስጠት ሙሉ ፈቃደኝነት የነበራቸው፣ አቅማሚዎች እና ፈቃደኝነት ያልነበራቸው፡፡

መረጃ ለመስጠት ሙሉ ፈቃደኝነት ያሳዩት ወገኖች ስማቸው ቢገለፅ፣ መልካቸው እና ድምፃቸውም ቢቀረፅ የማይቸገሩ በአጠቃላይም የሚያውቁትን ለመግለፅ ሙሉ ተባባሪዎች የነበሩ በአብዛኛውም አፋሮች ሲሆኑ፤ አቅማሚዎቹ ወገኖች ደግሞ መረጃውን ቢሰጡ ሊከተል የሚችል ነገር ይኖራል ብለው ሥጋት የገባቸው እና የመረጃውን አጠቃቀም እና አገልግሎት ልክ እንዲሁም ማስተማመኛም አጥብቀው

የጠየቁ በአብዛኛውም አማሮች ነበሩ። ፊፅሞ ፈቃደኞች ያልነበሩት ደግሞ እጅጉን የገነገኑ እና "መረጃው ለምን ተፈለገ?"፣ "መረጃውን በመስጠታችን ምክንያት ያልገመትነው እና ያልጠረጠርነው ችግር ቢከተልስ?" ወዘተ በሚል ሥጋት የገባቸው ነበሩ። ይሁንና ዓላማዬን በውል በተረዱልኝ እና እነርሱንም በሚግባቧቸው ሰዎች ጠገግ በመቅረብ የእነዚህንም ወገኖች ሥጋት ለማስወገድ መልካቸው ሳይታይ፣ ድምፃቸው ሳይሰማ፣ ስማቸው ሳይጠቀስ መረጃውን እንዲሰጡ ማግባባት ተችሏል። በእርግጥ እዚህም ላይ መረጃ በመስጠት ሂደቱ ላይ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች መፈጠራቸው በራሱም ሊፍታታ እና ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ነገር መሆኑ ይታያል። ምናልባትም ጊዜ ከማን ጋር እንደሆነም ይጠቁም ይሆናል። "ጊዜ የሰጠው" እና "ጊዜ የከዳው" ወይም "ጊዜ የጣለው" እንዲሉ።

በዚህም መሰረት ምንም እንኳን መረጃውን ለመስጠት ያልተቸገሩት፣ ጊዜም ሳይፈጁ በፈቃደኛነት መረጃ የሰጡት ማንነታቸው ቢገለፅ ቅሬታ እንደማይሰማቸው የገለፁትን የመረጃ ተባባሪዎች በተፀውዖ ሥማቸው፣ የተፀውዖ ሥማቸው እንዲገለፅ ያልፈቀዱትን ደግሞ በፍጥር ሥም እንዲሁም አንዳንዶቹን በደመምሳው የአካባቢው ነዋሪዎች በሚል እንዲገለፁ አድርጊያለሁ።

በአጠቃላይም ቃለ መጠይቁ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይቶቹ ተጎራባቾቹ ሕዝቦች ማህበራዊ አደረጃጀት፣ ሥርዓተ አኗኗር፣ በገበያ፣ በከብት ማስማሪያ፣ በእርሻ ሥራ አካባቢ ያላቸውን ግንኙነት፣ አተያይ፣ አኳኋን እና ዝንባሌ እንዲሁም የግጭት መንሥኤዎች፣ የግጭት ትውስታዎች፣ ግጭቶቹ ያስከተሏቸውን ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሣራዎች ወይም በአጠቃላይ በተጎራባቾቹ ዘንድ ደርሰው የነበሩትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድቀቶችና ሁኔታዎች፣ ግጭቶቹም የተፈቱባቸውን የሽምግልና ሂደቶች ለመረዳት ጥቅም ላይ የዋለ የመረጃ ዘዴ ነበር ማለት ይቻላል።

የቃለ መጠይቁ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይቱም ጥያቄዎች ጎንታይ እና ጨዋታ አስከፋች ዓይነት እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። ይህም የሆነበት ምክንያት የመረጃ ተባባሪዎቹ ነፃነት እንዲኖራቸው፣ ባልተገደበ ሁኔታም ሐሳባቸውን እንዲያፈሱ ለማድረግ ሲባል ነው። የጥያቄዎቹ ወግ አነቃቂ ዓይነት መሆንም የመረጃ ተባባሪዎቹ የመመርመር እና የመናዘዝ ስሜት እንዳያድርባቸው አድርጓል። ምክንያቱም የመረጃ ተባባሪዎቹ በናሙና ጥናት ወቅት ግንቦት 2002 ዓ.ም እንዳስተዋልኳቸው ብዙውን ጊዜ ቀጥተኛና መደበኛ ዓይነት ውይይትን አይፈቅዱም ነበር። በፈቀዱበትም ጊዜ ቢሆን

መቅረፀ ድምፅ /Tape/ እና መቅረፀ ምስል ወድምፅ /Video-Camera/ መሣሪያዎችን የማፈርም፣ ሐሳብ የመቋጠርም ሁኔታዎችን ያሳዩ ስለነበር ረጅም ወግ ብጤ መጀመር፣ መቅረፀ-ድምፅ ወምስልን እንዲሁም የተማሪ ዓይነት ማስታወሻ አወሳሰድን በማቆም እና ጨዋታውን በኩርኩራ ማስቀጠልን እመርጥ፣ አዘወትርም ነበር፡፡ እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ወረቀት እና ብዕር ሲያዩ የሚናገሩት የጠፋቸው ይመስል ነበር፡፡ እናም እጅግ የተሻለ ሆኖ ያገኘሁት የዝንጋታ ቆይታን (ከተሜው ሻይ ቡና እንበል የሚለው) ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተገኙትን ሐሳቦችም ከመረጃ ተባባሪዎቼ አጠገብ ስሆን ባጫጭሩ መመዝገብ፣ ዘለግ ያለ ጊዜ ሳገኝም ደግሞ የሰማኋቸውን ሁሉ በያዝኳቸው ኃይለ ቃሎች ወይም መሪ አንቀፆች መሰረት እያስታወስኩ በዝርዝር ማስታወሻ ላይ ማስፈር ነበረብኝ፡፡ ስለዚህም የጥናቱ መረጃዎች ጥቂት በድምፅ እና በምስል፣ በብዛት ደግሞ ከቃለ ምልልሱ ፍፃሜ በኋላ የቃለመጠይቁን ፍሬ ሐሳብ ሳልረሳው በትኩሱ በማስታወሻዬ ላይ በማስፈር እና በመያዝ የተሰነዱ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

ሦስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፅሞናዊ ምልከታ ነው፡፡ ፅሞናዊ ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን የተጠቀምኩት ሁለቱ ሕዝቦች በአኗኗር ማለትም በአሰፋፈር፣ በከብት ማሰማሪያ፣ በእርሻ ሥራ፣ በገበያ አካባቢ ያላቸውን ግንኙነትና የአተያይ፣ የአካኋን እና ዝንባሌ ሁኔታ ለመመዘን ነው፡፡ በዚህም ሥርዓተ አኗኗራቸው ጀርባ የማያስጥል እና አቆብቋቢነት የሚስተዋልበት መሆኑን ለማጤን ችያለሁ፡፡ ማህበራዊ አደረጃጀታቸውም የጥቃት ሥጋት መኖሩን የሚያመለክት፣ ዝግጁነትንም የሚጠይቅ መሆኑን ታዝቢያለሁ፡፡

የጥናቱ አራተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጽሑፋዊ እና ወጋዊ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቅን የተጠቀምኩትም ከተጋጪዎቹ ድንበርተኛ ሕዝቦች ተወላጅ ተማሪዎች የአማርኛ እና የአፋርኛ ሥነቃሎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይኸውም የተደረገው ከተተኳሪ የመረጃ ተባባሪዎቼ ዘንድ አንዳንድ ግጭት ተኮር ሥነቃሎች በየጨዋታችን ጣልቃ ሲነገሩ ብሰማም በቀጥታ ተረት ንገሩኝ፣ ሽላሎና ፉከራ አስደምጡኝ፣ የሥራና የሰርግ ዘፈን ዝፈኑልኝ፣ ሙሾ አውርዱልኝ ለማለት አልደፈርኩም፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው የግንቦት 2002 ዓ.ም. የቅኝት ጥናቴ ወቅት ግጭት ተኮር ሥነቃሎችን ከቀወት ወረዳ አዋቂዎች ከአቶ ሰጥአርጌ ደርሶ (06/09/2002) እና አቶ ደመቀ ሲሻህ (13/09/2002) እንደበት ለመስማት እና ለመሰብሰብ ሞክሬ አዛውንቶቹ አቀራረቤን የዋህ፣ ሥራዬንም "የልጅ ሥራ" አድርገውብኝ ስለነበር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት

የሁለቱን ሕዝቦች ሥነቃሎች አጭር መጠይቅ በማዘጋጀት፣ ከድንበርተኞቹ ወረዳዎች ለተገኙ እና በሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር በመመካከር፣ ስለ መጠይቁም አመላለስ አጭር ገለፃ በመስጠት በየአካባቢያቸው የሚሰሟቸውን ልዩ ልዩ ሥነቃሎች ለማሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ከተሰበሰቡትም ሥነቃሎች መካከል አንዳንዶቹን በኋላ ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ጋር ቃለ ምልልስ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ባደረግሁበት ወቅት እያነሳሁ አስተያየታቸውን እንዲሰጡባቸው አድርጊያለሁ፡፡ አንዳንዶቹንም ሥነቃሎች እራሳቸው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ለነገር ማጥበቂያነት በየጨዋታችን መካከል ሲያነሷቸው እየሰማሁ በቀጥታ ያጣኋቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ማግኘት እና ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

ሥነቃሎቹም የተሰበሰቡት በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል የርስበርስ /ውስጣዊ/ እና የጉርብትና /ውጫዊ/ የግጭት መንሥኤዎቹ በሥነቃል አማካኝነት የሚገለፁበት፣ ግጭትን የሚተክሉበት እና እንደ ልማድም የሚያነሱበትን አግባብ እና አጠቃቀም ለመመርመር ነው፡፡

የሁለቱን ሕዝቦች ሥነቃሎች የሰበሰብኩትም ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት በቀጥታ የሚጠቀሱትን የግጭት መንሥኤዎቹ እና ምክንያቶች ከመመርመር በተጨማሪ በተዘዋዋሪም ግጭትን የሚያበረቱ ሁኔታዎች በሥነቃሎቹ ውስጥ መኖራቸውን የመረጃ ተባባሪዎቼ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት በየአጋጣሚው በማንሳታቸው ነው፡፡ በዚሁም መሰረት በሁለቱ ሕዝቦች የሥነ ቃል ሀብት ውስጥ የሁለቱን ሕዝቦች ጉልቆ ትውልድ፣ ግጭት ተኮር ግንኙነት አፈ ታሪኮች፣ ግጭት ተኮር መልዕክቶች በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች ማለትም በሽላሎ፣ ፉከራ፣ በሥራ፣ በሰርግ፣ በለቅሶ ግጥሞች እንዲሁም በምሳሌ እና በተረት ወዘተ ውስጥ በድግግሞሽ በመታየታቸው ግጭታቸው እንደምን በሥነ ቃል አማካኝነት እንደተተከለ፣ ሕዝባዊም ሊሆን እንደቻለ እና እንደቀጠለም ለማጤን ተሞክሯል፡፡

በዚህም ሂደት ሁለቱ ሕዝቦች ግጭትን የሚመለከቱበትንና የሚገልፁበትን፣ የሚናኙበትንና የሚተክሉበትን፣ የሚያራምዱበትንም ቃላዊ ሀብታቸውን /ሥነቃላቸውን/ በመሰነድ እና በመመርመር ሥነቃሎቹ በግጭት አመነጫጨት ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና በአንክሮ ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ሀገረ ሰባዊ ሕይወትን ለመረዳት የሥነቃል ጥናትና ምርምር ጉልህ ሚና አለውና ነው፡፡ ከዚሁ ጋርም ሁለቱ ሕዝቦች ያሏቸውን ቃላዊና ጽሑፋዊ ተረኮች እንዲሁም ስለ ግጭት፣ ብቀላ፣ ገዳይነት

ስለ ጦር መሣሪያ፣ ስለ ሽምግልና እርቅና ግልግል ያላቸውን አተያይ በሥነቃሎቻቸው ውስጥ ከተዘሩት መልዕክቶች ውስጥ በመንቀስ ማዕከላዊ ማጠንጠኛ ሐሳባቸውን ለማውጣት ተጥሯል፡፡ ይህም ዓይነቱ አጠናን በተለይ ህቡዕ ወይም ታህታይ ንድፈ-ሐሳብን /grounded theory/ ለመረዳት ያስችላል (Glasser and Strauss, 2006)፡፡

የዚህ ጥናት አምስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የቤተ መዛግብት ጥናት መሆኑ በጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መሪ አንቀፅ ላይ መጠቆሙ ይታወሳል፡፡ እናም እዚህም ዘዴው እንደምን እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ መግለፅ ተገቢ ይሆናል፡፡

የቤተ መዛግብት ጥናቱ የተደረገው የሁለቱን ሕዝቦች የአስተዳደር እና የፍርድ ቤት ቤተ መዛግብት እንዲሁም ስለ ሁለቱ ሕዝቦች የተደረጉ ጥናቶችን ለመቃኘት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱ ወረዳዎች መስተዳድሮች እና የፍትህ ቢሮዎች ቤተመዛግት ውስጥ በሥርዓቱ የተደራጀ መዝገብ እና ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በሁለቱም ተጎራባች ወረዳዎች ውስጥ ስለ ሕዝቦቹ አኗኗር የሚጠቁም ሰነድ ሊገኝ ያልቻለውም በሁለት ምክንያቶች መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በዚህም መሰረት በቀወት ወረዳ ውስጥ የአስተዳደር እና የፍርድ ቤቶች መዛግብት ሊገኙ ያልቻሉት ሥርዓት በተቀየረ ቁጥር መዛግብት ሲዘረፉ እና ሲቃጠሉ የኖሩ በመሆናቸው እንደሆነ እንዲሁም በአማራ እና በአፋር መካከል ተናጠላዊ ግጭት እና ግድያ ቢፈፀምም ክሶች የማይመሰረቱ በመሆኑ ነው፡፡ በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳም በኩል ሰነድ ላለመኖሩ የሚነሳው ምክንያት ወረዳው አዲስ ስለሆነ ነው የሚል ነው፡፡ ሌላኛው ምክንያት ደግሞ እንደ ቀወቱ ሁሉ በአፋር እና በአማራ መካከል ተናጠላዊ ግጭት ቢከሰትም ክስ የማቅረብ ልማድ ያለመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ የቤተመዛግብት ጥናቱ በተለይ የተደረገው የሁለቱን ሕዝቦች ታሪካዊ ግንኙነት ከጽሑፍ ታሪክ አኳያ ለመማተር እና የሚተያዩበትን ሁኔታ ከቃል ታሪካቸው ጋር ለማመሳከር እንዲሁም በቀድሞው የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሸዋ ጠቅላይ ግዛት "ሸዋ ማህደር" ውስጥ ደግሞ ስለ አስተዳደራዊ ሁኔታቸው እና ፀጥታ ጉዳይ የተደረጉ መፃፃፎችን ለመመርመር ነው፡፡ የጽሑፍ ታሪክ ቅኝት የተደረገበትም ዋና ምክንያት የቃል ታሪኩን እውነትነት ለማስተያየት እና ለማንጠር ነው፡፡

በተለይ በጽሑፍ ታሪክ ቅኝቱ ውስጥ የነገሥታቱ የግዛት ዘመን አንዳንድ ጊዜ የተጣረሰ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ እንደማይጠፋ ከወዲሁ መጠቆም ተገቢ ይሆናል፡፡ ይኸውም የሚሆነው የተለያዩ ሰነዶች የአንዳንዶቹን ነጋሢዎች የግዛት ዘመን በወጥነት

ባላማስፈራቸው ነው፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ የጽሑፍ ታሪክ ቅኝቱን ያደረግሁበት ዋና ምክንያት የጥናቴ ዓቢይ ጉዳይ የሆነው ግጭት ተኮር ፎክሎር ሐሰት የሌለበት መሆኑን ለማስረገጥ የጥናቱንም መረጃዎች ከሦስት አቅጣጫ ማለትም ከቃለመጠይቅ፣ ከሥነቃል እና ከጽሑፍ ታሪክ አኳያ ሁሉ ለማረጋገጥ እና እሙንቱን በበቂ ማስረጃ ለማሳየት በማለም መሆኑ እንዲታወቅልኝ እሻለሁ፡፡

በዚህም መሰረት በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች፣ በየፈርጃቸውና በየሴማቸው እንደየአግባባቸው በየክፍላቸው ለማስቀመጥ እና ማእከላዊ መልዕክታቸውንም ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

በተለያዩ ዘውግ ተዘርተው የሚገኙትን ሥነቃሎች ማዕከላዊ ሐሳቦች በማጤንም ሁለቱ ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭት የሚያፈሩባቸውን፣ ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸውን፣ በድንበርተኝነታቸው የሚጋጩባቸውን፣ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸውን ሥርዓቶች፣ የሥርዓቶቻቸውን ትሩፋቶች እና ውሱንነቶች (በነገራችን ላይ ውስብስብ ሥርዓቶች ያሉት በተለይ በውስጣዊ ግጭት አፈታት ውስጥ ነው፡፡ ኋላ እንደምናየውም በውጫዊ ግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የምናገኘው ውስብነት ያለው ሥርዓት ሳይሆን ማስታገሻ ዘዴ ዓይነት ነው) እንዲሁም ስለ ግጭት እና እርቅ ያላቸውን አመለካከት መዞ ለማውጣት እና ለማመልከት ጥረት ተደርጓል፡፡

በመረጃዎቹም ላይ በመመሥረት ተጠኚዎቹ ማህበረሰቦች የሚኖሩበትን ሥርዓተ ሕይወት ለመመርመር፣ በግጭት እና እርቅ ዙሪያም ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረውም እንግዲህ በዚህ ጥናት የሁለቱ ተጎራባች ሕዝቦች ግጭቶች የሚመነጩባቸውን ወይም የሚከሰቱባቸውን ሁኔታዎች እና እርቅም የሚፈፀምባቸውን፣ እርቅ ቢፈፀምም ደግሞ ዘላቂነትም የሚያጣባቸውን አጋጣሚዎች ለመፈለግ፣ ለመመርመርና ለመተንተን ትኩረትና ጥረት ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ የድንበርተኞቹ አማሮችና አፋሮች ግጭት መንሥኤዎች፣ ገፅታዎች፣ ዕድገት ሂደቶች፣ ተስተጋብቶና አሕዝቦት፣ ሥርፀት፣ ሥርጭት፣ መከሰቻ አጋጣሚ እንዲሁም ማርገቢያ፣ መግቻ ወይም መፍቻ እና መቆጣጠሪያ ሥልቶች እና ሥርዓቶች ሀገረሰባዊ እውቀቶች እና ልማዶች በምሉዕነት ተመርምረዋል፡፡ ተተንትነዋልም፡፡

እዚህ ላይ ለመሆኑ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የጥናት ዓይነት እና መረጃ መሰብሰቢያዎች ዘዴዎች የሚጠኙት በምን ዓይነት ገፀ-ምድራዊ ገፅታ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ሕዝቦች ናቸው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህም ከዚህ በማስከተል ጥናቱ የሚካሄድባቸውን የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ገፀ ምድር፣ ሕዝብ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ለማመልከት ይሞከራል፡፡ ስለዚህም አሁን ወደዚሁ ዝርዘራ እዘልቃለሁ፡፡

# 4. የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ዳራዊ ገለፃ

በዚህ ምዕራፍ ለመግለፅ የሚሞከረው ጥናቱ የተካሄደባቸውን ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች መገኛ ማለትም ገፀ ምድራዊ ሁኔታ፣ የሕዝብ ብዛት እና አኗኗር፣ ኃይማኖት፣ እምነት፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ይዞታ ማለትም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብት፣ መሰረተ ልማት፣ የኑሮ መሰረት ወዘተ ነው፡፡ ይኸውም የተደረገው አንድ ሕዝብ የሚኖርበት አካባቢ ወይም ገፀ ምድር፣ የሚከተለው ኃይማኖት፣ በልማድ የያዘው እምነት፣ ሕይወቱን የሚመራበት የኑሮ መሰረት እና ያለበት ምጣኔ ሀብታዊ ደረጃ፣ አገልግሎት የሚያገኝባቸው መሰረተ ልማቶች አቅርቦት ዓይነቶች፣ ብዛት እና ሥርጭት ይዞታዎች የሕዝቡን አዕምሮታዊ እና ቁሳዊ ሀብት ዕድገት እና ደረጃ ስለሚገልፁ ነው፡፡ ስለዚህም የአንድን ሕዝብ ለግጭት ተጋላጭነት ሁኔታ ለመመዘን አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤውን ማለትም የሕዝቡ ሕይወት የተመሰረተበትን የሥራ ባህል፣ አመለካከት፣ ልማድ እና ፍላጎት እንዲሁም ከሌሎች ጎረቤቶቹ ጋር ያለውን የግንኙነት ሁኔታ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ስለ ግጭት መከሰት፣ መለመድ እና መዝለቅ በተዘዋዋሪም ቢሆን አመልካቾች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ እዚህም የቀረቡት ጉዳዮች በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ በጥናቱ ላይ አስተዋፅኦ ያላቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገለፃዎቹ የአንድን ክስተት፣ ግብር አኳኋንና ሁኔታ ለመረዳት እና በሚጠናውም ጭብጥ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ የማሳደር ሚና አላቸው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በአኗኗራቸው፣ አድራጎታቸው፣ ባህርያቸው መገኛ ምድራቸውን እና አካባቢያቸውን ይመስላሉና ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ሕዝብ የሰፈረበት ምድር አቀማመጥ፣ የሚሰጠው ፍሬ፣ ያቆረው ሀብት፣ የነዋሪዎቹን ሥርዓተ ሕይወት የመቅረፅ ሚና አለው፡፡ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎችን አጠቃላይ ከባቢያዊ ሥዕል መስጠትና ማመላከት አስፈላጊነትም የሚመነጨው ከዚህ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መንገድ ነው፡፡

ስለዚህም ከዚህ ቀጥሎ የሁለቱን ወረዳዎች ገፀ-ምድር፣ ሥርዓተ-አኗኗር፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁናቴ ባጫጭሩ እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያም ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች የት ናቸው? የሚለውን በማስከተልም የወረዳዎቹን ገፀ-ምድራዊ፣ ሥነ ሕዝባዊ፣ ሥርዓተ ሕይወታዊና ታሪካዊ

ማለትም እምነት፣ ኢኮኖሚ፣ መስረተ ልማት፣ የሥራ ባህል፣ ቤት አሰራር አመጋገብ፣ የተጎራባችነት ሁኔታ? ወዘተ እንመለከታለን፡፡

## 4.1. የቀወት ወረዳ ሕዝብ፣ መልክዓ ምድር እና ማህበራዊ ግንኙነት

የአማራ እና የአፋር ክልል ከሸዋ ደቡባዊ ምሥራቅ ጫፍ እስከ ሰሜን ወሎ ምሥራቅ በረኸርሙ በኩታ ገጠምነት የሚዋሰኑ ድንበርተኞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች የተባሉት የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ብቻ ናቸው፡፡

ቀወት ወረዳም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኙት ሃያ ሰባት ወረዳዎች አንዱ ሲሆን የሚገኘውም የኢትዮጵያን ተፋሰስ ወደ ምዕራብና ወደ ምሥራቅ በሚያካፍለውና በሚለየው የተራራ ሰንሰለት እና ገመገም ምሥራቃዊ ክፍል፣ ከአዲስ አበባ-ደሴ መንገድ በግምት ሁለት መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ገደማ ላይ በጥቅል ስሙ ይፋት በመባል በሚታወቀው አካባቢ ማዕከላዊ ክፍል ውስጥ ነው፡፡

ይህ የአማሮች እና የአፋሮች ግጭት እና ግጭት አፈታት ጥናትም የተደረገው ከሸዋ ሮቢት ከተማ ምሥራቅ እና ሰሜናዊ ምሥራቅ አካባቢ፣ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ከሚወስደው አውራ መንገድ በስተቀኝ አቅጣጫ አማሮቹ እና አፋሮቹ በድንበርተኝነት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ነው፡፡

ቀወት ወረዳን በሰሜን ኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ በምሥራቅ ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ፣ በደቡብ ምዕራብ ጣርማ በር-ማፉድ ወረዳ፣ በምዕራብ ሞጃና ወደራ መዘዞ ወረዳ፣ በሰሜን ምዕራብ ማማ ምድር ወረዳ ያዋስኑታል፡፡ በሥሩም ሃያ ሁለት የገጠር እና አራት የከተማ ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡

የቀወት ወረዳ ቆዳ ስፋት አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ስምንት ሄክታር ይደርሳል፡፡ በሕዝብ አሰፋፈር ጥግግቱም አንድ መቶ ዘጠና ያህል ሰዎች በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ውስጥ እንደሚኖሩ ይገመታል (አቶ አክመል መሐመድ የቀወት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤት ባለሙያ 23/09/2002 ዓ.ም.) ፡፡

የቀወት ወረዳ ሕዝብ ብዛት አንድ መቶ አሥራ ስምንት ሺ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ሲሆን (C.S.A. 2008:64) ከነዚህም መካከል ከመቶ ሺህ በላይ የሚሆኑት

በገጠር ቀሪዎቹ ዐሥራ ሥምነት ሺ.ህ ገደማ ደግሞ በከተማ የሚኖሩ ናቸው። ከወረዳው ነዋሪዎች መካከልም ብዙኃኑ አማራ ሲሆኑ፣ ሁለተኛውን ደረጃ አርጎባ[11]፣ ሦስተኛውን አፋር የመጨረሻውን ደግሞ አሮሞ ይይዛሉ።

በቋንቋ ረገድ ዛሬ ከቀወት ወረዳ ነዋሪዎች መካከል ሰማኒያ ስምንት ከመቶ የሚሆኑት አማርኛን፣ አራት ከመቶ የሚሆኑት አሮምኛን፣ ሁለት ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ አርጎብኛን እና አፋርኛን በአፍ መፍቻነት ይናገራሉ፣ በጥቅሉም ደግሞ በማናቸውም ማህበራዊ ግንኙነት እና ተግባቦት ወቅት ሁሉ በአማርኛ ቋንቋ ይግባባሉ (ሰለሞን ይብዛ ቀወት ወረዳ መስተዳድር ጽህፈት ቤት 24/09/2002 ዓ.ም) ።

የወረዳውን ነዋሪዎች እምነት ስንመለከትም ሰማኒያ ከመቶ የሚሆኑት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናን፣ ሃያ ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ እስልምናን ቀሪውን ዝቅተኛ መቶኛም ፕሮቴስታንቶች እንደሚከተሉ ይገመታል (አቶ አክመል መሐመድ የቀወት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤት ባለሙያ 23/09/2002 ዓ.ም.) ።

ቀወት ወረዳ ከላይ እንደተጠቆመው አማሮች፣ አርጎባዎች፣ አፋሮች፣ ጅሌ አሮሞዎች፣ ተጎራብተው አልፎ አልፎም ተሰጋስገው የሚኖሩበት በመሆኑ በጉርብትና፣ በገበያ፣ በውኃ፣ በከብት ማስማሪያ ግጦሽ ሣር፣ በእርሻ መሬት ፍለጋ ምክንያት ሁሉ ቅርብ ግንኙነት አላቸው።

በተፈጥሮ ሀብት በኩል ከቀወት ወረዳ ወደ ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የሚፈሱ ጀብ ውኃ፣ ታቦር፣ ሮቢ እና ጉልፈታ የሚባሉ ወንዞች እና ፍል ውኃዎችም አሉ። ወንዞቹ ክረምት ሲሆን አዋሽን ይቀላቀላሉ። በጋ ሲሆን ግን አንዳንደቹ ወንዞች አዋሽ ሳይደርሱ ከወዲሁ ይቀራሉ። ፍል ውኃዎቹ ደግሞ ለልዩ ልዩ በሽታዎች ፈውስ ይሰጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ብዙዎችም ይጠመቁባቸዋል፣ ይዘፈዘፉባቸዋልም (አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ 06/09/2002 ዓ.ም እና አቶ ከፈለኝ ድረሴ 12/09/2002 ዓ.ም) ።

---

[11] እዚህ ላይ አንድ ሊታወስ እና ሊጤን የሚገባው ጉዳይ አርጎባዎች የሚኖሩት ቀወት ወረዳ ውስጥ ብቻ እንዳልሆነ ነው። በታሪክ እንደሚታወቀው አርጎባዎች ወላስማ የተሰኘው ሥርወ መንግሥታቸው በውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭት ከተዳከመ እና ከከሰመ በኂላ የመገኛቸው መልክዓ ምድራዊ ትስስር የተቆራረጠ ሆኗል። የሚኖሩት መልክዓ ምድራዊ ጥግግት በሌለው ሁኔታ ነው። ስለዚህም ኬሚሴ አካባቢ ሾንኬ በተባለ ኮረብታ፣ ሸዋ ሮቢት ከተማ ውስጥ፣ በሸዋ ሮቢት ከተማ ምሥራቃዊ እና ሰሜን ምዕራባዊ ኮረብታዎች፣ በአስጎሪ፣ በጨኖ፣ በጋቸኒ፣ በአልዩ አምባ እንዲሁም መንዝ አዳባይ ጅረት አጠገብ እና በምሥራቃዊ እና ማዕከላዊ የአገሪቱ ከተሞች ተሰራጭተው ይኖራሉ። በአንፃራዊ ሁኔታ አንድ ልዩ ወረዳ ለመሆን የሚያስችል የሕዝብ ብዛት እና ጥግግት ያላቸውም በአፋር ክልል ጋቸኒ ብቻ ነው።

በዱር እንስሳት ረገድም ለምግብነት የሚውሉ (ሳላ፣ በኸር፣ ወንደቤ፣ አጋዘን፣ ድኩላ፣ ሰስ፣ ሚዳቋ፣ እንሹዬ፣ የሜዳ ፍየል፣ ቆርኬ፣ ቆቅ፣ ጅግራ፣ ድርጭት፣ ሶረን) እና ለክብር ማግኛነት የሚታደኑ (ነብር፣ ነብር አርት) እና ሌሎችም (ሾላ፣ ቀበሮ፣ ተኩላ፣ የሜዳ አህያ፣ አራጅ ወዘተ) የዱር እንስሳት በወረዳው ይገኛሉ፡፡

የቀወት ወረዳ ሕዝብ ሕይወቱን የሚመራውም በእርሻ፣ በአትክልት ምርት፣ በእንስሳት እርባታ፣ በንግድ፣ በዕደ ጥበባት /ሽመና፣ ቅጥቀጣ፣ ሸክላ እና የቆዳ ሥራ/ እና በመንግሥት ሥራ ተሰማርቶ ነው፡፡

በአዝርዕት እና ዕፅዋት ረገድ በተለይ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበር አካባቢ የሚገኘው "ምድር ያፈራውን ሁሉ ያበቅላል፣ ያበላል" ነው የሚባለው፡፡ ስለዚህም የቀወትም ወረዳ ሕዝብ "አዝመራው ማለፊያ ነው" በሚባልበት ጊዜ በምርቱ የወረዳውን እና አጎራባች ወረዳዎች ነዋሪዎች ሸማቾችን የማሽላ፣ የበቆሎ፣ የዘንጋዳ፣ የጤፍ፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የአትክልት ፍላጎት ያሟላል (አቶ ሀብተወልድ ተጌ የቀወት ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት የተፈጥሮ ሀብት ኃላፊ 24/09/2002 ዓ.ም.)፡፡

በመሰረተ ልማት ረገድ በአሁኑ ወቅት በወረዳው ውስጥ አሥራ አራት ከአንድ እስከ አራት፣ ሃያ ስድስት ከአንድ እስከ ስምንት፣ አንድ መሰናዶ፣ አንድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ የመሰናዶ እና የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤቶቹ ግን ለቀወት ወረዳ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ አይደሉም፡፡ ለሸዋ ሮቢት ከተማ እና ለአጎራባችም ወረዳዎች ጭምር በጋራ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በጤና አጠባበቅ በኩልም ቀወት ወረዳ 19 ጤና ኬላዎች፣ አንድ ጤና ጣቢያ አሉት፡፡ ከወረዳው አሥራ ስምንት ቀበሌዎች መካከልም አሥራ አምስቱ ቀበሌዎች ገመድ አልባ ስልክ ተጠቃሚዎች መሆናቸው ይነገራል (ሰለሞን ይብዛ ቀወት ወረዳ መስተዳድር ጽህፈት ቤት፣ 24/09/2002 ዓ.ም )፡፡

የመኖሪያ ቤት አሰራርን በተመለከተም ቀወቶች በድንጋይ ግንብ፣ በግድግዳ፣ በሣር ወይም ቆርቆሮ ክዳን በአመዛኙ ክብ የሆኑ ቤቶችን ይሰራሉ፡፡ ከቤታቸው ውጪም እንዲሁ ክብ አጥራቸውን ያጠነክራሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያኖቻቸው፣ የቤተ ክርስቲያኖቻቸው አጥሮች እና አፀዶቻቸውም እንዲሁ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ክብነት በቤት እና በአጥር ብቻ ሳይሆን በበርካታ የቤት ውስጥ ቁሶቻቸው እና ከቤት ውጪም ባሉ መገልገያዎች ላይ ሁሉ ይታያል፡፡

የቀወት ወረዳ ሕዝብ የዘወትር ምግብ እንጀራ ነው፡፡ ማባያዎቹ የሽሮ፣ የክክ፣ የሥጋ፣ የዓሣ የጎመን ወጥ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎም የኑግ፣ የሰሊጥ የሱፍ ድልዝ፣ እንዲሁም ወተትም አይታጡም ነው የሚባለው፡፡ እነዚህ ሲታጡ እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመሃልም ቃሪያም ማባያ ይሆናል፡፡ ዳቦ፣ ቂጣ እንዲሁም የገብስ፣ የሽምብራ ቆሎ እና የባቄላ የአተር፣ የበቆሎ፣ የስንዴ፣ የአደንጓሬ ንፍሮ መለዋዎጫዎች እና ማማሻዎችም ናቸው፡፡ መጠጡ ጠላ፣ ቅራሬ፣ አረቂ /ካቲካላ/፣ ወተት /ትኩስ፣ እርጎ፣ አሬራ ወይም አጓት/ ወዘተ ነው፡፡ እነዚህ ሲታጡ ደግሞ ነዋሪዎቹ እንደሚሉት "ጥሬ ቅጭ ቅጭ፣ ውኃ ግርግጭ" ዓይነት ሕይወት ይመራል፡፡ ወደ ማህበራዊ ግንኙነት እና አደረጃጀታቸው ገለፃ እንሸጋገር፡፡

የቀወት ወረዳ አማሮች በመሰረታዊ ሁኔታ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እና አደረጃጀታቸውን የሚመሰርቱት በትውልድ ሐረግ መዘዛ ወይም ቆጠራ ነው፡፡ ከትውልድ ቆጠራ ቀጥሎ ማህበራዊ ግንኙነት የሚመሰርቱት በጋብቻ፣ በጡት አባትነት፣ በጡት እናትነት፣ በክርስትና አባትነትና እናትነት፣ በአደራ ልጅነትና አባትነት፣ እናትነት፣ በሰንበቴ ማህበርተኝነት፣ በጉርብትና፣ ዕድር፣ በደቦ፣ በወዳጅነት ወዘተ ነው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፌለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

በጋብቻ ረገድ በአካባቢው ጋብቻ የሚፈፀመው ብዙውን ጊዜ በተጋቢዎች መካከል እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የሥጋ ዝምድና አለመኖሩ ተቆጥሮ ነው፡፡ የአካባቢው አረጋውያን ይኸውም የጋብቻ ባህል የተተከለው ጥንት በስብስቴ ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል እያሉ ይተርካሉ (እዚህ ላይ አንዳንዶቹም የስብስቴ ዘመን የሚሉት እጅግ በጣም ጥንት ለማለት መሆኑን ተረድቻለሁ)፡፡ ይሁንና ይህ ቃል ታሪክ ከጽሑፉ ታሪክ ጋር የተስማማ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እስከ ሰባት ቤት ድረስ ዝምድና አለመኖሩ ተቆጥሮ ጋብቻ እንዲፈፀም ያወጁት ስብስቴ ሳይሆኑ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው፡፡ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ በግዛታቸው ውስጥ የሚገኝ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት ተከታይ ሕዝብ ሁሉ ጋብቻ ሲፈፅም በተጋቢዎቹ መካከል እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ዝምድና አለመኖሩን ቆጥሮ እንደሚፈፅም ማወጃቸው ተፅፏል (ጌታቸው፣1997፡192) ፡፡

ቀወት ውስጥ ጋብቻ ከመፈፀሙም በፊት ለጋብቻ በተጫጨት ወይም በተፈላለጉት ወንድ እና ሴት መካከል የክርስትና፣ የጡት አባትነት፣ እናትነት ወንድምነት፣ እህትነት ወይም ልጅነት፣ አለመኖሩ ይረጋገጣል፡፡

ቀወቶች ማህበራዊ ትስስራቸውን ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መንገዶች ሁሉ ቢመሰርቱም ዛሬ በአሰፋፈራቸው ላይ እነዚህ ዘወትር አይታዩም፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ቤቶቻቸውን የሚሰሩትና የሚሰፍሩት በቤተ ትውልድ እና ቤተ-ዝምድና ወይም የትውልድ ሐረግ ግንኙነት ላይ ተመስርተው አይደለም፡፡ ቦታቸውን ቆርቁረው የሚሰፍሩት በመንግሥት ተለክቶ በተሰጣቸው የገመድ መሬት እና ለመኖር ያመቻል በሚሉት፣ ውኃ በቅርብ በሚያገኙበት፣ የፍሳሽ መውረጃ የሚሆን እና የጓሮ እሸት ማልሚያ ማሳ ባለበት፣ የከብት መውጫ መግቢያ ማለትም ማሰማሪያ ባመቸበት ቦታ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ደግሞ ክፍት ሥፍራ ፈልገው በማቅናት ወይም ከርስት ተወላጆቻቸው በውርስ በያገኙት ቦታ ላይ ይሰፍሩ እንደነበር ይወሳል፣ ይታወሳልም፡፡ ስለዚህም ቀወቶች ጎረቤታቸው ዘመዶቻቸው ይሆኑ ዘንድ የግድ አይጠብቁም ወይም አጎራባቾቻቸውን አይመርጡም፡፡ ምቹ የሚሉትን መስፈሪያ መሬት መርጠው እራሳቸውን ይተክላሉ እንጂ፡፡ ቀወቶች "ደግ ወንድምን ክፉ ጎረቤት ይጠራዋል" የሚሉትም ይህንኑ ለመግለፅ ይመስላል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ገፀ-ምድር፣ ሕዝብ፣ እምነት፣ ኢኮኖሚ፣ መሰረተ ልማትና አመጋገብ እንዲሁም ማህበራዊ አደረጃጀት ገለፃ ይቀርባል፡፡

## 4.2. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ሕዝብ፣ መልክዓ ምድር እና ማህበራዊ ግንኙነት

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የሚገኘው በአፋር ክልል ዞን አምስት ውስጥ ሲሆን በክልሉ ካሉት ሰላሳ ሁለት ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ወረዳው የተቋቋመው ከ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥ በኋላ ሲሆን ማዕከልነቱም ቀድሞ በቀወት እና ማፉድ ወረዳዎች (እነዚህም ወረዳዎች ከ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥ በኋላ የአማራ ክልል ተብሎ በተለየው ውስጥ ተካተዋል) ሥር ይተዳደሩ ለነበሩ አሥራ ሁለት ቀበሌዎች ነው፡፡

ሰሙ·ሮቢ ገለአሉ የሚለው የወረዳው መጠሪያ ሥም የተሰየመውም በውስጡ ከሚኖሩ ሦስት የአፋር ጎሳዎች ማለትም አይዳሂሶ፣ አይጡር እና ጊዶቦሶ ጎሳዎች መገኛ አካባቢዎች የቦታ ሥያሜዎች በማጣመር እንደሆነ ይነገራል (አቶ ዓሊ ሰይድ የወረዳው መስተዳደር አባል 26/09/2002 ዓ.ም) እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት (ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሉሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሉ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ፡፡

በዚህም መሰረት "ሰሙ" የሚለው ሥም አይዳሂሶ ከሚባለው ንዑስ ጎሳ መኖሪያ አካባቢ ሥያሜ፣ "ሮቢ" የሚለው ሥም አይጡር ከሚባለው ዓቢይ ጎሳ መገኛ አካባቢ ሥያሜ፣ "ገለአሉ" የሚለው ሥም ደግሞ ጊዶቦሶ በመባል ከሚታወቀው ሌላ ዓቢይ ጎሳ መኖሪያ አካባቢ የጎጥ ሥያሜ የተገኙ ሲሆኑ ተጣምረውም "ሰሙ·ሮቢ ገለአሉ" የሚለውን የወረዳ መለያ ሥም እንዲሰጡ የተደረጉ ናቸው፡፡ Akmel (2010) ም ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡

ሰሙ·ሮቢ ገለአሉ ወረዳን የምናገኘው ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ በሚወስደው መንገድ ከሸዋ ሮቢት ከተማ በስተምሥራቅ በኩል ነው፡፡ የወረዳው ከተማ ኩማሜም ከአዲስ አበባ ሁለት መቶ ዘጠና ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ከሰመራ አራት መቶ ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከዞን አምስት ከተማ ዳሊፋጊ ደግሞ ሦስት መቶ ሰማኒያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው፡፡

ሰሙ·ሮቢ ገለአሉ ወረዳን የሚያዋስኑትም በሰሜን ሀዴሌኤላ፣ በምሥራቅ ቡሬ ሙዳይቱ እና አሚባራ፣ በደቡብ ጣርማ በር፣ በምዕራብ ቀወት ወረዳዎች ናቸው፡፡

የሰሙ·ሮቢ ገለአሉ ወረዳ ገፀ-ምድር ሜዳማና ኮረብታማ ነው፡፡ በውስጡ ሮቢ ወንዝና ሌሎች ትናንሽ ጅረቶች ይፈሱበታል፡፡ ሜዳማው የወረዳው ክፍል ጊዶቦሶዎች የሚኖሩበት ገለአሉ ነው፡፡ የገለአሉ ሜዳ ምሥራቃዊ ክፍሉም የአዋሽ ወንዝም የሚረገረግበት ነው፡፡ ኮረብታማው ደግሞ ቀደም ባለው ዘመን በአካባቢው "ገገር መደብ" ተደርጎ ይቆጠር ከነበረው "አሻይማራ" ዝርያ የሚመደቡት አይዳሂሶዎች የሚኖሩበት ሰሙ ጉብታ እና ዙሪያ ገባው ነው፡፡

የአይጡር ጎሳ አባላት ደግሞ በሮቢ ወንዝ ተፋሰስ ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ ሮቢ ወንዝ ከላይ ከደጋማው ቀወት ወረዳ የሚወርድ፣ ሸዋ ሮቢት ከተማንም ለሁለት ሰንጥቆ የሚያልፍ፣ የአይጡር ጎሳዎች የሚኖሩበትን አካባቢ የሚያረሰርስ ነው፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ውስጥ ከሰላሳ ሁለት ሺህ በላይ ሕዝብ ይኖራል (C.S.A.፣2008፡7) ፡፡ በወረዳው ከሚኖረው ሰላሳ ሁለት ሺህ ሕዝብ መካከልም ሰላሳ ሺህ የሚሆኑት በገጠር፣ ሁለት ሺህ የሚሆኑት ኩማሜ ከተማ ውስጥ እንደሚኖሩ ከወረዳው መስተዳድር ጽህፈት ቤት የተገኘ መረጃ ያመለክታል (ቃለ መጠይቅ፡- አቶ ዓሊ ሰይድ የወረዳው መስተዳደር አባል 26/09/2002 ዓ.ም) ፡፡

ከነዋሪዎቹም መካከል ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ አፋሮች ሲሆኑ ቀሪውን አንድ መቶኛ ደግሞ በልዩ ልዩ መስክ ተሰማርተው የሚገኙ የሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ተወላጆች ይይዛሉ፡፡

በእምነት ረገድ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ሕዝብ እንደ ክልሉ የአፋር ሕዝብ ሁሉ ሙሉ በሙሉ የእስልምና እምነት ተከታይ ነው፡፡ አፋሮች በወጥነት የእስልምና ኃይማኖትን እንደ ኢትዮጵያ ሶማሌ፣ አደሬ፣ አርጎባ፣ ስልጤ እና ወለኔ የሚከተሉ ሕዝቦች ናቸው፡፡ እንዲያውም ሰሙሮቢ ገለአሎዎችም ሆኑ ሌሎቹ "አንድ አገር፣ አንድ ኃይማኖት፣ አንድ ቋንቋ ያለን ሕዝብ ነን" ይላሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004)፡፡

በቋንቋ ረገድ አፋርኛ የወረዳው ነዋሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው፡፡ አማርኛም ቢሆን ግን በተለይ በዕድሜ ጠና ላሉት ብዙም አይቸግራቸውም፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ኑሯቸውን በእንስሳት እርባታና በከፊል አራሽነት ነው የሚመሩት፡፡ በእንስሳት እርባታ ረገድ ላሞች፣ ግመሎች፣ ፍየሎችና በጎችን እና የጋማ ከብቶችን ያረባሉ፡፡ የእንስሳት እርባታቸውን ለማካሄድም የአካባቢያቸውን መሬት ለበጋ እና ለክረምት ማጋጫነት እየለዩ የመቀረረር ልማድ አላቸው (ቃለ መጠይቅ፡- አቶ መሐመድ አይዳሂስ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ 26/09/2002 ዓ.ም) ፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች ከእንስሳት እርባታ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፊል አራሽ በመሆን በቆሎ፣ ማሽላ፣ ማሾ፣ ጤፍ፣ ለውዝ፣ ጥጥ ያመርታሉ፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ነዋሪዎች ሕይወታቸውን በዋነኛነት በእንስሳት እርባታ እና ከፊል ግብርና ይምሩ እንጂ ግመሎቻቸውንም በበረሃው ለሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች ያከራያሉ፡፡ አልፎ አልፎም ጨርቃጨርቅ፣ የእጅ መሣሪያዎች ማለትም ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ጥይት፣ የእጅ ቦምብ የመሳሰሉትን እንደሚነግዱ ይነገራል፡፡

በመሰረተ ልማት ረገድ ወረዳው በአሁኑ ወቅት የትምህርት፣ የጤና፣ የመንገድ፣ የስልክ አገልግሎቶች ተጠቃሚ በመሆን ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ አሥራ ሦስት መደበኛ ማለትም ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው እንዲሁም አሥራ ስምንት አማራጭ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

የጤና መሰረተ ልማትን በሚመለከትም ሦስት ጤና ጣቢያዎች ዘጠኝ ጤና ኬላዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡

በመንገድ መሰረተ ልማት በኩልም በወረዳው ሥር የሚገኙት አስራ ሁለት ቀበሌዎችን ከወረዳው ርዕሰ ከተማ ኩማሜ ጋር የሚያገናኙ የገጠር መንገዶች እንደተሰሩ፣ በስልክ አገልግሎት በኩልም አሥራ ሁለቱንም ቀበሌዎች ሊያገናኙ የሚችል የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት እንዳለ ለመረዳት ተችሏል (ቃለ መጠይቅ፡-አቶ አቶ ዓሊ ሰይድ የወረዳው መስተዳደር አባል 26/09/2002 ዓ.ም) ፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በተፈጥሮ ሀብት ረገድም በቀወት ቆላማ ክፍል የተጠቀሰውን ሁሉ ይጋራሉ፡፡

የወረዳው ሕዝብ የዘወትር ምግብ ከላም፣ ከግመል፣ ከፍየልና ከበግ የሚገኝ ወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ የበቆሎ ገንፎ፣ ቆሎ፣ ገንፎ፣ ቂጣ ነው፡፡ አፋሮች ትኩስ ወተትን አዘውትረው ይጠጣሉ፡፡ የበቆሎ ቂጣ ማባያቸውም ትኩስ ወተት ነው፡፡ ትኩሱን ከመጠጣት የተረፈው ወተት ደግሞ በእርጎነት፣ አሬራነትና አይብነት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ማህበራዊ አደረጃጀት እንመልከት፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ማህበራዊ ግንኙነት በጎሳ ጉልቆ ትውልድ ቆጠራ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ሰሙሮቢ ገለአሎዎች እራሳቸውን የሚያዩት ከሁለት ዓበይት ጥንድ ጎሳዎች ማለትም አሻይማራ እና አዶሂማራ የፈለቁት እና የወረዱት የአይጡር እና ጊዲቦሶ እንዲሁም የአንድ ንዑስ ጎሳ ማለትም አይዳሂሶ ዝርዮች አድርገው ነው፡፡ በዓቢይነት የሚታወቁትም አሻይማራ እና አዶሂማራ በመባል የሚታወቁ ጎሳዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ጎሳዎችም በመልክ እና በማህበራዊ ደረጃቸው የተለያዩ እንደሆኑ ይነገራል፡፡

የአሻይማራ ጎሳ ተወላጆች በመልካቸው ቀያይ፣ በማህበራዊ ደረጃቸው ገገር፣ መኳንንት፣ መሪ፣ የማናቸውም ሥርዓት ከበራ ተቀዳሚ እና ቡራኬ ሰጪዎች

ተደርገው ሲቆጠሩ፣ የአዶሂማራ ጎሳ ተወላጆች ደግሞ በመልካቸው ጠየም ጠየም ያሉ፣ በማህበራዊ ደረጃቸው የተራነት ወይም የዘገርነት፣ የተከታይነት ሚና ያላቸው ተደርገው ይታያሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ።

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ዓበይት የአሻይማራ እና አዶሂማራ እንዲሁም ንዑስ የጎሳ ሐረጋቸውን መቁጠር እስከቻሉም ድረስ በሚኖሩበት ወረዳ፣ ዞን እና ክልል ብቻ ሳይሆን ሌሎችም አፋሮች ወደሚኖሩባቸው አጎራባች አገሮች ኤርትራ እና ጅቡቲ መዝለቅ ይቻላቸዋል፡፡ ስለዚህም አፋሮችን የፖለቲካ ድንበር አያግዳቸውም፡፡ እንደሚታወቀውም ዛሬ አፋሮች በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ እና በጅቡቲ ግዛቶች ይኖራሉ፡፡ የጎሳ ሐረጉን እና ትስስሩን ለሚተርክ አፋርም መንገዱ በየትኛውም አቅጣጫ ክፍት ነው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ።

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ማህበራዊ ግንኙነት ዋነኛ መመሥረቻም ይኸው ዓቢይ ጎሳ እና ንዑስ ጎሳን መቁጠር እና በዚሁ የጎሳ ትስስር ቆጠራ መሰረት ተጠጋግቶ መስፈር ነው፡፡ በዚህም መሰረት ኬዶ /keexo/፣ ዳላ /xaala/፣ ቡራ /bura/ እና ጋንታ /gata/ የሚሰኙ በተዛማጅ ጎሳዎች፣ በአንድ ጎሳ ተወላጆች፣ በቅርብ ቤተሰቦች በሚመሰረቱ መንደሮች ተሰባስበው ይኖራሉ፡፡ ስለዚህም በአንድ አካባቢ ተጠጋግቶ ለመኖር የጎሳ ቤተ ዝምድና መሰረታዊ መስፈርት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህም ዓይነቱ የመንደር አደረጃጀት በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የአፋሮች መኖሪዎች የተለመደ እና የማህበራዊ ግንኙነት መፍጠሪያ፣ የግንኙነቱም መታያ እንደሆነም ይነገራል፡፡ በአጭሩም ሰሙሮቢ ገለአሎዎች የሚሰፍሩት እና የሚኖሩት ጎረቤቶቻቸውን መርጠው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከጎሳ ቤተ ዝምድና ቀጥሎ ሁለተኛው የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ማህበራዊ ግንኙነት መመሥረቻ ጋብቻ ነው፡፡ ጋብቻ በማናቸውም ኅብረተሰብ ውስጥ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠሪያነቱ የታወቀ ቢሆንም በሰሙሮቢ ገለአሎዎችም ሆነ በሌሎች አፋሮች ዘንድ ግን ዋነኛው ውስጣዊ የቅርብ ቤተሰቦች የቤተሰብ ማህበራዊ አንድነት መፍጠሪያ እና ማጥበቂያ፣ የወገን እና የሀብትም ማደርጂያ፣ በጥቅሉም

የጥንካሬ ምንጭ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህም መሰረት “አብሱማ” የተሰኘ ጥብቅ የጋብቻ ሥርዓት እና ወግ ልማድ ይከተላሉ፡፡ በዚህ የ “አብሱማ” የጋብቻ ሥሪት መሰረትም ወንድ የአባቱን እህት ልጅ፤ ሴት ደግሞ የእናቷን ወንድም ልጅ ያገባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጋብቻ መፈፀምም በባህሉ የተነወረ  እና የተከለከለ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ወግ ልማድ በመተላለፍ ጋብቻ ከተፈፀመም ቂም በቀል እና ግድያ ሊያስከትል ይችላል  (የተተኳሪ ቡድን ውይይት ፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ፡፡

ሌላኛው የሰሙሮቢ ገለአሉም ሆነ የጠቅላላው አፋሮች አንድነት ግዳዊ ግንኙነትና ተግባቦት መግለጫ “ዳጉ” /xaagu/ የተሰኘው የተግባቦትና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓታቸው ነው፡፡

“ዳጉ” /xaagu/ ማለትም አንድ አፋር በሚኖርበት እና በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ያለውን አጠቃላይ ሁነት፣ ክስተት፣ ድርጊት፣ ወሬ፣ እንግዳ ነገር ሁሉ በመንገዱ ላይ ለሚያገኘው ተላላፊ አፋር ብዙውን ጊዜ በቁጢጥታ አቀማመጥ ወይም በቁም ቆይታ የመግለፅ ልማድ ነው፡፡ ይህም ከሰላምታ ልውውጥ በኋላ መረጃን በቁም ወይም በቁጢጥታ የመጋራት ወግ፣ ልማድ በአፋሮች ዘንድ ለዘመናት የኖረ እና እስከ ዛሬም የዘለቀ ጉዳይ እንደሆነም ነው የሚተረከው፡፡ ስለዚህም ማናቸውም አፋር በሰላምታ ልውውጥ ወቅት ያየውን፣ የሰማውን ነገር ሁሉ የመግለፅ፣ የማካፈል እና የማሳለፍ ማህበራዊ ግዴታ አለበት፡፡ በሰሙሮቢ ገለአሉዎች ዘንድ መረጃን መጋራትም ማህበራዊ ኃላፊነት እና ግዴታ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ መረጃን በመጋራቱ ሂደት ወቅት የሚስተዋለው የቆምታ እና የቁጢጥታውም  ርዝመት የሚወሰነው በወሬው መድራት እና መቀዝቀዝ ነው፡፡ ወሬው ሲደራ ቁጢጥ፣ ሲያጥር ቆም ይላሉ፡፡ ይህ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓታቸውም አፋሮች ከኋላቸውም ሆነ ከፊታቸው ያለን ነገር ሁሉ አውቀው ይንቀሳቀሱ ዘንድ ይረዳቸዋል፡፡ “አፋር የሚያወራውንም የሚያደርገውንም አረጋግጦ ነው” /qafar nabta waa kee qabta waa heduk qabata/ የሚለውንም ምሳሌ ከዚሁ የተነሳ ይመስላል፡፡ ምሳሌውም በበኩሉ በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን ከፍ ሳያደርግላቸው የቀረ አይመስልም ፡፡

የሰሙርቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በጎሳ ትስስር፣ በቀለም፣ በቤተ ዝምድና ሐረግ ቆጠራ ተሰባስበው እና ተከፋፍለው እንደመኖራቸው ሁሉ በዕድሜም የመከፋፈልና ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያ እና ፖለቲካዊ ግዳጆችን የመወጣት ወግ ልማድ አላቸው፡፡

በሰሙርቢ ገለአሎ ነዋሪዎች ዘንድ በዕድሜ ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ የሥራና የኃላፊነት ክፍፍል አለ፡፡ በዚህ በዕድሜ ላይ በተመሰረተ የሥራ ክፍፍል መሰረትም ጎልማሶች ግጭቶችን የመወጣት ልምዶችን እና ተመክሮዎችን ለወጣቶች በማካፈል፣ በግጭቶች አፈታት ሽምግልና፣ በአካባቢ አስተዳደር እና ሥርዓተ ከበራዎች አመራር ኃላፊነቶች ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡ በአንፃሩ ወጣቶች ደግሞ ወጣቶች በውስጣዊ አካባቢያዊ ሰላም ጥበቃ፣ በግጦሽ ሣር እና ውኃ አሰሳ፣ በእንስሳት ሥምሪት እና ጥበቃ፣ በውጫዊ ኃይል መከላከል ሥልጠና መውሰድ እና ማጥቃት ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢስገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንደ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004)፡፡

በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ አባላት አስተያየት መሰረት የዕድሜ አቻዎች ቡድን /ፌኢማ /faima/ ከተመሰረተ በኋላ ግጭትን በመቀስቀስም ሆነ በመከላለክል ረገድ ጉልህ ሚና አለው፡፡ ምክንያቱም ቡድኑ ከተመሰረተ እና ከተደራጀ በኋላ የሚሰጡት ኃላፊነቶች ግጭት ተኮሮች ናቸው፡፡ ይህንን ቡድን በተመለከተ ከውይይቱ የተረዳሁትን ሐሳብም እንደሚከተለው አሰፍራለሁ፡፡

በቅድሚያም የዕድሜ አቻዎቹ ቡድን /ፌኢማ/ ውስጣዊ የባህላዊ አስተዳደር ሕግ እና ሥርዓትን እንዲሁም ሰላም እና ደህንነትን በማስከበር ረገድ ያለውን ሚና እንመልከት፡፡

ይህ የዕድሜ አቻዎች ቡድን /ፌኢማ/ faima/ በመዋያው አካባቢ የተከሰቱ ውስጣዊ ጥፋቶችን ለጎሳ መሪዎቹ የማሳወቅ፤ የጎሳ መሪዎች እና ሽማግሌዎቹም በውስጣዊ ግጭት ዳኝነት እና አፈታት ወቅት በጥፋተኝነት የሚፈርጇቸውን ሰዎች መያዝ፣ በጥፋተኛ ሰዎች ላይ አካላዊ ቅጣት ሲጥሉ የመግረፍ እና ውኃ ውስጥ የመንከር፣ የጥፋተኞች እንስሳት በቅጣት መልክ እንዲታረዱ ሲወስን እና ተባርከው ሲሰጡት የማረድ እና የመበለት ተግባር ይፈፅማል፡፡ በጎሳዎች መካከል ግጭት ሲከሰትም የጎሳ መሪዎቹ በሚሰጡት ትዕዛዝ መሰረት ጥፋተኛውን ይዞ የሚያቀርበው ይኸው የዕድሜ አቻ ቡድን ነው፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ዋነኛው የኑሮ መሰረት የእንስሳት እርባታ እንደመሆኑም ለእንስሳቱ መኖ እና ውኃ የሚገኝበትን አካባቢ የማሰስ እንዲሁም ከአደጋ የመጠበቅ ኃላፊነት የሚጣልበትም ይኸው የዕድሜ እኩያሞች ወይም አቻዎች ቡድን /ፌኢማ/ faima/ ነው፡፡ ይህንንም የዕድሜ እኩያሞች ቡድን /ፌኢማ/ faima/ መመሥረት የወጣቶች ማህበራዊና ባህላዊ ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም የዕድሜ እርከን ተልዕኮና ግዳጅ ነው፡፡ ማህበራዊ ሥሪት ስለሆነም የማይስተሃቀር ልማዳዊ ደንብ ነው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ ሁሴን አህመድ፣ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004)፡፡

የዕድሜ እኩያሞች ቡድን /ፌኢማ/ faima/ ከየትውልድ ቤተሰቡ መንደር እና ከየኅሳው አካባቢ እንስሳቱን ውኃና ሣር ወደሚገኝበት አካባቢ ይዞ የሚነቃነቅ በመሆኑም አዲስ ከሚሰፍርበት አካባቢ ነዋሪ ወይም ያገባኛል ባይ ወገንም ጋር ፀብ የሚያፈራ ነው፡፡ ቡድኑ ፀብ ካፈራም የገባበትን ፀብና ግጭት በውጊያ አሸንፎ ይወጣ ዘንድ ይጠበቃል፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በተለይ በክፉ ቀን ማለትም ድርቅ ባየለበት፣ ግጦሽ በጠፋበት ወቅት በደጀንና በተነቃናቂ ቡድን ይከፈላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ቋሚው ሰፈር የራሱ አመራርና አደረጃጀት ሲኖረው ተነቃናቂውም እንዲሁ የራሱ አመራር ይኖረዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ አጋጣሚም የደጀኑ እና የቋሚው ክፍል ሁለት አመራሮች በመቀናጅት ይሰራሉ፡፡

የቋሚው ወይም የደጀኑ አባ ወራዎች አመራር ተነቃናቂው ወጣት የዕድሜ እኩያሞች /ፌኢማ/ faima/ ቡድን በተሰማራበት አካባቢ በጠላት የማይጠቃበትን፣ እንስሳቱን ሳያስዘርፍ መቆየት የሚችልበትን የስንቅና ትጥቅ አቅም ያጎለብታሉ፡፡

በተለይም አዲስ አካባቢን በማሰስ እና በማቅናት ረገድ ንቅናቄው የሚደረገው በሁለት ዓይነት ሁኔታ ነው፡፡ በፈለሳ እና ሰፈር ከፈላ፡፡

ፈለሳ የሚባለው ንቅናቄ አዲስ የተገኘው አካባቢ ከነባሩ መንደር ለቆ ለእንስሶቻቸው ምቹ፣ ለእነርሱም አሰፋፈር ተስማሚ እና ሰላማዊ ሆኖ ሲያገኙት ቤቶቻቸውን አፍርሰው፣ ሌላም ጓዛቸውን አደራጅተው እና በግመሎቻቸው ጭነው ወደ አዲሱ ቅኜት ሰፈር ሄደው ሲሰፍሩ ነው፡፡

ሰፈር ከፈላ ደግሞ በአሰሳ ያገኙት አካባቢ ረዘም ላለ ጊዜ መቆያነት የማይመች መስሎ ከታያቸው ለጊዜው የእንስሶቻቸውን የቀለብና የውኃ ጊዜያዊ ችግር ለመፍታት ነባር ሰፈራቸውን ጨርሰው ሳይለቁ፤ ነባሩን ሰፈር እንደ ደጀን ለሥንቅና ትጥቅ ቋትነት እየተጠቀሙ እንስሳቱን የሚጠብቀውን ኃይል አስታጥቀው የሚያሰማሩበት ነው፡፡

በሁለቱም ዓይነት ንቅናቄችም ወቅት በተቀዳሚ ኃይልነት የሚሰማሩትም በልማዱ መሰረት ከላይ የተገለፁት የዕድሜ እኩያሞች ወጣቶች ናቸው፡፡

ይህ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የወጣት ዕድሜ አቻዎች ቡድን ከሚጣልበት ኃላፊነት አንዱም በውጫዊ ጅምላ ግጭት ወቅት ግጭቱን በኃይል መቋቋም መቻል ነው፡፡ ይህም የዩዘመኑ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ታዳጊ ኃይል የጦረኝነት አቅም እና ጉልበት መለኪያ ነው፡፡ ለዚህም የሚያበቃ ባህላዊ ወታደራዊ ሥልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ባህላዊ የውትድርና ሥልጠናውም ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ቀናት የሚዘልቅ ነው፡፡ በሥልጠናው ላይ በትኩረት የሚነሱትም ነጥቦች አዲስ የሰፈራ አካባቢ መቃኘት፣ ራስን መከላከል እና የጦርነት ወቅት ሥነ ምግባር ናቸው፡፡

አዲስ የሰፈራ አካባቢ መቃኘት እና ማቅናት የሚባለው የአካባቢውን ለምነት፣ የባለይዞታዎችን መኖር አለመኖር፣ የባለይዞታዎችን አቅም ወዘተ መፈተሽ ነው፡፡

ራስን መከላከል የሚባለው ደግሞ የቡድን የጉዞ አደራረግ፣ ምሽግ አያያዝ እና አጠቃቅ ማለትም አተኳኮስ፣ አመራረክ፣ አሰላለብ፣ እንዲሁም በጦርነት ወቅት ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈፀም፣ ከሰው ጋር ሰላምታ አለመለዋወጥ ወዘተ ነው፡፡

የጦርነት ሥልጠናውንም የሚሰጡት በገዳይነታቸው "ማራ" ወይም "ዲጊፍሌ" /diigifilee/ በመባል የሚታወቁ እና በገደሉት ጠላት ብዛት ላይ የተመሰረተ ማዕረግ ያላቸው ጀግኖች ናቸው፡፡ ስለዚህም የዕድሜ እኩያሞቹ ሰልጣኞች ከአሰልጣኞቻቸው ማህበራዊ ደረጃ እና ክብር ለመድረስ ሲሉ በአሰልጣኞቻቸው የተሰጣቸውን ሥልጠና በፍላጎትና በጀብደኝነት ያከናውናሉ፡፡

ከዚህ በላይ በተገለጠው ሁኔታ ለግዳጅ ዝግጁ የሆነው ኃይል እንስሳቱን ይዞ ግጦሽና ውኃ ለማሰስ የሚንቀሳቀሰው ወጣት ቡድን የጦር መሣሪያ ትጥቅ ማለትም ጨቤ /ጊሌ/፣ አውቶማቲክ ጠመንጃዎችና ፈንጂዎች ሁሉ የሚሟሉለት በመሆኑ በሄደበት አቅጣጫ አቅም የሌላቸውን እየገፋ እንስሳቱን በሣራቸው እና በሰብላቸው ላይ ይለቃል፡፡ የውጊያ አቅም ያላቸው፣ አልገፋም ባይ ወገኖች ካጋጠሙትም ይዋጋል፡፡ በእንዲህ

ዓይነት ዘመቻው ተዋግቶ ድል ከቀናውም የድሉ ብሥራት እስከ ደጀኑ ክፍል እና የጎሳው አባላት እንዲሁም ሌሎች ሁሉ ይበሰራል፡፡ በገዳይነት ለታወቁትም ወጣቶች የጀግና አቀባበል ይደረጋል፡፡ የጦርነት ዘፈንም ይዘፈናል፣ ይጨፈራል፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የየመኖሪያ ሰፈሮቹ የዕድሜ እኩያሞች ቡድናዊ ኃይል በሥምሪቱ ወቅት የሚያጋጥመውን ጥቃት ሁሉ እየተከላከለ፣ በኋለኛውም ደጀን እየተደገፈ ለጊዜው በተንቀሳቀበት አካባቢ የሚገኘውን ሣርም ሰብልም ለእንስሳቱ ይመግባል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ውጫዊም ንቅናቄ ወቅትም እንደነርሰው ሁሉ የግጦሽና የውኃ ሀብት ፍለጋ ከሚሰማሩት ድንበርተኞቻቸው ቀወት ወረዳ ነዋሪዎች ጋር ግጭት ውስጥ የሚገቡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ቡድኑ የተቃናቃኙን ወገን ኃይል መቋቋም እስከቻለ ድረስም የእንስሳት መኖ ችግሩ እስከሚቃለልለት በአዲሱ አካባቢ ይቆያል፡፡ የተሻለ የእንስሳት መኖ በነባር ሰፈሩ ባገኘ ጊዜም ይመለሳል፡፡ ይህም ካልተሳካ ቀጣይ አሰሳውን ያካሂዳል፡፡ የአፋር የዕድሜ እኩያሞች ቡድን የተንቃነቀበት አካባቢ ተቀናቃኝ የሌለበት ወይም የደከመበት ከሆነም ተረጋግቶ በመስፈር የኋላ ደጀኑንም ያስጠጋል፡፡ በድርቁ ወቅት ኃይል በዝቶበት እና ተጠቅቶ ከቀወት ወረዳ ስምሪቱ የሚመለስ ከሆነም እንደገና በለምና በጥጋብ ዘመን ቂሙን የመወጣት ማህበራዊ ጫና ያለበት ይኸው ቡድን ነው (ቃለ መጠይቅ፡- ባላምባራስ አይዳሂሶ አሎ 05/09/2002፣ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ 08/09/2002፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ 10/09/2002)፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው የቁልፍ መረጃ ተባባሪዎቹ አስተያየት መረዳት እንደሚቻለው የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ተፈጥሮ የልምላሜ በረከቷን ስትሰጥ በየሰፈሩበት አካባቢ ተረጋግተው ይኖራሉ፡፡ ተፈጥሮ ልምላሜዋን ስትነፍጋቸው ደግሞ ለእንስሳቶቻቸው ምቹ ሥፍራ ፍለጋ ውስጣዊና ውጫዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡ በድርቅም ሆነ በልምላሜ ዘመንም ደግሞ ከድንበርተኞቻቸው ቀወቶች ጋር ግጭት ያፈራሉ፡፡ ምክንያቱም በድርቅ ወቅት በተከሰተው ግጭት ሳቢያ ሽንፈት ከደረሰባቸው ቂም ቋጥረው ይቆያሉ፡፡ በድርቁ ወቅት የደረሳባቸውንና የቋጠሩትንም ቂም ለመወጣት የጥጋብ ዘመንን ይጠብቃሉ፡፡ በጥጋብ ዘመንም የቆየ ቂማቸውን ለመወጣትና ለመበቀል ይነሳሉ፡፡ በግጭትም ሂደት ወንድነትን ያገኛሉ፣ የተገኘውንም ወንድነት ለወገናቸው ይናኛሉ፡፡

የአንድ ሕዝብ ወይም ኅብረተሰብ መኖሪያ አካባቢ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና በመልክዓ ምድሩ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ ነዋሪዎቹ በሰላምም ሆነ በግጭት

ድባብ ውስጥ እንዲኖሩ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ገፀ-ምድሩ ለሰውና ለእንስሳት ኑሮ ምቹ የሆነ፣ የተፈጥሮ ሀብት ልምላሜና እርጥበት ያለው፣ ነዋሪውን መሸከም የሚችል የቆዳ ስፋት ያለው ከሆነ ቢያንስ በተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ ማለትም በእርሻ ማሳ፣ በድንበር፣ በውኃ፣ በግጦሽ፣ በደን ሀብት ምክንያት ሊቀሰቀሱ የሚችሉ የርስበርስና ውጫዊ ግጭቶችን ለመቀነስ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል፡፡

በአንፃሩ ገፀ-ምድሩ ከላይ የተጠቀሱትን ፀጋዎች ያልታደለ፣ ታድሎም ከፍተኛ እጥረት ማለትም የሕዝቡና የመሬቱ ስፋትና የመሸከም፣ የመመገብ ምጣኔ ያልተስተካከለ ከሆነ ደግሞ ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶች እንዲባባሱ የሚያበረክተው አሉታዊ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የተፈጥሮ ሀብት እጥረትና ሽሚያ ሕዝብን ለዘወትር ንቅናቄና ስደትም ሊዳርግ ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት በድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አራሽ ነዋሪዎች እና በሰሜ-ሮቢ ገለአሉ ተጎራባች አርብቶ አደሮች መካከል የሚታየው የማያቋርጥ ግጭት እና የግጭት ድግግሞሽ አንድ ምክንያትም ከዚህ በላይ ከተወሳው ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሚዛን ደፍቶ መናገር ይቻላል፡፡

የሁለቱን ሕዝቦች ማህበራዊ አደረጃጀትም ስንመለከት ቀወቶች ማህበራዊ ትስስራቸውን የሚመሰርቱት በሰባት ቤት ትውልድ ቆጠራ፣ በጋብቻ፣ በጡት ልጅ፣ አበ ልጅ፣ ሰንበቴ፣ ዕድር እና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያንት /አማራነት/ መሆኑን፤ ሰሙ-ሮቢ ገለአሉዎች ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን የሚመሰርቱት ከቀወቶች ሰፋ ባለ በጎሳ ቆጠራ እና ሰፈራ አንድነት፣ አፋርነት እና እስላምነት እንደሆነም አይተናል፡፡ በዚህም ረገድ ሲታዩ ሁለቱም ሕዝቦች በየፊናቸው ጠንካራ ቡድን እና እኔነት እና እኛነት አላቸው፡፡ ይህ እኔነት እና እኛነት ደግሞ ሁለቱን ሕዝቦች በየራሳቸው የተለዩ ሕዝቦችነታቸውን እንዲያጠነክሩ፣ እንዲገላለሉ እና እንዲቧደኑም ሳያደርጋቸው እንዳልቀረ እና ተገዳዳሪነትን ወይም አቻዊነትንም ሳይፈጥር እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡

# 5. የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፌ ታሪክ

በዚህ ምዕራፍ የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፌ-ታሪክ እንዴትና እንደምን እንደሚገለፅ ለመቃኘት ይሞከራል፡፡

የሁለቱን ሕዝቦች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፌ-ታሪክ መዳሰስ እና ማካተት ያስፈለገውም አፋዊ ታሪካቸው እና ተረካቸው በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ግጭትን በመትከል፣ በማህዘብ እና በማራገብ ረገድ የነበረውን እና የሚኖረውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አበርክቶ ለማስተዋልና ለመመርመር ነው፡፡

በዓለማችን የጽሑፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት የነበረው ታሪክ ሁሉ ቃል-ታሪክ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡

ቃል-ታሪክ ጽሑፋዊ ታሪክ ከመጀመሩ በፊት በዋነኛነት በኋላም በተጓዳኝነት የአንድን ሕዝብ ጥንተ አመጣጥ፣ ማንነት፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የፈጠረውን ግንኙነት፣ ያዳበረውን እሴት፣ ያጋጠሙትን ክስተቶች፣ ሁነቶች፣ ድርጊቶች እየሰነደ ከትውልድ ወደ ትውልድም የመረጃ ማስተላለፊያ ሆኖ አገልግሏል፣ በማገልገልም ላይ ነው፡፡ እንደዚህም በመሆኑ ፊደል ያልቀጠሩት እና ሀገረሰባዊ ሕይወት የሚመሩት ድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ስለየራሳቸው ማንነትና አመጣጥ ያላቸውን ቃል ታሪክ እዚህ በውስኑም ቢሆን ለማካተት ተሞክሯል፡፡ ይኸውም የተደረገበት ምክንያት Dan-Ben-Amos እደሚያወሱት ትልቆ ትውልዶች /genealogies/ እና አፌ-ታሪኮችም የኅብረተሰብ መረጋጋት ለማጠናከር ስለሚያገልግሉ፣ የእያንዳንዱ ኅብረተሰብ ውስጣዊ መጠናከር ደግሞ ትዕምርተ-ፖለቲካዊ ኃይል እና ታሪካዊ እውነት መግለጫ እና ማዛመቻ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡

ይኸውም የተደረገው ለድንበርተኞቹ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭት ሁኔታ ፍንጭ እንደሚሰጥ በማመን ነው፡፡ ፎክሎርም ከቃል ታሪክ የማህበረሰቦችን ተረክ፣ ተለምዶ፣ ሥርዓተ-ሕይወት፣ ወግ ልማድ በመመልከት መረጃ ያገኝበታል፣ ይጠቀምበታልምና ነው፡፡ እዚህም እንዲሁ፡፡

በመጀመሪያም የቀወት ወረዳ ነዋሪዎችን ማንነት የሚመለከተውን አፈ-ታሪካዊ ገለፃ እንመልከት፡፡

## 5.1. የቀወት ወረዳ አማሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፈ ታሪክ

የቀወት ወረዳ አማሮች /በነገራችን ላይ ቀወቶች አማራ ሲሉ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ማለታቸው ነው/ ከአፈ-ታሪክ አኳያ ጥንታዊ አመጣጣቸውን የሚያይዙት ከክርስቲያናዊው መንግሥት መስፋፋት ጋር እያቆራኙ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ዛሬ ወደሚገኙበት አካባቢ የመጡት በክርስቲያናዊው መንግሥት ሥር ከነበረው ከመንዝ እንደሆነ ይተርካሉ፡፡ ዝርዮቻቸው ከመንዝ ወደ ቀወት የወረዱትም የእስላም እና እስልምናን መስፋፋት ለመከላከል ሲባል እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ በተለይ አቶ ከበደ መንገሻ ተቀድመው ያጫወቱኝን እና የተተኳሪ የቡድን ውይይቱ አባላቱ እነ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ (24/01/2004) ያረጋገጡልኝን አፈ-ታሪክ የአተራረክ ቅደም ተከተሉን እና ፍሬ ሐሳቡን ይገፍ እንደሚከተለው ዘግቤዋለሁ፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የተተኳሪ ቡድኑ አባላት እንደተስማሙበት የይፋት አማራ የጥንት ዝርያ የመጣው ከመንዝ ሲሆን ጥንት አማራ ይፋትን መንዝ አፋፍ ላይ ሆኖ ቁልቁል እያየው፣ ለመኖሪያነት ሳይደፍረው ይኖር ነበርም ይባላል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ መንዝ ደጋ እና ወይና ደጋ ስለሆነ፣ ደገኛው ሕዝብ ለውሎ ገባ ጉዳይ ለአውሬ አደን፣ ለአረህ ማለትም ለቤት እና ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ምሰሶ እና ወራጅ ለሚሆን ለወይራ፣ ለጥድ፣ ለዝግባ፣ ለቀረሮ፣ ለክትክታ እንጨት ቆረጣ፣ ለማገዶ እንጨት ሰበራ እና ለሞፈር ቀንበር፣ ወረድ ብሎ ዋል አደር ያለ እንደሆን ንዳዱና ተውሳኩ ወዲያው ጠብ ያደርገው ስለነበር እንደሆነም ይወሳል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ አባላት አያቶቻችን እና አባቶቻችን ሲጫወቱ እንሰማ እንደነበረው እያሉ እንደሚተርኩትም በኋላ ላይ መንዝ የሰሎሞናዊው መንግሥት ማረፊያ እንደመሆኑ ሠራዊቱ እየበዛ፣ መሬቱ እየጠበበ፣ መንግሥቱ እየደረጀ፣ ግዛቱ እየሰፋ ሲሄድ፣ የእስላም ኃይልም እያጋጠመው እና እያየለበት ሲሄድ መንግሥቱ ሕዝቡንም በግዳጅ ወደ ይፋት ምድር እያወረደ፣ ደን እያስመነጠረ፣ ቀፎ እያስደረገ፣ ፍየልና በግ እያስረባ፣ ከብት እያስደረጀ፣ እርሻ እያሳረሰ፣ ሠራዊት እያደራጀ እና መለያ

ሥያሜም እየሰጠ (ከሰማኒቸው የምድብ ጦር ሥያሜዎች መካከልም አፍሮ አይገባ፣ የአዳል መብረቅ ወዘተ የሚሰኙ ናቸው) አካባቢውንም ከእስላም ወረራ እየተከላከለ እንዲኖር አስገደደው፡፡ ከሰፋሪውም ያለቀው እያለቀ፣ ቀሪው ቀስ በቀስ አካባቢውን እየተጣወረው (እየለመደው ለማለት ነው)፣ ንዳዱንም እየተቋቋመው መኖር ጀመረ፡፡ መንግሥቱም ሰፊ ግብር ማግኘት ጀመረ፡፡ አገሩም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ቀንቶ ለማ ነው የሚባለው እየተባለ ይወጋል ይላሉ የተተኳሪ ቡድን አባላቱ፡፡ ከብዙ ዘመናት የሰላም እና የጦርነት ግንኙነት በኋላ ግን እስላሞች ጠንክረው ግራኝ አህመድ የሚባል የእስላም መሪ በአፋሮች እና በሶማሌዎች እንዲሁም በሌሎችም እስላሞች እየተረዳ አማራውን ወደ ላይ ወደ ላሊማ ወደ ገፊገፉ ጥግ ገፋው፡፡ የእስላሙም ጦር የአማራውን ንጉሥ እያሳደደ ወደ ሰሜን ዘልቋል፡፡ በሂደቱም ተባራሪው በተፈጥሮ፣ አባራሪው በጦርነት እዚያው ቀርተዋል፡፡ ይሄም ሁሉ በሚሆንበት ወቅት አማራው በእስላሙ እየተገፋ ለብዙ ዓመታት በሸንተረራማው እና ገደላገደሉ የመንዝ መዳረሻ አካባቢ ይኖር ነበር ይባላል፡፡ ቆይቶ ደግሞ አማራው እንደገና ተመልሶ ወደ ነባር ይዞታው መውረድ የጀመረው የሸዋ ሰለሞናዊ ዘር የሆነው የልብነ ድንግል ልጅ ያዕቆብ የሚባለው "አለሁ፣ አገር አውላለሁ" ብሎ ከተነሳ በኋላ ነው ይባላል፡፡ እንደሚተረከውም የያዕቆብ አነሳሥ እንዲህ ነው፡፡ የያዕቆብ አባት ዐፄ ልብነ ድንግል ከእስላም ጦር ጋር እየተዋጋ ወደ ሰሜን ሲያፈገፍግ ያዕቆብ መንዝ ውስጥ ተሰውሮ እየኖረ እነ ገራም ፋሲልን፣ ሥግወ ቃልን ያፈራል፡፡ በዚህ መልኩ ንጉሣዊ ዝርያው መንዝ ላይ እግር ስለተከለ እና ስለተራባም የሥግወ ቃል ተወላጆች እነ አቤቶ ወረደ ቃል፣ ልብሰ ቃል፣ አቤቶ ነጋሢ ቀስ በቀስ ኃይል እያደረጁ፣ ሙሉውን መንዝ እና ክርስቲያን አጎራባቾቻቸውን አስተባብረው አማራው በእስላሞች ተቀምቶ የነበረውን የይፋት ምድር መልሰው ለመያዝ በመቻላቸው ነው (አቶ ከበደ መንገሻ ፣ 24/01/2004) ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበውን አፈ-ታሪክ ላወጉኝ አቶ ከበደ መንገሻ እና ላረጋገጡልኝም የተተኳሪ ቡድኑ አባላት እነ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መኪታ (24/01/2004) አንድ ሌላ ጥያቄም ሰንዝሬላቸው ነበር፡፡ ለመሆኑ "የመንዝ አማራ ከየት መጣ ይባላል?" የሚል፡፡

ከተተኳሪ ቡድኑ አባላት መካከል አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ ቀደም ብለው "መንዝማ ከጥንትም አማራ ነው ይባላል፡፡ እንደሚወጋው ከሆነ መንዝ ጥንት ከአክሱም፣ ከአገው፣

ከበጌ ምድር፣ ከወልቃይት፣ ከቤተ አምሓራ፣ ከአማራ ሳይንት፣ ከቦረና ተውጣጥቶ የመጣ፣ የሸዋ እና የይፋት አቅኚና መሥራች ወታደር ነው እኮ ነው የሚባለው" አሉ። አቶ ከበደም በቀረበው አፈ-ታሪክ ላይ የራሳቸውን ተጨማሪ አስተያየት ሰንዝረው ነበር። አስተያየታቸውን ወስጄ እንደሚከተለው አስፍሬዋለሁ።

በአቶ ከበደ አተራረክ መሰረት መንዝ ጥንትም አማራ ማለትም ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ነበር። መንዝ ከአክሱም እነ አንበሳ ውድም፣ እነ ድልነዓድ አረማውያን ሲያሳድዷቸው ሸሽተው የገቡበት እና የተሸሸጉበትም አገር ነው። ዋነቹም በዘመናቸው መጥተው ለማስገበር የሰፈሩበት አገር ነው። እንዲያውም መንዝ ውስጥ ኮረብታውም፣ የእርሻ መሬቱም በአቅኚዎቹ እና በሰፋሪዎቹ ጦር ሥም የሚጠራ ነው። እነ የአፋር መብረቅ፣ አፍሮ አይገባ፣ ቁርባን ወዘተ የሚባሉ ጎጦች መጠሪያ ወይም መለያ ሥሞች የጦር ሥሞች ናቸው። እንደገናም ማማ፣ ላሎ፣ ጌራ ወዘተ የሚባሉትም ከደቡብ ወደ ሰሜን የተስፋፉት ኦሮሞዎች የጦር መሪዎች እና "አቅኚዎች" ሥሞች ናቸው። እነ ፋሲል አምባ፣ ራስ አምባ ደግሞ በገገርዎቹ የተፀውዖ ሥም እና ማዕረግ እንደተሰየሙ ቀርተዋል። ስለዚህም አካባቢው ብዙ ማህበረሰቦች የነበሩበት በሂደትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖትን አጠንክረው የያዙበት ስለመሆኑ ከጥንት ጀምሮ ይወጋ ነበር ብለዋል። በኋላ ደግሞ በእስላም ወረራ ምክንያት ከሸዋ ወደ ሰሜን አፈግፍጎ የነበረው እና ጎንደር ላይ መደርጀት ጀምሮ የነበረው ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ተመልሶ የመጣበት እና እግር የተከለበት፣ የደረጀበትም ነው። አቶ ከፈለኝ ድረሴ ደግሞ "አዬ አንዱ ሲናገር ያፈዝ፣ ሌላው ሲናገር ያደነዝዝ ብጤ ነው። አሁን ሁለታችሁም ያላችሁት ሁሉ ይወጋል። ነገሩን እንደ ተረት እየሰማን ነው የኖርነው" የሚል መደምደሚያ ሐሳብ ሰነዘሩ።

ሌላው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ አቶ ከተማ አይሻር ደግሞ "ይሄ የሰው ዘር ታሪክ ብዙ ውጥንቅጥ ያለው ነው። አማራ የሚባለው እኮ ክርስትናን የተቀበለ ሁሉ እንጂ የአንድ ዘር መለያ አይደለም።" በማለታቸው ሁሉም እንደገና "እርሱማ እርግጥ ነው። ምን ጥርጥር አለው" ሲሉ ደመደሙ።

ከቀወት ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ መካከል አንዳንዶቹ ዝርዮቻቸው ከመንዝ ወደ አካባቢው የዘለቁበትን ዘመንም ጥንት፣ ዱሮ እያሉ ነው የሚገልፁት። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአንድ ሺ ዓመታት በፊት እያሉ ከአክሱም ሥርወ መንግሥት ዘመነ መንግሥታት ጋር እና ከሰባት መቶ ዓመታ በፊት እያሉ ከሸዋ ሥርወ መንግሥት

መመስረት ጋር ያይዙታል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡ እዚህ የተጠቀሱት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች ስለ አፈ ታሪኩ ካወጉኝ መካከል የአንዱን የአቶ ከበደ መንገሻን (24/01/2004) አገላለፅ በአብነት አስፍራለሁ፡፡

ከአፈ-ታሪኩ መረዳት እንደሚቻለው ቀወቶች ዛሬ ለሚገኙበት እና ለሰፈሩበት አካባቢ ከአንዴም ሁለት ጊዜ መጤዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ በመሬት ጥበትም፣ በእስላም ኃይል ተከላካይነትም ወደ አካባቢው ዘልቀዋል፡፡ ቀጥሎም በእስላም ኃይል ተገፍተው የለቀቁትን ሥፍራ እንደገና የሸዋው ክርስቲያናዊ መንግሥት ጉልበት ሲያገግም እና ሲያገኝ መልሰው ይዘዋል፡፡ ይሄም ቀጥሎ እንደምናየው ግንኙነታቸውን ፀበኝነት ያየለበት ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ ቀወቶች ከአጎራባቾቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት ሁኔታ የሚተርኩትን አፈ ታሪክ እንመለከታለን፡፡

ቀወቶች እንደሚሉት ከሚያጎራብቷቸው አርጎባዎች፣ አፋሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች ጋር "በዘር በኃይማኖት አንገኛኝም" ይላሉ፡፡ ስለዚህም ከአርጎባዎች፣ አፋሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች መካከል በአሁኑ ወቅት ከእነርሱ አማሮች ጋር ግጭት ውስጥ የማይገባው እና በተቃናቀኝነት ስሙ ጎልቶ የማይነሳው አርጎባ ብቻ ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚናገሩት ሌሎቹ በተለያዬ ሁኔታ ፀበኞች እና የፀቡም ሰለባዎች ናቸው፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደሚተርኩት ከአርጎባዎች ጋር እንደሌሎቹ ማለትም አፋሮችና ጅሌዎች አዘውትረው የማይጋጩበትንም ምክንያት የሚያስረዱት በአፈ-ታሪክ ማጣቀሻ ነው፡፡ በአፈ ታሪካዊ ማጣቀሻ ተረኩ መሰረትም ምንም እንኳን አርጎባዎች፣ አፋሮች፣ ከረዩዎችና ጅሌዎች በጥንቱ ዘመን የክርስቲያን መንግሥትና ክርስትናን በጋራ ለመመከት እና ለመቋቋም በተለያዩ ጊዜያቶች የተለያዩ የተቋቁሞ ውጊያዎችን ቢያደርጉም ኋላ ላይ የአርጎባዎች መሪ የነበሩት እና ጉልቆ ትውልዳቸውን ከወላስማ ሥርወ መንግሥት ገገር ቤተሰቦች ይስቡ ነበር የሚባልላቸው በተፀውዖ ሥማቸው መሐመድ ይባሉ የነበሩት አንድ ወቅት ላይ ከክርስቲያን መንግሥታት ጋር ስምምነት በመፍጠራቸው ምክንያት ከአፋሮች ጋር ተባብረው አማሮችን ለመውጋት ፈቃደኛ ስላልነበሩ ሰልፍ ቀይረው የኃይማኖት ወገኖቻቸውን ተፋልመዋል እየተባለ ይተረካል (ይህን የወላስማዎችን ሰልፍ ቅያሬ ሁኔታ ኋላ ላይ፣ ዝቅ ብዬ አመጣዋለሁ)፡፡ ከዚያ

ፍልሚያ በኋላም በተለይም አፋሮችን ወደታች ወደመጡበት አውሳ በረሃ ገፍተዋል፡፡ አርጎባዎች በእንዲህ ዓይነት መንገድ ከክርስቲያኖች ጋር በመተባባራቸውም በክርስቲያኖቹ እና እስላሞቹ አርጎባዎች መካከል መልካም ግንኙነት ሊመሰረት ችሏል፡፡ መልካም ግንኙነቱ ከተተከለ በኋላም ከአርጎባዎች ጋር የከፋ ቅራኔ እና ግጭት እንዳልተከሰተ ይነገራል፡፡ ዛሬም ቢሆን አማሮች እና አርጎባዎች አይጋጩም፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ ይህ የሆነበትን ዘመን በውል ባይጠቅሱትም ከግራኝ በኋላ እንደሆነ ግን ይገምታሉ፡፡ በተለምዶ ግራኝ የሚባሉትም በጽሑፍ ታሪክ አህመድ ቤን* (ታሪክ ጸሐፊዎች አንዳንድ ጊዜ ኢብንም ይሏቸዋል) ኢብራሂም የተባሉት እና የአፄ ልብነ ድንግልን ሰራዊት 1521-1535 ዓ.ም. ድረስ ድል በመምታት አብዛኛውን የአገሪቱን ክፍል ተቆጣጥረው የነበሩት መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በአፊ ታሪኩ መሰረት በቀወት አማሮች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች መካከል ዘመን ያላደበዘዘው፣ ሥርዓት ያልቀየረው፣ ታሪካዊና ነባራዊ የግጭት ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው በተረኩም፣ በድንበር መጋራቱም፣ መገፋፋቱም በጥቅሉም የተጠቃሚነት ፍላጎት ባስከተሉት ችግር እንዲሁም በማንነት አማራ /ክርስቲያን/ እና እስላም በመሆናቸው ነው፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደሚተርኩትም የግጭቱ ታሪክ የሚጀምረው አፋሮች በመጀመሪያ ከሰፈሩበት እና ሱልጣኔት ከመሰረቱበት የአውሳ በረሃ አዋሽን እየተከተሉና የወንዙንም ለምነት እየተጠቀሙ፣ በጥቅሙም እየተሳቡ ወደ ገፈገፉ ጥግ በመምጣታቸው ነው፡፡ ቀወቶች ገፈገፍ ጥግ የሚሉት ምዕራብ እና ምሥራቅ ኢትዮጵያን ከሰሜን እስከ ደቡብ የሚያካፍለውን የበልግም፣ የመኸርም ዝናብ የማያጣውን ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋውን፣ የኢትዮጵያ ምዕራባዊ እና ምሥራቃዊ ተፋሰስ መለያ የተራራ ሰንሰለት ነው፡፡ እናም አረጋውያኑ እንደሚያወሱት አፋሮች ግመሎቻቸው መሄድ እስከቻሉበት በመንቀሳቀስ እስከ ገፈግፍ ጥግ ሲቃረቡ ከደጋ ወደ ቆላ የሚፈሱትን ወንዞች እየተከተሉ የእርሻ ሥራ ከሚያከናውነኑት የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች ጋር ሊፋጠጡ ችለዋል፡፡ በዚህም ሳቢያ ሁለቱም ሕዝቦች የያዙትን አካባቢ ለማስጠበቅ ሲሉ በማያባራ ግጭት እና መበቃቀል ውስጥ ገብተዋል (የቀወት ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

ከተተኳሪ ቡድን አባላቱ የጋራ ውይይት እንደተረዳሁት የሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት በአጠቃላይ ከደጋ ወደ ምሥራቅ እየፈሰሱ መዳረሻቸውን በአፋር ምድር በሚያደርጉ ወንዞች ዙሪያ እንደተጀመረ እና ግንኙነትም በሀብት ተሻምቶ ምክንያት መሻከር እንደተጀመረና እንደቀጠለም መገመት ይቻላል፡፡

ስለዚህም አማሮችን እና አፋሮችን የደለል ማረፊያ የሆነው እና ለምነት ያለው አፈር እና ግጦሽ ሣር አካባቢ ይገባኛል ባይነት እና ተቆጣጣሪነት ፍላጎት በአጭሩም የጥቅም ተጋርቶና ሽሚያ አገናኝቷቸዋል፣ አስተዋውቋቸዋል፡፡ ለማያባራ ግጭትም ዳርጓቸዋል፡፡ ይሄ እንግዲህ ገፀ-ምድራዊ ተያያዥነትና ትይዩነት እንዲሁም ገፀ-ምድራዊ ሀብት ትስስርና ግንኙነት የፈጠረው ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በመረጃ ተባባሪዎቼ አፈ ታሪክ መሰረት ደግሞ ሁለተኛው የቀወቶች እና ሰሙሮቢ ገለአሎዎች ግጭት መንሥዔ የኃይማኖት ልዩነት ነው፡፡ ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች የክርስትና እና እስልምና ኃይማኖት ተከታይ መሆናቸው፡፡ ቀወቶች እራሳቸውን "አማራ" የሚሉትም ዛሬ በብሔርነት የምናውቀውን አማራ ሳይሆን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ለማለት ነው፡፡

በቀወት አማሮች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች መካከል በኃይማኖት ልዩነት ምክንያት ታሪካዊ ግጭት አለ የሚሉት የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት እንደሚተርኩት በቀወት ወረዳ እና አካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ አንድ የግንኙነትን መበላሸት፣ የፀበኝነትን መካረር የሚጠቁም እጅግ የተለመደ ብሂል አለ፡፡ "አማራና እስላም ነን፣ ሆነናል፣ ሆነዋል፣ እንሆናለን፡፡" የሚል፡፡ ስለዚህም ቀወቶች "እኔና እከሌ ከእንግዲህ አማራና እስላም ነን፣ ሆነናል፣ እከሌና እከሌም አማራና እስላም ናቸው፣ ሆነዋል" የሚሉት የግንኙነትን መበላሸት እና አይጠገኔነት ለመግለፅ ነው፡፡ ቀወቶች ይህንንም አባባል የሚጠቀሙት የእርስበርስ እንዲሁም ከአርጎባዎች፣ አፋሮች፣ ከረዩዎች፣ ጅሌዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የሻከረ ሲሆን ነው፡፡

ለመረጃ ተባባሪዎቼ ከዚህ በላይ በቀረበው በአካባቢው አነጋገር ላይ በመመሥረትም ለመሆኑ "አማራና እስላምነት" ምንድነው? የሚል ጥያቄ ሰንዝሬላቸው ምንጊዜም የማይጣጣም፣ የማይስማማ፣ ፀበኛ፣ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እና እስላም መሆን ማለት እንደሆነ አውግተውኛል፡፡ ይህንን አባባላቸውን ለማስተማመንም ወደ ኋላ እየሄዱ በክርስቲያኖች እና በእስላሞች መካከል የተካሄዱ የግጭትና የጦርነት ክስተቶችን በዐፄ እከሌ ዘመን፣ በጋሙድ ረሃብ ዘመን፣ በዱባለች የረሃብ ዘመን፣ እህል

ዱር ባደረበት፣ በጣሊያን ወረራ፣ በእንቅጥቅጥ (ርዕደ ምድር መሆኑ ነው) ዘመን ወዘተ እያሉ በእነርሱ እና በድንበርተኞቻቸው አፋሮች መካከል የነበረውን መጎሻመጥ እና ጦርነት ይተርካሉ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ከቀወት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ አባባል የምንረዳው አማራና እስላም መሆን ማለት ኦርቶዶክስ እና እስላም መሆን ማለት መሆኑን ነው፡፡ ኦርቶዶክስና እስላም ማለት ደግሞ ሁለት የተለያዩ ኃይማኖቶች፣ የተለያዩ ቀኖናዎች እና ሥርዓተ አምልኮዎች እና ሥርዓተ ከበራዎች ያሏቸው እንደመሆናቸው ልዩነታቸው የማይታረቅ ነው የሚል አንደምታ ይሰጠናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱም አባባል ከፍተኛ የግንኙነት መቋረጥና የፀበኝነት መግለጫ ነው፡፡

እዚህ ላይ ቁም ነገሩ "አማራና እስላምነት" የሚለው አባባል ከምን የሕይወት ልምድ መነጨ? የሚለው ነው፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እና የአካባቢውም ነዋሪዎች እንደሚሉት ምንጊዜም በእነርሱ አካባቢ ጦርነት የሚመጣው ከበስተምሥራቅ (ከአፋር እና ከጅሌ ኦሮሞዎች) በኩል ነው፡፡ ስለዚህም ዘወትር "ከምሥራቅ ተጠንቀቅ" ብለን ነው የምንኖረው ይላሉ፡፡ ይህ ስሜት እንዴት እንደተፈጠረባቸው እና እንዳደገባቸውም ሲጠየቁ አፋሮች ከጥንት ጀምሮ አማራን ለማስለም ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በየጦርነት አውድማው ላይ ያገኙትንም ሙትና ቁስለኛ እየሰለቡ ሲዘፍኑበት እና ማዕረግ ሲያገኙበት ኖረዋል፡፡ ዛሬም የሚሰልቡን እንደ ጥንቱ ባህላቸው ሊጨፍሩበት እና ገዳይ ተብለውም ጆሮ አውጥተው ሊዳሩበት ነው ይላሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ስጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

የቀወት ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደሚሉት አፋሮች በአሸነፉት አካባቢ ያገኙትን ሴት እና ልጅ ሳይቀር እየነዱ ባህር አሻግረው ባሪያ እያሉ ሲቸበችቡ ኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የክርስቲያን ነገሥታትን እና ሠራዊት የክርስቲያንን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ ሲሉ ከአፋሮች ጋር ለዘመናት ደም ሲፋሰሱ ኖረዋል፡፡ በይፋት ምድር ላይ ከአፋር ሱልጣኖች እና አሚሮች ጋር ሳይዋጋ እና መስዋዕትነት ሳይከፍል ያለፈ የጥንት ንጉሥ የለም፡፡

እንደ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ አባባል በተለይ ግራኝ አህመድ አማሮችን በኃይል አስልመዋል፣ ቤተክርስቲያናትን ዘርፈዋል፣ የወርቅ ዕላት፣ የወርቅ አልባሳትን ሁሉ ባህር እያሻገሩም ሲሸጡ ኖረዋል፡፡

ተረክ ያለ አንዳች ምክንያት አይፈጠርም፣ አይተረክምም፡፡ ስለዚህም "አማራና እስላም" የሚለው አባባልም የመጣው በቀድሞው ዘመን በአካባቢው የነበሩት የክርስትና እና የስልምና ተከታዮች የሆኑ መሪዎች ለረጅም ዘመን ካደረጉት ግጭት እና ጦርነት የተነሳ ሳይሆን እንደማይቀር በእርግጠኝነት መገመት ይቻላል፡፡ ይኸውም የተደረገው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያጋጫቸው ኃይሎች በየፊናቸው ተከታይ ለማፍራት ኢኮኖሚያዊ ግጭቱ በውል የማይታያቸውን እና የማይረዳቸውን ዘገሮቻቸውን በቀላሉ በሚታያቸው ኃይማኖት ልዩነት እና ግጭት ዙሪያ ለማሰለፍ እንዲቻላቸው በሽፋንነት ስለተጠቀሙበት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በዘመናችንም ከእውነተኛ የግጭት መንሥዔዎች እና አመክንዮ ይልቅ ለስሜት ቅርብ የሆኑ፣ የዋሃንን በቀላሉ ሊያነሳሱ የሚችሉ ሽፋናዊ የግጭት መንሥዔዎችን ማራገብ እንደቀጠለ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ሲወርድ ሲዋረድ እንደሰማነው እያሉ እንደሚተርኩት የአካባቢው ክርስቲያኖችና እስላሞች አንዳቸው በሌላኛቸው ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት ያካሄዱት የነበረው የተራዘመ ጦርነት እጅጉን የከፋ እና አሰልቺም ነበር፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ "እንደ ተአምር" እንደሚተርኩትም የዚያን ዘመን ሰው የተለየ ጉልበትና ወኔ ነበረው ይላሉ፡፡ እንደምን ሲባሉም በዚያ ዘመን ጦርነቱ ባመዛኙ ይካሄድ የነበረው በፈረስ ሲሆን የብዙዎቹም ተዋጊዎች የጦር መሣሪያቸው ጦር፣ጋሻና ጎራዴ ነበር፡፡ እናም የጨበጣ ውጊያ ይደረጋል፡፡ አንገት ይቆረጣል፡፡ ዘማችም ስለ ጦርነቱ ውሎ ለአዝማቹ መረጃ የሚያቀርበው በፉከራና በጭንቅላት ቸብቸቦ ነበር ይላሉ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ የጭንቅላት ቸብቸቦ የሚሉትም የተቆረጡ ጭንቅላቶችን በገዳይ ስለባነት እያቀረቡ መከመርን ነው፡፡ የዘመኑ ተዋጊ የቸብቸቦ ምርኮውን ዕረፍት በተደረገበት አደባባይ ላደረለት ጌታው በሚያቀርብበበት ወቅትም ለአሳዳሪው ታማኝነቱን፣ ተዋግቶ አሸናፊነቱን በሽለላና ፉከራ ይገልፅ እንደነበር ይወጋል፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ ፣አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እና ሌሎችም የቀወት ሰዎች እንደሚተርኩት አማሮቹ ከአፋሮች፣ ከጅሌዎች፣ ከከረዩዎች እና ከአርጎባዎች[12] ጋር ሥር የሰደደ የግጭትና የደመኝነት ታሪክ ነበራቸው። በአጭሩም ከሁሉም የአካባቢው እስላማዊ ኃይሎች ከይፋት ወላስማዎች፣ ከአፋር ሱልጣኔቶች እና በሁለቱ ሥር ወቅት እና ጊዜ እየለዩ ሰልፋቸውን ከሚያስተካክሉት ሌሎችም እስላሞች ጋር ሰላም አልነበራቸውም፣ የላቸውም። ዛሬም ቢሆን አማሮቹ ከአርጎባ በስተቀር ከሌሎቹ ጋር ጀርባ እሚያስጥል ሰላም የላቸውም። ለዚህም ምክንያቱን ሲጠየቁ የሚያነሱት አፋሮች ከታች ከአውሳ በረሃ ወጥተው አዋሽ ወንዝን ተሻግረው የመጡት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳን ጨምሮ ዛሬ የሰፈሩበትን ቦታ ሁሉ የያዙት በግራኝ ወረራ ጊዜ በመሆኑ ነው ይላሉ። የዚህንም አፈ-ታሪክ እውነትነት ለማንጠር ሞክሬያለሁ። እናም በአፈ ታሪኩ ውስጥ ያገኘሁት ሕፀፅ የዘመን ብቻ ነው። ነገሩም እንዲህ ነው።

አፄ ኢያሱ (1682-1700) ከጎንደር ተነስተው በሸዋ እና በጎንደር መካከል፣ በወሎ እና በቱለማ ሰፋሪዎች የተያዙ መሬቶችን በድብቅ አቋርጠው ሸዋ ይገባሉ። ሸዋ እንደገቡም በሸዋ አምባዎች ላይ በእስላሞች እና በኦሮሞዎች ተከበው እና ተቆርጠው የቀሩትን እና በውስጥ የመሬት እና የሥልጣን ሽኩቻ ተጠምደው የነበሩትን አማሮች /ክርስቲያኖች/ ባላባቶች ሰብስበው ውስጣዊ ግጭታቸውን አቁመው እና ግንባር ፈጥረው በኅብረት በቱለማ፣ በወሎ እና በሜጫ ሰፋሪዎች የተያዘባቸውን መሬት መልሰው እንዲይዙ፣ ይህንንም ለማሳካት ከይፋቱ እስላማዊ ወላስማ ጋር የትግል አንድነት እንዲፈጥሩ አዘው እና አስተባብረው ይመለሳሉ (ዓለማየሁ 2006፡194፣ ላጵሶ 1982፡242-243)። ከዚህ በኋላም በሸዋ አምባ ላይ የነበሩት የአማሮቹ ገገርዎች እና የይፋት ወላስማዎች በጋራ ለመቆም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። ከዚያን ጊዜ በኋላም የአማሮች እና የይፋት እስላሞች ግንኙነት መልካም የሚሰኝ ሆኗል። አፈ-ታሪኩም የሚጠቅሰው ይህንኑ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እዚህም ላይ ታዲያ የይፋት ወላስማዎች ከእስላም የእምነት ወገኖቻቸው ተነጥለው ከአማራ /ክርስቲያን/ ገገርዎች ጋር ለመስማማት የበቁት ቀደም ሲል ከአማራ ገገርዎችም፣ ከአፋር ሱልጣኖችም ጋር

---

[12] ዛሬ አማሮቹ ከአርጎባዎች ጋር ለወሬ እሚበቃ አለመግባባት እና ግጭት የላቸውም። የጥንቱም ግጭታቸው በሂደት ተፈቷል። የቀወት አማሮች ከጅሌዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ግን አሁንም አመርቂ አይደለም። ምክንያቱም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ግጭቶች ስለመኖራቸው ከኤፍራታ እና ግድም አካባቢ ሰዎች ሲነገር ይሰማል። በኤፍራታ እና ግድም በኩል ያሉ አማሮች የዚህ ጥናት ቀጥተኛ ተካታች አይደሉም እንጂ በዚያም በኩል ከጅሌዎች ጋር መልካም እና የሰከነ ግንኙነት እንደሌለ ይሰማል።

እየተዋጉ ጉልበታቸውንም ኢኮኖሚያቸውንም አድክመው ስለነበር በመጨረሻ ከአማሮች ጋር ሰላም መፍጠሩን የመረጡት ከያቅጣጨው ላለመጠቃት ሲሉ እንዲሁም እያንሰራራ ያለውን የንጉሣዊውን አገር ኃይል ሚዛን በመገምገም ሳይሆን እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡ አማሮችም ስምምነቱን ወደ አፋር እና ከረዩ፣ ጅሌ ኦሮሞዎች ያለ ሥጋት ለመጠጋት እና መስፋፋታቸውን ለመመከት ሳይጠቀሙበት አልቀሩም፡፡

ለተተኳሪ የቡድን ውይይት ሳታፊዎቼ "ከዚያ በፊትስ አፋሮቹ የት ነበሩ? ይባላል?" ብያቸው ነበር፡፡ እነርሱም "እታች ከአዋሽ ወዲያ ማዶ ነበሩ ነው የሚባለው" ብለውኛል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከቀረበው አፈ-ታሪክ የቀወት አማሮችና የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች በተፈጥሮ ሀብትም ይሁን በኃይማኖት ልዩነት ምክንያት ታሪካዊ ግጭት ያላቸው መሆናቸውን፣ ግጭቱም ያስከተለው ግድያና ዘረፋ በመልካምነት እየተዳነቀ፣ ክብርና ሞገስም እየተሰጠው፣ ገዳይነትም ወግ ማዕረግ እያስገኘ፣ ማዕረጉም ሥርዓተ ከበራ /ritual/ ም እየተደረገለት እስከዛሬ ድረስ ሊዘልቅ የቻለ ተግባርነቱን ማስተዋል እና መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ ቀወቶች ስለ ራሳቸው ሥርወ አመጣጥ ወይም ከየት መጥነት፣ እና ማንነት እንዲሁም ከጎረቤቶቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚመለከት ያላቸውን አፈ ታሪክ ለማየት ሞክረናል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የጥናቱ ሌላኛው ጠገግ የሆኑትን የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ከየት መጥነት፣ ማንነት እና ከአጎራባቾቻቸው ቀወቶች ጋር ስላላቸው ግንኙነት የሚተርኩትን አፈ-ታሪክ እንቃኛለን፡፡

## 5.2. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር አፈ-ታሪክ

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደሚተርኩት አፋሮች ዛሬ በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ እና በጅቡቲ ለመገኘት የበቁት በጥንት ዘመን ከደቡብ አረቢያ

በተለይም ከየመን ሀድራሞት[13] ተነስተው ወደ ዳህላክ ደሴት፣ ከዚያም ቀይ ባህርን አቋርጠው ወዲህ በመሻገር ከሰሜን እስከ ደቡብ ሶማሊያ ድረስ ዘልቀው በመግባታቸው ነው። ብዙዎቹ የሰሙሮቢ ገለአሎ ቂልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ጥንት እያሉ የሚገልፁትንም ዘመን አንዳንዶቹ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ይላሉ (ሼህ መሐመድ ሰይድ፣14/09/2002) ።

በአፈ-ታሪኩም መሰረት አፋሮች በመጀመሪያ በቀይ ባህር ዳርቻ ላይ መስፈር በጀመሩበት ወቅት በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ቀደምት ሕዝቦች ጋር የሰላምም የጦርነትም ግንኙነት እያደረጉ፣ በሂደትም የቀይ ባህርን ጠረፎች በሙሉ ተቆጣጥረዋል። የእስልምናንም ኃይማኖት በአካባቢው አስፋፍተዋል። ቀስ በቀስም በጦርነትም፣ በሰበካም፣ በንግድም ምክንያት የእስልምናን ኃይማኖት አስፋፍተው እና ተከታይ አብዝተው፣ ከአጎራባቾቻቸው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ሕዝቦች ጋርም ተባብረው የወላስማ ሥርወ መንግሥትን መመሥረታቸውን ይተርካሉ። ከዚያን ዘመን ጀምሮም እራሳቸውን ብሔረ-አፋር /ካፍራ-ኡማታ/፣ ቋንቋቸውን የአፋር ቋንቋ /ካፍራ-አፍ/ እያሉ እንደሚጠሩም ይናገራሉ[14]። በነገራችን ላይ አፋሮች እንደሚያስታውሱት ደርግ ወደ ሥልጣን እስከመጣበት የካቲት 1966 ዓ.ም. ድረስ ግን ጎረቤቶቻቸው ይህን ሳይቀበሉ በተለያዩ ሥም ማለትም አማሮች "አዳል"፣ ትግራዮች "ጥልጣል"፣ ሶማሌዎች ዖዳሊ፣ አረቦች "ደንከል" እያሉ ሲጠሯቸው እንደቆዩም ያስታውሳሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዳ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሀሚድ መሐመድ 19/01/2004)። አጥኚዎችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ (Getachew እና Shimels, 2008:93 ፣ Lewis, 1955:155)።

በአፈ-ታሪኩ መሰረት ጥንታዊያኑ አፋሮች ይኖሩ የነበረውም በአውሳ አካባቢ እና በአዋሽ ወንዝ መፋሰሻ አዶሂማራና እና አሻይማራ በሚባሉ በሁለት ጎሳዎች ተከፋፍለው

---

[13] ይህ የአፋር አረጋውያን "ሀድራሞት" የሚሉት በአረብኛው ደግሞ ሀድራማውት /Hadhramaut ወይም Hadramaut/ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስም Hazarmaveth በሚል ሥያሜ የሚታወቅ ሥፍራ በየመን ደቡባዊ የባህር ዳርቻ ከኤደን እስከ ዖማን የተዘረጋ ነው። አካባቢው ከፊል ስምጥ ሸለቋማ እና ለም እንዲሁም ከፊል በረሃማ ነው። የጥንታዊ ሥልጣኔ ማዕከል እንደነበርም የሚጠቁሙ ቅሪቶች እንደሚገኙ አውቃለሁ፣ ተረኮችም ሰምቻለሁ፣ አንብቢያለሁም።

[14] እነዚህም አነጋገሮቻቸው በአማርኛ ሕዝቦቹን ብሔረ አፋር ወይም የአፋር ብሔር፣ ቋንቋቸውን አፋርኛ የምንላቸው ናቸው።

እንደነበር፣ ዛሬ ወደ ሰፈሩበት ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የመጡትም በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ሁሉ ይተርካሉ፡፡

አፋሮች ወደ ሰሙሮቢ ገለአሎ እና ዙሪያ ገባው አካባቢ (በነገራችን ላይ አማሮች እና አፋሮች በሌሎችም ወረዳዎች ይዋሰናሉ) ገብተው የሰፈሩበትንም ምክንያት ከፊሎች ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ በውስጣዊ የጎሳዎች ግጭት ምክንያት ነው ሲሉ፤ ከፊሎች ደግሞ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአውሳ አካባቢ ብርቱ ድርቅ ተከስቶ ስለነበር፣ አይዳሂሶ በመባል የሚታወቀው ጎሳ መሪም ከአፄ ምልክ ጋር ቀረቤታ ስለነበራቸው ነው መጥተው መስፈር የቻሉት ይላሉ (ሼህ መሐመድ ሰይድ 14/09/2002) ፡፡

በመሰረቱ ዛሬ ሰሙሮቢ ገለአሎ ብለን ወደምናውቀው ወረዳ የገቡትም አፋሮች በትውልደ መኳንንትነት እና ተራነት ወይም ቤተ አለቃነት እና ምንዝርነት የሚፈረጁ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት አይዳሂሶ የሚባለው ገገር ክፍል ወደ ወረዳው ይዞ የገባው አይዳሂሶ፣ ጊዲቦሶ እና አይጡር በሚል ሥያሜ የሚታወቁ የአፋር ጎሳዎች ወይም ክፍለ ሕዝቦች እንደሆነ ይተረካል፡፡ እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው መለያዎች ያሏቸው ተደርገው ይታያሉ፡፡

የአይዳሂሶ ጎሳ በሚል ተለይተው የሚታወቁትም ክፍለ ሕዝቦች በገፅታቸው ቀላ ቀላ ያሉ፣ በማህበራዊ ማንነታቸው እና ደረጃቸው ደግሞ መስፍንነት እና መኳንንትነት ወይም ገገርነት ያላቸው ናቸው ይባላል፡፡

ጊዲቦሶ እና አይጡር ጎሳዎች አባላት ደግሞ በመልካቸው ጠየም ጠየም ያሉ በማህበራዊ ደረጃቸው ደግሞ ገባር እና ተከታይ ተደርገው የሚታዩ ክፍለ ሕዝቦች ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ከሚኖሩት ሦስት ጎሳዎች መካከልም ጊዲቦሶ የሚባለው ጎሳ እንደገና በሥሩ ሰባት ያህል ንዑሳን ጎሳዎች እንዳሉት እና በቁጥሩም እንደሚያይልም ሁሉ ይነገራል (አቶ መሐመድ አይዳሂስ የወረዳው መስተዳደር አባል 26/09//2001 ዓ.ም) ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው አፈ-ታሪክ መረዳት እንደሚቻለውም የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችም እንደ ቀወት አማሮች ሁሉ እራሳቸውን በመጤነት ያያሉ፡፡

ስለዚህም በአፈ-ታሪኩ ውስጥ ሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች በጥንተ-ዝርያ አመጣጥ እራሳቸውን መጤ ቢያደርጉም "ተቀዳሚው እኔ ነኝ፤ እኔ ነኝ" የሚልም የአፈ-ታሪክ ተሽምቶም ደግሞ አላቸው፡፡ አንደኛቸውም ከሌላኛቸው ይልቅ እራሳቸውን በአንፃራዊ ሁኔታ ነባር አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በጥናቱ የተካተቱትን

ሕዝቦች አስፋፈር ተረካዊ ልዩነት ያመለክታል፡፡ ልዩነቱም ደግሞ ግንኙነትን እንደሚያሻክር ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችን ጥንት አመጣጥ፣ ማንነት እንዲሁም ግንኙነት ሁኔታ ጽሑፍ ታሪክ እንቃኛለን::

# 6. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ጥንተ አመጣጥ፣ ማንነት እና ግንኙነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ

በዚህ ክፍል ስለ ቀወት ወረዳ አማሮች እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ-አመጣጥ ወይም ከየት መጥነት፣ ማንነት እና ግንኙነት ሁኔታ በጽሑፍ ታሪክ የተሰነደውን እና የታተተውን ሁነት፣ ክስተት እና አጋጣሚ ለመማተር ይሞከራል፡፡ ይህንንም ማድረግ ያስፈለገው ቀደም ሲል የሁለቱ ሕዝቦች አፈ-ታሪክ ወይም ቃል ታሪክ በተወሳበት ክፍል እንደታየው የሁለቱ ሕዝቦች ቃል ታሪክ ለግጭት መጫር፣ በቋሚነትም ለመቀጠል ሰበበ- ምክንያት መሆኑ ታይቷልና ነው፡፡ ስለዚህም በቃል ታሪኩ ውስጥ የተነሱትን ግጭት ተካይ እና አስቀጣይ ሁነቶች ማንጠር፣ የተረኮቹንም እሴት ማረጋገጥ የሚቻለው ጽሑፍ ታሪክንም በጥምረት አይቶ በመመዘን ስለሆነ ነው፡፡ ጽሑፍ ታሪኩንም የምንመለከተው እንደ ቀዳሚው ክፍል አቀራረብ ሁሉ እዚህም ከቀወት ሕዝብ ጽሑፍ ታሪክ በመነሳት እና ወደ ሰሙሮቢ ገለአሎ ሕዝብ ጽሑፍ ታሪክ በመዝለቅ እና ግጭት ተኮር መልዕክቱንም በማብላላት ይሆናል፡፡

## 6.1. የቀወት ወረዳ አማሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ

በጽሑፍ ታሪክ ረገድ የቀወት አማሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት የምንመለከተው ከጠቅላላው አማራ ሕዝብ ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ጋር አስተሳስረን ነው፡፡ ምክንያቱም በአመዛኙ ከሌላው አማራ የተለየ ታሪክ የላቸውምና ነው፡፡

አማራ ስለሚባለው ሕዝብ ጥንተ አመጣጥ እና ማንንትም የምናገኘው መረጃ እና ገለፃ የተለያዩ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አማራ የሚባለው ሕዝብ ጥንት አመጣጡ ከየት ነው? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ የምናገኘው አንድ ምላሽ ዛሬ አማራ በሚል የሚታወቀው ሕዝብ የመጣው በአረብ አገር ይኖሩ ከነበሩ ሂሚሪያት ወይም ሆሚሪት ከሚባሉ ሕዝቦች እንደሆነ፣ አማራ የሚለውም ስም የመጣው ከእነዚሁ ሂሚሪያት ወይም

ሆሚሪት ከሚሉት ቃላት ሳይሆን እንዳልቀረ ተዕፎ እናገኛለን (ተክለፃድቅ፣ 1965፣8)[15]፡፡

የቋንቋውንም ጥንተ አመጣጥ ስንመለከት የሕዝቡን ጥንተ አመጣጥ ተረክ የተከተለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክንያቱም አማርኛ ቋንቋ ምድቡ እናት ቋንቋው አፍሮ አዝያቲክ በሚል ከሚታወቀው ሴማዊ ቋንቋ ነው (ባህሩ፣ 1999፡ 4፣ Levine, 1979) ፡፡ ይሁንና በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ነገሩ ከዚህ የሰፋ፣ የገዘፈ እና የተወሳሰበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የስፋቱ፣ ግዝፈቱ እና ውስብስብነቱም አኳኋን እንዲህ ነው፡፡

ስለ አማራ ማንነት የሚያወሱትም ሰዎች የተለያዬ ዳራ ያላቸው ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ከሕይወት ልምዳቸው እና ተሞክሯቸው በመነሳት አውስተዋል፡፡ አንዳንዶቹ ነገሩን በምርምር ዓይን እና አግባብ ለማየት ሞክረዋል፡፡ አንዳንዶቹ አማራነትን ከፖለቲካ አንፃር ቃኝተዋል፡፡ ስለዚህም ስለ አማራነት እና አማርኛ ቋንቋ የሚነሱት ጥያቄዎች እና የሚሰጡት ምላሾች ስፋትም ጥበትም ያላቸው ናቸው፡፡ ይኸውም የሆነበት ምክንያት የጠያቂዎቹም ሆነ የመላሾቹ ወገኖች መነሻዎች እና መድረሻዎች የተለያዩ በመሆናቸው ሳቢያ እንዲሁም እውነትን በምርምር አግባብ ለማግኘት ባላቸው አቅም ጥንካሬ እና ውሱንነት የተነሳ ይመስላል፡፡ በዚhu ፈለግ ስለ አማራ እና አማርኛ የሚወሳውን እንመልከት፡፡

ስለ አማራ ሕዝብ ማንነት ከሕይወት ልምድ እና ተሞክሮ በመነጨ የሚደመጠው አንዱ ገለፃ አማራ የሚባለው ሕዝብ የአማራ፣ የትግራይና የሐማሴን ሕዝብ በአንድነት እንደሆነ፣ በአብዛኛውም የእስያና የአውሮፓ ደም የተቀላቀለበት ስለመሆኑ ኋላም የሸዋ፣ የወሎ፣ የየጁ፣ የጎጃም እንዲሁም ከአህመድ ቤን ኢብራሂም ወደ ሰሜን መዝለቅ በኋላ ደግሞ የኦሮሞ እና የአፋር ደም የተዋሃደበት ስለመሆኑ የሚያወሳው ነው (ተክለሐዋርያት፣ 1998፡160)፡፡ በዚሁ ፈለግ የሚጠቀሰው ሌላው ደግሞ በላይ (1995፡132-133) በርቱዕነት አማራ ነገድ አለመሆኑን፣ አማርኛም ቢሆን ከግዕዝ እና ከትግሪኛ የተውጣጣ የሠራዊት ምሥጢራዊ መግባቢያ ቋንቋ የነበረ እንጂ የነገድ ቋንቋ አለመሆኑን ያመለከቱበት ነው፡፡

---

[15] አማራ ስለሚባለው ሕዝብ አመጣጥ ከሚቀርቡት መላ ምቶች አንዱ እና እስከ አሁንም በሰከነ ሁኔታ በጽሑፍ ያለው መረጃ ይሄ ቢሆንም አሁን አሁን መላምቱ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አልቀረም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ መሆኗ እስካልተስተባበለ ድረስ ነገሩ የግርምቢጥ ይመስላልና ነው፡፡

አንዳንዶች ደግሞ ነገሩን በምርምር ዓይን እያዩ እውነቱ ላይ ለመድረስ እና የደረሱበትንም እውነት ለመፈንጠቅ ይሞክራሉ፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ዛሬ "አማራ ነኝ" የሚለውም ሆነ የሚባለው ሁሉ "አንድ ብሔረሰብ ሳይሆን ከብዙ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች በታሪካዊ የዕድገት ሂደት የተከሰተ አንድ ልዩ ማህበረሰብ ነው" (ላጵሶ 1983፡122)፡፡ ላጵሶ (1983፡119) ይህን ሐሳብ ያሰፈሩትም ማጣቀሻዎችን ጭምር አይተው መሆኑን ሲያስረግጡ "በደራሲው ቃል" ብለው አለቃ አጥመ ጊዮርጊስ ያሉትን እንዲህ ይጠቅሳሉ፡፡ "አማራ ከወዴትም አልመጣም፡፡ ከያይነቱ የተጠራቀመ ጥሩ የላስታ ወታደር ነው፡፡ ኃይለኛ፣ አድመኛ፣ ያልተማረ፣ ጨካኝ ጭፍራ ነው፡፡" ማለታቸውን፣ አማርኛም መነገር የጀመረው አማሮች ይኩኖ አምላክን ካነገሱ በኋላ መሆኑን፣ ይኸውም በዘመኑ "ፖለቲካ" እንደማለት ሁሉ እንደነበረ አስፍረዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ጋር በተመሳሰለ ሁኔታም አማራ የሚባለው አማራ የሆነ ሕዝብ መሆኑን፣ የአማራ ቋንቋ የሚባለው አማርኛም ከብዙ ማህበረሰቦች ቋንቋዎች በታሪካዊ ሂደት አማካኝነት የተፈጠረ መሆኑን፣ የሕዝብ ቋንቋም መሆን የቻለው በአጋጣሚ ማለትም በአንድ ወቅት የመንግሥቱን አስተዳደር ይዘው የነበሩ ሰዎች አማርኛን ይናገሩ ስለነበር፣ እነዚያም በመንግሥቱ አስተዳደር ላይ የነበሩ ሰዎች ከየቦታው የሚመለምሏቸው ወታደሮች የገገርዎቹን ቋንቋ በመናገራቸው እና በየሄዱበትም አካባቢ ቋንቋውን በማስፋፋታቸው፣ ነጋዴዎችም በየቦታው የንግድ ሥራቸውን ለማካሄጃነት የተጠቀሙበት በመሆኑ እንዲሁም በቤተ ክህነት ትምህርትም አማርኛ ግዕዝን እየተካ በመምጣቱ እንደሆነ የሚያወሱ አሉ (ጌታቸው በኢትዮጵያውያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን መጽሔት ውስጥ (1961፡76-81)፡፡ በዚሁ ፈለግ ስንመለከትም የዚህ ጥናት አንድ ጠገግ ተካታች የሆነው ቀወት ወረዳ በሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የሰሜን ሸዋንም ሕዝብ ማንነት ስንመለከት ከላይ የተጠቀሱትን መደበላለቆች የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ሰሜን ሸዋ የባህል ዝንቀት የሚታይበት አካባቢነቱን፣ ዛሬ አማራ የሚባለውም ሕዝብ ከተለያዩ ጎሳዎች የመጣነቱን፣ ቋንቋውም ከኩሽ፣ ከሰሜንና ደቡብ ሴም ቋንቋዎች የተውጣጣ መሆኑን በምርምር አረጋግጠው የፃፉ አሉ (Levine 1979፣ Aspen፣1994:99)፡፡ ስለዚህም የዛሬው አማራ በስም የተጠቀሱቱ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ብቻ ሳይሆኑ የትየለሌዎች የተዛነቁበት መሆኑንም በየዘመናቱ በሰላምም በጦርነትም በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች የተደረገውን የሕዝብ ንቅናቄ ታሳቢ በማድረግ መገመት ይቻላል፡፡

ብሔር-ተኮር ፖለቲከኞች ደግሞ ለተነሱበት ዓላማ እና ግብ እንደሚመቻቸው እየጠየቁ እንደሚመቻቸውም መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ በዚህም መሰረት አማራን አንድ የተለየ ዝርያ አድርገው ይፈርጃሉ፡፡

የቀወት ወረዳን ሕዝብ ነባራዊ የማንነት ገለፃ ስንመለከትም ሕዝቡ ራሱን አማራ አድርጎ የሚመለከተው ከኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ጋር አስተሳስሮ መሆኑን ከማናቸውም የአካባቢው ነዋሪ አንደበት እንሰማለን፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ስለዘራቸውም ሲጠየቁ "የሰው ዘሩ፣ የዘማት ሥሩ ምን ይታወቃል?" የሚል በምሳሌ የተደገፈ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ስለ ዘማት ምንነት ሲጠየቁም ዘማት የዛፍ ዓይነትነቱን፣ የሥሩም መሄጃ የተወሳሰበ እና በእዚህ ሲሉት በዚያ፣ በዚያ ሲሉት በዚህ እየተጋመደ እና እየተጣመረ የሚገኝነቱን፤ በቀላሉም ሂደቱን እና ውሉን ለመለየት እና ለማወቅ የሚያስቸግርነቱን ይናገራሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀወቶችን ሥርወ አመጣጥ እና ማንነት ከጽሑፍ ታሪክ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችን ከየት መጥነት፣ ማንነትና ከቀወቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሁኔታ ከጽሑፍ ታሪክ ቅኝት አኳያ እናያለን፡፡

## 6.2. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ጥንተ አመጣጥ እና ማንነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮችን ማንነት ለማወቅ በቅድሚያ በጥቅሉ የአፋሮችን ማንነት ማወቅ ያሻል፡፡ ምክንያቱም የሰሙሮቢ ገለአሎዎች ታሪክ የሚመዘዘው ከአጠቃላዩ የአፋር ጽሑፍ ታሪክ ስለሆነ ነው፡፡ የአፋርን ሕዝብ ሥርወ-አመጣጥ ከጽሑፍ ታሪክ አኳያ ስንመለከትም አፋሮች ከደቡብ አረቢያ በተለይም ከየመን ሀድራሞት ፈልሰው ዛሬ ወደሚገኙበት ክልል ገቡ የሚለውን አፈ-ታሪክ የሚፃረር ገለፃ እናገኛለን፡፡

ጽሑፍ ታሪኩ እንደሚያወሳው አፋሮች እና ሳሆዎች ከሰሜን ኬንያ እና ከደቡባዊ ኢትዮጵያ ተነስተው በተከታታይ ንቅናቄ ወደ ሰሜን እና ሰሜናዊ ምሥራቅ የአፍሪካ ቀንድ የዘለቁ ሕዝቦችነታቸውን፣ በቋንቋም ረገድ ቢሆን አፋሮች፣ ሳሆዎች፣ ሶማሊዎች

እና ኦሮሞዎች ምናልባትም ጥንት አንድ ቋንቋ ከነበራቸው ሕዝቦች የተገኙ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ነው የሚገመተው (Lewis፣1955:36)። በዛሬው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አከፋፈልም መሰረት በምሥራዊ ኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪነት የሚፈረጁ ናቸው (ባህሩ (2000:4) ፣ Levine, (1979:37) ፣ Trimingham (1952፣ 8-9)።

አፋሮች ጥንተ-አመጣጣቸው ከአንድ ምንጭ እንደሆነ፣ ጥንት አንድ የነበረው የዝርያ ግንዳቸው ግን በሂደት ወደ ጥንድ አዶሂማራና እና አሻይማራ ጎሳዎች እንደተከፈለ ተፅፏል። በዚሁም መሰረት ጥንዶቹም ጎሳዎች እንደገና በተለያዩ ንዑሳን ጎሳዎች እንደተከፋፈሉ፣ በአከፋፈሉም መሰረት አሻይማራ የሚባሉት በመልካቸው ቀዮች ሲሆኑ በማህበራዊ ኃላፊነታቸውም መኳንንትነት፣ መሪ፣ የማናቸውም ሥርዓት ከበራ ተቀዳሚዎች እና ባራኪዎች፤ አዶይማራ የሚሰኙት ደግሞ ጠየም ጠየም ያሉ እና በማህበራዊ ደረጃቸው የተራነት ወይም የዘገርነት፣ የተከታይነት ወይም የሁለተኛ ደረጃነት ማህበራዊ ቦታ ያላቸው እንደሆኑ ተዘግቧል። በሌላም በኩል ደግሞ ይህ አዶሂማራ እና አሻማራ የሚለው ክፍፍላቸው ፖለቲካዊም እንደሆነም ከአፈ ታሪካቸው ጋር በሚጣጣም መልኩ ተፅፏል Akmel (2010:12፣40)፣ Getachew (2001:53፣59) ፣ Levine (1979:5) ፣ Trimingham (1952፣13፣173)።

አፋሮች በፖለቲካዊ አደረጃጀታቸው በመደብ እና በመልክ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ገገር እና ተገገር ክፍለ ሕዝብ የፈጠሩትም ከአሥራ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሳይሆን እንደማይቀር መገመት ይቻላል። ይኸውም የሆነው ደግሞ በኢትዮጵያ ደቡባዊ ምሥራቅ ወሰን በባህላዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀታቸው ከክርስቲያናዊው መንግሥት የተለዩ፣ በተራሮች መከታ ውስጥ ያለውንም ክርስቲያናዊ መንግሥት የመስፋፋት እና የንግድ እንቅስቃሴ የገቱ እና እና የገደቡ በክፉ ዓይንም የሚያዩ አካባቢያዊ ሱልጣናዊ መንግሥታት ከመሰረቱ በኋላ ሊሆን እንደሚችል ሚዛን ደፍቶ መናገር ይቻላል። የገገር ወይም የአዛዥ እና የተገገር ወይም የታዛዥ ክፍፍሉም የመጣው ውስጣዊ እና ውጫዊ ማህበራዊ ደረጃን ለማስጠበቅ ሲባል መሆኑ አያጠራጥርም። ምክንያቱም በጽሑፍ ታሪክ ረገድ ከአሥራ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ጀምሮ በደቡባዊ ምሥራቅ ነበሩ ከሚባሉት ሱልጣኔቶች መካከል ተካተው ይጠቀሳሉ። ሱልጣኔቶቹም የይፋት ወላስማ እና የአፋር ሱልጣኔቶች በሚል የሚታወቁት ነበሩ። እነዚህም እስላማዊ ሱልጣኔቶች ቀስ በቀስ በደቡባዊ ኢትዮጵያ በኩልም ተስፋፍተው የሀርላ፣ የጎንጋ፣ የዳሞት፣ የሀዲያ፣ የሲዳማ እስላማዊ

ሱልጣኔቶች የሚባሉ ተዘርግተው እንደነበር ተጽፏል (ላጵሶ 1982፡102)፣ ዓለማየሁ (2006፡45-48)።

በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳም የሚገኙት የእነዚሁ ጥንድ ጎሳዎች የገገርው አሻይማራ ንዑስ ጎሳ አይዳሂሶ እና የተገገርው አዶሂማራ ዝርዮች ናቸው።

## 6.3. የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግንኙነት ተኮር ጽሑፍ ታሪክ

በዚህ ክፍል የቀወት ወረዳ አማሮችን እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮችን ግንኙነት ከጽሑፍ ታሪክ አኳያ ለመዳሰስ ይሞከራል። ይኸውም የተደረገው ቀደም ሲል የቀረበው የሁለቱ ተጎራባች ሕዝቦች አፈ ታሪካዊ ግንኙነት ተረክ ወይም ታሪክ ከሁለቱ ሕዝቦች ጽሑፋዊ ተረክ ወይም ታሪክ እንዲሁም ነባራዊ ግጭት አዘል ሕይወት ጋር ያለውን ተቀባባይነት እና ተደጋጋፊነት ለመመልከት፣ ፎክሎራዊ ሐቲቱንም ሐቅነት ለማንጠር ይቻል ዘንድ ነው። ይህንንም ማድረግ ለእንዲህ ዓይነቱ ምርም አደራረግ ግቡዕነቱ አሌ የማይባል ነው።

ከዚህ በፊት በቀረበው ምዕራፍ ሦስት እና በዚህም ምዕራፍ የመጀመሪያ ክፍልም እንደተመላከተው በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ዛሬ ላለው ግጭት ሁኔታ ቃል ታሪክ የራሱ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑ በግልፅ ታይቷል። ይህም ምዕራፍ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የግጭት ታሪክ መኖሩን በበለጠ ያጎላዋል። በቃል ታሪኩ የተተረከውንም ግጭት በጽሑፍ ታሪክ ውስጥ በማየት እና ተደጋጋፊነቱን ያረጋግጣል። የተነሱትንም ግጭት መሥራች ጉዳዮች በመንቀስ ለዛሬው የሁለቱ ሕዝቦች የሕይወት ሥርዓት ያስቀሩትን ቅሪት ያስጤናል።

Markakis (1994:217-220)፣ Levine (1979:30-35,70)፣ Yusuf,1973፡217-219)፣ Lewis (1955)፣ Paul (1954) እና Jones and Monroe (1935:218) በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ የተካሄዱ ታሪካዊ ክስተቶችን በማስረጃ እያጣቀሱ እንዳተቱት የአካባቢው ሕዝቦች መገኛ ምድር ለቋሚ ኑሮ የማይመች ስለሆነ፣ የአየር ንብረቱም አስቸጋሪነት ስላለው፣ ለም መሬት፣ ውኃ፣ ግጦሽ፣ መልካም የአየር ንብረት ለማግኘት ሲሉ የንቅናቄ እና የጦረኝነት ሕይወትን ተላምደዋል። ይህም የሕዝብ ንቅናቄ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ

አርብቶ አደሮች ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን አራሾችም ዘንድ መፈፀሙንም በሚያረጋግጡ ንቅናቄዎች የተመሰከረ ነው። ኢትዮጵያውያንም ባለፉት ክፍለ ዘመናት ከሰሜናዊ አምባማ ምድር ወደ ደቡባዊ አቅጣጫ፣ ከደቡብ እና ከምሥራቅም ወደ ሰሜን ያደረጓቸውን ንቅናቄዎችም፣ የሕዝብ ንቅናቄ በአፍሪካ ቀንድ ልሙድነቱን የሚያመለክቱ ናቸው ብለዋል።

ሲቃውንቱ (Markakis (1994)፣ Paul (1954) ፣ Lewis (1955) Levine (1979) እና Yusuf (1973) በዝርዝር እንዳመለከቱትም የምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ሕዝብ የንቅናቄ እና የስደት ታሪክ እውነታ ግብፆች ወደ ሱዳን፣ ኦሮሞዎች ከአፍሪካ ቀንድ ጫፍ ወደ ኢትዮጵያ አምባማ ምድር፣ ሶማሌዎች ከኤደን ባህረ ሰላጤ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ኮረብታዎች ጥግና ደጋማ ሥፍራዎች፤ የቤጃ ሕዝቦችም ወደ ኤርትራ በዘለቁበት ሂደት ሁሉ የሚመሰከር እውነታ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የስልምና ኃይማኖት ተከታዮችም ነበሩ። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባውም በድግና ሚካኤል ዘመነ መንግሥት (እ.ኢ.አ.656-682) መሆኑን ታሪካዊ መረጃዎች ያመለክታሉ (ጌታቸው፣ 1997፡186)።

> የእስላሞች መጀመሪያ ነቢይና ንጉሥ የመሐመድን የልጁን የፋጢማ ባል አሊን አብድርህማን የሚባል ገደለው። ያሊ ልጅ ከፋጢማ የተወለደው ሐሰን ነግሦ ነበርና በኋላም የሚነግሡ የመሐመድ የፋጢማ የዓሊ ልጆች ናቸውና የአብድርህማን ልጆችና ወገኖች ሁሉ የዓሊን ደም ተበቅለው ይፈጁናል ሲሉ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሸዋ በይፋት ተቀመጡ።

ጌታቸው በማያያዝም እነዚያም እስላሞችም በዚያም ዘመን ተከታትለው የነገሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት እና መኳንንትን እንዲሁም ካህናትን በገፀ-በረከትም፣ በመማለጃም በምንም በማሳነፍ ኃይማኖታቸውን በይፋት ምድር በአሊዩ አምባ፣ አርጎባ እና በሸዋ አዋሳኞች እንዲሁም ወሎ ለማስፋፋት እንደተቻላቸው አመልክተዋል።

ላጵሶ (1982፡85-96) ደግሞ እስላሞች ከዘጠነኛው እስከ አሥራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ ከዳህላክ ደሴት እና ከዜይላ ወደብ የገቡ የእስላም ነጋዴዎችና ሰባኪዎች በሲራራ ነጋዴ መስመሮች በመሃል አገር ከአዋሽ ሸለቆ እና ከጨርጨር ተራራዎች ባሻገር እስከ ታላላቅ ሐይቆች እና የጊቤ ወንዝ ዘልቀው በመላው የሀርላ-ሀዲያ ምድር የንግድ፣ የኃይማኖትና የመንግሥት ምሥረታ ትምህርትና ተግባራት እያስፋፉ እና ሥር እየሰደዱ ሄደው መንግሥት እስከ መመሥረት መብቃታቸውን አውስተዋል።

ላጵሶ (1982) እንደሚያትቱት ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የቀይ ባህር ጠረፎች እና መካከለኛው ምሥራቅ እንዲሁም ግብፅ በአረቦች እስላማዊ እንቅስቃሴ በመያዛቸው የአክሱም መንግሥታት ለዘመናት ከውጪው ዓለም ጋር የነበራቸው የንግድና የባህል ልውውጥ ግንኙነት ቀስ በቀስ እየተቋረጠ ሄዷል፡፡ በዚህም የተነሳ የአረቦች እስላማዊ የፖለቲካና የባህል እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን የወጪ እና የገቢ ንግድ በር ዘግቷል፡፡

በዚህም መሰረት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እና እስልምና በኢትዮጵያ የዘመኑ ፖለቲካዊ ጉዳዮች እየሆኑ በመምጣታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት የቀይ ባህር ጠረፍን በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ሊያጣ ችሏል፡፡ ከዚያ ወዲህም እስልምና በኢትዮጵያ እግሩን ለመስደድ እና ለመንሰራፋት ተችሎታል፡፡ በአገሪቱ የሲራራ ነጋዴ መስመሮች ላይ የነበሩም ሕዝቦች ወደ እስልምና ኃይማኖት ገብተዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የአማራው /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኑ/ መንግሥት ሥጋት ገብቶታል፡፡ የክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች በነበሩ ገገር መደቦችም ዘንድ የጥቅም ግጭት መከሰት ጀምሯል፡፡ እስልምናም ከአሥረኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ በቆላማው ክፍል ሕዝብና መሬት እየያዘ፣ ብርቱ ተፎካካሪም እየሆነ መጥቷል፡፡ የጠረፉም አካባቢ በየመን፣ በኢራቅ፣ በግብፅ ነጋዴዎች ተወሯል (ላጵሶ፣ 1982 ፡ 242-249፣ Tadesse፣ 1972፡43)፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የአክሱም ሥርወ መንግሥት ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከቀይ ባህር ጠረፍ በእስላም ኃይሎች እየተገፋ በመምጣቱ ከውድቀቱ በፊት ሥጋቱ በማየሉ ወደ ደቡብ አፈግፍጓል፡፡ በዚህም መሰረት የአክሱም መንግሥት በተለይ በ800 ዓ.ም. ወደ ደቡብ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ተዘርግቶ አዳዲስ አካባቢዎችን መቆጣጠር እና ማማከል ችሏል፡፡ በዚሁም እንቅስቃሴው ሂደት ቀድሞ በመሸርሸር ላይ የነበረውን መንግሥታዊ ቁመናውን ጨርሷል፡፡ በምትኩም የአገው ሥርወ መንግሥት አቆጥቁጧል፡፡ የአገው ሥርወ መንግሥትም በተራው በ1000 ዓ.ም. እንደ አክሱሙ መንግሥት ሁሉ ወደ ደቡብ ባደረጋቸው የተሳኩ ዘመቻዎች ተጨማሪ ግዛቶችን አካቷል (ዓለማየሁ 2006፡25፣ Abir 1980, 45፣ Reminick, 1973:86)፡፡ ምክንያቱም ከዛጉዌ ሥርወ መንግሥት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያናዊ መንግስትን ወደ ደቡብ እንዲስፋፋ ያደረጉት አሁንም በእምነት ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን፣ በቋንቋ ደግሞ አማርኛ ተናጋሪ ሕዝቦች ናቸው (Tadesse፣ 1972፡64-68)፡፡ በዚህም

መሰረት የሸዋ አማርኛ ተናጋሪዎች ከሙስሊሞች ጋር በማያቋርጥ ግጭት ውስጥ የገቡት ምናልባትም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡ ለዚህም አባባል ትክክለኛነት አንዱ ማረጋገጫ የሚሆነው ሸዋ ሀገረ መንግሥት ከሆነ በኋላ ይፋት ውስጥ እነማን ይኖሩ ነበር ብለን ታሪክን ስንመረምር የምናገኘው ምላሽ ነው፡፡

ዛሬ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ብለን በምናውቃቸው አካባቢዎች እና በዙሪያቸው ያለው ሁሉ በጥቅሉ ይፋት፣ አንዳንድ ጊዜም ይፋትና አፋር (በነገራችን ላይ የአፋርን የጥንት መጠሪያ መጠቀም አግባብ ሆኖ ስላልተገኘ በዛሬው ተቀይሯል) በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ይፋትና አፋር የሚባሉትም አካባቢዎች በሱልጣኖች ይገዙ ነበር፡፡ በወቅቱ የይፋት እና የአፋር ሱልጣኖች "ምሥራቃዊ ከፍታዎችን ይዞ አልፎ አልፎም የመሃከለኛውን ከፍታ ምሥራቃዊ ከፍል እየጨረፈ የተዘረጋ ነበር፡፡ የደዋሮ፣ የባሌ፣ የሐዲያና የፈጠጋር አውራጃዎች በኢትዮጵያው ስምጥ ሸለቆ ደቡባዊ ምሥራቅ ውስጥ ሁሉ የሚገኙ ሆነው በፖለቲካዊ ጥቅማቸው ያን ጊዜ ከእስላም ጋር የተሳሰሩ ነበሩ፡፡" (ዓለማየሁ (2006፡59)፡፡ ይህ የይፋት-አፋር ሱልጣኔቶች ይባል የነበረው ግዛትም ከሸዋ በስተምሥራቅ እስከ ሐረርጌ ደጋ፣ በጠረፍ በኩልም እስከ ኤደን ባህረ ሰላጤ እና ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርሰውን አካባቢ ያካትት እንደነበር ይገመታል (ላጵሶ (1982፣1999፡ 209-218)፡፡ በዚህ በጥቅሉ ይፋት በሚል በሚታወቀው አካባቢ ደግሞ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዘመን በቅደም ተከተል ሲታዩ ቀደምት ሰፋሪዎቹ አርጎባዎች፣ ተከታዮቹ አማሮች፣ ሳልሳዮቹ አፋሮች ፣ ራብአዮቹ ኦሮሞዎች ሆነው እናገኛቸዋለን (Ahmed 1994: 29-32፣ Chernet፣ 1990: 304-312፣ Trimingham 1965:62) ፡፡ ይህም ቦታው በፍርቅርቅ ይያዝ፣ ነዋሪዎቹም በዘርያ፣ በቋንቋ፣ በባህል ይቀያየጡ እና ይዛነቁ እንደነበር ይጠቁመናል፡፡

በዚሁም መሰረት አርጎባዎች እ.ኤ.አ ከ1108 ዓ.ም ጀምሮ በአካባቢው ተንሰራፍተው ስለነበር መስጊዶችን አስበሪ፣ ዋሲሱ-ኖራ፣ ጎዜ አራዳ፣ ጨኖ[16] ወዘተ ላይ መመስረታቸው እና የእስልምናንም ኃይማኖት ማስፋፋታቸው በአካባቢው ላይ የባለቤትነት እና የገገርነት ድርሻ እንደነበራቸው አመላካችነቱም ይጠቀሳል፡፡ ከአርጎባዎች በተጨማሪ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ፣ ኋላ ላይ የጠፉት ቀጭኖ፣ ሻጉራ እና ዶባ የሚባሉ ቀደምት ሕዝቦችም እንደነበሩ ይተረካል (Bairu፣ 1987፡248-256) ፡፡

[16] የተጠቀሱት ሥፍራዎች በሙሉ በጥቅሉ ይፋት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ ቀወት እና ሰሙሮቢም በዚሁ ጥቅል ሥም ውስጥ ተካታቾች ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበውን ዓይነት ማለትም በኢትዮጵያ የእስልምና መስፋፋት እና መጠናከር ጉዳይ በሌሎችም የታሪክ አብነቶች ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ በ1128 ዓ.ም. የሸዋ አማርኛ ተናጋሪዎች እና የወርጂ አርብቶ አደሮች መጋጨታቸውን፣ እ.ኤ.አ. ከ 1270-1294 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ማለትም ከላይ እንደተገለፀው ሸዋ ሀገረ መንግሥት ከሆነ በኋላ የሸዋ አማርኛ ተናጋሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከይፋት የወላስማ ሱልጣኔት እስላሞች ጋር ፀብ ማፍራታቸውን፣ እያደርም በሰለሞናዊው ሥርወ መንግሥት ትንሣኤ ዘመን አማርኛ ተናጋሪዎቹ የምዕዋን፣ የዘይላን፣ በጠቅላላውም የቀይ ባህር እና የኤደን ባህረ ሰላጤን የንግድና የዲፕሎማሲ መስመር ለመቆጣጠር ሲሉ ከይፋት ሙስሊሞች ጋር ተከታታይ እና ተራዛሚ ጦርነት ውስጥ መግባታቸውን ሁሉ እናነባለን፣ እንረዳለንም (Tadesse፣ 1972፣ ዓለማየሁ (2006) ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተውም በሸዋ የክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖቶች መሬት እና ሕዝብ መያዝ ፉክክር የተጠናከረው እ.ኤ.አ.1128 ጀምሮ በተለይም የአማራው /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን/ ገዢ በምሥራቃዊ የሸዋ አምባዎች ሥር የሚኖሩትን አርብቶ አደሮች ወረዳዎች እና የእስልምና ተከታዮች ለመውረር ከሞከረበት እና ከከሸፈበት ጊዜ ጀምሮ ነው (Tadesse ፣1972፡ 42) ፡፡ ይኸውም ወረራ አርብቶ አደሮቹ ከእስልምና ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት እንዲገቡ የማድረግ ሙከራ ነበር፡፡

ከዚህ በላይ በቀረበው ታሪካዊ ቅኝት እንደተጠቀመው የኢትዮጵያ መንግሥት በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከላስታ ወደ ሸዋ ከዘለቀበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የሸዋ አማሮች እና የይፋት ሙስሊሞች ግንኙነት ሁኔታ እጅጉን ግጭት የተመላበት እና የጎላበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንደሚታየው የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ተዳክሞ ሥልጣን በአፄ ይኩኖ አምላክ በ1262 ዓ.ም አማካኝነት ወደ ሸዋ ከተሸጋገረ ወዲህ የአገሪቱ ወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም ውጫዊ የመንግሥት ግንኙነት በአፋር ስምጥ ሸለቆ በኩል በቀይ ባህር እና በኤደን ባህረ ሰላጤ በኩል ነበር የሚካሄደው፡፡ ለዚህም አንዱ አስረጅ አፄ ይኩኖ አምላክ እና ተከታዮቹ ከዛጉዌ የወረሱትን ግዛት በማስፋፋት ከአክሱም መንግሥት የሚተካከልና እንዲያውም የሚበልጥ ገናና መንግሥት ለማቋቋም መብቃታቸው ነው (ባህሩ 1999፡7)፡፡ ይህ የአፄ ይኩኖ አምላክ ከይፋት ሙስሊም መንግሥታት ጋር መዋጋት መቻል እና የአፋር

ሸለቆን መቆጣጠር ጥረት፣ የቀይ ባህርን መዳረሻዎች እና እነ ዜይላን የመሰሉ ወደቦች ለንግድ በርነት ለመጠቀም አስችሏል፡፡ ይህም ውጤት ደግሞ የክርስቲያኑ መንግሥት የኢኮኖሚ እና ወታደራዊ አቅሙን እንዲያጎለብት፣ የቤተ መንግሥት እና ቤተክርስቲያንም መተጋገዝ ልቀት እንዲያሳይ መርዳቱ እሙን ነው፡፡

ላጵሶ (1982) እና ተክለፃድቅ (1965) እንደሚያወሱትም ይፋት በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት የራሱ ተፎካካሪ የሆነ ወላስማ ሥርወ መንግሥት ተወላጅ እና ዑመር የሚባል ባላባት ወይም ሱልጣን ነበረው፡፡ በዚያም ወቅት ዑመር የወላስማዎች ማዕከል የሆነችውን ይፋትን ከደገኛው መንግሥት ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ በመሞከሩ ከአማራው /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኑ መንግሥት በኩል በአካባቢው ላይ ተከታታይ ዘመቻዎች ተካሂደውበታል፡፡ በተለይም የቤተ መንግሥቱ እና ቤተ ክህነቱ በላቀ ደረጃ መተሳሰተር ክርስትናንም ለማስፋፋት ስለነበረ እና በአንፃራዊ ሁኔታም እስልምናንም በመጫኑ በክርስቲያናዊው መንግሥት እና በሙስሊሞቹ ይፋቶች እና አፋሮች ዘንድ አታካቹን ጦርነት ማስቀም፣ የሰከነ ሰላምም መፍጠር የተቻለ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ከአፄ ይኩኖ አምላክ አፍላ ዘመነ መንግሥት በኋላ በክርስቲያኑ በተለይም በአማርኛ ተናጋሪዎቹ እና በአፋሮቹ መካከል ግጭቶች መከሰታቸው ቀጥሏል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን ታሪካዊ እውነታዎች ማጤን ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ማዕከላዊ መንግሥት መሪዎች እና የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ቆላማ ክፍል እስላማዊ መሪዎች ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ ዘለግ ለሚል ዘመን ያካሄዱትን ዋና ዋና ግጭት እንደ አንድ ማረጋገጫ ወስዶ መመልከት ይቻላል፡፡ ሁለቱ ኃይሎች ከአሥራ ሦስተኛው እስከ አሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያደረጓቸው የኃይል መገዳደሮችም ዛሬ በቀወት እና በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ወረዳዎች ለሚገኙ ሕዝቦች ከጥንት የወረደ ጠላትነት ተረክ አንድ ማሳያ የሚሆን ነው፡፡ በዚህም መሰረት መንበረ መንግሥታቸውን በሸዋ አድርገው የነበሩት ክርስቲያናዊ አፄዎቹ አምደ ጽዮን ከሐቅ አድዲን /ሐቋዲን/፣ ጋማል፣ አድዲን /ገመልዲን/፣ ሰብረ አድዲን /ሰብረዲን/፤ አፄ ሰይፈ አርዕድ ከአሊ፤ አፄ ውድም አስፈሪ ከዳግማዊ ሐቋዲን፤ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከበድላይ ሺሀብ አድዲን መሐመድ (አርዌ በድላይ)፣ አፄ በዕደ ማርያም ከመሐመድ ቤን በድላይ፣ ከሱለይማን አህመድ፤ አፄ እስክንድር ከሻምለ

አድዲን መሐመድ ይፋት፣ የአፋር፣ የሐረርጌ እና የሶማሌ ኤሚሮቹ ወይም ሱልጣኖቹ ጋር ያካሄዱትን መፋለም ማስታወስ ይቻላል፡፡ ተክለፃድቅ፣ 1965፡47)፡፡

ታሪክ እንደሚያስረዳው ከ1270 ዓ.ም. እስከ 1600 ዓ.ም. የሸዋ "ሰሎሞናዊ" ሥርወ መንግሥት ወራሲዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ምሥራቅ እና ምዕራብ የሥልጣን ማስፋፋት ዘመቻዎችን አድርገዋል፡፡ በዚህም ወቅት ፋታ የማይሰጥ ተገዳዳሪ እና ተቋቋሚ ያጋጠማቸው ከይፋት ወላስማ እና ከአፋር ሱልጣኖች ነበር (ላጵሶ 1983፡120) ፡፡ እዚህ ላይ ለመሆኑ የይፋት ወላስማ ሥርወ መንግሥት የሚባለው በማን የተመሰረተ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ ለጥያቄውንም ምላሽ ሰጥቶ ማለፍ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የይፋት ወላስማ ሥርወ መንግሥት መሥራቾች ነን የሚሉት አርጎባዎች ናቸው፡፡ በእርግጥ አሁንም እንደገና "አርጎባዎችስ ደግሞ እነማን ናቸው?" የሚል ተከታይ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህን ጥያቄ በቅድሚያ ማስተናገድ ያለብኝም እራሳቸውን አርጎባዎች ስለራሳቸው እንዲናገሩ በማድረግ መሆን እንዳለበት፣ ለዚህም ተገቢ የሚሆን መልስ ደግሞ በቆዩ ማስታወሻዬ ውስጥ እንዳለ ታወሰኝ፡፡ በ1990 ዓ.ም. ስለ አርጎባ ሕዝብ እና ታሪክ አንድ ዘጋቢ ፊልም ለመሥራት አቅጄ ስሰራ ሐጂ በሺር ዳውድ የሚባሉ የአርጎባ ተወላጅ እና አዲስ አበባ የሚገኘው የአወሊያ ትምህርት ቤት እና መካ የሚገኘው ዓለማቀፋዊ እስላማዊ ድርጅት የኢትዮጵያ ተጠሪ የነበሩ በ 05/09/1990 ዓ.ም. ጠይቄያቸው የነገሩኝን እና በማስታወሻዬም ያስፈርኩትን ወዲህ አሸጋግሬ መልስ ይሆን ዘንድ ጣልቃ አስገብቸቼዋለሁ፡፡

ሐጂ በሺር ዳውድ (05/09/1990) እንደነገሩኝ አርጎባዎች ነቢዩ መሐመድ በተነሱ ዘመን ከሰባ እስከ ሰማኒያ የሚሆኑ ወንዶች እና ሴቶች ከሳውዲ ተነስተው በየመን አድርገው ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ገብተው ውቅሮ አካባቢ የሰፈሩ፣ ቀስበቀስም ከትግራይ እስከ ሰሜን ሸዋ ምሥራቃዊ ቆላማ ክፍል ተዘርግተው፣ ከትግራይ እና ከአማራ እንዲሁም ከየመን ነጋዴ አረቦች ጋር እየተዋለዱ፣ ዝርያቸውን አበርክተው የእስልምናን ኃይማኖት የተከሉ እና ያስፋፉ፣ ወላስማ የተሰኘ እስላማዊ ሥርወ መንግሥትም የመሰረቱ ሕዝቦች ናቸው፡፡ አርጎባ ማትም በአማርኛ "አርብ ገባ" እንደ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ጥንት የአረብ ነጋዴዎች ቅፍለት ወደ ዶቃቂት፣ ሐር አምባ፣

ዓይኔ፣ ጨኖ፣ አልዩ አምባ ከተሞች[17] ይገባ የነበረው በዕለተ አርብ ስለነበረ ሲሉ ሐጂ በሺር ዳውድ ነግረውኛል። ይህ ከዚህ በላይ የቀረበው የሼህ በሺር ዳውድ አገላለፅም ከጽሑፉም ታሪክ ጋር ተገጣጣሚነት አለው።

Encyclopedia Aethipica: (2010. v.4:1069-1070) እንዳሰፈረው "ወላስማ" በሰሜን ሸዋ ዞን ምሥራቃዊ ክፍል ይፋት በሚባለው አካባቢ በሚኖሩ አርጎባዎች ዘንድ ለከፍተኛ መሪዎች የሚሰጥ ልማዳዊ የማዕረግ ሥም ሲሆን፣ የወላስማ ሥርወ መንግሥት በመባል የሚታወቀውም የይፋት ሱልጣኔት ከአሥራ ሦስተኛው እስከ አሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከክርስቲያን ነገሥታት ጋር በተከታታይ ግጭት ውስጥ የነበረ ገገር መደብ ነው። ይሄም የወላስማ ሥርወ መንግት በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ህልውናው በሸንፈት ሲያከትምም አፄ በዕደ ማርያም የራሳቸውን ገገር በዚሁ ማዕረግ ሰይመው ይፋት ላይ ሾመው እንደነበር ሁሉ ሰፍሮ እናገኛለን።

ላጵሶ (1982፡122) ደግሞ በሸዋ እና ምሥራቃዊ ክፍሉ ሦስት ዓይነት ሱልጣኔቶች እንደነበሩ እነርሱም የሸዋ (እ.ኤ.አ 896-1285) የይፋት (እ.ኤ.አ. 1285-1415) ፣ የአፋር (እ.ኤ.አ.1515-1577) ሱልጣኔቶች እንደነበሩ ይዘረዝራሉ። የአፋር ሱልጣኔትም በተራው መግነን የጀመረው የወላስማ ሥር መንግሥት በውስጥም በውጭም ግጭት ከተዳከመ እና ካበቃ በኋላ ዋና ጠቅላይ በመሆን ነው።

ወደ ቀዳሚ ሥረ-ነገሬ ልመለስ። የይፋት ወላስማ እና የአፋር ሱልጣኖች እንዴት እና እንደምን የሸዋ አማራ /ክርስቲያናዊ/ መንግሥት ተገዳዳሪዎች ለመሆን እንደበቁ የጽሑፍ ታሪካዊ ማስረጃዎችን በማንጠሪያነት እየወሰድን ቀደም ሲል በአፈ-ታሪኩ ያያነውን እናረጋግጥ።

በአምደ ጽዮን ዘመን (1307-1337) በክርስትና እና በእስልምና ተከታዮች መካከል የተካረረ ግጭት ነበረ። ግጭቱም በመካረሩ የይፋቱ ወላስማ ሥርወ መንግሥት የወቅቱ ገገር ቀዳማዊ ሰብረዲን የሐዲያን ሱልጣን (ሱልጣኑ አመኖ ይባላሉ) አስተባብረው እና ግምባር ፈጥረው በአፄ አምደ ጽዮን ግዛት ውስጥ በነበሩት ክፍለ ሀገሮች ላይ ለመዝመት መነሳታቸውን፣ አፄውም የሚጠብቃቸውን መዓዜ ዕድል ከበድ ካለ ዛቻ ጋር ለአፄው እንዲህ እንደሚከተለው ይልኩባቸዋል (ላጵሶ፣ 1982፡102) ። ዛቻውን እነሆ።

---

[17] የተጠቀሱት ሥፍራዎች በሙሉ ይፋት በመባል በሚታወቀው አከባቢ የሚገኙ ናቸው።

"በመሃል እና በሰሜን ዳሞት፣ ወረብ፣ ዋጅ፣ አላማለል፣ ፈጠጋር፣ እንዳገብጠን፣ ሙገር፣ ግራርያ፣ ተጉለት፣ መንዝ፣ አምሐራ፣ እንደርታ፣ ጎጃም፣ በጌምድር፣ አንጎት... ላይ ገዢዎቼን እሾማለሁ። የአገሩም ንጉሥ እኔ እራሴ እሆናለሁ። የአፄውንም ንግሥት በምርኮ ወስጄ እንደ ገረድ እህል አስፈጫታለሁ። በክርስቲያኖችም ምድር በእስላሞች ዘንድ የተወደደውን ልዩ የጫት ተክል እተክላለሁ።"

ይህም የቀዳማዊ ሰብረዲን ዛቻ የሥልጣን የጥቅም፣ የ "ወንድነት" ፣ የእምነት፣ የማህበራዊ ክብር፣ የወግ ማዕረግ መፈታተን ተረክ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ግጭቱም ተከስቶ የነበረው ሙስሊሞች ረጅሙን የንግድ መስመር ተቆጣጥረውት ስለነበር፣ በዚህም ምክንያት ክርስቲያናዊው መንግሥት በቀይ ባህር በኩል ዘልቆ ነፃ የንግድ እና ግንኙነት እንቅስቃሴ ማድረግ ባለመቻሉ፣ የውጭ ግንኙነት መፍጠሪያ ክፍት በር ለማግኘት በመጣሩ ነበር። ስለዚህም የአማራው /ኦርቶዶክስ ክርስቲያናዊ/ መንግሥት ይህን ብርቱ ፍላጎቱን ለማሳካት ሲል በተከታታይ እና በማያባራ ግጭት ውስጥ ይገባ እንደነበር ይታወሳል (Tadesse (1972፣135)። ታደሰ ሁኔታውን በዝርዝር እንዳመለከቱት አምደ ጽዮን ከወላስማው ሱልጣን ዛቻው ከደረሳቸው በኋላ (1307-1337) እ.ኤ.አ በ1332 ዓ.ም ጦርነት ይገጥሟቸዋል። የወላስማውም ሱልጣን "አፍና ቅብቅብ ዘወትር አያበላም" እንዲሉ ሆኖባቸው በአምደ ጽዮን ጦር ለሽንፈት እና ለውድመት ተዳርገዋል። ላጵሶ (1982፡107-108) ም በዚሁ ወቅት አምደ ጽዮን ስለ ድላቸው ተናገሩት የተባለውን ከ Conti Rossini (1907) ጠቅሰው የሚከተለውን ታሪክ አስፍረዋል።

ከአገሬ በተነሳሁ በሁለተኛው ቀን ከሰባት ፈረሰኞች ጋር ወደ አንተ ከተማ ገባሁ።... ከዚያ በኋላ የተቀሩ ወታደሮቼ ደርሰው የይፋትን ምድር ፈፅመው አጠፉት። እኔም ከዚያ አገር እንደ አሸዋ የበዛ ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ ከብዙ አልባሳት ጋር ወሰድኩ። ቀጥሎም ወታደሮቼን ኩል፣ ጎራ፣ ገዳያ፣ ኩባት፣ ፈድሴ፣ ሃርጋያ፣ በቁልዛርና ሸዋ ወደሚባሉቱ የእስላም አገሮች በሙሉ ሰደድኩ። እነርሱም በእነዚህ አገሮች ሁሉ ጦርነት አካሄዱ።

አምደ ጽዮን ዘመን (1307-1337) በ1332 ዓ.ም ድል መታሁ የሚሉትም ሱልጣን ሰብረዲን የሚመሩትን ኃይል ነው። ኋላ ላይ ይህ የይፋት ወላስማ ሥርወ መንግሥት ላያንሰራራ የተደመሰሰው ግን ከምዕራብ የአማራ ነጋሢዎች፣ ከምሥራቅ ደግሞ የአፋር ሱልጣኖች በተከታታይ ባደረሱበት ጥቃት መሆኑ ይወሳል። ምክንያቱም የይፋት እና የአፋር ሱልጣኔቶች እርስበርሳቸውም ለበላይነት ይተጋገሉ ነበርና ነው።

ነገር ግን የይፋቱ የወላስማ ሥርወ መንግሥት ከተጠቀሰው ዘመን በኋላ የአማራው /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን/ መንግሥት ተገዳዳሪነቱ ያከተመ ቢሆንም የአፋሩ ሱልጣኔት ደግሞ እየደረጀ ሄዶ ነበር፡፡ እናም በአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ በአፋር ሱልጣኖች የሚመራ የክርስቲያን መንግስት ተገዳዳሪ ኃይል በዳግማዊ ሐቋዲን እና ሰዓዳዲን አማካኝነት ተመሥርቷል፡፡ ይኸውም የአፋር ሱልጣናዊ መንግሥት በአርጎባዎች፣ በሐረሪዎች እና በሱማሌዎች ሁሉ የሚደገፍ እና እስከ እ.ኤ.አ እስከ 1527 ዓ.ም ድረስም አዲስ የአማራ /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን/ መንግሥት ተፃራሪ ኃይል ለመሆን የቻለ ከዚያም በኋላ ወደ ሐረር እና አውሳ በረሃ አፈግፍጎ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በ1887 ሐረርን እስከተቆጣጠሩበት ዘመን ድረስ ህልውና እንደነበረው አይዘነጋም፡፡

በአምደ ጽዮን (1307-1337) እና በዳግማዊ ሐቋዲን ማለትም የአፄ አምደ ጽዮን ዘመንተኛ በነበረው የአፋር ሱልጣኔት መንግሥት መሥራች እና የወቅቱም ገገር ከነበረው ጋር በጦርነት መፈታተን በዝቶ ነበር (ዓለማየሁ 2006፡64-68፣ ማኅተመ ሥላሴ፣ 1962፡823) ፡፡ ይኸውም የሆነው በዚያን ዘመን አማሮቹ እና እስላሞቹ በቅርብ ተጎራብተው በይፋት ምድር ከአሥራ ሦስተኛው እስከ አሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ ስለነበር መሆኑን ታሪካዊ ሰነዶች ያረጋግጣሉ (ተክለፃድቅ፣ 1965፣ 16፣35፣85)፣ ላጵሶ (1982፣ 242-249)፡፡ ይኸውም ደግሞ አማራ /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና/ እና እስልምና በመልክዓ ምድር ረገድ እጅግ በተጠጋጉበት አካባቢ ግጭቱ ያይል እንደነበረ ነው የሚጠቁመን፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በምሥራቅ ኢትዮጵያ በተከታታይ የተካሄደው ጦርነት ዋና ምክንያትም ምንም እንኳን የንግድ መስመር ማጣት መቆጫጨት እና ማግኘት ፍላጎት የነበረ ቢሆንም በሁለቱ የግዛት ተቃናቃኞች ሕዝቦች መካከል ይሰበክ የነበረው የግጭቱ መሰረት ግን የእምነት ልዩነት (ክርስቲያንነት እና እስላምነት) እንደነበር ከኃይል አሰላለፉ እና ከቃልም ከጽሑፍም ተረክ እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም በይፋት ወላስማ ሱልጣኔት ሥርወ መንግሥትም ሆነ በአፋር ሱልጣኔት መንግሥት በኩል የነበሩት ደጀኖች በሙሉ እስላሞች በክርስቲያኑም በኩል ክርስቲያኖች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በአጭሩም ኢትዮጵያውያኑ እርስበርስ ይዋጉ የነበሩት በፖለቲካ እና አስተዳደር መርሐ ግብር ልዩነት አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን ክርስትናውም ሆነ እስልምናው በውስጣዊ

ሥሪታቸው መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ዓላማ እና ይዘት ያላቸው ቢሆኑም በይፋ ግን ውጊያቸው በእምነት ወይም ተረክ ልዩነት ምክንያት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት የታሪክ ዳናዎች መሰረት የአፄ ዘርዐ ያዕቆብንም ዘመነ መንግሥት የኋሊት ስንማትር ግጭቱ አላባራም ነበር፡፡ ምክንያቱም አፄ ዘርዐ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥታቸው (1434-1468) የአፋሩን ሱልጣን ወይም ንጉሥ በድላይን በጦርነት መተዋቸው ስለነበር ስመ-ጥርነታቸው ከፍ ብሎ ተዛምቶ እንደነበር እና የግብፅ ክርስቲያኖችም መመኪያ እስከ መሆን ደርሰው እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ በዚህ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1426-1460) የኢትዮጵያ እስላሞች የግብፅ ክርስቲያኖች መብት ማስጠበቂያ መያዣዎች እና መገዳደሪያዎች መስለው ይታዩ ነበር የሚባልበት ምክንያትም እንዲህ ነበር፡፡

አፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1434-1468) በዘመነ መንግሥታቸው ይፋት በመባል ይታወቅ የነበረውን አካባቢ እና የግብፅ መንግሥት አፍቃሪ የነበሩትን የይፋት ወላስማ እና አፋር ሱልጣኖች ሙሉ በሙሉ የግዛታቸው ገባሮች ማድረግ ተችሏቸው ነበር (ተክለፃድቅ፣ 1965)፡፡ በዚሁ ዘመን ደግሞ የግብፅ ክርስቲያኖች በግብፅ ሱልጣኖች ይገፉ እና ይዋከቡ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የግብፅ የዘመኑ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ (እ.አ.አ1428-1452) በግብፅ ክርስቲያኖች ላይ የደረሰባቸውን በደል ዘርዝረው ለአፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1434-1468) ልከው ነበር፡፡ አፄ ዘርዐ ያዕቆብም ለግብፁ ሱልጣን የሚከተለውን መልዕክት የያዘ ዲፕሎማሲያዊ ደብዳቤ ልከውላቸዋል፡፡ “እዚህ (ኢትዮጵያ) ያሉትን እስላሞች ማንም አይነካቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ እንደ ሌላው ሕዝብ ግብር እንኳን አናስገብራቸውም...እናንተ ግን የኃይማኖት ነፃነት ትገፋላችሁ” የሚል፡፡ በዚሁም መሰረት የግብፅ ሱልጣን አል-መሊክ አል-አሽሪፍ ሰይፉ አድ-ዲን በርስበይ (እ.አ.አ 1422-1438) ክርስቲያኖቹን በአግባቡ ወደ መያዝ ተመልሶ ስለነበረ ከላይ የተጠቀሱት የግብፅ ክርስቲያኖች ሊቀ ጳጳስ ለአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ምሥጋና የሚያደርሱ ልዑካኖችን ሁሉ ልከው እንደነበር፣ በግብፅ እስላሞች ለጠፉት ወይም ለወደሙት ቤተ ክርስቲያኖችም መታሰቢያ የሚሆኑ ቤተክርስቲያናትን ሁሉ ሸዋ ውስጥ በመታሰቢያነት አሰርተው እንደነበር እናነባለን (ጌታቸው ፣2003፡ 52-53) ፡፡

በተለይ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የንጉሡን አገዛዝ በኃይማኖትም በፖለቲካም ሰበብ ይቀናቀኑ የነበሩ ሰዎችን ንጉሱ “የጦር መምጫ ወደሆነው ወደ መንግሥቱ ምሥራቅ በትኗቸው” ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ ይህም የጦር መምጫ

የተባለው አፋር እንደነበር፣ በዘመኑም ከተካሄዱት ጦርነቶች መካከል የታወቀው ከኢማም በድላይ ጋር የተደረገው እንደሆነ፣ ይኸውም ታሪክ በንጉሡ ታሪክ ውስጥ እንዲሁም በተአምረ ማርያምና በገድለ ጊዮርጊስ እንደተመዘገበ ሁሉ ይታወቃል (ጌታቸው፣ 2003፡ 133)፡፡ ይህም የሚጠቁመን ቀደም ባለው ዘመን ይፋት መቀጣጫ ሥፍራም እንደነበር ነው፡፡ እንኳንስ ሙስሊሞች ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችም እንዲቸገሩ ወደ አካባቢው የሚጋዙበት፣ ከእምነታቸው ጋር በሚጣረስ ሁኔታም እንዲኖሩ እና እንዲሰቃዩ የሚደረግበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን እና እስላም መካከል መቃቃር፣ታሪካዊ ግጭትም መትከል እንደነበር እንረዳለን፡፡ ሌላው ቀርቶ የንጉሱ የኃይማኖት ተቀናቃኞች እሬሳ ሳይቀር በእስላም /በአፋር/ ምድር እንዲቃጠል ሁሉ የተደረገበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከአፋሩ ገገር ሱልጣን ጋር ይዋጉ ነበር፡፡ ተዋግተውም ድል ያደርጉታል፡፡ ድል ካደረጉት በኋላም የተቀበረበትን ቦታ ጭምር ያውቁ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለም እስጢፋኖስ ከተባለ መነኩሴ ጋር በኃይማኖት ጉዳይ ይጣላሉ፡፡ ፀባቸው የከረረ ስለነበርም መነኩሴውን ወደ አፋር ምድር በግዞት ይልኳቸዋል፡፡ መነኩሴውም እንደሚሞቱ ስላወቁ እስላሞቹ አስከሬናቸውን እንዳይነኩ ማለትም እንዳይገንዙ እና እንዳይቀብሩ ካስጠነቀቁ በኋላ ያርፋሉ፡፡ መነኩሴው ከአረፉ በኋላ ደግሞ ንጉሱ አስከሬናቸው የአፋሮች ገገር ከተቀበረበት ሥፍራ ላይ እንዲቃጠል እንዲህ ሲሉ ያዛሉ፡፡ "ይህ ሰው ከሐዲ ነው፤ አገሩን ሁሉ ወደ ትምህርቱ ሲያስኬድ ነበረ፡፡ ጠባዩ ሁሉ እንደዚህ እስላም ነው፡፡ ስሙ እስጢፋኖስ ነው፡፡ አሁንም በድኑን ውሰዱና አቃጥሉት፡፡" (ጌታቸው 2003፡111-114)፡፡ ይህም እንግዲህ እንኳን እስላም ክርስቲያንም "እስላም" የሚባልበት ሁኔታ እንደነበር ይጠቁመናል፡፡ "የአማራ እና እስላም ነን፣ ሆነናል፣ ሆኑ፣ ሆነዋል፣ ናቸው" ሁኔታም ከዚህ ሁሉ ጋር የተያያዘነቱን ያጤኗል፡፡ ከዚሁ ጋር በተስማማ መልኩ አንዳንድ የአማራ /ክርስቲያን/ ነገሥታት ዙፋናችንን ይነቀንቃሉ፣ ሥልጣናችንን ይቀማሉ ብለው የሚጠረጥሯቸውን የጦር አዛገሮቻቸውንም ከላላ /ከደከመ/ ሠራዊት ጋር ወደ አፋር እያስዘመቱ በዚያው እንዲቀሩ ያደርጉም እንደነበረ ሁሉ ይተረካል፡፡

ከዚህ በላይ በወፍ በረር የታሪክ ቅኝት ለማየት የሞከርነው በአማራ /ኦርቶዶክስ ክርስትና/ ተከታዩ መንግሥት እና በይፋት እስላሞች መካከል የተተከለው ግጭት በይኩኖ አምላክ (እ.አ.አ 1270-1285) ዘመነ መንግሥት ጀምሮ፣ በተወላጆቹ በየአግባባ

ጽዮን ሥመ መንግሥቱ ሰለሞን (እ.ኤ፣አ 1285-1294)፣ በእነ ጽንፈ አርድ፣ ሕዝበ አሰግድ፣ ቅድመ አሰግድ፣ ዣን አሰግድ እና ባህር አሰግድ የአንድ አንድ ዓመት የዙር ንግሥና ዘመነ መንግሥት (እ.ኤ.አ 1294-1299)፣ በውድም አርድ (እ.ኤ.አ 1299-1314)፣ በአምደ ጽዮን (1307-1337)፣ በአፄ ሰይፈ አርዕድ (እ.አ.አ.1344-171)፣ በአፄ ቴዎድሮስ (እ.አ.አ.1412-1413)፣ በአፄ ይሥሐቅ (እ.አ.አ.1414-1429)፣ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1434-1468)፣ በአፄ በዕደማርያም (1461-1471) በአፄ እስክንድር (1468-1484)፣ በአፄ ናኦድ (1488-1500)፣ በአፄ ልብነ ድንግል (እ.ኤ.አ.1508-1540)፣ በአፄ ገላውዴዎስ (1533-1551)፣ በአፄ ሚናስ (1559-1563)፣ በአፄ ሠርፀ ድንግል (1573-1585)፣ በአፄ ሱስንዮስ (1597-1625)፣ በአፄ ፋሲል (1632-1667)፣ ዳግማዊ ኢያሱ (1682-1706)፣ በአቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ (እ.አ.አ.1672-1705-1705)፣ በስብስቴ (እ.አ.አ.1705-1720)፣ ዓብየ (እ.አ.አ.1720-1745)፣ በአምኃየሱስ (እ.አ.አ.1745-1775)፣ በመርድ አዝማች አስፋ ወሰን (እ.አ.አ.1775-1708)፣ በራስ ወሰን ሰገድ (እ.አ.አ.1808-1831)፣ በሣህለ ሥላሴ (እ.አ.አ.1831-1844)፣ ኃይለ መለኮት (እ.አ.አ. 1844-1855)፣ በአፄ ቴዎድሮስ (1847-1860)፣ አፄ ተክለጊዮርጊስ (1860-1863)፣ አፄ ዮሐንስ (1864-1881)፣ አፄ ምኒልክ (በሸዋ ንጉሥነት (1857-1882) እና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት (1882-1905)፣ በአቤቶ ኢያሱ (1901-1909)፣ በንግሥት ዘውዲቱ (1909-1922)፣ በአፄ ኃይለሥላሴ (1923-1966)፣ በደርግ (1967-1983) ዘመነ መንግሥታት ሁሉ መዝለቁን እና አሁንም መቀጠሉን እንገነዘባለን ዓለማየሁ (2006)፣ ጌታቸው (2003) እና (1997)፣ ይልማ (1999)፣ Tadesse (1972 ፡ ተክለፃድቅ (1982)፣ stiz (1970:5-6፣ Mordechai (1968፡ 144፣ Ahmed 1997፡ 138-149) ፡፡

ከዚህ በላይ እንደማሳያ ከተጠቀሱትም ነጋሢዎች ዘመነ መንግሥታት ዘመናት መካከል በተለይ ከአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ድረስ ክርስቲያኖቹ ነገሥታት የአፋር ሱልጣኖችን በተደጋጋሚ ዘመቻ ለማስገበር ይጥሩ ስለነበር የሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት መቆራቆስና ግጭት የበዛበት ነበር (ይልማ 1999፡1-18) ፡፡ መቆራቆሱ፣ ግጭቱ እና ጦርነቱም አንድ ጊዜ በረድ ሌላ ጊዜ በርደድ እያለ ዘልቋል ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በደገኛው አማራ ማለትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታይ ሕዝብ እና መንግሥት እንዲሁም በቆለኛው የእስልምና ተከታይ ሕዝብ እና መንግሥት መካከል ረዥምም ዘመን የፈጀ

ኃይማኖታዊ ግጭትና ጦርነት ሲካሄድ መኖሩን መረዳት ይቻላል (ተክለፃድቅ 1965፡34-71፣ Tadesse (1972) ፣ ይልማ (1999) ፣ ዓለማየሁ (2006) ።

ለአብነትም ከላይ በተጠቀሱት ነገሥታት ዘመነ መንግሥታት ውስጥ የተፈፀሙ አንዳንድ ታሪካዊ ክስተቶችን አለፍ አለፍ ብለን በግጭቱ አኳኋን ማመላከቻነት እንመልከት።

ከአፄ አምደ ጽዮን (1307-1337) ዘመነ መንግሥት እስከ ናዖድ (1488-1500) ዘመነ መንገሥት ድረስ የነበረውም ዋናው ጦርነት ከአፋር ጋር እንደነበር ይታወሳል (ይልማ 1999፣10) ።

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻና አካፋይም ያኔ ይፋት ተብሎ በጥቅሉ በሚጠራው አካባቢ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች በየጊዜው ይዋጉ፤ እየተዋጉም በተቆጣጠሩት አካባቢ ላይ ሰራዊትና ሕዝብ ያሰፈሩ እንደነበር እና አካባቢው ላይ ይራኮቱ እንደነበር ተፅፏል (Bairu ፣ 1987፡47፣ ይልማ 1999) ።

ይህ ቀወትም ሆነ ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ይካተቱበት የነበረው እና ያኔ ይፋት በሚል ጥቅል ስም ይጠራ የነበረው አካባቢ ረዘም ላለ ዘመን ከግብፅ መንግሥት ጋር ቀረቤታ ፈጥሮ ስለነበርም በሚደረግለት እገዛ ምክንያት እራሱን ከሌላው የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት አግልሎ በራሱ ሱልጣኖች ይመራ እንደነበር፣ በዚህም ምክንያት ከደገኛዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥታትም ጋር ሚዛኑን ለመጠበቅና ኃይሉን ለማስቀጠል ትግልና ፉክክር ያደርግ እንደነበርም ሁሉ ይታወሳል (ያዕቆብ፣ 2000፡ 25-45) ።

በተለይም የከረዩ ጎሳዎች ይፋትን ዋነኛው ወደ ሰሜን መተላለፊያ እና መዝለቂያ ክፍት በራቸው ለማድረግ በቆረጡበት እና በተቆጣጠሩበት፣ እንደገናም በአማሮቹ በተገፉበት፣ አንዳንድ ጊዜም በተደራደሩበት ወቅት ሁሉ አፋሮች ወደ ላይኛው የይፋት ክፍል እንዳይወጡና በአውሳ አካባቢ ብቻ እንዲወሰኑ የማድረግ ጥረቶች እንደነበሩ፣ ኋላ ላይ ግን አማሮቹ ሠራዊት አደርጅተው እና ጉልበት አበርትተው እንደገና ከረዩዎቹን ከይፋት ገፍተው ለማስወጣት ቢቻላቸውም ከአፋሮቹ ጋር በቀጥታ እንዳፋጠጣቸውም ጭምር ሁሉ ይተረካል። ይህ ደግሞ የመንግሥታዊው አገር ወይም ደገኛው በተለይም አማርኛ ተናጋሪውና እና አፋሩ ሕዝብ በስፋት ይገናኙ ዘንድ በር እንደከፈተ እና እያደርም አፋሮቹ የክርስቲያኑ መንግሥት ገባሮች እንዲሆኑ ማድረጉ ሁሉ ተተርኳል (Bairu፣ 1987፡ 289)።

በጥቅሉ ሲታይ ይህ የአማሮች ከአፋሮች ጋር በጉርብትና የመስፈር ሁኔታ ከማዕከላዊ መንግሥት ጥንካሬና ድክመት ጋር ሁሉ የተያያዘ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያናዊው መንግሥት አንዳንድ ጊዜ እየተጠናከረ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እየተዳከመም መሄዱን፣ በሌላ በኩልም ደግሞ የአፋር እና ሌሎቹ የምሥራቅ ኢትዮጵያ እስላም መሪዎችም አንድ ጊዜ እየደከሙ ሌላ ጊዜ እየተጠናከሩ የሄዱባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩ ታሪካዊ ማስረጃዎች ያመለክታሉ (ያዕቆብ፣ 2000፣ ጌታቸው፣ 1997፣ ዓለሙ፣ 2005፣ ይልማ 1999፣ Tadesse ፣ 1972፣ ተክለፃድቅ፣ 1965) ፡፡

ለአማራው /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኑ/ መንግሥት መዳከም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ክስተቶችም መካከል አንዱ የይፋት ሥርወ-መንግሥት ተቀፅላ የሆኑት እና ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የተነሱት በተለምዶ ግራኝ አህመድ፣ በተፀውዖ ስማቸው አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ በሚል የሚታወቁት በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ልብነ ድንግል ይመራ የነበረውን የክርስቲያኑን መንግሥት ወደ ሰሜን መግፋት መቻላቸው፣ ከዚያም ጋር በተያያዘ ከእርሳቸውም ኋላ እግር በእግር ወደ ሰሜን በገሰገሱት ኦሮሞዎች መስፋፋት ምክንያት የአማራው /የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት ተከታዩ ሕዝብ/ ግዛት መጥበቡና ሕዝቡም ከቀደምት ይዞታዎቹ እየለቀቀ፣ ያልሸሸውም እየተደባለቀ እና እየተዋሃደ፣ ማንነቱም እየተለወጠ መሄዱ ነው፡፡ ሂደቱም እንደሚከተለው መሆኑ ይታወሳል፡፡

አፄ ልብነ ድንግል እና አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ (ግራኝ አህመድ) እ.ኤ.አ ከ1521-1522 ዓ.ም አንዳንድ ጊዜ አፄ ልብነ ድንግል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ እያሸነፉ ለአንድ ዓመት ያህል ሲሞካከሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት (በዛሬው ደብረ ዘይት እና ዱከም ከተማ መሃል ሳይሆን አይቀርም ተብሎ በታሪክ ፀሐፊዎች በሚገመተው ሥፍራ) ለአንድ ዓመት ያህል የዘለቀው ፍልሚያ በአህመድ ቤን ኢብራሂም አልቀዚ አሸናፊነት ተጠናቆ፣ አፄ ልብነ ድንግል ወደ ሰሜን ካፈገፈጉ በኋላ ሸዋ የክርስቲያናዊው መንበረ መንግሥት ሆኖ መቀጠል አልቻለም፡፡ ምክንያቱም የአፋሮች እና የሱማሌዎች መሪ የነበሩት አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ (ግራኝ አህመድ) በ1521 ዓ.ም. ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የተውጣጣ ሠራዊታቸውን ይዘው በዓፄ ልብነ ድንግል መንግሥት ላይ ባወጁት ጦርነት እና በተቀዳጁት ድል ላይ እየተረማመዱ እና እየገፉ ከደቡባዊ ምሥራቅ ጀምረው ወደ

ሰሜን በመግፋት ትግራይ ድረስ ዘልቀዋል። አፄ ልብነ ድንግልም በ1532 ዓ.ም. ደብረ ዳሞ ላይ አርፈዋል።

በታሪክ እንደሚታወቀው አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ (ግራኝ አህመድ) አፄ ልብነ ድንግልን አሸንፈው ወደ ትግራይ ካስፈገፈጓቸው በኋላ ንጉሡ ደብረ ዳሞ ላይ ቢያልፉም (በተፈጥሮ ቢሞቱም) ጦርነቱ ወራሴ መንግሥታቸው በነበሩት ልጃቸው አፄ ገላውዴዎስ እና በባለቤታቸው ንግሥት ሰብለ ወንጌል እና በተከታዮቻቸው እንዲሁም ንጉሡ በሕይወት ሳሉ በጋበዟቸው ፖርቱጌዞች አማካኝነት ቀጥሎ በመጨረሻ ኢብን ኢብራሂም አህመድ አልቃዚ ጎንደር ዘንተራ ላይ የካቲት 28 ቀን 1535 ድል ተገድለዋል፣ ሠራዊታቸውም ፈርሷል (ይልማ 1999፡193-207)። እዚህም ላይ የፖርቱጌዞቹ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በዘመኑ የነበረውን የፖርቱጌዞች የክርስትና እና የቱርኮች የእስልምና ኃይማኖት አስፋፊነት እና መከታነት ያስከተለነቱን፣ ጦርነቱም በኃይማኖት ልዩነት ተረክ ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ የኢትዮጵያም የክርስቲያን እና የእስላም ግጭት ዓለም አቀፍ ባህርይ እየያዘ መሄዱን ያመለክተናል።

በአህመድ ቤን ኢብራሂም (ግራኝ አህመድ) ዘመቻ ላይ የተከፈተውም አፀፋ ዘመቻ እንደገና ወደ ደቡብ ግንባር እንዲቀለበስ መደረጉ ይታወሳል (Levine 1975: 5-6)። በዚህም ዘመቻ የሸዋን አምባማ ምድር እና ዙሪያዎች መልሶ በማዕከላዊ መንግሥቱ እጅ እና ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ከአፋር እና ከምሥራቅ ኢትዮጵያ እስላማዊ ሱልጣኔቶች ጋር ትግሉ ቀጥሎ ቆይቷል። እነዚህም ትግሎች ሁሉ ታዲያ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች የሆኑትን ድንበርተኞቹን ቀወቶችና ሰሙሮቢ ገለአሎዎች ሳይነኩ፣ ሳያሳትፉ፣ በተሳትፎውም ሂደት ሰቆቃዊ ምሬት እና የሰቆቃዊ ምሬት ትውስታ ተረክ ሳያስከትሉ እና ሳይተክሉ ያለፉ አይደሉም። ምክንያቱም ከምሥራቅ ወደ ሰሜን፣ ከሰሜንም ወደ ደቡብ የተደረጉት ዘመቻዎች መተላለፊያዎች፣ መፋለሚያዎች፣ ቂም በቀል መወጣጫዎች ከመሆን አያመልጡምና ነው። ይህም የጦርነት ዑደት ደግሞ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የፀበኝነትን እና የተጋዳይነትን፣ በጥቅሉም የጦረኝነትን ባህል ሳይተክልባቸው የቀረ እና ያለፈ አይመስልም።

ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እና ቀጥሎም እንደሚታከለው የቀወት ወረዳ አማሮችና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ታሪካዊ የግጭት እና የሰላም ግንኙነት እና ሁኔታ ማየት የሚቻለው ከአጠቃላዩ የአማራ /ክርስቲያን/ እና አፋር እንዲሁም ሌሎች እስላም ሕዝቦች ግንኙነት አኳያ ነው። በመሆኑም በጽሑፍ ታሪክ

የሚታወቀው የአማሮች እና አፋሮች በኃይማኖት ተረክ ልዩነት ላይ የተመሰረተ እና በከፍተኛ ደረጃ የሚታወቅ ጦርነት የተካሄደው በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለመሆኑ በስፋት ተወስቷል (ዓለማየሁ፣ 2006) ፣ ላጵሶ ፣ 1982)፣ ተክለፃድቅ ፣ 1965)፣ Mordechai ፣ 1980: 45) ፡፡

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ክርስቲያናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት እና እስላማዊው የይፋት ወላስማ እና የአፋር ሥርወ-መንግሥታት ተከታዮች ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ እና የቆዩ ቁርሾዎችን እና ቂም በቀሎችን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሱበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ሙስሊሞቹ ቅዱስ ጦርነት /ጂሃድ/ የሚሉትን ክርስቲያኖች ደግሞ የእስላም /የግራኝ/ ወረራ የሚሉትን ጦርነት ተፋልመዋል፡፡ የዚህ ጦርነት የመጀመሪያው ምዕራፍ የተካሄደውም በአፋር ምድር በተለይም ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ እና ዙሪያ ገባው ስለነበር የጦርነቱ ክስተት የፈጠራቸው አጋጣሚዎች እስከዛሬ ድረስ የግራኝ ጦርነት በሚል በቃል የሚተረኩ ናቸው፡፡

ቃል ተረኩ አህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ (ግራኝ አህመድ) ቁመታቸው ሰባት ክንድ እንደነበረ፣ ለፈረሳቸው ማሰሪያ ትላልቅ የተጋደሙ ድንጋዮችን ብዙም ሳይደክሙ በግራ እጃቸው ፈንቀል አድርገው ያቆሙ እንደነበረ፣ ደረታቸው እጅግ ሰፊ፣ ጉልበታቸው የሰይጣን እንደነበረ፣ በክርስቲያን መንግሥት ላይ ያስነሳቸውም እግዚአብሔር እንደሆነ፣ እግዚአብሔርም ያስነሳቸው የክርስቲያንን መንግሥታት እብሪት ስለበዛ፣ በተለይም አፄ ልብነ ድንግል ያባቶቻቸውን የጦር አበጋዞች "ያባቴ ሙክቶች" እያሉ ይዘልፉ እና ያዋርዱ፣ ያስሩ፣ ይገድሉም ስለነበር፣ ቦካን ከሚባለው ከተማቸውም ሆነው ግንባቸውን በጦር እየወጉ፣ እግዚአብሔርንም ጦር አውርድ እያሉ ይማፀኑ፣ ምድርንም በአለንጋ ይጠበጥቡ ስለነበር፣ ነዳያንንም ያስርህራሄ ይፈጁ ስለነበር፣ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ልማድ ውጪ ትምባሆ ይምጉ እንደነበር፣ ከክርስቲያናዊ ልማዱም አፈንግጠው ከአንድ በላይም ሚስቶች እንደነበሯቸው፣ ቁባቶችም ይቆብቱ እንደነበር እና ይህን ሁሉ የሚያየው እግዚአብሔርም ተቆጥቶ እርሳቸውን ለማጥፋት የላካቸው እንደሆኑ ሁሉ ተደርጎ ይተረካል፡፡

በጽሑፍ ታሪኩም በኩል ስንሄድ አፄ ልብነ ድንግል እና አህመድ ቤን ኢብራሂም እየተዋጉም ሳሉ ይወራረፉም ሁሉ እንደነበር ተጽፎ እናገኛለን፡፡ አንድ አስረጅ እንመልከት፡፡ አህመድ ቤን ኢብራሂም በ1531 ብዙ ድሎች አግኝቶ ስለነበር ይህን ድል ለመቀልበስ የአፄ ልብነ ድንግል የጎጃም ነጋሽ የነበሩት እና በዘመኑም የመጨረሻው

ወሳኝ የጦር ጥበበኛ ይባሉ የነበሩት ወሰን ሰገድ ለአህመድ ቤን ኢብራሂም ምክር አዘል ደብዳቤ ሲፅፉላቸው ድል ዘላለማዊ እንዳልሆነች በሽምብራ ኩሬ፣ በአንፃኪያ፣ በዛሪ አካባቢዎች ያገኙት ድል ሊበቃቸው እንደሚገባ እና የዘረፉትን ይዘው ወደ ኋላ እንዲመለሱ አለዚያ ግን የወንድማቸው ገዳይ የሆኑት ወሰን ሰገድ እንደመጡባቸው እና እንደማይተርፏቸውም አድርገው ይልኩባቸዋል፡፡ አህመድ ቤን ኢብራሂምም በበኩላቸው "እኛ ባሮችን አንፈራቸውም፣ እናውቃቸዋለንና፡፡ ግን አንተ ነኝ የምትለውን ከሆንክ-በአገርህ ምድር ላይ ነውና ያለነው-እስቲ ስታስወጣን እንይህ" የሚል መልስ ይልኩላቸዋል፡፡ ወሰን ሰገድም ሞግደው ከልጅነት እስከ አረጋዊነት በተካኑት ውጊያ ላይ እንዳሉ መሞታቸው ተዘግቧል (ዓለማየሁ 2006፡127-128)፡፡ አሁንም በዚህ የመልዕክት ልውውጥ ውስጥ የምናየው የ "ወንድነት" እና የማንነት፣ የእኔ እበልጣለሁ፣ አታክለኝም ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ክርስቲያናዊው ኃይል አህመድ ቤን ኢብራሂምን ድል ከነሳቸው በኋላ ተከታታይ ዘመቻዎችን ወደ ደቡብ አካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት የአፄ ልብነ ድንግል ወራሴ መንግሥት የነበሩት አፄ ገላውዴውስም አህመድ ቤን ኢብራሂምን አልቃዚ (ግራኝ አህመድ) ጎንደር ዘንተራ ላይ ከገደሏቸውም በኋላ ወደ ሸዋ ተመልሰው ከእነ ኑር ኢብን እልሙጃሂድ እና ሌሎችም የእስላማዊ ኃይል መሪዎች ጋር ውጊያ መቀጠላቸው፣ የርሳቸውም ተከታዮች በዚሁ የውርስ ጦርነት መዝለቃቸው አልቀረም፡፡

በአፄ ገላውዴዎስ (1533-1551) ፣ በአፄ ሚናስ (1559-1563) ፣ በአፄ ሰርፀ ድንግል (1573-1585) እና በእስላማዊው የአህመድ ቤን ኢብራሂም ተከታዮች በእነ ኑር ኢብን ኢብራሂም መካከል (እነዚህም የአፋር ሱልጣኔት አስቀጣዮች የሆኑ መንበራቸውንም ከክርስቲያናዊው መንግሥት ጥቃት ለማራቅ ሲሉ ከአፋር ወደ ሐረር ያዛወሩ ወገኖች መካከል) ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ ጦርነቱም የአፄ ገላውዴዎስን ሕይወት ጭምር 1559 ላይ በልቷል (ዓለማየሁ 2006፡146-167) ፡፡

በአፄ ሰርፀ ድንግል (1573-1585) ዘመነ መንግሥትም የአፋሩ ሱልጣን ድንበርተኞቻቸውን ክርስቲያኖች ወግተዋል፡፡ በአፀፋውም ደግሞ ዐፄ ሰርፀ ድንግል ዘምተው ለአያሌ ምዕተ ዓመታት በንጉሠ ነገሥታዊው አገር ላይ ሥጋት ሆነው የቆዩትን እስላማዊ ኃይሎች ሥጋት ከማይሆኑበት ደረጃ አድርሰዋቸው እንደነበር ሁሉ ተጽፏል (ዓለማየሁ 2006፡ 163፣ ዓለሙ 2005፡65) ፡፡

በተለይም ከአፄ ገላውዴዎስ (1533-1551) ኅልፈተ ሕይወት በኋላ የሸዋ የመንግሥት መቀመጫነት ወደ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም ጣና ሐይቅ ዳርቻ እና ጎንደር እንዳፈገፈገ የቀየው የአፋሮችን እና የኦሮሞዎችን የሥልጣን ተፎካካሪነት ኃይል መቋቋም ስለተሳነው መሆኑ አይዘነጋም፡፡

በአማራ /ክርስቲያን/ መንግሥት ማንሰራራቱ ሂደት ዝና ከነበራቸው ነገሥታት አንዱ የሆኑት ሱስንዮስም (1597-1625) በይፋት ምድር ያስቀመጡትን ሹማቸውን የአፋሩ ሱልጣን ስላጠቁባቸው ነባሩን የማስገበር ወግ ልማድ ተከትለው ወደ ይፋት ዘምተው ጥቃት ሰንዛሪዎቹን ሙስሊሞች መቅጣታቸው ተዘግቧል (ዓለሙ፣ 2005፣ 35፣75) ፡፡

በዚሁ ተከታታይ የዘመናት ውጊያ እና መልሶ ግዛት የማስፋፋት እና አገር የማቅናት ዘመቻ ሂደት አማርኛ ተናጋሪው ሸዋም እንደገና በተለይ ከመንዝ አጋንቻ በተነሱት አቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ (1696-1703) አማካኝነት መልሶ በማንሰራራት ቀድሞ የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ግዛቶች የነበሩትን እና በመሃል አፈንግጠው የነበሩትን አካባቢዎች በየተራ መልሰው መቆጣጠራቸውን እና መስፈር መቻላቸውን፣ በዚሁም መሰረት ወደ ሰሜን እስከ ቆቦ፣ በምሥራቅ እስከ መንግሥት እና እስከ ሮቢ በደቡብ እስከ ጣርማ በር እና በታች በኩልም እስከ አዋዲ አቅንተው የመንዝ ዘመዶቻቸውን መምራት እና መትከላቸውንም እናነባለን (ላጵሶ 1982፡ 242-249፣ stiz, 1970:5-6)፣ Bairu (1987)፡፡ ለአብነትም ይሄ ጥናት የሚካሄድበት አካባቢ እና ዙሪያ ገባው እንዴት ወደ አንድነት እንደገባ እና እንደገበረ ለዳግም የተጠናከረ ማዕከላዊ መንግሥት ምስረታ መነሻም እንደሆነ የሚከተለውን አስረጅ ማስታወሱ በቂ ይሆናል፡፡

ከአህመድ ቤን ኢብራሂም አልቃዚ ወረራ በኋላ የመንግሥቱ መቀመጫ ወደ ጎንደር በመዛወሩ ምክንያት እንኳንስ ሸዋ የሚባለው ክፍለ ሀገር መንዝ[18] ራሱ በብዙ ባላባቶች ተቃራጭነት ተይዞ ይገዛ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት አንዱ የመንዝ ክፍል የሆነው አንፆኪያ በዘሚካኤል፣ ኤፍራታ በወልደ ገብርኤል፣ ግድም በለታ፣ ከፊሉ

---

[18] ይህ በጥቅሉ መንዝ በመባል የሚታወቀው አካባቢ መልክዓ ምድሩ የተወሰነ ቢሆንም በአገላለፅ ረገድ ግን ይሰፋልም ይጠባልም፡፡ የሚሰፋው በውጫዊ አገላለፁ ሲሆን የሚጠበው ደግሞ በውስጣዊ አገላለፁ ነው፡፡ መንዝ በሚለው ክፍል ከሚካተቱት ወረዳዎች መጠሪያዎች መካከልም ማማ ምድር፣ ላሎ ምድር፣ ጌራ ምድር የተሰኙት መጠሪያዎቻቸውን ያገኙት ከእቅኚዎቹ ሥሞች ነው፡፡ በዚህም መሰረት እዚህ የተጠቀሱት ማማ፣ ላሎ፣ ጌራ የባላባቶች እና ማዕረግተኛ ሥሞች ናቸው፡፡ ባላባቶቹ እና ማዕረግተኞቹም ኦሮሞዎች ስለመሆናቸው በጥናት ተረጋግጧል (Levine,1972፣ ዓለሙ፣ 1998)፡፡ በሌላ በኩል ግን ከላይ እንደተጠቆመው ይፋትም አንዳንድ ጊዜ በመንዝ ውስጥ ተጠቃሎ እንደሚገለፅ ከላይ በተገለፀው የባላባቶቹ አገዛዝ ዝርዝራ መረዳት ይቻላል፡፡

መንዝ በማማ፣ ሌላው ክፍል በላሎ፣ ግሼ በአውሳብዮስ፣ ዶባ በጌታቸው፣ ደብብ በፀጋ፣ መራቤቴ በኮራን እና በወልዱ፣ ሞረት በጥዱ፣ ተጉለት በይገባዋል፣ ወግዳ በሀርያቆስ ይገዙ ነበር (ዓለማየሁ 2006፣ 242-243)። የእነዚህንም ባላባቶች ሥም አሚሻሾች እስከዛሬ ድረስ የአካባቢዎቹ እውቅ ሰዎች ሲሞቱ በየሙሾው ሐረግ እየመዘዙ እና እያጣቀሱ፣ ሟቾች የባላባት ልጅነታቸውንና ወገንነታቸውን በማስታወስ ለማላቀሻነት ይጠቀሙበታል።

ከላይ የተዘረዘሩት ባላባቶች ሥሞች ከሚነሱበት የለቅሶ ግጥምም መረዳት የሚቻለው ቀወቶች አማራ የሚሉት የተለየ ዘር ሳይሆን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን መሆኑን ከግድሙ ባላባት ለታ መሆን እንገነዘባለን። ምክንያቱም "ለታ" በዛሬው ዘመን አፈራረጅ ኦሮሞነትን ጠቃሽ እና ጠቋሚ ነው። ስለዚህም በተለይ በሸዋ አማራነት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት ተከታይነት/ የተለያዬ ዝርያ ያላቸው ሰዎች የተወራረሱበት፣ የተቀላቀሉበት እና የተዋሃዱበት ባህል ሆኖ እናገኘዋለን።

በመሰረቱ የሸዋ አንድነት እና መንግሥታዊ አገርነት ምሥረታ ሂደት ብርታትም ድክመትም የተፈራረቁበት ነበር ማለት ይቻላል። የቀወቶችም አንድ ጊዜ ወደ ምዕራብ ሌላ ጊዜ ወደ ምሥራቅ መነቃነቅ ከዚሁ ሂደት ጋር ይያያዛል፣ ይሳሳባል። ይኸው የሸዋ ማንሰራራት ሂደትም ከአቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ በኋላም በተወላጅ ተከታዮቹ ስብስቴ (1705-1720)፣ አምኃየሱስ (1743-1774)፣ አስፋወሰን (1774-1708)፣ ወሰን ሰገድ (1808-1812)፣ ሣህለ ሥላሴ (1813-1847)፣ በአፄ ምኒልክ (1882-1905)፣ በአቤቶ ኢያሱ (እ.ኤ.አ 1901-1909)፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ (1923-1966) እንዲሁም በደርግ (1966-1983) እና በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ዘመነ መንግሥታት ሁሉ መዝለቁን፣ በአማሮች እና በአፋሮችም መካከል ያለው ግጭት አለመቆሙን እናያለን፣ እናስታውሳለን (አጥናፍ ሰገድ 2006፣71)፣ ጳውሎስ 2003:27፣ ዓለማየሁ 2006፣ Mordechai (1968 ፡ 144)፣ Greenfield (1965፡ 171-172)።

እዚህ ላይ የይፋቱ ገገር መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን እና የሞረቱ ገገር ለአዝማሪ አቀብለው ያስዘፈኑት ወይም የተላላኩት ነው የሚባለውን እና እስከ ዛሬም የሚባለውን ውስጠ-ወይራ የግጥም ምልልስ አስታውሶ ማለፍ ተገቢ ይመስለኛል። የይፋቱ ገገር መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ሞረትን ለመጠቅለል በከጀላቸው፡-

ለሞፈር ለቀንበር የሚሆነኝን፣
ሳልቆርጠው አልቀርም ዘንድሮ ጥዱን።

ያስብላሉ። ይህን የሰሙት እና መልዕክቱንም የተረዱት ጥዱ ደግሞ መልሱን ሲሰጡ፡-

አስፋ ወሰን ይፋት ጠንክረው ይረሱ፣

ሞረት ጥዷል ብለው ከሚመላለሱ።

አስባሉ ይባላል። አስፋ ወሰን ወደ ሞረት ከሚያልሙ እና ከሚነቃነቁ ይልቅ ይፋት ላይ ጠንክረው እንዲቆሙ፣ እንዲያቀኑ እና እንዲያለሙ በመጠቆም።

አሁንም ስለ ሣህለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሰማሁትን የአማሮች እና የአፋሮች ግጭት ሁኔታ አንድ ግጥማዊ አስረጅ ጠቅሼ የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት ታሪካዊነት ጠቁሜ አልፋለሁ። በሸዋ "ና ገለሌ" የሚባለውን የጀግንነት ሙገሳ ግጥም ያፈለቁት እና ያኸዘቡት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ናቸው ይባላል። ንጉሡ በወጣትነት የንግሥና ዘመናቸው እስከ አዋሽ ማዶ ዘልቀው መሐመዳውያን ተቃናቃኞቻቸውን አጥቅተው በተመለሱበት ወቅት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ገጥመው ያስፎከሩት ነው ይባላል። ግጥሙ ባለ ሁለት፣ ሁለት ስንኝ መንቶ ነው። እነሆ (አቶ ከተማ አይሻር፣ 15/01/2003)።

ና ገለሌ! ና ገለሌ!፣

አዋሽ ማዶ ከቁልቁለቱ፣

ደፋው ባናቱ፣

አዋሽ ማዶ ዱብ ዱብ ይላል፣

ያ ልጅ ይሆናል።

የጊዜ ቅደም ተከተሉን እየጠበቅን ባይሆንም አሁንም በሰበር ሌሎች የአማራ እና የአፋር ግጭት አረጋጋጭ አብነቶችን እንመልከት። የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች ግጭት ተረካዊ መሆኑን በማሳያዎች ለማስረገጥ። አፄ ቴዎድሮስም በዘመናቸው "እስላምና አማራን ባንድ ሰደቃ አበላለሁ" ብለው ዝተው እንዳበሉ፣ በዚሁም አድራጎታቸው ምክንያት ከወሎ እስከ አንኮበር ጥግ የነበሩ ሙስሊሞች "የቴዎድሮስን ፊት አታሳየን" እያሉ ፈጣሪያቸውን ይማፀኑ እንደነበር፣ አፄ ቴዎድሮስም በእስልምና ተከታዮች እና በእርሳቸው መካከል ያለው ልዩነት እና ቂም ከነቢዩ መሐመድ ጀምሮ የነበረ ነው ብለው ያስቡ እንደነበር ተፅፏል (ተስፋዬ፣ 2004፡ 56) ።

አፄ ዮሐንስም በዘመነ መንግሥታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥታዊ አንድነት ሊፈጠር የሚችለው እና የሚፀናው አገሪቱ አንድ ኃይማኖት ብቻ ስትከተል ነው የሚል እምነት ነበራቸው (ዓለማየሁ 2006፡ 292-293)። በነገራችን ላይ አፄ ዮሐንስ ከሱዳን

ማህዲስቶችም ጋር በተወዛገቡበት እና ወደ መተማ ጦርነት ከመግባታቸው እና ሕይወታቸውንም ከማጣታቸው በፊት የሱዳኑ ካሊፍ አብዱላህ "መስቀልህን አቃጥለህ እንደኔ እስላም ከሆንክ የሰላም ውል እናደርጋለን፡፡ ሰላም ፈላጊ ከሆንክ ከሀገርህ የያዝካቸውን እስረኞች ወንዶችና ሴቶች፣ ሽማግሌና ወጣት ባሮች በሙሉ ትለቃለህ፡፡ ይህ ከሆነ እኔም በእጄ የሚገኙትን የአበሻ እስረኞች እለቃለሁ፡፡ ይህን የማትቀበል ከሆነ በጦር ሜዳ እንተያያለን፡፡" የሚል መልዕክት ያለው ደብዳቤ ልከላቸው እንደነበር ተፅፏል (ዓለማየሁ፣ 2006፣ 306)፡፡ አፄ ዮሐንስ የኃይማኖት አንድነት ለአገር አንድነት ይበጃል የሚል እምነት ስለነበራቸው በአገሪቱም ውስጥ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮችን ክርስትና እያስነሱ ሹመትና ማዕረግ ይሰጡ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህንንም ከእነ ንጉሥ ሚካኤል (ኃይማኖታቸውን ከእስልምና ወደ ክርስትና ለውጠው የወሎ ገገርነታቸው የፀደቀላቸው) ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ በነገራችን ላይ አፄ ዮሐንስ እንኳንስ በእስልምና ላይ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና አንጃዎች መካከልም ያለውን ልዩነት ለማጥፋት ቆርጠው፣ አንድ ዓይነት ኃይማኖት እና ልማድ ለማስፈን ይተጉ እንደነበር፣ ይህ ሐሳባቸው እና እቅዳቸው እንዳይሳካ የሚያደርጉትንም ለአካላዊ ቅጣት ማለትም ከንፈር እና አፍንጫ ፉነና እና መሰል ቅጣቶች ይዳርጓቸው እንደነበር፣ በዚህም የተነሳ በተለይም እስላሞች ሥጋታቸው ሲያይል ወደ ሱዳን ይሰደዱ እንደነበር አፈ ታሪክም ጽሑፍ ታሪክም ይነግረናል (ዓለማየሁ 2006፣ 294)፡፡

አፄ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ እና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ዘመንም የማዕከላዊ እና ደቡባዊ አፋሮች ከአማሮች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከፊል ሰላም፣ ከፊል ግጭት የነበረበት መሆኑ ይታወሳል፡፡ ምክንያቱም እ.ኤ.አ 1874 አፋሮች በሙዚንገር ፓሻ የተመራውን እና በማዕከላዊ አፋር በኩል ወደ መሃል ኢትዮጵያ ለመግባት የሞከረውን የግብፅ ወራሪ ጦር የአውሳ አካባቢ አፋሮች በመምታታቸው ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጋር መልካም ግንኙነት እንደነበራቸው እና ከአውሳ በረሃም ወደ ላይ እየዘለቁ መስፈር ችለው እንደነበር፣ ኋላ ላይ ግን የአውሳ ሱልጣን ከኢጣሊያን ጋር በማበራቸው የምልኒክ ጦር እ.ኤ.አ በ1895 አውሳን ወሮ እንዳስገበረ፣ ሱልጣኑንም እንደያዛቸው እና ወደ አዲስ አበባ እንዳመጣቸው፣ እዚሁም እንዳረፉ፣ ሌላ ሱልጣንም ተተክቶ ለማዕከላዊ መንግሥት እንዳደረ ተፅፏል (Greenfield, 1965፡ 171-172)፡፡

በዚሁ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሐረር በግብፅ መንግሥት በሚደገፍ የእስላም ኤሚር እጅ ስለነበረ፣ የወቅቱ መሪ የነበሩት አሚር አብዱላሂ ለማዕከላዊው

መንግሥት እንዲያድሩ እና እንዲገብሩ ተጠይቀው ለአፄ ምኒልክ በላኩት ገፀ በረከት እና መልዕክት የእስልምናን ተፎካካሪነት በብርቱ አሳይተዋል። በዚሁም መሰረት አሚሩ ለንጉሠ ነገሥቱ በላኩት መልዕክት "በሰለምክ ጊዜ ለለቃነትህን ልቀበል እችላለሁ" ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ የሰጡት ምላሽ ደግሞ "ወደ ሐረር እመጣለሁ፣ መስጊዱንም በቤተክርስቲያን እተካዋለሁ፣ ጠብቀኝ !"[19] የሚል ነበር (Greenfield 1965፡ 77) ፡፡

በልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት እና ኋላም በተለይ እ.ኤ.አ. ከ1912-1935 ድረስ የይፋት አማሮች፣ አፋሮች እና ኦሮሞዎች እርስበርሳቸው ከመጋጨታቸውም በላይ ከማዕከላዊ መንግሥቱም ጋር ሰላም ስላልነበራቸው ልጅ ኢያሱ በ1905 ወደ አፋሮች ዘምተው እንደነበር፣ ነገር ግን የልጅ ኢያሱ ዘመቻ ደም መፋሰስን ያላስከተለ ይልቁንም የጋብቻ ትስስርን ያስከተለ እንደነበር አጥናፍ ሰገድ (2006፣71) እና Ahmed (1997፡138-140) አስፍረዋል። ለነገሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበሩት የኢትዮጵያ ከፍተኛዎቹ ገገር መደቦች "የዘር ጥራት" የሚባል ነገር የሚያውቁም አይመስሉም።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ክስተቶች ስናጠቃልላቸውም በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ድንበርተኞች መካከል የሚስተዋሉት ግጭቶች የተረክ ልዩነቶች የፈጠራቸው እና ከትውልድ ወደ ትውልድም እንዲሁ በተረክ ያዘለቋቸው ይመስላሉ።

ስለዚህም ከዚህ በላይ በነገሥታቱ እና ሱልጣኔቱ አድራጎት ላይ በመመሥረት የቀረበው የአማሮች /ክርስቲያኖች/ እና የሙስሊሞች ታሪካዊ ግንኙነት ቢሆንም በቅርበት የቀወትና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ታሪካዊ ግንኙነት፣ በተራዛሚም የጠቅላላው የአማሮች /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች/ እና የአፋሮች /ሙስሊሞች/ ግንኙነት ሁኔታ አመልካች ነው። ምክንያቱም በቅርበት የሚገናኙት ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ዛሬም የአፈ-ታሪክ ውርስ እና ቅርስ አራማጆች፣ በተግባርም አረጋጋጮች ሆነው ይገኛሉ። የእኔም ጥናት ከዚህ ታሪካዊ ቅኝት የሚለቅመው ፍሬ አካባቢ ተኮር ቃላዊና ጽሑፋዊ ተረኮችና ታሪኮች ውስጥ እነዚህ ሐቲቶች ያላቸውን ሚና ለማጤን ነው። ይህም የተደረገው የቀወትና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎችን ግንኙነት ለማሳየት፣ ግንኙነቱም የፈጠረውን የግጭት እና የእርቅ ባህል ለመመርመር ይቻል ዘንድ ነው።

[19] እነዚህ እና መሰል አገላለፆች ፎክ ታሪክነት ያላቸው መሆናቸውን ያጤኗል። ጽሑፍ ታሪክ በፎክ ታሪክ ጭምር የተመላነቱንም እንዲሁ።

እዚህ ላይ በቅርብ ዘመን በአካባቢው የተካሄዱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ አንዳንድ መዛግብትንም በአስረጅነት ማከል እና ከተነሳንበት የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ተኮር ግንኙነት አንፃር መመልከት ይቻላል፡፡

ዛሬ ቀወቶች እና ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በየፊናቸው ጥንት መሬቱ "የኛ ነው!"፣ "የኛ ነው!" በሚል ከሚገዳደሩበት እና ከሚጋጩበት፣ በቅርብ ርቀትም ውስጥ እየተያዩ ሰፍረው ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከል ከቀወት በኩል ሰፌ በረት፣ ደብርና ጀጎል፣ ዓባይ አጥር እና ኩሬ በረት እንዲሁም ከሰሙሮቢ ገለአሎ በኩል ደግሞ አዲሲሂጌ፣ ሐሪሐሙ፣ ሆቲመሮ፣ እና አስጋፊን ወዘተ ናቸው፡፡ በእነዚህ ውስጥ ደግሞ እጅግ ተቀራራቢ የሆኑ እንደ ዓባይ ነጌሶ፣ ኩመጉራ፣ ጉራሀራምሌ ወዘተ ኅጦችም አሉ፡፡ በዚህም መሰረት ለምሳሌ አንዱን ነጌሶ የሚባለውን እንደ አንድ ምሳሌ በመውሰድ "ነጌሶ የማን ነው?" የሚል ጥያቄ ለአካባቢው ነዋሪዎች አንስቼላቸው ነበር፡፡ መልሳቸው የቀወቶችም፣ የኤፍራታና ግድም አማሮችም፣ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችም እንደሆነ የሚጠቁም ነበር፡፡ ይሄም የሆነው ድንበሮቹ በየጊዜው ስለሚለዋወጡ ይመስላል፡፡ ኅጡ የማነው ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት ባለመቻሌም ሁኔታውን ለማጣራት ወደ አገር ግዛት ሚኒስቴር ቤተመዛግብት አምርቼ የቆዩ የአገር ግዛት ሚኒስቴር መዛግብትን (ሸዋ ማህደር) ለማየት እና ለመመርመር ሞክሬያለሁ፡፡ የተገኘውም መዝገብ ከ1940 ዓ.ም. እስከ 191957 ዓ.ም. ድረስ በተጠኚዎቹ ሕዝቦች መገኛ አካባቢ የነበረውን ገፅታ የሚጠቁም ከመንግሥት ጋር እና እርስበርሳቸውም ስለነበራቸው ግንኙነት ዓይነት እውቀት የሚጨምር ነው፡፡ በዚሁም መሰረት ከ1940 ዓ.ም. እስከ 191957 ዓ.ም. ድረስ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ለርስት መዝገብና የካርታ ዳይሬክተር፣ ለርስትና ውል ዋና ዳይሬክተር፣ ለሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ የሸዋ ጠቅላይ ግዛትም በበኩሉ ያኔ በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ ሥያሜ ይጠራ እና ይታወቅ ለነበረው የዛሬው ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች መገኛ ወይም መካተቻ ማለትም ለደብረሲና አውራጃ ግዛት ጽህፈት ቤት፣ ለመንዝና ይፋት አውራጃ ግዛት ጽህፈት ቤት፣ ለይፋትና ጥሙጋ አውራጃ ግዛት ጽህፈት ቤት፣ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ መረጃዎችን የሚጠይቁ ደብዳቤዎች ተፅፈው ወርደዋል፡፡ ለተላለፉትም መጠይቆች መረጃዎች ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ ከሸዋ ጠቅላይ ግዛትም ወደ አገር ግዛት ሚኒስቴር ወጥተዋል፡፡ እነዚያም ከአገር ግዛት ሚኒስቴር እስከ አውራጃ ግዛት የወረዱ እና የወጡ መፃፃፎች ዋነኛ ትኩረቶች አራት ነገሮች ላይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት

የመጀመሪያው በልዩ ስሙ ነጌሶ ቆላ፣ ነጌሶ ቂልጡ እና ነጌሶ ዓባይ የሚባለውን እና በዚህ ጥናት ተካታች የሆነውን ሥፍራ እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙ መሬቶችን ባለቤት እና ጥቅም ላይ አዋዋል ሁኔታ፣ ሁለተኛው ደግሞ የአካባቢውን ፀጥታ እና እርጋታ ደረጃ፣ ሦስተኛው በአካባቢው በርስትነት ባልተያዙ መሬቶች ላይ ቀላድ ስለመጣል፣ ቀላድ መጣሉም ስለሚያስገኘው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የፀጥታ ጥቅም፣ አራተኛው በአካባቢው ስለተከሰቱ ወይም ስለታዩ እንግዳ ነገሮች የሚገልፁ እና የሚዘረዝሩ ምልልሶች ነበሩ።

ከዚህ በላይ በአራት ነጥቦች የቀረቡትን ነገሮች በቅደም ተከተል እንመልከት። በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ ሥያሜ ይታወቅ በነበረው እና ዛሬ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች የሚገኙበት እና ድንበርተኞችም የሆኑበት ነጌሶ (ነጌሶ ቆላ፣ ነጌሶ ቂልጡ እና ነጌሶ ዓባይ)፣ ስለ ተናቃናቂ አርብቶ አደሮች መሬት እንዲሁም ሌሎች ሥፍራዎች መሬት ባለቤት እና ጥቅም ላይ አዋዋል የሚመለከተውን መፃፃፍ ስናጤን የሚከተለውን መልዕክት እናገኛለን። በአካባቢው በመንግሥት እጅ የሚገኝ መሬት ስለመኖር አለመኖሩ፣ ካለ የተባለው መሬት ልክና ሥሪቱ ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ቀድሞ የማን ይዞታ እንደነበረ፣ ተለቆ ከሆነ የተለቀቀበት ምክንያት፣ አሁን በማን እጅ እንዳለ እና ምን ሥራ እንደያዘ፣ ለመንግሥት ሥራ ያልተመደበና የደን ሀብት የሌለበት ስለመሆኑ፣ ተከራካሪ የሌለውና ካሁን በፊት በዓመት የሚሰጠው ጥቅም ጭምር እንዲገለፅ የሚጠይቅና የተገለፀበትም ነው። በዚህም መሰረት ልዩ ስሙ ነጌሶ ቆላ፣ ነጌሶ ቂልጡ እና ዓባይ ነጌሶ[20] የሚባለው መሬት ከ1928 ዓ.ም. በፊት በግብረ ጠልነት ተለቆ በመንግሥት ግምጃ ቤት ተይዞ የሚገኝ ስለመሆኑ፣ የአርብቶ አደር መሬት የሚባለውም መጠን ተዘጋጅቶ ስለመቅረቡ የሚያትት መፃፃፍ እናገኛለን።

በሁለተኛነት ለአሥራ ሰባት ዓመታት ያህል መፃፃፍ የተደረገበት ጉዳይ የአገሩ ፀጥታ ሁኔታ ነው። የዛሬዎቹ ተጠኚ ወረዳዎች ከሚገኙበት እና ቀድሞ በተለያዩ ሥም ከሚታወቀው አውራጃ ግዛት ጽህፈት ቤት በየወሩ ለሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ የሸዋ ጠቅላይ ግዛትም ለአገር ግዛት ሚኒስቴር ባስተላለፏቸው ተከታታይ ደብዳቤዎች ያገሩ ፀጥታ በጣም

[20] እዚህ የተጠቀሱት ሥፍራ ሥሞች በሙሉ በይፋት ውስጥ የሚገኙ ሆነው ሳለ ወረዳዎቹ በየዘመኑ ሲከለሉ ደግሞ በቀወትም በኤፍራታ እና ግድምም ውስጥ ሲጠቃለሉ የነበሩ ናቸው። የወረዳዎቹ ድንበር ፖለቲካው በተለዋወጠ ቁጥር አብሮ የሚለዋወጥ ነው። ዛሬ ሰሙሮቢ ገለአሎ የምንለውም ቀድሞ ያልነበረ አዲስ ፍጥር ወረዳ ነው። ስለዚህም የተጠቀሱት አካባቢዎች በኤፍራታና ግድም፣ በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ውስጥ የነበሩነታቸውን ታሳቢ ማድረግ ግቡዕ ይሆናል።

ረግቷል ለማለት እንደማይቻል፣ የተመደቡት የፀጥታ ኃይሎችም ማነሳቸውን የጠቀሱባቸው ደብዳቤዎች አሉ።

በሦስተኛነት የተነሳው ጉዳይ በአውራጃው ውስጥ ቀላድ ስለመጣል ነው። የአውራጃው ግዛት ጽህፈት ቤት በተለያዩ ጊዜ በፃፋቸው ደብዳቤዎች ቀላድ የመጣል ጉዳይ አስቸጋሪ እንደሆነበት ይኸውም የሆነው ደግሞ የክብር ዘበኛ ባልደረቦችና ባላባቶች በማስቸገራቸው እንደሆነ፣ ቀላድ ለመጣል የሚሰማሩ ባለሙያዎች እና የፀጥታ ኃይሎችም በየጊዜው በጥይት እየቆሰሉበት እና እየሞቱበት መቸገሩን አመልክቷል።

ከዚህ በላይ ከቀረበው የቤተመዛግብት ምልከታ ጥናት መረዳት የሚቻለውም በተለይ ቀወት እና ሰሙርቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበር አካባቢ የሚገኘው የነጌሶ አካባቢ መሬት ከ1928 ዓ.ም. በግብረ ጠልነት መለቀቁን እና በመንግሥት ግምጃ ቤት መያዙን፣ የአርብቶ አደር መሬት የሚባለውም መሬት መጠን መታወቁን የሚጠቁም ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በአካባቢው ቀላድ ለመጣልም ሲሞከር ግጭት ሲያጋጥም መቆየቱን እንረዳለን።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ ከአውራጃው ግዛት በተከታታይ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ የተፃፉት ደብዳቤዎች በአካባቢው የሰከነ ሰላም እንደሌለ እና የተመደቡትም የፀጥታ ኃይሎች ቁጥር አነስተኛ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ከእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች መምዘዝ የሚቻለውም ዛሬም የአካባቢው ነዋሪዎች እና የጥናቱ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች እንደሚያወሱት በድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች፣ አማሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች፣ በአፋሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች መካከል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ፀበኝነት እና የግጭት ልማድ መኖሩን ነው።

# 7. ከቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች የተሰበሰቡ ሥነቃሎች እና መልዕክቶቻቸው

በዚህ የቀወት እና ሰሙ-ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦችን ግጭት እና የግጭት አፈታት ጥናት ሂደት ትኩረት ከተደረገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ግጭት ተኮር ሥነቃሎችን መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቅኝት ጥናቴ ወቅት በሁለቱም ሕዝቦች ባህል ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ የሚገለፁ ግጭት ተኮር መልዕክት ያላቸው ሥነቃሎች መኖራቸውን ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደበት መስማት ችያለሁ፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ሥነቃሎቹን በቀይታችን መሃል አልፎ አልፎ ጣልቃ እያስገቡ ሲናገሩ በመስማቴም መሰል ሥነቃሎችን የአካባቢዎቹ ተወላጆች የሆኑ የሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲሰበስቡልኝ አድርጊያለሁ፡፡ በዚሁም ጥረት የተወሰኑ የአማርኛ እና የአፋርኛ ግጭት አመልካች ሥነቃሎች አግኝቻለሁ፡፡ የተሰበሰቡትንም ግጭት ተኮር ሥነቃሎች ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ጋር ቃለ ምልልስ፣ የተተኪረ ቡድን ውይይት ቆይታ ባደረግሁበት ወቅት በየርዕስ ነገራችን መሃል ጣልቃ እየገቡ ሐሳብ እና መልዕክት ማጠናከሪያ ሲሆኑ አግኝቻለሁ፡፡ ለአብነትም ግጭትን ከሚያሳዩት አፈ-ታሪኮች መካከል የተወሰኑትን በጥናቱ ምዕራፍ ሦስት ውስጥ ማመልከቴ ይታወሳል፡፡ ሌሎቹንም እንደየአገባባቸው በየቦታው አሳይቻለሁ፡፡ ይኸውም ሥነቃላዊ ማለትም ጥበባዊ አገላለፆች እና ተግባቦቶች /communications/ እና ክዋኔዎች የኅብረተሰብ ማህበራዊ እውነታ ማንጠሪያዎች እንደመሆናቸው የባህል ሥርዓት እና ልማድ እንደሚወራረስባቸው እና እንደሚጎዳኛቸውም፣ ግጭትም በዚሁ ውስጥ እንደሚተከል እና እንደሚሰርፅ ለማመልከት ሲባል የተደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም ፎክሎራዊ ገለፃዎቹ ውስጥ ተደጋግመው የሚመጡት ግጭት ተኮር ጭብጦች የማኅበረሰቡ አባላት በልምድ የተገነዘቧቸው፣ ያዳበሯቸው እና የተከኗቸው ጉዳዮች በመሆናቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ ፎክሎሩ በኅብረተሰቡ የተመረጡ ጭብጦች ላይ ይተኩራልና ነው፡፡ ስለዚህም የህብረሰብ ሰብአዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ተፈጥሯዊ እና ልዕለ ተፈጥሯዊ ነገሮች በፎክሎር ጥበባዊ አገላለፆች ውስጥ ተደጋግመው ስለሚመጡ ነው (Dan-Ben-Amos /http: /www. readingonline. jestor.org. 6/6/2012)፡፡

ድንበርተኞች ከሆኑት ከቀወት ወረዳ አማሮች እና ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች የተሰበሰቡት ጥበባዊ ገለፃዎች /artistic expressions/ ማለትም ሥነቃሎች በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎቻቸው ውስጥ ደጋግመው ከሚያነሷቸው የመባያ ጉዳዮች ወይም ጭብጦች መልዕክቶች እና ትዕምርቶች መካከል ፀበኝነት፣ ግጭት እና ጦርነት በየዘውጉ ተደጋግመውም ይነሳሉ። በሥነቃሎቹም ውስጥ የፀበኝነት፣ ግጭት እና ጦርነት መንሥዔዎች እና ውጤቶቻቸው ማለትም ያስከተሏቸው ሰቆቃዎች፣ ከሰቆቃዎቹም በአሸናፊነት ለመወጣት የተፈፀሙ የወንድነት /masculinity/ ተግባራት ይዘከራሉ። በአጭሩም በሥነቃሎቹ ውስጥ ፀበኝነትን፣ ተጋጪነትን እና ጦርኝነትን የሚዘክሩ እና የሚያበረታቱ መልዕክቶች ይገኙባቸዋል። ይህም ደግሞ ቃል-ተረኮች ጦርነት የማይለያቸው ቡድኖች የጦርነት መንሥዔዎቻቸውን እና ውጤቶቻቸውን፣ ያስከተሉባቸውንም ሰቆቃዎች እና ተሞክሮዎች መሰነጃዎችነታቸውን እና መግለጫዎችነታቸውን ያረጋግጥልናል (Veena፣ 1987:13)። ስለዚህም በዚህ ምዕራፍ ከአፈ-ታሪክ ውጪ የሆኑትን ሥነቃሎች (የሁለቱ ሕዝቦች አፈ ታሪኮች በምዕራፍ ሦስት ውስጥ መታየታቸው ይታወሳል) ለማየት እና ግጭት ተኮር መልዕክታቸውን ለማሳየት ይሞከራል። እንደሚታወቀውም ኅብረተሰብ ሥነቃልን የሚጠቀመው ለተለያዩ ዓይነት አገልግሎቱ ወይም ጠቀሜታው ማለትም ለተዝናኖት፣ ፍላጎት እና አመለካከትን ለማስረፅ፣ ተፈላጊ ባህርያትንና የሕይወት ግቦችን ለማስተማር፣ የሕይወት ተሞክሮን ለመሰነድ፣ ማንነትንና የሚኖሩበትን ዓለም ለመቀንበብና ለመግለፅ ነው (እነ ፈቃደ (2005)፣ ፈቃደ (1991፡16-22)፣ Okpewho (1992: 105-118)፣ Finnegan (1992)። ይሄም ሁሉ ደግሞ የሚገለፀው በራሱ በሰው ልጅ፣ በእርሱም ዙሪያ ባሉ ሕያው እና ግዑዛን ፍጥረታት ገፀ-ባህርያት አማካኝነት ነው። እዚህ ለማየት የሚሞከረውም በቀወት አማሮች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ዘንድ የግጭት ባህል በቃል ተረኮች አማካኝነት እንዴት እና እንደምን እንደተተከለ ነው።

ከቀወት ወረዳ የተሰባሰቡት ሥነ ቃሎች አፈ-ታሪኮች ሽላሎዎች፣ ፉከራዎች፣ ሙሾዎች፣ የፍቅር፣ የሰርግ፣ የሥራ ዘፈኖች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ እንቆቅልሾች፣ ምርቃቶች እና ተረቶች ናቸው። እነዚህ የሥነቃል ዘርፎች ከዘወትሩ ወይም ከአዘቦቱ መረጃ /information/ በአነጋገር፣ በሥነልሳን፣ በትርጉም የሚለዩበት ገፅታ ቢኖራቸውም የሚያስተጋቡት መልዕክት ግን የኅብረተሰቡን አጠቃላይ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ አተያይ ነው። ስለዚህም መታየት ያለባቸው ከራሳቸው አውድ

በተጨማሪ በኅብረተሰባዊ አውዱም ጭምር መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ እንደተጠቀመው አፈ-ታሪኮቹ የነዋሪዎቹን ጥንተ አመጣጥ፣ ትልቆ ትውልድ፣ ማንነት፣ መሬት አያያዝ /አሰፋፈር/ እና ተግባቦት ሁኔታ ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ ደግሞ ጦረኝነትን ወይም "ወንድነትን" በተለያዩ መንገድ እያነሱ ያኳሻሉ፡፡

ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተሰባሰቡትም አፈ-ታሪኮች፣ ሽላሎዎች፣ ፉከራዎች፣ የሥራ፣ የሰርግ፣ የወፍጮ፣ የሥራ ግጥሞች፣ የግመል ሙገሳዎች፣ ተረቶች፣ የአፋርን የፍቅር እና የሰርግ ግጥሞች፣ የዝናብ ምርቃት፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና እንቆቅልሾች እንደ ቀወቶቹ ሁሉ የአፋርን ታላቅነት እና ጦረኝነት ያነሳሉ፣ ያሞግሳሉ፡፡

ከሁለቱም ድንበርተኛ ወረዳዎች የተሰባሰቡት እና በተለያዩት ዘውጎችም ውስጥ ተዘርተው የሚገኙትን ማዕከላዊ መልዕክቶች ለመምዘዝ ስሞክርም ሽላሎዎቹ የየአካባቢዎቹን ነዋሪዎች ገዳይነት፣ ግጭት ዘወትራዊ ክስተት መሆኑን የሚያመለክቱ፣ ወንድነትን ማለትም ገዳይነትን፣ ኃይለኝነትን፣ ቂመኝነትን፣ የጦር መሣሪያ ባለቤት አፍቃሪነትን እና አምላኪነትን፣ ተጠራጣሪነትን፣ በቀልተኝነትን፣ እልከኝነትን፣ ደመኝነትን፣ ጋንፈኝነትን፣ አትንኩኝ ባይነትን የሚያንቀለጳጵሱ፣ አቅመ-ቢስነትን ወይም ደካማነትን ደግሞ የሚያንቋሽሹ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

የሽላሎ ግጥሞቹ መልዕክቶች ሲጠቃለሉም ለወንድነት (masculinity) ማለትም ጀግንነት የሚሰጠውን ከበሬታና አስፈላጊነት፣ እሴትነት የሚያጎሉ በአንፃሩም አቅመ-ቢስነትን ወይም ደካማነትንና ፈሪነትን የሚኮንኑ ናቸው፡፡

በጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እና በዚህ ርዕስም ሥር ከላይ እንደጠቆምኩት ቀጥሎ የቀረቡትን ግጭት ተካይ፣ አነሳሽ ወይም ቀስቃሽ እና አስታዋሽ ሥነቃሎች (በነገራችን ላይ በዚህ ምዕራፍ ከቀረቡት እና በሁለቱ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች ዘንድ ከሚደመጡት አስረጅ ግጭት ተኮር ሥነቃሎች በተጨማሪም መሰሎች በአባሪ አንድ ቀርበዋል፡፡) ሥነቃሎቹን የሰበሰብኳቸው በመጀመሪያ ትውልዳቸው እና ዕድገታቸው ቀወት ወረዳ ውስጥ በተለይም ሰፊ በረት፣ ደብርና ጀጎል፣ ዓባይ አጥር እና ኩሬ በረት ቀበሌዎች እንዲሁም ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ውስጥ በተለይ አዲሲሂጌ፣ ሐሪሐሙ፣ ሆቲመሮ እና አስጋፊን ቀበሌዎች ውስጥ ተወልደው ካደጉ እና የሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከሆኑ እንዲሁም ከሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ ነው (በመጠይቅ፣ ከእነ ጥላሁን ደምሴ፣ አንበርብር ጣሰው፣ ፍርዴ ሞላ፣ አበባው በድሉ፣ እምሬ ታቦር፣ ሰይፈ በለጠ፣ ዓሊ አደም፣ መሐመድ አህመድ፣

አደም ሙሣ 9A፤ ቤዛ ሰለሞን፣ ሂሩት አጉኜ፣ በለጠ ጣሴ፣ አድነው ተስፋዬ፣ ገነነ ተሰማ፣ ድረሴ ይልማ፣ ሐሚድ ሁሴን፣ ኢብራሂም አህመድ 9B፣ ሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) ያገኘሁት እና ለቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በየጨዋታችን መሃል አንስቼባቸው ያረጋገጡልኝ፡፡

ከአማርኛ ሽላሎዎቹ ልጀምር፡፡ ሽላሎዎቹ በቅርፅ ረገድ ብዙዎቹ መንቶዎች ናቸው፡፡ ምት ወይም ድለቃ አላቸው፡፡ አንዳንዶቹም የሰውን ስሜት እና ፍላጎትም በሰውኛ ዘይቤ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ወደ ግጭት ለመግባት መሻትን ከሚጠቁሙት መካከል አንዱን እንይ፡፡

ጥራኝ ደኑ ጥራኝ ዱሩ፣
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ተማደሩ፡፡

ይህ መንቶ ግጥም የልብን መሸፈት፣ ግጭት ውስጥ ለመግባት መነሳሳትን፣ ጫካ መግባት መፈለግን፣ ዱር ቤቴ ማለትን መሻትን ወይም መፈለግን ይጠቁማል፡፡ ይሄም በባህሉ ውስጥ የጀግንነት መለዮ መሆኑን እና ግጭት ናፋቂነትን አመልካች ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበውን ሽላሎ ግጥም መልዕክት እንመልከት፡፡

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ፣
ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ፡፡

በዚህ መንቶ ግጥም እየተላለፈ ያለው መልዕክት የአባት ውርስና ቅርስ የሆነውን ጀግንነት ወይም ወንድነት የማስቀጠል ፍላጎትን፤ በአንፃሩም ከኣባታዊ ልማድ ማፈንገጥ ማለት ወደ የአንስታይ ፆታ ተግባር ተብሎ በባህሉ ወደ ተፈረጀው ሙያ መንሸራተት እንደሆነ ነው፡፡ በአጭሩም መንቶው አባታዊ ወግ ልማዱን ተካይ እና አፅዳቂ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከአንበሳው መኻታ ጅቡ ተኻቶበት፣
ሲያባንነው ያድራል በልሙ እየመጣበት፡፡

በዚህም መንቶ ግጥም ውስጥ በአንበሳ ኃያልነት እና በጅብ ፈሪነት ተመስሎ የቀረበው ጀግና እስካለ ድረስ ፈሪ የያዘውን ነገር ማፅናት እንደማይቻለው እናም ፈሪ የማይገባውን ነገር ወይም ቦታ መንካት እንደሌለበት ነው፡፡ ቢነካም በእርጋታ እነደማይኖር፡፡

ቀወቶች በሚያስሚቸው የሽላሎ ግጥሞች ወንድነት ወይም ጀግንነት በጦር መሣሪያም መደገፍ እንዳለበት፣ የቶር መሣሪያም የክብር ማስጠበቂያ ስለመሆኑ ያነሳሉ፡፡ አስረጅ እንመልከት፡፡

እንኳን ግደል ብለው እንኳን ሰደውት፣
ከወገብ ላይ ሆኖም ያኮራል ጥይት፡፡

የጦር መሣሪያ ባለቤትነት ለቀወቶች የነፍስ መጠበቂያ፣ የዝና እና የክብር ማግኛም ነው፡፡ በየትኛውም ማህበራዊ ስብስብ እና ግንኙነት ወቅት ከሚነሱትም ነገሮች አንዱ "እከሌ ለነፍሱ መጠበቂያ ወይም ለእጁ መሣሪያ መሣሪያ አለው ወይ?" የሚል ነው፡፡ ይህም በሕዝቡ ዘንድ አፍቅሮተ-የጦር መሣሪያ መኖሩን ነው የሚነግረን፡፡ የጦር መሣሪያ ባለቤትነት ከወንድነት ጋር መቆራኘቱን፡፡ ቀወትን በጠቅላላው የሚመለከት አንድ የሽላሎ መንቶ ግጥም በማቅረብ አጠቃላይ የወንድነት ወይም ጀግንነት ማሳያ አቅርቤ ልለፍ፡፡

ታረሰ አሉ ይፋት በጥቋቁር በሬ፣
ዘንጋዳ ሲዘሩት ሊያበቅል በርበሬ፡፡

ይህ መንቶ ግጥም ተምሳሌት እየተጠቀመ ምንም እንኳን አካባቢው ግጭት ቢበዛበትም ማለትም በባሩድ ቢመታም ለጠላት የማይንበረከክነቱን፣ ይልቁንም የተጠበቀው ሳይሆን ያልተጠበቀው የሚሆንበት፣ የሚታይበት እና እውን የሚሆንበትነቱንም ይጠቁማል፡፡ ጠላት የሚያንበረክክ ወንድ በዖታው ብቻ ሳይሆን በባህርየ-ወንድነት ወይም ጀግንነት ደረጃ የሚፈረጅ ይወለድ ዘንድም መሻት፣ መመኘት፣ መናፈቅ እና ጠላትን በቋሚነት ለመቋቋም መመኘት ሁሉ አለ፡፡ ለዚህም ይህን የሽላሎ ግጥም ያስተውሏል፡፡

ወንድ ይወለድ እንጂ ወንድ እንዴት ይጠላል፣
አፋር አስጨንቆ ድንበር ያስከብራል፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎዎችም በኩል እንደ ቀወቶች ሁሉ የሽለላ ግጥሞች ይገኛሉ፡፡ ከሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዓሊ አደም፣ መሐመድ አህመድ፣ አደም ሙሣ 9A፣ ሐሚድ ሁሴን፣ አህመድ ኢብራሂም 9B (ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) ከሰበሰብኳቸው እንዲሁም ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በቃለ መጠይቅ ወቅት በየጣልቃው ከነገሩኝም መካከል የሚከተሉት ዓይነቶች የሽለላ ግጥሞች አሉ፡፡

የሽለላ ግጥሞቹም በቅድሚያ በትርጉማቸው ቀጥሎም በመገኛ ቋንቋቸው ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

አንጣላም ሀገር ያጣላናል፣
እንደኛ መሆን አትሞክሩ ተው አትንኩን ብለናል፣
ሥጋ እንደጠገቡ አሞራዎች በአንድ ላይ ተነስተናል፣
ጋሻ ጦር እንደሚከላከል፡፡

ይህ የአፋርኛ ሽላሎ ግጥም በአራት ስንኞች ውቅር የቀረበ ነው፡፡ የሚያስተላልፈውም መልዕክት አፋሮች የሚጣሉት በአገር ማለትም በመሬት ወይም ክልል ባለይዞታነት እና ማስከበር ሳቢያ መሆኑን፣ መሬታቸው ወይም አገራቸው ከተደፈረም በዋዛ እንደማይለቁ በኅብረትም እንደሚያጠቁ ነው፡፡ የሚቀጥለውም ባለ ሶስት መስመር ግጥም የሚያረጋግጠው አፋሮች በጦርነት ወቅት ለያኽ፣ ለገላጋይ የሚያስቸግሩ ኃይለኞች መሆናቸውን ነው፡፡

ማን ነው መድፈር የሚፈልገው አገራችንን፣
ተው የሚል መሪ አለን፣
አንተውም የሚሉ ጀግኖች አሉን፡፡

የቀወቶችን የፉከራ ግጥሞች መልዕክት ስመረምርም የፉከራ ግጥሞቹ እና ክዋኔው ከሽላሎ ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ዓላማውም የጀግንነት ሙያን ማለትም አተኳኮስን፣ ገዳይነትን፣ ቅልጥፍናን፣ በረኸኝነትን፣ አመለ ቁጡነትን ሀሞተ ኮስታራነት፣ ቆፍጣናነት፣ ቆራጥነትን፣ አልበገር ባይነትን በአጠቃላይም ወንድነትን /masculinity/ የሚያረጋግጡ እና በአደባባይ የሚዘረዝሩ፣ ፈሪነትንም የሚያወግዙ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ (መጠይቅ፣ ጥላሁን ደምሴ፣ አንበርብር ጣሰው፣ ፍርዴ ሞላ፣ አበባው በድሉ፣ እምሬ ታቦር፣ ሰይፈ በለጠ፣ 9A፤ ቤዛ ሰለሞን፣ ሂሩት አጉኔ፣ በለጠ ጣሴ፣ አድነው ተስፋዬ፣ ገነነ ተሰማ፣ ድረሴ ይልማ 9B ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) እና ለቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በየጨዋታችን መሃል አንስቼባቸው ያረጋገጡልኝ፡፡

እጥፍጥፍ ያለው እንደ ነጠላ፣
አተኳኮሱ በድንጋይ ጥላ፡፡

በዚህ መንቶ የፉከራ ግጥም እየተላለፈ ያለው መልዕክት የትክለ-ሰውነት ቅልጥፍነት ወይም የሰውነት በራስ ሥጋ አለመታሰር እና የመታኮሻ ሥፍራ አያያዝ

ችሎታ የጀግና መለዮዎችነታቸውን ነው፡፡ ይኸውም የወንድነት ሙያ ደግሞ ከልጅነት ዕድሜ ጀምሮ እየተኮተኮቱ ማደግን እንደሚሻ ቀጥሎ በቀረበው ባለ አራት መስመር የፉከራ ግጥም መልዕክት እናያለን፡፡

አባሮ ገዳይ እቁልቁለቱ፣
በረሃ ለምዶ በልጅነቱ፣
በተወለደ በአሥር ዓመቱ፣
አፈሰሰበት ጥይት በአንገቱ፡፡

ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በሰበሰብኳቸው የፉከራ ግጥሞችም ውስጥ አፋሮች እራሳቸውን የጦርነት አባት አድርገው እንደሚቆጥሩ የሚያመለክቱ የፉከራ ግጥሞች መኖራቸውን ተረድቻለሁ፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ምንጮቼ ደጋገመው እንዳወሱት አፋሮች እራሳቸውን ኃይለኛ፣ የጦርነት ልሂቅ፣ የወንድ በላይ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ይህም በፉከራ ግጥሞቻቸውም ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት የአፋር የፉከራ ግጥሞች የተገኙት ከሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከእነ ዓሊ አደም፣ መሐመድ አህመድ፣ አደም ሙሣ 9A፣ ሐሚድ ሁሴን፣ አህመድ ኢብራሂም 9B (ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) በመጠይቅ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በየጨዋታችን መሃል ያነሷቸው ሁሉ አሉባቸው፡፡ ከአፋርኛ ወደ አማርኛ የተመለሱትን የፉከራ ግጥሞች እነሆ፡፡

ማታ ጨረቃ ነን፣
ቀን ፀሐይ ነን፡፡

በዚህ የፉከራ ግጥም እየተላለፈ ያለው መልእክት አፋሮች ቀንም ሆነ ሌሊት ጠላታቸው ባለበት ቦታ ሁሉ ተገኝተው ማጥቃት የሚቻላቸው፣ ጊዜ የማይገድባቸው መሆናቸውን ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ደግሞ ጦርነትም ባህላቸው መሆኑን ነው የሚያስረግጥልን፡፡

እኛና ጦርነት እንተዋወቃለን፣
በታሪካችን፣
እሰከ ሰባት አያታችን፣
እናውቃለን ጦርነትና ሞትን፣

አዲስም አይደለን።

አሁንም ሌላውን የፉከራ ግጥማቸውን ስንመለከት በጦር መሳሪያዎቻቸው፣ በጦርነት ፈረሶቻቸው ዓይነቶች የሚመኩነታቸውን፣ ጠላት እንኳን ባይመጣባቸው በውስጣዊ ፀቦቻቸው ፈሪዎቻቸውን እና ጀግኖቻቸውን እየለኩ፣ ፈሪዎቻቸውን የሚኮንኑነታቸውን በአንፃሩም ጀግኖቻቸውን የሚያሞግሱነታቸውን እና "ወንድነታቸውን" የሚጠብቁነታቸውን፣ መጪውን እና የሚሆነውንም የሚተነብዩ ትንቢተኞች ያሏቸውነታቸውን ነው።

የሚያማምሩ የጦር መሣሪያዎች ባለቤቶች፣
የነጫጭ ፈረሶች ጌቶች፣
ነገር ፍለጋ የሚዘዋወሩ ሰይጣኖች፣
የሚጣሉት ቢያጡ ከራሳቸው ጋር የሚጣሉ አፋሮች፣
አሉን እንቅልፍ የማያውቁ የሌሊት አንበሶች፣
ቀድመው የሚያውቁ አሉን ትንቢተኞች፣
በፍርሃት ላብ የሚጠመቁም ምስኪኖች፣
አሉንም ከንቱዎች፣

ከዚህ በላይ በቀረቡት የፉከራ ግጥም ስንኞች ውስጥ እየተላለፈ ያለውን መልዕክት ስናጤን የመሣሪያዎቻቸውን ጥራት፣ የኃይለኝነታቸውን ወደር የለሽነት፣ የሚሆነውንም አስቀድመው የመገመት እና የማወቅ ብቃት አመልካች ሆነው እናገኛቸዋለን።

ወደ ቀወቶች ሙሾ ግጥሞች እንለፍ (መጠይቅ፣ ጥላሁን ደምሴ፣ አንበርብር ጣሰው፣ ፍርዴ ሞላ፣ አበባው በድሉ፣ እምሬ ታቦር፣ ሰይፈ በለጠ፣ 9A፤ ቤዛ ሰለሞን፣ ሂሩት አጉኔ፣ በለጠ ጣሴ፣ አድነው ተስፋዬ፣ ገነነ ተሰማ፣ ድረሴ ይልማ 9B ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) እና ለቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በየጨዋታችን መሃል አንስቼባቸው ያረጋገጡልኝ።

ከቀወት ወረዳ ሙሾ ግጥሞቹም ውስጥ ተደጋግመው የሚነሱት ግን የጀግና ክብር፣ አወዳደቅ፣ መመናመን እና የእናትና አባት አይተኬ ውለታ ናቸው ። ስለዚህም የእነዚህም የተለያዩ የመባያ ጉዳዮች ጨመቅና ዓቢይ እና ቀዳማይ ሐሳብ አሁንም ያው ወንድነትን መናፈቅ፣ ማሞገስ፣ ከበሬታ መስጠት ናቸው። አብነቶችን እነሆ።

በሬውንም ሽጡት ላወጣ ላወጣ፣
ጠመንጃውን ሽጡት ላወጣ ላወጣ፣
ጀግናው እንደሁ ቀርቷል ተመልሶ አይመጣ።
ጀግናችን ወደቀ ተሰበረ እንደ ቅል፣
ከብዷት የነበረ መሬት አለች እልል።

በካልኣይነት የሚቀነቀነው ደግሞ ጀግና የሚበላውን ጦርነት እና ምድር መውቀስ ይመስላል።

አንተ የራሳ ሜዳ እፋረድሃለሁ፣
አንተ የአዋዲ ጫካ እፋረድሃለሁ፣
ብዙ ወንድሞቼን ገብሬብሃለሁ።

በሙሾ ግጥሙ እየተላለፈ ያለው መልዕክት የተጠቀሱት አካባቢዎች ደም እየፈሰሰባቸው፣ አጥንት እየተከሰከሰባቸው፣ ሕይወት እየጠፋባቸው በጥቅሉም ሕይወት እየተገበረባቸው በቀወቶች ይዞታነት ፀንተው መቆየታቸውን ነው። ይህም ማለት ደግሞ በአካባቢዎቹ ላይ ግጭት ሲነሳባቸው መኖሩን ያመለክተናል። ወደ ታሪክ ማጣቀሻ ስንሄድም (እዚህ ላይ የሁለቱን ሕዝቦች ግንኙነት አፋዊ እና ጽሑፋዊ ታሪክ ክፍል ያጤኗል) ደግሞ አካባቢዎቹ የክርስትና እና እስልምና ተከታዮች መፋለሚያዎች እንደነበሩ እንረዳለን። ቀጥሎም ያሉት ሁለት ተከታታይ የሙሾ ግጥሞች የሚያረጋግጡልን ይህንኑ ነው።

የራሳንም እህል አልበላም እርሜ ነው፣
ያዋዲንም እህል አልበላም እርሜ ነው፣
ያረሰው ነጭ ቃታ ያበቀለው ደም ነው።
አፋርን በቤልጅግ የሚያተራምሰው፣
ጠለል ካለው ሜዳ ቆሞ እሚተኩሰው፣
በማይረባ ነገር የማይደፈርሰው፣
ሞቶ ተቀበረ አፈር ሆነ እንደ ሰው።

የሙሾ ግጥምን በተመለከተ በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ዘንድ በአቻዊነት የሚቀርብ የሙሾ ግጥም የለም። ምክንያቱም ሙሾም እራሱ የለም። አይደረግምም።

በቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የፍቅር ዘፈኖቻቸውም ውስጥ ተደጋግመው የሚነሱት ጀግንነት፣ የግብርና ውጤቶች፣ የምርት ዓይነት፣ አምራችነት፣ ማጣት፣ ፀፀት፣ ልባዊ ምኞት እና ሐሳብ፣ የስርቆሽ ፍቅር፣ መልክ፣ ሂያጅነት፣ ብድር፣ የቤትና ዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ተፈጥሮ እና ትክለ ሰውነት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ትክለ ሰውነት፣ መልካም አጥር፣ የጦር መሳሪያ እና አምራችነት በተደጋጋሚ ይወደሳሉ፡፡ ወንበዴነት፣ ኩነኔ ይፈራል፡፡ ሰቀቀንና ውሸት ይወገዛሉ፡፡ የነዚህም ሁሉ ጭምቅ ሐሳብ የግብርና ሥራ ሙያተኝነት፣ ኃይል እና የሚያስከትለው ሰቀቀን ወይም ፍርሃት እንዲሁም አካላዊ ቁመና ናቸው፡፡

አገርሽ ጉራንጉር ሥፍራሽ የወንበዴ፣
ስንቱን ዘለለና አንቺን አለ ሆዴ፡፡
አዳል ጎራዴውን ይይዛል በሆዱ፣
እንዴት ነው አንገትሽ ቅርፁና ቅርዱ፡፡

በዚህ የፍቅር ዘፈን ውስጥ የሚቀነቀነውም ሐሳብ የአካባቢው ድንጋያማነት፣ ወጣገባነት፣ ጫካማነት፣ ሸለቋማነት እና አስቸጋሪነት እንዲሁም የወንበዴ አገርነት፣ የጎራዴ አያያዝ ሥልት እና ልማድ ከአንገት አቀማመጥ እና ለዛ ጋር እየተነፃፀረ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የሰሙሮቢ ገለአሉዎች የፍቅር ዘፈን ወንዶች በሰፈር ከፈላ ወቅት እንስሶቻቸውን ይዘው በሚሰደዱበት ወቅት ምሽት ላይ ከግመሎቻቸው መሃል በጨለማ ተውጠው ወይም በጨረቃ ብርሃን ታግዘው በመንደራቸው ትተዋቸው የመጡትን ሚስቶቻቸውን እና ውሽሞቻቸውን በምናብ ወደ ኋላ እያሰቡ እና እያስታወሱ እርስበርሳቸው በምልልስ /ቅብብሎሽ/ የሚያዜሟቸው ናቸው፡፡

ፍቅረኛዬ ስትሞት
ግመል እሰጣለሁ፣
በሬም አቀርባለሁ፣
ውሽት ሊሆን ይችላል፣
የቀባሺውን ጎፈሬዬን እላጫለሁ፣
ግን እውነት ይሆናል፡፡

በፍቅር ዘፈኑ እየተጠቀሰ ያለው መልዕክት የሚወዷትን ሴት ሀዘን ለመወጣት ለሙት መታሰቢያነት የሚታረድ ግመል ወይም በሬ እሰጣለሁ ማለት የሐዘኑን

ልባዊነት አይገልፅም። ይልቁንስ እውነተኛ መሪር ልባዊ ሃዘንን መወጫ እና መግለጫ የሚሆነው የገዳይነት ምልክት የሆነውን ጎፈሬ መላጨት መሆኑን ነው።

ቀጥሎ የቀረበውንም ግጥም ስንመለከት በተለይ ፍቅረኞች በፀብ ወቅትም ቢሆን የማይለዩ እና የማይርቁ መከራ አጋፊዎች፣ አስታማሚዎች እና ተንከባካቢዎችነታቸውን ገላጭ እና አመልካች ነው።

እኔና ጓደኛዬ ከሌሎች ጋር በምንጣላበት ጊዜ ሁሉ፣
አዋቂዎች ይጠራሉ፣
መርፌዎችና ክሮችንም ያሰባስባሉ፣
ቁስላችንንም ይሰፋሉ።

በአጠቃላይ በግጥሞቹ ውስጥ ተደጋግመው የሚነሱት የጦረኝነት ምልክት፣ የጦር መሣሪያ፣ "ወንድነት"፣ ተወዳጅነት፣ ትክለ ሰውነት ናቸው።

የቀወቶችንም የሰርግ ዘፈኖች[21] ስንመለከት በግጥሞቹ ውስጥ ኃይለኝነት ይነሳል፣ ይወደሳልም።

አናስገባም በሩን፣
ሰርገኛውን።

በዚህ መንቶ ግጥምም ውስጥ የሚተላለፈው መልዕክት ገቺነት፣ ጉልበተኝነት እና ተከላካይነት ነው። ምንም እንኳን ጉዳዩ የዝምድና እና የማህበራዊ ግንኙነት ምሥረታ ሂደት ቢሆንም በር ላይ ቆሞ ሰርገኛን አላስገባም ማለት የጉልበተኝነት እና የጉብዝና መግለጫ እና ማሳያ መሆኑን ነው የምንረዳው። ቀጥሎም ያለው የሰርግ ዘፈን ይህንኑ ሐሳብ አረጋጋጭ ነው።

አጀባዬ አጀባ፣
ሁዷል ጭብጨባ፣
በየት ሊገባ።

---

[21] የቀወቶች የሰርግ ዘፈኖች የቀወት ማህበረሰብ የሰርግ ዘፈኖች አይደሉም። በዚህ ዘመን የከተሞች እና የጠቅላላው የአማራ ሕዝብ የሰርግ ዘፈኖች በመሆናቸው ሕዝባዊ ናቸው። ይሁንና እዚህ የቀረቡበት ምክንያት ልዩ በመሆናቸው ሳይሆን መልዕክታቸው ኃይል ገላጭ በመሆኑ ነው። ይሄ ማለት ደግሞ ፎክ ግጥሞቹ ሕዝባዊ ግጥሞች ለመሆን የበቁት ከፎክ ቡድኑ የወጡ ሰዎች ሰፊ አካባቢዎችን በማዳረሳቸው፣ ባህላቸውንም በሂደት በማስፋፋታቸው እና በብዙኃን መገናኛዎችም በማህዘባቸው ምክንያት ነው ለማለት ይቻላል።

አሁንም ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው የፍቅር ዘፈን ውስጥ የምናገኘው መልዕክት የሙሽራውን ገዳይ አለመሆን እና የጎራዴውንም በደም አለመጨቅየት እና የደም ምልክት የሌለውነቱን ነው፡፡

የሙሽራው ጎራዴ፣
ውስጡ አረንጓዴ፡፡

አሁንም አንድ ሌላ ኃይል ከኃይል የሚነፃፀርበትን የሰርግ ግጥም እንመልከት፡፡

ኸረ ይሂት ተነሳ፡፡ (2)
የእከሌ አንበሳ፡፡
ኸረ ይዘህ ተነሳ፣
እንዳይነጥቅህ አንበሳ፡፡

በዚህ ባለ አራት መስመር የሰርግ ዘፈን ውስጥ የሚተላለፈው መልዕክት ከኃይለኛም የበለጠ ኃይለኛ፣ ከአንበሳም የተሻለ፣ የበለጠ አንበሳ እንዳለ ነው፡፡ ይህም ምንጊዜም ኃይለኝነት እንደሚያስከብር፣ የፈለጉትንና የተመኙትንም እንደሚያስገኝ ነው የሚጠቁመን፡፡

ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተሰባሰቡትም የሰርግ ዘፈኖች እንደ ቀወቶቹ ሁሉ ቀልጣፋነት፣ ራስ ቻይነትን እና ወንድነት ይሞገሳል፡፡ ለአብነትም ቀጥሎ የቀረቡትን እንይ፡፡

እንደ ውኃ ቀስ እያለ የሚሄድ ሙሽራ መጣ፣
እንደ መስታወት የሚያንፀባርቅ ሙሽራ መጣ፡፡

ይህ ግጥም ሙሽራውን በሁለት ነገሮች በውኃ እና በመስታወት ይመስለዋል፡፡ በዚህም ምሰላው የሙሽራውን ልበ-ሙሉነት፣ ጎምላላነት እና ርጉነት በመስክ ላይ በሚንሰዋለል ውኃ፣ ፀዳሉን ደግሞ በመስታወት ይመስላል፡፡ የሚከተለውም የሰርግ ግጥም መልዕክት እንዲሁ በምሰላ የቀረበ ነው፡፡ የሙሽራውን ሽንጣምነት እና ራስ ቻይነት ወይም ስንፍ አያስገቤነት በነብር፣ የአንገቱን ሽንበቆነት እና የትክለ-ሰውነቱንም መለሎነት በእባብ መስሎታል፡፡

ሰውነቱን እንደ ነብር የሚደብቅ፣ እርዳታም የማይሻ ሙሽራ፣
እንደ እባብ አንገቱ ላይ ምልክት ያለው ሙሽራ፣
መጣ ውኃ እንደሚሻገር እባብ ዳሌው የሚውረገረግ ሙሽራ፡፡

ስለዚህም በተለያዩ አገላለፅ ተመላልሶ የሚነሳው ወንድነታዊ ተግባራት ማለትም የሥራ ውጤቶች፣ ባለሙያነትና ባልትና እንዲሁም እነዚህ የሚያስከትሉትና የሚያስገኙት ማህበራዊ ከበሬታዎች ናቸው፡፡

የወፍር እንጉርጉሮዎቹን ስንመለከትም በመመስያነት የሚጠቀሱት በሬ፣ የእርሻ መሳሪያና መሬት በናቸው፡፡ ከዚሁ ከወፍር እንጉርጉሮ ጋር ተያይዞ የቀረበውን የወፍጮ ላይ እንጉርጉሮ ስንመለከትም በቅርፁም መንቶ በይዘቱም ደግሞ የቤት ባልትናን አሞካሺ እና ሙያ ቢስነትን አውጋዥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም በጥቅሉ የሚያጠነጥነው በሁለገብ ጀግንነት ላይ ነው፡፡ አብነቶችን እንመልከት፡፡

አሆ በል ጎበዝ አሆ በል ጀግና ፣
የምርቱ ጀግና የጦሩ ዳኛ፡፡

እዚህ እየተተረከ ያለው አርሶ፣ ዘርቶ እና ኮትኩቶ ምርት አፋሽነት እና ጦረኝነት የጀግናነት መለዮነታቸው ነው፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሉዎችም በሥራ ግጥሞቻቸው ስንፍናን ያወግዛሉ፡፡ በጀግንነት ለሚሰሩም አፈሩም ሆነ ውኃው ልዩ ስለመሆናቸው እያሞገሱ ያንጎራጉራሉ፡፡

የአገራችን አፈሩ ወርቅ ነው፣
ውኃውም ማር ነው፡፡

ከሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች የተሰባሰቡት ተምሳሌታዊ ተረኮች ይዘት ሲታይም ብልጠትና ማታለል፣ የዋህነት እና ደግነት፣ ጀግንነት እና ደካማነት፣ ሞኝነት፣ ስንፍና፣ ሆዳምነት፣ ውሸት እና ክህደት፣ ኃይለኝነት እንዲሁም ጠላት ሥጋትቢሆንም ወንድነትንም ለማሳያነትት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ዝናን እና ስሙ-ጥርነትንም ለማግኘት ምክንያት እንደሚሆን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በጥቅሉም ተረቶቹ ሥነምግባራዊ እውነታን ስለሚወክሉ አለመግባባቶች እና ግጭቶች እንደምን እንደሚከሰቱ እና ዕልባትም እንደሚያገኙ የመግለጥ እና የማሳየት ኃይል አላቸው፡፡

አሁን በጥናቱ ወቅት በሁለቱም ድንበርተኛ ወረዳ ሕዝቦች ውስጥ ያገኘኋቸውን፣ ተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ያላቸውን እና በተለያዩ አገላለፅ የቀረቡትን "የአያ አንበሳ እና የጅቦች" እንዲሁም "ብልሁ ሰው" ተረቶች ላስከትል፡፡

## ተረት አንድ፡- አያ አንበሳና ጅቦች

አንድ አንበሳ እና ዘጠኝ ጅቦች ሆነው አደን ሄዱ ይባላል፡፡ ሲያድኑም አስሩም አስር ፍሪዳዎች አገኙ፡፡ ነገር ግን ምንም ቢዋደዱ የየድርሻን መካፈል አይቀርምና "ፍሪዳዎቹን እንካፈል ተባባሉ፡፡" በዚያን ጊዜ ከዘጠኙ ጅቦች አንዱ ብድግ ብሎ መቼም ፊሪ አይፀድቅምና "ዘጠኙ ፍሪዳ ለአያ አንበሶ፣ አንዱ ለዘጠኛችን ይሁን" ብሎ ተናገረና በዚሁ መሰረት ተካፍለው ወደቤታቸው ሄዱ፡፡ ዳሩ ግን ወደ ውጪ የዋለ ማታ መጠየቁ አይቀርምና የጅቦቹ እንጀራ አባታቸው የዋሉበትን ሲጠይቃቸው የሆነውን ሁሉ ይነግሩታል፡፡

እርሱም ተናዶ "እንዴት! እንዴት! ያለ ነገር ጆሮ የማይሰማው ነገር የለ ለአንድ አንበሳ ዘጠኝ፤ ለዘጠኝ ጅብ አንድ እንዴት ያለ መካፈል ነው፡፡ ላሚቱን ንዳልኝ አንዷን ሰጥቼ ዘጠኙን አስመልሳለሁ" እያለ ወደ አንበሳው ቤት እየፎከረ ይደርሳል፡፡ እንደደረሰም እውነትም የአቶ አንበሳን ፊት ሲመለከተው እንኳንስ አንዲቱን ተቀብሎ ዘጠኙን ሊመልስና ከአሥር ፍሪዳ አንዲቱ ስለጎደለችበት ለካ በሆዱ ፀፀት አድሮበት ኖሮ እሳት ለብሶ፤ እሳት ጎርሶ ኖሮ "በል የመጣህበትን ጉዳይ ተናገር" ይለዋል፡፡ "ዋ! ጌታዬ ሆይ! ያቺን የዘጠኝ ድርሻ ትሁን የተባለችውን ፍሪዳ አሥረኛ አድርገው እንዲቀበሉኝ በልጆቼ ስም ሆኜ እለምንዎታለሁ፡፡" ብሎ አበረከተው፡፡ አያ አንበሶም ከብልህ ቀንሶ ከሞኝ ጨርሶ የሚኖር ብልጥ ነውና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ በሳቅና በጨዋታ ሸኘው ይባላል፡፡

## ተረት ሁለት፡- ብልሁ ሰው

በድሮ ጊዜ አንድ ብልኃተኛ ሰው ነበር፡፡ እርሱም ብዙ ወርቅ ነበረው፡፡ ከብዛቱም የተነሳ የሚያስቀምጥበት ቦታ ተቸግሮ ነበር፡፡ በጎረቤት እንዳያስቀምጥ የሚያምነው ሰው አጣ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ግን አንድ ሐሳብ መጣለት፡፡ ያም ሌሊት እውድቅት ላይ ወርቁን ሰው ሳያየው እንጉሮ ቆፍሮ መቅበር ነበር፡፡ ባቀደው መሰረትም በውድቅት ሌሊት ተነስቶ በሩን ከፍቶ ሊቀብር ሄደ፡፡ በሩ ሲከፈት የነቃው ጎረቤቱ ደግሞ የሚሰራውን ሁሉ በአጥሩ ቀዳዳ አጮልቆ ይመለከተው ነበርና ቀብሮ ሲሄድ ቀስ ብሎ ሄዶ የቀበረውን አውጥቶ ወሰደበት፡፡ አስቀማጭም ማንም አላየኝም ብሎ ወርቅ የቀበረበትን ሥፍራ

ከዕለታት አንድ ቀን ቃኝት ቢያደርግ በቦታው ምንም ነገር የለም፡፡ በዚህም ጊዜ ይህን ሥራ ሊሰራው የሚችለው ጎረቤቴ ነው ብሎ በመጠርጠሩ ወደ ጎረቤቱ ቤት በመሄድ "ውድ ጎረቤቴ አንድ ነገር ላማክርህ ፈለግሁ መቼም ካንተ በላይ የማምነው ሰው የለምና" ይለዋል፡፡ ጎረቤትዮውም "ታዲያ ምን ችግር አለ? ላንተ ያልሆነ ለማን እሆናለሁ" ይለዋል፡፡ ከዚያም "እንግዲያው ይሄውልህ አሁን በርካታ ወርቅ አለኝ፡፡ ባለፈውም እንጎሮ ያስቀመጥኩት ነበር፡፡ አሁን ታዲያ ይህንኛውን አብሬ ላድርገው ወይስ ለብቻው? ይህንን ላማክርህ ብዬ ነው" ሲለው "አዬ ጓዴ ለየብቻ ከምታደርግ አንድ ላይ ብታደርገው ይሻላል፡፡ ምክንያቱም ለየብቻው ብታደርገው ቦታው ሊደናገርህ ይችላል" ይለዋል፡፡ ምክር ጠያቂም "እሺ እንግዲያው እንዳልከው አንድ ላይ ላድርግ" ብሎት ተለያይተው ወደየቤታቸው ይገባሉ፡፡ ያም ምክር የተጠየቀው ሰው የጎረቤቱን ወርቅ አጠቃሎ ለመውሰድ ስለጓጓ በፊት የወሰደውን ወርቅ በፍጥነት መልሶ ቀድሞ እተቀበረበት ቦታ አስቀመጠ፡፡

ከዚያም በኂላ ብልኃተኛው ሰው ሌሊት ተነስቶ ሙሉውን ጠጠር የተቋጠረ ትልቅ ከረጢት ተሸክሞ ሄዶ የቀድሞውን ጉድጓድ ምሶ ተወስዶበት የነበረውን ወርቅ አውጥቶ ጠጠሩን ቀብሮ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ እንደ ልማዱ ሲጠባበቅ የነበረው ቀማኛ ጎረቤቱም እየሮጠ ሄዶ የጓጓለትን ከረጢት አውጥቶ ቢመለከት የቋመጠለት ወርቅ ሳይሆን ጠጠር ሆኖ አገኘው፡፡ ብልሁም ሰው በጥበቡ ንብረቱን በእጁ አደረገ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት እና ከቀወቶችም ከሰሙሮቢ ገለአሎዎችም የሰማኂቸው ጥንድ ተረቶች ኃይለኝነት እና ብልጠት የሚያስገኙትን ትሩፋት ጠቋሚዎች እና አረጋጋጮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ በአስረጂነት የቀረቡት እና በአባሪም የተካተቱት ተረቶቹ የሚተረቱት ማታለልን፣ ብልጠትን፣ ክዳትን፣ ደግነትን፣ የዋህነትን፣ ስንፍናን፣ ደካማነትን እና ኃይለኝነትን ወይም ጀግንነትን በስልት ለመግለፅ እና ለማስተላፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ማታለሉ፣ ክዳቱ፣ ብልጠቱ የተፈጠሩበትን እና የመጡበትን ሥረ መንሥዔ በተረቶቹ ውስጥ ስንመለከትም ዞሮ አቅም ማጣት ያስከተላቸው ነገሮች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ስለዚህም እዚህም ውስጥ በገሃድም በስውርም እየተቀነቀነ ያለው ሐሳብ ኃይለኝነት እና ደካማነት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ደግነትም ቢሆን የኃይለኞች ልግስና ከመሆን የሚያልፍ አይመስልም፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮቹም ከሚያነሱት ውስጥ ፍጥነት፣ ድፍረት ወዘተ ይገኛሉ፡፡

ከመቀደም መቅደም፡፡

ሞት ላይቀር ፍርሃት፡፡

አመል ላይቀር ቅጣት፡፡

ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወራዳ የተሰባሰቡትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንመለከትም እንዲሁ "ወንድነትን" የሚመለከቱ አሉባቸው፡፡

ውጊያ በምንሽር፤ ጨዋታ በባላባቶች አንደበት ያምራል፡፡

ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ከተሰባሰቡት ሥነ ቃሎች መካከል አባባሎችም ይገኛሉ፡፡ አባባሎቹም የአፋሮችን በአላህ ዘንድ ተመራጭነት፣ ልዕልናዊ ማንነት፣ ታላቅነት፣ ጠረኝነት፣ የእርስ በርስ እና ውጫዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ናቸው፡፡

አላህ ታላቅ ነው፡፡

አፋር ታላቅ ህዝብ ነው፡፡

አላህና አፋር ከሁሉም በላይ ናቸው፡፡

በዚህ ግጥማዊ አባባል እየተላለፈ ያለው መልዕክት አፋሮችን የሚገዳደር ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ነው፡፡ እራሳቸውን ያስቀመጡበት ምሉዕ በኩለሄ እንዲሉ ዓይነት ከአላህ ተርታ ነው፡፡ ይሄ ዓይነት አስተሳሰብ ግጭትን በወግ ልማድነት የሚተክል አስተሳሰብ ነው፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ከፍተኛ ክብር ከሚሰጧቸው እና ኑሯቸውንም ከሚመሩባቸው እና ከሚመኩባቸው እንዲሁም ከሚከነከኑባቸው የቤት እንስሳት መካከል ዋናው ግመል ነው፡፡ ስለዚህም ስለ ግመሉም የማይጨነቅ አፋር ይንኳሰሳል፡፡ ግመል እና የግመል ሀብታምነትም ያስመሰግናል፣ ያስሞግሳል፡፡

ድምፁ ጎርናና ነው ከሌሎች ከእነ በግ ይበልጣል፡፡

ጠረኑ ልዩ ነው እንደ ከአህያ ይለያል፡፡

በዚህም አባባል ውስጥ በተምሳሌት የቀረቡት እና ተነፃፀሩት በግ፣ አህያ እና ግመል ናቸው፡፡ ግመል ስሙ በቀጥታ ባይነሳም በጠረኑ ልዩ መሆን ተገልፆ ተነስቷል፡፡ በልማዱ በግ በየዋህነቱ፣ አህያ በጭነት እንስሳነቱ፣ ድንዝዝነቱ፣ አይመረው አይተኩሰውነቱ ሲታወቅ ግመል ደግሞ በሁለገብ አገልግሎቱ፣ ማለትም በወተት ምንጭነቱ፣ በክቡር የዕርድ እንስሳነቱ፣ በረሽኝነቱ፣ ችግር ተወጪነቱ፣ ጠንካራነቱ ይታወቃል፡፡ በዚህም እንደምን ከወንድነት ጋር ተነፃፅሮ እንደቀረበ ማየት ይቻላል፡፡

ሙገሳዊ አባባሎቹን በሙሉ በሥርዓታዊ መንገድ ለማየት ስሞክርም የሚያነሷቸው ዓበይት ጉዳዮች የተወሰኑ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ እነዚህም የያዙትን መልዕት ስንመለከት ጥንቃቄ፣ ሙያ፣ ብልጠት፣ ትጋት፣ ሀብት፣ ክብር፣ ወገን፣ አቅም የመሳሰሉትን የተመለከቱ የያዙ ናቸው፡፡ እነዚህም የመባያ ቦታቸው የተወሰነ ባይሆንም እምቅና እቅብ አባባሎች በንግግር መሃል እየገቡ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲፋፋ የሚፈለጉትን እሴቶች ማለትም ጥንቁቅነት፣ ትጉነትና ክብርን ማስጠበቅ ለማስረፅና ለማጉላት የሚያገለግሉ ይመስላሉ፡፡

በመስክ ሥምሪት ወቅት ከተሰበሰቡት ሥነቃሎች ውስጥ እንቆቅልሾችም ይገኛሉ፡፡

ሰሙሮቢዎች "ከኃላው የሚፀንስ በአፉ የሚወልድ" የትም ብትሄድ የሚከተልህ /የማይቀር ነገር ታውቃለህ? ይላሉ ጠመንጃን፡፡

በእንቆቅልሾቹ የሚነሱትም ቤትና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ አዝርዕት፣ ምግብ፣ የሰው አካል፣ ተፈጥሮ ናቸው፡፡ እነዚህም ሲጠቃለሉ በአመዛኙ ቤት፤ የቤት ውስጥ መገልገያና የግብርና ውጤቶችን የተመለከቱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በእንቆቅልሾቹ ውስጥ የምናየውም አጠቃላይ መልዕክት ህፃናት አካባቢያቸውን እየተዝናኑ የሚተዋወቁ እና የሚረዱ መሆናቸውን ነው፡፡

ከድንበርተኞቹ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች የተወሰኑ ምርቃቶችና እርግማኖችም ተሰብስበዋል፡፡ ምርቃቶቹ በይዘታቸው ተመራቂው ረጅም ዕድሜና የምርት ሀብት ወይም ፀጋን ያገኝ ዘንድ የሚመኙና የሚማፀኑ፣ ምቀኝነትም ይርቅ ዘንድ የሚማልዱ ናቸው፡፡ እርግማኖቹ ደግሞ በተረጋሚው ላይ የዕድሜ ማጠር፣ ሞት፣ ምርት ወይም ሀብትና ፍሬ ወይም ዘር ማጣት እንዲደርስበት የሚማፀኑ ናቸው፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በምርቃት ወቅት ደጋግመው የሚያነሱትም ውኃ ለዘላለም እንዲንቆረቆር፣ እንስሳት እየተራቡ እንዲበረክቱ፣ ወተት እንዲትረፈረፍ ፣ ሰውም ወተት እንደልቡ እንዲያገኝ ነው፡፡

አላህ ዝናብ ያምጣ ሰማይ ዳመና ይሁን፣
መሬት ሳር ይሁን፡፡
መሬት በሙሉ አረንጓዴ ይሁን፡፡
ከብት ያለበት በሙሉ በረከት ይሁን፡፡

መሰል ምርቃቶችን አሁንም በአባሪ ሁለት፡- ሥነቃል፡- የአፋርኛ ምርቃቶች ሥር ይመልቱ፡፡

በአጠቃላይ ከቀወት እና ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ውስጥ የተሰበሰቡት ልዩ ልዩ የሥነቃል ዘሮች በተወሰነ ይዘት ላይ የሚሽከረከሩ ይመስላሉ፡፡ ይኸውም የይዘት አጠቃሎ ወንድነትን ማዳነቅ፣ አቅመ-ደካማነትን ወይም ፈሪነትን ማብጠልጠል፣ ትጉህነትን፣ አምራችነት /ሞያተኝነት/ ማሞገስ፣ ስንፍናን ማንኳሰስ ነው፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት ሥነቃሎቹ ውስጥ ለማየት እንደተሞከረው ተደጋግመው የሚመጡ መዋቅሮችና የተመረጡ የመባያ ጉዳዮች ወይም ጭብጦች አሉ፡፡

በዚህም መሰረት ጥበባዊ ገለፃዎቹም ሆኑ ጥበባዊ አስተምህሮዎቹ (ተረቶቹ) ለግጭት ምንነት፣ መከሰት፣ መስፋፋት መሽከርከሪት ወይም ሙሻዙር ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ምክንያቱም ከሁለቱም ወረዳዎች የተሰበሰቡት የተለያዩ ሥነቃሎች ወንድነትን እና አምራችነትን /ሞያተኝነት/ የሚያደምቁ፣ የሚያሞክሹ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ወንድነትን የሚያገኑ ሥነቃሎች በሁለቱም ወረዳዎች መገኘታቸውም ወንዳ ወንድነትን እና ገዳይነትን የመትከል፣ የማግነን እና የማህዘብ አገልግሎት /function/ ስላላቸው ነው፡፡

ሥነቃሎቹ የያዙት መልዕክት ወንድነትን መሻት፣ ማግኘት እና ማድነቅ እንዲሁም ማጣት እና መናፈቅን የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም ደግሞ በተለያዩ መንገድ ይገለፃል፣ ይፆዳልም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦችም ግጭት እና እርቅ በዚሁ መልክ ይፆዳል፡፡ ከዚህም በመነሳት የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ሥነቃሎች ግጭትን በመትከል እና በማህዘብ ረገድ ተመሳሳይ ሚና እንደሚጫወቱ ለማሳየት እና ለማስጤን ተሞክሯል፡፡

በተለይም የግጭቱ ሁኔታ በአፈ-ታሪክ፣ በወንድነት መለዮና መግለጫዎች እየተተከለ፣ እየተስፋፋም አትንኩኝ ባይነት፣ ፀበኝነት፣ ተፋላሚነት፣ የጦር መሣሪያ ባለቤትነት እና ጦረኝነት እንደ አንድ ምጡቅ ሙያ፣ የወንድነትም መለኪያነት እየተቆጠረ፣ በማህበረሰቡም ዘንድ ጥልቅ ተቀባይነት እያገኘ በዓለምም፣ በመከራም ጊዜ ሁሉ የሚጠቀስ፣ የሚለፈፍ ሆኗል፡፡ ጦረኝነት በዓለም ጊዜ በሰርግ፣ በሥራ፣ በስመ-በዓል፣ ዘፈን፣ በእንጉርጉሮ፣ በሽላሎ፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በምሳሌያዊ ንግግር ይነሳል፡፡ በመከራ ጊዜም በለቅሶ ግጥሞች /በሙሾ/፣ በሽለላና በፉከራ ይጠቀሳል፣ ይወሳል፡፡

ግጭት ንፅረተ ዓለማዊ /ርዕዮተ ዓለማዊ/ ወይም ዓለማዊ አመለካከት እና አገልግሎታዊም ነው፡፡ ምክንያቱም ንፅረተ ዓለምና አገልግሎት ፎክሎር ህልውና ከሚያገኝባቸውና ከሚመሰረትባቸው፣ ከሚሸዝብባቸው ምክንያቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት የተጠኚዎቹ የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግጭትን የሚያዩበት ሁኔታ፣ ለግጭት ያላቸው አስተሳሰብ፣ ዝንባሌና ባህርይ እንዲሁም አድራጎት በሥነቃሎቹ ውስጥ መኖሩ ግጭቱ የባህል ሥሪትነት እንዳለው ያመለክታል፡፡

ግጭት ውስጥ ገብቶ ከግጭቱ ውስጥ ባሸናፊነት መውጣት የሚያስገኘው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ እና እሴትም አለ፡፡ ይህም የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች ንፅረተ ዓለም ወንድነትን ማረጋገጥ፣ መግለፅ፣ እና ማፅናት በዚህም ዝናን ማግኘት፣ ገዳይነትን መናኘት፣ ማሞገስና በውጤቱም ወይም ግቡም መከበር ማለትም ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቀዳሚነትን ማግኘት ነው፡፡ እነዚህንም አስተሳሰቦች ማለትም ግጭትን በአዎንታዊነት ማየት፣ የተጋጪንም ነፍስ ማጥፋት ከዚያም የገዳይነትን ሞገስ መላበስ መቻልን ግቡዕና ቅቡል አድርጎ መውሰድ የሁለቱ ሕዝቦች ንፅረተ ዓለም፣ እሴትና የሕይወት ግብ መሆን መቻላቸውን ከግብሮቻቸው እና ግብሮቻቸው ከሚገለፁባቸው ሥነ ቃሎቻቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የጀግንነት፣ የገዳይነትና የወንድነት ገላጭ ንፅረተ ዓላማዊ እና ዝንባሌ እንዲሁም ፋይዳ አዎንታዊነት አመለካቾች የሆኑ ሥነ ቃሎች በሁለቱም ሕዝቦች የሥነ ቃል ሀብት ውስጥ ተዘርተው ይገኛሉ፡፡

እንደሚታወቀው በዓለም ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች ሁሉ ከሀብት ምንጭ ባለቤትነትና አያያዝ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ የግጭቶቹ መታያና መገለጫ መንገዶቻቸው ግን የተለያዩ ሽፋን ሊኖረው ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት አንዳንድ ጊዜ ዘርን፣ ነገድን፣ ጎሳን፣ ባህልን /የሥራ ባህልን፣ ማህበራዊ ባህልን፣ ቋንቋን፣ ኃይማኖትን፣ ልማድን ወዘተ/ ሌላ ጊዜ ደግሞ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህና ዕኩልነት ማጣት ጥያቄዎችን መሰረት ያደረጉ መስለው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

ግጭቶቹ የተለያዩ ዓይነት ስምና ሽፋን ቢሰጣቸውም መስተጋቢያዎቻቸው ድርጊት መከሰቱን ማመላከቻዎቻቸው፣ ማስታወቂያ እና ማህዘቢያቸው እንዲሁም ማርገቢያዎቻቸው ጥበባዊነት ያላቸው ገለፃዎችና ተረኮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ሚዛን

ደፍቶ መናገር ይቻላል። ከዚህም ጋር አስተሳስሮ የግጭት ማባባሻዎቹና መፍትሄ ማምጫዎቹ በጥበባዊ ገለፃዎቹ ውስጥ ተሸምነው እንደሚገኙ መገመትና መፈተሽ የተገባ ይሆናል። ስለዚህም የአንድን ግጭት መከሰት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ነዳጅ እየሰጠ የሚያነቃው፣ ከክስተቱም በኋላ የሚያረግበው ወይም ሥር የሚያሰድደው እና ከትውልድ ወደ ትውልድም ይተላለፍ ዘንድ የሚያበቃው ማስተላለፊያ መሣሪያው ጥበባዊ ገለፃና ተረክ ነው ብሎ ለመደምደም ይቻላል።

# 8. የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ግጭቶች እና የግጭቶች አፈታት

ከዚህ በፊት በቀረቡት ምዕራፎች ውስጥ የተነሱት ጉዳዮች ለዚህ ምዕራፍ መንደርደሪያነት የቀረቡ ዳራዎች ነበሩ፡፡ በዚህም መሰረት መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈራቸው በተወሳበት ክፍል ቅርርብ ያላቸው መሆኑ፣ የሕይወት ወይም የኑሮ መግፊያ እና መተዳደሪያዎቻቸው በተወሱበት ክፍል የተፈጥሮ ሀብት ተሸምቶ መኖሩ፣ ማህበራዊ አደረጃጀቶቻቸው በተገለፁበትም ክፍል ተገዳዳሪነት ያላቸው መሆናቸው፣ የሁለቱ ሕዝቦች ከየት መጥነት ወይም ጥንተ አመጣጥ አፈ-ታሪኮች በተወጉበት ክፍል ፋክክር መኖሩ፣ የአፈ-ታሪኮቹ ማንጠሪያዎች እንዲሆኑ የቀረቡት ጽሑፍ ታሪኮች በተቃኙበት ክፍልም የተረክ ፋክክሩን የሚያጠናክሩ ታሪካዊ ተቃርኖዎች እንደነበሯቸው፣ እንዲሁም የሁለቱ ሕዝቦች ሥነቃሎች በተታዩበት ክፍል ለግጭት መከሰት እና ልማዳዊነት መሆን አስተዋፅዖ ያላቸው መሆናቸው ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ሁሉ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የግጭት ዳራዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ውስጥም ስለ ግጭት ምንነት፣ ዓይነት፣ አከሳሰት እና አፈታት የቀረበው ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ለተጠኚዎችም ሕዝቦች ግጭት እና ግጭት አፈታት የሚስማማ ተግባራዊ ብያኔ ለመቀንበብ ሞክሯል፡፡ ይሄውም ንድፈ ሐሳብ እዚህ ለተነሱት ነገሮች ማስተንተኛ ሆኗል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ በተጨማሪም በተለይ ከምዕራፍ አራት እስከዚህ ምዕራፍ የቀረቡት ጉዳዮች የግጭት ምንጭ ዳራዎች በዚህ እና በተከታዮቹም ምዕራፎች ውስጥ ተመላልሰው የሚነሱ እና የሚወሱ፣ ከምዕራ ሁለት ጋርም እየተሳሳቡ የትንታኔ እና ትርጓሜ መስጫ ማዕቀፎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ደግሞ አሁንም የሁለቱን ድንበርተኛ ወረዳዎች ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ሕዝቦች ውስጣዊ ማለትም እርስበርስ እና ውጫዊ ማለትም የድንበርተኝነት ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት መንሥዔዎች እንዲሁም ውስጣዊና ውጫዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶቻቸውን ለመመርመር ይሞክራል፡፡ ምንም እንኳን የዚህ ጥናት ዓቢይ ትኩረት የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት እና አፈታት ለመመርመር ቢሆንም ውስጣዊ ግጭቶቻቸውን እና አፈታቶቻቸውን ማካተት ያስፈለገው ለንፅፅርም ጭምር ያመች ዘንድ መሆኑ ሊታወስ ይገባል፡፡

በዚህም መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎችን ነዋሪዎች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭቶች መንሥዔዎች እንዲሁም የግጭቶች አፈታቶች በዚሁ በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

## 8.1. የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የግጭት መንሥዔዎች

የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች ግጭትን እንዴት ያዩታል ወይም ይመለከቱታል? ስለ ግጭት ያላቸው አመለካከትና ዝንባሌስ ምን ይመስላል? ፣ የግጭቶቹ መንሥዔዎች ወይም አጋጣሚዎች እና ክስተቶች ምን? ምን? ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች ሰንዝሬ ያሰባሰብኳቸውን ምላሾች እዘግባለሁ፡፡ በመጀመሪያ ግን በመስክ ሥምሪት ወቅት በአካባቢዎቹ ስዘዋወር የተመለከትኩትን እና የታዘብኩትን አስቀድማለሁ፡፡

ቀወቶች ግጭትን የሚለማመዱት ገና በህፃንነት ዕድሜያቸው ሳሉ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የአካባቢውን ህፃናት አስተዳደግ ሁኔታ በአንክሮ የሚያስተውል ሰው ሁሉ ህፃናቱ ተሻምቶን፣ ለራስ ማድላትን፣ እልህን የሚለማመዱት ገና በእናቶቻቸው፣ አባቶቻቸው፣ አሳዳጊዎቻቸው እቅፍ ውስጥ ሳሉ እንደሆነ መገንዘብ ይቻለዋል፡፡

እናቶች እና የሕፃናት ሞግዚቶች የሚያሳድጓቸው ህፃናት ምግብ የመመገብ ፍላጎት ሲቀንስባቸው የመመገቢያ ማባባያ ወይም ማግባቢያ ዘዴያቸው ምግቡን ወደ ራሳቸው አፍ ወይም ወደ ሌላ ታዳጊ አፍ በማስጠጋት "እየው ስበላብህ፣ በላሁብህ፣ ጠጣሁብህ፣ ልበላብህ ነው፣ ልጠጣብህ ነው፤ ሊበላብህ ነው፣ ልትበላብህ ነው፤ ሊጠጣብህ ነው፣ ልትጠጣብህ ነው" ወዘተ እያሉ ማስቀናት እና ማሻማት ነው፡፡ ይህም እንግዲህ ህፃናቱ በደመ ነፍስም ቢሆን እየተሻሙ እና እየጓጉ እንዲመገቡ ማድረጊያ ዘዴ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ እያደር ህፃናቱ እያደጉ በሄዱ መጠን አብሮ እያደገ የሚሄድ፣ የመሻማት መንፈስ፣ ዝንባሌ እና ልማድንም የሚተክል እና የሚያጠናክር ሊሆን ይችላል፡፡

ህፃናቱ ከእቅፍ ወርደው መዳህ፣ መንከላወስ፣ መራመድና መሄድ በቻሉበት ወቅት ደግሞ በራሳቸው አቅም ማነስም ይሁን በሌላ እንቅፋት ወይም ውልክፍት ተደናቅፈው ቢወድቁና ቢያለቅሱ ወይም በአጠገባቸው በነበረ ሰው ቢበሳጩ እና ቢነጫነጩ አሳዳጊዎቹ ማባባያቸው እና ማፅናኛቸው "የት አባቱ፣ ምናባቱ፣ መጥፎ፣

ባለጌ ወዘተ" እያሉ መስደብ፣ ህፃናቱም የሰሙትን ስድብ መልሰው እንዲሳደቡ ማድረግ እንዲሁም ደግሞ "ምራቅህን እንትፍ በልበት፣ ትፋበት፣ ምራቅሽን እንትፍ በይበት፣ ትፊበት፣ እርገጠው፣ እርገጪው፣ ምታው፣ ምቺው፣ ግደለው፣ ግደዪው እንዲሁም ይሄው እኔ መታሁልህ፣ መታሁልሽ" ማለትና ተውኔታዊ ዓይነት ምትም መፈፀም ነው፡፡ እነዚህም ድርጊቶች ህፃናቱ የስድብን፣ የድብደባን እና የብቀላን ባህርይ እየተላመዱ እንዲድጉ የሚያመቻቹ ሁኔታዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ህፃናቱ አቅማቸው ሲጎለብት ተውኔታዊውን ሁኔታ በግብር ያሳዩታልና ነው፡፡

የቀወት ወረዳ በርከት ያሉ አማሮች ወንዶች ልጆቻቸው ከህፃንንት ዕድሜ ከፍ ሲሉም ትከሻቸውን እየበጡ ጥንካሬ እና ኃይል ይሰጣል፣ ጥይት እና ቡዳ ይከላከላል ብለው የሚያምኑበትን ዕፅ ይቀብሩላቸዋል፣ ክንዶቻቸውም እንዲጠነክሩ እና ጡንቸኛሞች እንዲሆኑ በመመኘት በእሣት ይተኩሷቸዋል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ወኔያቸው ከፍ እንዲል፣ በወንድነታቸው እንዲከበሩ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደሚሉት ምን ጊዜም አረምና ጠላት ሳይዘሩት ስለሚበቅል ለመከላከል በመንፈስም በአካልም ዝግጁ መሆን ስለሚገባ ነው፡፡ "የነብር ዓይን ከፍየል፣ የፍየል ዓይን ከቅጠል" እንዲሉም አንዱ ለአንዱ ተኝቶ አያድርም፡፡ ስለዚህም አፀፋ መስጠት መቻልን እየተለማመዱ ማደግ ይገባል ይላሉ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ 06/09/2002፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002፣ አቶ ከተማ አይሻር 15/01/2003) ፡፡

ስለዚህም ቀወቶች የፀኝነትን መንፈስና ዝንባሌ መኮትኮት የሚጀምሩት ገና በህፃንነት እና በዳዴ ዘመናቸው መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡ ቀወቶች ግጭትን ከህፃንነት ዕድሜያቸው ጀምሮ እየተለማመዱ የሚያድጉ እንደመሆናቸውም በተለይ ወንዶች ልጆች ዱር መዋል ሲጀምሩ እና በዓመታዊ ክብረ በዓላት ወቅት እንደ ስፖርታዊ መዝናኛ የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ሁሉ ጉልበት የሚለካባቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌም ያህል ገና ወይም ጥንግ ጨዋታ፣ ለቡሄ ጅራፍ መግመድ፣ ማጮህ እና ግርፊያ ዓይነቶቹ ጉልበተኝነት የሚለካባቸው ናቸው፡፡ በገና ጨዋታ ጥንጓን ለማግኘት እና ለመምታት ሯጭነት፣ ሮጦ ደርሶም ተጋፊነት፣ ተጋፍቶ አንስቶም አክሮ መቺነት ጉልበት ይጠይቃል፡፡ ጉልበተኝነትም ያስከብራል፣ ያስደንቃል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጠንካራ ጅራፍ መግመድ እና ድምፁ በከፍተኛ ደረጃ እስከሚያስተጋባ ማጮህ መቻል እንዲሁ ጡንቸኛ ወይም ኃይለኛ ያሰኛል፡፡ በእኩያሞች መካከል የጅራፍ ግርፊያ ወይም መገራረፍ ጨዋታ ሲኖርም ጥሩ ተጋራፊ መሆን እንዲሁ ያስጀግናል፡፡

ግርፊያው ዓይን ካጠፋ፣ ብልት ካኮማተረ ወይም ካቆራመደም ደግሞ የግጭት ሰበብ ጭምር ይሆናል፡፡

የቀወት ልጆች ምራቃቸውን ከዋጡ፣ "ለአቅመ አዳም" እና "አቅመ ሔዋን" ከደረሱ፣ ከወለዱ፣ ከከበዱም በኋላ ቢሆን ዘገሮቹም ሆኑ መንፈሳዊ ትምህርት የቀሰሙት ሁሉ በፀሎታቸው ማሳረጊያ ላይ "ምቀኛ አታሳጣኝ፣ የምቀኛዬን አፍ አለምልምልኝ፣ ጠላት አታሳጣኝ" እያሉ ፀሎታቸውን ሲያሳርጉ ይደመጣሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ፡፡ ይህ ዓይነቱ አባባል በፀሎት ማሳረጊያ ላይ ለምን እንደሚታከል በአንክሮ የሚመለከት ነቂስ ታዛቢም በአካባቢው እምነት ምቀኛ እና ጠላት የወንድነትም የመሻሻልም ምንጭ ተደርገው እንደሚታዩ መገንዘብ ይቻለዋል፡፡ አመክንዮቱም እንደሚከተለው ነው፡፡

ቀወቶች ግጭትን የሚፈርጁትም ለመሻሻል እና "ጀሮ ለማውጣት" ማለትም ታዋቂ ለመሆን ምክንያት የሚሆን እና የሚበጅ የሚሉትን ቀላል፤ የሕይወት እና የንብረት ጉዳት የሚያስከትለውን ደግሞ ከባድ፣ አጥፊ እና የከረረ ፀብ እያሉ ነው፡፡ ይህ ግጭትን ቀላል እና ከባድ እያሉ የመፈረጅ ልማድም የመጣው ግጭቱ ያስከተለውን ወይም ግጭቱ ትቶት ያለፈውን ድህረ ሁኔታ በመመዘን እንደሆነ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ይናገራሉ፡፡ ሁኔታውን ከመረጃ ተባባሪዎቼ አንዱ የሆኑት አቶ ከፈለኝ ድረሴ (12/01/2003) ባጫወቱኝ ምሳሌ እንየው፡፡

ሁለት ሰዎች በአንዳች ምክንያት ቢጣሉ እና አወዛጋቢ ጉዳያቸውን በራሳቸው መጨረስ ባይችሉ በአንደኛቸው አነሳሽነት ወይም በጋራ ወይም በቤተ ዘመድ አማካኝነት ወደ ሽምግልና ቢቀርብ የሁለቱ ተቀናቃኞች ወቀሳ ተደምጦ እና ተመዝኖ የአንደኛው ወገን ሐሳብ ውኃ የሚያነሳ ማለትም እውነት ሆኖ በሽማግሌዎቹ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝለት "እከሌ የነገር ከሽ ከሽ አያውቅም፣ ነገሩ ጥብቅ ነው፣ ክርካር ነው፣ ዋዘኛ አይደለም" ወዘተ የሚል ስም ያስገኝለታል፡፡ ይህም በአካባቢው ስመ-ጥር ወይም ታዋቂ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ አሁንም ግጭት ውስጥ ከገቡት ወገኖች አንዱ ተበድያለሁ ብሎ ነገሩን ወደ ዳኛ ቢወስደው እና ዳኝነት ታይቶ ፍርዱ ለአንዱ ሲፈረድለትም "እከሌ በፍትህ ከሄደች በቅሎው ያለ ፍትህ የሄደች ጥርኝ ቆሎው ታንገበግበዋለች፣ እከሌ የነገር

ብልት ያውቀል፣ እከሌ የአደባባይ፣ የሸንጎ ሰው ነው፣ ዘንገኛ ወይም ተሟጋች ነው" ወዘተ የሚል ስም ያተርፍለታል።

ከሽምግልና እና ከፍርድ ቤት ውጪም ቢሆን ተሰድቦ ስድቡን ተቀብሎ የማይሄድ እና ተመጣጣኙን የሚመልስ፣ ሲሸለሉበት አፀፋውን የሚሰጥ፣ ሲመቱት ሲሉ መልሶ ካልገደልኩ የሚል ከሆነ፣ በትር ሲያሳርፉበትም መልሶ የሚመለጉድ ከሆነ "እከሌ አትንኩኝ ባይ ነው፣ ከነኩት ሰይጣን ነው፣ እከሌ ጥግ አትድረሱበት" ወዘተ ይባልለታል። ስለዚህም እንዲህ ዓይነት ሥም እና ዝና ማትረፍ የሚገኘው ከግጭት በኋላ በመሆኑ ግጭት አይጠላም። ፀበኝነት አይነወርም። የሚነወረው መጠቃት ነው ወይም ጊዜ ጠብቆ ጥቃትን አለመወጣት። አንድ የአካባቢው ነዋሪ እንደነገሩኝም ቀወት ውስጥ "እንኳንስ ግጭት ክፉም ቀን ቢሆን ሳይርቅም ሳይቀርብም ጥሩ ነው" ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም ወዳጅ እና ጠላትን ያስለያል። የ "ምቀኛ አታሳጣኝ" እና "ጠላት አታሳጣኝ" በፀሎት እርጋት ላይ መጨመርም ምክንያቱ ይሄው ነው ይላሉ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ አቶ ከፈለኝ ድረሴ ። በነገራችን ላይ በብዙ ቦታዎች የተለመደው የፀሎት ማሳረጊያም "ምቀኛዬን ያዝልኝ" እና "ምቀኛዬን ጣልልኝ" የሚል መሆኑንም ያጤኗል። ሌሎች የመረጃ ተባባሪዎቼም በአገላለፅ ቢለያዩም በዚሁ ሐሳብ ይስማማሉ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ 06/09/2002፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002፣ አቶ ከተማ አይሻር 15/01/2003) ።

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት የቀወት ወረዳ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች እርስበርሳቸው ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸውን ሁኔታዎች ዘርዘር አድርገው እንዲያጫውቱኝ አንስቼባቸው ነበር።

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደገለፁልኝ የግጭት ሰበቡ ብዙ ነው። ከእነዚህም መካከል ነገረ አኳን፣ የመሬት ይገባኛል ጉዳይ ማለትም የመሬት ጥበት እና ወረራ፣ ድንበር መጋፋት፣ በእርሻ ማሣ ላይ የሚለቀቅ የውኃ ፍሳሽ፣ የውርስ ሀብት፣ ንብረት ወይም ገንዘብ መካካድ፣ የከብት አፍ፣ ሴት ማለትም የሰው እጮኛ ወይም ሚስት መድፈር ማለትም ማማገጥ ወይም መጥለፍ፣ አፍ እላፊ፣ ማለትም በተለይም ዘርን መሰረት ያደረገ ስድብ (ይህንን የአካባቢው ነዋሪዎች አጥንት ማጉደፍ ይሉታል) ፣ ሐሜት ወይም ስም ማጉድፍ፣ አሽሙር፣ ለበጣ፣ ዘለፋ፣ እህል እና እንስሳት ሥርቆት ወይም ዘረፋ፣ ንብረት ቃጠሎ እንዲሁም የቆየ ቂም በቀል /አበደምነት/፣ በሐሳብ ልዩነት ወይም አለመግባባት፣ አለመጣጣም፣ በመጠጥ ሞቅታ እና የክብር ማስጠበቅ ጉዳይ

“ሰይጣን”፤ በእነዚህ በተጠቀሱትም ምክንያቶች ሁሉ የሚከተል ድብደባ ማለትም የሥጋ መቀጥቀጥ፣ የጭንቅላት መፈንከት፣ የደም መፍሰስ፣ የፊት ገፅ መበላሸት፣ የዓይን መፍሰስ፣ የሆድ መቀደድ፣ የእጅ ወይም እግር መሰንከል ማለትም የአጥንት ስብራት ወይም መከስከስ እና የሕይወት መጥፋት በግጭት መንሥዔነት ይጠቀሳሉ። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች እንደምን ግጭትን እንደሚያስከትሉም አንዳንዶቹን በየተራ እንመልከታቸው።

ከላይ እንደተገለፀው ነገረ አኳን አንዱ የግጭት መንሥዔ ነው። ነገረ አኳኋን የሚባለውም በአስተያየት፣ በፊት ገፅታ (ፈገግታና ቅጭምታ)፣ በአረማመድ እና በአካሄድ (ሰላ ብሎ በማለፍና አታሜ በመምታት)፣ በአቀማመጥ (ተስፋፍቶ፣ አንፈራጦ እና ሸርቆጥ ብሎ በመቀመጥ)፣ በጋቢ ወይም ነጠላ አከናነብ (ቅንድብን በመሸፈን እና ክንብንብን በማውረድ እና ባለማውረድ)፣ በበትር እና ጠመንጃ አያያዝ አቅጣጫ (በመዘቅዘቅ እና በድግን መልክ በመያዝ) ወዘተ ልዩነት የሚገለፅ እና ግጭትን የሚያስከትል አስተያየት፣ አካሄድ፣ አቀማመጥ፣ አከናነብ፣ መሣሪያ አያያዝ ትርጉማ ነው። እነዚህም ሁኔታዎች ሲጠቃለሉ አካላዊ እና ትዕምርታዊ የተግባቦት ገፅታዎች ናቸው። አካላዊ ተግባቦቶች በመሆናቸውም በባህሉ ተጋሪዎች ዘንድ የሚያስተላልፉት መልዕክት አዎንታዊ እና አሉታዊ ስሜት ይፈጥራል። በተለይም አሉታዊው ለፀብ እና ግጭት ይዳርጋል። ይህም ኢ-ንግግራዊ መግባቢያዎች በንግግር ከሚፈፀመው ተግባቦት ያላነሰ ምናልባትም የበለጠ ተግባቦትን ለመፈፀም እና መልዕክትን ለማስተላለፍ፣ ትርጉምም ለመስጠት ያገለግላሉ የሚለውን የእነ Samovar and Porter (1972፡169) ነቁሳዊ ምልከታ ጥናት ውጤት ያረጋግጥልናል።

በአካባቢው የግጭት መነሻ ከሚባሉት መካከልም አንዱ የመሬት ወረራ እና ውርስ የሚያስከትለው ነው። የመረጃ ተባባሪዎቼ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ 06/09/2002፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002፣ አቶ ከተማ አይሻር 15/01/2003) እንዳመለከቱትም እንዲያውም ይሄ ዋነኛው የፀብ መነሻ ነው። ይህ የመሬት ወረራ እና ውርስ ግጭት የሚፈጠረው ወላጆች ለልጆቻቸው፣ ልጆች ከሌሏቸውም ለቅርብ ወራሾቻቸው ድርሻ፣ ድርሻቸውን በኑዛዜ ቃል ሳያመለክቱ ከሞቱ በወራሾች መካከል “ይህ ለኔ ይገባኛል፣ አንተ ወይም አንቺ በዚያ ተወሰን ወይም ተወሰኚ” ዓይነቱ የይገባኛል ጥያቄ እና አተካራ ሳቢያ ነው።

የመሬት ጥበት አንዱ የአካባቢው የግጭት ምክንያት ነው፡፡ በዚህም አኳያ ጠፍ መሬትን በማቅናት ወቅት አንዱ የመነጠረውን አካባቢ ሌላኛው መጥቶ በሚያለማበት ጊዜ፣ አንዱ በሌላው ወይም በጎረቤቱ ማሳ ላይ እንስሳቱን በሚነዳበት፣ በሚያሰማራበት ወቅት መሬቴን በውኃ ታሸረሽራለህ በሚልበት፣ እንዲሁም በስጥ ማስጫ እና በአውድማ ሽሚያ እና መተነኳኮስ ምክንያት ግጭቶች ስለሚቀሰቀሱ ነው፡፡

ድንበር መጋፋት ሌላው የግጭት መንሥዔ ነው፡፡ በተለይ ለምነት እና ውኃ ገብነት ባላቸው ሥፍራዎች ይዞታን ለማስፋት ሲባል የድንበር ምልክት ቅርቃር በመግፋት ክንድም ይሁን ስንዝር መሬት ወደ ራስ ማሳ ወይም የአትክልት ቦታ በማስገባት ሂደት የሚመጣ ግጭት እንዳለ ነው የሚወሳው፡፡

በተዳፋትማ አካባቢዎች በተለይ በዝናብ ወቅት አንዱ ወገን የይዞታ መሬቱ በውኃ እንዳይሸረሽር እና ለማንጣፈፍም ሲል ከላይ በቦይ መርቶ በሚለቀው ወራጅ ውኃ ምክንያት ግጭት ይቀሰቀሳል፡፡ የሚቀሰቀሰውም ግጭት ይዞታን በውኃ ላለማስከላት በሚደረግ "ውኃህን በራስህ መሬት ላይ በቦይ አሳልፍ ወይም ወደ አንተ የሚመጣውን ውኃ በአግባቡ አልተከላከልህም" በሚል አለመግባባት እና አተካራ ሳቢያ ነው፡፡

በከብት አፍ ምክንያትም ግጭት የሚቀሰቀሰው እንስሳትን በሰው ሰብል ወይም ጥብቅ ሣር፣ በአውድማ፣ በማስጫ ላይ በመልቀቅ ምክንያት የሚመጣ ፀብ ነው፡፡

የቆየ ቂም በቀል ወይም አበ-ደምነት አንዱ የአካባቢው የግጭት መቀስቀሻ ነው፡፡ አበ-ደምነት የግጭት መነሻ የሚሆነውም በተጋጪዎቹ ወይም በተወላጆቻቸው መካከል የቆየ ከአባት፣ ከአያት፣ ቅድመ አያት የወረደ ደም መቃባት ሲኖር ነው፡፡ ይኸውም ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚሄድበት፣ እርቁም ፅኑ እና ዘላቂ የማይሆንበት፣ መበቃቃልንም የሚያስከትልበት ምክንያት ብዙ እንደሆነ ነው የሚሰማው፡፡ እንዲህ ዓይነቱም ፀብ የሚያገረሸው ድግስ ባለበት፣ የነተረ ጠላ እና ጠጅ በሚጠጣበት፣ አረቄ በሚታከልበት፣ ጨዋታ በደራበት፣ አዝማሪ ግጥም በሚቀበልበት እና የነሸጠውም በሚሸልልበት ወቅት እንደሆነ እነ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ (06/09/2002)፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ (13/09/2002)፣ አቶ ከተማ አይሻር (15/01/2003) አጫውተውኛል፡፡ በተለይ አቶ ከተማ አይሻር (15/01/2003) የጠላ እና የአረቄን ፀብ አነሳሽነት ሲያወሱልኝ ቀወቶች በመጠጥ አይታሙም፡፡ ይህም ሆኖ ግን መጠጥ ሲበዛ ነገር እንደሚያስከትልም ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ይህንንም የሚገልፁበት አባባል አላቸው፡፡ "አንድ አይቀመጥም፤ ሁለት አይጨለጥም፤ ሦስት ያሞቃል፣ ያጫውታል፤ አራት ያጨቃጭቃል /ያጣላል/፤ አምስት

ያደባድባል፤ ስድስት ያጋድላል" የሚል። ይሁንና ብሂሉ ቢኖራቸውም ግን ዋንጫ ከጨበጡ፣ ብርሌ ከአነቁ፣ መለኪያ ከያዙ እያወቁትም ቢሆን ፀብ ውስጥ መግባታቸው አይቀርም ብለውኛል። በተለይም በዚህ በመጠጥ ወቅት ጠመንጃ፣ ሽጉጥ ይዞ መፎከር የሚያስከትለው ጣጣ ብዙ እንደሆነም ነው የሚነገረው። ምክንያቱም አንዱን መሣሪያ ታጣቂ በቅርብ የሚያውቀውም ይሁን የማያውቀው ሰው የቆየ ያልተወጣው ቂም ወይም ደም እንዳለ ካወቀ በጠላ፣ በጠጅ እና በአረቄ ግፊት በለበጣ፣ በአሽሙር፣ ለአዝማሪ ግጥም በማቀበል ወዘተ አማካኝነት የረሳውን፣ የዘነጋውን ወይም ይዋል ይደር ያለውን ነገር ያስታውሰዋል። እንዲህ ዓይነቱም አድራጎት በአካባቢው የተለመደ ነው። በአካባቢው ልማድ አበ-ደሞች ወይም ደመኞች ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ደም የተቃቡ እና በአንድ ጣራ ወይም ዳስ ሥር የተሰባሰቡ ሰዎችን የዋለ ያደረ፣ የሰነበተ ደመኝነት እያስታወሱ ደሙን ሳይወጣ የቀረውን እና አርፎ የተቀመጠውን ሰው በነገር ልምጭም ይሸነቁጡታል ። በዚህ በመጠጥ ግፊትም በሚቀሰቀስ ሽለላ፣ ለአዝማሪ ግጥም መስጠት ወቅት ደሙን ያልተወጣውን ሰው ደሙን ስላለመወጣቱ፣ የወገኑ ደም ደመ-ከልብ ሆኖ ስለመቅረቱ እያነሳሱ ይለብጡታል። ወደ አዲስ ፀብም እየገፋፉ ያስገቡታል (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ 06/09/2002 ።

በወቅቱ ከአቶ ሰጥአርጌ (06/09/2002) እንደበት ከሰማኋቸውም መካከል የሚከተሉት ቅብብሎሾች ይገኙባቸዋል።

ፈሪ ብረት ገዛ ይገድል ይመስል፣
ከፍ ዝቅ ሲያደርግ ታፋውን ሊያቆስል።
ሽልለው ሽልለው ምንድነው ምላሹ፣
ባዲሱ ጠመንጃ ደምን ታልመለሱ።
ባዲሱ ጎራዴ ደምን ታልመለሱ።

በሽላሉ ግጥሙ መልዕክት መጎሸሙን የተረዳው ወገን ደግሞ ተነስቶ በበኩሉ ለጊዜው ደሙን ያልተወጣበትን ምክንያት ይገልፃል፣ በቀሉም እንደማይቀር እንዲህ በማለት ያውጃል (አቶ ሰጥአርጌ፣ 06/09/2002) ።

ኧረ ጅግራ በራ ከእንቁላሏ ላይ፣
ኧረ ቆቅም በራ ከእንቁላሏ ላይ፣
ላሳልፍ ያለ ሰው ሞኝ ይባላል ወይ፣
ወንድማችን ሞቶ ከርመን ሐዘን ላይ፣

ቤታችን ተቃጥሎ ከርመን አመድ ላይ፣
እንታረቅ ቢሉስ እርቁ ይፀናል ወይ፡፡

ደመኞችን ማቆጫጨቱ የሚገለፀው በሽላሎ እና በአዝማሪ ግጥም ብቻም አይደለም፡፡ አዋቂዎች የደመኝነትን ሁኔታ በእሳት ዳርም ይሁን በሌላ አጋጣሚ በሹክሹክታም ይሁን በይፋ በጨዋታ መሃል እያነሱ፣ ታዳጊዎችም ያንን እየሰሙ የሚያድጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሄም ታዳጎዎቹ ቂም እየቋጠሩ እንዲያድጉ፣ አቅማቸው ሲፈቅድም እንዲበቀሉ ይዳርጋቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደመኝነት ስለመኖሩ የደም ተቃቢዎቹ ተወላጆች ባያውቁም እንኳን ሌላው ከዳር ያለው ሰው ነገሩን በየአጋጣሚው በለበጣም፣ በአግቦም፣ ወዘተ እያነሳሳ ተወላጆቹን ስለሚያስታውሳቸው እና ስለሚጎናንጣቸው የደም ቤት ተወላጆቹ በአጋጣሚ ወይም በዕለት ግጭት ወቅትም ያንን በማስታወስ ፀቡን የሚያከሩበት እና የሚበቃቀሉበት ሁኔታ እንዳለ የመረጃ ተባባሪዎቹ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ 06/09/2002፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002፣ አቶ ከተማ አይሻር 15/01/2003) ገልፀውልኛል፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ በተተኳሪ ቡድን ውይይትም ወቅት እንዳረጋገጡት አቡ-ደምነት ጊዜ የማይሽረው ወይም የማያደበዝዘው የአዲስ ግጭት መከሰቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል የተፈፀመ መጎዳዳት እና መበዳደል ከነበረ በወቅታዊ ግጭት ሁኔታ ላይ “የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ” እንዲሉ ነገር ማባባሻ ይሆናል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)፡፡ ይህንንም የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱን አባባል ከአካባቢውም የተገኘው የሽላሎ ግጥም ጭምር ያረጋግጣል፡፡ ግጥሙ እንዲህ የሚል ነው፡፡

አሸዋ ላይ ፈሶ ጤፍ አይታፈስም፣
በአርባ[22] ዓመቱም ቢሆን ቂም አይበሰብስም፣
ቢቆይ ነው እንጂ የሰው ደም አይቀርም፡፡

[22] እዚህ ላይ ቁጥሩ ወጥ አይደለም ለግጥም እንዳመቻቸው ይመስለኛል የሚቀያይሩት እናም እስከ ሺ ይደርሳል፡፡

በአፍ እላፊ ምክንያት የሚከሰት ግጭት የሚባለውም ከዚህ በላይ በተጠቀሰው እና ከአበ-ደምነት ጋር ተያይዞ ከተገለፀው ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም የአፍ እላፊ ግጭት የሚባለው የሚቀሰቀሰው በጠላ፣ በጠጅ፣ በአረቂ መሸጫ ቤቶች እንዲሁም በሰርግ፣ በክርስትና፣ በሰንበቴ፣ በተዝካር፣ በደቦ ድግስ ላይ በጨዋታ እና በነገር አለመግባባት ምክንያት በአግቦ፣ በሽሙጥ ወይም ለበጣ እና አጥንት ማጉደፍ በመሳሰለው የሚቀሰቀሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱም ግጭት ባመዛኙ የሚቀሰቀሰው በመጠጥ ኃይል እና መገፋፋት ሳቢያ መሆኑ ይነገራል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)።

በሴት የሚነሳ ግጭት የሚባለውም ባል ወይም እጮኛ ወይም በቁባትነት አስቀማጭ ያላትን ሴት በመጥለፍ፣ በመቀማት፣ በማማገጥ ሳቢያ የሚቀሰቀስ ነው። ይኸውም በጥቅሉ በ "ሂያጅነት" ማለትም በአመንዝራነት ምክንያት የሚከሰት ግጭት ተደርጎ ይፈረጃል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)።

አጥንት በማጉድፍ ወይም ዘርን በማንቋሸሽ ምክንያት ግጭት የሚመጣውም አንድን ሰው በሌለበት በሐሜታ፣ ባለበት በለበጣ እንዲሁም በቀጥታ በመስደብ እና በማዃዘል ነው። ይኸውም በአካባቢው አጥንት ማጉደፍ ወይም ማጥቆር የሚባለው አንድን ሰው "አንተ ጠይብ፣ ባለእጅ፣ ቀጥቃጭ፣ ቡዳ፣ ባሪያ፣ አባትህን ጠርተህ እናትህን የማትደግም ወይም እናትህን ጠርተህ አባትህን የማትደግም፣ መጫኛ ነካሽ" ወዘተ ብሎ መስደብ ወይም ከላይ እንደተጠቀሰው በለበጣ "እከሌ እኮ አባቱን ጠርቶ እናቱን አይደግምም፣ እናቱን ቢጠራ አባቱን አይደግምም፣ አራት አያቱን አይቆጥርም፣ ስምንቱማ አይታሰብም" ወዘተ እያሉ የሰውን ትውልደ-ሐረግ እየመዘዙ እና እየቆጠሩ የጨዋ ልጅ አለመሆኑን ማመልከት፣ ማህበራዊ ክበሬታም ማሳጣት የመሳሰለው ነው።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶችም ሁሉ ድብደባ፣ አካል ማጉደል እና ግድያ ሊከሰት ይችላል። በዚህም መሃል ሁሉ ደግሞ ፀበኞችን፣ ተደባዳቢዎችን ለመገላገል ጣልቃ በሚገባበትም አጋጣሚ ሁሉ ያልታሰበ፣ ድንገተኛ ማለትም በአካባቢው የዕለት ግጭት የሚባለው ይከሰታል።

የዕለት ግጭት የሚከሰተው በተለይ ተጋጪዎችን በቅንነት ለመገላገል የገባው ሰው ባልጠበቀው ሁኔታ ከተገላጋዮቹ አንዱ ወገን ቢጎሸመው፣ በትር ቢያሳርፍበት ወይ በአንዳች ነገር ቢስተው ገለልተኛ ገላጋይነቱ ቀርቶ "ይቺን ይወዳል ይፋቴው!"፣ "ይቺን ይወዳል ቀወቴው!" ብሎ እራሱም ወደ ተደባዳቢነት ይገባል፣ ሚናውም ከገላጋይነት ወደ ፀበኝነት ይቀየራል (አቶ መኮንን በረደድ 19/01/2003፣ አቶ ከበደ መንገሻ 25/012003) ። እኚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንዳጫወቱኝ ቀወቶች ፀበኝነታቸውን የሚገልፁባቸው እና የሚፈፅሟቸው አነጋገሮች፣ ስድብ፣ ድብደባ፣ አተኳኮስ እና ግድያ የሚገለፁት ተለዋዋጭነት ባላቸው፣ ሁነቱንም ለዛ እና ደረጃ ባለው መልክ በሚገልፁ ቃላት ነው። ከስማኒቸውም መካከል ጥቂቶቹን እነሆ።

በንግግራቸው "የተናገረው አይለወጥ፣ "የተናገረው አይለበጥ"፣ "ቃሉ አይሥተሃቀር"፣ "ንግግሩ እሬት ነው" ፣ "ንግግሩ መሬት ጠብ አይልም፣ የሚወድቅ የለውም"፣ "ንግግሩ ሥፍር ነው" ፣ በፍርድ አሰጣጣቸውም "የፈረደው አይገለበጥ" ይላሉ።

ስድብ በተለያዬ መልኩ ማለትም ዘለፈው፣ ሞሸለቀው፣ ዘረጠጠው፣ አረከሰው፣ አጎደፈው፣ አነወረው፣ አገዘለው፣ አወራረደው፣ አንጨፈጨፈው፣ እስከ ዶቃ ማሰሪያው ነገረው፣ የጠባው ሳይቀር አወጥቶ ነገረው፣ ስድቦ ለሰዳቢ ሰጠው፣ ለበጠው ወዘተ በሚል ይገለፃል። እነዚህም ሁሉ የስድቡን ክብደት እና የሚያስከትለውንም ፀበንነት ደረጃ አመልካቾች ሆነው ይቆጠራሉ። ድብደባም እንዲሁ በተለያዬ የአገላለፅ ደረጃ ይገለፃል። ከአገላለፆቹም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ድብደባ በቀወቶች ዘንድ የሚገለፀው ክብደቱን ወይም ደረጃውን በሚለካ እና በሚያመለክት መልኩ ይመስላል። በዚህም መሰረት መታው፣ ነረተው፣ ወገረው፣ ተመተመው፣ ከካው፣ ወቃው፣ ወቀጠው፣ ፈለጠው፣ አጨደው፣ ቸበቸበው፣ ቀለጠመው፣ ቀጠቀጠው፣ ቆመጠው፣ ሰበረው፣ ለወሰው፣ አጨደው፣ አጠናገረው፣ ጨረገደው፣ ለሸለሸው፣ ፈነከተው፣ አዳሸቀው፣ አባዘተው፣ አደባየው፣ አሄደው፣ አረባየው፣ ከሸከሸው፣ ረገጠው፣ አዛረጠው፣ እንዳይሞት እንዳይድን አድርጎ ለቀቀው ወይም ተወው ወዘተ በሚል ይገለፃል። በነገራችን ላይ ቀወቶች በሰው አመታት ችሎታ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትም አስተራረድ ችሎታቸው "ያረደው አይፈራገጥ" እያሉ ይመካሉ። በዳኝነት ሥራ የተሰማሩ እና በሐቅ የሚፈርዱትንም "የፈረደው አይገለበጥ፣ የተናገረው አይለበጥ" እያሉ ያኳሻሉ።

ቀወቶች ለአተኳኮስም ደረጃ ይሰጣሉ፡፡ ለአብነትም በጭንቅላቱ፣ በግንባሩ፣ በደረቱ፣ በሽንጡ፣ በታፋው፣ በጉልበቱ ላይ ከተተበት፣ አገባበት፣ አገባበት፣ ለቀቀበት፣ አጋየው፣ ቆጋው፣ ቆላው፣ አርከፈከፈበት፣ አነደደው፣ አቃጠለው፣ ጠቀጠቀው፣ ቆጠረበት፣ ለቀቀበት ወዘተ ይላሉ፡፡

አገዳደልም ቢሆን የሚገለፀው የአጋዳደሉን ደረጃ በሚያመለክት፣ የሚቹንም ወገን በሚያቆጫጭ መልኩ ነው፡፡ እከሌ እከሌን ወይም የእከሌን ልጅ፣ ወንድም፣ እኅት፣ ዘመድ ደፋው፣ ቆጋው፣ አጨሰው፣ አንጫረረው፣ አደበነው፣ አጠናቀቀው፣ ከነበለው፣ አሰናበተው፣ አከረረው ፣ ከነተረው፣ ሲጥ አረገው ወዘተ በሚል ይፈረጃል፡፡

በእነዚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ አገላለፅ መሰረትም ከዚህ በላይ የተጠቆሙትን እና የተዘረዘሩትን፣ በደረጃም የተገለፁትን የስድብ የአመታት፣ የአገዳደል ሁኔታዎች በሙሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ቀላል እና ከባድ ግጭት እያሉ በመፈረጅ ይመድቧቸዋል፡፡

ለማጠቃለል ያህልም በቀወቶች ዘንድ ቀላል ግጭት የሚባሉት የሚከሰቱት በነገረ አኳኋን ማለትም በአስተያየት፣ በአረማመድ፣ በአነጋገር ሁኔታ ማለትም በዓይን ቂጥ በማየት፣ በግንባር በመናገር፣ በአረማመድ ሁኔታ ማለትም በሰው ፊት ሲያልፉ ሰላ ባለማለት እና በመጣሰስ፣ በአለባልታ፣ በከብት አፍ፣ በዶሮ፣ በስጥ ማስጫ፣ በእንስሳት ማስወጫ እና ማሰማሪያ፣ በልጆች እና ሴቶች ጭቅጭቅ በነገር አለመግባባት፣ በአጥር ወይም ድንበር መግፋት፣ በመስኖ ውኃ፣ በመጠጥ ውኃ መቅጃ፣ በመጠጥ ግፊት እና ቀላል አፍ እላፊ ምክንት የሚቀሰቀሱ እና ባለመግባባት፣ "ቆይ ታየኛለህ!፣ ጠብቀኝ!" ወዘተ ስድብ እና በዛቻ የሚገለፁ እና የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት የማያስከትሉ ናቸው፡፡

በቀወቶች ዘንድ በአንፃራዊ ሁኔታ ከባድ የሚባሉት ግጭቶች ደግሞ በአበደምነት፣ በመሬት ይገባኛል፣ በንብረት ወይም ገንዘብ መካካድ፣ በአጥንት ማጉደፍ፣ በሴት ወዘተ ምክንያት የሚቀሰቀሱት እና የአካል፣ የነፍስ እና የንብረት ጥፋት የሚያስከትሉቱ ናቸው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)፡፡

ከዚህ በላይ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደገለፁት እና በምሳሌዎችም እንዳመለከቱት የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች ግጭትን የሚያዩት እንደ አይቀሬ የሕይወት

አካል አድርገው ነው። ምክንያቱም በምሳሌያዊ ንግግሮቻቸውም ውስጥ “ሰው እንኳን ከሰው ከራሱስ ጋር ይጣላ የለም ወይ?”፣ “ሰው ሆኖ ሳይጋጩ መኖርስ እንዴት ይቻላል?”፣ “እጇን በእጇ ቆረጥኩት”፣ “ነገሩ እጇን በእጇ ነው”፣ “አፍ ከእጅ ይጣላል” ፣ “የሆድ ጠላቱ አፍ ነው” ፣ “እጅ በአፍ ይጠናል/ ይጨክናል” ። ወዘተ የሚል ብሂል አላቸው። ግጭት ሩቅ ነገር አለመሆኑን ለመግለፅ። ግጭት የመቀራረብ፣ የአብሮነትም፣ የግንኙነትም ውጤት መሆኑንም ለማመልከት። በጥቅሉም ግጭት በአብሮነት፣ በእሴትነት፣ በተግባቦት እና በልማድ ምክንያት የሚቀሰቀስ መሆኑን ለማስገንዘብ።

ከዚህ በማስከተል ደግሞ ቀወቶች በተለያዩ ምክንያት የሚያፈሯቸውን ግጭቶች እንደምን እና እንዴት እንደሚፈቷቸው እንመለከታለን።

## 8.2. የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የርስበርስ ግጭቶች አፈታት

ቀወቶች የሚያጋጥሟቸውን የእርስበርስ ቀላልና ከባድ ግጭቶች እንደምን ይፈታሉ? የሚለውን ሁኔታ ማወቁ በአንድ በኩል የውስጥ ግጭት አፈታት ሥርዓታቸውን ለማወቅ ስለሚረዳ በሌላ በኩል ደግሞ የውስጥ ግጭቶችን ለመፍታት የሚከተሏቸው ሂደቶች እና የሚፈፅሟቸው ሥርዓቶች ከአፋሮች ጋር ከሚፈፅሟቸው የእርቅ ሂደት ሥርዓቶች፣ አፈፃፀሞች እና እርጋቶች ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማጤን ስለሚበጅ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) እና የአካባቢው ነዋሪዎች የነገሩኝን እና ያረጋገጡልኝን እንደሚከተለው እዘረዝራለሁ።

እንደ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ (አቶ መኮንን በረደድ 19/01/2003፣ አቶ ከበደ መንገሻ 25/012003) እና አካባቢውም ነዋሪዎች አገላለፅ ቀወቶች ቀላል እና ከባድ ውስጣዊ ማለትም የእርስበርስ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱት በብዙ መንገዶች ነው። በዚህም መሰረት ከቀላል እስከ ከባድ የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶች እዚህ በቀረቡበት መንገድ በቁስ፣ በመነኩሴ፣ በአዋቂ ወይም በጠንቋይ፣ በሰፈር ሽማግሌ፣ በአገር ሽማግሌ፣ በመንግሥት የፍትህ መዋቅር፣ አገር በማስለቀቅ ወይም በማሰደድ ወዘተ አማካኝነት ሁሉ የሚፈቱበት አጋጣሚ አለ።

ከዚህ ርዕስ በፊት በቀረበው "የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች የግጭት መንሥኤዎች" ሥር እንደተገለፀው ቀላል እና ከባድ የሚሰኙ ግጭቶች አሉ፡፡ ቀላል የሚሰኙትም ግጭቶች መነሻቸው ብዙ ቢሆንም ከከባድ ስድብ ወይም ዘለፋ፣ ነቀፌታ፣ ከከባድ የጥቃት ሙከራ፣ ከድብደባ፣ ከአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት ወዘተ በመለስ ያሉት ናቸው፡፡ በአጭሩም የሰው ሕይወት ያልጠፋባቸው፣ ከባድ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ያልተከሰተባቸው፣ ለዘወትርም የሚያስከነክን የአፍ እላፊ ያልተፈፀመባቸው ግጭቶች ናቸው፡፡ እነዚህም በቤተሰቦች ወይም ቤተ ዘመዳሞች፣ በጎረቤታሞች፣ በአንድ ጎጥ ነዋሪዎች፣ በሰንበቴ ወይም ፅዋ ማህበርተኞች፣ በዕድርተኞች፣ በዕቁብተኞች፣ በአብሮ በላዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው፡፡

በቀላልነት የተፈረጁትም ግጭቶች የሚፈቱት በአመዛኙ በየደረጃው ባሉ የቤተሰብ እና የጎጥ ወይም የመንደር ሽምግልናዎች እና አዋቂዎች /ጠንቋዮች/ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ቀላል ግጭቶች በቅርብ ቤተሰቦች መካከል ሲከሰቱ በቤተሰቡ ኃላፊዎች አባት፣ እናት እንዲሁም ቤተ ዘመዶች ማለትም በአጎት፣ በአክስት፣ በጡት አባት፣ በጡት እናት፣ በክርስትና አባት፣ በክርስትና እናት፣ እንዲሁም ነገሩ ከረር ሲል በንስኃ አባት ሽምጋይነት እና ገላጋይነት ሊፈቱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡

በቅርብ ቤተሰቦች መካከል ከሚፈጠሩት ግጭቶች መካከል የሚካተቱትም የባልና ሚስት እና የወላጆች የልጆች እንዲሁም የልጆች የርስበርስ አለመግባባት ወይም ጭቅጭቅ ዓይነቶቹ ነው፡፡ ለዓብነትም የባልና ሚስት አለመግባባት እንደምን እንደሚከሰት እና እንደሚፈታ እንመልከት፡፡ የባልና ሚስት አለመጣጣም የሚባለው የሚከሰተው እና የሚገለጠው አልጋ በመለየት፣ ትዳርን ቸል ማለት፣ ዲቃላ በመውለድ፣ ዲቃላ ልጅን ያለ አንዳች እውቂያና ካሣ ወደ ቤት በማስገባት፣ ገንዘብ በማግለል፣ በትዳር ላይ በመማገጥ ወዘተ ሳቢያ ነው፡፡

ከላይ የተገለፀው ዓይነት የባልና ሚስት ግጭትም የሚፈታው የግጭቱ ሁኔታ ለብዙ ቤተሰብ ሳይነዛ ወይም ሳይነገር በሚስጢር ተይዞ ለንስኃ አባት ብቻ በመግለጥ ነው፡፡ የንስኃ አባትም ጉዳዩን ካብላሉ፣ ባልና ሚስቱንም ለማወያየት ከሞከሩ በኋላ ከቻሉ ብቻቸውን፤ ካዳገታቸውም የባልና ሚስቱን ወላጆች ወይም እጅግ የተወሰኑ የባልና ሚስቱን ኑሮ ውስጥ አዋቂዎችና ታማኝ አብሮ በላዎች ይዘው የሚያዩበት እና እልባትም የሚያስጡበት ነው፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቼ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት እንዳወሱልኝም የባልና ሚስት ፀብ ብዙውን ጊዜ ምሥጢራዊ መወቃቀስ እና ምክክር ተደርጎበት ስምምነት ላይ ከተደረሰ በበዳይነት የተፈረጀው ወገን ካሣ ከፍሎ አለመግባባቱ በእርቅ ይደማደማል፡፡ ካሣውም ከሽምጋዩ ወይም ሽምጋዮቹ ውጪ ለሆኑ ሰዎች ካሣነቱ የሚታወቀው "ይህቺን ላም ወይም በሬ የግሏ /የግሉ እንዲያደርግ ተስማምተናል እያሉ ከተናገሩ ነው፡፡

በባልና ሚስት መካከል ከሚከሰቱ ግጭቶች ሁሉ ለመሸምገል አስቸጋሪ የሚሆነው በተለይ አልጋ የመለየት ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ አልጋ የመለየት ጉዳይ ከንስኃ አባት ሽምግልና በላይ የሚሆንበት እና ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ሁኔታ እንደሚያጋጥም ይነገራል፡፡ ይኸውም የሚሆነው ብዙውን ጊዜ አልጋ የተለየበትን ምክንያት ባል እና ሚስቱ ይፋ በማያደርጉበት ወቅት ነው ይባላል፡፡ እንደ ብዙዎቹ የመረጃ ተባባሪዎቼም አልጋ የለዩ ባልና ሚስት አልጋ የለዩበትን ምክንያት የማይናገሩት አንደኛቸው የተፈጥሮ ግዴታቸውን ለመወጣት መሄድ ሲሳናቸው እና ሌላኛቸው ደግሞ ገና ብርቱ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ሳይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ፡፡

በቤተሰብ ግጭትነት ከሚታዩት መካከል ቀደም ሲል እንደተጠቆመው የወላጆች እና የልጆች እንዲሁም የልጆች እርስበርስ አለመግባባት ናቸው (አቶ መኮንን በረደድ 19/01/2003፣ አቶ ከበደ መንገሻ 25/012003) ፡፡ እነዚህም የሚመነጩት በወላጆች ልጆችን የመቆጣጠር ከፍተኛ ፍላጎት፣ ማደሪያቸውን የመወሰን ሁኔታ፣ የጉልማ ማለትም የወደፊት መተዳደሪያ እርሾ የሚሆን ንብረት አሰጣጥ፣ የውርስ ድልድል ወዘተ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው፡፡ ከመረጃ ተበባሪዎቼ እንደተረዳሁት እነዚህም ዓይነቶቹ ግጭቶች በቅርብ ዘመዶች እና በንስኃ አባቶች ሽምጋይነት የሚፈቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አቅም በላይ ሲሆኑም ወደ ከፍተኛ ግጭት ፈቺዎች የሚሸጋገሩበት ሁኔታ አለ፡፡

በአካባቢው ሰው ሰራሽ ችግር ሲከሰት እና የችግሩ ፈጻሚ ባልታወቀበት ሁኔታ የሚነሳ መቃቃርን እና ጉምጉምታን ደግሞ "አዋቂ" ወይም በጠንቋይ የመፍታት ልማድም አለ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡-አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)፡፡ በዚህም መሰረት በግብርና እና በባልትና ውጤቶች

ማለትም በአውድማ ምርት፣ ገለባ፣ ድርቆሽ፣ ሣር፣ በዱር አትክልት፣ ሰብል፣ በቤት ዕቃ፣ በስጥ ማፌስ፣ በዱቄት መዛቅ፣ በባልትና በንብረት መቆንጠር ወይም ሥርቆት፣ በአልባሳት በተለይም በአዲስ ልብስ ባልታወቀ ሁኔታ መቦጨቅ፣ በአሉባልታ፣ "በሰለባ" ማለትም ምርት በአስማታዊ ኃይል ከአንዱ ወደ ሌላው ተዟዙሯል በሚል እምነት ምክንያት፣ የኃይማኖታዊ ቁሶች እና ዕላቶች ሥርቆት ወዘተ የሚቀሰቀሱ ግጭቶች በ "አዋቂዎች" /ጠንቋዮች/ ይፈታሉ ተብሎ ስለሚታመን ወደ እነዚሁ አካላት የሚቀርብበትና የሚታይበት ልማድ አለ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ለእነዚህ "አዋቂዎች" /ጠንቋዮች/ ለሚባሉት ወገኖችም የሚቀርቡት ጉዳዮች ባመዛኙ ሲታዩ በቂ ማስረጃ ማቅረብ የማይቻልባቸው እና በጥርጣሬዎች ላይ የተመሰረቱ ሁኔታዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከቅርብ ቤተሰብ ውጪ የሚፈጠሩት ግጭቶች ደግሞ ተጋጪዎቹ በሚገናኙባቸው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የማህበራዊ ግንኙነት መፍጠሪያዎች ማለትም በሰንበቴ /ፅዋ/ ማህበር፣ በዕድር፣ በዕቁብ አባልነት የሚገናኙ ሰዎች ግጭቶች ደግሞ በእነዚሁ ስብስቦች በሚመረጡ ሽማግሌዎች ሽምጋይነት እና ገላጭነት የሚፈቱበት ሁኔታ እንዳለ ከላይ በተተኳሪ ቡድን ውይይትተሳታፊነት የተጠቀሱት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እና የአካባቢው ነዋሪዎች ሁሉ ይገልፃሉ፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በቅርብ ቤተሰቦችም ሆነ በማህበራዊ ግንኙነት ተጋሪዎች መካከል የሚፈጠሩ ቀላል ግጭቶች በሰፈር ሽማግሌዎች ሽምግልና ሲፈቱ ማሳረጊያው በአጥፊነት የተፈረጀው ወገን ይቅርታ እንዲጠይቅና ተገላጋዮቹ "ይቅር ለእግዚአብሔር" እንዲባባሉ እና እህል ውኃም በጋራ እንዲፋተቱ ማድረግ ነውየመረጃ ተባባሪዎቹ (አቶ ስጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)፡፡

በአጠቃላይ በቀወቶች ዘንድ ቀላል ግጭቶች በሚል የሚፈረጁ ግጭቶችን ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውሉት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የግጭት መፍቻ መንገዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሱት ቀላል ግጭቶች ወደ ከባድ ግጭትነት ከተሸጋገሩ እና በአጋጣሚውም የጉልበት ወይም ኃይል ሥራ ከታከለበት ግጭቶቹ ሙሉ በሙሉ ከጎጥ ወይም መንደር ሽማግሌ ሽምግልና አልፈው ወደ አገር ሽማግሌ ሽምግልና የሚደርሱበት እና የሚፈቱበትም አጋጣሚ እንዳለ ከተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት የመረጃ

ተባባሪዎቹ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ተረድቻለሁ።

የመንደር ሽማግሌዎች ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት የግጭት መንሥዔዎች በተጨማሪም እጮኛ ወይም ባል ያላትን ሴት በማማገጥ እና መጥለፍ ሳቢያ የሚነሱ ግጭቶችን ይሽመግላሉ። ግጭቶቹ ድብደባና የአካል ጉዳት ያስከተሉ ከሆኑ የመንደር ሽማግሌዎቹ ለተጎጂ ወገን የማስታመሚና የደም ማድረቂያ አስሰጥተው እርቁ ተጎጂው ለአደባባይ ሲበቃ እንዲፈፀም ይቀጥራሉ። ተጎጂው ለአደባባይ ሲበቃም እንደ ጉዳቱ መጠን የካሣ ክፍያ ይቆርጣሉ። ጉዳቱ አነስተኛ ከሆነም ተጎጂ በደም ማድረቂያው ካሣ ብቻ እንዲቀር በማድረግ እንዳይከዳዱ መኃላ በማስፈፀም ያስታርቃሉ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡-አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ፡፡

በሌላ በኩል ቀደም ሲል ከላይ በተዘረዘሩት ቀላል ግጭቶች ውስጥ የገቡት ሰዎች የቅርብ ቤተሰብነት፣ ዝምድና እና ማህበራዊ ግንኙነት የሌላቸው የአንድ አካባቢ ወይም ቀበሌ ወይም ድንበርተኛ ቀበሌዎች ነዋሪዎች ከሆኑ ግጭቱን ለመፍታት ጥረት የሚደረገው በአመዛኙ የሁለቱን ተጋጪዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክበሬታ በሚያወቁ ሰዎች ኅትኅችነት እና አነሳሽነት እንዲሁም ተጋጪዎቹ በጋራ በሚመርጧቸው እና በሚሰይሟቸው የአካባቢ ወይም የአገር ሽማግሌዎች ወይም የሁለቱ ቅይጥ ሽምግልና ነው። አንዳንድ ጊዜም የተጋጪዎቹ ግጭት ውስጥ መግባት የሚያሳስባቸው የመንደር እና የአገር ሽማግሌዎች ራሳቸው በራሳቸው ተነሳስተው ተጋጪዎቹን ወገኖች አቀራርበው የሚሽመግሉበት ሁኔታ አለ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)። ይሁንና እንዲህ ዓይነቱን "ተስማሙልንና ታረቁልን" ጥያቄ ከአካባቢም ሆነ ከሰፈር እና ከአገር ሽማግሌዎች የሚያገኙት ተጋጪዎቹ ወገኖች በምግባራቸው የተመሰገኑ፣ በኑሯቸው የደረጁ፣ የአገር አዋይ፣ የአገር አባት፣ የአገር አውራ የሚባሉ ዓይነት ሰዎች ናቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቋቆሙት ቀላል ግጭቶች በመንደርና በአገር ሽማግሌ የሽምግልና ደረጃዎች ሳይፈቱ ሲቀሩ ደግሞ ወደ ቀበሌ ሸንጎና ወደ ወረዳ ፍርድ ቤትም

የሚሄዱበት ሁኔታ አለ፡፡ ተጋጪዎቹ ወገኖች ከመሰረታዊ ግጭታቸው ውጪ እያለፉ ማህበራዊ ደረጃቸውን የሚነካኩ እና አጥንት ማጉደፍ ማለትም ዘር ቆጠራ እየገቡ አፍ እላፊ ካከሉበት እስከ መገዳደልም ይደርሳሉ፡፡ ቀወት ውስጥ መገዳደል ብርቅ አይደለም፡፡ ነጋ ጠባ የሚፈፀም ልማድ ነውም ብለውኛል፡፡

በቀወት አማሮች ዘንድ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ልማድ መሰረት እንኳንስ ሰው መግደል[23] ኃይለኛ የዱር አውሬ[24] አንበሳ፣ ነብር፣ ዝሆን፣ አውራሪስ፣ ድኩላ፣ ሰስ ወዘተ መግደልም የወንዶች ቁንጮ ሲያሰኝ እንደኖረ ይተረካል፡፡ ዛሬም ቢሆን ታዲያ ገዳይነት ቁንጮ ያስደርጋል፡፡ ሎቲ ያስጠለጥላል፡፡ ያስጎፍራል፡፡ ሹሩባ ያሰራል፡፡ ክብር ያስጨምራል፡፡ ሰው መግደል ደግሞ ከዚህ ሁሉ ይልቃል፡፡ ስለዚህም አንድ ሰው በገደላቸው ሰዎች ቁጥር ልክ የፈረስ ወይም የሞጋሳ ሥም እንዲያገኝ ያስደርጋል፡፡ ለምሳሌም አንድ ሰው የገደለ "በሃቱ"፤ አሥር የሞላ "ቢተዋ" ይባላል፡፡ ስለዚህ ታሪካዊ ጠላትን፣ የእምነት ተቀናቃኝን ብቻም ሳይሆን የእምነት ወገንንም ቢሆን መግደል ያስከብራል፡፡

የከባድ ግጭትም መታያው እና መገለጫው ግድያ ነው፡፡ ስለዚህም በግጭቱ ሂደት የሰው ሕይወት የጠፋ እንደሆነ ሽምግልናው የሚያዘው በአገር ሽማግሌዎች ነው፡፡ ሽምግልናውም እንደ ተሸማጋዮቹ እና እንደ ሽምጋዮቹ ስምምነት እና ፍላጎት በተለያዩ ሥፍራ እና በበዓላት ቀን ሊካሄድ ይችላል፡፡

የአገር ሽማግሌዎች የሚባሉትም በነገር ብልት አዋቂነታቸው ማለትም "ነገር የበሉ" ማለትም የተረዱ ወይም ጠንቅቀው ያወቁ በመሆናቸው፣ ተደማጭነታቸው፣ ምክር አዋቂነታቸው፣ በተጋጪዎቹ መካከል እርቀ ሰላም ካልተፈጠረም ሊመጣ የሚችለውን ነገር ሁሉ አስቀድመው በመገመት ችሎታቸው፣ በተከበረ የአኗኗር

[23] ቀወቶች ሰው መግደል እንደሚበጅ በሥነቃሎቻቸው ሁሉ ያረጋግጣሉ፡፡ "ሰው ግደሉ ሰው መግደል ይበጃል፣ ሰው ያልገደለ ሰው ሲሄድ ያንጎላጃል" እንደሚሉት፡፡ ይሁን እንጂ የራሳቸውን አካባቢ ተወላጅ ሲገድሉ ደግሞ ደም መቃባቱም፣ መበቃቀሉም፣ እርቅም ቢወርድ ደግሞ አካባቢ መልቀቁም ሁሉ አለ፡፡ ስለዚህ ሰው በመግደል የሚገኘው ክብር ከፍ የሚለው ከአካባቢያቸው ያልተወለደን በአንፃራዊ ደረጃ "ሌላ ሊባል የሚችል" ሰው ሲገድሉ ወይም ቡደን ሲመክቱ እና ሲቋቋሙ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንንም በምሳሌ ማስደገፍ ይቻላል፡፡ በቀወት ወረዳ በተለይም ጥናቱ በተካሄደባቸው ቀበሌዎች ውስጥ አየለ አገር፣ ታዬ አገር፣ ተሰማ አገር ወዘተ በሚል የሚታወቁ ጎጦችም፣ ሰፈ አከባቢዎችም ይገኛሉ፡፡ የእነ እከሌ አገር እንዲሉ፡፡ እነዚህም ሥያሜዎች የተገኙት ከግለሰቦቹ የወንድነት ሙያ ጋር ጠያይዞ እንደሆነ ይጤኗል፡፡

[24] የቀወት አረጋውያን እንደሚተርኩት ቀደም ባለው ዘመን እና እስከ አፄ ኃለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ አንዳንድ የቀወት ተወላጆች እዚህ የተጠቀሱትን የዱር አውሬዎች በአካባቢያቸው ባያገኙ እንኳን ወደ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተጉዘው ገድለው ይመለሱ እና የግዳይ ሰለባ ወይም ውጤት ያስመርቁ ነበር፡፡ ይሄም የክብር መግለጫ ሆኖ በቁምም በሙትም ከፍ ያለ ዋጋ ወይም አገልግሎት ሲያስገኝ ቆይቷል፡፡

ሥርዓታቸው፣ በተከበረ ሥነ ምግባራቸው እንዲሁም በቤተ ትውልዳቸው ጨዋነት እና ተከባሪነት እና ተቀባይነት ያላቸው፣ በአገር ልማድ እውቀታቸውን ዕድሜያቸው የበሰሉ አንቱ የሚሰኙ በፆታም ወንዶች የሆኑ ናቸው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ፡፡

ወደ ከባድ ግጭት ሽምግልናው ሂደት እና አፈፃፀም ሁኔታ እንመለስ፡፡ የደም መቃባት ሲከሰት ሽምግልው የሚያዘው እና እርቁ የሚፈፀመው እንደ ግጭቱ አከሳሰት፣ እንደ ተጋጪዎቹም ማንነት ሁሉ በተለያዩ ሁኔታዎች ነው፡፡ የሽምግልና እና እርቁ ሁኔታዎቹም የሚወሰኑት እንደተጋጪዎቹ የወገን፣ የሀብት፣ የከበሬታ ደረጃ ነው፡፡

በአካባቢው በወገንም፣ በሀብትም፣ በጨዋነታቸውም ስመ ጥር የሆኑ፣ የታወቁ ሰዎች ከባድ ግጭት ውስጥ ሲገቡ በአገሩ ላይ የታወቁ ሽማግሌዎች በነገሩ ሽምግልና ይገቡበታል፡፡ ለአገር ሽማግሌዎቹ የሚከብዳቸውም ሲሆን የተከበሩ ቀሳውስትና መነኮሳት ይታከሉበታል፡፡ ተጋጪዎቹ ለአገር ለሽማግሌ እንዲገዙም የአካባቢው አድባራት መስቀል ጭምር ወጥቶ ይማለዳሉ፡፡ በዚህ መልኩ ሽምግልናው እንዲያዝ እና እንዲጀመር ስምምነት ከተደረገ በኂላም የሽምግልና ሥፍራ መረጣ ይደረጋል፡፡

የከባድ ግጭት ሽምግልናውም ሥፍራ የሚመረጠው ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው በተጋጪዎቹ ወገኖች እና በሽምጋዮቹ ስምምነት ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ሽምግልናው በዲብ /ኮረብታ/፣ በጫካ፣ በወንዝ፣ በቤተክርስቲያን ሊደረግ ይችላል፡፡ ቀናቱም ወንድ በዓላት ቀናት /አቦ፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ፣ መድኃኔ ዓለም እና በዓለወልድ ዕለተ ክብሮች/ ናቸው፡፡ ሽምግልናውም በአመዛኙ ቀን፣ ቀን፣ አልፎ አልፎ ሌሊት ሊደረግ ይችላል፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደነገሩኝ ሴት በዓላት ለነፍስ ግድያ ሽምግልና አይመረጡም፡፡ በሴት በዓላት የሚደረገው የመለስተኛ ግጭቶች ሽምግልና ነው፡፡

የሽምግልናው ሥፍራ አመራረጥም የተጋጪዎቹን ዝንባሌ ከግምት ያስገባ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንዳንዶች የሽምግልናው መጀመር እሰው ጆሮ እና አፍ እንዳይገባ ልጅ፣ ሴት፣ ሕዝብ ከማይደርስበት ሰዋራ ሥፍራ በጫካ ወይም በዲብ በሌሊት ወይም በቀን እንዲደረግ ሲሹ፤ አንዳንዶች ደግሞ በቤተክርስቲያን አፀድ ሥር እንዲሆን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ እናም በእንደነዚህ ዓይነት መልኩ የአገር ሽማግሌዎች የተያዘ ሽምግልና ድርድር ሲሰምርም እርቁ በኮረብታ ወይም በጫካ ወይም

በቤተክርስቲያን አፀድ አጥር ውስጥ ወይም ሥር ይፈፀማል፡፡ እርቁም በገዳይ ላይ ልዩ ልዩ ገደቦች ይጥልበታል፡፡ ለምሳሌም በሟች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ፀሎት፣ ሥመ-በዓላት /ክብረ በዓላት/፣ በለቅሶ፣ በውኃ መቅጃ፣ በእርሻ ሥፍራ አካባቢ፣ በከብት ማሰማሪያ ሥረጌ አካባቢ፣ በሸንጎ ላይደርስ ታቅቦ እና አካባቢውን ለቆ እንዲሄድ ይወሰንበታል፡፡

እርቃቸው በቤተክርስቲያን እንዲሆን የሚመርጡት አንዳንዶቹ ተጋጪዎች ደግሞ የፈቀዱት አድባር ቤተክርስቲያን መስቀል ቀርቦላቸው፣ በፈቀዱት መኃላ አስፈፃሚ ቄስ ወይም መነኩሴ ፊት መስቀል ጨብጠው "ይህን እርቅ ብከዳ እንዲህ እንደ መስቀሉ ይበሳሳኝ" እያሉ መኃላ በመፈጸም ይታረቃሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ላለመካካድ በቄስ ወይም በመነኩሴ ይገዘታሉ ወይም የግዝት ቃል ይቀበላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ የቤተክርስቲያኑን በር መዝጊያ በመዝጋትና "ይህን እርቅ ብከዳ መላዕክቱ፣ ሰማዕቱ ይፍረድብኝ፣ ወላዲተ-አምላክ፣ እመ-ብርሃን ትፍረድብኝ" እያሉ ላለመከዳዳት የእርቅ ማፅኛ ቃለ-መኃላ ይፈፅማሉ፡፡

ቀደም ባለው ዘመን ደግሞ የእውቅ ሰዎች ደም እርቅ የሚፈፀመው ታቦት ጭምር እየወጣ ነበር፡፡ በተለይ ባላባቶቹን የሚያነካካ ደም መቃባት ከተከሰተ ታቦታቱ ዋነኛ የምልጃ መማፀኛና ማስታረቂያዎችም ነበሩም ይባላል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱን ዛሬስ ብያቸውም "ዛሬ ዛሬ ግን ብዙውን ጊዜ እንደዚህ አይደረግም፡፡ አልፎ አልፎ ነው እንዲህ ዓይት እርቅ አፈፃፀም የሚሰማው" ብለውኛል፡፡ ምክንያቱን ምንድነው ብዬም ጠይቄያቸዋለሁ፡፡ እነርሱም እንደነገሩኝ "የዛሬው ሰው ሽምግልናን ብዙውም አይፈቅደውም የሚሮጠው ወደ ፖሊስ እና ፍርድ ቤት ነው"፡፡ እኔም ጨዋታችንን በመቀጠል "ከሽማግሌ እና ከፖሊስ ከመደበኛው ፍርድ ቤት የትኛው ይቀርባል? ወጪና ጊዜስ ይቆጥባል?" ብያቸውም ነበር፡፡

ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ አንዱ የሆኑት አቶ ሰጥአርጌ (06/09/2002) በምሳሌ እንደጀመሩት "ውኃ ከጥሩ፣ ነገር ከሥሩ" የሚባል ነገር አለ፡፡ ሽማግሌ የያዘውን ነገር አበጥሮ ነው የሚፈታው እና የሚያስታርቀው፡፡ ድብብቅ ነገር አይኖርም፡፡ እነዚህ ዘመናዊዎቹ ግን ነገሩን ከሥሩ ማየት እንደማይፈልጉ ነው የሚሰማው፡፡ አዳፍኔ ምስክር /ውሸታም ምስክር ለማለት ነው/ የሰጠውን ቃል ይዘው ፍርድ ይሰጣሉ፡፡ በመማለጃም ይሸነገላሉ፡፡ ሽማግሌ የሚያየው ነገር እኮ እግዜር እንዳየው ነው የሚቆጠረው፡፡ ስለዚህ በአገር ሽማግሌዎች ዘንድ የውሸት ምሥክርነት አይሰጥም፡፡ ሽማግሌዎች በአብዛኛው

የደም ተቃቢዎቹን ቤተሰቦች ነው የሚያስተማምኑት፡፡ ወደ ሦስተኛ ወገን አይሄዱም፡፡ አልፎ አልፎ የምሥክርነት ቃል ቢቀበሉም መስካሪዎቹ አይዋሹም፡፡ ምክንያቱም ከዋሹ ከአገር ዕድር ይወጣሉ፣ ይሰደባሉ፡፡ ከነቤተሰባቸውም ይዋረዳሉ፡፡ ስለዚህ ሽምግልና ለማጭበርበር ምቹ አይደለም፡፡ ሽማግሌ ያየውም ነገር ይግባኝ የለውም፡፡ ምክንያቱም "በመረጠው ዳኛ የተረታና መሃል አገዳውን የተመታ አንድ ናቸው"፡፡ ስለዚህ ከሽማግሌም የሚተርፍ ነገር የለም፡፡ በልማዱም "ነገሩ ከሽማግሌ ላይተርፍ፣ ከአፍ ከፍ ከፍ ዋጋ የለውምና እረፍ" ነው የሚባለው፡፡ መደበኛው ፍርድ ቤት ግን እንደዚህ ዓይነት ጥንቃቄ የለውም፡፡ ማስረጃ ነው የሚመዝነው፡፡ ትኩረቱ እውነትን መፈለግ አይደለም፡፡ ማስረጃ ደግሞ የሐሰትም ቢሆን ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሐሰት ማስረጃ ሰጪውም ነገ ከማን ጋር እኖራለሁ ብሎ አይጨነቅም፡፡ አንድ ቀን መስክሮ ዘወር ይላል፡፡ ስለዚህም እውነትን በመፈለግ፣ መልካም ግንኙነትንም በመጠበቅ ረገድ ሽምግልና ይሻላል ብለውኛል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ ፖሊስ እና መደበኛ ፍርድ ቤት የሚሄዱትም ጉዳያቸውን በሽምግልና ዳኝነት የሚያይላቸው ሲያጡ፣ በደል ፈፃሚዎችንም ሥራ ማስፈታት እና ረጅም ጊዜ በቀጠሮ ማጉላላት ሲሹ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በደል ፈፃሚዎቹ ማህበራዊ ከበሬታ የሌላቸው ሆነው ሲገኙ መሆኑን ከቀወት ወረዳ ተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት ተረድቻለሁ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.)፡፡

ከባድ ግጭት በሚባለው በነፍስ መጠፋፋት ምክንያት ሽምግልና የተያዙ ሰዎች ከኃይማኖታዊው የቤተክርስቲያን እርቅ ውጪም ልማዳዊ እርቅ የሚፈፅሙበት ሁኔታ እንዳለ ተረድቻለሁ፡፡

በዚህም መሰረት የደም እርቅ ሽምግልና የተያዙት ታራቂዎች ስምምነት ላይ ሲደርሱ እርቁን ለማፅናት እርጥብ ሣር ወይም ቄጠማ እየነጩ "ይህን እርቅ ብከዳ እንዲህ ይንቀለኝ፣ ዘር ይንሳኝ" እያሉ እንዲሁም ደግሞ አንዳንዶቹ ሦስት የጎረሱ ጠመንጃዎችን እየተራመዱ "ይሄ ቢስተኝ፣ ይሄኛው አይሳተኝ" እያሉ ይማማላሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ አንድ የብልት በተለይም የሽንጥ ሥጋ በጋራ እየተቋረጡ "እርቁን ብከዳ እንዲህ እራቁቴን ያስቀረኝ" እያሉ እና የተቋረጡትንም ሥጋ እየጎረሱ፣ እየተየተጎራረሱም እንዲሁም ከዚሁ መኃላ ጋር ጠላ በአንድ ዋንጫ እየተጎነጩ እርቁን

ይደመድማሉ። እነዚህም የመኃላ ሥርዓቶች በአካባቢው እጅግ የተለመዱ እንደሆኑ ተረድቻለሁ።

የጦር መሣሪያዎችን በመራመድ፣ ሽንጥ ሥጋ በመቋረጥ፣ እርጥብ ነገር በመንጨት፣ በመቁረጥ፣ መስቀል በመጨበጥ ወዘተ የሚፈፀመውም መኃላ የሚወሰነው እንደተጋጪዎቹ ሰብዕና እየታዬ ነው። በጥሩ አራሽነት የሚታወቁት በሥጋ መቋረጥ፣ እርጥብ በመንጨት ወይም በመቁረጥ፤ በወንዳወንድነት የሚታወቁት የጦር መሣሪያ በመራመድ፣ ለነፍሳቸው ያደላሉ የሚባሉትን በመስቀል መኃላ በማስፈፀም። በመጨረሻም እህል ውኃ በማፋተት እና የእርጋት ፀሎት በማድረስ እርቁ እንዲደመደም ይደረጋል።

ከመረጃ ተባባሪዎቹ በተደጋጋሚ እንደሰማሁትም ቀወት ውስጥ የነፍስ ግድያ ሽምግልና ማካሄድ ከባድ ነው። ምክንያቱም የሽምግልና ሂደቱም ሆነ የመገላገያ ሐሳብ ማቅረቡ ደመኝነቱን እስከ መጨረሻ አያስቀረውም። ይህም ሆኖ ግን በአካባቢው ልማድ ሰው የገደለ ሰው ድምፁንና ኮቴውን አጥፍቶ ቅሌን ጨርቁን ማቁን ሳይል አገር ጥሎ ከተሰደደ ግጭቱን ያረግበዋል። ስለዚህም ሰው የገደለ ሰው አካባቢውን ጥሎ ካልሄደ በራሱ እና በወገኑ ላይ የሚያስከትለው መዘዝ የትየለሌ እንደሆነ ነው የሚነገረው። የአገሩ ልማድ "ገደለ ተነቀለ" ነውና። ቀደም ባለው ዘመን "ገደለ ተነቀለ" በሚለው ልማድ መሰረት አገር ጥሎ መጥፋትም አንድ የግጭት መፍቻ እንደነበር ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ጫውተውኛል። በቀድሞው ሆነ በአሁኑ ባህል መሰረትም አገር ጥሎ መጥፋትን የሚያስከትለው ነፍስ ማጥፋት፣ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ፣ ቤትና ንብረትን በእሳት ማጋየት የመሳሰለው ጥፋት ነው። አጥፊው ከእነዚህ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሁለቱን ከፈፀመ በኋላ ተጠቂዎቹ ወገኖች ለሕይወቱ እንደማይራሩለት ከጠረጠረ፣ አቅሙም እንዳላቸው ካመነ፣ የአገር ሽማግሌም ይሁን የሰፈር ሽማግሌ እንደማያሸንፋቸውም ከተገነዘበ ያለው አማራጭ አገር ጥሎ መጥፋት ነው።

አገር ጥሎ የመጥፋትን አመጣጥ ምክንያት እንዲነግሩኝ የመረጃ ተባባሪዎቼን ሁሉ ጠይቂያቸው ነበር። ይሁንና ለዚህ ጥያቄዬ አንድ ወጥ እና ቁርጥ ያለ ምላሽ አላገኘሁም። አንዳንዶቹ እንደሚሉት የገዳይ አገር ጥሎ መሰደድ ልማድ ከጥንትም የነበረ እና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። አገር ጥሎ የመሰደድ ልማዱም የመጣው ከቤተርስት ከመነቀል ጋር ተያይዞ ነው። የዚህም አድራጎት መነሻው እስከ ዐፄ ምኒልክ

ዘመነ መንግሥት ድረስ የነበረው "ሰው የገደለ ሰው ከቤተ ርስቱ ይነቀል" የሚለው ሥሪት እንደሆነ ይገምታሉ። ከሌሎቹ ደግሞ ነፍስ ገዳይ አገር ጥሎ እንዲሄድ የሚያደርገው ምሪትና ልማድ የመጣው የማያባራ መበቃቀልን ለመግታት ሳይሆን እንደማይቀር ያወሳሉ። ምክንያቱም "ዓይን ደም ይጠላል" እንዲሉ ገዳይ በገደለበት አገር የሚኖር ከሆነ የሟች ወገኖች ደመኛቸውን እያዩ በሰላም መኖር ስለማይቻላቸው እንደሆነ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ አገር ለቆ መሄድን ያስከተለው በተለይ ጠላትን ብቻ ሳይሆን አስቦ እና አቅዶ መላ ቤተሰቡን መግደል እና ንብረቱን ማውደም ወይም ከሁለቱ አንዱን መፈፀም እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህም የሚሆንበትን ምክንያት ሲያብራሩ እንደዚህ ዓይነቱ የተደራረበ ጥፋት ለሽምግልና እና ለሽምጋይም ስለሚያስቸግር አጥፊው እራሱ ከአካባቢው ለቆ የሚጠፋበት ሁኔታ መኖሩን፣ እንዲሁም ሁኔታው ለሽምግልናም ቢቀርብም እንኳን ሽምጋዮችም ጥፋተኛው ጥፋቱን በፈፀመበት አካባቢ ቢኖር በራሱም ቤተሰብ ላይ እርቅ የማያደበዝዘው በቀል ሊከተለው ስለሚችል፣ በሌላም በኩል ደግሞ ሌሎችም "እከሌ እከሌን እንዲህ አድርጎት ምን መጣበት?" እያሉ የልብ ልብ እንዳይሰማቸው፣ ተመሳሳይ ድርጊትም እንዳይፈፀም ከአካባቢው ማግለያ ዘዴ እንደሆነም ነግረውኛል (አቶ ሰጥአርጌ 06/9/2002 እና አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002) ።

የዚህን የጥፋተኛ ሰዎችን ከአካባቢ የማግለል ሥረ መሰረት ለማወቅ አሰሳ ለማድረግ ሞክሬያለሁ። በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ቅዱስ መፃሕፍት በማቴዎስ ወንጌል 10፡23 "ከዚች ከተማ ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላዋ ሽሹ" የሚል፣ በፍትሐ ነገሥትም (1958፡542) "መግደል የተከለከለ እንደ ኃጢአትም የተቆጠረ ነው። የገደለ ይገደል" የሚሉ መኖራቸውን አይቻለሁ። አሁንም እዚህ ላይ የቀወት ወረዳ ሕዝብ ጥፋተኛን ጥፋት ከፈፀመበት አካባቢ የማስወጣት ልማድን ከእነዚህ ቅዱስ መጻሕፍት ለምዶ ነው ወይስ አድራጎቱ አገር በቀል ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በአጭሩም ጥያቄው ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት እና ከልማዱ ማንኛቸው ይቀድማሉ? ነው። ሚዛን ደፍቶ መገመት የሚቻለው ምናልባት ጥፋተኛን ጥፋት ከሰራበት አካባቢ የማግለል ባህል ከኦርቶዶክስ ክርስትና በፊትም የነበረ ልማድ ሊሆን ስለመቻሉ ነው። ይህንንም ለማለት የሚያስችለው ብዙ ዓይነት ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና አስተምህሮት ጋር የማይሄዱ ነገሮች ከኃይማኖቱ አማኒያን አድራጎት ውስጥ ተዛንቀው መገኘታቸው ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ያጤኗል።

በቀወትም ሆነ በሌሎች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት በሚከተሉ ሥፍራዎች ለአድባር፣ ለወንዝ፣ ለባህር፣ ለገደል፣ ለከረብታ ዓመታዊ እርድ መፈፀም ወይም ደም ማፍሰስ፣ በግንቦት ልደታ ቤትን እና ግቢን በቂጣ ቆሎ ማሻተት፣ ቦረንትቻ መስጠት እንዲሁም በቤተክርስቲያን ክብረ-በዓላት ዕለትም እንዲሁ እርድ መፈፀም፣ የዛር መፍለቅ እና መነሳትን መደለልና መካደም፣ በመኃላ ማሳረጊያትነም ጠመንጃ፣ ጦር ጎራዴ መራመድ፣ ሽንጥ ሥጋ መቋረጥ፣ ቂጠማ ወይም ሣር መንጨት ወይም መባጠስ ወዘተ ሁሉ አለ፡፡ ስለዚህ ቀወቶች ጥፋተኞች የሚሏቸውን ሰዎች ከአካባቢያቸው እንዲለቁ የሚያደርጉት ከነባር ልማዳቸው በመነሳት እንጂ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከገባው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት በመነጨ አለመሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም (አቶ መኮንን በረደድ 19/01/2003፣ አቶ ከበደ መንገሻ 25/012003) ይህ አገር ጥሎ የመሄድ ልማድ የመጣው ከደም እርቅ አፈፃፀም ጋር በተያያ ሳይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው አስቦና አቅዶ የሰው ሕይወት ማጥፋቱ በአገር ሽማግሌ የታየበት "ሽማግሌ አየ እግዜር አየ" እንዲሉ የነፍስ ገዳይ እና የሟች ቤተሰቦች በሰላም የሚኖሩት ገዳይ አካባቢውን ለቆ፣ ወንዝ ተሻግሮ ለመሄድ ከተስማማ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ልማድ ስላለም በገዳይ ወይም በሟች ወይም በሁለቱም ልዩ ልዩ ተቀባይነት የሌላቸው ባህርያት ምክንያት ከደመኞቹ ጋር የሚያስታርቀው የአገር ሽማግሌ ያጣ ነፍስ ገዳይ በራሱ ውሳኔ አካባቢውን በመልቀቅ እና በመሰደድ የአገሩን ልማዳዊ ሕግ በራሱ ላይ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡ በዚህም አድራጎቱ የራሱን እና የሟችን ወገኖች ሥራዬ ብሎ መበቃቀል ያስወግዳል ይባላል፡፡

"በቀወት ወረዳ ነዋሪዎች መካከል የተደረገ የደም እርቅ ፅናት ምን ይመስላል?" በማለት የጠየቅኋቸው የተተኳሪ ቡድን አባለቱ እንደመለሱልኝ ማናቸውም የመኃላ ሥርዓት ከተፈፀመ በኂላ ብዙውን ጊዜ መኃላ አይፈርስም፣ እርቅም አይደፈርስም፣ ፀብም አያገረሽም፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ አባላት እንደሚሉት መኃላ ያፈረሰ ወገንም መቅኖ አያገኝም፡፡ ስለዚህ መኃላ ይፈራል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ ፀቡን የሚያስገረሽ ምክንያት ያጋጥማል፡፡ የሚያስገረሸው ነገር ከሌለ ግን ይቆያል ይላሉ፡፡ የተተኳሪ ቡድን አባላቱ እንደሚሉት ብዙውን ጊዜ የደም ቤትን ቂም አያጣውም፡፡ የታረቁት ካለፉም በኂላ ልጆቻቸው ሊያፈርሱት ይችላሉ፡፡

ለቀወት ወረዳ ተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላትም (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ከዚህ በላይ ያነሳኋቸውን ጥያቄዎች አንስቼባቸው ነበር፡፡ ያገኘሁትም መልስ ከላይ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ እና አረጋጋጭ ዓይነት ነበር፡፡

ገዳይ አገር ጥሎ በመጥፋቱ ብቻ የሟች ወገኖች መበቀላቸውን ያቆማሉ ወይ ያልኳቸው የተተኳሪ ቡድን አባላቱመም ሆኑ ሌሎች አካባቢው ነዋሪዎች እንዳሉት ገዳይ በአገር ቤት ታዬ እስካልተባለ ድረስ ደም ለመመለስ መሯሯጥ የለም፡፡ ገዳይ ከጠፋ ተቻኩሎ ደም መመለስ የለም፡፡ ይሁንና "የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም" እንዲሉ ነውና የገዳይ ወገኖች ከሟች ወገኖች ጋር "የደም ቤት" መሆናቸውን አውቀው ተጠንቅቀው መኖር አለባቸው፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቹ ከአባቶቻችን እንደሰማነው እያሉ እንደነገሩኝም ጥንት የደም ጉዳይ ካለ ትውልድ እየተቋጠሩ ሁሉ መፋጀት ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን ገዳይን አገር እያስለቀቁ ማስታረቅ እየተለመደ መጥቷል፡፡ እያደርም ሰው የገደለ ሰው ዞሮ ዞሮ አገር መልቀቁ እንደማይቀር እየተረዳው ስለሄደ፣ ደም መቃባቱም ሳይበራከት፣ ሽማግሌም ሳያስቸግር፣ አገር እየለቀቀ ወደ አርሲ፣ ባሌ፣ ሲዳሞ፣ ከፋ እና ኢሉባቡር መጥፋቱን ተያያዘው ይላሉ፡፡

አንዳንዶቹ የመረጃ ተባባሪዎቹ ደግሞ ዛሬ ዛሬ አዲስ አበባም የነፍስ ገዳይ መሸሸጊያ እና መደበቂያ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት አገሮች እንደ ወትሮው ለባይተዋሮች መጠጊያነት ምቹ አልሆኑም፡፡ መተነኳኮሱ በዝቷል፡፡ ስለዚህም እዚችው እቅርቡ አዲስ አበባ ነፍስ-ገዳዮች "እሰው ጫካ ውስጥ መሸሸግ ጀምረዋል" ብለዋል (አቶ ሰጥአርጌ 06/9/2002 እና አቶ ደመቀ ሲሻህ 13/09/2002)፡፡ ስለዚህም አሁን አሁን የግድያ ግጭት አካባቢን በመልቀቅ የሚፈታበት ሁኔታ እንደሚበዛ ሁሉም የመረጃ ተባባሪዎቹ አውግተውኛል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004 ዓ.ም.) ፡፡

በአጠቃላይም የቀወት ወረዳ አማሮች ግጭታቸውን በእርቅ ከቋጩ እንደየጎጡ የተለያዩ ቃለ መኃላዎች ይፈፀማሉ፡፡ በዚህም መሰረት ሣር እየነጩ፣ ጠመንጃ ወይም ጎራዴ እየተራመዱ፣ አፈር እየጨበጡ፣ ክር እየበጠሱ፣ በኃይማኖት የቤተክርስቲያን በር

እየዘጉ፣ መስቀል እየጨበጡ፣ ወንጌል፣ ድርሳናት፣ መልክዓ አማልዕክት እየጨበጡ ግዝት እየተቀበሉ እርቃቸውን ይደመድማሉ፣ ያፀናሉም፡፡ “ነገር ሁሉ በመኃላ ይፀናል” እንዲሉ፡፡

## 8.3. የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭቶች መንሥዔዎች

በዚህ ርዕስ ሥር የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች እርስበርሳቸው ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸውን ምክንያቶችን ለመመርመር እና ለመዘርዘር ይሞከራል፡፡ በዚህም መሰረት ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንዲሁም ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች ያገኘሁትን እና ያብላላሁትን የአካባቢውን የግጭት መንሥዔ ዘገባ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ወንዶች ልጆቻቸው “ወንድነትን” እንዲላበሱ የሚያደርጉት ገና በህፃንነት ዕድሜያቸው እንደሆነ ነው የሚነገረው፡፡ አባ ወራዎች ህፃናቱ ገና እንደተወለዱ የጀግንነት መንፈስ እና ኃይል ይሰጣል ብለው የሚያምኑበትን ዕፅ በእውቅ ጀግና እጅ እንዲጠጡ ወይም እንዲጋቱ ያደርጋሉ፡፡ እውቅ ጀግና የሚባለውም ከጎሳው ውጪ የሆኑ ከአሥር እስከ አሥራ ሁለት ሰዎችን የገደለ “ገዳይ” ወይም “ጀግና” የተሰኘ ሰው ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ጀግና ተፈልጎ ከታጣም ከአሥር በታችም ቢሆን የገደለ ተፈልጎ ህፃናቱን “ጀግንነት ያሰርፃል ተብሎ የሚታመንበትን ዕፅ” ቀጥቅጦ ከውኃ እና ከወተት ጋር ደባልቆ ያጠጣቸዋል ወይም ይግታቸዋል፡፡ ይህም ህፃናቱ በጀግናው እጅ ቀማሚነት ከወተት ጋር እንዲጠጡት የሚደረገው ዕፅ በህፃናቱ ውስጥ ጀግንነትን ያሰርፃል፣ ከአዕምሮኣቸውም ውስጥ ፍርሃትን ያርቃል፣ ድፍረትን ይጨምራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ጀግንነትንም በታዳጊዎቹ ውስጥ እንደ መትከል ይቆጠራል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡-ግራዝማች ኢስገሌ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ አቶ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ፡፡

ህፃናቱ ከፍ ካሉም በኋላ ወተት እንዲጠጡ፣ ገንፎ እንዲበሉ የሚባበሉት መሻማትን በሚያለማምድ መልኩ ነው፡፡ ወተቱን ጠጣሁብህ /ጠጣሁብሽ፣ ገንፎውን በላሁብህ /በላሁብሽ እየተባሉ ነው፡፡ በዚህ መልኩ እየተመገቡ ቆይተው መንቀሳቀስ ሲጀምሩም የሚያወላክፉቸው እና የሚያነቅፉቸው ነገር ሁሉ ሲያስለቅሳቸው እናቶች ያነቀፉቸውን ነገር የመደብደብ ድራማ እየፈፀሙ ያረጋጓቸዋል፣ ድብደባንም ያስተምሯቸዋል፡፡ በተለይም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያደጉት ታዳጊዎችም በመኖሪያ

አካባቢቸው ካሉ መሰሎቻቸው እና የጎሳ ወገኖቻቸው ጋር የእንስሳት ጥበቃ እንዲያካሂዱ በሚደረግበት ወቅት እራሳቸውን ከጥቃት የመከላከል ልምድ እንዲኖራቸው ይደረጋሉ። ጊሌ ይታጠቃሉ፣ ጠመንጃ ይይዛሉ፣ አጠቃቀሙንም ይለማመዳሉ። በዚህ ሁኔታ እራሳቸውን ከጥቃት መከላከል ይችላሉ ተብሎ በሚታመንበት ዕድሜም ላይ የዕድሜ አቻዎች እራሳቸውን፣ እንስሳቶቻቸውን እና አካባቢያቸውን ከተቀናቃኝ የመጠበቅ ኃላፊነት መወጣት ይችሉ ዘንድ በእውቅ ጀግኖች አማካኝነት ባህላዊ ወታደራዊ ሥልጠና ይሰጣቸዋል (ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ 08/01/2002፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ 10/09/2002፣ አቶ ሁሴን አህመድ 17/09/2002)።

በሰውነት የጎለመሱት እና ራስን የመከላከል ችሎታ ያዳበሩት ወጣቶች በተለይ ድርቅ በበረታ ወቅት ለእንስሶቻቸው ግጦሽ እና ውኃ ፍለጋ ሲሉ ከአንዱ ጉሳ ወደ ሌላው ጎሳ ቀበሌ ለመግባት ይገደዳሉ። በእንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ወቅትም ውኃ እና ግጦሽ ባለበት መሬት ላይ ይሻማሉ፣ ውስጣዊ ፀብ ያፈራሉ። በዚህ ዓይነቱ ክስተትም አንዱ ጎሳ ወደ ድንበርተኛ ጎሳው ክልል የሚገባበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ሰሙ ሮቢዎች "ነገር ወይም ግጭት በእግር ይመጣል" እንደሚሉትም በእንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ሳቢያም የተለያዩ ጎሳዎች ግጭት ውስጥ ይገባሉ። በዚህም መሰረት የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ውስጣዊ ግጭት ከሚቀሰቀስባቸው ምክንያቶች አንዱ ውኃ እና የእንስሳት ግጦሽ ነው ማለት ይቻላል።

የመረጃ ተባባሪዎቼ (ባላምባራስ 05/09/2002፣ አይዳሂስ አሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 14/09/2002) እንዳወሱልኝ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች እርስበርሳቸው ከሚጋጩባቸው ምክንያቶች ሁለተኛው ደግሞ የሣር ቁርርን መድፈር ነው። ምክንያቱም በአካባቢው የግጦሽ ሣር አጠቃቀም ልማድ የበጋውን ቁርር በክረምት፣ የክረምቱን ቁርር በበጋ ማስጋጥ የተከለከለ ነው። ስለዚህም ክልከላውን እና ልማዱን መጣስ የግጭት መንሥዔ ይሆናል።

ሌላኛው የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች የውስጣዊ ግጭት መንሥዔ ደግሞ ውኃ ገብ የሰብል እና የአትክልት ማልሚያ መሬት ቅርምት ነው። በውኃ ገብ መሬት አካባቢ የሚኖሩ አፋሮች ደለላማ ሥፍራዎችን ማረስ እና አትክልትም ማልማት ስለሚሹ እና በመሬቱም ላይ ሽሚያ ስለሚፈጥሩ ግጭት ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለ ነው የሚነገረው (ሼህ አደን ጋለሎ 12/09/2002፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም 16/09/2002 እና አቶ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ።

በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ዘንድ እንደ አንድ የውስጣዊ ግጭት መንሥዔነት የሚነሳው ሌላው ምክንያት ደግሞ የውርስ ሀብት ክፍፍል ነው፡፡

በሴት ምክንያት የሚቀሰቀስ ውስጣዊ ግጭትም አለ፡፡ የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ሀብታም ወንዶች ከአንድ በላይ ሚስት ስለሚያገቡ እና የሚያገቧቸውም ሴቶች በተለያዩ ሥፍራ ስለሚኖሩ ወንዶቹ በሴቶቹ መኖሪያ ቤት የሚገኙት በዙር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሴቶቹን ለማማገጥ የሚሞክሩ ሰዎችም ከጠርጣሪ ባሎች ጋር ግጭት ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሁን እና የሰው ሚስት በማማገጥ ላይ የተገኘው ወንድ በአካባቢው ልማድ መሰረት አድራጎቱን ለመካድ እና ባልዮውን ለማጥቃት እስካልሞከረ ድረስ ግጭቱ የከፋ እንደማይሆን ነገር ግን የሰው ሚስት በማማገጥ ላይ ሳለ የተያዘው ሰው ለማምለጥ ወይም ባልዮውን ለማጥቃት ከሞከረ የከረረ እንደሚሆንም ነው የሚወሳው (ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ 08/01/2002፣ ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ 05/09/2002) ፡፡ ይህም "ግጭት በብልት ይመጣል" /bodu kaasak namate/ እንደሚሉት አንዱ የግጭት ሰበበ ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪም ደግሞ ቤተሰባዊ ጋብቻን ባለማክበር ወይም በቤተሰባዊ ጋብቻ ባለመወሰን፣ የጎሳ መሪዎችን ሐሳብ እና ትዕዛዝ ባለማክበር፣ በጎሳ ሕግ ባለመገራት እና ባለመገዛት ምክንያት ግጭት ይከሰታል፡፡

ሌላው የውስጣዊ ግጭት መነሻ የአካባቢውም ነዋሪዎች "ችግር ወይም ግጭት ሁሉ በምላስ ይመነጫል" /tabi kee bodu kulmaki, qaraba, firr/ እንደሚሉት በአፍ እላፊ ማለትም በሐሜት፣ ሽሙጥ፣ አሉባልታ፣ ስድብ ወይም ዘለፋ፣ በንግግር አለመግባባት ወዘተ በመሳሰሉት የሚከሰት ነው፡፡

ሰሙሮቢ ገአሎ ውስጥ በጎሳዎች መካከል ግጭት የሚቀሰቀሰው ደግሞ በወረዳው ውስጥ የሚኖሩት ጎሳዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው አንደኛው የሌላኛውን የመኖሪያ አካባቢ እና የእንስሳት ማሰማሪያ ሥፍራ በመጋፋት፣ በእንስሳት መሰራረቅ እና መዘራረፍ ወዘተ ምክንያት ግጭት የሚያፈሩበት ሁኔታ እንዳለ ነው የሚነገረው፡፡ ይህንንም "ነገር ወይም ግጭት በእጅ ይመጣል" /tabi kee bodu gabaat tamate/ እያሉ ይገልፁታል (ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ 08/01/2002፣ ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ 05/09/2002) ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ አቶ አህመድ

ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) በተተኳረ ቡድን ውይይት ወቅት እንዳጫወቱኝ ምንም እንኳን ግጭቶች ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊቀሰቀሱ የሚችሉ ቢሆኑም በአከሳሰታቸው ግን የተለያዩ ደረጃ ወይም የመክረር እና የመላላት ሁኔታ አላቸው፡፡

በዚህም መሰረት ከላይ በተጠቀሱት ሰበቦች በአንድ ጎሳ አባላት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ብዙውን ጊዜ የማይካረሩበት እና ለመሸምገልም የማያስቸግሩበት ሁኔታ አለ፡፡ በግጭቱ ውስጥ ቀላል እና ከባድ ድብደባ እንዲሁም የሕይወት መጥፋት ከተከሰተ ግን ግጭቶቹ ይከራሉ፡፡

በሌላ በኩል ግን ግጭቶች ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በተለያዩ ጎሳዎች መካከል ከተከሰቱ በድብድቡ መቅለል ወይም መክበድ እንዲሁም በጠፋው ነፍስ እና ንብረት ዓይነትና ብዛት ላይ ሳይተኮር በእንዴት እንደፈራለን እና እንነካለን በሚል ግጭቶቹ ብዙውን ጊዜ ወደ ከባድነት ማለትም ደም አፋሳሽነት እና ሕይወት መጥፋት የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደተረዳሁትም በተለይ በጎሳዎች መካከል የሚከሰት ግጭት በልዩነት ላይ ስለሚያተኩር እና ያለፉ መጥፎ የግንኙነት ሁኔታዎችን ስለሚጠቅስ ይከራል፡፡ በተለይ ቀደም ሲል ተከስቶ የነበረ ግጭት ታሪክ እና ደመኝነት ካለ ግጭቱ የበረታ፣ ሰብኣዊና ቁሳዊ ኪሣራው የከፋ፣ ግልግሉም የሚያለፋ እንደሆነ ነው የሚተረከው (የተተኳረ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሣ ሣንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሀመድ 19/01/2004)፡፡ ስለዚህም በአንድ ጎሳ አባላት መካከል እና በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ደረጃቸው ለየቅል ነው፡፡ የእርስበርሱ ግጭት ባመዛኙ ቀላል አልፎ አልፎ ከባድ ሲሆን በጎሳዎች መካከል ያለው ግጭት ግን ብዙውን ጊዜ  ቀላል አይሆንም፡፡

በአካባቢው በዕለትም ይሁን በቆየ ቂም በቀል ግጭት ሲቀሰቀስም መደባደብ እና መገዳደል የተለመደ ነው፡፡ የገደለም ሰው ብዙውን ጊዜ ወደ አባቱ ጎሳ ሄዶ ይደበቃል፡፡ በምሳሌያቸውም "ስትገድል  ወደ አባትህ፣ ሲርብህ ወደ እናትህ ጎሳ ግባ" /ixa, waa, ababura qafkasta waa ina meela ula/ ይላሉና፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቼ (ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ 08/01/2002፣ ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ 05/09/2002) እንደተረኩልኝም በአፋር ባህል ሰው የገደለ ሰው በገደለ

ሰሞን ግልገል ፍየል /በከል/ አርዶ፣ ከቤቱ ሳይወጣ እንደ አራስ ለሁለት ሣምንታት ያህል እየተቀለበ ይቆያል፡፡ ያረደውንም ፍየል ጭራ በግንባሩ ላይ ያስራል፡፡ በእጁም ላይ አምባር ያጠልቃል፡፡ በጠመንጃውም ላይ ልዩ ልዩ የገዳይ ምልክት የብር፣ የመዳብ ጥምዝ ያደርጋል፡፡

ገዳይ ከቅልብነት ከወጣም በኋላ ስለ ግዳዩ ለቤተዘመዱ እና ለቅርብ እና ለሩቅ የጎሳው አባላት እየዞረ ይነግራል፣ የሰማ ወገኑም ላልሰማው እንዲያሰማ ያደርጋል፡፡ የግዳይ መረጃውን ናኝቶ ካበቃም በኋላ ድግስ ደግሶ ቤተዘመዱን ጠርቶ ያበላል፡፡ ግዳዩንም በድግሱም ላይ በመፎከር እና በማስፎከር ያውጃል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ድግስ ላይ የታደሙ ወገኖችም ገዳይነቱን ያፀድቃሉ፣ ከዚያን ቀን በኋላም ለገዳይ የሚገባውን የ "ወንድነት" ክብር እና ማዕረግ በወግ ልማዱ መሰረት ይሰጣሉ፡፡

በሌላ በኩል ግን በግዳይ ማብሰሪያ ድግስ ላይ የተካፈሉ እና ግዳይ የሌላቸው አፋሮች ይቆጫጫሉ፣ ይከነከናሉ፡፡ ስለዚህም እነርሱም በተራቸው ገድለው እንደ ልማዱም ደግሰው ለማብላት እና ገዳይ ለመሰኘት የሚገድሉበትን ጊዜ በናፍቆት ይጠብቃሉ፡፡

## 8.4. የሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳ ነዋሪዎች የርስበርስ ግጭቶች አፈታት

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች እንደ ድንበርተኞቻቸው ቀወቶች ሁሉ በውስጣቸው የሚከሰቱ ግጭቶቻቸውን ቀላል እና ከባድ እያሉ ይፈርጃሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከከባድ የአካል ጉዳት እና ግድያ በመለስ ያሉ ግጭቶች በሙሉ ቀላል፣ ከባድ የአካል ጉዳት እና የነፍስ መጥፋፋትን ያስከተሉ ግጭቶች ደግሞ ከባድ ይሰኛሉ፡፡ ሰሙሮቢ ገለአሎዎችም እነዚህን ከቤተሰብ እስከ ጎሳ የሚዘልቁ ልዩ ልዩ የእርስበርስ ግጭቶቻቸውንም የሚፈቱባቸው የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ባህላዊ የሽምግልና ዳኝነት ተቋማት አሏቸው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሀመድ 19/01/2004) ፡፡

እነዚህም ውስጣዊ የእርስበርስ ግጭቶቻቸው የሚፈቱባቸው ባህላዊ የሽምግልና ዳኝነት ተቋማት አደረጃጀት ኬዶክ /keexo/፣ ዳላ /xaala/፣ ቡራ /bura/፣ ጋንታ /gata/ የሚባሉትን የመኖሪያ መንደሮቻቸውን አቆራቆር እና ማህበራዊ ግንኙነት አመሰራረት

ሁኔታ የተከተሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በየመንደሮቹ ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች በቀዶ፣ በዳላ፣ በቡራ እና በጋንታ መሪዎች ተቀዳሚነት የሽምግልና ዳኝነት አማካኝነት ይፈታሉ፡፡

በዚህም መሰረት ለምሳሌ በኬዶ ደረጃ የሚታዩት ግጭቶች የልጆች ሥርዓት ማጣት እና የቤተሰብ ስምምነት ማጣት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ስለዚህም ልጆች እና ወጣቶች እንዲሁም ጎልማሶች ጥፋት ሲፈፅሙ የማስተካከሉ ኃላፊነት የወላጆች እና የቤተሰብ ብቻ ስላልሆነ ልጆችንም፣ ወጣቶችንም፣ ጎልማሶችንም በማረም እና በማቃናት ሂደቱ የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ይሳተፋሉ፡፡ ምክንያቱም በባህላቸው ልጆች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች የእናት እና አባታቸው፣ የቤተሰባቸው ብቻ አይደሉም፡፡ የመንደሩ ማለትም የቅርብ ቤተዘመዶቻቸው ሁሉ ናቸው፡፡ ስለዚህም አንድ አፋር ሲያጠፋም ሆነ ሲያለማ የቅርብ ተወላጆቹ እና የጎሳው አባላት ሁሉ ዓይንና ጆሮ ይከተለዋል፡፡ ሲያለማ በቅርብ ቤተሰቡ ይመሰገናል፤ ሲያጠፋ ደግሞ ምክር ይለገሳል፡፡ በምክሩም ካልተስተካከለ አካላዊ ቅጣት ይደርስበታል፡፡ ቅጣቱም ውኃ ውስጥ መድፈቅ፣ በእርጥብ አለባቆ መጠብጠብ፣ በአርጩሜ መገረፍ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በጥፋተኝነት የተፈረጀው ግለሰብ በቅጣቱ ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግምም ቤተሰቡ እና መንደርተኛው ሁሉ ደግሞ እንደገና ተንከባክቦ ያስታምመዋል፡፡ ይህ ሁሉ ተፈፅሞበትም ሆነ ተፈፅሞለት ከስህተቱ የማይማር ከሆነም ካለው የእንስሳት ሀብት ላይ ሁለት ከብት በቅጣትነት ተወስዶ በቤተዘመዱ ታርዶ ይበላበታል፡፡ በዚህ ሁሉ ቅጣት የማይታረም ከሆነም ከሚኖርበት አካባቢ ተነስቶ ወደ እናቱ ጎሳ ወገኖች እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ እዚያም ማህበሩ የጠላበትን ይተው ዘንድ በጥብቅ ይመከራል፡፡ ተመክሮ ካልተመለሰ እና ጥፋተኝነቱ እየባሰ ከሄደም ወደ ዓቢይ ጎሳው /ሜላ/ ተላልፎ ከማህበሩ እንዲነቀል የሚያደርግ ውሳኔ ሊተላለፍበት ይችላል፡፡

በቅርብ ንዑስ ጎሳዎች መካከል በስድብ፣ በእንስሳት ሥርቆት፣ በባልና ሚስት አለመግባባት፣ በገንዘብ መካካድ ወዘተ ምክንያት የሚፈፀሙ ግጭቶችን ደግሞ በመንደሩ የበላይ ጎሳ መሪ "ዳላ አባ" /xaala aba/ ተቀዳሚነት አማካኝነት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ በአጥፊውም ላይ እንደ ጥፋቱ ደረጃ እንስሳቱ ሊታረዱበትና ሊበሉበት ይችላሉ፡፡

በዓቢይ እና በንዑስ ጎሳዎች መካከል በጎሳ ልዩነት፣ በእንስሳት ሥርቆት፣ በነፍስ ማጥፋት ወዘተ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶችን ደግሞ "ቀዶ አባው" ተቀዳሚ ሆኖ ይፈታል፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በተለያዩ ምክክንያቶች ግጭት ውስጥ ከገቡና ግጭቱ የኃይል እርምጃ መወሳሰድን ካስከተለ ወይም ከተሸጋገረ ግን ሽብሩን እና የኃይል አድራጎቱን ለጊዜው የሚያስቆሙት፣ ግጭት የማስቆም ማህበራዊ ኃላፊነት የሚጣልባቸው የጎበዝ አለቆች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት እነዚህ የጎበዝ አለቆች ግጭት በተከሰተበት ሥፍራ ፈጥነው ደርሰው ፀቡን የማብረድ፣ ከቻሉም ፀበኞቹን ይዘው ለጎሳ አለቆቻቸው የማቅረብ፣ ካልቻሉም የደረሰውን የግጭት ሁኔታ ለጎሳው መሪ ዘርዝረው የማስረዳት ኃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህ ማህበራዊ ኃላፊነት የተጣለባቸው የጎበዝ አለቆች ግጭት በተከሰተበት አካባቢ ደርሰው ሰላምና ፀጥታ በማስከበር ላይ ሳሉ ተጋጪዎቹን በአካል ካገኟቸው እና ከያዟቸውም ለአካባቢው የጎሳ መሪ ያቀርባሉ፡፡ የጎሳ መሪውም ቀላል ግጭቶችን እንደየደረጃቸው ከዕለቱ ጀምሮ በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ያደርጋል፡፡

ቁልፍ የሰሙሮቢ ገለአሎ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደገለፁልኝ ቀለል ያለ ጥፋት ለምሳሌም አንድ ሰው የሌላ ሰው ሚስት በማማገጥ ላይ ሳለ ባልዬው ከደረሰበት እና ከተያዘ ወይም ከተገኘ የሰውዬው እና የሴትዮዋ ጨርቅ ተቋጥሮ ወይም ተቆራኝተው ወደ አካባቢው ጎሳ መሪ ወይም ሽማግሌ የሚሄዱበት ሁኔታ አለ፡፡ ሚስቱ ከሌላ ሰው ጋር ስትማግጥ አይቶ እና ቀርቦ ጨርቃቸውን ማቆራኘት ያልደፈረ ሰው ደግሞ በጩኸት ሰው እንዲደርስለት እና እንዲያይለት በማድረግ በሽማግሌዎቹ ፊት በጥፋተኛው ላይ እንዲመሰከርበት ያደርጋል፡፡ ከሴት ጋር ተቆራኝቶም ለጎሳ አለቃ ዳኝት የቀረበ ሰው ስለ ጥፋቱ እና እርምትም እንዲሆነው የቀንድ ከብቶችን ወይም ግመሎችን በካሣነት ይከፍል ዘንድ ይወሰንበታል፡፡ ነገር ግን የሰው ሚስት አማግጦ ሲደረስበትም በልማዱ መሰረት ወደ ጎሳ መሪው የሽመግልና ዳኝነት ለመቅረብ ያንገራገረ ወይም በባል ላይ ጉዳት ለማድረስ የሞከረ ደግሞ እንደ ጥፋቱ ክብደት ተጨማሪ ቅጣት ይጣልበታል፡፡

በሌላም በኩል ግጭት ከተከሰተ በኋላ በተጋጪዎቹ መካከል አካል የማይሰነክል፣ ሥራ የማያስተጓጉል ዓይነት ጥፋት ተፈፅሞ ከሆነ በነገር አነሳሽነት እና አጥፊነት የሚፈረጀው ወገን ትምህርታዊ ቅጣት እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ በአጥፊውም ላይ የሚወሰዱት ትምህርታዊ ቅጣቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ጥፋቱ እጅግ ቀለል ያለ ከሆነ እና አጥፊውም ወደፊት ሊሻሻል እንደሚችል የሚገመት ከሆነ አካላዊ ቅጣት እንዲፈፀምበት ይደረጋል፡፡ አካላዊ ቅጣቱም እሥራት፣ በእርጥብ አለባቆ እንጨት መደብደብ፣ በልምጭ

መጠብጠብ፣ ወይም በጉማሬ አለንጋ መገረፍ፣ በወንዝ ውኃ ውስጥ መንከር ሊሆን ይችላል (ባላምባራስ አይዳሂሶ 90509/2002) እና ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002)፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ዘንድ ቀላል ጥፋት የፈፀሙ ሰዎች የሚጣልባቸው ሌላው ዓይነት መለስተኛ ቅጣት ደግሞ አጥፊው አንድ ወይም ሁለት እንስሳትን አርዶ ለሽምጋዮቹ እና ተሸማጋዮቹ እንዲያበላ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ መለስተኛ ጥፋት ፈፃሚው ተደጋጋሚ ጥፋቶችን ከፈፀመ በአባቱም በእናቱም ጎሳዎች ወገኖች እና መሪዎች እንዲመከር ይደረጋል፡፡ ተመክሮም ከጥፋቱ ለመታረም ፈቃደኛ ካልሆነ ደግሞ ጥፋቱ ከባድ ማለትም በተደጋጋሚ አፋሮችን እንደ መግደል ዓይነት ተደርጎ ስለሚቆጠር ከጎሳውም ሊገለል ይችላል፡፡

ውስጣዊ ግጭቱ ድብደባ፣ ቁስለት፣ የአካል ጉድለት አስከትሎ ከሆነ ጉዳተኛው አገግሞ ለመሸማገል እስከሚበቃ ድረስ አጥቂዎቹ የማገገሚያ ወይም የማስታመሚያ ፍየሎች እንዲያቀርቡለት ይደረጋል፡፡ ተጎጂው እስከሚያገግምም ድረስ የማስታመሚያ ፍየሎቹን የሚያቀርቡት ደብዳቢው ወይም የቅርብ ዘመዶቹና የጎሳ ወገኖቹ ናቸው፡፡ የማስታመሚያ ፍየሎቹንም ቁጥር እና ዓይነት የሚወስኑት የሽምግልና ዳኞቹ ናቸው፡፡

ተጎጂው ካገገመ እና ከዳነ በኋላም ሽምግልናው ታይቶ ተመጣጣኝ ካሣ ይቆረጥለታል፡፡ የካሣውም መጠን የሚወሰነው በተደብዳቢው ላይ በደረሰው አካል ወይም የገፅታ መበላሸት ሁኔታ ላይ በበመስረት ነው፡፡ ለምሳሌም ግንባሩ፣ ፊቱ የተበላሸ ከሆነ፣ በእጁ ወይም በእግሩ ወይም በሌላ ሰውነት አካሉ ላይ በደረሰው ድብደባ ምክንያት እንደ ቀድሞው ለመንቀሳቀስ እና ለመሥራት የሚቸገር ከሆነ ወይም ደግሞ ጉዳቱ በትክለ ሰውነት ገፅታው እና በሕይወቱ ላይ ለውጥ ያላመጣ ከሆነ የጉዳቱ መጠን ታሳቢ እየተደረገ ካሣ ክፍያ ይቆረጥለታል ወይም ይተመንለታል፡፡ ስለዚህም የካሣው መጠን እነዚህን ሁሉ ከግምት ያስገባ ነው የሚሆነው፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ ለአካል ጉዳት ለተዳረገ ሰው የሚከፈለው የካሣ ክፍያ መጠን የሞት የካሣ ክፍያን አያህልም፡፡ ለአካል ጉዳት የሚከፈለውም የካሣ መጠን እንደ ጉዳቱ ደረጃ ከሰላሳ አምስት እስከ ሃምሳ ግመል ወይም ቀንድ ከብት ሊደርስ ይችላል፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ዘንድ የመጨረሻው ከባድ ግጭት የነፍስ ማጥፋት ነው፡፡ ስለዚህም በውስጣዊ ግጭት ወቅት ግድያ ተፈፅሞ ከሆነ እና ገዳይ ተይዞ ከሆነ ግን የጎሳ መሪው ሽምግልናው በተለይ የነፍስ መጥፋትን ጉዳይ ለሚታይበት "መድዓ/ /maaxaa/ እና የሽምግልና ዳኝነቱን ለሚያዩት "መካባን" /maakabana/ እንዲቀርብ

ያደርጋል። በነገራችን ላይ ይህ "ማድዓ" የሚሰኘው ባህላዊ ዳኝነት ተቋም የነፍስ ማጥፋትን ጉዳይ የመመልከት ሥልጣን ያለውም በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ብቻ ሳይሆን በአፋሮች ዘንድ ሁሉ መሆኑን በተለያዩ የክልሉ ዞኖች እና ወረዳዎች በተለያዩ የትምህርት መስኮች በተለያዩ አጥኚዎች የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ (ካህሣይ በአነ ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘ፣ አሰፋ ፍስሃ፤ 2004 ውስጥ፣ Getachew (2001:54-57)፤ Kelemework (2000)፤ Akmel (2010:46-69) እንዲሁም Getachew and Shimels በ Alula, and Getachew (2008) ውስጥ።

የሽምግልና ዳኝነቱን የሚያዩት የጎሳ መሪዎች ወይም ዳኞችም ግድያ የፈፀመውን ሰው በእጅ-ጠብቅ እንዲቆይ አድርገው፣ ምርመራውን ለመጀመር አርባ የምርመራ ቀናት ቀጠሮ ይሰጣሉ። ምክንያቱም በአካባቢው ብዙውን ጊዜ የግዳይ ሽምግል ወይም ዳኝነት የሚጀመረው ሟች አርባ ቀናት ካለፉት በኋላ ነው። በአካባቢው ልማድ መሰረት ሰው ከሞተ ለአንድ ሳምንት ያህል ፀጥ፣ ዝም ይባላል። ከሳምንት በኋላ አንድ ወይ ሁለት ሰዎች ለግልግል መንቀሳቀስ ይጀምራሉ። ሽምግልናውንም ለመጀመር ከገዳይና ከሟች ወገን አሥር አሥር የሚሆኑ ሰዎች ለሽምግልና ይመለመላሉ።

በሌላ በኩል ግን አንድ አፋር ሌላ ሰው ባልሰማው እና ባላየው ሁኔታ በአካባቢው ተገድሎ ከተገኘ የሟች ገዳይ ተለይቶ እስከሚታወቅ ድረስ አስከሬኑ በጊዜያዊ የማቆያ ቀብር ውስጥ እንዲቆይ ተደርጎ፣ ገዳዩ እንዲለይ ይደረጋል። ሟች የተሟላ ቀብር የሚደረግለት የአካባቢ ባህላዊ የሽምግልና ዳኞች "መካባን" /maakabana/ በቂ መረጃ ካገኙ እና ገዳዩም ከታወቀ በኋላ ነው። እንዲህ ዓይነቱም ግድያ የሚፈፀመው ገዳይ በቂ ጥንቃቄ አድርጎ ሲገድል ነው። ይሁን እንጂ የአካባቢው ነዋሪዎች "ሰዎች ሁሉ አንድ ነገር ይፈራሉ፤ እርሱም እውነት ነው። ያለ እውነትም መኖር አይቻልም" /shaax kulmaki, inkitu. Meesta wun mcan kiini num. male mataka/ እንደሚሉት የገዳይ ማንነት እስከ መጨረሻው ተደብቆ አይቆይም። ይኸውም የሚሆነው በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ነው የሚነገረው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንደ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሀመድ 19/01/2004) ።

የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱ እንደሚሉት አንደኛው ምክንያት በ "ዳጉ" /xaagu/ ማለትም የዜና ወይም የመረጃ ማነፍንፍ እና ልውውጥ ሥልታቸው ገዳዩን ማወቅ መቻላቸው ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ገዳይ ምንም እንኳን ግድያውን በድብቅ ቢፈፅምም ስለ አገዳደሉ ሁኔታ ለወገኖቹ ማሳየት እና ማሳወቅ ስላለበት፣ በገደለበት ሥፍራ ድንጋይ የሚቆልል ወይም የሚከምር በመሆኑ፣ የግዳይ ምልክት ተመልካቾቹን ሰዎች ማንነት እና ጎሳ በይፋም በሥውርም በማጥናት፣ "ይህ የማነው ቁልል" ከሚለውም የስሚ ስሚ ወሬ በመነሳት ነው።

በሦስተኛ ደረጃ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በድብቅ ከገደሉ እና መግደላቸውንም ካስመሰከሩ በኋላ የመጨፈር እና የመፎከር፣ የጎሳ መሪዎቻቸውንም የማሳወቅ ልማድ ስላላቸው የገዳይነቱ ጉዳይ ይፋ ሊሆን ስለሚችል ነው። በዚህም "ማን ፎከረ?"፣ "ማንንስ ገደለ?" የሚል ጥያቄ ስለሚያስከትል የገዳይን ማንነት ይፋ ያስደርገዋል። ስለዚህም ገዳይም ቢሆን መግደሉን ለመደበቅ የሚሞክረው ለትንሽ ጊዜ እንጂ እስከመጨረሻ አይደለም። ምክንያቱም የገዳይነት ዝናውን እና ክብሩን አጥብቆ ይሻዋል። የግድያ ግቡም ጀግና "ወንድ" ለመሰኘት እና የሚያስገኘውንም ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጥቅም ለማግኘት ነውና።

በአካባቢው ልማድ መሰረት በይፋም ሆነ በኀቡዕ በተፈፀመ የነፍስ ግድያ ምክንያት የሚያዝ የሽምግልና ዳኝነትም የሚጀመረው ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሟች አርባ ቀናት ካለፉት በኋላ በመሆኑ የሟች ቤተሰቦች በአርባዎቹ ቀናት ውስጥ በገዳይ እና በቤተሰቦቹ ላይ በቀል እንዳይፈፅሙ ለሽምግልና ዳኞቹ የመኃላ ቃል እንዲሰጡ ይደረጋሉ። ነፍስ ያጠፋውም ሰው ተይዞ ከሆነ እስከ ሽምግልናው ቀን ቀጠሮ በጎሳው ባላባት እጅ ተይዞ ይቆያል። ካልተያዘም በቀን ቀጠሮው ዕለት በጎሳ መሪው አማካኝነት ይቀርባል።

ቁልፍ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የመረጃ ተባባሪዎቼ (ግራዝማች ኢስገሌ ኢነሃባ 08/01/2002፣ ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ 05/09/2002) እንደነገሩኝ በተለይ የነፍስ መጥፋትን ያስከተለን ግጭት ለመፍታት የሚሞከረውም በመጀመሪያ የሟችንና የገዳይን ቤተሰቦች ለየብቻ በማወያየት ነው። ጊዜ ቀጠሮውም ሲደርስ ሽማግሌዎቹ እንዲሰየሙ ይደረጋል። ሽማግሌዎቹም ሽምግልናውን ለመጀመር ገዳይ በእርቁ ለመግፋት መቁረጡን ለማረጋገጥ አሥራ ሁለት ከብቶች በሽማግሌዎች እጅ እንዲያሲዝ ያድርጋሉ። ከዚያም ተበዳዮች ለእርቅ እንዲያድሩ፡-

ለአላህ ብላችሁ ታረቁ፣
ለነቢይ ብላችሁ ታረቁ፣

ወዘተ እያሉ  ይማልዳሉ፡፡

በተለይም በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የሕይወት መጥፋት ያስከተለን ግጭት ለመሽምገል የሽምግልና ዳኝነቱ ሲጀመር ከገዳይ ወገኖች በኩል አንድ ግመል እንዲቀርብ እና እንዲታረድ ያደርጋሉ፡፡ ይኸውም እሚደረገው ሽምግልናው የሰመረ እንዲሆን ጠቃሚ የሥምረት ምልክትና ምልኪ ተደርጎ ስለሚቆጠር እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህንን ዓይነቱን የነፍስ መጠፋፋት እና ከነፍስ መጥፋት በመለስ በጎሳዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችንም ለመሽምገል እና ለመዳኘት የሚመረጡት ከተጋጪዎቹ ጎሳዎች ውጪ የሆኑ የሩቅ ሰዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የደምም ሆነ ከደም በመለስ ያለው ግጭት  በአንድ ጎሳ አባላት መካከል ከሆነ በሽምግልና ዳኝነቱ ላይ የሚቀመጡት ግጭቱ ውስጥ የገቡት ጎሳ አባላት ሲሆኑ የሚታረደውም እንስሳ ግመል ሳይሆን ከግመል ያነሰ ሊሆን ወይም ጭራሹኑ ደግሞ ላይታረድም ይችላል፡፡

በተለይ በነፍስ መጥፋት ምክንያት የሚያዘው የሽምግልና ዳኝነት ከቀጠለ በኋላም የሽምግልና ዳኞቹ "አላግባብ" ሰው ሞቷል የሚል እምነት ካሳደሩ  ለሟች ወገኖች የሚከፈል የእንስሳት ካሣ ይቆርጣሉ፡፡ የእንስሳት ካሣው መጠን፣ አከፋፈል እና ጊዜያቱንም እንደ ዘመኑ እና እንደየ አገዳደል ሁኔታው እያዩ ይደለድላሉ፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ልማድ መሰረትም ለነፍስ መጥፋት የሚቆረጠው እና ለሟች ቤተሰቦች የሚከፈለው የደም ካሣ ወይም ወጀ መጠንም ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ አንድ ሺህ[25] ግመል ወይም የቀንድ ከብት ይደርሳል፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንዳወሱልኝ የካሣ ክፍያ እንስሳቱ መጠን የሚወሰነው እንደ አገዳደሉ ድንገተኛነት እና የታቀደነቱ እየታዩ ነው፡፡ ለምሳሌም በተራ ግድያ አንድ መቶ አምስት ከብት ካሣ ይከፈላል፡፡ በሴራና በግፍ አስቦና አቅዶ የተፈፀመ ግድያ ሲሆን እስከ አንድ ሺ ግመል ወይም የቀንድ ከብት ይደርሳል፡፡

---

[25] ይህ በካሣነት የሚቆረጠው የግመሎች ቁጥር ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ ሺህ መሆን ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ በተደጋጋሚ የተነሳ ነገር ነው፡፡ ይሄ በተጨባጭ ይደረጋል ወይ ሲባሉም በተደጋጋሚ የሚሰጡት ምላሽ የካሣ አከፋፈሉ በተለያዩ የጊዜ እንደሚፈፀም፣ የተወሰነውም ካሣ በምልጃ እና በምህረት ሊቀር እንደሚችልም ነው፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ አንድ ሺህ ግመል የተከፈለበትን አጋጣሚ በገዜ እና በቦታ አስረግጠው አይጠቅሱም፡፡ ከጥንት ከአባቶች ጀምሮ ለተባባሰ እና በጎሳዎች መካከል ለሚያጋጥም የነፍስ ግድያ የሚቆረጥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የካሣ አቆራረጥ ወይም አወሳሰን ልማድ እንደሆነ ነው የሚያወሱት፡፡ ስለዚህም አንድ ሺህ ግመል የሚባለው ተግባራዊ ካሣ ሳይሆን ተምሳሌታዊ ካሣ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

"ገዳይ በአንድ ጊዜ ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ ሺ ግመል ለሟች ወገኖች መክፈል ይቻለዋል ወይ?" ያልኳቸው የመረጃ ምንጮቼም የአከፋፈል ሁኔታውን እንደሚከተለው ነግረውኛል፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቼ እንዳወሱልኝም በመጀመሪያ ደረጃ እስከ አንድ ሺህ ግመል ወይም የቀንድ ከብት ድረስ ካሣ የሚቆረጠው የግጭት አነሳሱ እና አገዳደል እጅግ የታሰበበት፣ አሰቃቂነት ያለበት፣ ወደፊትም ሊያስከትል የሚችለው መዛዔ ሁኔታ እና የተጋጪዎቹም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ግምት ውስጥ ገብቶና ተመዝኖ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃም በካሣነት የተቆረጡት ከአንድ መቶ አምስት እስከ ሺህ የሚደርሱ ግመሎች ወይም የቀንድ ከብቶች በሙሉ ይከፈሉ ቢባልም እንኳን ክፍያው የሚፈፀመው በተለያዩ ጊዜ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የደም ካሣው ሲቆረጥ ወዲያው የሚከፈል የከብት መጠን አለ፡፡ በሂደትም የሚከፈል አለ፡፡ ይህም ሁሉ ሲደረግ ደግሞ የደም ካሣውን የሚከፍለው ገዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ግድያው በአንድ የጎሳ አባላት መካከል የተፈፀመ ከሆነ ካሣውን አዋጥተው የሚከፍሉት የገዳይ የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው፡፡

ግድያው የተፈፀመው በሁለት ጎሳዎች አባላት መካከል ከሆነ ደግሞ ካሣውን አዋጥተው የሚከፍሉት የገዳይ ጎሳ ወገኖች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የጎሳው አባላት ሁሉ አዋጥተው የደም ካሣውን የመክፈል እና የጎሳ አባላቸውን የመርዳት ባህላዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ የአንድ ጎሳ አባል የሌላ ጎሳ አባልን ገደለ ማለትም የጎሳው አባላት ሁሉ ካሣ ከፋይ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ባመዛኙ አርብቶ አደሮች እንደመሆናቸውም ትልቅ ንብረቶቻቸውም እንስሳት ናቸው፡፡ በተለይ በውስጥ ግጭት ወቅት እንስሶቻቸውን በደም ካሣነት መክፈላቸውም ያንገበግባቸዋል፡፡ ከውስጣዊ ግጭትም የሚያቅባቸው ይህን ዓይነት ብዙ ቁጥር ያለው የእንስሳት ካሣ መክፈላቸው ነው (ባላምባራስ አይዳሂስ 05/09/2002 ዓ.ም.) ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የደም ካሣ ግመሎቹ ወይም እንስሳቱ የሚከፈሉት የድርቅ እና የልምላሜ ወቅት እየታየ ነው፡፡ በመሆኑም በድርቅ ወቅት ካሣ አይከፈልም፡፡ የካሣ ክፍያው የሚፈፀመው በልምላሜ ማለትም ዝናብ ከጣለ በኋላ በብላጊ ወቅት ነው፡፡ ምርቃቱም "ምድር ለም ይሁን፡፡ እንስሳት ሣር ያግኙ፡፡ ሰው ወተት ያግኝ" /barr mca take lh qassu geni shaaxa cani geenitn/ ነውና፡፡

በአራተኛ ደረጃ ደግሞ ለተጎጂ ቤተሰቦች መልካም ምግባር በማሳየት እና በመማለድም ቀሪው የደም ካሣ በምህረት እንዲቀር ስለሚደረግ በመጀመሪያ የተቆረጠው ካሣ ቀስ በቀስ ወደ ግማሽ እና ከዚያም በታች ሊወርድ ይችላል፡፡ ከዚህም የካሣ ክፍያ አቆራረጥ እና አከፋፈል ሂደት ለመረዳት የሚቻለው ተምሳሌታዊነት ያለው ጭምር መሆኑን ነው፡፡

ብዙውን ጊዜም የነፍስ ግድያ የሽምግልና ዳኝነት እና እርቅ የሚታረገው ልማዳዊ እና ኃይማኖታዊ መኃላ በመፈፀም ነው፡፡ ልማዳዊ መኃላዎቹ ጠመንጃ መራመድ፣ በከብት ደም መታጠብ፣ በጉበቱ መለቅለቅ፣ የከብት እበት መጨበጥ፣ እርጥብ ሣር መንጨት እና ከብት ያሳጣን፣ ዘር ያሳጣን እያሉ ልጅና ከብት ጨብጦ መማል ሲሆኑ ኃይማኖታዊው ደግሞ ቅዱስ ቁርኣንን በመያዝ የሚፈፀም ነው (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሐመድ 19/01/2004) ፡፡

ሰሙሮቢ ገለአሎዎች ውስጣዊ ግጭቶቻቸውን ከዚህ በላይ በቀረበው አኳኋን ሲፈቱም የሽምግልና ዳኞቹ የራሳቸውን ፍርድ ከሰጡ በኋላ በሽምግልና ዳኝነት እና እርቅ ሥርዓቱ ላይ የተገኙ፣ አስተያየት እና ትችት መስጠት የፈለጉ ሁሉ እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡ ይሁንና የተቺዎቹ ሀሳብ ውሳኔውን አያስለውጥም፡፡ ምክንያቱም የሚፀናው ውሳኔ በሽምግልና ዳንነቱ ላይ በተቀዳሚነት የተሰየመው የጎሳ መሪ እና ተመርጠው የተቀመጡት ሽማግሌዎች ፍርድ ነው፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ውስጣዊ ግጭት አፈታት የሽምግልና ዳኞቹ ፍርድ ከተሰጠ ወይም ከተሰማ በኋላ በተለይም በውሳኔው ላይ ለውጥ የማያመጣ አስተያየትና ትችት ለምን እንዲሰጥ ይደረጋል? ፋይዳውስ ምንድነው? የሚል ጥያቄ የሰነዘርኩላቸው ሼህ መሐመድ ሰይድ እንደነገሩኝ እና ሌሎቹም እንዳረጋገጡልኝ በአፋር ባህል ሐሳብን በግልፅ መናገር የተለመደነቱን፣ ሐሜት ነውርነቱን የሚጠቁም ነበር፡፡ በተለይ ሼህ መሐመድ ሰይድ እንደሚሉት አፋር መናገር የሚፈልገውን ሳይናገር አይተውም፡፡ ስለዚህም በአደባባይ መነገር የነበረበትን ነገር በኋላ ዘወር ብሎ በድብቅ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ሐሜት መፈፀም የለም፡፡ ሁሉም በተሰጠው ውሳኔ ላይ የታየውን ይናገራል፡፡ ውሳኔው እንኳን እርግጠኛ የሆነ ቅር የሚያሰኝ ነገር ቢኖረው ሌላ ጊዜ ለሚፈፀም እርቅ ማጣቀሻና ማረሚያ ይሆናል፡፡ የሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በአንድ ወቅት

የተሰጠን የሽምግልና ውሳኔ አሰጣጥ ሌላ ጊዜ ለሚሰጥ ፍርድ ወይም ውሳኔ እንደማጣቀሻ አድርገውም የመውሰድ ልማድ አላቸው የሚል ነበር። በልማዱ በአንድ ወቅት የተሰጠ የሽምግልና ውሳኔ በተጋጪዎቹ የጎሳ ወገኖች ዘንድ ሁሉ ይዳረሳል። የተዳረሰውም ውሳኔ እየተተረከ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል። እናም አመርቂውም ሆነ ሕፀፅ ያለበት ውሣኔ በአፋሮች ዘንድ አይዘነጋም። ያለፈ ውሣኔ ለወቅታዊ ውሣኔ አሰጣጥ እንደማጣቀሻ ያገለግላል የሚባለውም ከዚህ የተነሳ ነው።

ሼህ መሐመድ ሰይድን ውሳኔው እንዴት ይወሰናል? ይፃፋል ወይ? ብያቸውም ነበር። እርሳቸውም እንደመለሱልኝ አፋር እንኳን በራሱ ዕድሜ የተፈፀመን ነገር ይቅርና ዝርያው የተገኘበትን፣ የሄደበትን መንገድ፣ ያጋጠመውን፣ የራሱን ትውልድና የጎሳ ግንድ እንዲሁም በየጊዜው የተደረገ ክስተትን፣ ሁኔታን ሁሉ የማስታወስ ልማድ አለው ብለውኛል።

በአጠቃላይ በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ዘንድ ውስጣዊ ግጭት ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን ሲደመደምም ለሽማግሌዎች እና ለተገላጋዮች ምሣ  በግ ይታረዳል።

በሌላ በኩል አንድ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋር ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ባህላዊ ሽምግልና ወይም ዳኝነት መሰረት የማይገዛ እና የማያድር ከሆነ እንዲሁም በተደጋጋሚ አፋሮችን በመግደል የታወቀ ከሆነ ከጎሳው፣ ከአካባቢው እንዲገለል ይደረጋል። አካባቢውን ፈፅሞ እስከሚለቅም ድረስ ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ሁሉ ይገለላል። ለመገለል ምልክት የሚሆኑትንም ነገሮች ለሽማግሌዎቹ ወይም ዳኞቹ አቅርቦ ይፋዊ የስንብት ሥርዓቱ ይፈፀምበታል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሣ ሣንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሀመድ 19/01/2004) ።

ስለዚህም የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ግጭት አፈታት ሥርዓት በአወቃቀሩ ረገድ ሲታይ በየእርከኑ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን በክልል፣ በማዕከላዊ ደረጃ የሚደራጁ ዘመናዊ ፍርድ ቤቶችን ይመስላል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ቀላል ግጭቶች  በቀዶ /keexo/ ፣ ዳላ /xaala/፣ ቡራ / bura/፣ ጋንታ /gata/፣ ሜላ / meela/ እንዲሁም ከባድ ግጭቶች ማድዓ በተሰኘው ማህበራዊ ተቋም ይፈታሉ። በእነዚህ ማህበራዊ አደረጃጀቶች እና አሰፋፈሮች ውስጥ የየጎሳዎቹ መሪዎች በተዋረድ የሚገኙ በመሆናቸው በየደረጃው የሚከሰቱ ግጭቶችን በየደረጃው ከሚገኙ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ይፈታሉ። ከአቅማቸው በላይ የሆነውንም ወደ ላይኛው የጎሳ መሪ ያስተላልፋሉ

በአጠቃላይም የሰሙ·ሮቢ. ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች ግጭቶቻቸውን በየደረጃው በተዋቀሩ የጎሳ መሪዎች ተቀዳሚነት የሽምግልና ዳኝነት እያዩ በእርቅ ይቋጫሉ፡፡ እርቁንም ያፀናሉ፡፡ "አፋሮች እርስበርሳቸው ሲጣሉ እበት፤ ከሌሎች ሲጣሉ ድንጋይ ይወራወራሉ" /qafar itna tame wadi laa tsigede qak marana tame, wedixexa qabessa/ እንደሚሉትም ግጭቶቻቸውን በሽምግልና ከፊቱ በኋላ በቀላሉ አይካካዱም፣ አይበቃቀሉምም፡፡

## 8.5. የቀወት እና የሰሙ·ሮቢ. ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግጭቶች መንሥኤዎች

በዚህ ክፍል የሚነሳው እና የሚወሳው ዓቢይ ጉዳይ የተጠኚዎቹ የቀወት እና የሰሙ·ሮቢ. ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበብ ወይም ምክንያት ነው፡፡

በቅድሚያ በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች አኗኗር፣ የሥራ ሥምሪት እና አንደኛቸው ለሌላኛቸው ባላቸው አተያይ ዙሪያ በምልከታ የታዘብኩትን አቀርባለሁ፡፡

ድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙ ሮቢ. ገለአሎ ወረዳ አፋሮች መኖሪያ መንደሮች በአንዳንድ አካባቢዎች ለምሳሌም እንደ ዓባይ አጥር[26] ባሉት አካባቢዎች በአማካይ ግምት የሚራራቁት እስከ ሁለት ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ስለዚህም በሥምሪታቸው ጎን ለጎን ይውላሉ፡፡ እንስሶቻቸውንም በቅርብ ርቀት ያሰማራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም የሚቀላቀሉበት ሁኔታ አለ፡፡ የእርሻ ሥራቸውንም ቅርብ ለቅርብ ያከናውናሉ፡፡ በቅርብ ርቀት ዓይን ለዓይን ይተያያሉ፡፡ እጅግ የተለማመዱትና የተዋወቁት አልፎ አልፎ ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ አጠቃላይ ሁኔታቸው ሁሉ በመካከላቸው የሰከነ ሰላም እንደሌለ ይጠቁማል፡፡ ይህንን ለማለት ያስቻለኝን ሁኔታም እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች ግጭትን አቆብቁበው እና በቋፍ ሆነው እየተጠባበቁ እንደሚኖሩ አንዱ ምልክት ዓባይ አጥር ቀበሌ በተለይም ነጌሶ ጎጥ ውስጥ የሚመሩት ሕይወት ነው፡፡

---

[26] ይህ ሥያሜ አካባቢው ቀደም ባላው ዘመን የከብት ማሰማሪያ እና ማሳደሪያ እንደነበር፣ ሥያሜዎች ከተግባር ወይ አገልግሎት ወይም ሙያ ጋርም እንደሚያያዙም ሁሉ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስላል፡፡

ዓባይ አጥር ጎጥ የሚኖሩት አማሮች እና አፋሮች ዘወትር የሚታዩት ጠመንጃ አንግበው፣ ጩቤ ሽጉጠው፣ አካባቢያቸውን እንደ ጦር ሜዳ ቀጠና ደጋግመው እየቃኙ እና በዓይነ ቁራኛ እየተያዩ ነው፡፡ በዓባይ ነጌሶ አካባቢ ሁለቱም ሕዝቦች በቅርብ ርቀት እየተያዩ የሚኖሩ በመሆናቸው አማሮቹም ሆኑ አፋሮቹ የጦር መሣሪያዎቻቸውን ከትከሻቸው፣ ደረታቸው እና ወገባቸው ላይ አያወርዱም፡፡ ትጥቃቸውን እንዳነገቡ ነው የሚስተዋሉት፡፡ ሥራ በማይሰሩበትም ሰዓት ለምሳሌም ተቀምጠውም ከሆነ ጠመንጃዎቻቸው የሚገኙት ጭኖቻቸው ላይ ነው፡፡ ይህንን የተመለከትሁት የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች አኗኗን ስለከነከነኝ ወደ አንዱ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ መኖሪያ አካባቢ በማምራት ላይ ሳለሁ አንዱን የአካባቢውን ነዋሪ በእግረ መንገዴ አነጋግሬው ነበር፡፡ ሰውዬውን ያገኘሁት ግንቦት 07/2002 ዓ.ም. ወደ ግራዝማች ኢሰገሌ ቤት እየተጓዝሁ ሳለሁ ነበር፡፡ በመንገዴ ላይ ያገኘሁት ሰው ጠመንጃ ተሸክሞ፣ ጩቤ ከቀበቶው ሥር ሰክቶ እያረሰ ነበር፡፡ ለመግባቢያ እንዲሆነን ብለን እኔና መንገድ መሪዬ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት "የእግዜር" ሰላምታ ሰጠነው፡፡ አጭር ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ከሰላምታው በኋላ ማንነታችንን እና ወደ አካባቢው የዘለቅንበትን ምክንያት ገለጥንለት፡፡ በመቀጠልም "አገሩ አማን አይደለም ወይ? ለምን ይህን ሁሉ የጦር መሣሪያ ተሸክመህ ታርሳለህ? እንዴትስ ይመችሃል?" አልኩት፡፡ ሰውዬው "የዋህ እንግዶች ናችሁ፡፡ ለመሆኑ አሁን እናንተ እዚህ በረሃ ውስጥ የመጣችሁት ምን ተማምናችሁ ነው? እንደማያችሁ የነፍስ መጠበቂያ እንኳን የላችሁም፡፡ ምናልባት ፈንጂ በኪሳችሁ ይዛችሁ ካልሆነ" አለን፡፡ መንገድ መሪዬ ፈጠን ብሎ ትውልድ ሀረጉን መዞ እራሱን አስተዋወቀ፡፡ ከዚያም በኋላ ገበሬው ፈታ ብሎ ያጫውተን ጀመር፡፡ እንዲህም አለን፡፡

"የዚህ አካባቢ አፋሮች አንድ ወፍራም ሰው ሲገድሉ እንደ ሁለት ነው የሚቆጥሩት፡፡ ስለዚህ ቆይታችሁን አሳጥሩ፡፡ አማሮቹም አንድ ደልዳላ አፋር ስንገድል እንዲሁ ደስ ይለናል፡፡" ካለን በኋላ ለማናቸውም ጠንቀቅ ብለን፣ ጀርባችንን ሳንጥል ጉዳያችንን አድርሰን እንድንመለስ መካከረን፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ ገበሬው ዓይኑን እያቅበዘበዘ አካባቢውን ይማትራል፡፡ ጆሮውንም አንቅቶ ኮሽታውን ሁሉ ያዳምጣል፡፡ ከበላዩና ከበታቹ እንደርሱው ጠመንጃ እንዳነገቡ የሚያርሱትም ገበሬዎች "አማን ነወይ?" እያሉ ይጠያይቁታል፡፡ እኔ ጥያቄዬ በቀጥታ ስላልተመለሰልኝ እንደምን አድርጌ ላስታውስው እያልኩ በማውጣት ማውረድ ላይ ሳለሁ አንድ ሌላ የታጠቀ ወጣት መጥቶ

በሮቹን ተቀበለው። እኔም ትንሽ እንዲያወጋኝ ብዬ "ወንድሜ ቅድም ለምን መሣሪያ ታጥቀህ ታርሳለህ ብዬህ ነበር። ሳትመልስልኝ ወደ ሌላ ጨዋታ ገባን" አልኩት። እርሱም "እረግ! አይ ነገሩ የገባህ መስሎኝ ነው። ፍሬ ካገኘህበት እነግርሃለሁ" ብሎኝ እንዲህ ቀጠለ (ግንቦት 07/2002 ዓ.ም.)፡፡

> ይሄ እኮ ነጌሶ በረሃ ነው። ደም የለመደ ሥፍራ ነው። ደም ሲጠጣ የኖረ ሥፍራ። አፋሮች ዘወትር ደም ይጠማቸዋል። ስለዚህ መቼ እንደሚተኩሱብንና እንደሚጥሉን አናውቅም። እኛም አንዘናጋም። ምክንያቱም ይህ አካባቢ አማራ እና አፋር ዘወትር ተጠባብቀው የሚገዳደሉበት፣ የሚበቃቀሉበት ነው። ስለዚህ እዚህ መኖር የሚቻለው እንዲህ ታጥቆ ነው። መዘናጋት የለም። ዕግዜር የሰጠውን ዕድሜ ጨርሶ አልጋ ላይ የሚሞተው ወንድ ልጅ በልክ ነው። አይመረው አይተኩሰው ብጤ ከሆነ ብቻ ነው። ሌላው የሚሞተው በረሃ በጥይት ነው። አባቶቻችንማ 'የወንድ ልጅ አሟሟት ስጠኝ!'፣ 'ፈጣሪዬ ሆይ! አሟሟቴን እንደ ሴት በአልጋ ላይ እንዳታደርገው!' እያሉ ነበር የሚፀልዩት። በደፈጣ እንዳይሞቱ፣ ከአፋር ጋር ተዋግተው እንዲሞቱ ነበር የሚመኙት። እና ይህንን አኗኗራችንን እኮ ማንም መንግሥትም ጭምር ያውቀዋል። ነገር ግን ሁሉም እንደ ልማድ ያየዋል።

ከዚያም የአካባቢው አማሮች በሥፍራው የሚኖሩት ነፍሳቸውን በእግራቸው ጥፍር ይዘው እንደሆነ ማለትም ትንሽ እንቅፋት ቢመታቸው ነፍሳቸው አብራ እንደምትጠፋ ዓይነት መሆኑን ዘረዘረልኝ። ይህ በመንገዱ ላይ ያገኘሁት አርሶ አደር እንደሚለው ጎረቤቶቹ የሰሙርቢ ገለአሎ አፋሮች ሰው የመግደል ልማድ እንደ ሱስ አለባቸው። እርሱ እና የአካባቢውም ሰዎች እንደ በቅሎ ጌጥ ክላሽንኮብ ጠመንጃ እና ጨቤ ተሸክመው ከበሬ ጋር የሚንገላቱት ወደው አይደለም። የኑሮ፣ የነፍስያ ጉዳይ ስለሆነባቸው ነው። አርሶ አደሩ የብሶት ጨዋታውን በመቀጠልም "ወንድሜ እኛ እዚህ የምንኖረው ዕድሜያችንን ሙሉ እንዲሁ ተጠባብቀን፣ ሳት ያለም ቀን ተሟሙተን፣ ሙታችንንም ቀብረን፤ ደግሞም ሲመችን ተበቅለን፣ ደማችንን ተወጥተን ነው የምንኖረው" እያለ የአኗኗራቸውን አኳኋን ዘረዘረልኝ። አርሶ አደሩ እኔን እና ጓደኛዬን እየሸኘንም ስለነበር አንድ ሌላ ጥያቄ ጣል አደረኩለት።

"ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር ለምን እርስበርሳችሁ ትገዳደላላችሁ? አንድ ጊዜስ ግጭት ተከስቶ የሰው ሕይወት ከጠፋ በኋላ እንዳይደገም ሽምግልና እና እርቅ አይደረግም ወይ?" አልኩት። አርሶ አደሩም "የአማራና የአፋር እርቅ እንደ በቆሎ ንፍሮ ነው። ዛሬ ታበስለዋለህ። ነገ ጥሬ ነው። ሽምግልናውና እርቁ ለጊዜው ነው። ፋታ

ለማግኘት። በየጊዜው መጋደል፣ ፀቡ ባስ ያለ ሲሆን ደግሞ በየጊዜው መታረቅ። ዘወትር ይኸው ነው" አለኝ።

ከዚህ በኋላ ገበሬው ጉዟችንን ወዳመራንበት ወደ አንዱ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ መኖሪያ ጎጥ እየተጠጋን መሆኑን ጠቆም አድርጎን ከፊት ለፊታችን ግራር ሥር ተቀምጠው የሚታዩንን አፋሮች እያመለከተን:-

> አያችኋቸው እነዚህን ግመሎች፣ ፍየሎች፣ በጎች እና ላሞች የሚጠብቁት አፋሮች እዚያ ቅጠሉ ሥር ተኝተዋል፣ ይሄን ጊዜ ጠመንጃዎቻቸውን በእኛ ላይ እያለሙ ይጫወቱ ይሆናል። ምክንያቱም እንግዶችነታችሁን ወዲያው ነው የሚያውቁት። በዚያ ላይ ደግሞ ገና ከታች አንድ አፋር አይቷችሁ ከሆነ ይሄን ጊዜ መምጣታችሁን እዚህ ያሉት አውቀው ይሆናል። አፋሮች በጣም ተጠራጣሪዎች እና አደገኞች ናቸው። ባይተዋር ሰው ካዩ ወዲያው ነው መረጃ የሚለዋወጡት። አደጋውም የከፋ ነው። ስለዚህ ገና በጣም ከመቃረባችሁ በፊት ወደ እከሌ ቤት የሚወስደው መንገድ የቱ ነው? በሏቸው። አለዚያ ሰውነቱ ሞላ ያለ በተለይም ባይተዋር ሰው ሲያዩ ተኩሰው ለመጣል ስለሚጓጉ ከየቅጠሉ ሥር ለማለም ይሽቀዳደማሉ። ስለዚህ ገና ከወዲሁ ከርቀት የግራዝማች ሰዎች መሆናችሁን እያወጃችሁ መሄዱ ጥሩ ነው። እኔ ከዚህ እመለሳለሁ። ለእኔ ከዚህ በታች መውረድ ደም መጠማት፣ የሬሳ ጨርቅንም ይዞ እንደመዞር ነው።

ብሎን ወደመጣበት ተመለሰ (ግንቦት 07/2002 ዓ.ም.። እኔ እና መንገድ መሪዬም መንገዱ ጠፍቶን ሳይሆን በአርሶ አደሩ እንደታቀደልን፣ በየግራሩ ሥር ጠመንጃዎቻቸውን በየፊት ለፊታቸው አስተኝተው፣ ጩቤ (እነርሱ ጌሌ የሚሉትን) ወገባቸው ላይ አገንድረው፣ በደረታቸው ተኝተው፣ ገበጣ እየተጫወቱ እንስሳት የሚጠብቁትን እና እያጠያጠያኑ የሚመለከቱንን ወጣት የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ገና ከሩቁ "ይኸ መንገድ ወደ ግራዝማች ኢሰገሌ አቤት ያደርሰናል ወይ?" እያልን በቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ ስመ ጥር ስም እያለዘብናቸው አለፍን። ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ ዘንድም ደረስን።

ከረጅም የትውውቅ እና የዓላማ ገለፃ እንዲሁም ማቅማማት እና መስተንግዶ በኋላ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ በሕይወት ዘመናቸው ስለ አፋር እና አማራ ግጭት እና እርቅ የሚያስታውሱትን ይነግሩኝ ዘንድ ጠይቄያቸው ያወጉኝን በራሴ አገላለፅ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

ግራዝማች ኢሰገሌ እንደነገሩኝ በቀወት እና ሰሙሮቢ ወረዳ ድንበር ላይ ዛሬ የሚኖሩት አማሮች እና አፋሮች የሚጋጩባቸው ምክንያች ብዙ ናቸው። ለምሳሌም የውኃ እጥረት ወይም በረሃማነት፣ ውኃ እና ውኃ-ገብ መሬት ሽሚያ፣ የአካባቢ መሬት

ባለቤትነት፣ ድንበር፣ ደም ምለሳ ወይም ብቀላ፣ ታሪክ-ጠቀስ ቂም፣ የገዳይነት ወግ፣ ለማድነት ወዘተ ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህንም በየተራ እንያቸው፡፡

የሁለቱ ድንበርተኛ ወረዳ ነዋሪዎች አንዱ የግጭት ምክንያት የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮች የሚኖሩበት አካባቢ በረሃማ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በተለይ የሮቢ ወንዝን ተከትለው ወንዙም የሚፈስበትን እና የሚያለመልመውን ዙሪያ ገባውን ለእንስሶቻቸው መኖነት ተማምነው የሚኖሩት አፋሮች የወንዙ ፍሰት ሲቀንስ እና በተለይ ድርቅ ሲበረታ ወደ ቀወት ወረዳ ዘልቀው ቀወት ምድር ውስጥ በተለይም በኩታ ገጠሞቻቸው ሰፌ በረት፣ ደብርና ጀጎል፣ ዓባይ አጥር እና ኩሬ በረት ቀበሌዎች ዘልቀው ይገባሉ፡፡

በተለይ ድርቅ በበረታበት ወቅትም የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች የእንስሳት ማሰማሪያ፣ የግጦሽ ሣር፣ የውኃ እጥረት ስለሚያጋጥማቸው የጎሳ መሪዎቹ ሸንጎ ተቀምጠው ክፉውን ቀን እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው የሚመካከሩበት እና ለጎሳው አባላት ጉባዔም ቀርቦ ስምምነት የሚደረስበት ሥርዓት አለ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ አማራው አካባቢ ገብቶ፣ የሚመጣውንም ችግር ተቋቁሞ አስቸጋሪውን ወቅት ማለፍ ይሻላል የሚል ከሆነ የዕድሜ እኩያሞች የሚባለው እና ከሁለት እስከ ስምንት ሰዎች እየሆነ በየመንደሩ የሚደራጀው እና በጎሳው አባላት የሚታዘዘው ወጣት የጦር ጓድ ዓይነት ኃይል እንስሳቱን ይዞ ለመቆያነት ወደተመረጠው አካባቢ ጉዞ ያደርጋል፡፡ በተደራጀ ሁኔታም ሆኖ እንስሳቱን በሣርም፣ በሰብልም ላይ ይለቃል፡፡ አማራው ደግሞ በመሬቱ ላይ ሰብልም፣ አትክልትም፣ ሣርም አልምቶበት ስለሚቆይ በይዞታው ላይ ስምሪት ሲደረግበት በጋራ ተነሳስቶ ይመክታል፡፡ በዚህም ዓይነት ሁኔታ የጅምላ ግጭት ይፈጠራል፡፡ አቅም ያገኘው ወገንም ነፍስ ያጠፋል፣ ይሰልባል፣ ቤት፣ መስጊድ እና ቤተክርስቲያን ያቃጥላል፣ እንስሳት ይዘርፋል፣ ከመኖሪያም አካባቢም ያፈናቅላል፣ ያሰድዳል፡፡

ግራዝማች ኢሰገሌ እንደሚተርኩት በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ የአካባቢው አማራ የሚኖረው በእርሻ ስለሆነ እና የእርሻም መሬት ስለሚያንሰው ወደ አፋር ይዞታ እርስ በርሱ እየተቋጠረ፣ እየተደራጀ እና እየታጠቀ ደን እያቃጠለ እና እየመነጠረ ገብቶ ይሰፍራል፡፡ መሬቱም ጥንት የራሱ እንደነበረ፣ አፋር መጤ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራል፡፡ በእርግጥም ቀወቶች ይፋት የሚባለው አገር የራሳቸው ብቻ እንደሆነ

አድርገው የሚቆጥሩበት የሽላሎ ግጥም እንዳላቸው ከአቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ 06/09/2002) እና ከሌሎችም ሰምቻለሁ፡፡

አገራችን ይፋት ለኛ መቼ አነሰን፣

እምቢ አለ እንጂ አረሙ መጭ እየወረሰን፡፡

በዚህ ግጥም በሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ያለው "መጭ" የሚለው ቃል መጤ ለማለት ነው፡፡ ስለዚህም መልዕክቱ መጤዎች አስቸገሩን የሚል ነው፡፡ መጤዎች የሚባሉት ደግሞ በቀወቶች አገላለፅ አፋሮች መሆናቸው ነው፡፡

ግራዝማች ኢሰገሌ እንደሚያውቁት አማሮቹ ወደ አፋር ይዞታ እየገቡ ሲሰፍሩም አፋሮቹ ደግሞ በበኩላቸው በትናንሽ ቡድንም በትላልቅ ቡድንም እየሆኑ የአፀፋ ጥቃት ይሰነዝሩባቸል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታም አፋሮቹም አማራን መግደል የጀግንነት ምልክት አድርገው ስለሚቆጥሩት፣ አማራውም በበኩሉ አፋርን መግደል የወንድነቱ ልክ ማሣያ አድርጎ ስለሚቆጥረው ሁለቱም ሥፍራ ሲያመቻቸው ተጠባብቀው ይገዳደላሉ፣ ይበቃቀላሉ፡፡ ምክንያቱም ገዳይነት በአፋርም ሆነ በአማራ በኩል ዋና የክብር እና የማዕረግ ማግኛ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

የቀወት አማሮችን እና እና የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችን የግጭት መንሥዔ እንዲያስረዱኝ ለሌላው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ ባላምባራስ አይዳሂስ (05/09/2002) አንስቼባቸው ነበር፡፡

ባላምባራስ አይዳሂስ አይዳሂሶ የሚባለው የአፋር ጎሳ ተወላጅና መሪ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተሰሚነት የነበራቸው የይፋትና ጥሙጋ አውራጃ ግዛት የአስተዳደር ጉዳይ አማካሪ ነበሩ፡፡ በደርግም ዘመን እንዲሁ በአፋር በኩል የሚነሱ ጉዳዮች ምክር ለጋሽ ነበሩ፡፡ የነገሩኝን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ባላምባራስ አይዳሂስ (05/09/2002) እንደነገሩኝ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት የማያባራው በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ ዋና ዋና የግጭት መነሻዎች በማለት የሚያነሷቸውም የመሬት ጥበት፣ ውኃ፣ የግጦሽ ሣር፣ በእርሻ ሰብል ላይ በወረራ መልክ እንስሳትን ማሰማራት፣ የእንስሳት ዘረፋ፣ የመሬት ወራራ ማለትም መሬትን በቅኔት መያዝ፣ ተናጣላ አማሮችን ወይም አፋሮችን አዩኝ አላዩኝ ብሎ አድፍጦ የመግደል ልማድ፣ አመቺ ጊዜ እና ሁኔታ ሲያጋጥም ደግሞ ገድሎም ብልትን መስለብ ናቸው፡፡

ባላምባራስ በዕድሜያቸው እንዳስተዋሉት በተለይ አማሮች ምንጊዜም መሬት ይጠባቸዋል፡፡ በተለይ በክረምት ደግሞ መሬታቸው ሰብል ስለሚይዝ የከብት ማሰማሪያም ይቸግራቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በቡድን ሆነው ሁለቱ ወረዳዎች በሚዋሰኑበት አካባቢ የሚገኘውን በተለምዶ “ፈሪ መሬት” የሚባለውን ማለትም የድንበሩን አካባቢ ክፍት መሬት እየመነጠሩ እና በእሳት እያቃጠሉ ወደ እርሻነት ያስገባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከብት ለማሰማራት ወደ አፋር መሬት ይገባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በአደን መልክ እስከ አፋሮች ከብት ማሰማሪያ እና መስፈሪያ ይገባሉ፡፡ አፋሮችም ደግሞ በበጋ ወራት በተለይም በሚያዚያና በግንቦት ውኃው ይደርቅባቸዋል፣ የእንስሳቱም መኖ ያጥራቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ብላኔ ወደማያጣው ቀወት ምድር እየገፉ ይገባሉ፡፡ ስለዚህም በነዚህ ወቅቶች ግጭቱ ይበረታል፡፡ የሕይወትና የንብረት ጥፋት ይከተላል፡፡ ይሄ ሁሉ አልፎ ጥጋብ ሲኖር ደግሞ የየወገኑን ወይም የየጎሳውን ደም ለመመለስ ሁሉም በየፊናው ይነሳሳል፡፡ ይህንንም ዓይነቱን ሁኔታ ባላምባራስ (05/09/2002) እንዲህ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> አፋር በተለይ የመንግሥትን ሕግ አያውቅም፣ የአካባቢው የመንግሥት አካላትም ጠበቅ አድርገው አይከታተሉትም፡፡ ቀድሞም ሆነ ዛሬ አንድ አማራ እና አንድ አፋር ሲጋደል ከወገኑ እና ከጎሳው ውጭ ሌላ ዘወር ብሎ ነገሬ ብሎ የሚያይ የለም፡፡ በመንግሥት በኩል ትኩረት የሚያገኘው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት የጅምላ ሲሆን ነው፣ ጉዳቱ የፀጥታ ችግር ሲሆን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሁለቱ መገዳደል ወሬ ለአካባቢው ልማድ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡

ባላምባራስ አይዳሂስ እንደሚሉት በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል በውኃ፣ በግጦሽ፣ በሰብል ላይ እንስሳትን በመልቀቅ፣ እንስሳትን በመዝረፍ፣ መሬትን ገፍቶ በመያዝ አማካኝነት የሚከሰተው ግጭት ብዙውን ጊዜ የጅምላነት ወይም የቡድን መልክ አለው፡፡ ምክንያቱም የአማራም ሆነ አፋር ቡድን እነዚህን ሀብቶች ኑሯቸውን ለመግፋት ሲሉ የሚፈልጓቸው ስለሆኑ በበላይነት ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ የጥቅም ግጭት ወቅትም የቡድን ፀብ እና ግድያ ይከሰታል፡፡ በተለይም የአካባቢው አማራ አራሽ ስለሆነ ጠፍ የመሰለውን መሬት ለማልማት ሲል አፋሮች እንስሶቻቸውን የሚያሰማሩበትን፣ ውኃ እና ልምላሜ ያለበትን ሥፍራ ለእርሻ እያዋለ አፋሩን ይገፋዋል፡፡ አፋርም ይህን ውኃና ለም ቦታ ማጣት ስለማይፈልግ ሁለቱ ሕዝቦች የደቦ ግጭት ውስጥ ይገባሉ ይላሉ፡፡

ባላምባራስ (05/09/2002) እንዳጫቱኝ የአማራ እና አፋር ግጭት እና መገዳደል ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የሀብት ጥሪቶች መቆጣጠር እና ይገባኛል ባይነት ፍላጎት ላይ ብቻም የተወሰነ አይደለም፡፡ ጥቅም ያላገናኛቸው፣ እንዳችም ፀብ ያላፈሩ፣ የማይተዋወቁ አማራ እና አፋርም ድንገት በመንገድ ሲተላለፉ ተገማምተው ይገዳደላሉ፡፡

ባላምባራስ አይዳሂስን "ፀብ፣ ቂም በቀል፣ የጥቅም ሽሚያ የሌላቸው ሰዎች ለምን ብለው ይገዳደላሉ?" ብያቸውም ነበር፡፡

ባላምባራስ አይዳሂስ የመለሱልኝ "ይሄማ ባህል ነው፣ የቆየ ታሪክ፣ ወግ ልማድ ነው ከጥንት የወረደ" በማለት ነበር፡፡ ሁኔታውን ሲያብራሩልኝም አማራ እና አፋር በአሳቻ ሥፍራ በአነስተኛ ቁጥር ወይም በተናጣላ ከተገናኙ፣ አለዚያም የአንዱ ቡድን ደርጀት ያለ ሆኖ የሌላኛው በሳሳበት ወቅት ሁሉ ይገዳደላሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ሁኔታው ገድሎ ለማምለጥ አመቺ መስሎ ከታያቸው፣ በአገር አማን በለስ የቀናው ገድሎ ዘወር ይላል፡፡ በተለይ ደግሞ ግድያው የተፈፀመበት አካባቢ ፀጥ እረጭ ያለ ከሆነ አፋሩ የአማራውን ብልት ሰልቦ፣ አማራውም ጨርቁን ደም አስነክቶ አንዳንድዬም እንደ አፋሩ ሰልቦ ወደቀዬው የሚገባበት አጋጣሚ እንዳለ አውግተውኛል፡፡ ይሄም ሁሉ በሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች የሚፈፀመው ጎፈሬ ለማሳደግ፣ ለመቀባት እና ቆንዳላ ለመስራት፣ ገዳይ ለመባል እና በገዳይነትም ጀግና የሚያሰኝ ማዕረግ ለማግኘት፣ በማዕረጉም ደግሞ ማህበራዊ ክበሬታን ከፍ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ የአማራና አፋር ግድያ የወንድነት ወግ ማዕረግ ተደርጎ በሁሉም ወገን የሚሸለልበት የሚፎከርበት ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ገዳይነት በሁለቱም ወገን የወንድ ልጅ መለዮነት ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ ይሁንና ዛሬ ዛሬ ይህ የገዳይነት ወግ ማዕረግ የሚባለው ፀጉርን የማጎፈር፣ መቀባት እና ቆንዳላ የመስራት፣ የወንድ ልጅን ብልት የመስለብ ነገር ከቀድሞው እየቀነሰ ቢመጣም ተናጠላዊ መገዳደል ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ቀወቶች እና ሰሙሮቢ ገለአሎዎች አንደኛቸው ወገን በሌላኛቸው ወገን ላይ ያደረሰውን የሕይወት እና የንብረት ውድመት በቂምነት በመቋጠርም እንደገና ወደ ግጭት ይገባሉ፡፡

ሌላኛው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ አቶ አሎሃ ሃንዶ (14/09/2002) ደግሞ ቀወቶች እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች ቂም የሚቋጠሩባቸውን እና መበቃቀላቸውም የሚባባስባቸውን አጋጣሚዎች አውስተውልኛል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት የቀወቶች እና

የሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች ግጭት የተባባሰ የሚሆነው በአንዱ በኩል እጅግ ድርቅ በበረታበት በአንዱ ወገን ደግሞ መልካም አዝመራ በሚያጋጥምበት እና ጥጋብ በሆነበት ጊዜ ነው። አቶ አሎሃ ይህም የሚሆንበትን ምክንያት ሲያብራሩ እጅግ ድርቅና እጅግ ጥጋብ ለአፋርና ለአማራ መገዳደል ምክንያት የሚሆኑት ሁለቱም አጋጣሚዎች ሰዎችን ከቀበሌያቸው ስለሚያነቃነቁ እንደሆነ አውግተውኛል። ይኸውም እጅግ ድርቅ ሲሆን በድርቁ የተጠቃው ወገን እርጥበትና ውኃ ወዳለበት ወደ ተሻለ አካባቢ እንስሳቱን ይዞ ስለሚጓዝ ስለሆነ እና ይሄም የውኃና የግጦሽ ሣር ሽሚያን ስለሚያስከትል፣ የእንስሳት ስርቆትና ዘረፋም ከዚሁ ጋር ስለሚከተል፣ ስለሚያታኩስ እና ስለሚያጋድል፣ አካባቢያዊ ዘረፋን እና ቤት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ መስጊድ ሁሉ መቃጠልን ስለሚያስከትል ነው።

በሌላ በኩል እጅግ ጥጋብም ሲሆን ግድያው የሚበዛው የጠገበው ወገን የቆየ ቂሙ ሲፀፅተው የነበረው ሁሉ በጥጋብ ጊዜ የጦር መሣሪያ መግዛት ስለሚቻለው እና እንስሳት እንደሚያድን ሰው ቂም ወደቋጠረበት ጎሳ ጠጋ እያለ ስለሚገድል ነው። እናም እንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ በጣም እንደሚፈራ አቶ አሎሃ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ያወጋሉ።

ከቀወት ወረዳ ነዋሪ የመረጃ ተባባሪዎቼ ከእነ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ (06/09/2002) እንደሰማሁትም "አማራው አፋሩ ሲጠግብ ሥጋት ያድርበታል። እንዲያውም አፋሩ ዘንድሮ ለወረራ ተነሳስቷል፣ አቆብቁቧል" የሚልበትና የሚሰጋበትም ጊዜ አለ። ይኸውም የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮች ከብቶቻቸው የጠገቡበትና የተራቡበት በመጠኑ የሚያለሙትም አዝርዕት ፍሬ የሰጠበት እና ጠመንጃም በብዛት እየገዙ የሚታጠቁበት ወቅት መሆኑ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ከቀወትም ሆነ ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ያገኘኋቸው የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደሚሉት ለቀወት አማራ እና ለሰሙሮቢ ገለአሎ አፋር ጥጋብም ሆነ ክፉ ቀን መተላለቂያዎች ናቸው። እዚህ ላይ በተለይ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ በሕይወታቸው የታዘቡት አንድ የሚገርማቸው ነገርም እንዳለ አጫውተውኛል። ነገሩ እንዲህ ነው። አፋሮች በጥጋብ ዘመን የገዙትን ጠመንጃ፣ ሽጉጥ እና ጥይት በድርቅና በረሃብ ዘመን ለአማሮች ይሸጣሉ። እንደዚሁም ሁሉ ደግሞ አማሮችም በጥጋብ ዘመን የሰበሰቡትን ጠመንጃ፣ ሽጉጥ እና ጥይት "በቀጭን ቀን" ማለትም በችጋር ጊዜ መልሰው ለአፋሮች ይሸጣሉ። በዚያው መሣሪያቸው ደግሞ በግልም በቡድንም ይገዳደላሉ። ስለዚህም አንደኛቸው ለሌላኛቸው መሞቻውን ያቀብላል። የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች አኗኗር እንዲህ ዓይነት ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ነው።

አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ (06/09/2002 ዓ.ም.) እንደሚያወሱት ቀወቶች አፋሮችን ታሪካዊ ደመኞቻቸውም አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ እንዲያውም ቀወቶች ይህን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ፀበኝነታቸውን የሚገልፁበት ሽላሎ እንዳላቸውም ነግረውኛል፡፡

ጠላት ከውጭ አገር መች ይገስግሳል፣
ጠላት ከባህር ማዶ መች ይገስግሳል፣
አካኂን እያዩ ከዚሁ ይነሳል፡፡

አቶ ሰጥአርጌ እንደሚሉት ቀወቶች ማለዳ ተነስተው ፀሐይ ስትፈነጥቅ ወደ ምስራቅ የሚመለከቱት እንደሌሎች አካባቢዎች ነዋሪዎች የፀሐይ ጨረርን ለማየት እና ለመሞቅ ብቻ አይደለም፡፡ በአፋር በኩል አገሩ አማን ማደሩን ለመማተርም ነው፡፡ የዚህም ምክንያቱ አካባቢው ከጥንት ጀምሮ በዚያ በኩል ሲጠቃ በመኖሩ፣ ጥቃቱም ሲዘከር በመኖሩ እና ዛሬም ባለማባራቱ ወይም ባለማቋረጡ ነው፡፡ የሽላሎውም ግጥም ይህንኑ ማስረገጫ ነው፡፡ አቶ ሰጥአርጌ ደርሶን ትንሽ እንዲያጫወቱኝ ብዬ የዝንጋታ ቆይታ ጊዜ እንዲሰጡኝ አድርጊያቸውም ነበር፡፡ እናም ዘለግ ላለ ጊዜ ቆይታ አድርገን ነበር፡፡ በቆይታችን ወቅት ታዲያ ያነሱልኝ ሌላው የቀወቶች እና የሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች ግጭት መነሻ ጥጋብ እና ቀጭን ቀን ጭምር ነው፡፡ በቀወቶች ዘንድ የጥጋብ ዘመን የሚባለውም የበልግም የመኸርም አዝመራው የሰጠ ሲሆን እና ሰብሉ ተሰብስቦ፣ ምርቱ ከጎተራ እና ከጉድጓድ ከገባ በኋላ ባሉት ወራት በተለይም ከጥቅምት እስከ ግንቦት ያለው ጊዜ ነው፡፡ በቀወት እና አካባቢው ቀጭን ቀን የሚባለው ደግሞ አዝመራው ሲርቅ፣ መሬቱም ልምላሜ ሲያጣ ነው፡፡ ረሃብን የሚያስከትለው ድርቅ የሚበዛባቸውም ወራት ብዙውን ጊዜ ሚያዚያ፣ ግንቦት እና ሰኔ ናቸው፡፡ የከፋ ድርቅ የሚባለው የሚከሰተው ግን በየዓመቱ ሳይሆን በየተወሰኑ ዓመታት ባመዛኙም በሰባት እና በየአሥር ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚመላለሰው ነው፡፡ ይህም የአካባቢው የረሃብና የድርቅ ዑደት ሁኔታ በሥነቃልም ጭምር የሚገለፅነቱ፣ በሥርዓቱ መፍታታቱ እና መተንተኑ አይዘነጋም (ፈቃደ 1996)፡፡

ይሁንና አማራ እና አፋር በያመቱ ከሚያዚያ እስከ ሰኔ ወይም መስከረም ላይ መጋጨቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ግጭት ዓመታዊ ግብር ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህ ሕዝቡም የወረዳ የመንግሥት አካላትም ጭምር የአካባቢውን አማሮች እና አፋሮች ግጭት ሲሰሙ ሰምተው እንዳልሰማ፣ አይተው እንዳላዩ የሚሆኑበት፣ እጅግ ወሬው ከደመቀም "ያው የተለመደ ዓመላቸው፣ ልማዳቸው ነው" ብለው የሚያልፉበት ሁኔታ

እንዳለ ነው የሚነገረው (የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) ።

ለሌላው የመረጃ ተባባሪዬ ሼህ መሐመድ ሰይድ 10/09/2002) የድንበርተኞቹን የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ሕዝቦች ግጭታዊ ግንኙነት ሁኔታ ያወጉኝ ዘንድ አንስቼባቸው ነበር።

ሼህ መሐመድ ሰይድ ከዚህ በላይ ለሰነዘርኩት ጥያቄ የሰጡኝ ምላሽ የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ግንኙነት የነገሩኝ በምሳሌ አስደግፈው ነው። እንዲህ አሉኝ፡ “መደበኛ ፍርድ ቤት ምስክርነት ቀርበህ ታውቀለህ?” አሉኝ። የእኔ ምላሽ “መስክሬ ባላውቅም ሲመሰክሩ አይቼ አውቃለሁ” የሚል ነበር። ሼህ መሐመድ ሰይድ የሰፍ “ያው ነው ታውቃለህ ማለት ነው” ብለው ቀጠሉ። “አየህ ዳኛው የምስክሩን ቃል ከመስማቱ በፊት ከከሳሽ እና ከተከሳሽ ጋር ያለውን ግንኙነት ሁኔታ የሚጠይቀው ‘ከከሳሽ ወይም ከተከሳሽ ጋር ፀብና ዝምድና አለህ ወይ?’ በማለት ነው። የአፋር እና የአማራም ግንኙነት ሁኔታ ዘወትር ፀብ እና ዝምድና የተቀላቀለበት ነው” አሉኝ። ሼህ መሐመድ ሰይድ እንዳብራሩልኝ ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች አንድ ጀምበር ሰላም፣ አንድ ጀምበር ደግሞ ግጭት አያጣቸውም። በሰላም ቀን እየተያዩ ይተሳለፋሉ፣ ይገበያያሉ። በቅርብ የሚተዋቁት ሰላምታ ይለዋወጣሉ። ሰላም በራቃቸው ቀን ደግሞ ሰላምታውን ወደ ፉከራ ይቀይሩታል። እዚያው እገበያውም ላይ ይጋጫሉ፣ ይገዳደላሉ። በዚህም ምክንያት በተለይ በድንበሩ አካባቢ የሚኖሩ አማሮች እና አፋሮች ዘወትር ፀብም ዝምድናም የሚፈራረቁባቸው ናቸው ይላሉ።

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) እንዳወጉኝ ግጭቱ በፈሪ መሬት ድንበር ግፊትም፣ በውኃ ፍለጋም፣ በእንስሳት ግጦሽ ሣርም፣ በእንስሳት ዘራፋም፣ እንስሳትን በሰብል ላይ በመልቀቅም፣ በቆየ ቂም በቀልም፣ ዝና ለማግኘት ሲባልም አንድን አማራ ወይም አፋር በመግደልም ምክንያት ሁሉ ሊቀሰቀስ፣ ቂም ሊያስቋጥር እና ቡድናዊ ባህርይ ሊይዝ፣አጋታሚ ጠብቆም ሊያዋጋ እና ሊያጋድል ይችላል። ስለዚህ ትልቁ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ችግር አንደኛቸው ወገን የሌላኛቸውን ወገን ሕይወት ለማጥፋት ዘወትር እንደ ዱር አውሬ አዳኝ የሚተጉ መሆናቸው ነው። በአካባቢው አማራ አፋርን፣ አፋር አማራን መግደል መቻላቸው በየወገናቸው በኩል ክብር

ያስገኝላቸዋል፡፡ በጥቅሉ በአካባቢው ሰው መግደል ያኮራል፣ የአደባባይ ሰው ያደርጋል፣ ያስከብራል፣ ያስሞግሳል፡፡

"ለመሆኑ ሰው መግደል እንዴት ነው የሚያስከብረው?" የሚል ሐሳብ ለሼህ መሐመድ ሰይድ ሰንዝሬላቸው ነበር፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) እንዳወጉኝ አፋሮች እና አማሮች ሰው ሲገድሉ የሚያሳዩት የወንድነት ማሳያ ምልክት ነገር አላቸው፡፡ አንዳንዱ አማራ አፋር ሲገድል ለአንድ ዓመት ፀጉሩን ያጎፍራል፣ ቆንዳላ ይሰራል፡፡ ይህ ሼህ መሐመድ ያጫወቱኝ የገዳይ መለዮ አደራረግም በልማዱም "ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያረጋግጡ ወሬ" በሚል ምሳሌ ይገለፃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አፋር የገደለ አማራ እጁ ላይ አምባር ያጠልቃል፡፡ በጎራዴው እና በጠመንጃውም ላይ የመዳብ ሽቦ ይጠመጥማል፡፡ በአንገቱም ላይ ሻሚ ያንጠለጥላል፡፡ በጣቱም ላይ የብር ቀለበት ያጠልቃል፡፡ ሰው መግደል ትጉ እና ንቁ፣ ጠርጣራም እንደሚያደርግ እና እንደሚበጅም እያዳነቀ ይሸልልማልም፡፡

ሰው ግደሉ ሰው መግደል ይበጃል፣

ሰው ያልገደለ ሰው ሲሄድ ያንጎላጃል፡፡

በልማዱም ቀወቴ ከአራት በላይ አፋሮችን ከገደለ ጆሮውን ተበስቶ ሎቲ ያንጠለጥላል፡፡ ሼህ መሐመድ ሰይድ እንደሚሉት አማራ በልማዱ እንኳን አፋር ገድሎ አንበሳ እና ዝሆንም ሲገድል ይጋጌጣል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ሕግ ስለሚፈራ ገድሎም ቢሆን የገዳይነት ምልክቱን አያንጠለጥልም፣ አይጊያጌጥም፡፡

በአንፃሩ ደግሞ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮችም ከአንድ እስከ አሥራ ሁለት ሰዎችን፣ ዝሆኖችን፣ አንበሶችን መግደል ለቻለ ሰው እንደ አገዳደሉ ሁኔታ፣ እንደገደላቸው ሰዎች አኳኋን ወይም ሁናቴ ማህበራዊ ክብር እና ማዕረግ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም መሰረት አንድ አፋር አንድ ሰው፣ አንድ ዝሆን እና አንድ አንበሳ ከገደለ በፀጉሩ ላይ የሰጎን ላባ ይሰካል፡፡ ጨቤው ወይም ጊሌው ላይ ድምፅ የሚሰጥ ወይም የሚያቃጭል ነገር ያንጠለጥላል፡፡ ከሁለት እስከ አሥራ ሁለት ሰዎችን፣ ዝሆኖችን፣ አንበሶችን መግደል መቻልም የተለያዩ የፈረስ ወይም የሞጋሳ ስሞችን ያስገኛል፡፡ ስለዚህም በስያሜ ረገድ አንድ የገደለ "በመርጠ"፣ ከሁለት በላይ የገደለ "ዔለማ" ይሰኛል፡፡ "ዔለማ" የሚሰኘውም ሰው እንደገና በገደላቸው ሰዎች፣ ዝሆኖች እና አንበሶች ቁጥር እየተለየ ይጠራል፡፡ በዚህም መሰረት አሥራ ሁለት የገደለ አንደኛ ዔለማ፣ ሃያ አራት የገደለ ሁለተኛ ዔለማ፣ ሰላሳ ስድስት የገደለ ሦስተኛ ዔለማ እየተባለ ይጠራል፡፡

አሥራ ሁለት ሰዎችን ብቻ የገደለ ደግሞ "ዒላማ ኪቡ" የሚል ስያሜ ይሰጠዋል፡፡ በዚሁም መሰረት አንድ የገደለ በግራ እጁ ላይ የነበረውን አንባሩንም ወደ ቀኝ እጁ ያዛውራል፡፡ ከአራት እስከ ስድስት ጠላት የገደለ ደግሞ ጆሮውን ይበሳል፣ ጠመንጃውንም በተለያዩ ነገሮች ያስጌጣል፡፡ የብልት ሰለባ ካቀረበም የበለጠ ይከበራል፡፡ ወጣት ከሆነ የአጎቱን ሴት ልጆች ያማርጥበታል፣ ያፎካክርበታል፡፡ ጎልማሳም ከሆነ ቅምጥ ያፈራርቅበታል፡፡ በአደባባይም ከጎሳ መሪዎች እና ከሽማግሌዎች ቀጥሎ ለመናገር እና ለመተቸት ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በማናቸውም ማህበራዊ ግንኙነት ወቅት ገዳይ የሆነ ሰው "እሱ ይናገር ! " እየተባለ የነገር መሪነት ተቀዳሚነት ያገኛል፡፡ ስለዚህ የብልት ሰለባ የጣለ ገዳይ ሳይቀደም ሌሎች አይከተሉም፡፡ ስለዚህም ገዳይነት ብቻ ሳይሆን ገድሎ ሰለባ ማቅረብ እጅጉን በማህበረሰቡ ዘንድ ይደነቃል፣ ይሞገሳል፣ ይከበራል ይላሉ፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) እንደሚተርኩት በተለይ "ዔለማ" ደረጃ ያለው ሰው እርሱ በሄደበት መንገድ ያልገደለ አይሄድም፡፡ ዔለማው በመንገድ ሲሄድም መንገድ ይለቀቅለታል፡፡ መሽቶ በእንግድነት በሚያድርበትም ቦታ ሁሉ የሚተኛው ያልገደለ ሰው ሽማ ተነጥፎለት ነው፡፡ ገበታ ተሰርቶ ማዕድ ሲቀርብም "ዔለማ" ሳይቀምስ ሌላ አይቀምስም፡፡ የአፋር ወንድ ወጣቶች ከአሥር እስከ አሥራ ስድስት ዓመት በሚሆኑበት ጊዜ በሚካሄደው የግርዛት "ወኢነቦ" የዘፈንና ጭፈራ ወቅት ገዳይ ሳይቀደም ሌሎች ቀድመው አይጨፍሩም፡፡ በአጠቃላይ "ዔለማ" ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ተከባሪ ስለሆነ ለሁሉም ነገር ተቀዳሚ እና ተመራጭም ነው፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) እንደሚሉት የአፋር ወንድ ገድሎ ካልሰለበ እና ምልክት ካላሳየ ከወንድነት ተራ የወጣ ይመስለዋል፡፡ የብልት ሰለባ ግን ጥንት የአፋር ባህል አልነበረም፣ የሰለባ ባህል የነበራቸው ጅሌዎች ናቸው፡፡ አማራም አሁን በቅርብ ጊዜ ከጅሌና ከአፋር እያዩ መስለብ ጀምሯል፡፡ ይሁንና እንደምሰማው አማራ በሰለባው ብዙም አይመጻደቅም፡፡ ለተወሰኑ ብጤዎቹ አሳይቶ ቅቤውን ተቀብቶ ዝም ይላል፡፡ ሰለባውን በየአደባባዩ መታወቂያና መለያ አያደርገውም፡፡ መግደሉ ከታወቀለት በአካባቢው የመፈራት እና የመደመጥ ክብር ያገኛል ብለውኛል፡፡ እኔም እዚህ ላይ ሰለባ በቀወቶችም ሆነ በሰሙሮቢዎች ዘንድ ከባድ መበቃቀያ እና የከፍተኛ ጠላትነት መታያ ወይም መከሰቻ እና መገለጫ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ እንደሚታወቀውም ሰለባ የሚፈፀመው ከሟችም ከቋሚም ላይ ነው፡፡ ይህም ድርጊት በየበኩላቸው ሲደርስባቸው

ቀወቶችም ሆኑ ሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች እጅግ አስነዋሪ ድርጊት እንደተፈፀመባቸው እና እንደተደፈሩ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሲፈፅሙት ይህንኑ የተቆጫጩበትን እና የተብከነከኑበትን ነገር አቻ ለአቻ እንደተወጡ እና እንደተበቀሉም አድርገው ይረኩበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይ አፋሮች ለማህበራዊ ክብር መጎነፀፊያነትም ይገለገሉበታል፡፡ ስለዚህም ሰለባ በአቻዊ ምልልስነት እና በእከሌ እንዲህ ተደረገ ወይም በእንዲህ ያለ ሁኔታ ሞተ በሚል እየተተረከ ለዘመናት የቀጠለ ተግባር በመሆኑ ሰፋ አድርጎ ለማየት ያህል ለመረጃ ተባባሪዎቼ ሁሉ ደጋግሜ አንስቼባቸዋለሁ፡፡ የነገሩኝንም ሁሉ ለመተረክ ሞክሬያለሁ፡፡ እናም ወደ ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) ልመለስ፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) ሰለባው በአፋሮቹ በኩል እንዴት እንደሚታይም አጫውተውኛል፡፡ "አፋር በተለይ ምድሩ ለምለም ሆኖ ሰፈሩ ጥጋብ ከሆነ፣ አሥራ ሁለት ዓመት እስከ አሥራ ስድስት ዓመት የሆኑ ወንዶች ልጆቹ የመፎከሪያ ጊዜያቸው ነው፡፡ ይሄ ዕድሜ ለአፋር ወጣቶች ግዳይ ማቅረቢያ ጊዜው ነው፡፡ የወንድነትም መለኪያ ነው፡፡" ሼህ መሐመድ ሰይድ እንዳስተዋሉት ሰለባ ያቀረበ ወጣት አፋር በባህሉ የከበረውን የ"አብሱማ" ጋብቻ ሥሪት ተከትሎ ሚስት መርጦ ለማግባት፣ በጎሳው ውስጥ የጎበዝ አለቃ ለመሆን እንዲሁም ለልዩ ልዩ ማህበራዊ ምክክርና ትብብር ይታጫል፡፡ ካገባም በኋላ ደግሞ ሚስቱ ከሌሎች ሰለባና ግዳይ ከሌላቸው ሰዎች ሚስቶች ቀድማ ውኃ ትቀዳለች፡፡ ፈረሱም ከሌሎች ካልገደሉ ሰዎች ፈረሶች ቀድሞ ውኃ ይጠጣል፡፡ ስለዚህም በአፋር በኩል ግዳይና ሰለባ ከፍተኛ ማህበራዊ ከበሬታን ያስገኛል ብለውኛል፡፡ ሼህ መሐመድ ሰይድ እንዳብራሩልኝ አፋር በተለይ ግርዛቱ ከሚፈፀምበት አሥር ዓመቱ ጀምሮ እስከ አሥራ ስድስት ዓመቱ የመፎከሪያ ጊዜው ስለሆነ በተለይ ምድሩ ለምለም እና ጥጋብ ከሆነ ግዳይ ማቅረቢያ ጊዜው ነው፡፡ ምክንያቱም የምድሩ መለምለም እንስሳቱ ግጦሽ፣ ሰዎችም ወተት እንደልባቸው እንዲያገኙ ይረዳቸዋልና ነው፡፡

ሌላኛው ቁልፍ የመረጃ ምንጬ አቶ አህመድ ኢብራሂም (16/09/2002 ዓ.ም) እንዳወሱልኝም በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ለሚስተዋለው ግጭት መካረር አንዱ ዋና ምክንያት ከላይ ሼህ መሐመድ ሰይድ ያነሱት የብልት ሰለባ ነው፡፡ በተለይ የብልት ሰለባ ጉዳይ አፋሮቹንም ሆነ አማሮቹን እጅግ በጣም ለተካረረ መበቃቀል የሚያነሳሳ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አፋሮቹም ሆኑ አማሮቹ

ወገናቸው የሆነ ሰው ከመገደሉ ይልቅ መሰለቡ ያንገበግባቸዋል፡፡ ጊዜ ሳይሰጡም ለበቀል እንዲነሳሱ ይገፋፋቸዋል፡፡ የብልት ሰለባ ሁለቱንም ለጅምላ ግጭት ጭምር ይዳርጋቸዋል፡፡

እኚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ እንደሚሉት የቀወት አማሮችም ሆኑ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ሰው መግደልን እና መስለብን አኩሪ ልማድ፣ መልካም ምግባር አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ስለዚህ በልማዱ ሰው መግደል እና ሰለባ ማቅረብ እንደ ጥሩ ምግባር እየታየም በሕይወትም በሞትም ያስከብራል፣ ያስወድሳል ይላሉ፡፡ በተለይ አፋሮች ስለ ሰለባ ያላቸውን አስተሳሰብም ሲገልፁ "አፋሮች ሰለባን እንደ ባህል አጥብቀው ይዘውታል፡፡ የወንድ ልጅ ብልት በግዳይ ሰለባነት ማቅረብ ማህበራዊ ክበሬታ ያስገኛል፡፡ በተለይ ቀደም ባለው ዘመን የአፋር ልጅ አማራ ከገደለ ሰለባ ይዞ መገኘትንና ማቅረብን እንደ ከፍተኛ ጀግንነትና ጀብዱ ይቆጥረው ነበር፡፡" ከገለፃቸው መረዳት እንደሚቻለውም ሰው የገደለ ሰው በሕይወት ሲኖር ካልገደሉ ሰዎች የበለጠ ክብር ያገኛል፡፡ ሲሞትም ይጨፈርለታል፣ ይፎከርለታል፣ ይመሰልለታል፡፡

አቶ አህመድ ኢብራሂምን (16/09/2002 ዓ.ም) "ሰለባን መፈፀም ማህበራዊ ክበሬታን ከማስገኘቱ በተጨማሪ ሌላ መነሻ ምክንያት የለውም ወይ?" ብያቸውም ነበር፡፡ እርሳቸውም ወደ ኋላ ሄደው የሚያስታውሱ ትን እንዲህ አወጉኝ፡፡

አቶ አህመድ ኢብራሂም 16/09/20002 ዓ.ም) በዚሁ በሰላባ ጉዳይ ላይ ከቀደምት አባቶችም እሰማው ነበር ያሉትን አክለውልኛል፡፡ እንዲህ ቀጠሉ፡፡

> *ከአባቶች እሰማው እንደነበረው አንዳንድ ጊዜ የአፋርና የአማራ ግጭት መንደሮችን ሁሉ እስከማጥፋት ይደርስ ነበር፡፡ መንደሩ ቀዬው የጠፋበት፣ ወገኑ በአሰቃቂ ሁኔታ ያለቀበት ወገን ደግሞ ጠላቴ የሚለውን ወገን ብልት እየቆረጠ ቀሪ ወገኑን ማፅናናትን ሥራዬ ብሎ ተያይዞት ነበር፡፡ ያም ጦርነት የአፋርና የአማራ ግጭት መንደሮችን ሁሉ እስከማጥፋት ይደርስ ነበር፡፡ እናም ቀዬው የጠፋበት፣ ወገኑ በአሰቃቂ ሁኔታ ያለቀበት ወገን፣ ጠላቴ የሚለውን ወገን ብልት እየቆረጠ ቀሪ ወገኑን ማፅናናትን ሥራዬ ብሎ ተያይዞት ነበር እያሉ ይጫወቱ ነበር፡፡ ብልቱም የሚቆረጠው የተገዳይ ብቻ አልነበረም፡፡ የሚያድግ ልጅ፣ እቤት የዋለ ሽማግሌ ሁሉ ሳይቀር በአጠቃላይ ወንድ የሆነ ሁሉ ነበር፡፡ ይሄም ሰለባ የሚፈፀመው የግዳይ ጥሎሽን ቁጥር ለማብዛት፣ ደግሞም የጠላትን ወገን ዘር ለመቀነስ ወይም ለማጥፋትም ሁሉ እንደነበረ ይነገር ነበር፡፡*

ይላሉ፡፡ አቶ አህመድ ኢብራሂም (16/09/2002 ዓ.ም) በተለይ ስለ የብልት ሰለባ መሰረታዊ አመጣጥ ሰምቻለሁ የሚሉትን እና የሚያስታውሱትን እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> በጥንት ዘመን የአፋር እና የአማራ መሪዎች ዘወትር ይዋጉ ነበር። የአማራውም ጦር ከብዛቱ የተነሳ የአፋርን ጦር ያጠቃ ነበር። በዚያም ተደጋጋሚ መጠቃት ምክንያት የአፋር መሪዎች በማያቋርጥ ሁኔታ ከላይ እየተንደረደረ የሚወራቸውን እና የሚያጥለቀልቃቸውን ጦር ኃይል ቁጥር ለማመናመን፣ የሠራዊታቸውንም የውጊያ ሞራል ከፍ ለማድረግ እያንዳንዱ የአፋር ሰራዊት የገደለውንም ሆነ የማረከውን ወንድ ሁሉ ብልቱን እየቆረጠ በመሪዎቹ ፊት እንዲያቀርብ፣ ስለ ጀግንነቱም እንዲጨፈርለት እና ስለ ጀግንነቱም ባቀረበው የሰለባ መጠን ሽልማት እንዲደሚያገኝ ያውጃሉ። ሠራዊቱም በታዘዘው መሰረት ይፈፅማል። ልማዱም ከዚያ ወዲህ የጀግንነት መግለጫ ሆኖ እንደቀጠለ ይነገራል።

ብለውኛል። አቶ አህመድ ኢብራሂምን "በእርስዎ ዕድሜ የሚያውቁት ሰለባ አለ ወይ?" ብያቸውም ነበር።

> አሁን በዕኔ ዕድሜም ቢሆን ይኸው ይፈፀማል። በተለይ ድሮ ደግሞ በዚህ መልኩ በህፃንነታቸው የተሰለቡ ናቸው የሚባሉ ሰዎች በብዛት እንደነበሩ እና አሁንም እንዳሉም አውቃለሁ። በእኔም ዕድሜ የሚገኙ ስልቦችም አሁንም እንዳሉም አውቃለሁ፣ በብዛትም በዚያ በአባላሽኝ ዘመን የተሰለቡ አሉ። ከዚያም ወዲህ ደግሞ የተገደሉ አማሮች ተሰልበው ስለመገኘታቸው ሲነገር በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ። አሁን አሁን ደግሞ የተገደለ ሰው ተሰልቦ ቢገኝም በምሥጢር እየተያዘ ስለሚቀበር ብዙ ሰው ሟች በአፋር ወይም በአማራ ስለመገደሉ እንጂ ስለመሰለቡ አያወራም። የሚያውቀው አስከሬኑን ያነሳው የቅርብ ቤተሰቡ ብቻ ነው።

በማለት መልሰውልኛል (16/09/2002 ዓ.ም) ።

እዚህ ላይ አቶ አህመድ "አባላሽኝ" ያሉት የኢጣሊያ ወረራ ወቅት ማለትም ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም. ያለው ጊዜ ነው። ያ የአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ወረራ በአካባቢው የ "አባላሽኝ" ጊዜ በሚል ይታወቃል። እናም ይህ የሰለባ ነገር በተለይ በዚያ ወቅት ተባብሶ እንደነበር ነው አቶ መሐመድ ኢብራሂም ያስታወሱት። አቶ አህመድ ኢብራሂም እንደሚሉት በዚያን ጊዜ ሰለባው ሊባባስ የቻለውም ኢጣሊያ የአበሻን ወረራውን የመመከት ኃይል ለማዳከም የተለያዩ ከገገርነት ጋር የተያያዙ የብሔር፣ ብሔረሰብ ልዩነት እና መጎሻሸም ቁርሾዎችን እያነሳች እና እያፋፋች አንዳንድ የአፋር እና የጅሌ ኦሮሞዎችን በማስታጠቅ በተጎራባች አማሮች ላይ ታዘምት ስለነበር ነው።

በዚህ በጅምላ የወንድ ልጅ ብልት ሰለባ ላይ ከቀወት በኩል መረጃ እንዲሰጡኝ ከጠየቅኋቸው መካከል አንዱ አቶ ኪዳኔ መከታ 19/01/2003) የአቶ አህመድ ኢብራሂምን (16/09/2002) ገለፃ ትክክልነት በማስተማመን እርሳቸውም እንዲህ ሲሉ ያክላሉ።

የጅምላ ስለባ የሚበዛው በተለይ መንግሥት ደከም ባለ ጊዜ ነው፡፡ እስከዚህ ዘመን ድረስ መንግሥቱ አማራ /ክርስቲያን/ ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም አማራ መንግሥት ባይሆንም፣ መንግሥት የሆነ ይመስል ትንሽ ግርግር ሲፈጠር በአማራ ላይ ጥቃት የመሰንዘር ልማድ አለ፡፡ አማራውም ይሄ ስለመረረው እና ስለገባው በተለይ በድንበር አካባቢ ያለው አልጋ በተናጋ ጊዜ ከመቼውም በበለጠ እራሱን ለመጠበቅ ይዘጋጃል፡፡

አቶ ኪዳኔ አልጋ የሚሉት ዙፋንን ነው፡፡ ዙፋን የንጉሥ መቀመጫ እንደመሆኑ ንጉሡ ወይም መሪው በመንበሩ በሰላም ለመቀመጥ በታወከ ጊዜ የሚከተል ብጥብጥ እና ግጭትን ለመግለፅ፡፡

አቶ ኪዳኔ መከታ 19/01/2003) እንደ ምሳሌም ያነሱልኝ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት እና በ1953 ዓ.ም. ታዘብኩ የሚሉትን ነው፡፡ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች እና የአፄ ኃይለሥላሴም ጦር ማይጨው ላይ ከተሸነፈ በኋላ በአካባቢው ብርቱ ሥጋትና ጉዳትም ደርሶ እንደነበር እንዲህ ያስታውሳሉ፡፡

> የኢጣሊያ ወታደራዊ አዛገሮች ሁሉንም ጦርነት ብቻቸውን እንደማይወጡት በማመን እና እዚህ አካባቢ ያለውንም የግጭት ልማድ በመጠቀም ለአንዳንድ የአፋርና የጅሌ ሰዎች መሣሪያ አስታጥቀው አብረዋቸው በጎረቤቶቻቸው ላይ እንዲዘምቱ አድርገው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በዚያን ጊዜ  ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት ውድመት በአማራው ላይ እስከ ደጋው መንዝ ድረስ ዘልቆ ነበር፡፡ የዚያ ጦርነትና ወረራ ጠባሳ ታዲያ ዛሬም አለ፡፡ ከይፋት እስከ መንዝ ብዙዎች በሕፃንነታቸው ብልታቸውን አጥተው እስከ ዛሬ ስልብ እየተባሉ የሚኖሩ ልሂቃንም “ዘገሮችም” አሉ፡፡

ይላሉ አቶ ኪዳኔ፡፡ አቶ ኪዳኔ “ዘገር” የሚሏቸው ያልተማሩትን ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል በስምና በመልክ የሚያውቋቸውንም ያነሳሉ፡፡ እዚህ መዘርዘሩ ግን ሥነ ምግባራዊ ስላልሆነ አልፌዋለሁ፡፡ በነገራችን ላይ ከ1928-1933 ዓ.ም የዘለቀውን አምስቱን የኢጣሊያ ወረራ ዘመን አብዛኛቹ የቀወት አረጋውያን የሚያስታውሱት የአባላሽኝ እና የአፋጀሽኝ ዘመን እያሉ ነው፡፡

አቶ ከተማ አይሻር (15/01/2003) ከዚሁ ከሰለባ ጋር አያይዘው በአብነት መልክ ያጫወቱኝም አለ፡፡ ጨዋታውን እነሆ፡፡

> በደርግ ጊዜ አንድ ዘመናዊ ትምህርት ቀመስ የሆኑ ስልብ ሰውዬ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ውስጥ በቀበሌ ገንዘብ ያዥነት ተመርጠው ኃላፊነት ይረከባሉ፡፡ ሥራቸው የቀበሌ ቤቶችን ኪራይና ልዩ ልዩ ገቢዎች መቀበል ነበር፡፡ አንድ ቀን አንዲት ሴት የቤት ኪራይ ልትከፍል ወደ ቢሯቸው ትሄድና ሂሳቡን ይቀበሉኝ ትላቸዋለች፡፡ እርሳቸውም ‘ባለፈው የከፈልሽበትን ደረሰኝ አምጪ! አለዚያ እስከመቼ እንደከፈልሽ ማወቅ አይቻለኝም’ ይሏታል፡፡ እርሷም በዚህ ጊዜ ሰውዬው በሴቶች ዘንድ ሲታሙ

የነበሩበትን ነባር ቁስል ትቀሰቅሳለች፡፡ 'ለምን እርስዎ ጉርዱ ላይ አይፈልጉትም፣ ጉርዱ አይጠፋም እኮ' ትላቸዋለች፡፡ ሰውዬው ተስፈንጥረው ከመቀመጫቸው ተነስተው ሴትዮዋ ላይ ይከመሩባታል፡፡ ሴትዮዋም 'ጉርዱ ይታይ ባልኩ እንዴት እደፈራለሁ' ብላ ትጮሃለች፡፡ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ይገላግሏቸዋል፡፡ ሰውዬው ከዚያ በኋላ 'ግደሉኝ እንጂ የቀበሌ አመራር አልሆንም፣ አሻፈረኝ' ብለው ይቀራሉ፡፡ ብዙ የስልቡ ዘመዶችም በሴትዮዋ ጥርስ ነክሰውባት ስለነበር በኋላ ላይ አካባቢውን ለቃ ዘወር ትላለች፡፡

እናም ይሄ የሰለባ ነገር ሲነሳ ደሙ የማይንተከተክ የለም፣ የሞተ ይረሳል፣ በሕይወት ያለ ጉዳተኛ ግን ቂም እንዳይሞት፣ እንዳይረሳ ያደርጋል በማለት አጫውተውኛል፡፡

አቶ ከተማ ከዚሁ ከላይ ከቀረበው ሁኔታ ጋር በማያያዝ በ1953 ዓ.ም. በአካባቢው የመሬት መንቀጥቀጥ ደርሶ በነበረበት ወቅት አጋጥሞ የነበረውን ሥጋት ያስታውሳሉ፡፡ እንደሚያስታውሱት የአካባቢው ነዋሪ የመሬት መንቀጥቀጡ ገደሉን ሁሉ እየገመዳደለ ሲያወርደው ሕዝቡ ሴትና ልጁን የሚያሸሸው ወደዚያው ወደ ገደሉ ወደ አምባማው መንዝ በኩል ነበር፡፡ ይኸውም የሆነው ከታች ከአፋር እና ከጅሌ ኦሮሞ በኩል ሊሰነዘር ይችላል ተብሎ የተሰጋውን ጥቃት ማለትም ግድያና ሰለባ ለማምለጥ ነው፡፡ በመኖሪያ አካባቢያቸው የቀሩት ንብረታቸው ያጓጓቸው ትጥቅ ያላቸው ወንዶች ብቻ ነበሩም ይላሉ፡፡ ከአቶ ከተማ አገላለፅ መረዳት የሚቻለውም ቀወቶች ከአፋ ጥቃት ይልቅ በርዕደ ምድር መሞትን መርጠው ገደላገደሉ እየተቀረፈ ወደሚወርድበት አምባ ለመጠጋት መምረጣቸውን ነው፡፡ ወደ ሌላ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ እና ጥያቄዬ ልለፍ፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ አቶ ከተማ አይሻር ሲሆኑ ጥያቄዬ ደግሞ የሚከተለው ነበር፡፡

"ለመሆኑ አማሮች ከግድያ አልፈው መሰላለብን እንዴት ሊያዳብሩት የቻሉ ይመስልዎታል?" አቶ ከተማ አይሻር (15/01/2003) ለዚህ ጥያቄዬ የሚመስላቸውን ሰበበ-ምክንያት እንዲህ አካፍለውኛል፡፡

> ወገኑ የተገደለበት ቤተሰብ ስለ ገዳዩ ወገን በጨዋታ ማለትም በተረትም፣ በትውስታም፣ በሽላሎም፣ በለቅሶም፣ በአሽሙርም በየምክንያቱ እና በየአጋጣሚው ነገሩን እያነሳ የመቆጫጨት ስሜቱ እንዲያድግ አቅሙ የፈቀደለትም ጊዜና አጋጣሚውን ባገኘ ቁጥር ጥላቻ ያሳደረበትን ወገን እንዲገድል ብቻ ሳይሆን እንዲሰልብም ሳይገፋፋው አልቀረም፡፡ መቼም በእኛ በአማሮች የቤተ-ትውልድ ቆጠራ አለ፡፡ እናም እከሌ ዘመዳችን፣ አጎታችን፣ የአክስታችን ልጅ የሞተው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነው እያሉ በጨረቃም፣ ማታ ማታ ደግሞ በየእሣቱ ዳርም ጨዋታ፣ በየወፍሩ /ደቦ/ ሥራ፣ በየሰንበቴውም፣ ክርስትናውም፣ በየሰርጉም በየማርገጃው ለቅሶ፣ በየተዝካሩም ጭምር ይነሳል፣ ይወጋል፡፡ ታዲያ ይህን ዓይነቱን ነገር እየሰማ

ያደገ ልጅ ለወንድነት ሲደርስ ይገድላል፣ ይሰልባል፡፡ ሰለባ ከጣለ በኋላ ደግሞ ክብሩ፣ ዝናው ከፍ ይላል፣ የወገኑም መታፈሪያ ይሆናል፡፡

በማለት ይሄ ይሄ ሁሉ ሰለባን ያበረታታው እንደሚመስላቸው ነግረውኛል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በአፋሮች ዘንድ የሰለባ መነሻው የተሰላቢውን ወገን ዘር ለመቀነስ ቢሆንም እያደር ግን የጀግንነት ሙያ ማስቆጠሪያ፣ ማሳያ እና ማረጋገጫ፣ የማህበራዊ ከበሬታና ዝናም ማካበቻ እየተደረገ መጥቷል፡፡

እዚህ ላይ ቁልፍ የሰሙሮቢ ገለአሎም ሆኑ የቀወት የጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይት አባላቶቹ የመረጃ ተባባሪዎቼ (አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) በተናጠልም በተተኳሪ የቡድን ውይይትም ወቅት እንዳወሱት በተለይ ቀደም ባለው ዘመን አፋሮች በጦር ሜዳ ያገኙትን እንዲሁም በወረራ ወቅት በመንደሩ የተገኘውን ለጦርነትም ያልተሰለፈውን ወንድ ሁሉ ማለትም በመንደር የተገኘ ህፃን፣ ጎልማሳና አረጋዊ ሁሉ ብልት የመቁረጥ ልማድ ነበራቸው፡፡ ይኸውም የግዳይ ብዛት እና የወንድነት ልክ ማሳያ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አፋር አማራን ሲገድል እና ሲማርክ ብልቱን መቁረጡን ልማድ አድርጎታል፡፡ አማራም ለበቀል ሲል መስለቡን ተያይዞታል፡፡ ዛሬም አልፎ አልፎ ሰለባ የሚፈፀመው ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው አፈ-ታሪክ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ነው የሚተረከው፡፡

አፈ-ታሪክ እያጣቀሱ ከሚናገሩት የመረጃ ተባባሪዎቼ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው መንግሥትን በከፍተኛ ቁጥር እየተጠጉ በውትድርናም ይሁን በሌላ ሙያ ያገለግሉ የነበሩት በቀወቶች እና በሰሙሮቢ ገለአሎዎች አገላለፅ አማሮች ማለትም ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ስለነበሩ፣ ቁጥራቸውም ከአፋሮቹ ይልቅ ስለነበረ፣ ዛሬም ከሚስተዋለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ስንመዝን ምናልባትም አፋሮቹ ሰለባን የጀመሩት የአማራን /ኦርቶዶክስ ክርስቲያን/ ዘር ለመቀነስ በማለም ሳይሆን አይቀርም ብሎ መጠርጠርም ይቻላል፡፡

የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱ እንዳወሱት አፋሮች በሰለባ የሚታወቁትን ያህል አማሮችም መቀባት የሚሉት ባህል አላቸው፡፡ ስለዚህ አማራ ጎፈሬውን በአግር ሽማግሌዎች፣ በጀግኖች እና በቤተ ዘመዱ ፊት ቅቤ የሚቀባው ሰው ከገደለ ብቻ ነው፡፡ "ጉሮ ወሸባ፣ ገዳይ ሲገባ" የሚባልለትም ይህን ሥርዓት ሲያሟላ

ነው፡፡ ካልገደለ በሰው ፊት አይቀባም፡፡ እንዲያውም አንድ የአማራ አባ ወራ ከልጁ እንኳን መረር ያለ ፀብ ሲፈጥር 'እንዳልቀባብህ!' ነው ዛቻውና ማስፈራሪያው፣ ታዲያ ይሄ ምንድነው? ያው እገድልሃለሁ ማለት አይደለምን?" ብለውኛል (የጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) ፡፡

ከዚህ በላይ ስለ ሰለባ ከቀረበው ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የቀወት አማሮች እርስ በርሱ ሲገዳደሉ ሰለባ አይፈፀምም፡፡ አፋሮችም እርስ በርሱ ሲገዳደሉ አይሰላለቡም፡፡ ስለዚህም ሰለባ የሚፈፀመው ድንበርተኞቹ የቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ነዋሪዎች በሚጋጩበት እና በሚገዳደሉበት ወቅት ወቅት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም በአንዱ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ውስጥ የሚፈጠር ግጭት ደም መመላለስን ቢያስከትልም ሰለባን አያስከትልም፡፡ ሰለባ የሚፈፀመው አማራ ከአፋር ወይም ከጅሌ ኦሮሞ ጋር፣ አፋር ከአማራ ወይም ከጅሌ ኦሮሞ ጋር፣ ጅሌ ኦሮሞ ከአማራ ወይም ከአፋር ጋር ሲገዳደሉ ብቻ ነው፡፡

እዚህ ላይ በአፋሮች በኩል ሰለባ የሚፈፀመው የተለያዩ ግቦችን ለማሳካት ቢሆንም በአማሮቹ /ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖቹ/ በኩል ግን ሰለባ የሚታየው እጅግ የወንድነትን ክብር በሚነካ እና እጅግ የከፋ ድርጊት ተደርጎ ነው፡፡ አድራጎቱንም የሚያዩት እጅግ አስነዋሪ እና የዘላለማዊ ፀበኝነት ተምሳሌት አድርገው ነው፡፡ ስለዚህም አማሮች የሚሰልቡት አፋሮች የገደሉትን አማራ ሰልበውት ከሆነ ብቻ ነው አፀፋውን በተመሳሳይ መንገድ ለመመለስ ብቻ ነው፡፡ ደማቸውን መሳ ለመሳ በሆነ መንገድ ለመወጣት፡፡ የሰለቡትንም ብልት ወስደው በአደባባይ አይፎክሩበትም፣ አያሳዩትምም፡፡ አማሮች /ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች/ ገዳይነትን በብልት አቅርቦት አያረጋግጡም፡፡ መግደላቸውን ማረጋጋጫቸው ከቻሉ የጠመንጃቸውን ወይም የጨርቃቸውን ጫፍ የሚችን ደም ማስነካት ነው፡፡ ሌላው ማረጋገጫቸው ደግሞ ምንጊዜም የአካባቢው ሰዎች ከራሳቸው ብሔር ወይም ጎሳ ውጪ የሆነን ሰው ለመግደል ሲያስቡ ለበጎም ለክፉም ብለው አንድ የቅርባቸውን ሰው ስለሚይዙ ያ ሰው ይመሰክራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ግድያ ከተፈፀመ በኋላ ገዳይ የሚችን ጎሳ ሴቶች ካገኘ የተገደለውን ሰው አስከሬን እንዲወስዱ ስለሚነግር የገዳዩን ትክለ ሰውነት በማየት የሚናገሩበት ሁኔታ እንዳለ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ እርስበርሳቸው ሲገዳደሉም ሆነ አፋሮችን ሲገድሉ ዘወትር ብልት

የመስለብ ልማድ የላቸውም (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ አቶ መኮንን በረደድ፣ አቶ ኪዳኔ መከታ፣ አቶ ከበደ መንገሻ 24/01/2004) ፡፡

በሌላ በኩል ግን አፋሮች ከገደሉ በኋላ ለሕይወታቸው የሚያሰጋ ነገር አለመኖሩን ካረጋገጡ ሰልበው ይሄዳሉ፣ ሰለባውንም ለጎሳ አባሎቻቸው ያሳያሉ፡፡ በጨረታና በምሽት በሚደረግ የወጣቶች ጭፈራ ላይም ያሳያሉ፡፡ በጅሌ ኦሮሞዎችም ዘንድ ብዙውን ጊዜ ሰለባ የሚፈፀመው እንደ አፋሮቹ ሁሉ ወንድ ገዳይነትን ለማስመስከር ነው፡፡

እዚህ ላይ በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች መካከል እንደ አንድ የግጭት መንሥዔ የሚታየውን የሰለባ ጉዳይ እና ጥንተ አመጣጥ ሁኔታ ማገናዘብ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም የትናንትን ሁነት ታሪካዊ አመጣጥ ማወቁ፣ የዛሬውን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት፣ የዛሬውንም መረዳቱ ደግሞ በተራው የነገውን ለመተንበይ ያስችለናልና ነው፡፡ ስለዚህም ወደዚያው እንዝለቅ፡፡

በተለይ የሰለባ ተግባር ከዚህ በላይ እንደታየው ከመረጃ ተባባሪዎቼ እንደበት አንድ የግጭት ማባባሻ መሆኑ ተደጋግሞ ተነስቷል፡፡ በቡድን ውይይትም ወቅት እውነትነቱ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህም ሁኔታውን ሰፋ አድርጎ ማየት፣ ታሪካዊ ዳራውንም መቃኘት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሰረቱ ሰለባ በተጎራባቾቹ አፋሮችም ሆነ አማሮች ዘንድ ሥር የሰደደ የወንድነት መግለጫ ሆኖ የቆየ ክስተት ነው፡፡ የመረጃ ተባባሪዎቼ የሰለባን አመጣጥ በውል መናገር እና መግለፅ ባይቻላቸውም አድራጎቱ በጥናቱ ተተኳሪዎች አፋሮችና አማሮች ብቻ ሳይሆን በኩታ ገጠሞቻቸው ከረዩና ጅሌ ኦሮሞዎችም የሚፈፀም የወንድነት ማሳያ፣ መግለጫ፣ ክብርና ግርማ ሞገስ ማግኛና መናኛ በጥቅሉም የወንድነት ስምና ዝና መፍጠሪያ ነው ይላሉ፡፡ በአማሮቹ ዘንድ የገዳይ ስሙ በአደባባይ በክፉ አይነሳም፣ ድንበሩ አይገፋም፣ ቁርሩ አይነካም፣ አጥሩ አይነቀነቅም፣ ሚስቱ አትደፈርም፣ ልጆቹ አይኮረኮሙም፣ ወገኑ አይተነኮስም፡፡ ከብቶቹ እንኳን ድንገት በሰው ሰብል ውስጥ ቢገቡ ጠጠር አይወረወርባቸውም፣ በበትር አይመቱም፣ በጅራፍ አይገረፉም፡፡ በውስ ክስ ይባረራሉ እንጂ፡፡ ገዳይ ባለቤትም እንስሳቱ የሰው ሰብል ስለማጥፋታቸው የሚነገረው እና የሚወቀሰው "አያ እከሌ! እረ ከብቶች ሳት እያሉ ሰብል እያበለሹ ነውና ልጆቹ አዩ እንዷላቸው ብታደርግ" በሚል

የለሆሳስ ቃል ነው። ይህም እንግዲህ "የገዳይ እንኳንስ ሚስቱ ፈረሱም ይከበራል" እንደሚባለው መሆኑ ነው።

አፋሮች ሰለባን የሚፈፅሙት ሚስት ለማግባት እንደ ቅድመ ሁኔታ ስለሚታይ ነው የሚሉ አሉ። አቶ አሎሃ ሃንዶ እንዳጫወቱኝ አንድ ወጣት ሚስት ለማግባትና ተመራጭ ለመሆን፣ ወንድነቱንም ከፍ ለማድረግ አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለትም ሦስትም ፍሬ ቁላዎች ቆርጦ በአንጭት እያንጠለጠለ ለመንደሩና ለጎሳው መሪ ማሳየት ከዚያም በግርዛቱ ወቅት (የዕድሜ ሽግግር ሥርዓት መሆኑ ነው) ማስጨፈር መቻል አለበት። ይህንንም ያደርግ ዘንድ ማህበሩ ይጠብቀዋልና። ስለዚህም ሰለባን መፈፀምና ማሳየት የወንድነት መግለጫ፤ የክብር ማግኛ ነው ይላሉ። የመረጃ ምንጮቹ እንደሚያወሱት የገዳይነት ክብሩ መገለጫም ሚስት መምረጥ ማስቻሉ ወይም ለመመረጥ ክብር ማስገኘቱና ማስጨፈሩ ብቻ አይደለም። የገዳይ ሚስት ካልገደሉት ሴቶች ቅድሚያ ተሰጥቷት ውኃ ትቀዳለች። እንስሳቱም ከሌሎች ካልገደሉ ሰዎች እንስሳት ቅድሚያ አግኝተው ውኃ ይጠጣሉ። ገዳይ በአደባባይ ለመናገር፤ ለመተቸት ሁሉ ቅድሚያ ይሰጠዋል። ልጆቹና ቤተሰቦቹ ይከበራሉ።

በአጠቃላይ የገዳይ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን ሞቱም ቢሆን ይደምቃል። ስለዚህም ሰለባ የእነዚህ ማህበራዊ ክብሮች ሁሉ ማግኛ መንገድ በመሆኑ አቅም ያለው ሁሉ ሊፈፅመው እንደሚነሳሳም መገመት ይቻላል።

አማሮች ሰለባን "መቀቢያ" አድርገው ይቆጥሩታል። መቀቢያ ማለት አንድ አማራ አፋር ወይም ከረዩ ወይም ጅሌ ኦሮሞ ሲገድል ግዳዩን ለማረጋገጥ የግዳይ ሰለባ ይዞ የመመለስ ልማድ አለው። በዚህም መሰረት መግደሉን ለማረጋገጥ የሚችን ብልት ቆርጦ በድጉ ጫፍ ቋጥሮ በማምጣት ለአገር ሽማግሌዎች እና የጎበዝ አለቆች ያሳያል። የገዳይነት ምልክቱን በአደባባይ ካስረገጠ በኋላም ጎፈሬውን ቅቤ ይቀባል። ይኸውም የቅቤ መቀባት ሥርዓት በአካባቢው አነጋገር "መቀባት" በሚል ይታወቃል። በዚህም የተነሳ የአካባቢው አማሮች ከማናቸውም ሰው ጋር ሲጋጩና የፀብ ኃይለ ቃል ሲለዋወጡ "ዋ ! እቀባብሃለሁ"፣ "ነግሬሃለሁ ! እንዳልቀባብህ!" የሚል የዛቻ ብሂል አላቸው። የዚህም ብሂል ምንጩ ከአጎራባቾቻቸው አፋሮች፣ ጅሌዎችና ከረዩዎች ጋር በዘመናት ሂደት ግጭታቸው እና ደም መቃባታቸው ሂደት የፈጠሩት ልማድ ውጤት መሆኑ ነው።

በአጠቃላይ ይህ ሰለባን የመፈፀም ነገር በተለይ ይህ ጥናት በተደረገበትና በድንበርተኝነት በሚኖሩት በአፋር፣ በጅሌ ኦሮሞና በአማራ አካባቢዎች ቀደም ባለው ዘመን በስፋት ዛሬ ዛሬ ደግሞ በውስን መልኩ የሚፈፀም ተግባርነቱን ከመረጃ ተባባሪዎቼ ለመረዳት ችያለሁ። የሰለባ ተግባር ዛሬ በመጠኑም ቢሆን ትንሽ እየቀነሰ እንደመጣ ይነገራል። ይኸውም ሊሆን የቻለውም መስለብን እንደነውር፣ ኢሰብአዊ አድራጎት የሚቆጥሩት ወገኖች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ነው ይባላል። ይህም የሀገረሰባዊ ባህል ለውጥ ባህርይ ነው። ሀገረሰባዊ ባህል እራሱን ይለውጣል። በዚህም ምክንያት ሰለባ በዝቅተኛ ባህልነት ተፈርጆ ሊሆን ይችላል።

ይህን የሰለባ ታሪክ ወደ ኋላም ሄጄ ከአንዳንድ ታሪካዊ ሰነዶች ውስጥ ለመፈለግና ለመቃኘት ሞክሬ ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ ሰለባ የሚባለው ነገር ሁለት ዓይነት መሆኑን ልብ ይሏል። እጅግ የተለመደው እና የታወቀው ሰለባ የጦር ምርኮ የሚባለው ነው።

ሁለተኛው ሰለባ ደግሞ ብልት የሚለውን ቃል በመግደፍ ባጭሩ ሰለባ የሚባለው ነገር ግን የወንድ ልጅ ብልት ቆረጣው ነው። በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ዓይነት ሰለባ እንግዲህ በኢትዮጵያም በሌላውም ዓለም የተለመደው ዓይነት መሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረውን የሰላባ ዓይነት እንመልከት።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ነገሥታት ወይም ገገርዎች አንድን ከግብር መክፈልና እራሱን ከማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ውጪ ለማድረግ፣ አንዳንድ ጊዜም ለመንገሥ ወይም የአካባቢ ሥልጣን ለመያዝ በማሰብ የማፈንገጥ ሙከራ ያደረገ ተቀናቃኝ፣ተዋጊ ጭፍራ ወይም ሠራዊት በብዛት የሰበሰበን መስፍን፣ መኳንንት፣ ባላባት፣ አባ ቆሮ ወርረው እና ዘርፈው የማስገበር ልምድ እንደነበራቸው ግልፅ ነው። በእንዲህ ዓይነቱም ዘመቻ ወቅት የአመፀኛው ወይም የተሸናፊው ግዛት ክፍል ሕዝብ ሚስቶች፣ ልጆች እና ንብረት ሁሉ የአሸናፊው ወገን ሠራዊት የጦር ምርኮ ወይም ሰለባ ይሆኑ ነበር። በተለይም የኃያሉ ወገን ወራዊት በግዳይ ሰለባነት የሚያቀርቡት የገደሉትን ተዋጊ ቆሮ እና ጭፍራ ጭንቅላት በሰይፍ እየቆረጡ በአዋጊዎቻቸው ፊት በማቅረብ እንዲሁም በመፎከር እንደነበር የቀደምት ነገሥታቱ ዜና መዋዕሎች ይተርካሉ (ጌታቸው (1997) እና (2003)፣ ተስፋዬ (2004)፣ ዓለሙ (2005)፣ አምባቸው (2005)።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ቀደምት መንግሥታት ጥፋተኞች ብለው በሚፈርጇቸው ሰዎች ላይ በአደባባይ የተለያዩ አካላዊ የቅጣት ዓይነቶችን ይፈፅሙ

እንደነበር የተለያዩ ሰነዶች ያረጋግጡልናል፡፡ በዚህም መሰረት በከፍተኛ ጥፋተኝነት የተፈረጁ ሰዎችን በጦር መንደልና መግደል፤ ከግድያ በመለስ ደግሞ እግር፣ እጅ ከንፈር እና ምላስ ጡት፣ መቁረጥ፣ ጆሮ መቀንጠብ፣ የቋንጃ ሥር መበጠስ፣ ዓይን ማንቆር፣ አፍንጫ መፎነን፣ በድንጋይ መውገር፣ በጅራፍ መግረፍ የተለመዱ ቅጣቶች እንደነበሩ እንረዳለን (ጌታቸው፣ 2003፡94-215፣ ተስፋዬ፣ 2004፣145፣ 156፣182፣ አምባቸው፣ 2005፡ 220-223) ፡፡

እዚህ ላይ ከተጠቀሱት ቅጣቶች መካክልም ለምሳሌ ጆሮ መቁረጥ በዚህ ጥናት አንድ ጠገግ ቀወት ወረዳ ሕዝብ ዘንድ ዛሬ በተግባር ባይፈፀምም የልጆች ማጫወቻም ማስፈራሪያም ሆኖ ያገለግላል፡፡ የልጆች ማስፈራራትን ጉዳይ ካመጣሁ ዘንድም ቀወት ወረዳ ውስጥ ልጆች በብልት ቆረጣ ቅጣትም ይስፈራራሉ፡፡ የዚህኛውን ጉዳይ ግን ወደ ኋላ አመጣዋለሁ፡፡ ምክንያቱም እዚህ በቀደምት ነገሥታቱ ቅጣት ውስጥ አልተዘረዘረምና፡፡ ወደ ሌሎቹ ቅጣቶች ልመለስ፡፡ በተለይም ደግሞ በጦር ሜዳ የጠላትን አንገት መቁረጥ እና ቸብቸቦ እየከመሩ በአለቃ ፊት መፎከር ዋነኛው የግዳይ ጥሎሽ አቀራረብ ሥርዓት እንደነበርም እንረዳለን፡፡ በተለይ ቸብቸቦ ማለትም የተዋጊ ጠላትን ጭንቅላት እየቆረጡ ግድያ መጣል እና ማቅረብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ ልማድ ሆኖ የቆየ ክስተት ነው (ጌታቸው፣ 1997፡116፣ ተስፋዬ፣ 2004፣ 97፣104)፡፡

የብልት ሰለባ ግን ከእነዚህ ጋር የተጠቀሰበት ሁኔታ የለም፡፡ ነገሥታቱም እላይ ከተዘረዘሩት ውጪ የብልት ሰለባን ስለማካሄዳቸውም የጽሑፍ ታሪክ ማረጋገጫ አላገኘሁም፡፡

ስለዚህም እዚህ ላይ ስለ ብልት ሰለባ አመጣጥ ጥቂት ነገሮችን ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ የቀወት አማሮች ስለ ብልት ሰለባ ሲጠየቁ በነባር ባህላችን የብልት ሰለባ ልማድ አልነበረንም፡፡ ነገር ግን ጎረቤቶቻችን አፋሮች እና ጅሌ ኦሮሞዎች የእኛን ሰዎች በሙትም በቁምም ስለሚሰልቡ አፀፋውን በአምሳያው ወይም በአቻ ደማችንን ለመመለስ እና በቀላችንን ለመወጣት ነው የምንፈፅመው ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል አፋሮችም ስለ ሰለባ ሲጠየቁ ደግሞ እነርሱም ሰለባን የለመዱት ከጅሌ ኦሮሞዎች እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ጥያቄውን ገፋ በማድረግ "መልመዱንስ ለመዳችሁት ግን ጥቅሙ ምንድ ነው?" ሲባሉ ደግሞ የወንድነት፣ የገዳይነት ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው በገደለው ሰው ቁጥር አከባባዊና ባህላዊ ማዕረግ እና ክብር ያገኛል፡፡ የገደለውን ወንድ ብዛት ማረጋገጫውም በገደለ ቁጥር የሚያቀርበው

የተሰለበ ብልት ቁጥር ነው ይላሉ፡፡ ሰለባ ከግዳይ ክብር ማግኘት እና ጀግና ከመሰኘት በላይ ሌላ ተጨማሪ ጥቅም የለውም ወይ ? ሲባሉ ደግሞ ልማዱ ከጥንት ከአባቶቻቸውም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንደሆነ፣ አንዳንድ አባቶቻቸውም ስለ ሁኔታው ሲጠየቁ ቀደምት አባቶቻቸው ሰለባን የጀመሩት የአማራ ቁጥር ብዙ ስለነበረ፣ በወረራ ወቅትም ያጥለቀልቃቸው ስለነበረ፣ ቁጥሩን ለማመናመን እንደ ነበር፣ ታዳጊ አፋሮችም ወንድ መግደልን እንዲለምዱ፣ እንዲኮሩበት እና ወንድነታቸውንም እንዲያሳዩበት እንደነበረ ይተርካሉ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ምንጮቼ በተለይም በቡድን ውይይት ወቅት እንደነገሩኝ አማራ እና አፋር ጥንትም በቁጥር የማይመጣጠኑ ስለነበሩ አፋሮች በአማራ ላይ የማይረሳ ቅጣት አድርገው የወሰዱት ሰለባን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት እንኳንስ በውጊያ ሜዳ ያገኙትን በእረኝነት፣ በካብ ሥር፣ በእቅፍ ያገኙትን ወንድ ሁሉ በመስለብ፣ የተሰለቡት ሁሉ መቀጣጫ እንዲሆኑ፣ እርባታቸውም እንዲቀንስ እና አማራ ዳግመኛ አፋሮችን እንዳይተናኮል ለማድረግ ይጥሩ እንደነበር ያወሳሉ፡፡ ይሁንና የሰለባው ልማድ እያደር በአፋሮችም ዘንድ የወንድነት ማሳያ፣ የተፈላጊነት መጨመሪያ በጥቅሉም የማህበራዊ፣ ክብር ማግኛ እየሆነ እንደመጣ ያወሳሉ፡፡

ስለዚህም አፋሮች የብልት ሰለባን በድንበርተኞቻቸው የቀወት አማሮች /በጥናቱ ተተኳሪዎች አባባል ኦርቶዶክስ ክርስቲያን/ ላይ የሚፈፅሙት ብዛትን ለመቀነስ ሲሉ በጦርነት ሲመቷቸው የነበሩትን አካባቢዎችን ወንዶች ህፃናት እና ታዳጊዎች የመራቢያ አካላትን መጎንደልን እንደ አማራጭ ሳይወስዱት የቀሩ አይመስልም፡፡ ይህም ሁኔታ በሂደት ታዲያ የሞተውንም ያረጀ ያፈጀውንም ወደ መስለብ እና የግዳይ ቁጥርን ወደ ማበራከቻነት በዚያም ክብር ወደ ማግኘት ሳያመራ እንዳልቀረም መገመት ይቻላል፡

በአንፃሩ የቀወት ወረዳ አማሮች የብልት ሰለባን ከጎረቤቶቻቸው ሳይለምዱት እንዳልቀሩ እና ለመገዳደሪያነትም ሳይጠቀሙበት እንዳልቀሩ መረዳት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል በቀወት አማሮች ዘንድ ከቀደምት መንግሥታት ቅጣት ዓይነቶች አንዱ የሆነው ጆሮ መቁረጥ ዛሬም ቀወት ውስጥ የልጆች ማስፈራሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል ጠቁሚያለሁ፡፡ ሌላ የልጆች ማስፈራሪያ እንዳለም ፍንጭ ሰጥቼ ኋላ ላይ እመለስበታለሁ ብዬ ነበር፡፡ ይኸውም የልጆች ማስፈራሪያ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው ምንጩ በእርግጠኝነት በውል ያልተረጋገጠው የብልት ቆረጣ ነው፡፡ ቀወቶች አንድ ሕፃን የጠየቀውን ነገር ማቅረብ ሲያዳግታቸው እና ሳይቻላቸው ሲቀር

ወይም ችኮ ሆኖ ሲያናድዳቸው አለያም እንደ ቀልድ ሲናገሩ "ዋ! እምቢ ካልህ፣ አላርፍ ካልህ ሙርጥን /መሸኛህን፣ ብልትህን/፣ መሸኛህን ነው የምመነድብልህ፣ የምቆርጥልህ" ሲሉም ይደመጣሉ። እናም ይህን ያጤነ ሰው እንዲህ መሰሉ አድራጎት በክርስቲያን ገገሮቹ መንግሥታት ዘንድ ከሌለ ቀወቶች ይህን ልማድ ከየት አመጡት? ወይም እንዴት ተከሉት? ብሎ እንዲያስብ የሚገፋፋው ይመስለኛል። ምክንያቱም ቀወቶች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኑ መንግሥት አካል ወይም ኃይል ወይም ተቀፅላዎች ተደርገው ይታያሉና። እዚህ ላይ ታዲያ የባህል ለመዳ ሁኔታንም ስንመለከት አንድ ባህል በመጀመሪያ በታችኛው ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ እየተለመደ ሳለ፤ ያ ቡድን ወይም ኅብረተሰብ በአንዳች አጋጣሚ ሥልጣን ለመያዝ ሲበቃ ልማዱን ሕዝባዊ የማድረግ እና የማስለመድ፣ የመትከል እና የማህዘብ አጋጣሚ እንደሚያገኝ የታመነነቱን ሳንዘነጋ ነው። በሌላ በኩል ግን ማህረሰቦቹ በእውኑ ዓለም በገሃድ የማያደርጉትን፣ ሐራም ወይም ነውር ተግባር ተደርጎ የተፈረጀን ተግባር ወይም አድራጎት በዘዴ ለመተንፈስ በልጆች ማስፈራሪያ መልክ እየተናገሩም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በልዩ ልዩ ምክንያት የተነወሩ ነገሮች በፎክሎር ማለትም በሥነቃል፣ በሀገረሰባዊ እምነት እና ወግ ልማድ፣ ትውን ጥበባት እና ቁሳቁስ አማካኝነት የሚገለፁበት እና የሚተነፈሱበት አጋጣሚ አለና ነው።

ከላይ እንደተገለፀው አማሮች እና አፋሮች የብልት ሰለባ ተግባር የእኛ ነባር ባህል አይደለም ማለታቸውን፣ እንዲያውም አማሮቹ ከአፋሮች እና ከጅሌዎች መልመዳቸውን፣ አፋሮቹም ደግሞ ከጅሌዎች ነው የለመድነው ማለታቸውን ተመልክተናል። በዚህም እርግጡን ለመናገር እንዳልተቻለ ሁሉ መዝነናል። ይሁንና በጅሌዎች የተሳበበውን የብልት ሰለባ ጥንተ አመጣጥ እውነትነት ከጅሌዎች አንደበት ሰምቶ ማረጋገጥ አልተቻለም። ምክንያቱም እነርሱ የጥናቱ ተካታቾች አይደሉም። ነገረ ግን ኦሮሞዎች በጥንቱ ዘመን ሚስት የሚያገቡት፣ ውሽማም የሚይዙት ሰው ከገደሉ እና ስለ ግዳያቸውም ካስዘፈኑ በኋላ እንደነበር የሚያወሳ ተረክ መኖሩን ተመልክቻለሁ (ጌታቸው 1997፡178-182) ።

በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ያለውን ግጭት የሚያባብሰው ሌላው ምክንያት ብቀላ ነው። ግራዝማች ኢሰገሌ (08/01/2002) ስለ ብቀላ ሁኔታም ሲያወሱ አንድ አፋር በአንድ አማራ ከተገደለ የሚቹ አፋር ጎሳ አባላት ያገኙትን አንድ አማራ ወይም ከቀናቸው ከዚያ በላይ በመግደል ደማቸውን ይመልሳሉ። አንድ አማራ በአንድ

አፋር ከተገደለም የሚቹ ዘመዶች ወይም አንድ አማራ በአፋር መገደሉን የሰሙ አማሮች ተነስተው ከቻሉ የገዳዩን ጎሳ ለይተው ከጎሳው አባላት ይገድላሉ፣ ካልቻሉም አንድ አፋር በመግደል ደማቸውን ይገዳደራሉ፡፡ በዚህ ዓይነቱ ግዳይ ወቅት በአንዱ ወገን ሰለባም ተፈፅሞ ከሆነ ደግሞ ሌላኛውም ወገን በዕኩሌታ፣ መሳ ለመሳ ወይም በአቻዊነት አፀፋውን ለመመለስ ይሰልባል፡፡ ግራዝማች እንደሚሉት እንዲህ ዓይነቱ የአማራ እና የአፋር መገዳደልም ሁኔታ በሁለቱም ወገን ጀግና ያሰኛል፡፡ የግዳይ ቁጥሩ በጨመረ ቁጥርም የገዳይ፣ የገዳይ ቤተሰብ እና ወገን ክብሩ ከፍ ከፍ ይላል፡፡ በአማራም ሆነ በአፋር በኩል ገዳይ ከሌሎች የበለጠ ይከበራልና ይላሉ፡፡

ለምሳሌም በአፋር ግመል የሚባርክ ገዳይ ነው፡፡ መንገድ የሚመራ፣ በማዕድ ላይ ቀድሞ የሚቀመጥ፣ በሸንጎ ቀድሞ ሐሳብ የሚሰነዝር እና የሚተች ገዳይ ነው፡፡ በአማራም በኩል ገዳይ ሳይፎክር የሚፎክር የለም፣ ገዳይ ሳይቀመጥ በገበታ ዙሪያ የሚቀመጥ የለም፣ ገዳይ ሳይቀደም ከፊቱ የሚሄድ የለም፣ ስለ ፀጥታም ጉዳይ ገዳይ አስተያየት ሳይሰጥ ሌላ አይሰጥም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአማራ ባህል ፀጉሩን ለማጎፈር እንኳ መብት ያለው ገዳይ ነው፡፡ አለዚያ "ሳይገድሉ ጎፈሬ፤ ሳያረጋግጡ ወሬ" እየተባለ ይመሰልበታል፡፡ ስለዚህም ገዳይነት ክብር ነው ይላሉ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ፡፡ በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ስለ ገዳይነት ያለው አስተሳሰብም ዓይን ለዓይን፣ ጥርስ ለጥርስ ዓይነት የሚመስል መሆኑን ከመረጃ ተባባሪዬ ገለፃ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም በኩል ደምን መመለስ እና ጥቃትን መወጣት ማህበራዊ ክብርን ያጎናፅፋል፣ ስመ-ጥርም ያደርጋል፡፡ በአንፃሩ ደምን አለመመለስ፣ ጥቃትንም አለመወጣት ደግሞ ፈሪ፣ ቦቅቧቃ፣ ልበ-ቢስ፣ ወኔ-ቢስ፣ መንደር መቺ፣ ሴት አውል፣ አውደልዳይ፣ ሆድ-አደር፣ ሆዳም፣ ዘር አሰዳቢ፣ ማፈሪያ ወዘተ ያሰኛል፡፡ ያስዘልፋል፣ ያስዋርዳልም (አቶ ከተማ አይሻር 15/01/2003) እና ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002)፡፡ እኚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ እንዳጫወቱኝ አቅራሪ እና ገጣሚም እንዲህ ዓይነቱን ሰው እያራከሰ፣ እካብ የማይገባ ድንጋይ አድርጎ በየድግስ ቤቱ ይገጥምበታል፡፡

ለምሳሌም ሴት ወዳዱን፣ አምባ መቺውን፣ ቀለዋጩን እና ወኔ-ቢሱን፡-

ይወለድና ጥርሰ ነጫጭ፣
የጋለሞታ ከንፈር መጣጭ፡፡
ይወለድና ጫማው ሰፋፊ፣

ሆኖ ይቀራል መንደር ለፋፊ*። /መንደር ለመንደር ሴት ሲያማግጥ፣ ወሬ ሲያመላልስ የሚውል ሙያ ቢስ ለማለት/። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቶቹ ግጥሞች በቀወት ወረዳ ብቻ የሚደመጡ አይደሉም። በሌላውም የአማራ ክልል የሚደመጡ ናቸው። ስለዚህም ከግጥሞቹ መካከል አንዳንዶቹ አካባቢያዊ ውሱንነት ሌሎቹ ደግሞ ሕዝባዊነት ያላቸው መሆናቸውም ይታያል። የሚቀጥለውም ግጥም ታዲያ እንደላይኛው ሁሉ በብዙ ቦታ ከሚደመጡት እና ቀወቶችም ከሚጋሩት አንዱ ነው።

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ፣
ወደ ዳገት በሉት ሳር ይብላ እንደ በሬ።
ስፈር ቀለብ ስፈር ዘንጋዳ፣
ግዳይ ለሌለው ስፈር ዘንጋዳ፣
ቢኖር አይጠቅም ቢሞት አይጎዳ።

በልማዱ ወንድ ልጅ የወንዶች ሁሉ ወንድ፣ የወንዶች ቁና ወይም መስፈሪያ ተደርጎ የሚቆጠረው ኃይለኛ አራሽ፣ አግተምታሚ፣ ተደባዳቢ፣ ተኳሽ፣ ገዳይ ሲሆን ነው። ከዚህ ግብሩ ሲወርድ የሚፈረጀው ከእንስሳቱ ክፍል ነው። በሁለተኛውም ስንኝ ውስጥ የምናገኘው መልዕክት ወንድነት ወይም ጀግንነት የሌለው ሰው የአባቱን አገር አያስከብርም፣ ለአገር፣ ለወገን መከታ እና መመኪያ፣ መታፈሪያ አይሆንም እንደ ማለት ነው። በፈሪ ላይ እንደሚሸለልበት ሁሉ ይመስሉበታልም። እንዲህ። ምድር ሲያረጅ መጭ ያበቅላል፤ አገር ሲያረጅ ወንድ /ጀግና/ ይጠፋል (አቶ ከተማ አይሻር፣ 15/01/2003) ።

ቀደም ብዬ ከላይ የጠቀስኳቸው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ በነገሩኝ እንዲሁም ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎችም ባረጋገጡልኝ መሰረት ሌላው የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ነዋሪዎች የግጭት መንሥዔ "ጥንት መሬቱ የኛ ነው፣ የኛ ነው" በሚል ቅሬታ እና ይገባኛል ባይነት በዚህም የተነሳ መጋፋት መኖሩ ነው። በዚህም ረገድ በየጊዜው የሚከሰተውን ግጭት ሁኔታ ግራዝማች ኢሰገሌ በአንድ ምሳሌ አስረድተውኛል።

በዐፄ ምኒልክ፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ፣ በደርግ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ዘመነ መንግሥታት አፋሮች የሚኖሩበት እና መስቀል በር በመባል የሚታወቅ ሥፍራ አለ። በአካባቢው አማሮች አይኖሩም። ነገር ግን አማሮቹ ቦታው የኛ ነው አፋር በምን ምክንያት ነው "መስቀል በር" የሚል አካባቢ

የሚኖረው ስለዚህ ቦታው የአፋር አይደለም የሚል እምነት ስላላቸው እስከዚያ ድረስ የኛ ነው በሚል እዚያ ባደርሱም ወደ ሰሙሮቢ ገለአሎ ይዞታ በቡድን እየገቡ ያርሳሉ፣ ይሰፍራሉም።

በሌላ በኩል አፋሮች ማፉድ ድረስ የኛ ነው። ማፉድ የሚባለው ሥፍራ ማህፉዝ የሚባለው የአፋር ጦር መሪ ከአማሮች በተለይም ከአፄ ልብነ ድንግል ሠራዊት ጋር ሲዋጋ የሞተበት ሥፍራ ነው። ስለዚህም የጥንት ይዞታችን ነበር ይላሉ። ይሁንና የቀወት አረጋውያን ደግሞ የሚተርኩት ማህፉዝ የሚባለው ዝርያው ከቱርክ የሆነ፣ በየመን በኩል አድርጎ ወደ ዘይላ  የተሻገረ፣ የይፋት፣ የአፋር እና የምስራቅ ኢትዮጵያ እስላሞች አስተባባሪ እና አሳማጭ፣ አባ ቆሮ ወይም መሪ ሆኖ ከክርስቲያን መንግሥት ሠራዊት ጋር በየጊዜው ውጊያ እየከፈተ ሲያስቸግር የነበረ፣ ኋላም ከላይ በተገለፀው መሰረት ፍፃሜውን ያገኘ ሰው አድርገው ነው።

ጽሑፍ ታሪኩ ደግሞ ማህፉዝ ከሦስት ተከታታይ አፄዎች ማለትም ከአፄ እስክንድር፣ አፄ ናኦድ እና አፄ ልብነ ድንግል ጋር በአልገብርም ባይነት ሞግዶ እየተዋጋ የቆየ፣ በመጨረሻም ዛሬ በስሙ በሚጠራው ሥፍራ ከአፄ ልብነ ድንግል ሠራዊት ጋር ሲዋጋ አባ ገብረ እንድርያስ በተባሉ ዲዳ መነኩሴ (ዲዳነታቸው በንጉሱ ምላሳቸውን ስለተመነደቡ ነው ይባላል) የጦር አቢጋዝ አንገቱን በጎራዴ ተቀልቶ የሞተ ሰው መሆኑን ይገልፃል (ላጽሶ 1982፡122)። ወደ መጀመሪያ ጉዳዬ ልመለስ።

ቀወቶችም ሆኑ ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚያነሷቸው የነባር ባለቤትነት ጥያቄዎች ብዙ እንደሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችም አረጋግጠውልኛል። በዚሁም መሰረት በተለይ የአዳሂሚራ ጎሳዎች በጀቡሃና አዋዲ ጅረቶች መካከል ሰፍረው የሚኖሩ በመሆናቸው አካባቢውን ነባር ይዞታቸው አድርገው ሲቆጥሩ በአንፃሩ ቀወቶች ደግሞ አፋሮቹ ቦታውን የያዙት በወረራ ነው የሚል እምነት አላቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ዛሬ የአማሮች በኩሬ በረት፣ ሰፊ በረት፣ ጉልት በረት እና ዓባይ አጥር፣ ጀጎል አካባቢ መገኘት በአፋሮች ዘንድ ነባር ይዞታቸው በወረራ እንደተያዘባቸው ይቆጥራሉ። እንደ አንዳንዶቹ የሰሙሮቢ ገለአሎ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ አገላለፅም  አማሮች ወደ ታች እየወረዱ አንዳንድ ሥፍራዎችን የያዙት በመንግሥት በተለይም በአፄ ኃይለሥላሴ እና በደርግ ድጋፍ ማለትም በቅደም ተከተል ልማት እና ሰፈራ በሚል ፕሮግራም ሰበብ ነው።

ከተተኳሪ ቡድን አባላቱ ውይይት እንደተረዳሁት ዛሬ አፋሮች ከሚኖሩባቸው ቀበሌዎችም መካከል አንዳንድ ጎጦች የእኛ ናቸው ብለው የሚከነከኑ የቀወት ወረዳ ነዋሪዎች ስላሉ መሬታቸው እንደተወሰደ አድርገው የቁጭት ስሞታዎች ሲያሰሙ ይደመጣሉ፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ወቅት ባላምባራስ አይዳሂስ እንዳብራሩት በዓባይ አጥር በኩልም ሆነ በሌሎች አካባቢ ያሉ አንዳንድ ጎጦች ነባር ባለቤት አፋር ነው፤ አማራ ነው የሚለው ጉዳይ አከራካሪነቱ ግልፅ ቢሆንም አባባሉ ከሁለት ወይም ሦስት ትውልድ አያልፍም፡፡ ምክንያቱም ከዚያ በፊት የነበረውን ሁኔታ ከአፈ ታሪኩ ውጪ የሆነውን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ የለም፡፡ አፋር ምንጊዜም እንደተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ስለዚህ አጥርቶ የሚቆጥረው የጎሳ ሐረጉን እንጂ የሰፈረበትን ምድር ባለቤት አይደለም፡፡ አፋር በመሰረቱ የሚገኝበት ሥፍራ በረሃ ስለሆነ፣ ውኃና ሣር ለማግኘት በኅብረት የሚነቃነቅ በመሆኑ ግመሎቹ መሄድ እስከቻሉበት ድረስ እየሄደ ይኖራል እንጂ አንድ መሬት ላይ አይረጋም፡፡ በመሬት ይዞታው ላይ ካልተገፋ በስተቀር ለብዙ ትውልዶች ረግቶ የሚቆየው አማራው /ክርስቲያኑ/ ነው፡፡

በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ላይ ከተካፈሉት ቀወት ወረዳን ከወከሉት አንዱ አቶ ሰጥ አርጌ በበኩላቸው ጥንት መሬቱ የአማራ ነበር እየተባለ እንደሚነገር፣ ነገር ግን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ደግሞ ብዙ ሰው ያልሰፈረበት ጠፍ መሬት ስለነበር አማሮች በቡድን እየተደራጁ እና ደኑን እየመነጠሩ፣ አፋሮቹም ሲመጡባቸው እየመከቱ እንደሰፈሩበት ደግሞም በጥንት ጊዜ በጎሳው የሚጠራው ሰው እንጂ መሬቱ እንዳልነበር፣ መሬቱ ምንጊዜም የኃይለኞች እንደነበር አውስተዋል፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) እና አቶ አሎሃ ሃንዶ (14/09/2002) ደግሞ ከአባቶቻችንም ስንሰማው እንደኖርነው እያሉ እንደተናገሩት ብዙ መገፋፋት እንደነበር በዚህም የተነሳ የአማራ እና አፋር ድንበሩ አንድ ጊዜ ወደ ላይ፤ ሌላ ጊዜ ወደ ታች ሲል እንደኖረ እና ዛሬ መስቀል በር የሚባለው አካባቢም የአማራ ይዞታ ነው፣ ማፉድ የአፋር ነበር የሚለው አከራካሪ እንደሆነ፣ ነገር ግን ታሪኩን ትቶ ይዞ መገኘት በሚለው እንኳን ሁኔታው ቢታይ ሁለታችንም የምንኖርንበት ስለሆነ የሁለታችንም ነው፡፡ ስለዚህ ተስማምተን እንኑር ማለት እና መስማማቱ እንደሚሻል አውስተዋል፡፡

ከሁለቱም ወገን ከተውጣጡት የተተኳሪ ቡድን ውይይት አአባላት አስተያየት መረዳት እንደሚቻለውም አንዳንድ የሁለቱ ወረዳዎች ድንበር አካባቢ ከአማራም ሆነ ከአፋር ጉልበት ያለው ሁሉ እየገባ የሚኖርበት ነው፡፡

እዚህ ላይ አማሮቹ ወደ ታች፤ አፋሮቹ ወደ ላይ ነባር ይዞታ ነበረን፣ ተቀምተናል ወዘተ  የሚሉት በቃል ታሪክ ወይም ተረክ ላይ በመመስረት መሆኑንም ያጤኗል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱ እንደሚሉት በተለይ በጥንቱ ዘመን አማራ እና አፋር በውኃም፣ በግጦሽ ሣርም፣ በገበያም፣ በቆየ ቂም በቀልም፣ እንዲሁም ከሜዳ ተነስቶ አንዱ ወገን ሌላውን ሲተናኮለው ጎሳ ከነመሪው፣ ምንዝር ከነጌታው እየተንቀሳቀስ ይዋጋ ነበር፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት አፋሮች ወደ ቀወት ምድር ዘልቀው በመግባታቸው እና ነዋሪችን በማፈናቀላቸው፣ አብያተ ክርስቲያነትንም በማቃጠላቸው፣ ነዋሪዎችም በዚሁ ግጭት በመሞታቸው የይፋት አማሮች ተጠራርተው አቅም ያለው ሁሉ እንዲዋጋ እና ደሙን እንዲበቀል ከተማማሉ በኋላ በማለዳ ለመውረር የሌሊት ጉዞ ሲደረግ፣ እና ከተሳካ የደም ምላሳ በኋላ እንዲህ እንደሚከተለው ተሸልሎ ነበር ይባላል፡፡ የሚቀጥለው ግጥም ደግሞ ቃላዊ-ቀመራዊነት ይሁን ወይም በሥራቱ መሆኑን ማረጋገጥ ባይቻልም አካባቢያዊ አሻራ ይታይበታል፡፡

እንደዚህ ጦር ሰርተን፣
ሰልፉን አሳምረን፣
ተጉዘን ተጉዘን፣
የት ነው ማረፊያችን፣
ያልበቃን እንደሆን፣
አፋር ለምሳችን፡፡

በዚህ መንፈስ ወደ አፋር ተዘምቶ፣ ደሙ በደም በደም፣ ንብረቱም በንብረት፣ ዓይነቱ በዓይነቱ ተመልሶ መልስ ሲደረግም፡-

ወርደን ነበር አፋር መርጠን ተመራርጠን፣
ተመልሰን መጣን አመራሮ ቆርጠን፡፡

ይሁንና ዛሬ ግን እንደዚያ ዓይነቱ የደቦ ጦርነት ቶሎ ቶሎ እንደማያጋጥም፣ ግጭቱ ግን ከጥንት የወረደ በመሆኑ ምንጊዜም እንዳለ እና ይሄም በየጊዜው በሚከሰት የተናጠል ግጭት እና መገዳደልም እንደሚታይ ይወሳል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ የመረጃ ተባባሪዎቼ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለውም በሁለቱም ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ “የአማራነት” እና “የእስላምነት” አሻራ ያላቸው የሚመስሉ የቦታ ስሞች ይገኛሉ፡፡ ለአብነትም በቀወት

ውስጥ ማፉድ እና ጀጎል፣ በሰሙሮቢ ውስጥ መስቀል በር የሚሉ ሥያሜዎች አሉ። ከእነዚህ ስሞች በመነሳት ሁለቱ ሕዝቦች ወደ ላይም ወደ ታችም በአቻዊነት ሲነቃነቁ መኖራቸውን እና መገፋፋትም የነበረ መሆኑን በዚህም ምክንያት የባህል መነባበር መከሰቱን እና እስከ ዛሬም ድረስ መዝለቁን ነው።

ከተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ገለፃ እንደተረዳሁት ሌላው የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት የሚያባብሰው ሁለቱ ሕዝቦች ከጥንት ጀምሮ በደመኛነት መተያየታቸው እና ስምምነትም ያልነበራቸው፣ ዛሬም የሌላቸው መሆናቸው ነው። ምክንያቱም የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ ግጭቱ ምንጊዜም እንዳለ መሆኑን ነገር ግን ከጥንቱ የሚለየው ቀደም ባለው ዘመን አፋርና አማራ የሚወራረሩት በፈረስ ስለነበር ነው። ከውይይቱ እንደተረዳሁት የፈረስ ወረራ አማራ ወይም አፋር ከተገደለ፣ እንስሳቶች በአንድ አፋር ወይም አማራ ከተዘረፉ በጅምላ የሚወራረሩበት የለየለት ጦርነት ነበር። በፈረስ መውረር ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ እየቀረ መጥቷል። የፈረሰኛ ወረራም ሊቀር የቻለው የወቅቱ የመንግሥት ባላሥልጣናት፣ ባላባቶችና የጎሳ መሪዎች ባደረጉት ብርቱ ጥረት ነው።

የፈረስ ወረራ የቀረውም በተለይ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከ1933 ዓ.ም. በኋላ ከፍ ያለ ጥቃት ሲፈፀም ለንጉሡ ነገሥቱ ከአካባቢው አማሮችም አፋሮችም በኩል አቤቱታ ይቀርብላቸው ስለነበር ግጭቱ የሚቆምበት ሁኔታ እንዲፈጠር ቀድሞ መንዝና ይፋት ይባል ለነበረው አውራጃ ተከታታይ ገገርዎች ትዕዛዝ ተላልፎላቸው ስለነበር፣ አወራጃ ገገርዎቹም የአፋር እና የአማራ ባላባቶችን አቀራርበው በማነጋገር ግጭቱ ስለሚቆምበት ሁኔታ ምክክር ስለተደረገ፣ ለጎሳ መሪዎቹ እና ለባላባቶቹም አደራ ስለተጣለባቸው፣ እነርሱም የየወገናቸውን ሕዝብ በመምከራቸው እና በመቆጣጠራቸው አንዳንድ ጊዜም መንግሥት ፀበ አጫሪ ነው በሚባለው ወገን ላይ ነጭ ለባሽ እያዘመተ ይቀጣ ስለነበር ነው።

ሌሎችም አካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ብዙ የአፋር ጎሳ መሪዎች እና አፋሮች አማሮችን እንደ ጠላት ያያሉ። እንደ ምክንያትም የሚያነሱት ሱልጣኖቻችንን እና አሚሮቻችንን እየወጉ ሲያስገብሩ ሲገድሉ፣ ሕዝባችንን እና እንስሳቶቻችንን የጦር ምርኮ እያደረጉ ሲወስዱ ኖረዋል የሚል ምሬት አላቸው። ይህንንም በየጨረቃ እና እሳት ዳር ጨዋታው፣ በየጎሳ ስብሰባው፣ በየግጭት አጋጣሚው ላይ ሁሉ ያወራሉ። ስለዚህም በአማሮች ላይ ሥር የሰደደ ጥላቻ አለ። በአማራም በኩል ቢሆን ዛሬ ዛሬ

እየቀረ መጣ እንጂ አፋርን አፋር ብለው እንኳን ለመጥራት አይፈልጉም፣ ብዙ ስም ነው የሚሰጡት ይላሉ። የስም ጉዳይ ከተነሳ ዘንድ እዚህ ልፅፈው ባይገባም አፋሮችም ለአማሮች ሌላ የቤት ውስጥ *ሥም* እንዳላቸው ሰምቻለሁ። በዚህም የተነሳ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ተጋጪነት "አማራ አማራ ነው፣ አፋር አፋር ነው" እየተባለ እንደሚገለፅ ተረድቻለሁ።

ከሁለቱም ወረዳዎች ለተውጣጡት እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ ለተሳተፉት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼም በአማሮች እና በአፋሮች መካከል በዚህ ዘመን ግጭት እና ግድያ የሚከሰትባቸውን ሁኔታዎች ባወሱበት ወቅት "አማራ  እና እስላም ነን" የሚለው ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የልዩነት እና የፀበኝነት መግለጫ ዛሬም እንዳለ አንስተዋል። አንደኛው ሌላኛውን እንደ አደን እንስሳ የሚገድለውም ዘወትር በሁለቱ ሰዎች መካከል በተጨባጭ በመካከላቸው የጥቅም ግጭት ኖሮ ሳይሆን መገዳደል ልማድ ስለሆነ መሆኑን አውስተዋል። ይሄ ልማድ የተባለውም ከታሪክ-ጠቃሽ፣ ቂመኝነት እና ፀበኝነት የመነጨ መሆኑን እንደሚከተለው አንስተዋል። በዚህም መሰረት አማሮቹ "ጥንትም ቢሆን አማራ እና እስላም ሰላም አልነበረውም፣ ዛሬም ቢሆን ያው ነው። ከጥንቱም ቢሆን አገራችን ስትደፈር የነበረችው በእስላም ነው፣ አፋሮች ይህን እና ያን አድርገውን ነበር" እንደሚሉ አፋሮቹም በፊናቸው  "ጥንትም ቢሆን አፋር /እስላም/ እና አማራ /ኦርቶዶክስ ክርስቲያን/ ሰላም አልነበረውም፣ የዛሬውም ፀብ የያኔው ቅጥያ ነው። አማሮች /ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች/ ይህን እና ያን አድርገውን ነበር" ወዘተ የሚል ወሬ እንደሚዘወተር ይተርካሉ  (የጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንደ 27/01/2004) ።

በአጠቃላይ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደነገሩኝ ይህ በገፀ ምድር ሀብት፣ በታሪካዊ ፀበኝነት ተረክ እና በሌሎችም ኢ-ተጨባጭ ምክንያቶች የሚቀሰቀሰው የአማራ እና የአፋር ግጭት የሚበረታባቸው ወቅቶችም እንዳሉ ይነገራል። የተናጠልም ሆነ የጋራ የተተኳሪ ቡድኑ አባላት እንዳመለከቱት ግጭቱ ባመዛኙ በያመቱ በግንቦት እና ሰኔ፣ መስከረም እንዲሁም በጥጋብ እና በችግር ዘመንም የሚያጋጥም እና የሚመላለስ ክስተት ነው። የየዓመቱም ግጭት የሚለያየው በሚያስከትለው የሰው ሕይወት እና

የንብረት ውድመት ልዩነት መጠን ብቻ ነው፡፡ በአጭሩም ግጭቱ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ዓመል ወይም ባህርይ፣ ልማድ እና ባህል ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡

በሌላ በኩል በተለያዩ ወቅት የተከሰተው ግጭት ያስከተለውን ሰብአዊ እና ቁሳዊ ኪሣራ ሁኔታ የሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች ወገኖች በየአጋጣሚው በተሰባሰቡበት፣ ድግስ ባለበት፣ ወጣቶች ስለ ወላጆቻቸው፣ አያት፣ ቅድመ አያቶቻቸው እና ዘመዶቻቸው ያለፈ ሕይወት መስማት በሚፈልጉበት የምሽት ወግ እና ጨዋታ ላይ ሁሉ የጥቃት፣ የበቀል፣ የሰለባ ነገር እንደሚያነሱ እንዲሁም ደግሞ "አባቶች በጨረቃ የተጫወቱትን ልጆች በፀሐይ ያወሩታል" እንዲሉ ታዳጊዎቹም የግጭቱን ተረክ እየተጋቱ ስለሚያድጉ፣ አቅም ሲያገኙም በግጭቱ ውስጥ ስለሚገቡ በመሆኑ እንደሆነ ነው የሚወሳው፡፡ በዚህ መልኩ ስለ ጥቃት፣ ሰለባና ግድያ እየሰማ የሚያድግ ልጅ ሲጎለምስ ሰበብ ፈልጎ እንደገና ሕይወትና ንብረት ለማጥፋት ይነሳሳል፡፡ ስለዚህም ነገሩ እንዲህ እያለ መቋጫ ሳኖረው ይቀራል ማለት ነው ይላሉ (የጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) ፡፡

ከሁለቱም ወረዳዎች ለተውጣጡት እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ለተሳተፉት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ "አማራ እና እስላም ነን" ወይም "አማራ አማራ ነው፣ አፋር አፋር ነው" የሚለውን አባባል ዘርዘር አድርገው እንዲያስረዱኝ አንስቼባቸው ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ  አንዳንዶቹ ዛሬ እኔ እንዳነሳሁባቸው ሁሉ እነርሱም በልጅነታቸው እንደኔው ለአረጋውያን ሁሉ  ያነሱ እንደነበር ከአስታወሱ በኋላ አባባሉን ወደ ማብራራት ገብተዋል፡፡

ቁልፍ የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ ተባባሪዎቼ (የጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይት፡- አቶ ሰጥ አርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ መሐመድ አደን ጋለሎ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) እንዳብራሩልኝ "አማራ አማራ ነው" ማለት "አማራ ክርስቲያን ነው፡፡ ክርስቲያን ደግሞ ከጥንትም ጠላት ነው፣ የጥንት ሱልጣኖች እና አሚሮችንም ሲያጠፋ የኖረ ነው፡፡ ስለዚህም ጠላት ነው ማለት ነው፡፡ "አፋር አፋር ነው" ማለትም አፋር እራሱን ልዩና ታላቅ ሕዝብ  አድርጎ እንደሚቆጥር በዚሁም መሰረት "አላህና አፋር ከሁሉም በላይ ናቸው" እያለ እራሱን እንደሚገልፅ፣ በራሱም ላይ በተለያዩ ዘመን ከአማሮች ጋራ ፍፃሜ የሌለው የጥፋት ጦርነት ቢካሄድበትም ክብሩን እና መሬቱን

አሳልፎ ያልሰጠ፣ ለጦርነትም የማይንበረከክ ሕዝብነቱን፣ በአጠቃላይም ለጠላት የማይመች እርስበርሱ ግን የማይጨካከን ሕዝብነቱን ለመግለፅ እንደሆነ አውስተውልኛል፡፡ ይህንንም የቁልፍ መረጃዎቼን አባባል የሚያጠናክር የአፋሮች ምሳሌ መኖሩን ሰምቻለሁ፡፡ "አፋሮች እርስበርሳቸው ሲጣሉ ኩበት፤ ከሌሎች ሲጣሉ ድንጋይ ይወራወራሉ" የሚል፡፡

ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ሁሉ እንደተረዳሁት ዛሬ በቀወት እና በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል የሚታየው ፀበኝነት እና መገዳደል የመነጨው ያለው ከአጠቃላዩ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እና ሙስሊም አስተሳሰብ ጋር ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይኸውም ሁኔታ በሥነቃል አማካንት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተነገረ እና እየተላለፈ በመሆኑ በየጊዜውም ድንበር ላይ ግጭት እያስከተለ እና እያተነኳኮሰ ቀጥኋል ማለት ይቻላል፡፡

በተለይ ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተውጣጡት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ፣ አቶ አህመድ ኢብራሂም፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ሐሚድ መሀመድ 19/01/2004) እንዳወሱት ጥንታዊ የአፋር ሱልጣኖችን እና አሚሮችን ለማስገበር የአማራ ነገሥታት በአፋር ላይ ሲዘምቱ ኖረዋል፡፡ የአካባቢውም አፋሮች ዘወትር ከባድ እና የማያቋርጥ ጦርነት የሚመጣው ከበስተምዕራብ አቅጣጫ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ያወሳሉ፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼን አፋሮች ጦርነት የሚመጣው ከበስተምዕራብ አቅጣጫ ነው የሚሉበትንም ምክንያት እንዲያብራሩልኝ አንስቼባቸው ነበር፡፡ በተለይ ግራዝማች ኢሰገሌ ቅድሚያ ወስደው ስሰማው ካደግሁት፣ በዕድሜየም ካየሁት እያሉ እንደተናገሩት ከጥንት ጀምሮ የሸዋ ነገሥታት የአፋርን ሱልጣኖች እና አሚሮች እየወጉ ሴቶች እና ልጆችን ወደ ደጋ እያጋዙ፣ ባሪያ እያሉም ሲገዙ ኖረዋል፡፡ እንስሳትንም እያረዱ እና እየነዱ ለጦራቸው እና ለቤተ መንግሥታቸው እርድ ሲዳርጉ ኖረዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሼህ መሐመድ ሰይድ እንዳወሱትም በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ያለው ግጭት መንሥዔ የአጠቃላዩ አማራ /ክርስቲያን/ ማለትም በእርሳቸው አገላለፅ የክርስቲያን እና እስላም ግጭት ሳቢያ የመጣ እና ሥርም የሰደደ ነው፡፡ የአማራነት /ክርስቲያን/ እና እስላምነት ግጭት ከጥንት እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደሚሉትም በእምነት ልዩነት ላይ የተመሰረተው መፈራረጅ በቀወት እና

በሰሙ·ሮቢ ገለአሎ ብቻ ሳሆን በሌሎችም አካባቢዎች የሚስተዋል ነው። ምክንያቱም ይህ የ "አማራነት" እና ሌላነት ጉዳይ በቀወት እና በሰሙ·ሮቢ ገለአሎዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የሚደመጥ መከፋፈያነቱ ወይም መለያነቱ ይስተዋላል።

ለአብነትም ይህ አጥኚ በሥራ አጋጣሚ በተዘዋወረባቸው የቀድሞዎቹ ደቡብ ሸዋ፣ አፋር፣ አርሲ፣ ሐረርጌ፣ ሱማሌ፣ ባሌ፣ ደቡባዊ ኢትዮጵያ አካባቢዎች፣ ከፋ፣ ኢሉባቡር አካባቢዎች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች የሆኑ አማሮችም፣ ትግራዋዮችም፣ ጉራጌዎችም፣ ኦሮሞዎችም ወዘተ በጥቅሉ "አማራ" በሚል እየተለዩ እንደሚጠሩ መታዘቡን ያስታውሳል።

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002 ዓ.ም.) ጥንት ሆነ የሚባለውንም ሲገልፁ ጥንት ቀይ ባህርን ተሻግረው የመጡት አፋሮች አገር አቅንተው፣ እስልምናን አስፋፍተው ቢኖሩም የአማራው /ክርስቲያን/ ነገሥታት ሲለፍፉ የኖሩት እና ዛሬም በኩራት የሚናገሩት ስደተኛ እስላሞችን በእንግድነት ተቀብለው፣ ማረፊያ ሰጥተው እንዳስተናገዷቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እራሳቸው አማሮችም ቢሆኑ ሥርወ አመጣጣቸው ከደቡብ አረቢያ እንደሆነ ነው የሚተርኩት። እስከ ዛሬ ድረስ አማራም ሆኑ አፋር ከኢትዮጵያ አፈር በቀልን ብለው አያውቁም። ሁለቱም የሚናገሩት መጤዎችነታቸውን ነው። ስለዚህ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ጉዳዩ የእኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ ያስከተለው ፉክክር እና ገርዎቹም መደቦች ለተራው ሕዝብ ያወረሱት ቂም በቀል ቅጥያ ነው የሚመስለው ።

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002 ዓ.ም.) እንደሚሉት አፋሮች በምሥራቃዊው የኢትዮጵያ ቆላማ ክፍል የእስልምና ኃይማኖትን ካስፋፉ በኋላ የአማራ /ክርስቲያን/ መንግሥታትን የሚገዳደር ሱልጣን በይፋት ምድር በመመሥረት ኢትዮጵያን የመቆጣጠር እና የማስተዳደር ጥረት ቢያደርጉም ከአሥራ አምስት ዓመታት ገደማ የአህመድ ቤን ኢብራሂም ዘመን ግዛት ውጪ እስከዛሬ እንዳልተሳካላቸው፣ በጠቅላላውም እስላሞችም ቢሆኑ እንደ ባለ አገር እንደማይታዩ፣ እስከ ዛሬም ድረስ በእንግድነት እንደሚታዩ፣ በአማራው /ተዋህዶ ክርስቲያኑ/ ውስጥ የሚኖሩት የኃይማኖት ወንድሞቻቸው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአመዛኙ በሸማኔነት እና ነጋዴነት እንደኖሩ እና እርስትም እንዳልነበራቸው፣ ዛሬ በቀወት እና በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳ ድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች መካከል የሚታየውም ግጭት የጠቅላላው አማራ /ክርስቲያን/ እና እስላም ነባር ግጭት ውርስ እና ነፀብራቅ እንደሆነ አመልክተዋል።

እዚህ ላይ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተተኪ ቡድን ውይይት አባል የሆኑት ሼህ መሐመድ ሰይድን ለመሆኑ ይሄ የነገሩኝ ሁሉ እውነት መሆኑ በምን ይረጋገጣል? ከአፈ-ታሪክ ብቻ አይደለም ወይ? ብያቸውም "መቼም እንግዴህ እኛ አሁን የምንነግርህ ያለፈ፣ ያልኖርንበትን ዘመን ታሪክ ነው፡፡ ቢሆንም የአፋር ሽማግሌዎች ያልነበረውን ከየት ያመጡታል? የነበረውን እና የሰማነውን ነው የምንነግርህ፣ እኔ ደግሞ ትንሽም ቢሆን ያነበብኩትንም ጭምር ነው የማስታውስህ" ብለውኛል፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት አፋሮችም አማሮችን ያሸንፉ በነበረበት ወቅት ልክ እንደ አማሮቹ የወረሩትን አካባቢ ያጠፉ፣ ይዘርፉ፣ ወንዱንም ይሰልቡ፣ ሴትና ልጁንም እየማረኩ፣ እያሰሩ፣ በጉልበቱም እየተገለገሉ፣ እያጋዙም ሁሉ በዘይላ በኩል ወደ የመን እያሻገሩ ይሸጡ ነበር፣ ከዚሁ ጋርም በዚያው በጥንቱ የአማራ እና የአፋር ግጭት ምክንያትም የአፋር ሱልጣኖች እና አሚሮች እንደ እነ ኤሚር ማህፉዝ፣ አህመድ ቤን ኢብራሂምን የመሳሰሉት በአማራ ነገሥታት ተገድለዋል፡፡ ሼህ መሐመድ ሰይድ እንደሚያስታውሱት ከጥንት የአማራ ነገሥታትም መካከል በአፋር ምድር ከእስላሞች ጋር ሲፋለሙ እነ አፄ እስክንድር፣ አፄ ናኦድ፣ ገላውዴዎስ፣ ሱስንዮስ፣ አብዬ እና ሌሎችም ስማቸውን የዘነጋቸው ነገሥታት ተገድለዋል፡፡

ሌላኛው የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ተወላጅ ለሆኑት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ ለአቶ አሎሃ ሃንዶ የድንበርተኞቹ ሰሙሮቢ ገለአሎዎች እና ቀወቶች የግጭት ምክንያቶች ምንድናቸው ? የሚል ጥያቄ ሰንዘሬላቸው ነበር፡፡

አቶ አሎሃ ሃንዶ የሰጡኝ መልስ ቀዳሚዎቹ የመረጃ ተባባሪዎቼ ከመለሱልኝ የተለየ አልነበረም፡፡ ይልቁንም አረጋጋጭ ነበር፡፡ አቶ አሎሃ እንደሚሉት አፋርና አማራ ብዙውን ጊዜ የሚጋጩት ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የጠላትነት ስሜት፣ በቆየ ታሪካዊ ጠላትነት "እስላምና አማራነት" ደም ብቀላ፣ በመሬት ይገባኛል፣ በሣር፣ በውኃ፣ በእንስሳት ሥርቆትና ዘረፋ እንዲሁም በእነዚህ ምክንያት በሚቀሰቀስ ግጭት ወቅት በመንደር፣ ቤተ እምነት፣ ሰብል ቃጠሎ፣ ንብረት ዘረፋ እና በብልት ሰለባ ምክንያት ነው (14/09/20002 ዓ.ም)፡፡ አቶ አሎሃ እንደሚሉት በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶችም አፋር እና አማሮች ይገዳደላሉ፣ ይዘራረፋሉ፡፡ በዚሁም ዓይነት ሁኔታ ዘወትር እንደተጠባበቁ እና እንደተዳደኑ ይኖራሉ፡፡

ለአቶ አሎሃ ሃንዶ አንድ ሌላ አስተያየት መሰል ጥያቄ አንስቼባቸው ነበር። "ለመሆኑ እነዚህ ያነሷቸው በተለይም የአፋርና የአማራ ግጭቶች የሚባባሱበትን ወቅት መለየት ይቻላል ወይ?" የሚል።

አቶ አሎሃ ሃንዶ እንደነገሩኝ ግጭቱ ምንጊዜም አለ። ምክንያቱም ማናቸውም የአካባቢው አፋርም ሆነ አማራ ወንድ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ጎልማሳ፣ ወጣት፣ ልጅ ሳይባል ስለዚህ ጉዳይ ቢጠየቅ መልሱ አጭር ነው "አፋር አፋር ነው። አማራ አማራ ነው። ያው ማራ እና እስላም ነን" የሚል መልስ ይሰጥሃል። እናም እንደዚያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ደግሞ አረጋውያኑን ብትጠይቅ ከጥንት የወረደ ግጭት ታሪክ እንዳለን ትረዳለህ ብለውኛል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም ስለ ታሪኩ እንዲያወጉኝ አንስቼባቸው ነበር። እርሳቸው ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣው እና እንደሰማሁት እያሉ እንደተረኩልኝ ነገሩ እንዲህ ነው። በጥንት ዘመን የአማራ ነገሥታት አፋርን ለማስገበር፤ አፋርም ላለመገበር ሲሉ ይፋለሙ ነበር። በዘመቻውም አማሮቹ /ክርስቲያኖቹ/ ድል ባደረጉ ቁጥር የአፋር ሱልጣኖችን አንገት ይቆርጡ፣ ሠራዊታቸውንም ይገድሉ፣ በሕይወት የተረፉትን እና ያገኟቸውንም ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ከእንስሳት እና ንብረቶቻቸው ጋር ይማርኩ እና ያግዙ፣ ባሪያም እያደረጉ ያሰሩ ነበር። አንዳንዶቹም ምርኮኞቻቸውን ለባሪያ ነጋዴዎች ይሸጧቸው ነበር። በዚህ ሁኔታ የተማረሩት አፋሮችም በሱልጣኖቻቸው እየተመሩ አካባቢያቸውን ላለማስወረር በትጋት ይዋጉ፣ እነርሱም ድል ሲያገኙ የደረሰባቸውን በተመሳሳይ መንገድ ይበቀሉ እንደነበር እና አንዳንድ ጊዜም ንጉሥ ሳይቀር እየገደሉ እና ጭንቅላቱን እየቆረጡ በግዛቶቻቸው ያዞሩ፣ በከተሞቻቸውም ይሰቅሉ ነበር ይባላል ይላሉ።

አቶ አሎሃ ሃንዶ (14/09/20002 ዓ.ም) በዕድሜዬ እንዳየሁት፣ ከአረጋውያንም እንዳደመጥኩት እያሉ እንደነገሩኝ አፋሮች እና ሌሎች የኃይማኖት ወንድሞቻቸው እስላሞች የአማራዎችን ገገርነት እና ጨቋኝነት፤ የእስላሞችን የተገገርነት እና የተጨቋኚነት ቀንበር ለመስበር ጠንክረው ወደ ደጋ ሲወጡ የዘመኑ ነገሥታት ለሕዝባቸው "ኃይማኖትህን የሚለውጥ፣ ሚስትህን የሚደፍር፣ ርስትህን የሚቀማ ወራሪ መጣብህ" እያሉ ተከታዮቻቸውን ያበዙ እንደነበር፣ በአንፃሩ እነርሱ ወደ ቆላው ሲዘምቱ ደግሞ "ለንጉሠ ነገሥታችን ግብር አልገብርም ብሎ ያመፀውን፣ በአካባቢው ያሉ አማሮችን በየጊዜው የሚገድለውን እና የሚሰልበውን እስላም ለመቅጣት እና አገር ለማቅናት ዘምተናልና ተከተለን" ይሉ እንደነበር በዚህም ምክንያት በሁለቱ ሕዝቦች

ዘንድ የከረረ የግጭት ሁኔታ እንዳለ እና ምንጊዜም ለመከሰት ትናንሽ ሰበብ ብቻ እንደሚበቃው አጫውተውናል፡፡

አቶ አሎሣ ሃንዶ በተለይም አማራው (በእርሳቸው አነጋገር አማራ የሚሉት ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑን ነው) እነሱ አፋርን ለማስገበር ሲዘምቱ "አገር አቅኚ"፣ አፋሩ አቅም አግኝቶ እነሱን ለማስገበር ሲዘምት "ወራሪ" አንዳንድ ጊዜም "የውጪ ወራሪ" እያሉ እንደሚያጥላሉ፣ ከዚያም አልፎ ተርፎ አህመድ ቤን ኢብራሂም ኢትዮጵያን ለመግዛት በሞከሩበት እንደ ሰው አለመሆናቸውን (ሰብዕናቸውን) እያራከሱ እንዳጥላሏቸው፣ በዚህም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ተከታዩ ሕዝብ የተለየ ምድራዊ ያልሆነ ፍጡር እንደመጣበት አድርጎ በአህመድ ቤን ኢብራሂም ላይ እንዲነሳ ማድረጋቸውን ያወሳሉ፡፡ አቶ አሎሣ በመከንከን ስሜት እንዳጫወቱኝ "ታላላቅ የሚባሉ የታሪክ ምሁራን ጭምር በአማራ ነገሥታት ሴራ ውስጥ ገብተው ማህፉዝን፣ አህመድ በድላይን፣ አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚን ወዘተ ወራሪ እያሉ ጽፈዋል"፡፡ በጽሑፍ ታሪክ እንደሚታወቀውም እዚህ የተጠቀሱት አህመድ በድላይ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ ማህፉዝ በአፄ ልብነ ድንግል መሸነፋቸው ይታወሳል፡፡

እኚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ እንደሚሉት "አማራ (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን) ወደ ምሥራቅ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ሲስፋፋ እና ሲገዛ አገር አቅኚ፣ አፋር እና የኃይማኖት ወንድሞቹ እና የዘር ወገኖቹ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ዜጎች ኢትዮጵያን ለመግዛት ሲነሱ ወራሪ እያሉ መፈረጅ ትክክል አይደለም"፡፡ እናም ዛሬ በቀወት አማራ እና በሰሙሮቢ ገለ አሎ አፋር መካከል ያለው ግጭት እንዲህ ዓይነቱ "የእሣት ዳር እና የጨረቃ ላይ የአኗኗር እና የግንኙነት ታሪክ ጨዋታ" ያስቀጠለው ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ በዚህም መሰረት አማራም ይሁን አፋር ከተመልካች ዓይን ሰወር ባለ ቦታ ከተገናኙ እና የቅርብ ትውውቅ ከሌላቸው አንደኛው ሌላኛውን ለመግደል መከጀሉ፣ ከተሳካለትም መግደሉ አይቀርም፡፡ ከላይ የወረደ ስለሆነም መገዳደል ልማድ ነው ይላሉ አቶ አሎሣ፡፡ እኚህ የመረጃ ተባባሪዬ እንዳወሱልኝ አፋር እና አማራ ምንጊዜም በጥንቃቄ፣ ተጠባብቀው ነው የሚኖሩት፡፡ ስለዚህ ጀርባ የሚያስጥል ሁኔታ የለም፡፡ ድንበርተኞቹ የሚኖሩት ዘወትር በመጠባበቅ ነው፡፡ አካባቢው ሰላምም ጦርነትም ያለበት ነው ይላሉ፡፡

የአማራ እና የአፋር የመረጃ ተባባሪዎቼ (አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ ድረሴ፣ አቶ ከተማ አይሻር፣ ሼህ መሀመድ ሰይድ፣ አቶ አሎሣ

ሃንዶ 27/01/2004) የተተኳሪ ቡድን ውይይት ባደረጉበት ወቅት የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት መንሥኤዎች የሚሏቸውን ነጥቦች እንዲያነሱልኝ ባወያየኋቸው ወቅት ሁለቱ ሕዝቦች የሚጋጩት በምክንያትም ያለ ምክንያትም እንደሆነ ነው የገለፁልኝ። ምክንያታዊ የሚሉትም የግጭት ሁኔታ በውኃ፣ በመሬት፣ በድንበር፣ በግጦሽ፣ በእንስሳት ዘረፋ፣ በብቀላ ወዘተ ምክንያት የሚከሰተው እና ወደ ቡድን ፀብነት እና መገዳደል፣ መዘራረፍ፣ ንብረት እና ቤተ እምነት ማቃጠል፣ መፈናቀል የሚሸጋገረው ነው።

ሌላው ምክንያት የለሽ የሚባለው ደግሞ ብዙውን ጊዜ አንድ አማራ አንድን አፋር ወይም አንድ አፋር አንድን አማራ በተናጠል እና በአሳቻ ሥፍራ ካገኘው የሚገድልበት፣ ጊዜ ካመቸውም የሚሰልብበት ዓይነቱ ነው።

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ እንዳወሱት ይህ ምክንያት አልባ የሚባለውም መገዳደል አንዳንድ ጊዜ ምንም ዓይነት የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ሀብት ተሸምቶ ባልተፈጠረበት ሁኔታ በግልም በቡድንም የሚፈፀም እና የተወሰኑ አፋሮች ወይም አማሮች አንደኛቸው ሌላኛቸውን የሚገድሉበት አጋጣሚ ነው።

ለተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ እንዲህ ዓይነቱ ሰበብ የለሽ መገዳደል መንሥኤ ምን ይመስላችኋል? የሚል ጥያቄ ሰንዝሬላቸውም ነበር።

የተተኳሪ ቡድን ተሳታፊዎቹ ደጋግመው እንዳነሱትም ለእንዲህ ዓይነቱ ግጭት ዋናው ምክንያት ነው ብለው የሚገምቱት ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የአካባቢውን አማሮች እና አፋሮች "አማራ እና እስላም" ወይም "እስላምና አማራ ነን" ልማድ ነው።

"አማራ እና እስላም" ወይም "እስላም እና አማራ ነን" የሚለው አባባል በድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ዘንድ የተለመደ እና የከረረ የፀበኝነት መግለጫ አነጋገር መሆኑን፣ አማራ እና አፋር ከጥንት ጀምሮ ፀበኞች መሆናቸውን፣ አንደኛቸው ሌላኛቸውን መሬት በወረራ ይዟል፣ ኃይማኖት አርክሷል፣ ኃይማኖት አስሸሯል ወይም አስቀይሯል፣ ቤተ ክርስቲያን እና መስጊድ አፍርሷል፣ ሰልቧል፣ ይሰልባል፣ ባሪያ ፈንግሏል ወዘተ ብሎ የሚከነክነንነቱን በዚህም የተነሳ ጊዜ እና አጋጣሚ እየጠበቀ በመገዳደል ላይ መሆኑን ገለፀውልኛል።

በጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ላይ የተካፈሉት የአማራ እና የአፋር የመረጃ ተባባሪዎቹ (የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣

አቶ ከፈለኝ አደፍርስ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004) እንዳወሱት በተለይ የቀደምት ክርስቲያን ነገሥታት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኤሚሮች እና ሱልጣኖች ታሪካዊ ፀበኝነት ሁኔታ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ በየአጋጣሚው የሚተረክ እንደሆነ፣ በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከልም የቡድን ፀብ ሲቀሰቀስ ቤተክርስቲያን እና ቤተ መስጊድም ስለሚደፈሩ፣ በሁለቱም ቤተ እምነት አገልጋዮች በኩልም አንደኛቸው ሌላኛቸውን ሊያጠፉ እንደተነሱ ተደርጎ የሚሰበክበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ አንስተዋል፡፡

ሁለቱም ወገኖች በውይይቱ ላይ ባነሱት ሐሳብ መሰረትም በአፋር እና በአማራ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል የሚስተዋለው ግጭት አንዱ መንሥዔ ከጥንት ከነገሥታቱ እና ከአሚሮቹ እና ሱልጣኖቹ የፀበኝነት ታሪክ ጋርም ተያይዞ ሲወርድ ሲዋረድም የመጣ ነው፡፡ በተለይ በቡድን ውይይቱ ላይ የተሳተፉት የአፋር ተወላጆች እንዳመለከቱት አፋሮች ከሽማግሌዎች የሚሰሙትን ነገር ሁሉ መቀበልን እና መፈፀምን እንደ ግዳጅ ስለሚቆጥሩት የአፋር አሚሮች እና ሱልጣኖች ከክርስቲያን ነገሥታት ጋር በየዘመኑ ያደረጉትን ተጋድሎ እና አፋሮች በየጊዜው የነገሥታቱ ጦር ሰለባ ሲሆኑ ኖረዋል የሚለውን ሲሰሙ የመቆጨት እና የቂመኝነት ስሜት አላቸው፡፡ ከዚህም ሁሉ ጋር ደግሞ አፋሮች በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ሱማሌዎች ጋር በመተባበር በአህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ አማካኝነት አማሮችን ለማስገበር እና ስልምናንም ለማስፋፋት አገሪቱን ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ለመቆጣጠር ቢችሉም አማሮች ከሰሜን እስከ ደቡብ ተባብረው፣ የእስላም ፀር የሆነ የውጪ ኃይልም ይዘው አጥፍተዋቸዋል የሚል ታሪክም ስለሚነገር ማናቸውም አፋር አማራን የሚያየው ተቀናቃኝ እና ፀሩ አድርጎ እንደሆነም ይነገራል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የድንበርተኖቹ አማሮች እና አፋሮች ግጭት ምክንያት በመጀመሪያ የሲራራ ነጋዴ መስመር ቁጥጥር እና የንግድ ቀረጥ ሀብት ቁጥጥር ፍላጎት፣ የተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ ማለትም መሬት፣ ድንበር፣ የግጦሽ ሣር፣ ውኃ፣ የእንስሳት ስርቆት፣ ዘረፋ፣ ብቀላ ወይም ቂመኝነት፣ "ወንድነት"፣ የባህል /ሥልጣኔ/፣ ወግ፣ ልማድ፣ የእምነት ልዩነት ማለትም "እኛነት" እና "እነሱነት" ልዩነት ትረካ ወዘተ ያስከተሉት ነው፡፡

## 8.6. የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ነዋሪዎች ግጭቶች አፈታት

በዚህ ርዕስ ሥር በመሰረታዊነት የምንመለከተው በቀወት አማሮች /ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች /እስላሞች/ መካከል ቀላል እና ከባድ ግጭት ሲከሰት የሚበርደው እና የሚቆመው እንዴት ነው? የእርቅ አፈፃፀም ሂደቱ እና አደማደም ሥርዓቱስ ምን ይመስላል? የሚለውን ነው፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እንዳወጉኝ በድንበርተኞቹ ሕዝቦች መካከል ተናጠላዊም ሆነ ጅምላዊ ግጭት አንድ ጊዜ ከተቀሰቀሰ በኋላ የሚገታው በተለያ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌም ግጭቱ የተናጠል ሲሆን ተጠቂው ወገን ቂሙን ቋጥሮ ሊቆይ እና ለመወጣት አመቺ አጋጣሚ ሊጠብቅ ይችላል፡፡ በዚህም ፋታ ይገኛል፡፡ ተጠቂው ወገን አመቺ አጋጣሚ አግኝተ ደሙን በደም ሲበቀል ደግሞ ግጭቱ አሁንም ዑደቱን ይቀጥላል፡፡ ግጭቱ የጅምላ ሲሆን ደግሞ አንዳንድ ጊዜ አቻዊ የሕይወት እና የንብረት ኪሣራ በመድረሱ ሁለቱም ወገኖች ለተወሰነ ጊዜ አደብ ሊገዙ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በአንዱ ወገን አሸናፊነት እና በሌላው ተሸናፊነት የሚረግብበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ግጭቱ የከረረ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሣራ ሲያስከትል እና አድማሱም የሰፋ ሲሆን ደግሞ ግጭቱ ውስጥ ባልገቡ የጎሳ መሪዎችና ባላባቶች ጥረትና ሽምግልና ይረግባል፡፡ በዚህ ረገድ በቀወት በኩል ባላባቶች ወይም የአካባቢ ታዋቂ ሰዎች እና የቀበሌ አመራሮች እንዲሁም በሰሙ ሮቢ ገለአሎ በኩል ደግሞ የጎሳ መሪዎች ጣልቃ በመግባት ግጭቱን ለማስታገስ መሞከራቸውም የቅርብ አፋጣኝ መፍትሔ ማግኛ ተደርጎ እንደሚቆጠር ተረድቻለሁ፡፡ ግጭቱ የከፋ ሲሆን ደግሞ በመንግሥት ጣልቃ ገብነት የሚቆምበት ልማድ እንዳለ ሰምቻለሁ፡፡ ይሁንና ግጭቱን በመንግሥት ደረጃ ለመፍታት የሚደረገውም ጥረት በአሁኑ ወቅት ረዘም ያለ፣ ጊዜ-ፈጅነት ያለው ሂደት መሆኑን ከመረጃ ተባባሪዎቼ ሁሉ ተገንዝቤያለሁ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎቼ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎዎችን ግጭት በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ያጋጥማሉ ያሏቸውን እና የታዘቧቸውን ተግዳሮቶች አውግተውኛል፡፡

የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደሚሉት በአፄ ኃለሥላሴ እና በደርግ ዘመን የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች አንዳንድ ቀበሌዎች በይፋት እና ጥሙጋ አውራጃ ሥር ስለነበሩ የጋራ የወረዳ አስተዳዳሮች ነበሯቸው፡፡ የጋራ የአውራጃ እና የወረዳ አስተዳደሮችም

ስለነበሯቸው በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የከፋ ግጭት ሲያጋጥም ባለሥልጣናቱ በዘመቻ መልክ በሁለቱም ሕዝቦች አካባቢዎች እየገቡ ግጭቱን የማረጋጋት፣ ፀበኛውን የመለየት፣ ተጻማዮቹን የቡድን ተጋጪዎች የማስማማት ጥረት ያደርጉ ስለነበር ግጭቱ ረጅም ጊዜ ሳይወስድ ይቃለል ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች በአማራ እና በአፋር ክልል ከተካተቱ በኋላ የጋራ አስተዳደር ስለሌላቸው ግንኙነቱ ወረዳ ከወረዳ ወይም ዞን ከዞን ወይም ደግሞ ክልል ከክልል በመሆኑ ሂደቱን ያረዘመው መሆኑን ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ያወሳሉ፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ በተመሳሳይ መንገድ እንደገለፁት በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ድንበርተኛ ወረዳዎች እና ዞኖችም መካከል የሰከነ መደማመጥ ያለ አይመስላቸውም፡፡ ለዚህም እንደ አስረጅ የሚያነሱት ሰፋ ያለ ግጭት በተከሰተ ቁጥር ወረዳዎቹ እና ዞኖቹ ተቀራርበው እና ተደማምጠው ስለማይመካከሩ፣ የሁለቱ ክልሎች ባለሥልጣኖች ጣልቃ እየገቡ ሲረባረቡ የሚመለከቱ መሆናቸውን ነው፡፡ ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ገለፃ መረዳት እና መጨመቅ የሚቻለውም የክልሎቹም ባለሥልጣኖች መላ ብለው የዘየዱት እና የፈጠሩት የሁለቱ ድንበርተኛ ወረዳዎች የጋራ የሰላም ኮሚቴ የሚባለው እንደ መቀናጆ በሬ ወደያገሩ ስለሚስብ የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት በመንግሥት ደረጃ ለመፍታት የሚደረገው ጥረት በአሁኑ ወቅት መንገታቶች የሚስተዋሉበት መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በአንድ ወቅት የተጫረው ግጭት በአካባቢ የአገር ሽማግሌዎችም ሆነ በተሳካ የመንግሥት ጥረት የተፈታ እና ትንሽ የሰላም ፋታ የተገኘ ቢመስልም እርቁ ከአንጀት ስላልሆነ እና የሟች ወገን ቂሙን ስለማይረሳ አጥቂውን ወገን ለመግደል ይነሳል፡፡ በዚህም ረገድ “የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም” እየተባለ የሚመስለው ነገር በሁለቱም ዘንድ በተግባር ያለ ይመስላል፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ በተናጠልም፣ በጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅትም እንደነገሩኝ በቀወቶችም ሆነ በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ዘንድ ተናጠላዊ ግጭት ለሽምግልና አይበቃም፡፡ ምክንያቱም ቀላል እና ተለመደ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህም ለሽምግልና የሚበቃው ጅምላ ግጭት ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ጅምላ ግጭቱም የሚመነጨው ደግሞ ከተናጠላዊ ግጭት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ጅምላ ግጭት ተከስቶ ከሆነ የሽምግልና ጥያቄውን በቀዳሚነት የሚያነሳው ብዙ ጉዳት ማድረሱን የተረዳው ወገን ነው፡፡ ለምሳሌም ሰሙሮቢ ገለአሎዎች በቀወቶች ላይ

የጅምላ ጥቃት ስንዝረው የሕይወት እና የንብረት ጉዳት አድርሰው ከሆነ እና ከቀወቶች በኩል የተሰነዘረው ወይም ሊሰነዘር የሚችለው አፀፋ የከፋ ሊሆንባቸው እንደሚችል ከገመቱ ግጭቱን ለማብረድ በሽምግልና አባባይነት /አቃጣሪነት/ ወደ አማሮቹ የሚልኩት በዕድሜ ጠና ያለች ሴት መልዕክተኛ ነው፡፡ ይህች ሴት መልዕክተኛም ወደ ታዋቂዎቹ የቀወት የአገር ሽማግሌዎች መገኛ አካባቢ ከተጠጋች በኋላ የጩኸት ድምፅ በማሰማት የመጣችበትን ምክንያት ታስረዳለች፡፡ የቀወት ወረዳ የአገር ሽማግሌዎችም የሽምግልና ጥሪውን ከሰሙ በኋላ ምላሹን ተመካክረው እንደሚነግሯት በማሳወቅ መልዕክተኛዋን ያሰናብቷታል፡፡

በአንፃሩ ቀወቶች በሰሙሮቢ ገለአሎዎች ላይ ጉዳት ሲያደርሱ እና ጅምላ መነሳሳቱን ለማቆም ሲሹ ሽምግልና የሚጠይቁት እንደ ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች በሴት መልዕክተኛ አይደለም፡፡ አማሮቹ የሚልኩት የእርቅ ጥያቄ አቅራቢ መልዕክተኛ ስሙ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ በምንም መጥፎ ነገር ተነስቶ የማያውቅ ዕድሜው ገፋ ያለ አዘውንት ነው፡፡ የእርቁ ጥያቄ በዚህ ሁኔታ ከቀረበ በኋላ ለሽምግልናው ከሁለቱም ወገን ሃያ፣ ሃያ ሽማግሌዎች ተመርጠው ይሰየማሉ፡፡ የሽምግልናውም ቦታ ይመረጣል፡፡ ከዚያም ድርድሩ ይቀጥላል፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ዋናው ፀብ ጫሪ፣ አጥፊ ወይም ጉዳት አድራሽ ሽምግልናው ላይ አይቀርብም፡፡ ከአፋር በኩል የሚቀርበው የአጥፊው ወይም ጉዳት አድራሹ የጎሳ አለቃ ነው፡፡ ከአማራው ወገን ደግሞ ባላባቱ ይህም በሌለበት ሁኔታ የጎበዝ አለቃው ወይም ደግሞ የቀበሌ አመራሩ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ተደራድረው ካበቁ በኋላ ለተጎጂ ወገን የገንዘብ ወይም የእንስሳት ካሣ በመቁረጥ ለእርቅ ይበቃሉ፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ የሱፍ እንዳጫወቱኝ የካሣ ክፍያው ገንዘብ መጠንም ሆነ የእንስሳቱ ብዛት የሚቆረጠው እንደ ጊዜው ሁኔታ እየታዩ ነው፡፡ ልምላሜውና ምርቱ ከፍ ሲል የምርቱና የእንስሳቱም ዋጋ ከፍ ሲል ካሣውም ከፍ ይላል፡፡ ልምላሜው ሲርቅ ምርቱና ገበያውም ሲያሽቆለቁል ደግሞ እንዲሁ ዝቅ ይላል፡፡ ብዙውንም ጊዜ አማሮች ገንዘብ፣ አፋሮች ከብት ነው የሚክሱት፡፡ በዚህም መሰረት አማሮችም ሆኑ አፋሮች ሲጋጩ እና ሲታረቁ ለግድያ አሥራ አምስት ሺህ ብር፣ ለቁስል አምስት ሺህ ብር፤ ይካካሣሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አማሮች እህል እንጂ ብዙ ከብት ስለሌላቸው፣ እህሉን ሸጠው ብር ስለሚከፍሉ፣ አፋሮችም እንስሳት እንጂ ብዙ ለገበያ የሚበቃ እና ብር የሚያመጣ ምርት ስሌላቸው እንስሳቱን ሸጠው በብር ስለሚከፍሉ ነው፡፡

እርቅ ሲፈፀምም በየወገናቸው ፀብ ቀስቃሾችን አደብ ለማስገዛት ቃል ይገባባሉ፡፡ ይኸውም ቃል መገባባት የሚታሰረው በየኃይማኖታቸው መኃላ በመፈፀም ነው፡፡ በየበኩላቸው መኃላ ከፈፀሙም በኋላ ብዙውን ጊዜ ጊደር ተለዋውጠው ያርዳሉ፡፡ የጊደሮቹ ሥጋ በእርቁ ላይ ለተገኙት ሁሉ የማይበቃ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ላም ወይም በሬ አቅርበው የተገኘውን አቅርበው እና ተለዋውጠው አርደው ጎን ለጎን ተቀምጠው በልተው ይለያያሉ፡፡ የሚታረደው ከብት ብዛት እንደ ግጭቱ ስፋት እና እንደታራቂዎቹ ብዛት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እስከ አሥራ ሁለት ከብት ይደርሳል፡፡ ይሄም ሁሉ ሆኖ ታዲያ እርቁ መፍረሱ አይቀርም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሁለት ዓመት አይዘልም፡፡ ምክንያቱም ቀወቶችም እንደሚሉት "መታረቁን ታረቅ፣ ቂምህን ግን አትልቀቅ" እንዲሉ ነው ነገሩ፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) "ለመሆኑ እርቁ ለብዙ ጊዜ የማይቆየው ለምን ይመስልዎታል? መኃላው አይፈራም እንዴ?" ብያቸውም ነበር፡፡

ሼክ መሐመድ እንደሚሉት ከሁለቱም ወገን እርቁን የሚያፈርሱት ብዙ ጊዜ ወጣቶች ናቸው፡፡ በእርቁ ላይ ያልታደሙ ወይም ለመታደም ያልደረሱ፡፡ እነዚህ ታዳጊዎች በየአካባቢያቸው ስለ ተፈፀመው ጥቃት፣ ስለጠፋው ሕይወት፣ ስለወደመው ንብረት በየቦታው ሲነገር ሲሰሙ ይቆያሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የቆዩ ታዳጊዎች አቅም ሲያበጁ የማያውቁትን አፋር ወይም አማራ በመግደል ቁጭታቸውን ለመወጣት ይሞክራሉ፡፡ በዚያውም ደግሞ ገዳይ ተብሎ ለመሞገስ እና ማህበራዊ ከበሬታንም ለመጨመር ይጓጓሉ፡፡ ሚስት መርጦ ለማግባት፣ በየሄዱበት ክብር ለማግኘት፡፡ እሱ ይቀደም እየተባሉም በምክሩም፣ በግብዣውም ላይ ሁሉ ለመቀደም፡፡ እንዲህ ከተወያየን በኋላም ለሼህ መሐደመድ ሰይድ "ሌላስ ምክንያት የለውም ወይ? ለምሳሌ አፋሮች እርስበርሳቸው በመሣሪያም በቅዱስ ቁርዓንም ከተማማሉ በኋላ ቃላቸውን አያፈርሱም ይባላል፡፡ አልፎ አልፎ የሚያፈርስ ሲገኝም በጎሳው አባላት ሁሉ ይወገዛል፡፡ ከማናቸውም ማህበራዊ ግንኙነት ይታገዳል፡፡ ቀዬውንም ጭምር ይለቃል የሚባል ነገር አለ፡፡ ታዲያ ከአማራ ጋር ሲሆን ይህ ዓይነቱ የእርቅ አፈፃፀም እንዴት ጥንካሬ ያጣል?" የሚል ጥያቄ ሰነዘርኩላቸው፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ ይህን ጥያቄ የመለሱልኝ እንዲህ በማለት ነበር፡፡

> ቀደም ሲል እርቁን የሚያፈርሱት የአፋርም የአማራም ወጣቶች ናቸው ብዬሃለሁ፡፡ አሁን እንዳልከውም ደግሞ አፋር ብቻ ሳይሆን አማራም የነፍስ ግዳይን ነገር ተሸማግሎ የጦር መሣሪያ በመራመድ፣ የቤተ ክርስቲያን በር በመዝጋት፣ መስቀል በመጨበጥ፣ እርጥብ ሣር በመባጠስ፣ ሽንጥ ሥጋ

በመቋረጥ እና አካባቢንም በመልቀቅ ጭምር እና እንዲህ በመሳሰለው ሁሉ መኃላ ከፈፀመ በኂላ አይከዳዳም።
ሲሉ አረጋግጠውልኛል።

ይህም የሆነበት ምክንያት እንዲያብራሩልኝ አንስቼባቸው "እርቁ የግለሰብ ከግለሰብ ሳይሆን የቡድን ስለሆነ ነው። የገደለው አፋር ወይም አማራ ተለይቶ እርቅ አይፈፅምም። ግድያው የእርስበርስ ሲሆን ግን በሁለቱም ወገን ገዳዩ ተለይቶ ታውቆ ነው የሚፈፀመው። ስለዚህ ይሄም ለእርቁ መላላት አንዱ ምክንያት ሳይሆን እሚቀር አይመስለኝም" የሚል ግምት ሰንዝረዋል።

ስለ አማራና አፋር ግጭትና እርቅ አፈፃፀም ሁኔታ ያወያየኂቸው ሌላኛው መረጃ ተባባሪዬ ባላምባራስ አይዳሂስ (05/09/2002) ናቸው። ለእርሳቸውም "አፋርና አማራ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ እርቁ የሚፈፀመው እንዴት ነው?" ባላምባራስ አይዳሂስ ስለ ሽምግልናው ሂደት የነገሩኝን እንደሚከተለው አጠናቅሬዋለሁ። በአማራና በአፋር መካከል ደም መፋሰስና መገዳደል ሲኖር እርቅ የሚደረገው ከሁለቱም ወገን ሃያ ሃያ ሰዎች ባላባቶች ተውጣጥተው ነው። እርቁም የሚፈጸመው አሁን አሁን ለቆሰለ አምስት ሺ ብር፣ ለገደለ አሥራ አምስት ሺህ ብር ካሳ በማስከፈል ነው። ገንዘቡ እንዲህ ያደገው አሁን ነው። ፊት እንዲህ አልነበረም።

ለባላምባራስ አይዳሂስ (05/09/2002) ለመሆኑ አሥራ አምስት ሺህ ብር መክፈል የተጀመረው ከመቼ ወዲህ ነው? አልኳቸው።

በአጭሩ "ይሄ አሁን በዚህ በኢህአዴግ /በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር/ ዘመን ነው። እዚህ ሰፈ በረት አካባቢ በተደረገ እርቅ ነው የተጀመረው።" አሉኝ። ለባላምባራስ አይዳሂስ እንደመጨረሻ ጥያቄ የወረወርኩት "ለመሆኑ እርቁስ ለምን ያህል ጊዜ ፀንቶ ይኖራል?" ሚል ነበር።

ባላምባራስ አይዳሂስ (05/09/2002) የመለሱልኝ "ግጭቱ ለጊዜው በእርቅ ቢበርድም፣ እርቁ ብዙ ዘመን አይቆይም። አንዱ ወገን ሲጠግብ የጎሳውን ቂም ይወጣና ያፈርሰዋል። ወይ ደግሞ ሲቸገር ያንኑ ውኃ፣ ግጦሽ፣ መሬት ሲፈልግ እንደገና ያድሰዋል። እርቁ ዘወትር በእሳት የተያያዘ ቤትን እንደማጥፋት ያህል ነው። እሳቱና ቤቱ ምንጊዜም አብረው ናቸው። አይራራቁም" በማለት ነበር። እኔም ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት በማለም "ለመሆኑ በእርቁ ላይ ቃለ መኃላ ይፈፀም የለም ወይ? ለምንድነው የማይፀናው?" አልኳቸው።

ባላምባራስ አይዳሂስ የቀጠሉት እንዲህ በማለት ነበር፡፡ "መኃላው አለ፡፡ መኃላውንም የሚፈፅሙት ሰዎች መኃላውን አያፈርሱም፡፡ የሚያፈርሱት ሌሎች መኃላው ላይ ያልነበሩት ናቸው፡፡ አዳዲሶቹ ገዳይ ለመባልና ለመከበር የሚሹት፡፡" እዚህ ላይ ባላምባራስ አይዳሂስ "መኃላው አለ፡፡ መኃላውንም የሚፈፅሙት ሰዎች መኃላውን አያፈርሱም፡፡ የሚያፈርሱት ሌሎች መኃላው ላይ ያልነበሩት ናቸው፡፡ አዳዲስ ገዳይ ለመሆን የሚሹት፡፡" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? የሚል ማፍታቻ መስጠት የተገባ ይመስለኛል፡፡

"አንዱ ወገን ጥጋብና ጉልበተኝነት ሲሰማው የጎሳውን ቂም ይወጣና ያፈርሰዋል፡፡ ወይ ደግሞ ሲቸገር ያንኑ ውሃ፣ ግጦሽ፣ መሬት ሲፈልግ እንደገና ያድሰዋል፡፡ እርቁ ዘወትር እሳት እንደማጥፋት ሥራ ነው" ይህም ሆኖ ታዲያ ከሁለትና ሦስት ዓመታት የማይዘል ዕድሜ የሚኖረው ጊዜያዊ የማስታገሻ እርቅም ቢሆን ሲፈፀም ሥርዓት አለው፡፡

አንደኛ ነገር በአፋር እና በአማራ እርቅ ወቅት እርቅ የሚፈፅሙትና መኃላውን የሚፈጽሙት የጎሳ መሪዎች እና ባላባቶች ወይም ታዋቂ ሰዎች ናቸው፡፡ ነፍስ አጥፊው እና የተጎዳው ቤተሰብ የሆኑት የአፋር ወይም የአማራ ተወላጆች አይደሉም፡፡ ምክንያቱም እርቁ የቡድንና የጅምላ ነው፡፡ በአፋርም ሆነ በአማራ በኩል የጎሳ መሪዎቹና ባላባቶቹ ገዳዩን ለይተው ቢያውቁትም በእርቁ ላይ አንጥረው አያወጡትም፡፡ "የእኛ ሰው የናንተን ሰው መግደሉን እውቀናል" ብቻ ነው የሚሉት፡፡

ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ እንደሚሉት አማራ እና አፋር ሲጋጩ ማለትም ሲዘራረፉ እና ሲገዳደሉ እርቅ የሚፈፅሙት ቀጥተኛ ፀበኞቹ (ተጋጪዎቹ፣ ተዘራራፊዎቹ እና ተገዳዳዮቹ) ወገኖች እና ቤተሰቦች አይደሉም እርቅና መኃላ የሚፈፅሙት፡፡ ታራቂዎችም መኃላ ፈፃሚዎችም የየአካባቢያቸውን ቀጣይ ደህንነትና ሰላም ለማረጋጋት የሚተጉ ሰዎች ናቸው፡፡ ግድያውንም ቢሆን የሚያዩት እንደ ልማድ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ተሸማጋዮችና መኃላ ፈፃሚዎች በእርግጥም መኃላቸውን ያከብራሉ፡፡ ነገር ግን በሽምግልናው ላይ ያልነበሩ እና ቃለ መኃላውንም ያልፈፀሙ አዳዲስ ጆሮ አውጪዎች ገዳይ ለመሰኘትና ገዳይነት የሚያስገኘውን ክበሬታ ለማግኘት ሲሉ የውኃም፣ የግጦሽም፣ የእንስሳት ሥርቆትንም ሰበብ አድርገው ታሪካዊ ጠላት አድርገው የሚቆጥሩትን ወገን ሰው ይገድላሉ፡፡ ቀደም ባለው ዘመን ደግሞ መግደል ብቻ ሳይሆን ይሰልባሉ፡፡ ይሄም እንግዲህ ማታ በጨረቃ እና በእሣት ዳር እንዲሁም

በየድግሱ ቤት እከሌ የሞተው እንደዚህ ነው። እከሌ ገዳይ የሆነው እንዲህ አድርጎ ነው የሚለውን ወሬ እየሰሙ የሚያድጉት እና በየሸላሉውም፣ በየለቅሶውም፣ በተረቱም ፀበኝነትንና ገዳይነት መሞካሸቱን እያዩና እየሰሙ ያደጉቱ ናቸው ማለት ነው።

ሌላኛው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ አቶ ከበደ መንገሻ (25/01/2003) ናቸው። ለእርሳቸውም ያነሳሁላቸው ጥያቄ "አማራ ከአፋር ጋር ሲጋጭ የእርቁ ሥርዓት ምን ይመስላል?" የሚል ነበር።

የአቶ ከበደ መንገሻ መልስ "የአፋርና የኦሮሞው የጎሳው አለቆች፤ የአማራው ደግሞ የአካባቢው ታዋቂ ሰው (ድሮ ባላባቱ ነበር) ተሰብስበው ያስታርቃሉ። አፋሮቹ በተለይ ከፈለጉ ወንጀለኛውን ይዘው በመቅረብ ይታረቃሉ። አለዚያ ደግሞ ግድያውን ወይም ዘረፋውን የፈፀመው የኔ ጎሳ አይደለም ይላሉ።" የሚል ነበር። በማስከተል "እርቁስ እንዴት ነው?" የሚል ጥያቄዬ ሰነዘርኩ።

አቶ ከበደ መንገሻ እንዲህ ነበር ያሉኝ።

> እርቁ ለቁስለኛ እና ለሞተ ሰው የደም ካሣ በመቁረጥ ነው። እሱም ከአማራ ወገን የሚከፈለው ብር ነው። ብሩ ከአጥፊውም ከወገንም ከአካባቢም የሚሰበሰብ ነው። የብሩም መጠኑ እንደጊዜው እና እንደኑሮው ሁኔታ ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል። ለቁስል ዛሬ ወደ አምስት ሺህ ብር ነው። ለሞት አሥራ አምስት ሺህ ደርሷል። አማራ የሚከፍለውም የሚቀበለውም ገንዘብ ነው። አፋርም ለአማራ በካሣነት የሚከፍለው ገንዘብ ነው። አማሮችም ገንዘብ እንጂ ከብት አይከፍሉም። ከብት ለአፋርና ለኦሮሞ ነው።

አቶ ከበደ እንዳጫወቱኝ እርቁ በዚህ መልኩ ከተጠና በኋላም አማሮቹም አፋሮቹም አንዳንድ ከብት አዋጥተው፣ ያመጡትንም ከብት ተለዋውጠው አንድ ቦታ ላይ አርደው እንደየእምነታቸው ባርከው፣ አርደው፣ እንደየፍላጎታቸውም አዘጋጅተው በልተው መለያየት ነው። አፋሮች ኃይማኖታቸው ከአማራው የተለዩ ስለሆነ ከአማራው ጋር ሲታረቁ አማራውም እነሱም ለእርድ ያመጧቸውን ላም እና በሬ ከብቶች ይለዋወጡና አርደው ጎን ለጎን ተቀምጠው በልተው ተመራርቀው ይለያያሉ (አቶ ከበደ መንገሻ (25/01/2003) ።

ለእኚህ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ "ለመሆኑ እንዲህ የተደከመበት እርቅ ለምን ያህል ጊዜ ይፀናል?" የሚል ጥያቄም ማንሳቴ አልቀረም።

አቶ ከበደ መንገሻ እንዳወሱልኝ "እርቁ ይፀናልም ይፈርሳልም። ነገሩ እንደ በቆሎ ንፍሮ ነው። እያደር ይጠነክራል። የበቆሎ ንፍሮ ዛሬ ቢበስልም ነገ ተመልሶ

ይጠነክራል፡፡ ሲቆይ ተመልሶ ጥሬ እየሆነ ነው የሚሄደው፡፡ ከአባቶች እንደሰማነው እኛም በሕይወታችን እንዳየነው ትንሽ አረፍ ይልና ቆይቶ ደግሞ ያገረሽበታል፡፡”

ሌላኛው ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዬ ሼህ መሐመድ ሰይድ (10/09/2002) ደግሞ እንደተረኩልኝ አፋሮች እርስበርሳቸው ሲጋጩ እና ሲታረቁ ከአማራው ጋር ከሚደረገው የተለየ የካሣ አቆራረጥ፣ አወቃቀስ እና እርቅ አፈፃፀም እና አስተራረግ ሥርዓት አላቸው፡፡ “አፋር እርስበርሱ ሲገዳደል ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ ሺህ ግመል ወይም የቀንድ ከብት የደም ካሣ ይቆረጣል፡፡ ካሣውን የሚከፍለው ገዳዩ ብቻ አይደለም፡፡ ቤተሰቡና ጎሳው ያዋጣለታል፣ ይከፍልለታልም፡፡” በእንዲህ ዓይነቱ የአፋሮች የእርስበርስ ግጭት እርቅ የማውረድ ሥርዓት ወቅትም አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ገዳዩን እሟች ቤት አስገብተው እህል ውኃ አፋትተው እርቁን ይደማድማሉ፡፡ በዚህ መልኩ እርቅ ከተፈፀመም በኋላ በአፋሮች መካከል መከዳዳት የለም፡፡ ከሼህ መሐመድ ሰይድ አንደበት እንደተሰማውም የመኃላው ቃል  እንዲህ የሚል ነው፡፡

> ከከዳሁ ይሽ ይክዳኝ ብለው ገዳይና የሟች ወገን ይማማላሉ፡፡ ላለመከዳዳት ጠመንጃ መራመድ አለ፡፡ አፋሮች በከብት ደም ይታጠባሉ፣ በጉበቱ ይለቀለቃሉ ወይ የከብት እበት ይጨብጣሉ፣ ወይም እርጥብ ሣር ይነጫሉ፡፡ ከብት ያሳጣን፣ ዘር ያሳጣን እያሉ ልጅና ከብታቸውን ጨብጠው ወይም ይዘው ይምላሉ፡፡ ያቆሰለ ወይም የገደለ በውሸት እንዲህ ብሎ አይምልም፡፡ አማራው እበት አይጨብጥም የቆመውን ከብት ይጨብጣል፡፡ አንዳንዴም እንደ አፋሮቹ በደምና በጉበት እጁን ይለቃለቃል፣እርጥብ ሣር ይነጫል፡፡

ከቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቼ ገለፃ እንደተረዳሁት በቀወቶች እና በሰሙሮቢ ገለአሉዎች መካከል የጅምላ ግጭት ሲከሰት እና ግድያ ሲፈፀም ሽምግልናው እስከ አምስት ወር ድረስ ይፈጃል፡፡ ሽምግልናውም ሲሰምር ለሟች ወገን እስከ አሥራ አምስት ሺህ ብር የደም ካሣ /ወጆ/ ይከፈላል፡፡ ለቆሰለ ደግሞ አምስት ሺህ ብር ካሣ ይቆረጥለታል፡፡ በዚህ መልኩ የተቆረጠውን ካሣም የሚከፍለው ከአፋር በኩል የጎሳው ባላበት ነው፡፡ የጎሳው ባላባት  በተሳተፈበት እርቅ ላይ የተቆረጠውን ካሳ ከአጥፊው ብቻ ሳይሆን ከጎሳው አባላት አሰባስቦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ የጎሳው አባላት በአጥፊው ወገናቸው ላይ የተቆረጠውን ካሣ ለመክፈል ፈቃደኞች ካልሆኑ የጎሳ መሪው ጥፋተኛውን አሳልፎ ለዳኛ ሊሰጠው ይችላል፡፡

በአማራ በኩል የሚከፈለውን የካሣ ገንዘብ አዋጥቶ የሚከፍለው አጥፊው የሚኖርበት ቀበሌ ሕዝብ ነው፡፡

ለመሆኑ እንዲህ የተደከመበት እርቅ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ያልኳቸው አቶ አሎሃ የመለሱልኝ እንዲህ በማለት ነው፡፡

> አፋርና አማራ የሚፈፅሙት እርቅ ትንሽ የተሻለ ጊዜ ይቆያል፡፡ ብዙ ጊዜም በእነርሱ መካከል የተፈፀመ እርቅ የሚፈርሰው በእርቁ ላይ ባልተገኙ ወጣቶችና ጎረምሶች ነው፡፡ ደግሞም አፋር ሰው ገደለ ተብሎ ፍርድ ቤት ስለማይቀርብ፣ እንደ ጀግንነት ማሳያም ስለሚቆጠር፣ አመቺ ሁኔታ ጠብቆ ያገኘውን አማራ የመግደል ልማድ አለ፡፡ አማራም ቂሙን የሚመልሰው የገደለበትን አፋር ማንነት ለይቶ አይደለም፡፡ በድንገት ያገኘውን አፋር ለቂም መወጫነት እና ደም መመለሻነት ይገድላል፡፡

አፋርም ሆነ አማራ ነፍስ ሲያጠፉ ወደ ፍርድ ቤት የመሄድ፣ ከስ የመመስረትና ዳኝነት የማግኘት ጥረት የለም ወይ? የሚል ጥያቄም ለአቶ አሎሃ ሃንዶ አንስቼባቸው ነበር፡፡

አቶ አሎሃ ሃንዶ (14/09/2002 ዓ.ም.) እንደሚሉት "ሰው የገደለ አፋር ጎሳውን እየቆጠረ የትም መሄድ ስለሚችል ቶሎ አይገኝም፡፡ አፋር አማራ ገደለ ብሎ የሚያድን የጎሳ መሪም ሆነ የመንግሥት አካል የለም፡፡ ሰው በመግደሉ ከአካባቢው የተሰወረ ወይም የተደበቀ አፋር ሊገኝ የሚችለው የጎሳው መሪ እንዲቀርብ ካዘዘው ብቻ ነው፡፡" አቶ አሎሃ ሃንዶ እንደነገሩኝ የጎሳው መሪ ደግሞ የደረሰው ጥፋት አደገኛ እና አስቸጋሪ ካልሆነበት በስተቀር ገዳዩን ለመንግሥትም ለእርቅም አያቀርብም፡፡ ለመንግሥት አሳልፎ የሚሰጠው የደረሰው ጉዳት መንግሥትን የሚያስቆጣ ጎሳውንም የሚጎዳ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ አፋር የራሱን ጎሳ አሳልፎ አይሰጥም፡፡

አቶ አሎሃ ሃንዶን "በአማሮች በኩልስ እንዴት ነው?" ብያቸውም ነበር፡፡ "አማራው ግን የተገደለበትን ሰው ለፖሊስ ያስመዘግባል፡፡ በተለይ ደግሞ ከአጎራባች ቀበሌ ጋር ሲሆን እና ነገሩ ጅምላ ሲሆን ለፖሊስ የማመልከት ሁኔታ አለ፡፡ ያም ሆኖ አፋር አይያዝም፡፡ አፋር ወገኔ ተገደለም ብሎ ወደ ፖሊስ አይሄድም፡፡ አማራ ሲገድልም ወደ ፖሊስ የሚቀርብበት መንገድ የለም፡፡ የጎሳ መሪው ለጎሳው ደህንነት ሲል ይዞ ካላስረከበው፡፡"

ከጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላቱም እንደተረዳሁት ቀድሞም ሆነ አሁን የቀወት ወረዳ ፖሊስ አፋር መሬት ወርዶ ነፍሰ-ገዳይ አያድንም፡፡ አሁን ደግሞ የሁለቱ ሕዝቦች አስተዳደር በክልል እና በወረዳ ስለተለያዩ ሂደቱ ረጅም ሆኗል፡፡ በድንበርተኞቹ ወረዳዎች መስተዳድሮች መካከል አንዳንድ የመተባበር ጥረቶች ቢኖሩም ግን ጠንካራ አይደለም፡፡ መስተዳድሮቹም የሚንቀሳቀሱት ከበድ ያለ ነገር ሲያጋጥም እና የበላዮቻቸው

ሲያዟቸው ብቻ ነው (የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፡- አቶ ስጥአርጌ ደርሶ፣ አቶ ደመቀ ሲሻህ፣ አቶ ከፈለኝ አደፍርስ፣ ሼህ መሐመድ ሰይድ፣ ሼህ አደን ጋለሎ፣ አቶ አሎሃ ሃንዶ 27/01/2004)፡፡

በመጨረሻም አማራና አፋር እርቅ ሲፈፅሙ የሁለቱ ኃይማኖቶች ኦርቶዶክስ ክርስትና እና እስልምና ሚና ምን እንደሚመስል እንዲነግሩኝ የጠየቅኋቸው የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት እንደነገሩኝ የኃይማኖት ሰዎች በእርቁ ላይ ቢገኙም በአማራና በአፋር እርቅ ላይ የጋራ ኃይማኖታዊ መኃላ የለም፡፡ ለእርቁ የቀረበውን መሰናዶ በየኃይማኖታችን ባርከን ከመብላት በስተቀር ብለውኛል፡፡ በአንፃሩ በአፋሮች መካከል እርቅ ሲፈፀም ግን አልፎ አልፎ መኃላው የሚፈጸመው ኪታብ በማስጨበጥ እንደሆነም አጫውተውኛል፡፡

አማራ ከአፋር ጋር ነፍስ ሲጠፋፋ የሚክሰውም የሚካሰውም አሥራ አምስት ሺህ ብር ነው፡፡ ለቁስል አምስት ሺህ ብር፡፡ ምክንያቱም አማራ አራሽ ስለሆነና ብዙ ከብት ስለሌለው ይላሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ሲል ከላይ የተጠቀሱት ሌላኛው የመረጃ ተባባሪዬ አቶ አሎሃ ሃንዶ (14/09/2002 ዓ.ም) ናቸው፡፡ እርሳቸውንም “አማራና አፋር ሲገዳደሉ የእርቅ ውሳኔ አሰጣጡ እንዴት ነው?” ብያቸው ነበር፡፡

> ብዙ ጊዜ አማራ እርስበርሱ ሲገዳደል ገዳዩን ለይቶ አውቆ ወደ ህግ ነው መሄድ የሚፈልገው፡፡ መበቀልም እያሰበ ቢሆን ለህግ ያስመዘግባል፡፡ ከአፋር ጋር ሲሆን ግን አፋር ለሕግ እንደማይገዛ ስለሚያውቅ በጅምላ ሊያጠቃ ይነሳሳል፡፡ በአማራና በአፋር፤ በአማራና በጅሌ ኦሮሞ መካከል ግጭት ሲከሰት የጅምላነት የጎሳ ጠብ የሚሆነው ለዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ከአማራ የአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ወይ ባላባቶቹ እንዲሁም ከአፋሩና ከጅሌው የጎሳ መሪዎቹ ተሰባስበው እርቅ ይፈፅማሉ፡፡ እርቁ ከአማራ ጋር ሲሆን ለቁስለኛ እስከ አምስት ሺህ፣ ለሙት እስከ አሥራ አምስት ሺህ ብር ደርሷል፡፡ ወጆው መሆኑ ነው፡፡ አማራ ከብት አይክስም አይካስምም፡፡ አፋርና ጅሌ ከብት ነው ወጆ የሚከፍሉት፡፡

የአማራና የአፋር ግጭት የእርቅ አፈፃፀም እና ሂደት እንዲሁም አደማደሙስ ምን ይመስላል? ያልኳቸው ሼህ መሐደመድ ሰይድ (14/09/2002) እንዲህ ይቀጥላሉ፡፡

> በተለይ አፋር ከአማራ ጋር ሲጋጭ ወደ አማራው የሚልከው ሴት መልዕክተኛ ነው፡፡ እሷ ታቃጥራቸዋለች፡፡ ከሁለቱ ወገን ሃያ፤ ሃያ ሽማግሌዎች ይወጣጣሉ፡፡ አማሮቹና ኦሮሞዎቹ ከአፋር እርቅ ሲጠይቁ ዕድሜው ገፋ ያለ አማካይ ሰው ይልካሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሽምግልናው ቦታ ይመረጣል፡፡ ድርድሩ ይቀጥላል፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ዋናው አጥፊ አይቀርብም፡፡ የአጥፊው የጎሳ አለቃ ይቀርባል፡፡ ከዚያ በየኃይማኖታቸው መኃላ ይፈጽማሉ፡፡ ከብት ላም ወይም በሬም አቅርበው

ተለዋውጠው አርደው ጎን ለጎን በልተው ይለያያሉ፡፡ የሚታረደው ከብት ብዛት እንደታራቂዎቹ ጎሳዎች ወገን ብዛት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እስከ አሥራ ሁለት ይደርሳል፡፡ ይሄም ሁሉ ሆኖ ታዲያ እረቁ መፍረሱ አይቀርም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሁለት ዓመት አይዘልም፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (14/09/2002) በአማራ እና በአፋር መካከል ያለውን ድህረ ግድያ ሁኔታ አብራርተውልኛል፡፡

> አማራ ብዙ ጊዜ እርስበርሱ ሲጋጭ እና የደም ወደር ካለ ማለትም እኩል የሕይወት መጥፋት ከደረሰ ብዙውን ጊዜ ገዳዩን ለይቶ አውቆ ለመክሰስ ወደ ህግ ነው መሄድ የሚፈልገው፡፡ መበቀልም እያሰበ ቢሆን ለህግ ያስመዘግባል፡፡ አማራ ከአፋር ጋር ሲገዳደል ግን አፋርን ወደ ሕግ ለማቅረብ ስለማይቻለው ደሙን በቀጥታ የሚመልሰው ከቻለ የገዳዩን ጎሳ አባል ወይም ሰፈርተኛ፣ ካልቻለም ያገኘውን አንድ አፋር በመግደል ነው፡፡ ምንም እንኳን አማራ ወደ ዳኛ የመሄድ ልማድ ቢኖረውም ከአፋር ጋር ሙግት ለመግጠም እንደማይቻለው ያውቃል፡፡ ምክንያቱም ገዳዩን አፋር በቀላሉ አግኝቶት የክስ ወረቀት ወይም መጥሪያ ወረቀት መስጠት አይቻለውም፡፡ ቀድሞ ሁለቱ ሕዝቦች በአንድ ወረዳ ሥር እንኳን እየተዳደሩም ሳሉ ቢሆን ፖሊስ ወደ አፋር ገብቶ የአፋር ወንጀለኛ አድኖ ይዞ ለሕግ አቅርቦ አያውቅም፡፡ ምክንያቱም ወደ አፋር ዘልቆ አይገባም፡፡

ሼህ መሐመድ ሰይድ (14/09/2002) እንዳጫወቱኝ በንጉሡም ሆነ በደርግ ዘመነ መንግሥታትም ቢሆን አልፎ አልፎ ወደ አፋር ቀበሌዎች የሚገባው የጅምላ ወንጀል ማለትም ግድያ፣ ንብረት ዘረፋ፣ ቤት ቃጠሎ ወዘተ ሲበዛ እና አማራ አቤቱታ ሲያሰማ ነበር፡፡ ያም በወረራ መልክ የሚደረግ እና ከአፋር ጎሳ መሪዎች ጋር በመተባበር የሚፈፀም ነበር ይላሉ፡፡ ዛሬ ደግሞ ሁለቱም ሕዝቦች በተለያዩ ሁለት ክልሎች ውስጥ ስለ ተካለሉ ጥፋተኛውን ለማቅረብ መንገዱ ቀላል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሼህ መሐመድ እንዳብራሩልኝ አፋር ከገደለ በኋላ እራሱን ስለሚሞሸር፣ በጎሳ ዝርዮቹም ቤት እየዞረ ስለ ገዳይነቱ የሚቀለብ ስለሆነ ነው፡፡

ከቃለመጠይቀቅ፣ ከተተኳሪ ቡድን እና ከጋራ ተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ሂደት እንደተረዳሁትም አፋር አማራ በመግደሉ የጎሳው መሪም ይሁን በጎሳ መሪው የሚታዘዙት የፀጥታ አስከባሪዎች አይዙትም፣ ለዳኝነትም አያቀርቡትም፡፡ ይልቁንም የገደለውን ሰው ሁኔታ፣ የአገዳደሉን አኳኋን እየተቀባበሉ ይነዙለታል፡፡ እጅግ ክትትል ቢበዛ እንኳን "ነፍስ ስታጠፋ ወደ አባትህ ጎሳ፤ ሲርብህ ወደ እናትህ ጎሳ ግባ" የሚል ብሂል ስላላቸው ከአፋር ወጪ የሆነን ሰው የገደለ ወደ አባቱ ጎሳ የመግባት እና የመደበቅ መብት አለው፡፡ የአባት ጎሳ ወገንም ሰው ገድሎ የመጣ ወገኑን መከታ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህም አፋር ከራሱ ብሔር ሲገድል በጎሳ መሪዎቹ በኩል

ሽምግልና ዳኝነት እና እርቅ ቢያካሂድም ግድያው ከራሱ ብሔር ውጪ ሲሆን ወደ ሕግ ወይም ሽምግልና የሚያስገድደው ሁኔታ የለም፡፡ አፋር ከአማራም ሆነ ከሌሎች ጋር ተናጠላዊ ግድያ በማድረጉም ከጎሳው በኩል ተፅዕኖ አይደረግበትም እንዲያውም ይሞካሻል፡፡ ተፅዕኖ የሚደረግብት በፈፀመው ግድያ ሳቢያ በጎሳው አባላት ላይ ወይም በአካባቢው አፋር ላይ የጅምላ ፀብ እና ግጭት፣ በግጭቱም የሕይወትና የንብረት ውድመት የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ወይም ካስከተለ ብቻ ነው፡፡ አማራም ብዙውን ጊዜ በአፋር ላይ በጅምላ የሚነሳሳው አፋርን በፖሊስ እና በመደበኛ ፍርድ ቤት በኩል ማቅረብ እና መዳኘት አስቸጋሪነቱን ስለሚያውቅ ነው፡፡ በአማራና በአፋር፣ በአማራና በጅሌ ኦሮሞ መካከል ግጭት ሲከሰት ጅምላዊ የጎሳ ጠብ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው ይላሉ የመረጃ ምንጮቼ፡፡

ስለዚህም በአማራና በአፋር መካከል ደም መፋሰስ ሲከሰት የፀቡ ሁኔታ ተከታታይ የሆነ የቡድን ግጭትን እንደሚያስከትል የገመተው እና ሁኔታው ያሳሰበው ወገን የሽምግልና አመቻቺ የሚሆን ሰው ወደ አንድ ታዋቂ ሰው ዘንድ በይፋ ይልካል፡፡ለሽምግልና አመቻቺነት የሚላኩትም ሰዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከአማራ ወገን ለሽምግልና አመቻቺነት ወደ አፋር የጎሳ መሪ የሚላከው ሰው በሁለቱም ድንበርተኞች ዘንድ ስሙ በመልካም የሚነሳ፣ በዕድሜው የሸመገለ፣ ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት እና የመግባባት ችሎታው የተመሰገነ መሆን ይኖርበታል፡፡

የሽምግልና ጥያቄው የሚቀርበው ከአፋር ወገን ከሆነ ደግሞ አፋሮች የሚልኩት በዕድሜዋ የጠናች ሽማግሊት ሴት ነው፡፡ ሽማግሊቷም የእርቅ ጥሪውን የምታቀርበው ብዙ ሰዎች በአንዳች ምክንያት ተሰብስበው በሚታዩበት ሥፍራ ከሚገኝ ከፍ ካለ ኮረብታ ላይ ወጥታ ትደመጥ ዘንድ ጩኸት በማሰማት ነው፡፡ በልማዱ አንዲት የአፋር ሽማግሊት ሴት ወደ አማሮች አካባቢ ተጠግታ ሰው በተሰበሰበበት አካባቢ በቀን ጩኸት ካሰማች አመጣጧ ለሽምግልና መሆኑ ስለሚታወቅ የአከባቢው እውቅ ሰዎች እንድትቀርብ ምልክት ሰጥተው የመጣችበትን ሁኔታና መልዕክት ጠይቀው ይረዳሉ፡፡ ለሽምግልና ድርድር ማካሄጃ በአፋር በኩል የታሰበውን ዕለት፣ ቦታ እንዲሁም በሽምግልናው ላይ ስለሚገኙት ሰዎች ማንነት ማብራሪያ ትሰጣለች፡፡ በዚህም መሰረት አማሮቹ የጥፋት አድራሹን ጎሳ ለይተው ካወቁ እና እነርሱ የሚያውቁት የጎሳ መሪ በሽምግልና ላይ መገኘቱን ካረጋገጡ የሽምግልና ጥሪውንና ቀጠሮውን ይቀበላሉ፡፡

የሽምግልና ጥሪው ተቀባይነት ካገኘ በኋላም ሽምግልናውን ለማካሄድ ከአማራ ወገን የአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ወይ ባላባቶቹ እንዲሁም ከአፋር በኩል የጎሳ መሪው ወይም መሪዎቹ ተሰባስበው ሽምግልናው ይካሄዳል። በሽምግልናው ላይ ቀርበው የሚዋቀሱትም ከሁለቱም ወገኖች ግጭቱ የተቀሰቀሰበትን ሁኔታ የሚያወቁ ወይም በግጭቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ብዙውን ጊዜ በአፋርና በአማራ መካከል የሚከሰት ግጭት ከንብረት ውድመትና ዘረፋ ይልቅ የሕይወት ማጥፋትን ስለሚያስከትል እና ሕይወት በጠፋበትም ግጭት ገዳይ ለሽምግልና አይቀርብምና ነው። በዚህ አኳኋን ከሰመረ በኋላም ተሸማጋዮቹ ማለትም የሁለቱም ወገኖች ታዋቂ ሰዎች እርቅ ይፈፅማሉ።

የአማራ እና የአፋር ታዋቂ ሰዎች የእርቅ አፈፃፀምም የሚጠናቀቀው ከሁለቱ ወገኖች የተውጣጡት የየአካባቢዎቹ ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ተሰባስበው የግጭቱን አከሳሰት ከመረመሩና ተንኳሹን ከለዩ በኋላ ተጎጂ ለሚሉት ወገን የካሣ ክፍያ በመቁረጥ ነው። የካሣ ክፍያ አመዳደቡም ለቁስለኛ እስከ አምስት ሺህ፤ ለሙት እስከ አሥራ አምስት ሺህ ብር ካሣ ነው። ለሙት የሚከፈለውም የደም ካሣ ወይም ወጆ የሚከፈለውም በልማድ እንደ ሕግ ሆኖ ስለሚሰራበት መሆኑን ሼህ መሐመድ (14/09/2002 ዓ.ም.) አውግተውኛል።

ሼህ መሐመድ እንዳጫወቱኝ አፋርና ጅሌዎች ተጋጭተው የሰው ሕይወት ካለፈ እርቅ የሚያወርዱት ወጆ በመክፈል ነው። ወጆውም የሚከፈለው በከብት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሼክ መሐመድ እንዳስረዱኝ ሁለቱም ከብት አርቢዎች ስለሆኑ ነው። ነገር ግን ግጭቱ የተፈጠረው እና ሕይወት ያለፈው በአፋርና በአማራ መካከል ከሆነ የደም ካሣው /ወጆው የሚከፈለው በብር ነው። ሼክ መሐመድ እንደዘረዘሩልኝ አማራ ከጅሌም ጋር በነፍስ ግድያ ጉዳይ ቢሸማገል የወጆ አከፋፈሉ በገንዘብ ነው። ሼህ መሐመድ እንደሚሉት ይህም ሊሆን የቻለው አማራ አራሽ ስለሆነና ከብት በብዛት ስለሌለው የአፋርና የጅሌንም ከብት በካሣ ተቀብሎ በበረቱ አያስገባም። በጥቅሉ አማራ ለአፋር ከብት አይክስም፣ አይካስምም። አማራ እንስሳውን የሚሰጠው ለማስታመሚያ ብቻ ነው። ይኸውም ከራሱ ወገን ጋር ሲጋጭና ድብደባ ወይም አካል ማጉደል ከተፈጠረ እና ነገሩ ለሽማግሌ ከደረሰ ከእርቅ በፊት ለተጎጂ ወገን የማገገሚያ ሙክት መስጠት ነው ይላሉ ሼክ መሐመድ ሰይድ (14/09/2002)።

አማራ አፋር ሲገድል በእጁ ላይ ማልዲያ ያደርጋል፣ በአንገቱም ላይ ሻሚ ያስራል፣ በጠመንጃውም ላይ ጌጣጌጦች ያደርጋል፣ ጆሮውን ተበስቶም ሎቲ ያንጠለጥላል። ሲሞትም በገደለው ሰው ቁጥር ሽንበቆ ተቆርጦ ይጨፈርለታል፣ ኋላም በመቃብሩ ላይ ይጣልለታል።

በመጨረሻ ለማየት የምሞክረው በአማራ እና አፋር መካከል ግጭት የሚቀሰቅሱ ግጭቶችን፣ የግጭት መከላከያና መፍቻ እንዲሁም እርቅ ሥርዓት ሂደቶችን ነው። የአማራና የአፋር ሽማግሌዎች ከሰጡኝ ቃለ መጠይቅ እና ከተተኳሪ ቡድን ውይይት እንደተረዳሁት የእርስበርስም ሆነ የተጎራባች ጎሳዎች ግጭቶች የሚቀሰቀሱት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ክብር እና ማንነት መሰረት፣ በ "ወንድነት" ወግ፣ ልማድ ማስከበር እና ተረክ ፍሰት ምክንያት ነው። ስለዚህም ዋነኛው የግጭት መንሥዔ ከጥንት እስከ ዛሬ ከባህር ጠረፍ መቆጣጠር፣ መሬት እና ከመሬት የሚገኝ ሀብት ማለትም የእርሻ መሬት፣ ግጦሽ፣ ውኃ፣ ከማንነት እና ከእምነት ልዩነት ተረክ፣ ከጀግንንት ወይም "ወንድነት" የባህል ሥሪትነት እና ወግ ልማድነት ጋር የተሳሰረ ነው ለማለት ይቻላል።

በሁለቱ ድንበርተኛ ወረዳ ሕዝቦች መካከል የሚቀሰቀሰው ግጭትም በየጊዜው ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚፈታው በተለያዩ መንገድ ነው። ግጭቱ ተናጠላዊ ሲሆን ጊዜ በሰጠው አሸናፊነት እና ተበቃይነት ወይም አቻዊ ብቀላ ይታገሳል። ግጭቱ ጅምላዊነት ሲኖረው በድርድር ይረግባል። ይህንንም ድርድር የሚመሩት የአገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች ናቸው። እነዚህም የአገር ሽማግሌዎች እና የጎሳ መሪዎች ሙት እና ቁስለኛ ላስከተለ ግጭት የማገገሚያ እና የደም ካሣ ወይም ወጆ እንዲከፈል ያደርጋሉ። የካሣ ክፍያውም አፈፃፀም እንደተጋጪዎቹ ወገኖች የኑሮ መሰረት በከብትና በገንዘብ የሚከፈል ነው። በዚህም መሰረት አፋሮች እርስበርሳቸው ሲጋጩ በከብት፤ አማራ እርስበርሱም ሆነ ከአፋር ሲጋጭ በገንዘብ ይክሳል። ይካሣልም።

የቀወት አማሮችም ሆኑ የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ውስጣዊ ግጭቶቻቸውን በእርቅ ሲፈፅሙ እርቃቸውን ለማፅናት የተለያዩ የመኃላ ሥርዓቶችን ይፈፀማሉ። በዚህም መሰረት አፋሮች እርስበርሳቸው ሲታረቁ በተለይ ሕይወት የጠፋበት ግጭት ከሆነ ገና ከመጀመሪያው እርቁ እንዲሰምር የግመል እርድ ይፈፀማል። ከግድያ በመለስ ከሆነም ተጋጪዎቹን ወንዝ ውስጥ በመንከር፣ የከብት እበት በማስጨበጥ እና "ብከዳ

ይህን ይንሳኝ" በሚል፣ ከብት አርዶ በጋራ በመብላት፣ አንዳንድ ጊዜም በቅዱስ ቁርኣን መኃላ በመፈፀም ያሳርጋሉ።

የአማራና የአፋር እርቅ ሲደመደምም ብዙ ጊዜ ከብት በመጨበጥ፤ ከብት ተለዋውጦ ለምሳሌም የአማራውን አፋሩ የአፋሩን አማራው ጎን ለጎን አርደው በአንድ ሥፍራ በኩታ ገጠም በመብላት፣ ጠመንጃ በመራመድ፣ የመኃላ ሥርዓት ይፈፅማሉ።

# 9. የቀወት ወረዳ አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች ግጭት እና እርቅ አፈፃፀም ትንተና እና ትርጎማ

በድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች መካከል ለዘመናት (በዚህ ጥናት እንደተመለከተው ወደ ሰባት መቶ ሃምሳ ዓመታት ለሚጠጋ ዘመን) የዘለቀውን ግጭት ሥረ መንሥዔ ለማወቅ በጥናቱ ሂደት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሙሉ ማየት እና ጭምቅ ሐሳባቸውን መዞ ማውጣት፣ ጭምቅ ሐሳቦቹንም መተንተን እና መተርጎም ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ ግጭቶች መንሥዔዎች ለመምዘዝ እና ለማውጣት በልዩ ልዩ መልክ እና አጋጣሚ የሚባሉትን ቃል ታሪኮች፣ የጽሑፍ ታሪክ እንዲሁም ሥነቃሎች እንዲሁም የመረጃ ተባባሪዎቹን ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድኖቹን ውይይት ማዕከላዊ ሐሳብ መመልከት ይኖርብናል፡፡ እያንዳንዳቸውንም ከቅርብ ጊዜ ወደ ሩቅ የኋልዮሽ እንያቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከሁለቱ ሕዝቦች ቃል ታሪክም ሆነ ጽሑፍ ታሪክ (በነገራችን ላይ ጽሑፍ ታሪኩም በፎክሎር የተመላ ነው) እንደምንረዳው ጥንታዊ ክርስቲያን ገገሮች እስከ ቀይ ባህር በመዝለቅ እና በመቆጣጠር ወጪ እና ገቢ ንግድ ለማካሄድ ሲሹ በአንፃሩ እስላም የአፋር ሱልጣኖች እና አሚሮችም የቀይ ባህርን ጠረፍ ተከትለው እንደመስፈራቸው የአካባቢውን ወጪ እና ገቢ ንግድ በራሳቸው ቁጥጥር ሥር ማድረግ ይፈልጉ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በሁለቱ ሕዝቦች ገገሮች ዘንድ የጥቅም ግጭት ተጭሯል፡፡ ስለዚህም የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት የተጀመረው ገገሮቻቸው ቀይ ባህርን በበላይነት ለመቆጣጠር በነበራቸው የግዛት የበላይነት እና የሀብት ወይም የጥቅም ማካበት ፍላጎት ሳቢያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የ "አማሮች" እና አፋሮች ገገሮች የጥንታዊ ግጭታቸው አንድ መነሻ የቀይ ባህርን የንግድ መስመር በበላይነት መቆጣጠር ይሁን እንጂ ገገሮቹ የግጭት ሰበብ አድርገው ወደ ተገገሮቻቸው ያወረዱት እና ያሰረፁት የሕዝቡን የመረዳት አቅም እና ስስ ብልቱን አይተው በቀላሉ ጅምላ ተከታይ እና ተዋጊ ሊያስገኝላቸው በሚችል፣

አመክንዮ በማይጠይቅ ለስሜት ቅርብ በሆነ የኃይማኖት[27] ልዩነት ላይ የተመሰረተ ግጭት አድርገው ነው። ይሄውም ግጭቱ በክርስትና እና በእስልምና ኃይማኖት ልዩነት ሳቢያ የመጣ አድርገው መሳላቸው እና መተረካቸው ነው። ይህም ሁለቱም ሕዝቦች የራሳቸው ባልሆኑ ከውጪ በገቡ እና በተናኙ ሕዝባዊ ኃይማኖቶች ባህሎች /ሥልጣኔዎች/ ሳቢያ ማለትም በተረክ ልዩነት እና ተረቴ ይበልጣል ንትርክ ውስጥ መግባታቸውን ነው የሚያሳየው። ስለዚህም ግጭታቸው ባህል /ሥልጣኔ/ ፉክክር ወለድ ግጭት ሆኗል ማለት ይቻላል። ይህንንም ዛሬ ቀወቶች እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች "አማራ" እና "እስላም ነን" እየተባባሉ፣ ጎራ ለይተው በማያባራ ግጭት ውስጥ ከመሆናቸው መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም ዛሬ ድንበርተኞቹ ነዋሪዎች "አማራ እና እስላም ነን" የሚለውን መፈራረጅ ወይም "እኛነት" እና "እነሱነት" ከምንም አላመጡትም፣ አልተከሉትም፣ አላደበሩትምም። ይህም ማለት ደግሞ በመጀመሪያ ተጨባጭ የነበረው የግጭት መነሻው ቀስ በቀስ ወደ ኢ-ተጨባጭ የግጭት ማጠናከሪያ እና ማባባሻ ማለትም የኃይማኖት ልዩነት እንደተለወጠ ይጠቁመናል። ገገርዎቹ ተጨባጭ ግጭቱን ወደ ኢ-ተጨባጭ ግጭት የለወጡትም በሕዝባቸው ዘንድ የማይታረቅ ዓይነት ልዩነት ፈጥረው እራሳቸውንም የኦርቶዶክስ ክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖት ቀናዒ ጠባቂ አድርገው ለማሳየት በዚያም ላይ በመመስረት በበላይነት ለመዝለቅ እና ጥቅማቸውንም ለማረጋገጥ አስልተው ዘወትር ማዋጋትን ይሆነን ብለው በመያዛቸው እንደሆነ ሚዛን ደፍቶ መገመት ይቻላል። በዚህም ላይ በመመሥረት ዛሬ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች በመካከላቸው ተጨባጭ የግጭት ሰበብ በሌለበትም የሚገዳደሉት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው እና ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ተረክ ምክንያት እንደሆነ አስረግጦ መናገር ይቻላል። ምክንያቱም ተረክ የሕይወታቸው አካል፣ የሕይወት ዘገባቸው እና ሰነዳቸው እንደመሆኑ በልዩ ልዩ መልክ የሁለቱን ሕዝቦች የፀበኝነት ሁኔታ የሰነዱት ተረኮችም

[27] ኃይማኖት አመክንዮ የሌለው፣ የማይመረመር፣ የማይረጋገጥ፣ በተለይም በድህረ ዘመናዊነት ደግሞ የበዛ፣ የተለጠጠ፣ ልል እና የይምሰል ፍፁም ስሁት ንቃተ ኅሊና /false conciousness/ እንደመሆኑ የተዛባ የሕይወት ነፀብራቅ ነው። ይህንንም ስሁት ንቃተ ኅሊና ወይም አስተሳሰብ ገገርዎች ለኃይል ማደርጃያነት፣ ለጥቅም ማስከበሪያነት እና የሚገዙትንም ኅብረተሰብ አስተሳሰብ ለመስለቢያነት ወይም ለመግሪያነት ምናልባትም ማደንዛገሮነት እንዲያም ሲል ለማቧደኛነት መጠቀም የጀመሩት ከጥንት ጀምሮ ይመስላል። በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ገና የሥራ ክፍፍል (አራሽነት፣ አርብቶ አደርነት፣ ሰባኪነት፣ ወታደርነት፣ የዕደ ጥበብ ሙያተኝነት ወዘተ) እንደተጀመረ። እዚህም የምናየው የዚህኑ አስተሳሰብ እና አድራጎት መዋቅራዊ ቀጣይነትና ዝልቀት ነው።

አውዳቸውን እየጠበቁ የሚፈፀሙ በመሆናቸውም ግጭቱም እነዚህኑ ሁነቶች ተከትሎ እንዲከሰት እና እንዲያድ አድርጎታል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሐሳብ ጋር አያይዞም በኢትዮጵያ የጥቅም እና የሥልጣን ተቀናቃኝን በኃይማኖት እየለዩ የመፈረጅ ልማድም ከጥንት ጀምሮ የተለመደ እና የቀጠለም እንደሆነም ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በጥንቱ የአክሱም ዘመነ መንግሥት የጥቅም እና የሥልጣን ተፎካካሪዎች አሕዛብ እና አሪታውያን /እስራኤላውያን/፣ በመካከለኛው ዘመን ደግሞ ፈለሻ እና ወንጌላውያን /ኢየሱሳዊያን/፣ ፀጋ (ሦስት ልደት) እና ቅባት (ሁለት ልደት) በሚል እየተሻኮቱ እና እየተፈራረጁ ሲተጋገሉ ኖረዋል፡፡ ዛሬም በብሔር ቅርፅ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ቅንቀና ይስተዋላል፡፡ ይህም አቦዳደን ብዙውን ጊዜ ክፍለ ሀገራዊ ቅርፅ የነበረው እና ያለው ነው፡፡

ለምሳሌም ያህል የፀጋ (ሦስትት ልደት) እና የቅባት (ሁለት ልደት) ተዋህዶ ክርስትና አንጃ እንኳን ብንመለከት ክፍለ ሀገራዊ ገፅታ እንደነበረው እና እንዳለውም እንገነዘባለን፡፡ ምክንያቱም ፀጋ (ሦስትት ልደት) በሸዋ፣ ቅባት (ሁለት ልደት) በጎጃም፣ እንዲሁም የዚሁ የቅባት ተቀፅላ ካራ በሚል በትግራይ ይቀነቀኑ እንደነበር እና ተቀባይነትም እንደነበራቸው፣ ዛሬም ቢሆን አስተሳሰቦቹ ጨርሰው እንዳልከሰሙ የሚታወቅ ነገር ነው፡፡ ይህም የመጨረሻው ክፍለ ሀገራዊ ገፅታ መያዝ እና አቧደኝነት በቀደምቶቹም ውስጥ ይሄው ልማድ እንደነበረ አረጋጋጭ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ኃይማኖትና መንግሥት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ልዩነት ስላልነበራቸው ገገርዎቹ የተነሱባቸው አካባቢዎች የኃይማኖት ተቋማት ድጋፍ እንዳይለያቸው እና የመጡበትም አካባቢ አስተምህሮት የበላይነት እንዲይዝ በመሻታቸው እና በመፈራረጅ ተከታዮቻቸውን ያበዙ እንደነበር፣ በጦርነት የበላይነት ማግኘትም ለገገርነት ያበቃ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ከዚህም በመነሳት በኋላም የቀጠለው እና "አማራ" እና "እስላም" የሚለው የተተከለው በዚሁ ባህላዊ ወግ ልማድ እና ሥልት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህም በእምነት መፈራረጅ እና ተከታይንም እምነትህን የሚነካ ጠላት መጣብህ እያሉ ማቧደን ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ፣ ዛሬም የቀጠለ ልማድ መሆኑን በሌሎችም ኢ-ተጨባጭ ፍረጃዊ ውርሶች ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው የ "አማራነት" ፍረጃ ከድንበርተኞቹ ቀወቶች እና ስሙሮቢ ገለአሎዎች ነዋሪዎችም በላይ የዘለቀ እና የሰፋ የእኛነት እና ሌላነት መፈራረጃ መሣሪያ መሆኑን ነው፡፡

በተለይ በኢትዮጵያ የክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖቶች ተከታይ ገገር መደቦች የሥልጣን እና የጥቅም ግጭታቸውን የክርስቲያን እና የእስላም ግጭት አድርገው መፈራረጃቸው ደግሞ በሂደት አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን ዓለማቀፋዊ ገፅታ ጭምር እየያዘ መምጣቱም አይዘነጋም፡፡ ለተከታታይ ዘመናት የዘለቀው የ "አማሮች" እና የይፋት እስላሞች የበላይነት ፉክክር በከፍተኛ ደረጃ የታየውም ኢብን ኢብራሂም አህመድ አሸንፈው አገሪቱን ለአሥራ አምስት ዓመታት ለመግዛት በበቁበት፣ አፄ ልብነ ድንግል ለሽንፈት በተዳረጉበት እንዲሁም ኋላ ላይ አፄ ገላውዴዎስ በኢብን ኢብራሂም አህመድ ላይ በተቀዳጁት ድል እንደገናም በተከታታዩ ጦርነት ሕይታቸውን ባጡበት ክስተት ሁሉ ነው፡፡ እዚህም ላይ "አማሮቹ" ወደ ፖርቹጋል፣ እስላሞቹ ወደ ቱርክ የድጋፍ ጥያቄ ያቀረቡበትን፣ የተደረገላቸውንም እርዳታ ሁሉ አብሮ ያጤኗል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው እና በጥናቱም ሂደት እንደታየው በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎዎች መካከል ወደ ሰባት መቶ ሃምሳ ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ በዘለቀው አለመግባባት፣ ቅራኔ እና ግጭት ሂደት ውስጥ እስከ አፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ማለት ይቻላል የየዘመኑ መንግሥታት ዋነኞቹ የግጭቱ አራጋቢዎች ነበሩ ለማለት ያስደፍራል፡፡ ምክንያቱም የክርስቲያኑ /አማራ/ እና የአፋሩ /እስላሙ/ ገገር መደቦች የግጭቱ ዋነኛ ተዋናዮች እየሆኑ አልፈዋል፡፡ ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ ግን የነበረው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በግዛት ውስጥ ሰላም እና መረጋጋትን የማስፈን ጥረት አካል ተደርጎ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም በዳግማዊ አፄ ምኒልክ፣ በአፄ ኃለሥላሴ፣ በደርግና አሁንም በኢሕአዴግ መንግሥታቱ በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ወቅት ጣልቃ የሚገቡት ግጭቱ የበረታ ሲሆን ነው፡፡ ይህም ጥረት የሁለቱን ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ለዘለቄታውም ባይሆን ለጊዜው ለማርገብ ያህል ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በጥናቱ ሂደት እንደታየው የአማራ እና የአፋር ግጭት በተለያዩ ዘመነ መንግሥታት በቋሚነት ቀጥሎ "አማራ እና እስላም ነን"፣ "እስላምና አማራ ነን" የሚለውን መፈራረጅ ፅድቅ አድርጎታል፡፡ ድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮችም ከላይ እንደተገለፀው ይህንኑ በተረክነት ይዘውታል፡፡ በዚሁም መሰረት ደግሞ የተረኩ ሰለባዎች እና ወራሲዎች ሆነዋል፡፡ ስለዚህም ለዚህ ዘመን የቀወት አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ግጭት አንዱ መነሻ ከየቀደምት ገገርዎቻቸው ያገኙት የተረክ ውርስ መኖሩ እና በሕይወት ዘመናቸውም ያዳበሩት የግጭት ባህል እና ባህርይ

ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ሕዝቦች የመበቃቀል ማለትም ጥቃትን በአቻዊነት የመመለስ እና የመወጣት ልምድ እንዲያዳብሩ ዳርጓቸዋል፡፡ በተለይ በዚህ ረገድ ሰሙ-ሮቢ ገለአሎዎች አፋርን በጠቅላላው የሚገልፅ ምሳሌም አላቸው፡፡

የሚወደድ አገር አላት፣

የማይወደድ ታሪክ አላት፣

ምን ጊዜም በዓይኔ ቁራኛ ያያታል ጠላት፡፡

ሁለተኛው የሁለቱ ሕዝቦች የጥንታዊ ግጭታቸው መነሻ ደግሞ ምንም እንኳን ቃላዊ እና ጽሑፋዊ ታሪኮቻቸው በሁሉም መልክ ተጣጣሚነት እና ተደጋጋሪነት ባይኖራቸውም እንኳን ሁለቱም ሕዝቦች እራሳቸውን ከተለያዩ ዝርያ እና አቅጣጫ የመጡ አድርገው በመቁጠራቸው "አማራ አማራ ነው" እና "አፋር አፋር ነው" ብለው ተዋግነዋል ወይም ተቧድነዋል፡፡ የሁለቱ ሕዝቦች መቧደንም በየፊናቸው የራሳቸውን ማንነት መለዮዎች እንዲፈጥሩ እና እንዲያዳብሩ ዳርጓቸዋል፡፡ እንደሚታወቀው ማንነቶች በውስብስብ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ትስስሮች ምክንያት ህልው የሚሆኑ ሥሪቶች ናቸው፡፡ እነዚሁም ሁነቶች ደግሞ ከወግ፣ ከሚት፣ ከታሪክ፣ እና ከአፈ ታሪክ ጋር የተቆራኙ ስለሚሆኑ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ልዩነትን አጠንክረው ሊስሉ፣ በሁለቱም ሕዝቦችም ዘንድ ደግሞ ቡድናዊ ጋርዮሾች ሆነው አማራ እና አፋር የሚለውን ልዩነት ሊያስቀጥሉ ችለዋል፡፡ በሌላ በኩልም ምንም እንኳን ማንነቶች ዘላለማዊነት ወይም ዘላቂነት እና ርጉዕነት ባይኖራቸውም በመኖር ሂደት ማቧደኛዎች እና መከፋፈያዎች በመሆናቸው የግጭት ምንጭ እና መሸጋገሪያዎች ሆነው ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡

በሁለቱም ሕዝቦች የቃል እና የጽሑፍ ታሪክ ውስጥ እንደታየውም ሁለቱም ሕዝቦች ወደ አካባቢው የዘለቁት በተለያዩ ዘመን፣ከተለያዩ አካባቢ ነው፡፡ ሁለቱም ሕዝቦች በአካባቢውም ላይ ቀዳሚ ነዋሪ " ነባር " እና ባለቤት "እኔ ነኝ"፤ "እኔ ነኝ " ባዮች ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ አንደኛቸው እራሱን ቀዳሚ ሌላኛቸውን ተከታይ ወይም "መጤ" አድርጎ ተመልካች ነው፡፡ ለአብነትም ቀወቶች እራሳቸውን ነባር፣ የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮችን መጤ አድርገው ያያሉ፣ ይቆጥራሉ፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን ግጥሞች እናገኛለን፡፡

አገራችን ይፋት ለኛ መቼ አነሰን፣

አላስበላ አለ እንጂ መጭ እየወረሰን፡፡

ይህም ዓይነቱ አስተሳሰብ በቀወቶች እና በሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች መካከል የነባርነት እና የመጤነት አመለካከት መኖሩን አመልካች ነው፡፡ ምክንያቱም ታሪክ እንደሚነግረን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዛሬ መገኛ ሥፍራዎቻውን የያዟቸው በየጊዜው ባጋጠመ ድርቅ እና በተካሄደ ጦርነት ሳቢያ እየፈለሱ ነው፡፡ ድርቁን እንኳን እንደ አንድ አብነት ብንመለከት ኢትዮጵያ በየአሥርት ዓመቱ በድርቅ ትመታለች፡፡ በየአሥር ዓመቱ የሚመላለሰው ከፍተኛ ድርቅ፣ የሕዝቡም ብዛት እየጨመረ መሄድ፣ የተፈጥሮ ሀብቱም መመናመኑ፣ በረሃማነትም መጨመሩ ሁሉ ተደማምረው በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ነዋሪዎች ሰላምና መረጋጋት ላይ የራሳቸውን ጎጂ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አልቀረም፡፡ ሁለቱ ወረዳዎች የሚዋሰኑበት አካባቢ መሬት ልምላሜም ድርቅም ይፈራረቁበታል፡፡ ስለዚህም በእርሻም ሆነ በእንስሳት እርባታ ተረጋግቶ ለመተዳደር አስቸጋሪነቱ ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም ድርቁ በበረታበት ወቅት አራሾቹ ለምነት ያላቸውን የወንዝ ተፋሰሶች ለማልማት፣ በከፊል አራሽነት እና አርብቶ አደርነትም የሚተዳደሩት እንዲሁ ያሉትን ውሱን ርጥበታማ ሥፍራዎች ለመቆጣጠር ይሻማሉ፡፡

ሦስተኛው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት መንሥዔ ሁለቱ ሕዝቦች በኃይማኖት እና በዝርያ አመጣጥ የተለያዩ እንደመሆናቸው "የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ" ፉክክር መፍጠራቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ፉክክራቸውን በጦርነት፣ በዘረፋ፣ በማጋዝ፣ በማስገበር የበላይነት ማረጋገጥ ስለሚሹ በየዘመኑ አውዳሚ ጦርነቶችን ማካሄዳቸውንም ልብ ይሏል፡፡ የቀወቶችም አንድ የሽላሎ ግጥም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡ ግጥሙ እንዲህ የሚል ነው፡፡

ታረሰ አሉ ጨፋ መሬቱ ገራና፣
ታረሱ አሉ ፉርሲ መሬቱ ገራና፣
ታረሱ አሉ ጨኖ መሬቱ ገራና፣
ታረሱ አሉ አዋሽ መሬቱ ገራና፣
ይፋት ብቻ ቀረ ጋሬጣው[28] በዛና፡፡

[28] በነገራችን ላይ በዚህ የሽላሎ ግጥም ውስጥ ምልክቱ ያለበትን ቃል እሾሁ እና ድንጋዩ እያሉም እንደሚለዋውጡት ተረድቻለሁ፡፡

ከግጥሙ መልዕክት እንደምንረዳው ጨፋ እና አዋሽ በሚሉ የተገለፁት በአመዛኙ የእስላሞች መኖሪያዎች ናቸው፡፡ ይፋት ደግሞ አማሮች (ክርስቲያኖች) መገኛ ምድር ነው፡፡

ምክንያቱም ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንዳረጋገጡት እስከ ዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል በፈረስ የታገዘ ወራራ ይካሄድ ነበር፡፡ ከዚያም ወዲህ መጠኑ ቢቀንስም ግጭቱ እንዳለ ነው፡፡ ይሄም ሁኔታ ደግሞ የዘረፋ እና ሰው የመግደል ልማድን አበረታቷል፡፡ ይህም በበኩሉ የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት እንዳያባራ አድርጎታል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ሕዝቦች መበቃቀል እና መገዳደልን የወንድነት መግለጫ አድርገው፣ አወድሰው እና የማህራዊ ክብር መጎናፀፊያ አድርገው እየተረኩ መቀጠላቸው ነው፡፡ይህም ሁኔታ ጦረኝነትን የወንድነት፣ የጅግንነት መግለጫ፣ የክብር ማግኛ መሰረት አድርገው እንዲያዩ፣ የጦር መሣሪያ እንዳይለያቸው፣ የጦር መሣሪያንም እንደ መለዮ አርማነት ጭምር እንዲያመልኩ እና እንደ ባህልም እንዲይዙ ዳርጓቸዋል፡፡

በጥናቱ መረጃ ውስጥ እንደታየውም አንድ አማራ ሲገደል አንድ አፋር፣ ሁለት አማራ ሲገደል ሁለት አፋር መግደል፣ አንድ አማራ ሲሰለብ አንድ አፋር መስለብ ወይም በተቃራኒው መፈፀም ወዘተ ወንድነትን በአቻዊነት ማሳየት ተደርጎ ይታያል፡፡ አቻዊነት መኖሩም ግጭቱ ዑደታዊነት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ይህም በአቻዊነት ሰው መግደል ቡለቱም ወገኖች ዘንድ በጀግንነት ያስፈርጃል፣ ያስሞግሳል፣ በአደባባይም በስምሪትም ለመናገርም፣ ለመመገብም፣ ለመከበር እና ለመሾምም ቅድሚያ ያስጣል፡፡

አራተኛው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ቀጣይነት ምክንያት የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ታሪካዊ እና ማህበራዊ ግንኙነታቸው የሻከረ በመሆኑ ነው፡፡ በአፍ ታሪኩም ሆነ በጽሑፍ ታሪኩ እንደታየው ሁለቱ ሕዝቦች ለዘመናት በፀብ እና በጦርነት ኖረዋል፡፡ በፀበኝነት በመኖራቸውም ደግሞ ይህንኑ የግጭት ታሪካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ በተረክነት አስተላልፍዋል፣ እያስተላለፉም ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ማህበራዊ ግንኙነት መመሥረቻ እና ማጠናከሪ መንገድ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን ጥንታዊያኑ የሁለቱ ሕዝቦች ገገሮች አልፎ አልፎ ፖለቲካዊ ጋብቻ በመፈፀም ለመተቃቀፍ መሞከራቸውን ታሪክ ቢነግረንም የሚበዛው የግጭት ታሪካቸው ነው፡፡ በገገሮቹ መካከል ተፈፅመዋል ከሚባሉት ፖለቲካዊ ጋብቻዎች መካከል እንደ አንድ ማስረጃ የሚቆጠረውም አፄ ልብነ ድንግል የአፋር ባላባት ተወላጅ የሆኑት እቴጌ

ሰብለወንጌልን አግብተው አፄ ገላውዴዎስን መውለዳቸው ነው፡፡ ተገገርዎቹ ደግሞ በዚህም አይተሳሰሩም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ባለው ዘመንም ቢሆን በአንዳንድ አስገዳጅ ሁኔታዎች ማለትም በጦርነት በመመራረክ፣ አካባያዊ ሥልጣንን በማስጠበቅ እና ታማኝነትን በማረጋገጥ ረገድ አልፎ አልፎ መጎዳኘቶች ቢኖሩም አማሮች እና አፋሮች ጋብቻን አቅደው እንደተቋም አይመሰርቱም፣ አማሮች በምርኮ ያገኟቸውን ሴቶች የሚያገቡ ቢሆኑም ኃይማኖት ለውጠው የሚኖሩ ናቸው፡፡ በአፋሮቹም በኩል እጅግ አልፎ አልፎ የሚፈፀም መመማገጥ እና አብሮ መኖር ቢኖር ሁኔታው ከአማሮቹ የተለየ አይደለም፡፡ ስለዚህ ሴቶች በሆነ አጋጣሚ ወደ አማሮችም ሆነ አፋሮች ወንዶች ከወደቁ ኃይማኖታቸውን ለውጠው እንዲኖሩ የሚገደዱ ናቸው፡፡

አሁንም ማህበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ አማሮች እና አፋሮች አብረው ከአንድ ማዕድ አይቋደሱም፣ ጉዲፈቻ አይሰጣጡም፣ ጡት አባትነትና እናትነት አይያያዙም፡፡ ባህላዊ መድኃኒት አይጠይቅም፣ አይሰጣጡም፣ አንዱ ወደ አንደኛው ሂዶ መንፈሳዊ ፈውስ አይጠይቅም፣ አያስጠነቁልም፡፡

አምስተኛው የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት ምክንያት ሁለቱም ሕዝቦች ግጭትን እና የግጭት ማክረሪያ መሣሪያዎችን በአዎንታዊነት የመመልከት ንዕረተ ዓለም ወይም ዓለማዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቀወት እና ሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ድንበርተኛ ሕዝቦች ንዕረተ ዓለም ወይም ዓለማዊ አመለካከት ውስጥ ወንድነትን ማረጋገጥ፣ መግለፅ እና ማፅናት በዚህም ዝናን ማግኘት፣ ገዳይነትን መናኘት፣ ማሞገስና በውጤቱም ወይም ግቡም መከበር ማለትም ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቀዳሚነትን ማግኘት ግቡዕ ተደርጎ ይታያል፡፡ ስለዚህም ግጭት ውስጥ ገብቶ ከግጭቱ ውስጥ በአሸናፊነት መውጣት የሚያስገኘው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ እና እሴትም አለ፡፡ እነዚህንም አስተሳሰቦች ማለትም ግጭትን በአዎንታዊነት ማየት፣ የተጋጪንም ነፍስ ማጥፋት ከዚያም የገዳይነትን ሞገስ መላበስ መቻልን ግቡዕና ቅቡል አድርጎ መውሰድ የሁለቱ ሕዝቦች ንዕረተ ዓለም፣ እሴትና የሕይወት ግብ መሆን መቻላቸውንም ከግብሮቻቸው እና ግብሮቻቸው ከሚገለፁባቸው ሥነቃሎቻቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የጀግንነት፣ የገዳይነትና የወንድነት ገላጭ ንዕረተ ዓላማዊ እና ዝንባሌ እንዲሁም ፋይዳ አዎንታዊነት አመለካቾች የሆኑ ሥነ ቃሎች በሁለቱም ሕዝቦች የሥነ ቃል ሀብት ውስጥ ተዘርተው ይገኛሉና፡፡

በተለይ የአፋር ወጣቶች ወንድ ገድለው የብልት ሰለባ ካሣዩ እጮኛ ለማግኘትም እድጉን ተመራጮች መሆናቸው፣ አማሮችም አቻዊ የብልት ሰለባ ሲፈፅሙ ጠላታቸውን በመበቀላቸው ቅቤ የመቀባት ሥርዓት የሚፈፀምላቸው መሆኑ እና "የተቀባ" መሰኘታቸው እንደገናም ከሁለቱም ወገን ገዳዮች በገዳይነታቸው ከሌሎችም ለመለየት በእጃቸውም ጠመንጃዎቻቸውም ላይ አምባር፣ መዳብ፣ የፍየል ጅራት ወዘተ የማሰር ልማድ ያላቸው መሆናቸው ገዳይነት ወንድነት፤ ወንድነትም ገዳይነት መሆኑን በማህበራዊ እሴትነት መትከያዎች እና ማህዘቢያዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ሁሉ እንግዲህ የፀበኝነት ማስቀጠያዎች ናቸው፡፡ በጥናቱም ውስጥ እንደተወሳው እንኳንስ ሰው መግደል አውሬም መግደል ያስከብራል፡፡ እንደገናም ደግሞ እንኳንስ ገዳይ የገዳይም ሚስት ከወንዝ ውኃ በቅድሚያ ለመቅዳት ቅድሚያ ታገኛለች፡፡ የገዳይ ፈረሱ እና እንስሳቱ እንኳን ካልገደሉ ሰዎች ፈረስ እና እንስሳት በቅድሚያ እንዲጠጡ ቅድሚያ ያሰጣል፡፡

ስለዚህም እነዚህ ሁሉ የግጭት አፈ-ታሪኮች፣ ሽለላዎች፣ ፉከራዎች፣ የሰርግ እና የለቅሶ ግጥሞች ወይም ሙሾዎች፣ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ የመቀባትና የመቀደም ሥርዓቶች ወዘተ በልማድነት በመያዛቸው፣ የሕይወትም መዘከሪያ እና መሰነጃ በመሆናቸው እነዚህም ሁነቶች ደግሞ ማቆሚያና ማባሪያም የሌላቸው በመሆናቸው ሰው መግደልን እያሞካሹ ግጭትን በማኅበረሰቦቹ ውስጥ ለማስረፅ እና ለማስተላለፍ እና የጦረኝነት መንፈስ እየተወደሰ ቀጣይነት እንዲኖረው አገልግለዋል፡፡ መገዳደልንም አበረታተዋል፡፡

በየትኛውም ዓለም እና ሕዝብ ታሪክ እንደሆነው ሁሉ በኢትዮጵያም ታሪክ ውስጥ ጦረኝነት ጀግና የሚያሰኝ እና የሚያስወድስ፣ በጉጉት የሚገቡበት ሙያ፣ ክብር፣ ሽልማት ማግኛ፣ ሹመት እና ማዕረግ መጎናፀፊያ ሙያና ተግባር ሆኖ ኖሯል፡፡ በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳ ሕዝቦችም ዘንድ ይኸው ልማድ ቀጥሎ ዛሬም ከራስ ወገን እና አካባቢ ያልሆነን በአንፃራዊ ደረጃም ሌላ የሚሰኝ ወገንን ሰው መግደል ለቤተ ዘመድ መመኪያ፣ ሚስት ለማግባት ማማረጫ መስፈርትነት፣ ለፀጉር ለማጎፈሪያ እና መቀቢያ፣ መፎከሪያ እና የክብር መጎናፀፊያ ሆኖ ይታያል፡፡ ስለዚህም ግጭቱ እነዚህ እሴቶች ተከብረው እስካስከበሩ ድረስ ጊዜ እየለየ የሚመላለስ እና የሚዘልቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪዎች የባህል ሥሪት እና አስተሳሰብ ውስጥ ጦረኝነትን መናፈቅ፣ ማወደስ፣ እራስንም ለጦርነት የተፈጠሩ አድርጎ የመቁጠር፣ የጦርነት ሰሪ እና ፈጣሪ አድርጎ የመታበይ ዝንባሌ እንዳለ፤ ይህም ሁኔታ በቃለ መጠይቅም፣ በሥነቃልም ውስጥ ታይቷል። በቁሳዊ ሀብት ውርስ እና ቅርስም አንፃር በሁለቱም ሕዝቦች ዘንድ የጦር መሣሪያ አፍቅሮት አለ። ምክንያቱም ሁለቱም ሕዝቦች ለወንድነት ወይም ጀግንነት ማግኛ የጦር መሣሪያ ከፍተኛ ፍቅር ስላላቸው ለአቅመ አዳም ለደረሱ ልጆቻቸቸው ጩቤ፣ ሽጉጥ ጠመንጃ መያዝ እና አጠቃቀሙንም ያስተምራሉ። ይሄም ሁሉ አፍቅሮተ ፀብ እና ፀበኝነት ወይም ጦረኝነት የሚያስገኘው የተተከለ እሴት ስላለ ነው። ከጦረኝነት ማትረፍ፣ በጦረኝነት ክብር መጎናፀፍ። የጦር መሣሪያ ፍቅር እና አምልኮ ሁኔታ በተራዛሚም ሲታይ በፖለቲካ ፓርቲ እና በክልል ሰንደቅ ዓላማ ላይ በአርማነት የማስቀመጥ ሁኔታ ሁሉ ይታያል። ለዚህም በምሳሌነት የአፋር ባህላዊ የጦር መሣሪያ የሆነው ጊሌ በአፋር ክልል ሰንደቅ ዓላማ ላይ ተቀልሞ ይታያል። ይህም ሁሉ እንግዲህ ማህበረሰብ የባህል ውጤትነቱን አመላካች ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ሰው ባህሉን ቢፈጥረውም፤ ባህሉም እንደገና መልሶ ሰውን ይፈጥረዋል፣ ይገዛዋልና። ሰው ራሱ በፈጠረው ሁኔታ ማመኑ የተለመደ ነውና።

በጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደት እንደታየው ስድስተኛው የሑለቱ ሕዝቦች ግጭት መንሥዔ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ሽሚያ ንቅናቄ ነው። ሁለቱም ድንበርተኛ ሕዝቦች ከአሁን እና ከቅርብ ጊዜ አኳያ ሲታይ በተለይ በድርቅ እና በእርሻ መሬት ጥበት ወቅት ይንቀሳቀሳሉ። በእንስሳት የሚተዳደሩት የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮች ለምነት ወዳላቸው እና በቀወቶች ወደተያዙ ሥፍራዎች ያመራሉ። አራሾቹ ቀወቶችም የሰፈሩበት መሬት ሲጠባቸው ወደ አፋሮቹ ይዞታ ዘልቀው ይገባሉ። እንደገናም ደግሞ አፋሮቹ ቀወቶቹ በቋሚነት ወደሰፈሩበት አካባቢ ሲመጡ እና ሲወሩ ይመክታሉ። ከዚህም በተጨማሪ ርጥበታማ ወይም ውኃ ገብ መሬትን ለመቆጣጠር ሲሉ ይጋጫሉ። ከዚህ ነባራዊ እና ተጨባጭ ሁኔታ አንፃርም የቀወት አማሮች እና የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ግጭት ሰበብ የውኃ፣ የግጦሽ ሣር፣ የእርሻ መሬት፣ የደን እና የዱር አራዊት ሀብት ተሻምቶ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ይህም የተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚነት ፍላጎት ከሁለቱ ሕዝቦች መሰረታዊ የሕይወት መግፊያ ማለትም መኖሪያ ሁኔታ ጋር የተቆራኘ ነው። መሬት፣ የግጦሽ ሣር እንዲሁም የዱር እንስሳት ለአደን የሚፈለጉትም ውኃ እስካለ ድረስ ነው። እናም እነዚህም የእርሻ መሬት፣ የግጦሽ ሣር፣ የዱር እንስሳት እና ውኃ

በአንድነት ውኃ ተብለው ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ምክንያም ሁለቱም የሕይወት ምንጭ ናቸው፡፡ ሕይወትም በብዛት የእርጥበት ወይም የፈሳሽ ውጤት ነው፡፡

ስለዚህም የቀወት አማሮች እና የሰሙ-ሮቢ ገለአሎ አፋሮች ግጭት ከድርቅ ጋር የተያያዘ ይሁን እንጂ በአንፃሩም ደግሞ ጥጋብ እንደዚሁ የቂም በቀል መወጫ መሆኑ በጥናቱ ታይቷል፡፡ በጥናቱ መረጃ እንደታው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ከድርቅ በተጨማሪም ከጥጋብ ጋርም ይያያዛል፡፡ በዚህም መሰረት በድርቅ ወቅት የተፈጥሮ ሀብት ዕጥረትና ሽሚያ፤ በጥጋብ ወቅት ደግሞ ያለፈ ቂም በቀል የመወጣት ፍላጎት ለግጭት ይዳርጋቸዋል፡፡ በጥጋብ እና በድርቅ ዘመን የሚከሰተውም ግጭት ከሌላው ማዕከላዊ ዘመን ጊዜ ግጭት ሁሉ ያይላል፡፡ በመሆኑም በተለይ በግንቦት፣ በሰኔና በመስከረም ወራት በተናጠል እና በቡድን መገዳደል፣ንብረት መዘራረፍ፣ ንብረት እና ቤተ-እምነት የማቃጠል ክስተቶች ያጋጥማሉ፡፡ ጅምላ ግጭትም የሚበዛው ከግንቦት እስከ መስከረም ባለው ጊዜ ነው፡፡ ግጭቱ በመከሰቻ ጊዜ ሲታይም ምልልስ አለው፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት በዘላቂነት ሊፈታ ያልቻለበትን ሁኔታ ለመመልከት እና ከላይ እንደተባለውም ግጭቱ ዑደታዊ የሆነበትን ምክንያት ለመግለፅ ይሞከራል፡፡ በመጀመሪያም የሁለቱን ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭት አፈታት እንመልከት፡፡

የቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭቶቻቸውን ብዙውን ጊዜ የሚፈቱት በሽምግልና ሥርዓት መሆኑን በጥናቱ ሂደት ከተሰባሰቡ መረጃዎች ተመልክተናል፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚያሰኘውም ቀወቶች የእርስበርስ መለስተኛ ግጭቶቻቸውንም ሆነ የነፍስ ግድያን በሽምግልና ለመፍታት የሚሞክሩ ቢሆኑም አልፎ አልፎ ወደ ዘመናዊ ፍርድ ቤቶችም ስለሚያመሩ ነው፡፡

ግድያን በተመለከተም ቀወቶች ባመዛኙ “ገደለ ተነቀለ” ወይም “ዓይን ደም ይጠላል” በሚለው ልማዳቸው መሰረት ገዳይ አካባቢውን ለቆ እንዲሄድ ያደርጋሉ፡፡ የደም ወደር ካለም ደምን በደም በማቻቻል ተጋጪዎቹ አካባቢያቸውን ሳይለቁ እንዲኖሩ በማሸማገል ያስታርቃሉ፡፡ በዚህም የግጭት አፈታት ሥርዓታቸው የሟች ወገኖች ሥራዬ እና ይሆነኝ ብለው የገዳይ ቤተሰቦችን እንዳይበቀሉ፣ ቀጣይም ደም መፋሰስ እና ትውልድ እየተቋጠሩ መበቃቀል እንዳይኖር ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ውጪም ለሽምግልና ያላደሩ እና ያልተገዙ ሰዎች ደግሞ ግጭታቸውን በዘመናዊ “ሕዝባዊ” ሕግ እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ አፋሮች ደግሞ መለስተኛ ግጭቶቻቸውንም ሆነ የደምን ጉዳይ ሁሉ የሚፈተቱት በተዋረድ በሚገኙት የጎሳ መሪዎች ሽምግልናዊ ዳኝነት ነው፡፡ ስለዚህም ሁል ጊዜም ከዚህ ሥርዓት ውጪ አይደሉም ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በአማራም ሆነ በአፋር በኩል ውስጣዊ ግጭቶች ደረጃቸው ቢለያይም በሽምግልና የሚፈቱበት ሥርዓት አለ፡፡ የሽምግልና ሥርዓቱንም እንዲፀና እና እንደ ሥርዓት ተከብሮ እንዲዘልቅ የሚያደርጉ የእርቅ መደምደሚያዎች ወይም ተቀባይነት እና ተከባሪነት ያላቸው የእርቅ ሥርዓተ መኃላዊ ፍፃሜዎች /rituals/ አሉ፡፡ እነዚህም ሥርዓተ መኃላዊ ፍፃሜዎች ወይም ማሳረጊያዎች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ ልማዳዊ እና ኃይማኖታዊ ቃለ መኃላዎች፡፡

በቀወት አማሮች የርስበርስ ግጭት እርቅ ሂደት ውስጥ የሚፈፀሙ፣ ቅቡልነትና ተከባሪነት ያላቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ ልማዳዊና ኃይማኖታዊ መኃላ አፈፃፀሞች ወይም እርጋቶች አሉ፡፡ ለምሳሌም በመለስተኛና በተገዳዳሪ ግጭቶች ወቅት ተጋጪዎች በቀጥታ ሽማግሌዎች ፊት ቀርበው የሚዋቀሱበትና እርቅ የሚፈፅሙበት ሁኔታ አለ፡፡ በዚህም ወቅት እርቁን ማስተማመኛ መኃለዎች ይፈፅማሉ፡፡ ከእርቅ ማስተማመኛና ማፅኛ መኃላዎቹም መካከል ጥይት የጎረሱ ሦስት ጠመንጃዎችን "ይሄ ቢስተኝ ይሄኛው አይሳተኝ" እያሉ ሦስት ጊዜ መራመድ አንዱ ነው፡፡ ሽንጥ ሥጋም ይቋረጣሉ፡፡ ይጎራረሳሉም፡፡ ምክንያቱም ሽንጥ ሥጋ ሲነሳ አከርካሪ ራቁቱን ይቀራል፣ ያለ ሥጋም ነፍስ አየቆምምና፡፡ እርጥብ ሣር በጋራ እየነጩ ይህን እርቅ ባፈርስ እንዲህ ያድርገኝ እያሉ ይምላሉ፡፡ እርጥብ ሣርም የሕይወት ተምሳሌት ነው፡፡ ምክንያቱም ሕይወት የሚመመጨው ከፈሳሽ ወይም እርጥበት ነውና፡፡

በኃይማኖትም መስቀል ጨብጠው "እርቁን ባፈርስ እንደ መስቀሉ ይበሳሳኝ"፣ እያሉ ቃላቸውን እንደሚያፀኑ ያረጋግጣሉ፡፡ ይህም መስቀሉ በጥንተ አመጣጡ መሰቀልን ስለሚወክል በኋላው ትርጉሙም መስቀል ኃይል እና ቤዛ ተደርጎ ስለሚቆጠር ጥበቃን ላለማጣት መሆኑ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተጋጪዎች አጥብቀውና አልቀው የሚያምኑበትን ቤተክርስቲያን ደጃፍ በር እየዘጉ "ይህን እርቅ ባፈርስ እንዲህ ይዝጋኝ" ይላሉ፡፡ የበር መዘጋት ድፍነት ነውና፡፡ መደፈንም ይፈራልና፡፡ እህል ውኃም ይፋተታሉ፡፡ በአንድ ማዕድ የቀረቡ እንደቆረቡ ስለሚቆጠሩ፡፡ እነዚህንም ሁሉ ለማድረግ ሁኔታዎች

ያልተመቻቹላቸው ደግሞ መኖሪያቸውን ለቀው፣ ስማቸውን ለውጠው እና ተሰደው ይኖራሉ፡፡ በዚህም ከማህበራቸው እራሳቸውን ያገላሉ፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎ የእርስበርስ ግጭት አፈታትና እርቅ አፈፃፀም ሂደትም ውስጥ የተለያዩ ሀገረሰባዊና ኃይማኖታዊ መኃላዎች ይፈፀማሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ተጋጪዎች ለሽምግልና ወይም ለባህላዊ ዳኝነት እንዲቀርቡ የሚደረጉባቸው ተፅዕኖዎች አሉ፡፡ ጎጂ ተጎጂን ሽማግሌ ልኮ የማሸማገል ጥያቄ የሚያቀርብበት ወይም ደግሞ የጎጂ ወገኖች ወይም የአካባቢና የአገር ሽማግሌዎች ጎጂን ለሽምግልና እንዲያድር ተፅዕኖ የሚፈጥሩባት ሂደት አለ፡፡ ይህም ከሆነ በኋላ ደግሞ ጎጂና ተጎጂ ወይም የተጎጂ ቤተሰቦች ፊት ለፊት ተቃርበው እንዲዋቀሱ፣ እንዲሸማገሉ በተለያዩ ደረጃ በሚገኙ ጎሳ መሪዎች እንዲዳኙና እርቅ እንዲፈፅሙ የሚደረጉበት ሥርዓት አለ፡፡

በሰሙሮቢ ገለአሎ ሀገረሰባዊ እምነት መሰረት ጥፋተኛ ሰው እንደ ጥፋቱ ደረጃ ውኃ ውስጥ ይነከራል፣ ይገረፋል፣ ይደበደባል፣ ይታሰራል፡፡ በእነዚህም ቅጣቶች ኃጢአቱን ያወርዳል፣ ይታጠባል፣ የእርድ እንስሳቱን ያበላል፡፡ ከዚያ በኋላም ሰውዬው ተመልሶ ጥፋት በመፈፀም ንፅህናውን ማርከስ ስለማይፈልግ እርቁን ላለማፍረስ ይጠነቀቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች እርስበርሳቸው እርቅ ሲፈፅሙ ተጋጪዎች ከብት፣ የከብት እበት ወዘተ ጨብጠው "ይህን እርቅ ብናፈርስ ይህን ርጥብ ይንሳን፣ ሀብት ይንሳን" ብለው ይምላሉ፡፡ መኃላውም የፀና ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ትዕምርቱ የሕይወት መግፊያቸው ነው፡፡ ውኃ፣ ሣር፣ እበት እርጥብነት ያላቸው ነገሮች በመሆናቸው የሕይወት ምንጭ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪም አፋሮች ጠመንጃ፣ ጊሌ በመራመድ መኃላ ይፈፅማሉ፡፡ እርቁ ይፀናል፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ብረት የነፍስ ማጥፊያ መሣሪዎች ይፈሯቸዋልና፡፡ በእነዚህ ሁሉ ለመገዛት ያልቻሉ ተጋጪዎች ደግሞ ከመኖሪያ ሰፈራቸው እና ከጎሳቸው ተነጥለው እንዲወጡ ይረጋሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ልማዳዊ እና ኃይማኖታዊ እርቅ አፈፃፀሞቻቸውን ስንመለከትም ቀወቶች ውስጣዊ እርቅ ሲፈጽሙ እርጥብ ሣር እየነጩ፣ ጠመንጃ ወይም ጎራዴ እየተራመዱ፣ አፈር እየጨበጡ፣ ክር እየበጠሱ፤ በኃይማኖት ረገድም የቤተክርስቲያን በር እየዘጉ፣ መስቀል እየጨበጡ፣ ወንጌል፣ ድርሳናት፣ መልክዓ አማልዕክት እየጨበጡ እርቃቸውን ለማፅናት ይማማላሉ፡፡

ሰሙ-ሮቢዎችም በልማድ እንስሳት እና እበት እየጨበጡ፣ የግርፋት ቅጣት እየተቀበሉ ጠመንጃ እየተራመዱ፣ በውኃ እየተነከሩ፤ በኃይማኖትም ቅዱስ ቁርዓንን መኃላ ይፈፅማሉ፣ እርቃቸውንም ያፀናሉም።

ከዚህ በማስከተል ደግሞ የቀወት እና ሰሙ-ሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦችን ውጫዊ ግጭት አፈታት ሁኔታ ለማየት እንሞክር።

ከጥናቱ ሂደት ለመረዳት እንደተቻለው በቀወት አማሮች እና በሰሙ-ሮቢ ገለአሎ አፋሮች መካከል የማያቋርጥ ተናጠላዊ እና ጅምላዊ ግጭት አለ። ይሁንና በጥናቱ መረጃ ስብሰባ ወቅት እንደታየው በድንበርተኞቹ ሕዝቦች መካካል የሚቀሰቀስ ተናጠላዊ ግጭት ብዙውን ጊዜ ለሽምግልና አይቀርብም፣ እርቅም አይፈፀምም። በአካባቢው ሽምግልና እና እርቅ የሚደረገው ጅምላ ግጭት ሲከሰት ነው። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ የመረጃ ተባባሪዎች እንደገለፁት የጅምላ ግጭት ሽምግልና እና እርቁም ቢሆን ከሁለትና ሦስት ዓመታት አይዘልም። ግጭቱ ተመልሶ ያገረሻል። ድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች በግጭት እና እርቅ ዑደት ውስጥ የሚኖሩትም እርቁ ዘላቂነት የሌለው ስለሆነ ነው። ስለዚህም የቀወቶች እና ሰሙ-ሮቢ ገለአሎዎች እርቅ ዘላቂ ሊሆን ያልቻለው እና የማይሆነውም በሚከተሉት ምክንያቶች መሆኑን ከጥናቱ መረጃ መገንዘብ ይቻላል።

አንደኛው የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት የማያባራበት ምክንያት ተናጠላዊ ግጭት ፈፅሞ ሽምግልና የማይሞከርበት መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት አንድ አማራ አንድ አፋር ሲገድል፤ የሟች ጎሳ አንድ አማራ ይገድላል። አንድ አፋር አንድ አማራ ሲገድልም ወገኖቹ አንድ አፋር ይገድላሉ። ሂደቱም እንዲሁ ይቀጥላል። ይህም ዓይነቱ መበቃቀል ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ከአቻዊነት ሊያልፍ የሚችልበት እና ወደ ጅምላነት የሚሸጋገርበት አጋጣሚም አለ።

ሁለተኛው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ቀጣይነት ምክንያት ምንም እንኳን ቀደም ሲል እንደተገለፀው በሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል ጅምላዊ ግጭት ሲቀሰቀስ የሽምግልና እና እርቅ ሥርዓት ቢኖርም የሚሸማገሉት እና እርቅ የሚፈፅሙት ወገኖች ደም ተቃቢዎቹ ወይም ተጎጂዎቹ አይደሉም። ስለ ቀጥተኛ ተጋጪዎቹ ተወክለው የሚሸማገሉትና እርቅ የሚፈፅሙት ከሁለቱም ወገን ግጭቱ እንዳይባባስ ብቻ የሚፈልጉት የሰሙ-ሮቢ ገለአሎ የጎሳ መሪዎች እና የቀወት ባላባቶች፣ የጎበዝ አለቆችና ቀበሌ አመራሮች ናቸው። ስለዚህም የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች የእርቅ ፅናት የለሽነት ምክንያት የእርቁ ጅምላዊ መሆን ነው። እንዲህ በመሆኑም ቀጥተኞቹ የግጭቱ

ተሳታፊዎች ተለይተው ወጥተው በእርቁ ሂደት ላይ በቀጥታ አይዋቀሱም። የሽማግሌ ፊት አይመታቸውም። ስለ ጥፋታቸውም ፀፀት አያድርባቸውም። በዚህም ምክንያት እርቅ በቀላሉ ይደፈርሳል። ግጭቱም ያገረሻል። ይሄም እንግዲህ አንዱ የመረጃ ተባባሪዬ "እርቁ የበቆሎ ንፍሮ ነው። በሰለ ሲሉት አድሮ ጥሬ ይሆናል።" እንዳሉት መሆኑ ነው። ስለዚህም የአማራና የአፋር ግጭት አፈታት ያልተጣሉ ሰዎች የሚሸማገሉበት እና የሚታረቁበት፤ ያልታረቁ ሰዎች ደግሞ "ወንድ" ለመሰኘት የሚገዳደሉበት ነው። እርቁ ያልተጣሉ ሰዎች የሚታረቁበት፤ ያልታረቁም ሰዎች የሚገዳደሉበት በመሆኑም ማቆሚያ የለውም ማለት ይቻላል። ስለዚህም የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች እርቅ ሁኔታ ከጊዜ መግገርነት የሚያልፍ አይደለም ማለት ይቻላል። ይህንንም አስረጅ እየጠቀስን እንመልከተው።

በመሰረቱ የእርቅ አስፈላጊነቱ እና ጥቅሙ የሻከረ፣ የተበላሸ ግንኙነትን መልሶ ማለስለሱ እና ማቃናቱ፣ ተጋጪዎችንም ቀድሞ ወደነበሩበት መልካም ግንኙነት እንዲመለሱ አስቻይ መሆኑ ነው። ይህንንም ለመፍጠር ተጋጪዎቹ ተቀራርበው በግልፅነት የተካነኩበትን፣ የተቀጩበትን ወደ ግጭትም የገቡበትን ሁኔታ ዘርዝረው ተናግረው፣ አሸማጋዮቹም የቀረበላቸውን ወቀሳ አመዛዝነው እና አቻችለው፣ ተጋጪዎቹንም አስተማምነው ተጋጪዎቹ እንዲፀፀቱ እና ወደ ነባር ግንኙነታቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ነው ትልቁ ቁም ነገር። ይህ የእርቅ ነገረ ተፈጥሮ አኳኋን ይዘን የቀወት አማሮች እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ አፋሮች እርቅ የሚፈፅሙት እንዲህ ነወይ? ስንል ግን የምናገኘው ሁኔታ ከላይ እንደተመለከትነው የተለየ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሁለቱ ሕዝቦች በጅምላ ተገዳድለውም ይሁን ተዘራርፈው ለሽምግልና ሲቀመጡ የተለመደውን እና የምናውቀውን ዓይነት የመወቃቀስ ሥርዓት አይፈፅሙም። አሸማጋዮቹም ወደዚያ ዓይነት ሂደት ውስጥ አይገቡም። ፀባቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልማድ መሆኑን ያውቁታልና። ከዚሁ ጋር ደግሞ ሁለቱም ሕዝቦች መገዳደልን እንደ ጀግንነት ወይም የተለየ ወንድነት ቆጥረውት በየባህላቸው አሸሼ ገዳይ ! እንደሚሉበት፣ እንደሚቀበብትም፣ እንደሚያጎፍሩበትም፣ አምባር እንደሚያጠልቁበትም ፣ የጦር መሣሪያቸውን እንደሚያስጌጡበትም ፣ የጦር መሣሪያዎቻቸውንም እንደ ነፍስ መጠበቂያ እና እንደ አባታዊ ቅርስ እና ውርስ እንደሚቆጥሯቸውም በዚሁም ክብርና ሞገስ እንደሚያገኙም ስመ ጥር እንደሚሆኑም ሁሉ ያውቃሉ። ስለዚህም በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል

የሚካሄደው እርቅ ደም የሚያደርቅ፣ ቂም በቀልን የሚያስቆም፣ የተበላሸ ግንኙነትን የሚጠግን እና የሚያቃና አይደለም፡፡

በሌላም በኩል በጥናቱ ውስጥ እንደታየው በተለይ ቀወት አማሮች በውስጣዊ ግጭት አፈታታቸውም ቢሆን ነፍስ ሲጠፋ በተጋጪዎቹ መካከል ዕኩል የጠፋ የሕይወት መገዳደሪያ ከሌላ ገዳይ ቀርቦ ከሟች ወገኖች ጋር አይደራደርም፣ አይዋቀስም፡፡ ግጭቱ ያልታሰበበት ድንገተኛ ከሆነ እና በሽምግልናም ሂደት ነገሩ እጅግ የሰላ ከሆነ ብቻ ነው በእርቅ ሥርዓቱ ላይ ብቻ ነው ቀርቦ መኃላ የሚፈፅመው፡፡ ከዚህ ውጪ ግጭቱ እና ግጭቱ ያስከተለው ግድያ በደመኝነት እና በቂም በቀለኝነት የተፈፀመ ከሆነ የገዳይ እና የሟች ቤተሰቦች ብቻ ተደራድረው እነርሱ ግጭቱን ላለማስቀጠል ተሸማግለው ይታረቃሉ እንጂ ገዳይ አይቀርብም፡፡ እንዲያውም አካባቢውን ለቆ ይሰደዳል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይም ደግሞ በውጫዊ ግጭቱ አፈታት ላይ የበለጠ ልልነት እንደሚኖር እንረዳለን፡፡

ሰሙሮቢ አፋሮችም ቢሆኑ አማራ በመግደላቸው ምክንያት ገዳዮቹ ከሟች ወገኖች ጋር ፊት ለፊት ቀርበው አይሸማገሉም፣ አይታረቁም፡፡ ይህንንም በውጫዊ ግጭት ሽምግልና እና እርቅ ሂደት ላይ እንዲያደርጉ ውስጣዊ ተዕእኖ አይደረግባቸውም፡፡ ስለዚህም ቀወት እና የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ድንበርተኛ ሕዝቦች ግጭት በተለይም የሚያመዝነው የነፍስ ግድያ እርቅ የማይሰምርበት አንዱ ምክንያት ይሄ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ስለዚህም ከላይ እንደተገለፀው የእርቁ ጅምላዊ መሆን እርቁን ተከባሪነት እና አይገሰሴነት ያለው እንዲሆን አላደረገውም፡፡ በመሆኑም ግጭቱም እርቁም ተፈራራቂ የሕይወት ገፅታዎች ሆነዋል ማለት ይቻላል፡፡

ሦስተኛው የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች እርቅ ልልነትና ፈራሽነት ምክንያት ሁለቱም ወገኖች ገዳይነትን የወንድነት መግለጫ እና ማሳያ ክቡር ልማድ አድርገው በመቁጠራቸው ምክንያት የጅምላ ግጭት ተከስቶ እርቅ ሲፈፀም እንኳን ከአምስት ሺህ እስከ አሥራ አምስት ሺህ የሚደርሰውን የደም ካሣ ወይም ወጀ ክፍያውን የሚከፍለው የየቀበሌዎቹ ሕዝብ እንጂ ዋነኛ ተጋጪዎቹ አይደሉም፡፡ እዚህ ላይ የደም ካሣውም ቢሆን አፋሮች በውስጣዊ ግጭት ወቅት ለሕይወት መጥፋት የሚቆርጡት የደም ካሣ ከአንድ መቶ አምስት እስከ አንድ ሺህ ግመል ወይንም የቀንድ ከብት ሲሆን ከአማራ ጋር የሚካካሱት በአማካይ የአንድ በሬ ዋጋ ብቻ ነው ማለት

ይቻላል፡፡ ይህም ደግሞ አሁንም ከአፋሮች ውስጣዊ ግጭት የከባድ አካል ጉዳት ከሰላሳ አምስት እስከ ሃምሳ ከብት የአካል ጉዳት ካሣ ጋር እንኳን እጅግ የራቀ ነው፡፡ ስለዚህም የካሣው ማነስም ቢሆን በራሱ መገዳደልን የሚያበረታታ ነው ማለት ያስደፍራል፡፡

በተለይም ስሙሮቢ ገለአሉዎች በገዳይ ላይ የሚቆረጠውን የካሣ ክፍያ የሚከፍሉት እንደ ግድያው አፈፃፀም ሁኔታ ማለትም ግድያው በአንድ ጎሳ አባላት መካከል ከሆነ የገዳዩ የቅርብ ቤተሰቦች፤ ግድያው በተለያዩ ጎሳዎች ውስጥ ከሆነ ደግሞ የጎሳው አባላት ሁሉ ናቸው ካሣውን አዋጥተው የሚከፍሉት፡፡ ይህም ግድያ እንደ ሙያ እንጂ እንደ ጥፋት እንደማይቆጠር ያመለክታል፡፡ በዚህ በኩልም ሲታይ "ወንድነት" የኑሮ ጣዕም መስጫ ተደርጎ እንደሚታይ መረዳት ይቻላል፡፡

በአጭሩም ገዳይነት የጀግንነት መግለጫ፣ የወንድነት ማግኛ፣ ስም ማስጠሪያ፣ ጆሮ ማውጫ፣ መቀቢያ፣ ማህበራዊ ክብር ማግኛ ተደርጓል ማለት ይቻላል፡፡ የአገዳደል ማለትም የአተኳኮስ፣ አሰላለብ ሁኔታም የእርድ እንስሳትን እንደ መበለት ችሎታ እየተዳነቀ ይወሳል፡፡ ይህም ደግሞ በንፅርተ ዓለምነትም ተተክሏል፡፡ የሕይወት እሴት እና ግብም ሆኗል፡፡ ስለዚህም በጥበባዊ አገላለፆቻቸው /ሥነቃሎቻቸው/ ያንቆለጳጵሱታል፡፡ በማንቆለጳጳስም ለትውልዶቻቸው ያስተላልፉታል፣ ያሽዝቡታልም፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ሁሉ የሁለቱን ሕዝቦች ግጭት ልማዳዊና ዑደታዊ አድርገውታል ማለት ይቻላል፡፡

በቀወቶችም ሆነ በስሙሮቢ ገለአሉዎች ዘንድ ነፍስ ማጥፋት የወንድነት፣ የጀግንነት መግለጫ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ የሕይወት መጥፋትን ያስከተለው ግጭት ውስጣዊ ሲሆን ማለትም በአማራ ወይም በአፋር ዘንድ እርስበርስ ሲሆን ወንድነትን፣ ጀግንነትን ቢያጎናጽፍም በዚያው መጠን ደግሞ ከሚኖሩበት ማኅበረሰብ ጋር ከሙሉ ከበሬታና መረጋጋት ጋር ለመኖር አያስችልም፡፡ ምክንያቱም በአማራም ሆነ በአፋር ዘንድ ገዳይ ከመግደሉ በፊት እንደነበረው ዓይነት ሕይወት በነበረበት መቀጠል አይቻለውም፡፡ ከአካባቢው ሊነቀልና ሊሰደድ ይችላል፡፡ አካባቢውን የማይለቅና የማይሰደድ ከሆነም ሌሎች ማህበራዊ ማዕቀቦች ይደረጉበታል፡፡ ለምሳሌም እንስሳቱ ከሌሎች እንስሳት ጋር አይሰማሩም፡፡ ልጆቹም ከሌሎች ልጆች ጋር አይውሉም፡፡ ሚስቱም ከጎረቤት እሳት አትጭርም፡፡ አንዳች ነገር ቢቸግራትም የሚያጋድዳት አይኖርም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በንብረቱ ላይ ጉዳት ቢደርስ አጋር የሚሆነው የለም፡፡ በቤተሰቡም ላይ የሞት አደጋ ቢከሰት አስተዛዛኝና አቃባሪ፣ መከራ አጋሬ አይኖረውም፡፡

በአንፃሩ ግጭቱ ውጫዊ ከሆነ ማለትም ግድያው የተፈፀመው በአማራና በአፋር መካከል ከሆነ ወንድነትን፣ ጀግንነትን ያላብሳል። ግላዊና ማህበራዊ ከበሬታን ያስገኛል። ማህበራዊ ከበሬታውም መነቃቃትን፣ ተቀዳሚነትን ማለትም ከሌሎች ይልቅ እሱ ይቅደም፣ እሱ ይናገር፣ እሱ ዋንጫ ይያዝ፣ እሱ ይባርክ፣ ሚስቱ ከሌሎች ቀድማ መንገድ ትሂድ፣ ውኃ ትቅዳ፣ አስተያየትም ትስጥ፣ እንስሳቱ ከሌሎች እንስሳት ቀድመው ይጠጡ፣ ይጋጡ የሚል ማዕረግ ያስገኛል። ስለዚህ አማራ አፋርን፤ አፋርም አማራን ሲገድሉ ሙገሳና ሞገስ ወይም ስመ-ጥርነትን ያገኛሉ። ይህም ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ለገዳይነት የሚሰጡት ከበሬታ ተመሳሳይነት፣ ግድያ እንዳያቋርጥ እንዲያውም በአዎንታዊነትም እንዲታይ እና የሕይወትም አካል እንዲሆን አድርጎታል።

አራተኛው የድንበርተኞቹ አማሮች እና አፋሮች ግጭት ዑደታዊነት ምክንያት ሁለቱ ሕዝቦች እርቅ ሲፈፅሙ የሚያሳርጉት ድንኳን ጥለው ወይም አንድ አመቺ ጥላማ ሥፍራ መርጠው ግራ እና ቀኝ ተቀምጠው አፋሮች ያመጡትን ጊደር እና አማሮች ያመጡትን በሬ ተለዋውጠው እና በየኃይማኖታቸው ባርከው፣ አርደው ጎን ለጎን ተቀምጠው የተለያዩ ማዕዳቸውን በልተው መለያየት ብቻ ነው። ሁለቱ ወገኖች ልታፈራ የምትችለውን ጊደር እና ዋነኛ የእርሻ ሥራ ማካሄጃ የሆነውን በሬ ተለዋውጠው አርደው መብላታቸው ትዕምርታዊነት ያለውነቱ እሙን ነው። ምክንያቱም ጊደር ማረድ ግጭት እንዳይወለድ፣ መክኖ እንዲቀር መመኘት ነው። በሬም ማረድ መሰረታዊ የሕይወት መግፊያን ማጣት ነው። ነገር ግን ግጭቱ እንደምኞቱ መክኖ አይቀርም። ያው መመኘት ብቻ ነው። ከአቀማመጣቸውም ቢሆን የምንረዳው ይህንኑ ነው። ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች የሚቀመጡት እና የሚመገቡት ጎን ለጎን በየፊናቸው እየተመለከቱ እንጂ አንደኛቸው ሌላኛቸውን ፊት ለፊት እየተያዩ አይደለም። ይህም እንደ የትየለሌ መስመር በየፊናቸው የሚሄዱነታቸውን ጠቋሚ ነው። ይህም ደግሞ አሁንም ሙሉ ለሙሉ ለመተያየት አለመፈቃቀድን፣ ነገም ግጭት መኖሩን ያመለክታል። በአጭሩም ከላይ እንደተባለውም ወደ ኋላ እንደሚባለውም የግጭት ማባባሻው ብዙ ነው።

አምስተኛው የሁለቱ ሕዝቦች እርቅ ፅናት የለሽነት ምክንያት የእርቁ ሥርዓተ አፈፃፀም /ritual/ ጋርዮሻዊነት፣ ገዥነት፣ ተከባሪነት እና አሳሪነት የሌለውነቱ ወይም ውስብስብ አለመሆኑ ነው። ሁለቱም ወገኖች የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነት እና ኃይማኖት የሚከተሉ በመሆናቸው በጋራ የሚያምኑበት የእርቅ ማዕኛ መኃላ የላቸውም። ስለዚህም

በጋራ የሚጨብጡት ነገር የላቸውም። አንድ በጋራ የሚራመዱት ነገር ቢኖርም የጦር መሣሪያ ነው። እርሱንም የሚራመዱት የጎሳ መሪዎች እና ባላባቶች፣ የቀበሌ አመራሮች ወዘተ ናቸው። እነዚህም ደግሞ ግንባር ቀደም ፀብ ጫሪዎች ያልሆኑ ሰዎች ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪም የሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ተጠሪዎች በእርቁ ላይ በጋራ የሚያምኑበት እና የሚሉትም ቃል /ተረክ/ የላቸውም። ስለዚህም የእርቅ አፈፃፀም ሥርዓቱ ወይም ሥርዓተ ከበራው ዝቅተኛ ነው። የእርቅ ሥርዓተ አስተራረጉ ዝቅተኝነት ወይም ውስብስብነት የሌለው በመሆኑም እምነታዊ ተከባሪነቱ ደካማ ነው ማለት ይቻላል። ደካማ በመሆኑም ፍርሃተ-እርቅ ማፍረስን ዝቅ ያደርገዋል። ፍርሃት አነሰ ማለት ደግሞ መከባበር ቀነሰ፣ መካካድ በዛ ማለት ነው። ስለዚህም እርቁ በቀላሉ ይፈርሳል። "የአማራ እና አፋር እርቅ ጉዳይ አድሮ ጥጃ " እና "የበቆሎ ንፍሮ አድሮ ጥሬ" እንዲሉ።

ስለዚህም የሁለቱ ሕዝቦች የግጭትና እርቅ ዑደት እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል።

በሁለቱም ወገኖች ቀደምት ገገር መደቦች በኩል ጥንት የባህር በር ተቆጣጣሪነት፣ እና የገቢ እና ወጪ ንግድ ተቆጣጣሪነት ፍላጎት ነበር። ያም ፉክክር የመጣው የእምነት እና የማንነት ልዩነት በመኖሩ ነው በሚል ሥር እንዲሰድ ተደረገ። ልዩነቱንም የሚያሳዩ ውስጣዊ እና ውጫዊ አመክንዮቶች ሁሉም ታዩ። እነዚያም በተረክነት ቀጠሉ። ከማን አንሼ ዓይነት "የወንድነት" አመለካከትን እና ማኅበራዊ ክብር አሰረፁ። በዚህ ላይ ደግሞ ዛሬም ደግሞ ለምነት ያላቸውን አካባቢዎች የመያዝና የመጠቀም ፍላጎት፣ ጥረት እና ሥምሪትም አለ። ይህንንም ተጋጪነት የሚተርክ እና የሚያሞካሽ የሥነቃል ሀብት አለ። በሥነቃል አማካኝነት የሚተረከውንም በሁለቱም ወገን ያሉ ታዳጊዎቹ እያዳመጡ ያድጋሉ። ቂመኝነትንም ይቋጥራሉ። ቂሙም እንደገና በሰበብ አስባብ ያገረሻል።

ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በድንበርተኞቹ የቀወት ወረዳ አማሮች እና በሰሙ ሮቢ ገለአሉ ወረዳ አፋሮች መካከል ለዘመናት የዘለቀው ግጭት ሥረ መንሥዔ የተፈጥሮ ሀብት ማለትም መሬት ነው። መሬቱም የሚፈለገው ሰብል ማብቀል እንስሳት መመገብ፣ የዱር እንስሳትን ለምግብነት እና ለአደን ማፍራት እስከቻለ ድረስ ነው። ስለዚህም የተፈጥሮ ሀብት ግጭቱ ተጠቃሎ ሲታይ ውኃ ወለድ ግጭት

ነው ማለት ይቻላል። ከዚህም በመነሳት የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት በውኃ እና በተረክ ምክንያት የመጣ እና የቀጠለ ነው ማለት ይቻላል። ይህ የተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ እና ባህል /ሥልጣኔ/ በተለይም ሥነቃል ተዳምረው የፈጠሩትም ግጭት እንደ ትውልድ ጅረት የሚፈስ እንደ ወቅቶችም የሚያድ ነው።

ከዚህ በማስከተል የሚነሳው ጥያቄ በቀወት እና በሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል በተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ ምክንያቶች እየቀጠለ እና ዑደታዊም እየሆነ ያለው ግጭት መግቻው ምንድነው? የሚለው ይሆናል። በመጀመሪያ በተጨባጭ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች እንደምን ሊገቱ እንደሚችሉ መላ እንበል።

በሕዝቦች መካከል በተጨባጭ ምክንያቶች ማለትም በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብት እጥረት እና ሽሚያ ሳቢያ የሚከሰቱ ግጭቶች የኅብረተሰብ አኗኗር እና የሕይወት ሥርዓት ሲለወጥ ሊወገዱ ይችላሉ። የኅብረሰብ ለውጡም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ገፅታዎች ይኖሩታል።

በዚህም መሰረት ፖለቲካዊው ርዕዮተ ዓለም ለዓለማዊ ሕይወት ለውጥ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ እና ቁርጠኝነት ሲኖረው እውቀት ያብባል። በዚህ ዓይነቱ የአብርሆት ዘመን ፈለግም ዘመናዊ ትምህርት ይስፋፋል፣ ይሰርፃል። ከተሞች እና ኢንዱስትሪዎችም ይስፋፋሉ። በኢንዱስትሪዎቹም ውስጥ የሚሰራ በአስተሳሰብ እና በሙያ የሰለጠነ ሕዝብ ይበራከታል። በእነዚህ ሂደቶች የገጠር ነዋሪዎችም ወደ ከተሞች ይገባሉ። ገብተውም በተፈጠሩት አዳዲስ የሕይወት መግፊያ ተቋማት ይገባሉ። ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ያገኛሉ። የአኗኗር ሥርዓታቸውም ይቀየራል፣ ይለወጣል። የሀገረሰብ ግጭቶችም በተዘዋዋሪ መንገድ ይገታሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የማህበራዊ ግንኙነት መሰረቶች አብረው ሊቀየሩ ይችላሉ። ለምሳሌም የገጠር ነዋሪዎች በወንዝ፣ በጎጥ፣ በጎሳ፣ በቤተ ትውልድ ሐረግ ላይ መስርተዋቸው የነበሩ ማህበራዊ አደረጃጀቶች፣ ማንነቶች፣ መለዮዎች እና መገለጫዎች እንዲሁም ግንኙነቶች ወደ ሌሎች የተለያዩ የከተሜ ሕይወት ማህበራዊ ግንኙነት መመሥረቻዎች ሊቀየሩ ይችላሉ።

ወደ ኢ-ተጨባጭ ግጭቶች አወጋገድ መላ እንለፍ። በመሰረቱ በተጨባጭ ምክንያቶች ከሚቀሰቀሱ ግጭቶች ይልቅ በኢ-ተጨባጭ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች ሳይንሳዊ አመክንዮ የማይጠይቁ፣ ለማሳመን ጊዜ የማይፈጁ፣ በቀላሉም እንሰደድ እሳት የሚቀጣጠሉ ጅምላ ተከታይ ለማፍራት የሚያስችሉ ናቸው። ዛሬ

በዓለም ዙሪያ ግጭቶች የተበራከቱትም በእነዚሁ ኢ-ተጨባጭ የግጭት ምክንያቶች ነው፡፡ አብነቶችን ጠቃቅሰን እንመልከት፡፡

በምዕራቡ ዓለም "ዓለማቀፍ እሴቶች" እና በእስልምና፣ በእስልምና እና በክርስትና፣ በእስልምና እና በሂንዱይዝም፣ በእስልምና እና በኮንፊዩሽስ፣ በአይሁድ እና በእስልምና፣ በክርስትና እና በአይሁድ ወዘተ መካከል እንዲሁም በእያንዳንዳቸው ንዑሳን ዘውጎች መካከል ያለውን የልዩነት እና የእኔ ይበልጥ ፉክክር ያስከተላቸውንም ውዝግቦች እናገኛለን፡፡ በተለይም በምዕራቡ ዓለም እና በምዕራቡ ዓለም ንፅረተ-ዓለም ተቀናቃኞች መካከል ያለው ልዩነት እልህ ያጋባ ሆኗል ለማለትም ከሚያስደፍርበት ደረጃ ደርሷል፡፡ በአገሮችም መካከል የምዕራቡ ዓለም በሚሰኙት እና ብዙውን ጊዜም በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፊታውራሪነት በሚመሩት አገሮች እና በእስልምና አገሮች መካከል፣ በቻይና፣ እና በጃፓን እንዲሁም በአፍሪካ ባህሎች መካከል በእነዚሁ ከላይ በተጠቀሱቱ ባህላዊ ጉዳዮች ምክንያት ያሉትን ልዩነቶች እናያለን፡፡ የግጭቱን አኳኋን በሕዝቦችም አኳያ ስንመለከተውም በእሥራኤል እና በፍልስጤም ይልቁንም በእሥራኤ እና በአረቦች ወይም በእስልምና እና በአይሁድነት፣ በቀድሞዋ ዩጎዝላቢያ ሪፑብሊኮች /በእስላሞች፣ በክሮኣቶች፣ ሰርቦች/፣ በቸቺንያ እና በሩሲያ፣ በቻይና እና በቲቤት፣ በህንድ እና በካሽሚር፣ በሩሲያና በዩክሬን፣ በቀድሞዎቹ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች እና በእንግሊዝ መካከል፣ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል፣ በእስልምና ኃይማኖት ተከታይ አገሮችም ውስጥ በኢራቅ፣ በሶርያ፣ በየመን ወዘተ በሱኒዎች እና ሺዓዎች መካከል እንደገናም በሰሜን ሱዳን፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሶርያ፣ በሩዋንዳውያን፣ በናይጀሪያውያን፣ በሁለቱም ሱዳኖች፣ በሶማሊያ በየውስጣቸው፣ አሁንም በኢትዮጵያውያን መካከል የሚስተዋሉትን በብሔር ላይ የተመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲ አደረጃጀቶችን እናገኛለን፡፡ እነዚህም የባህላዊ እና የማህበራዊ ማንነት፣ ንፅረተ ዓለም (ዓለማዊ እና መንፈሳዊ አመለካከት) ቅንቀናዎች ሁሉ የሀብት፣ የፖለቲካ እና የሥልጣን ግጭት ላዕላይ ሽፋኖች ናቸው፡፡ ስለዚህም በተለያዩ አገሮች የታዩትን እና በመታት ላይ ያሉትን በዘር /በብሔር/፣ እና በኃይማኖት ዙሪያ የተመሰረቱ የመቧደን አመለካከቶች እና ዝንባሌዎች መስፋፋት ስንመለከት ግጭቶች ከተጨባጭ ሀብት እና ሥልጣን መቆጣጠር ይልቅ በባህል /ሥልጣኔ/[29]

[29] ከሥነ ሰብዕ /Anthropology/ ምሁራን መካከል ባህል የሚለውን ሥልጣኔ እያሉ በፍርቅርቅ ወይም በአቻነት የሚጠቀሙ አሉ፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ ባህል እና ሥልጣኔ ይላሉ፡፡ እዚህ የተጠቀምኩት ግን በአቻ የሚጠቀሙትን ተከትዬ ነው፡፡

ምክንያት እየመነጩ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ ስለዚህም የግጭቶች ዋነኛው መንሥዔ ተረክ እና የተረክ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በአጠቃላይ በዓለማችን ላይ የሚስተዋሉ ኃይማኖትን እና ብሔርን መሰረት ያደረጉ በተረክ ላይ ከተመሰረቱ ግጭቶች መላቀቅ የሚቻል የሚመስለው የኅብረተሰብ አኗኗር እና የሕይወት ሥርዓት በእውቀታዊ መንገድ ሲለወጥ በተለይም ዘመናዊ ትምህርት እና እውቀት ልብስና ጉርስ ከማግኛነት በላይ ዘልቆ ሲሄድ፣ ብዙኃኑ ሕዝብ ከሕዝባዊ እና ሀገረሰባዊ ኃይማኖቶች፣ እምነቶች፣ ጎጣዊ አስተሳሰቦች ይልቅ በምጡቅ ሳይንስ እና ተጠየቅ ወይም አመክንዮ እያመነ ሲሄድ እና አስተሳሰቡም ፅድቅ ሲሆን ይመስላል፡፡ የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ሕዝቦችም ኢ-ተጨባጭ ግጭት ዐደት ማምከኛው ከዚህ በመለስ አይመስልም፡፡ ከዚህ በመለስ የሚደረጉ የግጭት መውጫ መንገዶች ማስታገሻዎች እንጂ ዘላቂ መፍትሔዎች የሚሆኑ አይመስሉም፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን መለስተኛ የሕይወት ሥርዓት ለውጦች እየተከሰቱ ቢሄዱም የግጭቱም መልክ እንዲሁ እየተለወጠ እና እየተሸጋገረ ይሄዳል፡፡

# 10. የጥናቱ ማጠቃለያ

ድንበርተኞቹን የቀወት አማሮች እና የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮች የግጭት ምክንያቶች እና ግጭት አፈታት ሂደት በዚህ ምዕራፍ ጠቅለል አድርጎ ማሳየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ መከንከን፣ መነሻ እና መነሳሳት የፈጠሩብኝን ነገሮች አስታውሳለሁ፡፡ በቀወት እና በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ሕዝቦች መካከል የማያባራ ግጭት እና እርቅ መኖሩን ከልጅነት እስከ እውቀት እየሰማሁ ማደጌ አንዱና ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ሌላው ምክንያቴ በ2002 ዓ.ም. ነገሩን ቀረብ ብዬ ለማየት በሞከርኩበት ወቅት ግጭቱ ምጣኔ ሀብታዊ ብቻ ሳይሆን ተረካዊነትም ያለበት መሆኑን በሚያመለክት መልኩ በፎክሎር ማለትም በሥነቃል ዘውጎች፣ ሀገረሰባዊ ወግ ልማዶች፣ ቁሶች እና እምነቶች ወዘተ ውስጥ ሁሉ ተናኝቶ እና ተዘርቶ መገኘቱን ማጤን መቻሌ ነው፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ በመመሥረትም የሁለቱን ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች ግጭት ከሁለት አቅጣጫዎች ማለትም ከተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-መንሥዔዎች አንፃር ለመመርመር ተገፋፋሁ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ነሻጭ ምክንያቶች ጥናቱን ሳደርግም በዒላማነት እመታዋለሁ ወይም አሳካዋለሁ ብዬ የተነሳሳሁት የሁለቱን ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ የግጭት መንሥዔ እንዲሁም የግጭት አፈታት አንድነት እና ልዩነት፣ ጥንካሬ እና ድክመት መለየት በተለይም የውጫዊ ግጭታቸውን ቋሚነት ምክንያት ለይቶ መምዘዝ ፣ ማውጣት እና ማመልከት ነው፡፡

የጥናቱንም ዓላማ ወይም ዒላማ ለመምታትም ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለመጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ዕሞናዊ ምልከታ፣ መጠይቅ እና የቤተ መዛግብት ምርመራ ናቸው፡፡ በእነዚህም የተለያዩ ነገር ግን የሚደጋገፉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭት መንሥዔዎች፣ የግጭት አፈታቶች ልማዶች፣ የግጭት አፈታቶቹንም ጥንካሬዎች እና ድክመቶች እናገኛለን፡፡ ግኝቶቹንም በመንተራስ ደግሞ ግጭቱንም በዘላቂነት መፈታት መቻል ወይም አለመቻሉን ለመፈከር እንሞክራለን፡፡

በግጭት ሰበበ-መንሥዔ አኳያ ሁለቱ የአማራ እና የአፋር ድንበርተኛ ወረዳዎች ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጫዊ ግጭት ውስጥ የሚገቡባቸው ምክንያቶች በአመዛኙ ተመሳስሎ፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ልዩነቶች የሚታይባቸው መሆኑም በጥናቱ ሂደት ታይቷል። ይኸውም እንደሚከተለው ሆኖ ገኝቷል።

የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች ሕዝቦች ውስጣዊ ግጭቶች የሚመነጩትም በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብት ባለቤትነት እና አጠቃቀም እጥረት እና ተሻምቶ፣ እምነት እና ንብረት ማጉደል፣ ዘረፋ፣ ሥርቆት፣ ንብረት ማቃጠል፣ የሰው ሚስት ማማገጥ፣ አፍ እላፊ፣ ደብደባ፣ ግድያ፣ ቂም በቀል፣ በነገር፣ በሥነቃል፣ በጉልቆ ትውልድ ቆጠራ፣ ወንድነትን ማሳየት እና ማህበራዊ ክብርን ማስጠበቅ ወዘተ ነው። ስለዚህም ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች የሕይወት እና የንብረት ውድመትን በሚያስከትሉ ውስጣዊም እና ውጫዊ ግጭቶች ውስጥ ሲገቡ የኖሩት እና አሁንም የሚገቡት በሁለት ዓበይት የግጭት ሰበበ-መንሥዔዎች ነው ማለት ይቻላል። በተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-ምክንያቶች።

ከተጨባጭ የግጭት ሰበበ-ምክንያት አንፃር የሚጠቀሱትም የተፈጥሮ ሀብት እና ሰው ሰራሽ ሀብት ሽሚያ ማለትም መሬት፣ ውኃ፣ ግጦሽ ሣር፣ ድንበር መግፋት፣ ሰብል ማጥፋት የመሳሰሉት ናቸው።

ከኢ-ተጨባጭ የግጭት ምክንያት አኳያ የሚጠቀሱት ደግሞ ተረክ ማለትም ጥንት መሬቱ የማን ነው?፣ ማንስ ያስገብር ነበር?፣ ግዛቱስ የት ይደርስ ነበር?፣ ማንስ ተቆጣጠረው ወይም ይቆጣጠረው ነበር? ወዘተ ከሚሉ የኋላ ታሪካዊ ተረኮች፣ የከየት መጣን?፣ እነ ማንስ ነን? አጎራባቾቻችንስ ከየት መጡ?፣ መቼስ መጡ?፣ እነ ማንስ ናቸው? እምነታችንን እና እምነታቸውስ ምን ይመስላል? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ላይ የሚመጡ፣ የማንነት እና የእምነት በተለይም የኃይማኖት ልዩነት ተረኮች ናቸው። ከእነዚሁ ጋር ግብር የሚገለፀው እና የሚስተዋለው ኢ-ተጨባጭ የግጭት ሰበበ-መንሥዔ ደግሞ ሁለቱም ሕዝቦች በየባህላቸው ውስጥ ያዳበሩት እና የዘሩት የገዳይነት ማለትም "ወንድነት" መንፈስ ሥርፀት ነው። የዚህም የ "ወንድነት" ነባራዊ ተረክ ሥርፀት እና ፍሰት በሁለቱም ሕዝቦች አፈ-ታሪኮች፣ ሽላሎዎች፣ ፉከራዎች፣ የሥራ፣ የሰርግ እና የፍቅር ዘፈኖች እንዲሁም ተረቶች፣ ምሳሌዎች፣ አባባሎች ውስጥ በአቻዊነት ተዘርቶ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም ምንም እንኳን ሰሙ

ሮቢ. ገለአሎዎች የሙሾ ግጥም ባይኖራቸውም በቀወቶች የለቅሶ /የሙሾ/ ግጥሞች ውስጥ ግን ይሄው ከላይ የተስተዋለው "ወንድነት" ጎልቶ ይታያል፡፡

በሁለቱ ሕዝቦች መካከል በአሁኑ ወቅት የሚከሰተው ግጭትም መነሻ ከተጨባጩ ይልቅ ኢ-ተጨባጩ ምክንያት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ምክንያቱም የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ጥንታዊያን ገገርዎች ቀይ ባህርን በመቆጣጠር ፉክክር የጀመሩት እና ዋነኛ ገፅታውን ለውጦ "የአማራነት እና እስላምነት" ጉዳይ ሆኖ እንዲቀጥል በመደረጉ ይመስላል፡፡ ይህም ከገገርዎቻቸው ወደ ተገገርዎቻቸው ሕዝቦች ተስተላልፎ የወረደው ግጭት "የአባት ዕዳ ለልጅ" እንዲሉ ዓይነት ሆኗል፡፡ ይህም ሁኔታ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የማንነት እና እምነት በተለይም ኃይማኖት ልዩነት ማለትም አማሮችን እና አፋሮችን በ "አማራነት እና እስላምነት" ያቧደነ እና ማቆሚያ የሌለው የግጭት ሰበብ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ ይሄም ያስከተለውን ተሳሳቢ ሁኔታ እንመልከት፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የሚታየው የማንነት እና የእምነት በተለይም የኃይማኖት ልዩነት ተረክ ማለትም ተረቴ ከተረትህ ይበልጣል አመለካከት ሁለቱ ሕዝቦች ውጫዊ ግጭት ከሚያፈሩባቸው ምክንያቶች አንዱ እና የተለየው፣ ግጭታቸውንም የሚያከረው ጉዳይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ማንነት እና ኃይማኖት በውስጣዊ ግጭቶቻቸው ውስጥ እጅጉን የሰፉ እና የገነኑ የግጭት መንሥዔዎች አይደሉም፡፡

በሁለተኛም ደረጃ ሁለቱ ሕዝቦች በድንበርተኝነት የሚኖሩበትን አካባቢ በነባር ባለቤትነት እና ባለይዞታነት "የእኛ ነው፣ የእኛ ነው" የሚል ጥያቄ እና ተረክ አላቸው፡፡ ይህ የተረክ ልዩነት "የእኛ ተረክ ትክክል ነው፣ የእናንተ ትክክል አይደለም" ዝንባሌ፣ አስተያየት እና አመለካከት ስለቀረፀ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ማባሪያ የሌለው የግጭት አዙሪት ማስከተሉ አልቀረም፡፡

በሦስተኛም ደረጃ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል አሁንም ወቅት እየጠበቀ በተረክም እየተደገፈ የሚከሰት የገዐ-ምድር ሀብት ሽሚያ እንዳለ ታይቷል፡፡ ይህም ከላይኞቹ ምክንያቶች ጋር ተደማምሮ ዑደታዊ መቆራቆስን፣ መዘራረፍን፣ መገዳደልን፣ መገፋፋትን ፈጥሯል፡፡

በአራተኛም ደረጃ ደግሞ በሁለቱም ሕዝቦች ዘንድ "ወንድ" እኔ ነኝ፤ እኔ ነኝ የሚል እምነት አለ፡፡ ሁለቱም ለወንድነት /masculinity/ እና ለወንድነት መግለጫ

የጦር መሳሪያ ከፍተኛ ከበሬታ ይሰጣሉ፡፡ ይህም ወንድነት የሚያስገኘውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ከበሬታ ያንራሉ ወይም አልቀው ያያሉ፣ ያምናሉም፡፡ ስለዚህም ወንድነቱ ለሚያስገኘው ክብር ይተጋሉ፡፡ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥም የተተከለ “ወንድነትን” ማህበራዊ አገልግሎት ወይም ፋይዳ የመጨረሻው ፍፁምነት መገለጫ አድርጎ የማየት ዓለማዊ አመለካከት አለ፡፡ ይህም ልማድ በሁለቱም ሕዝቦች ዘንድ የሰከነ ባህል ሆኗል፡፡ “ወንድነት” አግኛኝ ማህበራዊ ባህሉም በሥነቃል እና በአፍቅሮተ ጦር መሣሪያም በሥነቃልም እየተገለፀ፣ እየተተከለ እና እየተናኘም ቀጥሏል፡፡

የ “ወንድነት” አመለካከት በባህሎቻቸው ውስጥ ስለሰረፀም ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ያለ አንዳች ተጨባጭ የግጭት ሰበብም አንደኛው ሌላኛውን የአደን እንስሳ እንዳገኘ ዓይነት ቆጥሮ /እዚህ ላይ ተረካዊ ፀበኞች እና ተጋጪዎችነታቸውንም ልብ ይሏል/ በእንኳን ቀናኝ ብጤ አስተሳሰብ በተናጠል ሲገድለውም ጉዳዩ በሽምግልና አይያዝም፣ ገዳዩም ሥጋት አይገባውም፡፡ ጉዳዩም ለሽምግልና አይበቃም፣ እርቅም አይደረግም፡፡ ምክንያቱም ገዳዩን ወገን ለይቶ ከአንዱ ወረዳ ወደ ሌላው ወረዳ ገብቶ እና ተከታትሎ የሚያሲዘው የለም፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ሁለቱ ወረዳዎች ጆሮ ለጆሮ ቢሆኑም በክልል የተለዩ ናቸው፡፡ ስለዚህም ማንም በቀላሉ ወደ ሌላኛው ክልል ጥልቅ አይልም፡፡ ክስም ለመመሥረት አይቃጣም፡፡ ምክንያቱም የአስተዳደራዊ ግንኙነቱም ዙሪያ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ ግጭት ጫሪውን እና የሕይወት እና የንብረት ውድመት አድራሹን ግለሰብ ለፀጥታ እና ለሕግ አካላት ለማቅረብ ቢፈለግም ወንጀሉ የተሰራው በአንዱ ክልል፣ ወንጀለኛው የሚገኘው በሌላኛው ክልል ውስጥ ስለሆነ፣ የሁለቱን ወረዳዎች የጋራ የፀጥታ አካላትም ለማስተባበር ሁኔታው ቀላል ስላልሆነ፣ የመንግሥት አካላትም እንዲህ ዓይነቱ ተናጠላዊ ጉዳይ ውስጥ ተጣድፈው ጣልቃ ስለማይገቡ የሟች ደም በሟች ተቆርቋሪ ወገኖች እስከሚመለስ ድረስ “ደመ ከልብ” ሆኖ ይቆያል፡፡ ስለዚህም “ወንድነትን” በበጎነቱ የመመልከት፣ የማድነቅና የማህዘብ፣ ቀጣይነትም ይኖረው ዘንድ ሥነ ቃል መፍጠርም ግጭት፣ ጀግንነት ማለትም ወንድነት እና ማህበራዊ ከበሬታ ሰንሰለታዊ ተያያዥነት ያላቸው ዑደታዊ ክስተቶች እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ሁለቱ ሕዝቦች ቀደም ሲል እስከ ከ1983 ዓ.ም. ድረስ በአንድ ወረዳ ሥር በነበሩባቸው ዘመናትም ቢሆን በቀወትም ሆነ በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች የሚኖሩ የሟች ወገኖች ገዳይን ተከታትለው ለማስያዝ እና ለዳኝነት እንዲቀርብ የማድረግ ልማድ አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም ያኔም ቢሆን በተለይ የሰሙ ሮቢ ገለአሎ አፋሮች ግድያ

ቢፈፅሙም ወደቀያቸው ገብቶ መጥሪያ የሚሰጣቸው እና የሚከታተላቸው የፖሊስ ኃይል አደረጃጀት እና አሰራረር አልነበረም። ፖሊስ ወደ ወረዳቸው የሚገባው አጠቃላይ የፀጥታ ችግር ሲከሰት በዘመቻ መልክ ብቻ እንደነበር ነው መረዳት የተቻለው። እናም ሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች ለዘመናዊ ሕግ እና የፖሊስ እና የፍትህ ሥርዓት ቅርብ ተገገርዎች አልነበሩም።

በአንፃራዊ ሁኔታ ሲታይ ቀወቶች ከሰሙ ሮቢ ገለአሎዉች ይልቅ ለዘመናዊ ሕግ እና ሥርዓት አዳሪዎች ቢሆኑም እንኳን በሰሙ ሮቢ ገለአሎዎች ላይ ተናጠላዊ ግድያ ሲፈፅሙ ከሰሙ ሮቢ ገለአሎ በኩል ነገሬ ብሎ የሚከታተላቸው አልነበረም። ምክንያቱም አፋሮቹ ክስ የመመሥረትም፣ የመሟገትም ፍላጎት አልነበራቸውም። ዛሬም የላቸውም። ስለዚህ በሁለቱም በኩል ልማዱ ጥቃትን ዓይነት በዓይነት መመለስ ብቻ ነው።

በድንበርተኞቹ ሕዝቦች መካከል ጅምላዊ ግጭት ሲከሰት በሽምግልና የሚታይበት አግባብ እንዳለ በጥናቱ መረጃ ውስጥ ተስተውሏል። ይሁን እንጂ ሽምግልናው ቢኖርም የሽምግልና ሂደቱ ያልተጣሉ ሰዎች የሚሸማገሉበት እና የሚታረቁበት መሆኑ ታይቷል። ይሄም የዘመናችንን ዲፕሎማሲ የመሰለ ማለትም ዋና ተጋጪዎችን እና ተጎጂዎችን ያላሳተፈ፣ በአንፃሩ ግን ጅምላዊ ግጭትን ለመግታት ያህል ጎምቱዎቹ የሚያደርጉት መነቃነቅ እና ግጭት ማስታገስ ብቻ ነው ለማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ ደግሞ ሽምግልናው ሲካሄድም ሆነ ሲጠናቀቅ በእርቁ ማሳረጊያ ላይ በጋራ የሚፈፀሙ ልማዳዊም ሆኑ ኃይማኖታዊ መኃላዎቹ የሳሱ ናቸው። አንዳንድ ጊዜም አይኖሩም። አልፎ አልፎም ቢኖሩም ደግሞ በጋራ የሚታመንባቸው እና የሚፈሩም አይደሉም። ስለዚህ ለእርቅ ፅንዑነት አበርክቶ የላቸውም።

በአጠቃላይ ሁለቱ ድንበርተኛ ሕዝቦች ዛሬ የሚኖሩት የጥንት ገዚዎቻቸውን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ተረክ በእምነት እና በኃይማኖት ልዩነት /ተረክ/ ውስጥ ሰንቀው፣ እራሳቸውንም በነባርነት እና በባለቤትነት የተረክ ፋክክር ውስጥ ከተው፣ ዛሬም በተፈጥሮ ሀብት ሽሚያ በተለይም ውኃ ገብ መሬት ሳቢያ የሚገቡበትን ግጭት የወንድነት መለያ አድርገው እና ካለፉት ተረክ ውጤቶች ጋርም አያይዘው፣ ገዳይነትንም አወድሰው እና አሞግሰው ነው። ይህም በልማድነት የቀጠለ ግጭታቸው በአከባቢያቸው ዘመናዊ ትምህርት በስፋት እስከሚሰርፅ፣ ከተሞች እና ከተሜነት እስከሚስፋፋ፣ ኢንዱስትሪዎች እስከሚበራከቱ እና የገጠሩ ሕዝብ ሕይወት ወደ እነዚህ እስከሚሸጋገር

የሚቀጥል ይመስላል፡፡ ስለዚህም የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ለአንዴ እና ለመጨረሻ የሚያከትመው በሳይንስ ማመን የበላይነቱን ሲይዝ፣ ዓለማዊነት ሲያብብ፤ ኃይማኖት ሲያሽቆለቁል፣ በቀድሞ ታሪክ እና የጀግንነት መገለጫዎች ወጎች፣ ልማዶች እና ተረኮች ባህሎች መታጀል ሲያቆም ነው የሚመስለው፡፡ እነዚህ ህልው እስከሚሆኑ ድረስ ግን ግጭት እና ግጭትን ማስታገስ የአካባቢው የሕይወት ሂደት ከመሆን አይቀሩም፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች


ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፤ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፤ አንደኛ መጽሐፍ፤* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፤ 1982።

ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፤ *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም1900-1966* ፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፤1983።

*መጽሀፍ ቅዱስ* ፤ *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት፤ 1962።

*መንግሥቱ* ፍስሐ፤ "በርቱሳ፡-ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ" ፤ የኤም.ኤ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤1999።

*ሙሉጌታ ነጋሣ*፤ " በአድኣ ሊበን ወረደ የኦሮሞ ሴሬ ጨፌ ከግጭት አፈታት አንፃር"፤ የኤም.ኤ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 1997 ።

ሞላ *መኮንን* ፤ "በጉባ ላፍቶ ወረዳ የሸህ ለጋ ባህላዊ የግጭት ቁጥጥርና አፈታት" ፤ የኤም.ኤ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ፤1999 ።

ሰለሞን ተሾመ፤ "የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በስሬ ኦሮሞዎችና አማራዎች፡- ንፅፅራዊ ጥናት" ፤ የኤም.ኤ. ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 2002 ።

ሰለሞን ሣህሌ፤ "ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ሴሬ ኦሮሞዎች" ፤ የኤም. ኤ. ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤1998።

ስለሺ አባተ፤ "የሽካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት" ፤ የኤም.ኤ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 2002።

በላይ ግደይ አምሀ፤ *አክሱም*። አዲስ አበባ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፤1995 ።

ባህሩ ዘውዴ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 11847-1983* ፤አዲስ አበባ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፤1999 ።

ብርሃን አሰፋ፤ " ባህላዊ የግጭት አፈታት በወግዲና በቦረና ወረዳዎች"፤ የኤም.ኤ. ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤2002።

ተመስገን ምንዋጋው፤ "ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሔ ሥርዓት በዱኮ-ጋሞ"፤ የኤም.ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤1998 ።

ተስፋዬ አካሉ አበበ፤ *ኣጤ ቴዎድሮስ በሦስቱ ቀደምት ጸሓፍት፤ በደብተራ ዘነብ ኢትዮጵያዊ፣ በኣለቃ ወልደማርያም ዘምሁይ፣ ባልታወቀው ጸሓፊ፤* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ 2004 ።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፤* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም፤ ቀ.ኃ.ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፤1965 ።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፤ *ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፤* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፤1982።

ነፃነት መኮንን፤ "አበጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ"፤ የኤም.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፤1998 ።

አምባቸው ከበደ (ተርጓሚ)፤ *ከእንጦጦ እስከ ባሮ፤* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ ግል ማህበር ፤2005።

አበበ ኃይሉ፤ "ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ሥርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ" ፤ ኤም.ኤ.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ፤1999 ።

አብርሃም ታደሰ፤ *" ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ"፤* ኤም.ኤ ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 1999 ።

አጥናፍ ሰገድ ይልማ፤ *አቤቶ ኢያሱ አነሣሥና አወዳደቅ፤* አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤ 2006 ።

አየለ ፍቅሬ፤ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዶ (ወይጦ)" ፤ ኤም.ኤ ቴሲስ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤1998 ።

ኢትዮጵያውያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን፤ “ውይይት”፤ ቅፅ 2፣ ቁጥር 2 መጽሔት፣
አዲስ አበባ፣ 1961 ፡፡

ዓለሙ ካሣዬ፤ “ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ”፤
ኤም.ኤ.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ
ትምህርት ክፍል ፤1999 ፡፡

ዓለሙ ኃይሌ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ (1597-1625) የዐፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል፤*
(ከግዕዝ ወደ ወደ አማርኛ የተተረጎመ)፤ አዲስ አበባ፣ ሲራክ አሳታሚ ድርጅት፤
2005 ፡፡

ዓለማየሁ አበበ (ተርጓሚ)፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁኑ ዘመን፤*
አዲስ አበባ፣ ZA Printers ፣2006፡፡

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፤ *የአፄ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕል፤* (ግእዝና
አማርኛ) ፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤1999 ፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሰነዶች፤ “ሸዋ”፤ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ታሪኩ
ቤተመዛግብት፤ከ1940-1957 ዓ.ም.፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፤*አማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፤
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤1993፡፡

የወንድወሰን አውላቸው፤ *“ የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭትና አፈታት”*፤
የኤም.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ
ትምህርት ክፍል የቀረበ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤1998 ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ *የሥነቃል መምሪያ፤* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻሕፍት
ማዕከል፤ሁለተኛ ዕትም ፤1993 ፡፡

ያዕቆብ ኃይለማርያም፤ *አሰብ የማን ናት?* ፤አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤
2004፡፡

ይልማ ደሬሳ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን*፣ አዲስ አበባ፣
አዲስ አበባ፣ ሁለተኛ እትም፣1999፡፡

ይልማ ተፈሪ፤ “የሽምግልና ሥርዓት በወላይታ” ፤ ኤም.ኤ.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ
ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998፡፡

ዮሴፍ ተሸመ፤ “ በአሚባራ ወረዳ የአፋር ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ”፤
ኤም.ኤ.ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ

ትምህርት ክፍል ፤2002 ፡፡

ዮሴፍ ጌትነት፤ "ባህላዊ እርቅ በምስራቅ ጎጃም ዞን ደባይጥላትግን ወረዳ"፤ ኤም.ኤ ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል1998፡፡

ደበበ ዘውዴ፤ "በድሬዳዋ አስተዳደርና በሽኒሌ ዞን የሚኖሩ ኢሳዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት" ፤ ኤም.ኤ ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤2001 ፡፡

ገብሬ ይንቲሶ፣ፈቃደ አዘዘ፣አሰፋ ፍስሃ፤ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ፤* አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት የማስማማትና ዕርቅ ማዕከል፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፤ 2004 ፡፡

ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘ፣ አሰፋ ፍስሃ፤ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ፤* አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት የማስማማትና ዕርቅ ማዕከል፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፤ 2005 ፡፡

ጌታቸው ኃይሌ (ተርጓሚ)፤ *የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡-ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ፤* አዲስ አበባ ፤1997፡፡

ጌታቸው ኃይሌ (ተርጓሚ)፤ *ደቂቀ እስጢፋኖስ "በሕግ አምላክ"*፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ 2003 ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፣ አሰፋ ፍስሃ፣ ገብሬ ይንቲሶ፤ *በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ላይ የተከናወኑ ጥናቶች ኑትት መዘርዝር*፤ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት የማስማትና ዕርቅ ማዕከል፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፤ 2004፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ *ሰሚ ያጡ ድምፆች፤* አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ቤት ፤1996 ፡፡

*ፍትሐ ነገሥት፤* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤1958 ፡፡

ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፉቸው ደብዳቤዎች፤* አዲስ አበባ፤ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፤2003

Ahmed Hassen Omer. "State and Ethnic Relations in North Eastern Shawa /Ethiopia/1912-1935 in Ethiopia in Broader Perspective". Ed. Katsuyoshi Fukui, Eisei Kurimoto, Masayoshi Shegeta. Vol.1, xiiith Inetrnational Conference of

Ethiopian Sudies, Kyoto, 12-17 December 1997.

Ahmed Hassen Omer. "A Historical Survey of Ethnic Relations in Yefat and Temuga, North-Eastern Shoa (1889-1974)". M.A.Thesis for the Department of History, A.A.U., 1994.

Ahmed Hassen Omer. State and Ethnic Relations in North Eastern Shawa/Ethiopia/ 1912-1932.pp 138-149 in 13th International Volume 1.Kyoto,1997.

Akmel Mohammed Usman. "The Vitality of Local Institutions of Conflict Resolution among the Afar: The Case of Samu Robi Galao Wereda".

Alula, Pankhurst and Getachew, Assefa.editors. *Grass-roots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolution.* Addis Ababa: United Printers Plc., (2008).

Anderson J. Walker, Foster, Kuehn M. and McKinney Bruce. *Communication: Skills for Surviving Conflicts at Work.* New Jersey: Hampton Press, 1999.

Assefa, Jalta. *Oromia and Ethipia Satate Formation and Ethno-national Conflict 1862-1992.* London: Lonne Rienner Publishers, (2005).

Assefa, Tolera. "Ethnic Integration and Conflict: The Case of Indegeneous Oromo and Amhara Settlers in Aaroo Addis Alem, Kiramu Area, North-Eastern Wellega".ed.

Alula Pankhurst.Addis Ababa.A.A.U.,2009.

Asnake Menbere. "Inter Group Conflicts in the Awash Valley of Ethiopia: The Case of the Afare and Karrayu Oromo. M.A.Thesis for Addis Ababa University, 2010.

Aspen, Harald. "Spirits, Mediums, and the Human Words: The Amhara Peasants Of North Ethiopian Highlands and their Traditions of Knoweledge". University of Trondheim, Ph.D.Thesis, 1994.

Atikilt Daniel. "Farmer-Herder Conflict over Natural Resources in Northern Ethiopia: The Case of Qewet Wereda in North Shewa Zone of the Amhara State". M.A. Thesis for the Department of Regional and Local Development Studies: A.A.U., 2003.

Augsburger, David. *Conflict Mediation across Cultures*. London: West Minister, Joh Tenox Press, 1992.

Avruch, Kevin. *Culture and Conflict Resolution.* Washington: United States Institute of

Peace, 4th ed., 2004.

Avruch, Kevin.*Conflict Resolution.In Encyclopedia of Cultural Anthropology*, Volume 1, 1996.

Ayalew, Gabre. "The Arbore of Southern Ethiopia: A study of Inter-Ethnic Relations, Social Organizations and Production Practices". M.A.Thesis in Social Anthropology. A.A.U., 1995.

Bairu Tafla. *Asma Giorgis and His Works .History of the Galla and the Kingdom of Sawa*. Stuttgart, 1987.

Bartos, J. and Wher.*Using Conflict Theory*. UK: Cambridge University Press, 2001.

Bangura, Abdulkarim. (Ed.) *Research Methodology and African Studies*. Lanham, Mary land: University Press of America, 2007.

Berihun Mebrate. "Spontaneous Settlement and Inter-Ethnic Relations in Matekal, North West Ethiopia". M.A. Thesis A.A.U., 1996.

Betelhem Bayssaw. "Inter-Ethnic Conflict in Ethiopia: The Case of Karayu Oromo and Amhara." M.A.Thesis, A.A.U., 2010.

Boulding, Kenneth. *Conflict and Defense*. New York: Harper & Row Publishers, 1962.

Burton, John, (ed) .*Conflict: Basic Human Needs*.New York: St. Martin's Press,1990.

*The New Narrative Research in Education*. Reviw of Research in Education. http:/www.readingonline.org.7/6/2009/

Central Statistical Agency.*Population Census Commission, Population Size by Age and Sex*. Addis Ababa, 2008.

Chernet Tilahun. "Traces of Islamic Culture in Northern Shoa region". In Ahmed Zekaria & Taddese Beyene, (eds.). Proceedings of the first National Conferenceon Ethiopian Studies (A.A.U. IES, PP, 304-312, (1990).

Coser, Lewis. *Conflict and Order: Understanding Society.* 4th edition. Massachsetts: Allyn and Bascon, 1998.

Coser, Lewis. "Conflict, Social Aspect". International Encyclopedia of Social Sciences Vol.3.232-236. The mac millan Company & Press, 1968.

Coser, Lewis.*The Functions of Social Conflict.* New York: The Free Press, 1968.

Creswel, John. *Research Design: Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approaches.* California: Sage Publications, 2009.

Dan-Ben-Amos /http: /www. readingonline. jestor.org. 6/6/2012)::

Das, Veena. "The Anthropology of Violence and the Speech of Victims".In Anthropology Today (4):11-13.

Dejene, Gemechu. "Conflict and Conflict Resolution among the Walliso Oromo of Eastern Macha : The Case of the Gumo". Addis Ababa,A.A.U.,2007.

Deusdendit, R.K.Nkurunziza., Levis Muguma (Eds). *Developing A Culture of Peace and Human Rights in Africa.* Kambala: Konrad- Adeauer- Stiftung, 2003.

Deutsch, Morton, "Toward an Understanding of Conflict". International Journal of Group Tensions 1 (91971), 42-54.

Deutsch, Morton, "Conflicts: Productive or Destructive?" Journal of Social Issues 25 (1969), 7-41.

Eitzin, D.S.and Zinn, M.B. *In Conflict and Order: Understanding Society*. Massachsetts, Allyn & Bacon, 4th (Ed), 1998.

Ember Carol R.and Ember, Melvin. *Cross Cultural Research Methods*. New York: Altamira Press, 2009.

Eshleman, Ross, Cashion, Barabara, Basirico, Laurence. Sociology: An Introduction. New York: Harper Collins College Publishers, 4th Ed,1993.

*Encyclopedia Aethiopica*: Volume 4 O-X; Otto Harrassowith /Verlag.Wiesbaden, 2010.

Fisher, Ronald. *Social Psychology፡An Applied Approach.*New York: St.Martin's Press, 1982.

Fisher, Ronald in Zartman,William & Rasmussen,Lewis (1997). *Peace Making In International Conflict: Methods and Techniques:* Washington,United States Institute of Peace, 2005.

Fisher and Ibrahim. *Working with Conflict፡ Skills and Strategies for Action.* London: Bath Zed Books,2000.

Finnegan, Ruth. *Oral Literature in Africa*. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Galtung. John.*Theories of Conflict: Definitions, Dimensions, Negations, Formations.* University of Hawai' I, 1973.

Getachew Kassa Nigussie. *Among the Pastoral Afar in Ethiopia: Tradition, Continuity and Socio-Economic Change*.International Books in association with

OSSERA.Drukkerij and Haasbeek: Numankade, 2001.

Getachew Talachew and Shimels Habtewold. "Customary Dispute Resolution in Afar Society." In Grass Roots Justice in Ethiopia.The Contribution of Customary Dispute Resolution, ed. Alula Pankhurst and Getachew Assefa, 93-106.Addis Ababa: French Center of Ethiopian Studies,2008.

Glasser, Barney and Strauss, Anselm.*The Discovery of Grounded Theory:Strategies for Qualitative Research.*New Jersey: Rutgers-The State University, 2006.

Gray, Jerry. *Organizational Behavior and Applications.* The University of Manitobia. Charles Merril Publishing Company, 1984.

Greenfield, Richard. *ETHIOPIA: A New Political History.*London: Pall Mall Press, 1965.

Guliver, P.H.*Disputes and Negotiations:A Cross-Cultural Perspective*. New York. Academic Press, 1979.

Huntington, Samuel.*The Clash of Civilizations.* New York: Simon and Schuster.1993.http:// www. Proceestext.Com/ abclit.html.

Harcourt, S. *Coalitions and Alliances in Humans and Other Animals.* Hutchinson & Smith Oxford: Oxford University Press, 1992.

Http: //en WikiPedia Org/wiki/. "Social Conflict Theory". (10/9/2012

Imobigne, T.A. *The OAU (AU) and OAS in Regional Conflict Management: A Comparative Assesment.* Ibadan: Spectrum Books International Encyclopedia of Social Sciences , 2003.

Jones, A. H.M. and Monroe, E. *A History of Abyssinia*: Oxford: Clarendon Press, 1935. http://www.academicjournals.org/AJHC

Kelemework, Tafere.(2011). "Conflict and alternative dispute resolution among the Afar Pastoralists of Ethiopia". African Journal of History and Culture (AJHC) Vol. 3(3), pp. 38-47, April 2011. http://www.academicjournals.org/AJHC.

Kelemework Tafere. "Indigenous Institutions of Conflict Resolution among the Aba'ala, Afar of North-Eastern Ethiopia". M.A.Thesis, A.A.U. 2006.

Kiros Habte Selassie and Mazengia Dina.(Ed). *Ethiopia: A Short Illustrated History.* Addis Ababa: Berhanena Selam Haile SElassie I Printing Press,1972.

Kottak, Philip.*Cultural Anthropology*. New York: Mc Graw-Hill Inc, 5th ed.,1991.

Kreidler, W. "*Creative Conflict Resolution.More than 200 Activities for Keeping Peace*

*in the Classroom"*. Glenview, IL: Scott, Foresman & Company, 1984.

Kuper, Adam and Jessica Kuper (Eds). *The Social Sience Encyclopedia*, 2nd Edition. London: Routledge, 1996.

Levine, Donald. *Greater Ethiopia:The Evolution of Multi Ethnic Society*. Chicago: Univresity of Chicago, 2nd ed., 1979.

Levine, Donald. Wax and Gold: Tradition and Innovation in Ethiopian Culture.Chicago University of Chicago Press 5th Ed, 1972.

Levine, Donald N. "The Military in Ethiopian Politics: Capabilities and Constraint". In H. Bienanen, ed. The Military Intervenes. New York: Rusell Sage Foundations 1968.

Levinson, David and Melvin Ember (Ed). *Encyclopedia of Cultural Anthropology*, Vol.2.New York: Henry Holt and Company,1996.

Lewis, Ioan M. *Peoples of the Horn of Africa: Somali, Afar and Saho*. London. International African Institute, 1955.

Lisa, and Elinore .(1997).www.jestor.org.7/7/2012.

Lisa and, Elinor. "Journal of Narrative and Life History". Lawrence Erlbaum Associates, Inc, 1997.

Lulofs, Roxane and Cahn, Dudley. *Conflict From Theory to Action*. New York: Allyn and Bacon 2nd ed, 2000.

Markakis, John. *National and Class Conflict in the Horn of Africa*. Cambridge University Press, 1987.

Markakis, John. (ed). "Ethnicity and Conflict in the Horn of Africa".Ohio University Press, Athens, 1994.

Mayer, Bernard.*The Dynamics of Conflict Resolution*. John Wiley and Sons. Inc,2000.

Medhane Tadesse. "The Afar-Issa Conflict: Towards Functioning Dispute Settlement Regime.The Quest for Conflict Settlement in Ethiopia's Periphery".A.A.: Center for Policy Research and Dialogue, 2006.

Mordechai, Abir. *Ethiopia and the red sea: The rise and fall of the Solomonic Dynasty and Muslim-European Rivalary in the Region*. London: Frank Cass and Co.Ltd, 1980.

Mordechai ,Abir,. *Ethiopia: The Era of Princes, 1769-1855*. London: Longman Publising

Ltd.,1968.

Okpewho, Isidore.*African Oral Literature:Backgrounds, Character, and Continuity.* Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1992.

Paul , A. *A History of the Beja Tribes of the Sudan.*Cambridge: Cambridge University Press, 1954.

Markakis, John. *National and Class Conflict in the Horn of Africa.* Cambridge University Press, 1987.

Paul, A. *A History of the Beja Tribes of the Sudan.* Cambridge: Cambridge University Press, 1954.

Pearce, Barnett and Little, John, Stephen. *Moral Conflict: When Social Worlds Collide.* California: Sage Publications Inc, 1997.

Proctor, James, D. ed. *Science-Religion, and the Human Experience.*New York: Oxford University Press, 2005.

Polkinghorne, Donald E. *Narrative Knowing and the Human Sciences.*New York: State University of New York Press, 1988.

Reminic, Ronald A. *The Manze Amhara of Ethiopia: A Study of Authority Masculininity and Sociality.* A Dissertation of the Social Sciences in candidacy for the Degree of Doctor of Philosophy.University of Chicago, Department of Anthropology,1973.

Rummel፣ // http: /www. hawaii edu/powerskills 10/9/2012።

Salzman, Carl. *Understanding Culture: An Introduction to Anthropological Theory.* Illinois: Waveland Press, 2001.

Sandole, Dennis J. D., Byrne, Sean, Sandole-Staroste, Ingrid and Senehi, Jessica. *Hand Book of Conflict Analysis and Resolution.* Milton Park, Abingdon, Oxon: Routledge,2009.

Schellenberg, James A.*Conflict Resolution: Theory, Research and Practice.* New York: State University of New York Press, 1996.

Scholes, Robert. "Language, Narrative and Anti-Narrative". In W.J.T.Mitchell (Ed). On Narrative.Chicago-London: Universityof Chicago Press, pp 200- 208. (1981).

Samovar, Larry A.and Porter, Richard, E. *Inter Cultural Communication: A Reader.*

California: Belmont.Wadsworth Publishing Company, 1972.

Seymour, Smith. *The Dictionary of Anthropology***.** London: The Macmillan Press, 1986.

Syms, Martha & Stephens, Martine**.** ***Living Folklore.*** Logan: Utah University Press, 2000.

Stitz, V. "Amhara Resettlement of Northern Shewa during the 18th and 19th Centuries". A.A. Haileselassie I University. Pp 5-6 mimeogphed, 1970.

Tadesse Tamrat. *Church and state in Ethiopia*. Oxford Clarendon Press, 1972.

Tirisit Girshaw. "Indigeneous Conflict Resolution Mechanisms in Ethiopia፡The Afar Society". In First National Conference on Federalism, Conflict and Peace Building (ed). Gebreab Barnabas,56-57.A.A.United Printers Plc., 2003).

Trimingham, J.Sencer. *Islam in Ethiopia.* Oford University Press, 1965.

Trimingham, J.Spencer.*The Proceedings of the first United States conference on Ethiopian studies.* East laning.Michigan state university, 1975.

Yusuf Fadl Haan. *The Arabs and the Sudan*. Kharoum: Khartoum University, 973.

Yohannes Biirhanu. "Conflict and Conflict Resolution Among the People of Chihera**."** M.A. Thesis, A.A.U.,1998.

Zaretman, William and Rassmusen, Lewis. *Peace Making In International Conflict: Methods and Techniques:* Washington, United States Institute of Peace, 2005.

Zartman, William.Negotiation as a Joint Decission-Making Process". The Journal of Conflict Resolution, Vol. 21.No.4, December 1977, 619-638.

# አባሪ አንድ፡-ሥነቃል፡- ከቀወት ወረዳ የተሰባሰቡ ግጭት ተኮር ሥነቃሎች

## ሀ/ የአማርኛ ሽላሎ ግጥሞች

ከዚህ በታች የቀረቡት እና በተለያዩ ዘውግ የሚገኙት ግጭት ተኮር ሥነቃሎች ከቀወት ወረዳ የተሰበሰቡት በመጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ጭውውት ወቅት ነው፡፡ ለመጠይቁ ምላሽ የሰጡት እነ ጥላሁን ደምሴ፣ አንበርብር ጣሰው፣ ፍርዴ ሞላ፣ አበባው በድሉ፣ እምሬ ታቦር፣ ሰይፈ በለጠ 9A፣ ቤዛ ሰለሞን፣ ሂሩት አጉኔ፣ በለጠ ጣሴ፣ አድነው ተስፋዬ፣ ገነነ ተሰማ፣ ድረሴ ይልማ 9B፣ ከሸዋ ሮቢት መሰናዶ ትምህርት ቤት (ግንቦት 5-15/2002 ዓ.ም.) ሲሆን ቃለ መጠይቁ እና ጭውውቱ የተደረገው ደግሞ በአባሪ አራት ከተዘረዘሩት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎቹ ነው፡፡

1) ብለነው ብለነው ካልሆነ ነገሩ፣
ወርቅና ወንድ ልጅ የትም ነው አገሩ፡፡

2) የከፋው ሰው፣
የቆጨው ሰው፣
ወንድሙን ይገድላል እንኳንስ የሰው ሰው፡፡

3) ጎራው ጎራው ብሎ ምንድነው ምላሹ፣
አዲሱን ጠመንጃ በደም ካላሚሹ፡፡

4) እንኳን ግደል ብለው እንኳን ሰደውት፣
ከወገብ ላይ ሆኖም ያኮራል ጥይት፡፡

5) ወርካ ሞኙ ሳያብብ ያፈራል፣
አንዱን ካልገደሉት አንዱ መቼ ያርፋል፡፡

6) ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው፣
አስቀድሞ መግደል አሾክሻኪውን ነው፡፡

7) አለ ነገር አለ ነገር፣
ቁልቁለቱን ወርደን ወንዙን ስንሻገር፡፡

8) ስፈር ቀለብ ስፈር ዘንጋዳ፣

ግዳይ ለሌለው ስፈር ዘንጋዳ፣
ቢኖር አይጠቅም ቢሞት አይጎዳ።

9) አላቅራራም ብዬ ማላ ነበረብኝ፣
አንጎራጉራለሁ መሰደብ በዝቶብኝ።

10) በዲሞትፈር ጥይት ካልጎደጎዱት፣
በምንሽር ጥይት ካልጎደጎዱት፣
ቡክን አይጎዳም ሚስቱን ቢወስዱበት።

11) አይዞሽ ምንሽሬ ይገፎሽ እዞራለሁ፣
ውኃ ጠማኝ ብትይ ደም አጠጣሻለሁ።

12) ይህን ሣራችንን እስቲ ምን ይበጀው፣
ወይ ከብቶቹ አልበሉት ወይ እሳት አልፈጀው።

13) ስጡኝ መሣሪያ ከጥይት ጋራ፣
ግዝት ያርግብኝ አፋር ብፈራ።

14) ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ፣
ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ፣
ጎረምረም ጎረምረም ካላለ አንደበቱ፣
ያገባት የለም ወይ ሚስቱን ጎረቤቱ።

15) አረ ጥራኝ ቻካው አረ ጥራኝ ዱሩ፣
ላንተም ይሻልኃል ብቻ ከማደሩ።

16) አረ ጅል የሞተው አረ ጅል የሞተው፣
ሚስቱን ወሰዱለት በገመድ ጎትተው።

17) ይወለድና ጥርሰ ነጫጭ፣
የጋለሞታ ከንፈር መጣጭ።

18) አሯል ሆዴ ነዷል ሆዴ፣
እየቸገረኝ ነው ጠላቴን መውደዴ።

19) ወንድም የሌለው ሰው የሌለው አባሪ፣
ትከሻው ላይ ቀረ የዱላው ስባሪ።

20) ጥራኝ ደኑ ጥራኝ ዱሩ፣
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ተማደሩ።

21) ነካካቸው ጎንትላቸው አትስጣቸው ጤና፤
ምንጊዜም ደህና ሰው አይሉህምና።

22) ታረሰ አሉ ይፋት በጥቋቁር በሬ፣
ዘንጋዳ ሲዘሩት ሊያበቅል በርበሬ።

## ለ/ የአማርኛ ፉከራ ግጥሞች

1. ፈረሱ ዳማ ጭራው ቁጥርጥር፣
   ሳይዝ አይመጣም በወጣ ቁጥር።
2. ቡፍ ቡፍ ባይ እንደ ጉሽ ጠላ፤
   አባቱ ነብር ልጁ ግስላ።
3. አጅሬ ይፋት አጅሬ ራሳ፣
   እንደ አሞራ ነው ገድሎ ሲነሳ።
4. እሱስ ገዳይ ነው ነጌሶ፣ አባያ፣
   ጠላቱን ገዳይ መሃል ገበያ።
5. ቁጭ ብድግ ባይ እንደ ጋጋሪ፣
   በዝሁር ገድሎ በሱር ቀባሪ፣
6. ቀይ አዳል ገዳይ ባለሻህ አድሪ።
   ብቻውን ሲሄድ የለው ተመልካች፣
   ቀይ አፋር ገድሎ ምንሽር አንጋች።
7. እጥፍጥፍ ያለው እንደ ነጠላ፣
   አተኳኩሱ በድንጋይ ጥላ።
8. አተኳኩሱ መሬት ለመሬት፣
   ሐሰት ከሆነ ይንገር ጎረቤት።
9. አባሮ ገዳይ እቁልቁለቱ፣
   በረሃ ለምዶ በልጅነቱ፣
10. በተወለደ በአሥር ዓመቱ፣
    አፈሰሰበት ጥይት በአንገቱ።
11. ገለል ብሎ ወዲያ ሲነሳ፣

የሌሊት አውሬ የቀን ጃቡሳ፡፡

12. የማነው ይላል እሱ የማነው፣
እንደ ቅዳሜ ሁሉ ያወቀው፣
ወንድ የወንድ ልጅ ወንድ ያሳደገው፣
እንደ ፈጣሪ ያስደገደገው፡፡

13. ጎድፈር ጎድፈር አርጎ ይተኛል ነብር፣
አወይ ባባት አገር ተጨንቆ መኖር፡፡

14. እልም ነው ጭልጥ ነው ውኃ አይላመጥም፣
ጠላት ወዳጅ ላይሆን አልለማመጥም፡፡

15. ይተኩሷል እንጂ ቆንጥር አዘልሎ፣
አያባብሏትም ሴትን እንደ በቅሎ፡፡

16. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ፣
ወደ ዳገት በሉት ሳር ይብላ እንደ በሬ፡፡

17. አጋሙን ቀጋውን ትጥላለህ ምነው፣
አምላክን በሸሸት ያመለጠው ማነው፡፡

18. እሱ ሞቶ ሰው ይዞ ለመሞት፣
ተከትሎታል ወይ የነገር ጥልማሞት፣
ፍየል ቅጠል በልቶ ልቡ ቢሰባበት፣
እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት፡፡

19. ዲሞትፈር ክላሽን ምንሽር አንድ ነው ዓይነቱ፣
ተኳሽ ከተገኘ ከተት ያለ አሞቱ (አንጀቱ)፡፡

20. በለው በለውና አሳጣው መድረሻ፣
ጃስ ኩቲ ሲሉት ነው የሚባላው ውሻ፡፡

21. አገራችን ይፋት ውልዳችን ደንገዜ፣
ማን አባቱ ያዛል እምቢ ባልን ጊዜ፡፡

22. አየር ነው ወይ ሰማይ ነው ወይ ቤቱ፣
የኛ ቤት ተቃጥሎ የሱ መሰንበቱ፡፡

23. እርሳሱ መርዘኛ አንጎል የሚያዞር፣
ጋሻው ሀረጣ አንጎል የሚያዞር፣

ይህን እየሰራ ያኖረኝ የነበር፣
የአገሬ ጅግና አፋር ሲያባርር፡፡
24. ፊሪ ልጅ እምድጃ አመዱን ይጭራል፣
ጅግና ልጅ አረህ ላይ በደም ይጨቀያል፡፡
25. እሰይ የይፋት ልጅ አንበሳ ግልገሉ፣
ጎራዴው ቢሰበር ገባው በሽመሉ፡፡
26. ዘራፍ ብሎ ዘራፍ ሲነሳ፣
የሌሊት አውሬ የቀን ጃቡሳ፡፡
27. ኩፍ ኩፍ ባይ እንደ ጉሽ ጠላ፣
አባቱ ነብር ልጁ ግሥላ፡፡
28. እርካቡ አጫጭር ግላሱ ያውሬ፣
መንኖ ገዳይ በሰው ቀበሌ፡፡
29. ብቻውን ሲሄድ የለው ተመልካች፣
ቀይ አፋር ገድሎ ምንሽር አንጋች፡፡
30. ከታች ይገድላል ከታች ከግርጌ፣
አለሁ መጣሁ ሲል የአፋር ባለጌ፡፡
31. ከኋላ ሲሉት ይቀድማል ከፊት፣
እንደ ደንቃራ ገዳይ ከሰው ፊት፡፡
32. መገን የራሳ ልጅ እነ ጥይት ኪሱ፣
ምን ጌዜ ሰሙና ምን ጊዜ ደረሱ፡፡
33. እጥፍጥፍ ያለው እንደ ነጠላ፣
አተኳኮሱ በድንጋይ ጥላ፡፡
34. እጥፍ እጥፍጥፍ እንደ ኩታ ልብስ፣
አተኳኮሱ አንጀት የሚያርስ፡፡
35. ዱብ ዱብ አለ እንደ በረዶ፣
በልጅነቱ በረኃ ለምዶ፡፡
36. የአንተ ጎራዴ ምንድነው ጉዱ፣
እንደ ጨጎጎት ቋንጃ መውደዱ፡፡
37. ይገድሏል እንጂ አባ ዱላውን፣

የሌሊት አውሬ የቀን ጃቡሳ።

12. የማነው ይላል እሱ የማነው፣
እንደ ቅዳሜ ሁሉ ያወቀው፣
ወንድ የወንድ ልጅ ወንድ ያሳደገው፣
እንደ ፈጣሪ ያስደገደገው።

13. ጎድፈር ጎድፈር አርጎ ይተኛል ነብር፣
አወይ ባባት አገር ተጨንቆ መኖር።

14. እልም ነው ጭልጥ ነው ውኃ አይላመጥም፣
ጠላት ወዳጅ ሳይሆን አልለማመጥም።

15. ይተኩሷል እንጂ ቆንጥር አዘልሎ፣
አያባብሏትም ሴትን እንደ በቅሎ።

16. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ፣
ወደ ዳገት በሉት ሳር ይብላ እንደ በሬ።

17. አጋሙን ቀጋውን ትጥላለህ ምነው፣
አምላክን በሽሽት ያመለጠው ማነው።

18. እሱ ሞቶ ሰው ይዞ ለመሞት፣
ተከትሎታል ወይ የነገር ጥልማሞት፣
ፍየል ቅጠል በልቶ ልቡ ቢሰባበት፣
እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት።

19. ዲሞትፈር ክላሽን ምንሽር አንድ ነው ዓይነቱ፣
ተኳሽ ከተገኘ ከተት ያለ አሞቱ (አንጀቱ)።

20. በለው በለውና አሳጣው መድረሻ፣
ጃስ ኩቲ ሲሉት ነው የሚባላው ውሻ።

21. አገራችን ይፋት ውልዳችን ደንገዜ፣
ማን አባቱ ያዛል እምቢ ባልን ጊዜ።

22. አየር ነው ወይ ሰማይ ነው ወይ ቤቱ፣
የኛ ቤት ተቃጥሎ የሱ መሰንበቱ።

23. እርሳሱ መርዘኛ እንጎል የሚያዞር፣
ጋሻው ሀረጣ እንጎል የሚያዞር፣

ያንገቱ ሻሚ የሚያበራውን፣
እጁን ማልዲያ የበላላውን፣
እራሱን ሽበት የወረረውን፣
አንድ ቤት ሙሉ የወለደውን።

## ሐ/ የአማርኛ ሙሾ ግጥሞች

1. አንተ የራሳ ሜዳ እፋረድሃለሁ፣
   አንተ የአዋዲ ጫካ እፋረድሃለሁ፣
   ብዙ ወንድሞቼን ገብሬብሃለሁ።
2. የራሳንም እህል አልበላም እርሜ ነው፣
   ያዋዲንም እህል አልበላም እርሜ ነው፣
   ያረሰው ነጭ ቃታ ያበቀለው ደም ነው።
3. ዙጢ ገበያው ላይ በቤልጅግ አራሚ፣
   ደፋ ብሎ ቀረ እንደ እንጨት ለቃሚ።
4. ሲዋጋ ዋለና አመሻሽ ተጋተው፣
   ተረታ መሰለኝ ዘፍ አለ ፊታቸው፣
   የተቆጣ ነብር የሚያስፈራ ግርማው።
5. የሰው ጉድ እላለሁ ጉድ በራሴ ሞልቶ፣
   የጎበዝ ዝርያ በአፍጢሙ ተደፍቶ።
6. የተቆጣ ነብር ግርማው የሚያስፈራው፣
   ምን ወንደ አገኘና እጅ እግሩን አሰረው።
   ምን ወንድ ደፍሮ ነው እጅ እግሩን ያሰረው።
7. እጊዮርጊስ ጓሮ ስንደዶ እምትቀጪ፣
   ጀግናው ሁሉ ወደወቷል እንዳትረጋግጪ።
8. እንግዲህ ወደ ላይ ምን ያስወጣናል፣
   እንግዲህ ወደ ታች ምን ያስወርደናል፣
   ለዛሬ ሙያችን ጀግናው ይበቃናል።
9. ጠመንጃህም ለሰው አገርህም ለሰው፣
   እንግዲህ ባላንጣ አንጀቱን ያርሰው።
   እፈረስ ላይ ሆኖ ምርቱ እሚታፈሰው፣

አንተ ያገር ጀግና ቀረህ እንደ አንድ ሰው።

10. ጀግና ነው ይላሉ የታል ጀግንነቱ፣
ወንድ ነው ይላሉ የታል ወንድነቱ፣
በክር አይደለም ወይ የታሰረው ጣቱ።

11. በስተደጋም በኩል ዝናቡ ዘነበ፣
በስቆላም በኩል ዝናቡ ዘነበ፣
ዘር ያላችሁ ዝሩ የኛ ዘር ቀዘበ።

12. መንዝንም ተጋኘው ክፍቱን አደረና፣
ወደራም ተጋኘው ክፍቱን አደረና፣
ይፋትም ተጋኘው ክፍቱን አደረና፣
ያጥሩ ባለቤት ተኳሹ /እከሌ/ ቀረና።

13. ሲዋጋ ዋለና አመሻሽ ተጋተው፣
ተረታ መሰለኝ ዘፍ አለ ፊታቸው፣
የተቆጣ ነብር የሚያስፈራ ግርማው።

14. የሰው ጉድ እላለሁ ጉድ በራሴ ሞልቶ፣
የጎበዝ ዝርያ በአፍጢሙ ተደፍቶ።

15. የተቆጣ ነብር ግርማው የሚያስፈራው፣
ምን ወንድ ደፍሮ ነው እጅ እግሩን ያሰረው።

16. እጊዮርጊስ ጓሮ ስንደዶ እምትቀጪ፣
ጀግናው ሁሉ ወደወቋል እንዳትረጋግጪ።

17. እንግዲህ ወደ ላይ ምን ያስወጣናል፣
እንግዲህ ወደ ታች ምን ያስወርደናል፣
ለዛሬ ሙያችን ጀግናው ይበቃናል።

18. ጠመንጃህም ለሰው አገርህም ለሰው፣
እንግዲህ ባላንጣ አንጀቱን ያርሰው።
እፈረስ ላይ ሆኖ ምርቱ እሚታፈሰው፣
አንተ ያገር ጀግና ቀረህ እንደ አንድ ሰው።

19. እህል የጠፋ እንደሁ ይገኛል ባመቱ፣
ያባት ቃርሚያ የለው አንድ ጊዜ ከሞቱ።

20. የጊዮርጊስ መሬት እዚህ ተጎልቶ፣
ፊሪውን ይበላል እንኳን ጀግና አግኝቶ።

21. ፈሪ ቡና ጠጣ ስኳር ጨምረህ፣

ጀግናው የጀግናው ልጅ ሞተልን ብለህ።

## መ/ የአማርኛ የፍቅር ዘፈኖች

ገዳዬ ገዳዬ ገዳይ እወዳለሁ፣
ተኳስም አልጠላ ሲደክመኝ አርፋለሁ፣
ከጎፈሬው ጥላ።
ጥርስሽ ፍልቅቅ ፍልቅቅ፤ዓይንሽ ወጋ ወጋ፣
ዘመዶችሽ ብዙ ከስንቱ ልዋጋ።

## ሠ/ የአማርኛ የሰርግ ዘፈኖች

1) አናስገባም በሩን፣
ሰርገኛውን።
2) አጀባዬ አጀባ፣
ሁኗል ጭብጨባ፣
3) በየት ሊገባ።
አንተ የኔ ሎጋ፣ (2)
4) የሙሽራው ጎራዴ፣
ውስጡ አረንጓዴ።
5) አባቷ ጨዋ ሽንኅ አስታራቂ፣ (2)
እናቷ ጨዋ እንዝርት አራቂ፣ (2)
ልጅቷ ክብሯን ጠባቂ።
6) ኧረ ይሂት ተነሳ። (2)
የእከሌ አንበሳ፣
ኧረ ይዘህ ተነሳ፣
እንዳይነጥቅህ አንበሳ።
7) ኧረ ይዘህ ብረር፣
እንዳይነጥቅህ ነብር።

## ረ/ የአማርኛ የወፍር /የሥራ/ እንጉርጉሮ

1. አሆ በል ጎበዝ አሆ በል ጀግና፣
   የምርቱ ጀግና የጠሩ ዳኛ።
2. በሮቹ ጥቋቁር ጅራታቸው ፈንዛ፤
   ሰርተው እንዳይበሉ ምቀኛቸው በዛ።
3. በሬው ቀብራራ ሞፈሩ ወይራ፣
   መታለሚያው ላይ አይገኝ ውራ።
4. ናውጣ ና ውረድ ሲል እየሰማሁት፣
   የጠመደበትን ሥፍራውን አጣሁት።
5. መጋል መጋል ሆይ፣
   ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ።
6. እኔና በሬዬ አርሰንም ጠግበናል፣
   ከኛም አልፎ ተርፎ ለሌላም በቅተናል።
7. እርሻ እረሱ ለእርሻ አትመለሱ፣
   ቡና እንኳን ሲፈላ ይቸግራል ቁርሱ።
8. እዚያም እዚያም ማለት አይወድም ገላዬ፣
   ከነዶባ ጋር ነው ዘወትር ውሎዬ።

## ሸ/ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች

1) ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ።
2) ፍል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ።
3) የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው።
4) የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል።
5) ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ።
6) ዓይጥ በበላ ዳዋ ተመታ።
7) እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ።
8) አለባብሰው ቢያርሱ ባረም የመለሱ።
9) ምንም ቢከፉ ዘመድ፣ ምንም ቢጠብ መንገድ።

10) አህያውን ቢፈሩ ዳውላውን፡፡

11) ለምን ያለው ስልቻውን ጫን ያለው ኮርቻውን አያጣውም፡፡

12) ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል፡፡

13) ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ፡፡

14) በሬ ካራጁ ይውላል፡፡

## ሰ/ የአማርኛ ተረቶች

### አያ ጅቦ እና ተኩላ

አያ ጅቦና ተኩላ በአንድ መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ሁለቱ በጣም ከመቀራረባቸው የተነሳ አንድ ቀን አያ ጅቦ አንድ ሐሳብ እንዲህ ሲል አቀረበ፡፡ "ወዳጄ ኑሯችን እንዲሻሻል ከብት አናረባም ወይ?" አለ፡፡ ተኩላም በሐሳቡ በመደሰት "አያ ጅቦ ይህ ሐሳብ እንዴት መጣልህ ጥሩ ሐሳብ ስለሆነ ቶሎ ልንፈፅመው ይገባል" አለው፡፡ ከዚያም ገበያ ሄደው አያ ጅቦ በሬ ሲገዛ፤ ተኩላ ደግሞ ላም ገዝተው ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡

በመጀመሪያ ቀን ተኩላ ከብቶቹን ለግጦሽ አሰማራ፡፡ በደንብ ጠብቆም ወደቤታቸው መለሳቸው፡፡ አያ ጅቦም በተራው እንዲሁ አደረገ፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ አብረው ከቆዩ በኋላ የተኩላው ላም አረገዘች፡፡ ይህን ጊዜ አያ ጅቦ የተኩላው ላም ስትወልድ ሁለት ሊሆኑለት መሆኑን አሰበና ቅናት አደረበት፡፡ እናም ለተኩላው እንዲህ አለው፡፡ "አንተ ላሚ በድንገት ብትወልድ ልታግዛት አትችልም፡፡ በዚያ ላይ ስታምጥ ጩኸቷን ሰምቶ አውሬ ቢመጣ ለመከላከል ትቸገራለህ፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ እኔ ከብቶቹን ላግድ" አለው፡፡ ተኩላውም ላሚ በሰላም እንድትወልድ ስለፈለገ በሐሳቡ ተስማማ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላም ወለደች፡፡ አያ ጅቦም የላሚቱን ደም በሬው ላይ አብሶ ወደ ቤቱ ይዟቸው ተመለሰ፡፡ ተኩላውንም "የአንተ ላም ሳትወልድ የእኔ በሬ ቀድሟት ጥጃ ወለደ! ደሙን ተመልከት" አለው፡፡ ተኩላውም የእራሱ መሆኑን በመግለፅ ተከራከረ፡፡ በመጨረሻም ወደ ዳኛ ዘንድ ሄዱ፡፡ የዘመኑ የእንስሳት ዳኛም ጦጢት ነበረች፡፡ አያ ጅቦም የእኔ በሬ አርግዞ ወለደ፡፡ ተኩላ ግን የእኔ ላም ነች የወለደችው እያለ ክርክር ገጥሞኛል አለ፡፡

ጦጢትም ትንሽ ካሰበች በኋላ ዘንድሮ ሁለት ነገሮች አስገራሚ ሆነዋል፡፡ እኔም "ሰማይ ተሰንጥቆ ስሰፋ፤ ባህሩም ተቃጥሎ ሳጠፋ ነው የዋልኩት" አለች፡፡ በዚያን ጊዜ አያ ጅቦ ተናዶ "አትቀልጅ ጦጢት ሰማይስ እንዴት ይሰነጠቃል? ባህርስ እንዴት ይቃጠላል?" አላት፡፡ ጦጢትም "እሄሄ! አያ ጅቦ በሬስ እንዴት ይወልዳል?" አለችና ለተኩላ ተፈረደለት ይባላል፡፡

## ብልኃተኛዋ ጦጢት

አንድ አንበሳ ነበር፡፡ ከአንበሳውም ቤት ጅብ፣ ዝንጀሮ እና ጦጣ በአሽከርነት ይኖሩ ነበር፡፡ በአሽከርነት ሲኖሩም ጅብ እና ዝንጀሮ ጦጢትን ይመቀኟታል፡፡ በዚሁም ምቀኝነታቸው ሳቢያ ነገር ያሴሩባታል፡፡ አንድ ቀንም እሷ በሌለችበት ወደ አያ አንበሳ ዘንድ ቀርበው "ጌቶች ጦጢት ጫማ መሥራት እያወቀች እርስዎ በበዶ እግርዎ ለምን ይሄዳሉ?፣ ለምን ጫማ አትሰራልዎትም?" ይሉታል፡፡

አያ አንበሳም "በሉ ካወቀች ጥሯት!" ይልና ጦጢት ትጠራለች፡፡ እንደደረሰችም ኸረ ለመሆኑ ጫማ መስፋት እያወቅሽ እኔ በባዶ እግሬ ስሄድ ለምንድነው ዝም ማለትሽ?" ይላታል፡፡ ጦጢትም "አዬ ጌታዬ ማወቁን አውቅ ነበር፡፡ መሥሪያው ቆዳ አይገኝልዎትም ብዬ ነው፡፡" በማለት መልስ ትሰጣለች፡፡

አያ አንበሶም መልሶ "ለጫማው የሚያስፈልገው የምን ቆዳ ነው?" ይላታል፡፡ ጦጢትም "የጅብ እና የዝንጀሮ ቆዳ ድብልቅ ነው፡፡" ትላለች፡፡ አያ አንበሶም "ታዲያ እሱ ከሆነ ምን ችግር አለው?" በማለት ጅብና ዝንጀሮ ተጥለው እንዲገፈፉ ይወስናል፡፡ ገፈፋውንም እራሷ ጦጢት ለጫማ ሥራው እንደሚመቸኝ አድርጌ እኔው ልግፈፋቸው ትላለች፡፡ አያ አንበሶም ይፈቀድላታል፡፡

ጦጢትም ጅብና ዝንጀሮን አርዳ ስትገፍ የጣር ድምፅ ሲያሰሙ "የመከራችሁት ምክር ውጤት ነው" እያለች ትጨርሳለች፡፡ ይሁንና ጦጢት ስለ ጫማ ጫማ ሥራ ምንም አታውቅ ነበርና ሌላ ዘዴ በማቀድ "ቆዳውን እወንዝ ወስጀ እባህር ውስጥ ልዘፍዝፍ፣ ለጫማ ሥራ እሚመቸው ሲዘፈዘፍ ነው" ብላ አያ አንበሶን ታስፈቅዳለች፡፡ ወስዳም የጅብ እና የዝንጀሮን ቆዳ እወንዝ ውስጥ ትጨምራለች፡፡ በየዕለቱም እየሄደች ስታይ አንድ ቀን ጧት በፀሐይ ጨረር ትኩር ብላ ስታይ እውስጡ ጥላዋን ታየዋለች፡፡

ከዚያም ስትበር ትሄድና "ጌቶች! ጌቶች! አረ ቆዳውን ቀማኛ ወሰደብኝ" በማለት አቤቱታ ታቀርባለች።

አቤቱታ የቀረበለት አያ አንበሶም "እንዴት ያለ ወንድ ነው የእኔን ገንዘብ የሚነካ?" ሲል ይጠይቃታል። ጦጢትም "አረ እንድዲያው ቁርጥ እርስዎን ነው የሚመስል" ትለዋለች። ከዚያም አያ አንበሳ እና ጦጢት ተከታትለው አየበረሩ ሄደው ከባህሩ ዳር ይደርሳሉ። እንደደረሱም ጦጢት ጎምበስ ብላ ባህሩ ውስጥ ስታይ አሁንም ጥላዋን ትመለከታለች። ጥላዋንም እንዳየች "ይኸው! ይኸውና!" ብላ ስትል አያ አንበሶም ጎምበስ ብሎ በዚያ በፀሐይ ጨረር ሲያይ የራሱን ጥላ ያይና ቁርጥ እሱን የመሰለ ጠላት ያጋጠመው ይመስለዋል። ከዚያም ጠላቱን እባህሩ ውስጥ እንዳለ ለመያዝ ዘሎ ድርግም ይላል። እንደገባም እዚያው ትልቅ ባህር ውስጥ ገብቶ ይሞታል። ጦጣትም ጠላቶቿን በሙሉ በእንደዚህ ዓይነት ብልኃት ጨርሳ ኖረች ይባላል።

# አባሪ ሁለት፡- ሥነቃል፡- ከሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተሰባሰቡ ግጭት ተኮር ሥነቃሎች

## ሀ/ የአፋር  የሽላሎ ግጥሞች በአማርኛ

በሰሙ ሮቢ ገለአሎ ወረዳም የሚከተሉት ግጭት ተኮር ሥነቃሎች ተሰብስበዋል፡፡ ሥነቃሎቹ የተሰበሰቡት በመጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከቁልፍ የሰሙሮቢ ገለአሎ የመረጃ ተባባሪዎቼ ጋር ቆይታ ባደረግሁባቸው ወቅቶች በየጨዋታችን መሃል የነገር ማትቢያ፣ የአመክንዮ ማጠናከሪያ እየሆኑ በተነገሩባቸው አጋጣሚዎች ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በታች በልዩ ልዩ ዘውጎች የቀረቡት እና በግጭት ዙሪያ የሚሽከረከሩት ሥነቃሎች የተሰበሰቡት በመጠይቅ (አደም መሐመድ፣ ሐሰን ቢዳር፣ አሊ መሐመድ) እንዲሁም ቃለ መጠይቅ (ከአቶ ሁሴን አህመድ የአስጋፌን ነዋሪ እና አቶ አሎሃ ሃንዶ የሆቲመሮ ነዋሪ የነገሩኝ (17/09/2002) እና ከሌሎችም በየጨዋታው መሃል የሰማኋቸው ናቸው፡፡

በመጀመሪያ የሽለላ ግጥሞቹን እንመልከት፡፡ የሽለላ ግጥሞቹም በቅድሚያ በአማርኛ ትርጉማቸው ቀጥሎም በመገኛ ቋንቋቸው ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

## ሀ/ የአፋር የሽላሎ ግጥሞች በአማርኛ

1) አንጣላም ሀገር ያጣላናል፣
   እንደኛ መሆን አትሞክሩ ተው  አትንኩን ብለናል፣
   ሥጋ  እንደጠገቡ አሞራዎች በአንድ ላይ ተነስተናል፣
   ጋሻ ጦር እንደሚከላከል፡፡
2) ጀግና ሰው፣
   ጠበሳ እንዳለው፡፡
3) ሞት በከንፈራማ ሰው አያምርም፣
   መሸሽ በወፍራም ሰው ያስጠላል፡፡
4) ማን ነው መድፈር የሚፈልገው አገራችንን፣
   ተው የሚል መሪ አለን፣

አንተውም የሚሉ ጀግኖች አሉን፡፡

5) እንደተደረመሰ አጥር አንድ ላይ ሞተናል፣
በሞት አንጠፋም ሞት እንድንረባ ያደርገናል፡፡

6) እንዋጋለን ወዳጆቻችን አይደሉም፣
ያፈራሀውን ሀብት ጥለኸው አትሩጥ ሚስትህ ሳለችልህ፣
ጥለኸን አትሂድ ላሞችህ ሳሉልህ፣
አባቴ ጥለኸን አትሂድ ልጅህ ሳለሁልህ፣
ይዘኸን አትሩጥ ጠመንጃህ ሳለልህ፣

7) የጀግና ዓይን ሲቀላ የፈሪ አይን አቡጀዲድ ሲመስል፡፡
ሰው መሞት አለበት የባለቤቱ ጉዳይ ቢሆንም፡፡

## ለ/ የአፋር ሽላሎ ግጥሞች በአፋርኛ

Baxxo naysammele manaamammay

Ummatey maabina nee massagayyina

Ni cal maxaamina

Cadok cayte gumah innah uqut inki qabul abne

Data goobut wara lenna

Agirut anxa qalenna

Rabi- Sokto nabot gaca

Buki sarba nabot gaca

Mamaraay naagatak yaffareenim

Maabina iyya able abenno iyya urrule

Tiddigille gasoh innah raba sittin bagul abne

Nanrabak mabaynay rabak saadna

Aamenno sinam-ni-xaleyna hinna

Teddem macabin barra koktawaqdi

Yaddak makadin mayyi kokya waqdi

Yabbow yoo macabin baxi kok ya waqdi

Yoo luk makudin waddi kokta waqdi

Agri inti xuboyyoota celta waqdi

Bixxinti sawaacila celta waqdi

Num rabam meqe le numih kasammay

## ሐ/ የአፋር ፉከራ ግጥሞች በአማርኛ

1. ማታ ጨረቃ ነን፣
   ቀን ፀሐይ ነን፡፡
2. እኛና ጦርነት እንተዋወቃለን፣
   በታሪካችን፣
   እስከ ሰባት አያታችን፣
   እናውቃለን ጦርነትና ሞትን፣
   አዲስ አይደለን፡፡
3. የተጠሙ ከብቶች ውኃ ሲያገኙ ይረካሉ፣
   የጎርፍ ውኃ ባህር ይገባል፣
   ሽምግልና በባላባት ያልቃል፣
4. አፋር ጦርነት ያውቃል፣
   ከአፋር ጋር የተዋጋም ስለ ጦርነት ማውራት ያቆማል፣
   ጦርነት እራሱም ከአፋር በኋላ ሞታል፡፡
5. የሚያማምሩ የጦር መሣሪያዎች ባለቤቶች፣
   የነጫጭ ፈረሶች ጌቶች፣
   ነገር ፍለጋ የሚዘዋወሩ ሰይጣኖች፣
   የሚጣሉት ቢያጡ ከራሳቸው ጋር የሚጣሉ አፋሮች፣

አሉን እንቅልፍ የማያውቁ የሌሊት አንበሶች፣
ቀድመው የሚያውቁ አሉን ትንቢተኞች፣
በፍርሃት ላብ የሚጠመቁም ምስኪኖች፣
አሉንም ከንቱዎች፣

6. ጠላቶቻችን ያለቀሱ ጊዜ፣
ከብቶቻችን በተጨነቁ ጊዜ፣
ሴቶቻችን ያለቀሱ ጊዜ፡፡

7. ወድቀው እየጣሉ ጓደኞቼ ሲሞቱብኝ፣
አላህ አስቀድመህ ግደለኝ፣

8. ልጆቻቸውን አላሳድግም፣
የነሱን ሚስቶች አላገባም፡፡

9. እኛ እንሙት ሰውም እንግደል፣
ወደ ውስጣችን አትግቡ ውስጣችን ያቃጥላል፡

10. እነማን የእኛ እኩዮች ይሆናሉ፣
እኛ ስንቆጣ ሁሉም ፀጥ ይላሉ፣
እኛ ባንናገርም መሪዎቻችን ይናገራሉ፡፡

## መ/ የአፋር ፉከራ ግጥሞች በአፋርኛ

Bar alsa kinnino laqo ayro kinnino

Abuuy abbah daban rabaw koo naaxigeh

Laa dorat yaadiye

Lee badat taadiye

Yab abbat yaadiye

Qeebi net yaadiye

Kuclin bandoo galey

Qado faariisa ley

Seetanay seecale

Qamalliy kuulale

Butaytuy hadrale

Moominiy xooqale

Beedi sulluc iyye

Laa homoydoq iyye

Agbi boogew iyye

Innikissaay muda

Yaado rabta carra

Yallow yoo masuksin

Ken xaylo maynaba

Ken gubun maciksa

Ninnih rabnay xica sinam qidnay xica

Nek adda moobina adda nek dahanle

Ni qayda makkina

Kifno qeere kalleh

Nanmiyabnay makaaban yaabele

## ሠ/ የአፋርኛ የፍቅር ዘፈኖች በአማርኛ

1) ፍቅረኛዬ /ውሽማዬ/ ስትሞት በሬ ወይም ግመል እሰጣለሁ፣
በሬ አቀርባለሁ ውሸት ሊሆን ይችላል እላለሁ፣
በሐቅ ግን የቀባሽውን ጎፈሬዬን ግን እላጫለሁ።

2) እኔና ጓደኛዬ ከሌሎች ጋር በምንጣላበት ጊዜ ሁሉ፣
አዋቂዎች ይጠራሉ፣
መርፌዎችና ክሮችንም ያሰባስባሉ፣
ቁስላችንም ይሰፋሉ።
3) ጠላት ካልቀደመን፣
ቦታ ከተመችን፣
በደም እናጨቀያለን።
4) ሴቶች መንገድ ገብተው ሲሄዱ ጭንቅላታቸው ይታየኛል፣
የኔዪቱ ፍቅር ግን ደረቷ ይታየኛል።
5) ሴቶች የኔን ፍቅር መደበቅ አይቻላቸውም፣
ፍየሎችም ግመል መደበቅ አይችሉም።
6) ቤትሽ ጊደሮችን ከዝናብ ያስጠልላል፣
ድድሽ የጠዋት ዝናብ ደጋግሞ የደበደበው ጥቁር ድንጋይ ይመስላል፣
ቅቤ ያደረበት ስኒ የሚመስል ጥርስ አለሽ፣
የኔ ፍቅር የኔ ባልንጀራ /ጓዴ/ የኔ ቀይ አንካሴ እንደ ጊሌ ባለ ጌጥ ነሽ።
7) ፍቅሬ ቆንጆ ጥርስ አለሽና ሳሚኝ፣
ከአባትሽ ከወረሻቸው ላሞች ወተት አጠጪኝ።
8) ለቀይ ሴት ስስቃይ ከማድር፣
ጓደኛ ቢኖረኛ እዘምት ነበር፣
ፍቅረኛ ቢኖረኝ ሌሊት እሄድ ነበር፣
ኩብት ቢኖረኝ አረባ ነበር።
9) ያንች ቤት ወለል ብዙ ያራምዳል፣
ፀጉር ሰሪዎችሽ ሙሉ ቀን ይውላሉ።
10) በውሽማ ምግብ የሚያህልሽ የለም፣
11) ተራራ የሚወጣው ቀጭኔ ነው ወይስ የኔ ፍቅር ነው፣
የሚሰማው የፈረስ ጌጥ ነው ወይስ የኔ ፍቅር ጌጥ ነው።
12) ጣሊያን እንደሰራው አስፋልት መንገድ ነው እንጂ የሚበላሽ ጥርስ የለሽም።
13) ሰው ሁልዬ ከታመመ ይሞታል፣
ወንድ ግመል ሁልዬ ከጮኸ ሴት ግመሎች ካሉበት ይደርሳል፣

ሰማይ ሁልዬ ካስገመገመ ይዘንባል።
ፍቀረኛም ስለ ፍቅረኛው ካወራ ካለችበት ይደርሳል።

## ረ/ የአፋር የፍቅር ዘፈኖች በአፋርኛ

Ye-qasaalo rabteh iyyen carra Ala baahek saga baahe akke liyo

Ala baahe yok diraabammay saga baahen yok diraabammay atu tuskute a mo koh mooleliyo

Yoo kee kataysa dadhan carra bagi qakle marah see caanah, erab kee seed ari gaaboysaanaah,

Ceyalekket suge waynek yaaloy niqabal fixiixelem waaga mali

Agabuk moyyaayi yoh tanbullee yaalok faroodi yoh yanbullee

Agabow yaalo maqellissaana

Wadariy gala maqellissaana

Ruubuk daheela culsan qariliy

Emelelle meeme mandaytih afey

Subac elle xiine figgaanih afey

Yi mareytay gileh unxuxxay

Yi kataysaw qasa macxih daabow

Dataf yalli koh yeceeh neefugutey

Laa kabba koh cabeh nee mayisey

Qasa barray qasitak koh xiina

Kataysa Aaliyoy gaadak en

Mareyta Aalliyoy kulak en

Laaliyoy laa aylaaluk en

Ku qarik baaxa gexak raaqaanaah

Kaamok ruubi qaxak raagaanaah

Anaakar mareyti kooral le numey

Qaletaaqem daqamannaa yaalooy

Kakac ittam farasannaa yaalooy

Tilyan abte gitakkalah bayaf mantu

Num inki lak misek diiko mira

Rakub inki hindatek gala mira

Rob inki cankaxek baaxo mira

Anu amannah axce bar yaalo mira

## ሰ/ የአፋርኛ የሰርግ ግጥሞች

1. ሙሽራ ሆይ ልናሞግስህ ነውና አዳምጠን፣
   ሙሽራ ወንድማችን ነው ሙሽሪት እህታችን፡፡
2. የልጅ አባት ያርግህ፣
3. እንደ ውሃ ቀስ እያለ የሚሄድ ሙሽራ መጣ፣
   እንደ መስታወት የሚያንፀባርቅ ሙሽራ መጣ፡፡
4. ሙሽራው ገና ሎጋ ነው አልሸመገለም፣
   ሲራመድ አቧራ አያስነሳም፣
5. ሰውነቱን እንደ ነብር የሚደብቅ፣ እርዳታም የማይሻ ሙሽራ፣
   እንደ እባብ አንገቱ ላይ ምልክት ያለው ሙሽራ፣
   መጣ ውሃ እንደሚሻገር  እባብ ዳሌው የሚውረገረግ ሙሽራ፡፡

## ሸ/ የአፋር የሰርግ ዘፈን /Garammaggeda/ በአማርኛ

Qaroosow koo nassakaxxa waynah kohinnam ankacsitey qaruusow

Qaros nek salaay qibna nek maqanxa

Qadqarit baxi koh maacisay qaroosow

Kaalah innah sibirya qaros yemeee

Miryat innah abaaba qaros yemeete

Aros Awki baxakkal idaltu hinna

Aba gexot sarba siisa maaba

Kabqih innah dagar yaaqarow qaruusow

Kedoy digbah anih yoo caraysa miyya

Baadeysinnah alal barulow

Lee tabaatataba warri bagulow aroosow

## ቀ/ የአፋርኛ የሥራ ግጥሞች በአማርኛ

1. የአገራችን አፈሩ ወርቅ ነው፣
   ውኃውም ማር ነው።
   የአገራችን ጭቃ መዓዛማ ሽቶ ነው፣
   ድንጋዩም አልማዝ ነው።
2. ሙሉ ቀንም ስሩ አትቦዘኑ እንቅልፍን ቀንሱ ፣
   ጉድጓድም ቆፍሩ እርሻም እረሱ፣
   ውሃም አረስርሱ።
3. የትኛውም አገር፣
   ከኛ አገር ፣
   አይሻልምና ካልሰነፍን በቀር፣
   ለሀገር የሚበጅ ጉዳይ ላይ እንመካከር።

## በ/ የአፋርኛ የሥራ ግጥሞች በአፋርኛ

Ni rasuk saacil malabaay leekak dahaba

Ni rasuk kallayti miskiiy xaa kak kuculu

Bari bar xin kur aay laqo saalak asa

Daga qelwa buqre qiddaay efeqa

Mari baaxo marayso ni baaxok booledino

Agatah taysem mali ittallih wagit

## ተ/ የአፋርኛ ተረት /Hayyeyoona/

### ቁራ እና ቀበሮ

አንድ ቀን ቁራና ቀበሮ ተገናኝተው ሳሉ ቁራው ለቀበሮው ሊነግረው የሚፈልገው አዲስ ዜና እንዳለው ይነግረዋል፡፡ ቀበሮውም ለመስማት ተቻኩሎ "አዲሱ ዜና በማለት ምንድነው?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ቁራም ከዚህ ከምናው ሰማይ ወዲያ ባለው ሁለተኛ ሰማይ ላይ በዓይነ ስውራን አሮጊቶች የሚጠብቁ የፍየል ግልገሎች እንዳሉ አይቼ መጣሁልህ" ይልዋል፡፡

ቀበሮም "ቁራው ኧረ እባክህን አትዋሸ" ይለዋል፡፡ ቁራም የተናገረው እውነትነቱን መላልሶ ይነግረዋል፡፡ ቀበሮም "እኔ ክንፍ የለኝም ስለዚህ መብረር አልችልም እንዴት ሄጄ አያለሁ?" ይለዋል፡፡ ቁራም "ግድ የለም እኔ እወስድሃለሁ፡፡ ሄደህም በዓንህ አይተህ ታምናለህ" ይለዋል፡፡ ቀበሮም መልሶ "አንተ እንዴት አድርገህ እኔን ልትወስደኝ ትችላለህ?" ይልዋል፡፡ ቁራም "ግድ የለም አንተ የኔን እግር ትይዛለህ፣ ከዚያ እኔ እበራለሁ ስለዚህ በዚህ መንገድ ከእኔ ጋር ትሄዳለህ" ይለዋል፡፡

ቁራና ቀበሮ ለመብረር ከተስማሙ በኃላ ቁራው ለቀበሮው ስለአበራረራቸው ሁኔታ ሲያስረዳው "እኔ የተወሰነ ርቀት ከበረርኩ በኃላ እግሬን ስለሚደክመኝ

እጮሃለሁ፡፡ ያኔ አንተ ይዘኸው የነበረውን አንዱን እግሬን ለቀህ ሌላኛውን እግር ትይዛለህ" ይለዋል፡፡

በዚሁ ተስማምተው ይበራሉ፡፡ እንደተነጋገሩትም ቁራ ቀበሮን በአንድ እግሩ አንጠልጥሎ የተወሰነ ርቀት ከበረሩ በኃላ ቁራ ይጮሃል፡፡ ያኔም ቀበሮ ይዞት የነበረውን እግር ለቆ ሌላውን የቁራ እግር ሊይዝ ሲል ቁራ ሆን ብሎ እግሩን ሰብስብ አድርጎ ሲደብቅበት ቀበሮ ከሰማይ ምድር ወርዶ ተበታትኖ ሞተ ይባላል፡፡

## አንበሳ እና ሰጎን

በድሮ ዘመን አንበሳና ሰጎን አንድ ላይ ተባብረው ከብት ማርባት ጀምረው ነበር ይባላል፡፡ ከብት ማርባቱን የጀመሩትም ሰጎን ላም ይዛ፣ አንበሳ ደግሞ በሬ ይዞ ነበር፡፡ አንድ ቀን የሰጎን ላሞ ስትወልድ አንበሳ ሰጎንን "የወለደችው ላምሽ ሳትሆን የኔ በሬ ነው፡፡" ብሎ ጥጃዎን ይወስድባታል፡፡ ከዚያ በኃላ ሰጎን ለእንስሳት ጉባዔ አቤቱታ ታቀርባለች፡፡ ሁሉም ቢሰበሰብም፣ ሐቅ ቢታወቅም ጉባዔተኞቹ አንበሳን ስለፈሩት ሐቅ ተናግሮ የሚፈርድ ሰው ጠፋ፡፡ እንስሳቱ እንደዚህ እየተጨናነቁ ሳሉ በአጠገባቸው ቀበሮ ሲያልፍ ያዩና "ጋሽ ቀበሮ! አንድ ጊዜ ና እስቲ ለሽምግልና ተቀምጠናልናልና እርዳን" ይሉታል፡፡ ቀበሮም "የምን ሽምግልና ነው ?" ይላቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹም "ሰጎን እና አንበሳ በጥጃ ስለተጣሉ ነው፡፡ አንበሳ ጥጃ የወለደው የኔ በሬ ነው ይላል፡፡ ሰጎን ደግሞ ጥጃ የወለደችው የኔ ላም ናት ትላለች፡፡" ብለው ሲነግሩት "አልመጣም! በጣም እቸኩላለሁ፡፡ ምክንያቱም አባቴ ምጥ ይዞታል፡፡" ብሎ ትቷቸው ለመሄድ ይቻኮላል፡፡ ሽማግሌዎቹም "አትዋሽ ! አቶ ቀበሮ ከመቼ ወዲህ ነው ወንድ ምጥ የሚይዘው?" ሲሉት ቀበሮም በመጠል "በሬ ከመቼ ወዲህ ነው የሚወልደው? ቀልዱን ተውትና ጥጃውን ለሰጎን ስጡ" ብሎ ሲሮጥ አንበሳው በቀበሮ ፍርድ ተናዶ ሊያሳድደው በመሄዱ ሲከተለው ሰጎን ጥጃዎን ወሰደች ይባላል፡፡

## ቸ/ የአፋርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአማርኛ

1) ሰው ለመምሰል የሚደረግ ሙከራን እና የሰውን ምክር በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

2) የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፡፡

3) ከወነጀሉህ ነፃ ብትሆንም ለጊዜው ለንጀለኛ ትሆናለህ፡፡

4) የምታውቀውን ሁሉ የሚያውቅ ሰው ያስቸግርሃል፡፡

5) ፍቅር ካለቀ ይጣላሉ፡፡

6) ንግግር እንደ ቤት በር አለው፡፡

7) ደፋር መሆን ወይም ከዳኝነት መራቅ፡፡

8) ጉዳዩ ለሚመለከተቸው ሰዎች እና ለማይመለከታቸው ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ ሰዎች አሉ

9) ከጐረቤት ፀባይ ትወርሳለህ ከጐረቤት በሬ አይነት ትወርሳለህ፡፡

10) ካላዩ አያረጋግጡም ካለልኩ አያወጡም፡፡

11) ሀብታም ይቸገራል  መሀን ትከሳለች ተብሎ አይታሰብም፡፡

12) መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳትሰፋ የሰው ቀዳዳ ትሰፋለች፡፡

13) ውሻና መጥፎ ሰው በራሱ ቤት ይጨቃጨቃል፡፡

14) ከሞት በኃላ ፍላጐት አይኖርም፡፡

15) ደምህን የሚመልስልህ የአጐትህ ልጅ ፣ሐሜት የሚያናግርህ የአክስትህ ልጅ ነው፡፡

16) ለሚያልፍ ቀን የማያልፍ ቃል አትናገር፡፡

17) ንፋስ የዝናብ ምልክት ነው፤አባባሎች የወሬ ምልክቶች ናቸው፡፡

18) እያዩ ይቀራሉ ሳያዩ ይፈልጋሉ፡፡

19) የሰራ እጅ ይሞታል እንጅ የተሰራ ነገር አይሞትም፡፡

20) ነገር የማይገባህ ከሆነ በሽታ ነው ገብቶህ ዝም ካልክም በሽታ ነው፡፡

21) ነገርን በነገር መመለስ ቁስል በመድሀኒት መፈወስ፡፡

22) ፍርድና ውርስ በግልፅ መሆን አለበት፡፡

23) እሳትን አይቶ ወደ እሳት የሚመለስ ድስት ነው፡፡

24) ጓደኛን ማክበር ውሽማን መሳም፡፡

## ኀ/ የአፋርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአፋርኛ

Abita bit boolok koo qidaah marin kas ayrol koo caba

Bisol taniimih gaba ruubeenik gurummal tanim kok caxitta

Kol heenik koo ceele waytam matan

Atu taaxigem kollih yaaxige awki dabaanak raaqi koo mahaa

Meqem maxce temmekek yaameenih

Yab gitaleeh qari afale

Yaabak Alliiliiy yaabak

Yab ceela num leeh yaabah lafta mari yan

Cuggaanek cal kottabaah moynobuk bisi kottaba

Ablekal miyaaxigaanaay atce kal mayanxuqan

Gaddale taqbam mayakkalaanaay maxalayto qakkottam mayakkalam

Erba isit tan booha matab lay marat tan booha dammiyta

Uma num kee kota issi buxal koo qadowwussa

Nabsi rabek nabsi fayxi maraqta

Cane qammih baxi koh gacsaah cami nangali koh warsa

Cabu waa daban cabe waa magaq kot caba

Caacay robti meerraytuuy missile yabti meerraytu

Abaluk ruubaanaah able kal gorrisan

Abte gaba baytaah gaba abtem mabayta

Yab able waytam biyaakaay tubleh cabtam biyaaka

Yaabat yab haanaah, dalet caxa haan

Yab kee nagra qadok koh abaanam meqe

Gira tubleeh girah taduurem buuti

Yikaysaw ittek dagortam meqeeh yimareytay ittek fuguttam meqe

Allal hida meqeeh garil rooci meqe

## ነ/ የአፋርኛ ጀግንነታዊ አባባሎች በአማርኛ

1. አላህ ታላቅ ነው። አፋር ታላቅ ህዝብ ነው። አላህና አፋር ከሁሉም በላይ ናቸው።
2. አፋር ከተለያዬ አቅጣጫ ፍፃሜ የሌለው የጥፋት ጦርነት ባይለያትም፣ ድጋፍ በማጣቷ ብትጎዳም የአገሯን ክብር አሳልፋ አልሰጠችም።
3. አፋር ምን ጊዜም የጠላትን ጭቆና አልተቀበለችም፣ ወደፊቱም አትቀበልም።
4. የአፋርን ባህርይ የማታውቁ ካለችሁ እንንገራችሁ።
   አፋር ለጠላት አይመችም።
   የሚለያዩ ቢመስሉም አይለያዩም።
5. አንድ አገር አንድ ኃይማኖት አንድ ቋንቋ አላቸው፣
   ትግስትና አክብሮት ከጥንት ጀምሮ መለያቸው ነው።
6. እሷን አይፈልጓትም የሚፈለግ ነገር ግን አላት፣
   የሚወደድ አገር አላት፣ የማይወደድ ታሪክ አላት።
   ጠላት ምን ጊዜም በዓይነ ቁራኛ ያያታል፣
7. ሰዎች አፋርን ላይ ትልቅ ጥላቻ አላቸው፣
   አላህ ደግሞ ለአፋር ልዩ ፍቅር አለው።
8. ጦርነት ቢበዛም አፋር አያልቅም።
   በመጨረሻም አይቻልም።
9. አፋር አገሩን ለቆ እንደማይሄድ የታወቀ ነው፣
10. አፋር የሚያወራውንም የሚያደርገውንም አረጋግጦ ነው።
11. አፋር በሌሎች ዓይን ደካማ መስላ ትታየለች።
    አፋር ግን ይህን የማታውቅ ትመስላለች።
12. አፋሮች እርስበርሳቸው የማይዋደዱ ይልቁንም ሌላ የሚወዱ ይመስላሉ፣
    ይህቺ ማታለያ ነች አፋር ለሌሎች ክፉ ነች።
13. አፋሮች እርስበርሳቸው ሲጣሉ እበት ይወራወራሉ፣
    ከባዕድ ሲጣሉ ግን ድንጋዬች ይወረወራሉ።

## ኘ/ የአፋርኛ ጀግንነታዊ አባባሎች በአፋርኛ

Yalli nabaah Qafar nabayyunta

Ammaxe sinni baatil admoo kee wayta wayta qokol ramaccaa tet haa way

qigdu Qafar migaq maruubinna

Way maxaginna biidi amorramma sarra maxiqta baatilik falma

Aaxige waa maraw Qafar lelleh yaaxagu beedi dude waa calle

Sitta macabta cabtu waah xawle

Inki kasu inki diiniiy inkafle

Tibba tuhinna meq mariinok leeh,

Tet mafaaxaanay is faxaanamle

Kicnon agatle niqbon aydadle

Qangi rakekkel inti teetille

Seehada kaxxa naqbu teetihle

Yalli xuwawle kainu teetihle

Saabo macabta yeffereenim leeh

Baaxo macabta yeffereenim le

Asmite wayta yab magabbaqtaa, tismitem abta tismitam yabta

Isgarut inki boolalem celtaah

Aaxagih iggimaate lem celtaah

Ittah umaah garuh meqem celtaah

Woh lawisikkalah garah gacta

Sitta fanah kifiina qammissa

Beeda fanah balooda qammissa

# አባሪ ሦስት

## የመረጃ ምንጮች መዘርዝር

በዚህ ሥር የቀረቡት ሁለት ዓይነት የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ቁልፍ እና አጋዥ የመረጃ ተባባሪዎች፡፡ ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች የተባሉት ስለ ቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ድንበርተኛ ወረዳ ሕዝቦች ውስጣዊ እና ውጪያዊ ግጭት እና ግጭት አፈታት ሁኔታ መረጃ የሰጡ ሲሆኑ አጋዥ የተባሉት ደግሞ ስለ ሁለቱ ወረዳ ሕዝቦች በሥራ ኃላፊነታቸው የሚያውቋቸውን እና ለጥናቱ አካባቢ ገለፃ የሚበጁ ጥቅል መረጃዎችን የሰጡ የየወረዳዎቹ መስተዳድሮች የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ናቸው፡፡

## ቁልፍ የመረጃ ምንጮች መዘርዝር ከቀወት ወረዳ

| ተ.ቁ. | ሙሉ ሥም | ዕድሜ | ሥራ | ቀን | ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ስጥአርጌ ደርሶ | 70 | ጡረተኛ | 06/09/2002 | ሸዋ ሮቢት | እ.ጠ. |
| 2 | አቶ ደመቀ ሲሻህ | 75 | አርሶ አደር | 13/09/2002 | ዓባይ አጥር | " |
| 3 | አቶ ከፈለኝ ድረሴ | 68 | መምህር | 12/01/2003 | ዓባይ አጥር | " |
| 4 | አቶ ከተማ አይሻር | 72 | አርሶ አደር | 15/01/2003 | ኩሬ በረት | " |
| 5 | አቶ መኮንን በረደድ | 60 | " | 19/01/2003 | ደብር | " |
| 6 | አቶ ኪዳኔ መከታ | 74 | " | 22/01/2003 | ሰፊ በረት | " |
| 7 | አቶ ከበደ መንገሻ | 77 | " | 25/01/2003 | ሰፊ በረት | " |

*የቀወት ወረዳ የተተኳሪ ቡድን ውይይት የተካሄደው ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የተካተቱት ቁልፍ የመረጃ ተባባሪዎች በተገኙበት በ 23/01/2004 ዓ.ም.ሸዋ ሮቢት ከተማ ነው፡፡

## መጠይቅ በመሙላት የተባበሩ የቀወት ወረዳ ነዋሪ ተማሪዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ. | ሙሉ ሥም | ክፍል | አድራሻ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥላሁን ደምሴ | 9A | ሸዋ ሮቢት ት/ቤት | |
| 2 | አንበርብር ጣሰው | ” | ” | 15-29 /9/2002 |
| 3 | ፍርዱ ሞላ | ” | ” | ” |
| 4 | አበባው በድሉ | ” | ” | ” |
| 5 | እምሬ ታቦር | ” | ” | ” |
| 6 | ሰይፈ በለጠ | ” | ” | ” |
| 7 | ቤዛ ሰለሞን | 9B | ” | ” |
| 8 | ሂሩት አጉኜ | ” | ” | ” |
| 9 | በለጠ ጣሴ | ” | ” | ” |
| 10 | አድነው ተስፋዬ | ” | ” | ” |
| 11 | ገነነ ተሰማ | ” | ” | ” |
| 12 | ድረሴ ይልማ | ” | ” | ” |

## ቁልፍ የመረጃ ምንጮች መዘርዝር ከሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳ

| ተ.ቁ. | ሙሉ ሥም | ዕድሜ | ሥራ | ቀን | አድራሻ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግራዝማች ኢሰገሌ ኢነዛባ | 95 | ጡረተኛ | 08/01/2002 | አዳዲሲሂጌ | እ.ጠ. |
| 2 | ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ | 93 | ጡረተኛ | 05/09/2002 | ሸዋ ሮቢት | ” |
| 3 | ሼህ መሐመድ ሰይድ | 65 | ነጋዴ | 10/09/2002 | ሸዋ ሮቢት | እ.ጠ./ምሁር |
| 4 | ሼህ አደን ጋለሎ | 60 | አርብቶ አደር | 12/09/2002 | ሆቲመሮ | ጠንካራ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | አቶ አሎሃ ሃንዶ | 55 | ” | 14/09/2002 | አዳዲሲሂጌ | ጠንካራ |
| 6 | አቶ አህመድ ኢብራሂም | 70 | ” | 16/09/2002 | ሐሬሐሙ | ” |
| 7 | አቶ ሁሴን አህመድ | 73 | ” | 17/09/2002 | አስጋሬን | ” |
| 8 | አቶ ሐሚድ መሐመድ* | 63 | | 19/01/2004 | ሸዋ ሮቢት | ” |

*ተራ ቁጥር ስምንት ደግሞ በቃለ መጠይቅ ወቅት ያልተካተቱ ነገር ግን በኋላ በሰሙ ሮቢ ገለአሎ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ባላምባራስ አይዳሂስ አሎ ስላረፉ እርሳቸውን እንዲተኩ የተደረጉ ናቸው፡፡በሰሙሮቢ ገለአሎ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት የተሳተፉትም ስድስት ሰዎች ናቸው፡፡

የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የተተኳሪ ቡድን ውይይት የተካሄደው ዓባይ አጥር በግራዝማች ኢሰገሌ ኢነሃባ ቤት በ19/01/2004 ዓ.ም.ነበር፡፡

## መጠይቅ በመሙላት የተባበሩ የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ ነዋሪ ተማሪዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ. | ሙሉ ሥም | ክፍል | አድራሻ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዓሊ አደም | 9A | ሸዋ ሮቢት ት/ቤት | ግንቦት5-15/2002 ዓ.ም. |
| 2 | መሐመድ አህመድ | ” | ” | |
| 3 | አደም ሙሣ | ” | ” | ” |
| 4 | ሐሚድ ሁሴን | 9B | ” | ” |
| 5 | አህመድ ኢብራሂም | ” | ” | ” |

## የቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሉ ቁልፍ የመረጃ ምንጮች የጋራ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት

| ተ.ቁ | ሙሉ ሥም | ዕድሜ | ሥራ | የተጠየቁበት ሥፍራ | ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አቶ ሰጥአርጌ ደርሶ | 70 | ጡረታ | ሸዋ ሮቢ.ት | 27/01/2004 | እ.ጠ. |
| 2 | አቶ ደመቀ ሲሻህ | 75 | አርሶ አደር | " | " | " |
| 3 | አቶ ከፈለኝ ድረሴ | 55 | መምህር | " | " | " |
| 4 | ሼህ መሀመድ ሰይድ | 65 | ነጋዴ | " | " | " |
| 5 | ሼህ አደን ጋለሎ | 60 | አርብቶ አደር | " | " | " |
| 6 | አቶ አሎሃ ሃንዶ | 55 | አርብቶ አደር | " | " | " |

## አጋዥ የመረጃ ተባባሪዎች ከቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሉ ወረዳዎች

| ተ.ቁ. | ሙሉ ሥም | ሥራ | ቀን | ቦታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አክመል መሐመድ | የቀወት ወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ባለሙያ | 23/09/2002 | ሸዋ ሮቢ.ት |
| 2 | አቶ ሰለሞን ይብዛ | የቀወት ወረዳ መስተዳድር አባል | 24/09/2002 | " |
| 3 | አቶ ሀብተወልድ ተጌ | የቀወት ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የተፈጥሮ ሀብት ኃላፊ | 24/09/2002 | " |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | አቶ መሐመድ አይዳሂስ | የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ | 26/09/2002 | ኩማሜ |
| 5 | አቶ ዓሊ ሰይድ | የሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳ መስተዳድር አባል | 26/09/2002 | " |
| 6 | አደም መሐመድ | አርብቶ አደር | | |
| 7 | ሁሴን አህመድ | አርብቶ አደር | | |
| 8 | ሐሰን ቢዳር | አርብቶ አደር | | |
| 9 | ዓሊ መሐመድ | አርብቶ አደር | | |

**መፍቻ**

ምርመራ በሚለው ላይ እ.ጥ እና ጠንካራ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ቁልፍ የመረጃተባባሪዎቹ ስለተጠየቁት ጉዳይ ያላቸውን እውቀት ደረጃ ለማመልከት ነው፡፡ በዚህም መሰረት፡-

እ.ጠ.፡- እጅግ ጠንካራ/የተሟላ አካባቢያዊ የሁነት እና የተረክ እውቀት ያላቸው/፣

ጠንካራ፡- የቅርብ ሁነቶችን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸውን ለማመልከት የተቀመጡ ናቸው፡፡

## ማረጋገጫ

ይህ "የድንበርተኛ አማሮች እና አፋሮች ግጭት እና የግጭት አፈታት—በቀወት እና ሰሙሮቢ ገለአሎ ወረዳዎች" በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ጥናት ካሁን በፊት በማንም አካል ያልተሰራ፣ ለማንኛውም ተቋም ያልቀረበ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑን፣ በዋቢነት ያገለገሉ ድርሳናትም በትክክል የተጠቀሱ መሆናቸውን እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ ባለመብት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ሥም:- ዓለሙ ካሣዬ ፊርማ [signature] ቀን 30/06/2008